# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ-9



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ - 9


የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ



# የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት መልዕክት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው፤ በዚህ ረገድ የሚሠጡ የሰበር ውሣኔዎችን ፍርድ ቤቱ አሣትሞ ማሠራጨት እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሠረትም እስካሁን ድረስ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸው ፍርዶች ከቅጽ 1 እስከ ቅጽ 7 ድረስ በማሣተም ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲሠራጩ ተደርገዋል፡፡

እነዚህ ፍርዶች የሀገራችን ፍርድ ቤቶች የሚሠጧቸው ፍርዶች ወጥነትና ተገማችነት እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ የማይናቅ ሚና እየተጫወቱ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህን ቀጣይ ለማድረግ ቅጽ 8፣ 9 እና 10 እነሆ ለሕትመት በቅተዋል፡፡

አስገዳጅ የሰበር ውሣኔዎች ሥራ ላይ ከዋሉ አጭር ጊዜያቸው ነው፤ በአንፃራዊነት የብቃትም ሆነ የልምድ ውሱንነቶች በመኖራቸው እነዚህ እጥረቶች በሰበር ፍርዶቻችን ላይ አልፎ አልፎ መንፀባረቃቸው አልቀረም፡፡ በዚህ መስክ የረጅም ዘመናት ታሪክ ያሏቸው ሀገሮችም በተመሣሣይ ሁኔታ ውስጥ ያለፉ በመሆናቸው እኛም አቅማችንን በማጠናከር የእነዚህን አገሮች ተሞክሮዎች በማገናዘብና የሀገራችን የሕግ ባለሙያዎች በፍርዶቻችን ላይ የሚሠጡትን ገንቢ አስተያየቶችና ትችቶች ግብዓት በማድረግ ኃላፊነታችንን በአግባቡ ለመወጣት ጥረታችን እንደሚቀጥል በዚህ አጋጣሚ እየገለጽሁ የሕግ ትምህርት ቤቶቻችን፣ ሌሎች የሕግ ባለሙያዎችና ህብረተሰቡ በአጠቃላይ ለጥረታችን እውን መሆን የማይተካ ድርሻ አላቸውና ከጎናችን እንዲቆሙ ጥሪየን አስተላልፋለሁ፡፡

ተገኔ ጌታነህ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ፕሬዝዳንት

## በ2001 እና በ2002 ዓ.ም. የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸውን ውሣኔዎች

## ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ወንጀል** | | | | 1 |
| 1 | በወንጀል ጉዳይ የክስ ሂደት የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱ ሊመዘን የሚገባ ስለመሆኑ | 35697 | የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ<br>እና<br>ከበደ ወርቅነህ | ጥቅምት 20/2001 | 2 |
| 2 | • በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ የተሻሻሉና የተለወጡ ሁኔታዎች ከነባሩ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ጋር በቀጥታ ተጣምረው ሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባ ስለመሆኑ<br>• በወ/ሕ/ አንቀጽ 543(3) የተከሰሰ ሰው የዋስ መብት የሚከለከል ስለመሆኑ<br>የወ/ሕግ አንቀፅ 543 የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 63 | 35695 | የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ<br>እና<br>አቶ ተመስገን አዲስ | ህዳር 11/2001 | 5 |
| 3 | በተወሰነበት ፍርድ ላይ ይግባኝ እንደሚል ፍላጐቱን አሳውቆ እያለ ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት በኩል በተከሰተ መጓተት የይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ፍርደኛ የሚያቀርበው የማስፈቀጃ አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ | 39722 | ግርማ ሃይሌ<br>እና<br>ዐቃቤ ህግ | ታህሣሥ 23/2001 | 7 |
| 4 | የዳኝነትን ሥራ በማከናወን ወቅት የሚፈፀሙ ስህተቶች እና ጥፋቶች ሁሉ ዳኛን በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል ወንጀል ሊያስጠይቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ. 214/74 | 33075 | አቶ ብርቁ ገላነው እና የአማራ ብ/ክ/መ/የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን | ጥር 19/2001 | 9 |
| 5 | አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉ የሚቋቋምበት ህጋዊ፣ ግዙፍዊና፣ ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተጣምረው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 | 38161 | እነ ጀሚላ መሐመድ ሐጉስ እና የፌዴራል የመ/ደ/ዐ/ህግ | የካቲት 19/2001 | 11 |
| 6 | በወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ንብረት የሆነ ንግድ መደብር ጋር በተገናኘ ፍ/ቤቶች የንግድ መደብሩን በውስጡ ከያዘው ሸቀጦች በመለየት (በመነጠል) የሚሰጡት ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ | 44594 | የፌ/ሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግ እና እነ ካፋ መሐመድ (አራት ሰዎች) | ሐምሌ 15/2001 | 13 |
| 7 | በወንጀል ጉዳይ በእስራት እንዲቀጣ የተወሰነበት ሰው የእስራት ቅጣቱን ሳይፈፀም በገደብ እንዲቆይ ወይም እንዲለቀቅ ሊደረግ የሚችለበት አግባብ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 82,192,194 | 46382 | እነ ዳንኤል ገ/ዮሐንስ (አራት ሰዎች) እና የፌዴራል ዐቃቤ ህግ | ሐምሌ 28/2001 | 16 |
| 8 | አንድ ተከሣሽ በተፈፀመ ወንጀል ላይ ተካፋይ ነበር ለማለት ተከሣሹ በሙሉ ፈቃዱና ዕውቀቱ በወንጀል ድርጊቱ ተሣታፊ የነበረ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32, 33, 630, 25 | 44031 | ወ/ሮ ፈለቀች ኃ/ገብርኤል እና የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ | ሐምሌ 30/2001 | 19 |
| 9 | ከተሽከርካሪ ጋር በተያያዘ በድንገተኛ አደጋ ለሚከሰት የሰው ህይወት መጥፋት አሽከርካሪው በቸልተኝነት ወንጀል በማድረግ ሊጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ አንቀፅ 59(1), 543(2) እና (3)፣57 (2) | 42703 | ፋሲል ብርሃኑ እና ዓቃቤ ሕግ/የኦሮሚያ ክልላዊ ብሔራዊ መንግስት/ | ሐምሌ 22/2001 | 22 |
| | **ንብረት** | | | | 26 |
| 10 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ካርታ በማቅረብ ብቻ የሚረጋገጥ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 | 36320 | ወ/ሮ ዘውዴ ገ/ስላሴ እና ወ/ሮ ህይወት ባህታ | ጥቅምት 18/2001 | 27 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 11 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተገናኘ የንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ ተደርጐ ሊወሰድ የሚገባው ንብረቱን ለመገንባት የወጣው ወጪ (BooK value) ብቻ ሣይሆን ንብረቱ በወቅቱ ለገበያ ቀርቦ ሊያወጣ የሚችለው ዋጋ ( market value) ጭምር ስለመሆኑ | 35003 | አቶ አሽናፊ አብዱልቃድር እና እነ ወ/ሮ ሽቶ አብዱራሂም (አራት ሰዎች) | ህዳር 9/2001 | 29 |
| 12 | አንድ ተከራካሪ ተገቢነት ያለው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ አቅርቧል ለማለት ለክርክር መንስኤ የሆነው ንብረት በእጅ አድርጎ መገኘትና በዚሁ ንብረት ላይ በእውነት ለማዘዝ እንዲችል የንብረቱ አያያዝ ያልተጭበረበረና በማናቸውም መንገድ ህገ-ወጥ በሆነ ሁኔታ ያልተገኘ መሆን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149(1) | 36645 | ረዳት ሳጂን አያኖ አንጀሎ እና እነ ወ/ሮ አለሚቱ ጫሌቦ | ህዳር 11/2001 | 31 |
| 13 | የጋራ ንብረትን ለመካፈል በሚደረግ ሽያጭ የጋራ ባለኃብት የሆነ ወገን የቅድሚያ ግዥ መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1261(2), 1386 — 1409 | 37297 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ እታለም ተስፋ | ታህሣሥ 2/2001 | 35 |
| 14 | የጋራ ሀብት የሆነ ንብረት በመያዣ የተያዘ በመሆኑ የቅድሚያ መብት ያለ ቢሆንም የጋራ ባለሀብት የሆነ ወገን ንብረቱ በግልፅ ጨረታ ቀርቦ የሚያወጣውን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ግማሽ በመክፈል ማስቀረት የሚችል ስለመሆኑ | 37298 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ አለምነሽ ዋቅጂራ | ታህሣስ 2/2001 | 38 |
| 15 | የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታን ለማቅረብ አቤቱታ አቅራቢው ክርክር የቀረበበት ንብረት ባለሀብትነቱን ሳይሆን ባለይዞታነቱን ብቻ ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ | 38228 | ሐጂ መሐመድ አወል ረጃ እና እነ አቶ ዲኖ በሺር (ሁለት ሰዎች) | ታህሣስ 7/2001 | 40 |
| 16 | ባለመሬቱ ሳይቃወም በሌላ ሰው መሬት ላይ ህንፃ የሰራ ሰው የህንፃው ባለሀብት ሊሆን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179 | 36638 | በላይ አበበ እና እነ አበራሽ ዋቅጅራ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 21/2001 | 42 |
| 17 | በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ያለው ባንክ በንብረቱ ላይ ሊኖረው የሚችለው የመብት አድማስ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/, 3088/1/, 3110/ሐ/ | 36013 | ወ/ሮ ዘምዘም ኑሩ እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | ታህሣሥ 21/2001 | 45 |
| 18 | የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን የሁከት ተግባር ፈጽሟል ከሚባለው ሰው የተሻለ የይዞታ መብት ያለው መሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149 | 39940 | ወ/ሮ ነጂባ ነጋሽ እና ወ/ሮ ዚያዳ ዱታሞ | ግንቦት 27/2001 | 49 |
| 19 | ንብረትነታቸው የመንግስት የሆኑ ቤቶችን በተመለከተ የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ መንግስትን ወክሎ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2) | 38169 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የወ/ሮ ንጋቷ ዘለቀ ወራሽ አቶ እሸቱ ቦጋለ | ግንቦት 12/2001 | 51 |
| 20 | የይዞታ መብት ፍፁም ስላለመሆኑ እና በህግ አግባብ ይዞታው የተወሰደበት ሰው ተገቢ የሆነ ካሣ የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149(1), (2) አዋጅ ቁ. 7/1986 አንቀጽ 2(5), 21, 22, 24, 23 በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ- መንግሥት አንቀጽ 40 (8) አዋጅ ቁ. 455/1997 | 39539 | የአዲስ አበባ አስተዳደር ግብርና ቢሮ እና እነ አቶ አበበ ዓባይ(ዘጠኝ ሰዎች) | ሐምሌ 30/2001 | 53 |
| 21 | ከህግ የሚመነጭ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብትነትን አስመልክቶ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ | 38666 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ባላንባራስ ተስፋዬ ገ/እየሱስ | ሐምሌ 9/2001 | 56 |
| | **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | 58 |
| 22 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 2143 ላይ የጉዳት ካሣን አስመልክቶ የቀረበው የይርጋ ድንጋጌ የሞት ጉዳትን የሚያካትት ስለመሆኑ | 34544 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ወ/ሮ ፋጤ ዓሊ | ጥቅምት 11/2001 | 59 |
| 23 | ማንም ሰው ሥራው በሚያደርሰው ጉዳት ምክንያት ጥፋት ባይኖርበትም ከውል ውጭ ሃላፊነት ሊከተልበት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066- 2089(2069(1)) | 33201 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና ሼል ኢትዮጵያ | ጥቅምት 27/2001 | 61 |
| 24 | ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው (ልጅ) ሃላፊነትን የሚያስከትል ሥራ የሰራ እንደሆነ ወላጆች በፍ/ብሔር በሃላፊነት ሊጠየቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2125, 2124 | 31721 | ወ/ሮ ብዙነሽ ኃ/ዮሐንስ እና ወ/ሮ ስንታየሁ እሸቱ | ጥቅምት 25/2001 | 63 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 25 | የጉምሩክ ባለሥልጣን ተግባር ህጋዊ ነው ሊባል የሚችለው በህጉ መሠረት ሊሟሉ የሚገቡትን ሁኔታዎች አሟልቶ ሲገኝ እንጂ በማናቸውም ጥርጣሬ ምክንያት የግለሰብን ንብረት በመያዝ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.60/89 አንቀጽ 6, 58<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 2(28)<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26(1)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1193(1),(2), 2027, 2035, 2054, 2118 | 31171 | አብልሃሚድ የሱፍ እና የምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ ጽ/ቤት | ጥቅምት 27/2001 | 65 |
| 26 | ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ ከሆነና ጉዳቱ በተጐጂው የወደፊት ህይወት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር እንደሚችል ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለ እንደሆነ ካሣ ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ | 35034 | እነ ወ/ሮ ጥሩቀለም ደሴ እና እነ ወ/ሮ ጽጌ ከፍያለው | ጥቅምት 6/2001 | 68 |
| 27 | ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት የሰው ህይወት የጠፋ እንደሆነና ለጉዳቱ መንስኤ (ምክንያት) የሆነው ወገን ሃላፊነት የተረጋገጠ ከሆነ በጠፋው የሰው ህይወት የተነሣ ጉዳት የደረሰበት ሰው የሞተው ሰው ምን ያህል ጥቅም ያስገኝለት እንደነበር ወይም ምን ያህል ተጨማሪ ዕድሜ ሊኖር እንደሚችል ያላስረዳ ቢሆንም እንኳን ፍ/ቤት የጉዳት ካሣውን በርትዕ ሊወስን የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102 | 34314 | ወ/ሮ ግምጃ ኀበና እና እነ አቶ ወንድወሰን ወልዴ (ስድስት ሰዎች) | ህዳር 11/2001 | 71 |
| 28 | የጉምሩክ ባለሥልጣን ያለአግባብ በቁጥጥሩ ሥር አድርጐ ለሚያቆየው ንብረት በባለንብረቱ ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ በኃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ | 31704 | አቶ አማረ መኳ እና የድሬዳዋ ለጋር ጉምሩክ | ጥር 29/2001 | 74 |
| 29 | በጥቅም ላይ ባልተመሰረተ ግንኙነት በመኪና ተሣፍሮ የሚሄድ ተሣፋሪ ላይ ለሚደርስ አደጋ የመኪናው ባለቤት ካሣ የመክፈል ሃላፊነት የማይኖርበት ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089 | 38457 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ተመኝሁ እንደሻው | ሰኔ 2/2001 | 77 |
| | **የዳኝነት ስልጣን** | | | | 79 |
| 30 | የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የውርስ አጣሪ የመሾም ሥልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ እና በአዲስ አበባ መስተዳደር ውስጥ የውርስ አጣሪ ይሾምልኝ ጥያቄን የማየት የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1) (ሸ)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996(1) | 35657 | እነ ወ/ሮ እመቤት መክብብ እና አቶ በድሉ መክብብ | ጥቅምት 6/2001 | 80 |
| 31 | የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች ለክርክር መነሻ የሆነው ክስ በገንዘብ ሊተመን የማይችል የመብት ጥሰትን የተመለከተ በሆነ ጊዜ የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 50(1), 39 | 36338 | ገ/መስቀል ደመወዝ እና ወ/ሮ አፀደ መኰንን | ጥቅምት 25/2001 | 83 |
| 32 | የቅኔ መምህርነት ቀጥተኛ የሆነ መንፈሣዊ ሥራ በመሆኑ በሥራ ክርክር ችሎቶች ሊስተናገድ የሚችል ስላለመሆኑ | 34440 | መንበረፓትሪያክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና መ.ጋቢ. ሚስጢር መዝገቡ በላይነህ | ጥቅምት 6/2001 | 85 |
| 33 | የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የቤት ባለቤትነት ክርክር የቀረበበትን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(ረ) | 33841 | አቶ አስጨናቂ ረጋሣ እና እነ አቶ ገዛኸኝ ነጋሽ (ስድስት ሰዎች) | ጥቅምት 6/2001 | 87 |
| 34 | በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ በወታደርነት በማገልገል ላይ የሚገኙ የሠራዊት አባላት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የወንጀል አቤቱታዎችን ለማስተናገድ ወታደራዊ ፍ/ቤቶች ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.27/88, አዋጅ ቁ. 343/94 አንቀፅ 2(9),26(1) | 33368 | ሻምበል አሰፋ በላይ ዘገየ እና ወታደራዊ አቃቤ ህግ | ህዳር 9/2001 | 89 |
| 35 | የአ.አ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች በከተማው አስተዳድር ሥር ካሉ ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮችን ብቻ ለማየት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ | 34788 | የሟች አቶ ሰለሞን ሳሙኤል ወራሾች እና ማርታ ሰለሞን (2 ሰዎች) | ህዳር 2/2001 | 92 |
| 36 | በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በፍርድ ቤት ቀርቦ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚችል ስላለመሆኑ | 31906 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የአቶ መርስኤ መንበሩ ወራሾች | ህዳር 4/2001 | 94 |
| 37 | በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ከተወረሱና በቀላጤ ከተያዙ ቤቶች ውጭ ያሉ ቤቶችን አስመልክቶ የሚነሣ የቤት ክርክር ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች ማየት የሚችሉ ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ.47/67<br>አዋጅ ቁ. 110/87 | 37281 | አቶ አበበ ዓሊ እና እነ የ08 ቀበሌ ገ/ማህበር (ሦስት ሰዎች) | ታህሣሥ 16/2001 | 98 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 38 | በውጭ አገር የሚገኝ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ ክርክርን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማስተናገድ ስለመቻሉ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 37, አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ(4) | 37339 | ወ/ሮ ንግስት ኃይሌ እና አቶ ለገሠ ዓለሙ | ጥር 28/2001 | 101 |
| 39 | ወደ ቀድሞ የሥራ መደብ እንድመለስና ለመደቡም የተሰጠው ልዩ ጭማሪ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄ የወል ሥራ ክርክር ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ142(1) (ሀ) | 37016 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ማሞ | የካቲት 3/2001 | 104 |
| 40 | ከጉምሩክ ፖሊስ አባላት ጋር በተያያዘ የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን ለማየት የሚያስችል ስልጣን ለመደበኛ የሥራ ክርክር ችሎቶች ያልተሰጠ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 368/96 , አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 8(2) , መመሪያ ቁ.4/1996 | 39085 | የኢትዮትያ ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና እነ ወ/ር አስረሳች ወርቅነህ<br>(ሰማንያ ሰባት የጉምሩክ ፓሊሶች) | የካቲት 3/2001 | 106 |
| 41 | ቀደም ብሎ የተሰጠን የፍች ውሣኔ ወደጐን በመተው አዲስ የተደረገን ጋብቻ ህገ ወጥ ነው ማለት የማይቻል ስለመሆኑ | 38745 | እነ ወ/ሮ ሣሊያ ኢብራሂም (ሁለት ሰዎች) እና ሐጂ ሰማን ኢሣ | መጋቢት 10/2001 | 108 |
| 42 | የሸሪዓ ፍ/ቤቶች የይዞታ ክርክርን ማስተናገድ የማይችሉ ስለመሆናቸው | 36677 | ወ/ሮ ሻምሺ የኑስ እና ወ/ሮ ኑሪያ ማሚ | ሚያዝያ 30/2001 | 111 |
| 43 | የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀጮ እና ወለድ ላይ የሚቀርብ ይግባኝን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው ስለመሆኑ | 37866 | ሙሉጌታ አባይ እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን | ግንቦት19/2001 | 113 |
| 44 | የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶችም ሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳዬችን ለማየት የሚያስችል ስልጣን በህግ ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ | 41608 | እነ ሙላቱ አንበርብር<br>እና ወ/ት ታመነች ዮሴፍ መና | ሐምሌ 22/2001 | 115 |
| | **ባንክና ኢንሹራንስ** | | | | 117 |
| 45 | ዕቃዎችን ለሚያጓጉዝ የጭነት መኪና የተገባ የመድን ዋስትና ጋር በተያያዘ በመኪናው ላይ ተሣፍሮ ሲሄድ ለነበረና አደጋ ለደረሰበት ሰው መድን ሰጪው የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ | 42139 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ብያን ኡመር | ሰኔ 30/2001 | 118 |
| 46 | ኢንሹራንስ ሰጪ በውሉ መሠረት ከፈፀመ በኋላ በተሸሸገ ወይም በሀሰት ቃል የቀረበ ጉዳይ አጋጥሟል በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ የተሸሸገውን ወይም በሐሰት የቀረበውን ቃል ካወቀበት ቀን ጀምሮ ባለው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ 674(1),(2) | 42309 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ሰኔ 30/2001 | 120 |
| | **ውክልና** | | | | 122 |
| 47 | አደራ ተቀባይ የሆነ ወገን በአደራ የተቀበለውን ዕቃ መመለስ ያለበት ለአደራ ሰጪው ወይም ይቀበልልኝ ብሎ ላመለከተው ሰው ስለመሆኑ | 38289 | ወ/ሮ ነጂሃ ድዋሌ ዋይስ እና አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማ | ሰኔ 23/2001 | 123 |
| 48 | መንግስታዊ የሆነ ተቋም በሚከሰስበትም ሆነ በሚከስበት ክርክር የሚቀርብ ሰነድ የፕሮቶኮል ቁጥር እንዲሁም ስለአቤቱታው ጽሁፍ ትክክለኛነት በሚመለከተው ኃላፊና በወኪሉ መፈረም ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 80, 92, 93 እና 92(3) | 43875 | በወላይታ ዞን የቦዲቲ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እና አቶ ወንድሙ ኃይሌ | ሐምሌ 16/2001 | 125 |
| 49 | የዕቃ አስተላላፊ አካል እንደ አጓዥ ሆኖ የሚቆጠረው ከወደብ የተረከበውን ዕቃ በራሱ ማጓጓዣ ካጓጓዘ ብቻ ስለመሆኑ<br>ደንብ ቁ.37/90 አንቀጽ 2(1), 3(6),(7)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2251<br>የንግድ ህግ .ቁ. 683(3) | 37799 | የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ሐምሌ 29/2001 | 127 |
| 50 | በወኪል በኩል የሚፈፀም የመኪና ጭነት ውል በአስጫኙ እና በመኪናው ባለቤት መካከል እንደተደረገ የሚቆጠር ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 566 እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2251 | 34621 | ኒያላ ኢንሽራንስ አ/ማ<br>እና<br>አቶ ሐጎስ ገ/መድህን | ሐምሌ 30/2001 | 129 |
| | **የንግድ ሕግ** | | | | 132 |
| 51 | የንግድ ድርጅት በህግ አግባብ ለባለመብቶች ሊከፋፈል የሚችልበት ሁኔታ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 127 | 33954 | ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ እና<br>አቶ ዘውዱ ቢረዳ | ጥቅምት 20/2001 | 133 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 52 | የአሽሙር ማህበር መፍረስ በንብረት ክፍፍል ረገድ የሚያስከትለው ውጤት | 33470 | ወ/ሮ እጅጋየሁ ታደሰ እና መገርሳ ጉደታ | ህዳር 2/2001 | 136 |
| 53 | የጋራ ሀብት የሆነ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደሌላ ማናቸውም ንብረት ባለበት ሁኔታ በዓይነት ሊከፋፈል ወይም ደግሞ በሃራጅ ሊሸጥ የማይችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 542 | 34945 | ወ/ሮ መስታወት በላቸው እና አቶ ለገሠ ሣህሉ | ህዳር 2/2001 | 138 |
| 54 | የንግድ መደብርን የተከራየ ወገን ይህንኑ የንግድ መደብር ለሌላ ሶስተኛ ወገን ያለአከራዩ ፈቃድ ማከራየት ስለመቻሉ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 145 | 31264 | ወ/ሮ እመቤት መኰንን<br>እና<br>ወረዳ 20 ቀበሌ 29 አስ/ጽ/ቤት | ጥር 5/2001 | 140 |
| 55 | በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ጋር በተያያዘ በቅን ልቦና ዋጋ ሰጥቶ ስለመዋዋል የተመለከተው ድንጋጌ የንግድ መደብርን በተመለከተ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1161<br>የንግድ ሕግ ቁ. 124 | 34586 | አቶ ያለው ድልነሳው<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረግ<br>(አራት ሰዎች) | ጥር 28/2001 | 143 |
| 56 | ቼክን አስመልክቶ ክስ በቀረበ ጊዜ የተከሰሰው ወገን የቀረበበትን ክስ ለመከላከል እንዲፈቀድለት የሚያቀርበው ምክንያት ፈቃድ ሊያሰጥ የሚችል መሆን ያለመሆኑን አግባብነት ካላቸው ህግጋት አኳያ መታየት ያለበት ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 717<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 284, 285 | 43315 | ብራንድ ኒው የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ማዕከል<br>እና<br>አቶ መስፍን ታደሰ | ግንቦት 18/2001 | 146 |
| **አእምሯዊ ንብረት** | | | | | 148 |
| 57 | አንድን የሥነ-ጥበብ(ኪነ-ጥበብ) ሥራ ያለባለቤቱ ፈቃድ ኦርጅናሉ ወይም ቅጅው ለህዝብ እንዲታይ ማድረግ የኮፒ ራይት ህግ ጥሰት የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1791, 1771(1), 1790, 2090-2123<br>አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀፅ 7 | 42253 | መምህር ሙሉ ኃይለሥላሴ<br>እና<br>ዘመናዊ ማተሚያ ቤት | ሐምሌ 8/2001 | 149 |
| **ልዩ ልዩ** | | | | | 152 |
| 58 | የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መዋቅር ባልተዘረጋባቸው ክልሎች የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ወክለው/ተክተው/ ክርክሮችን ማስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 139/1//ለ/,154/1/,153,140 | 21214 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ለማ ኩማ<br>(ሦስት ሰዎች) | ህዳር 4/2001 | 153 |
| 59 | • የጡረታ መዋጮ በመዘግየቱ ምክንያት በአዋጅ ቁ. 345/95 መሠረት ተጨማሪ ክፍያ ሊከፈል የሚችልበት አግባብ እና<br>አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀጽ 7(3), 52(1),56<br>• የጡረታ መዋጮ በ2 ዓመት ውስጥ እንደተከፈለ የህግ ግምት ሊወሰድበት የሚችል የክፍያ ዓይነት ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(ሠ) | 35391 | የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>አንበሣ ጫማ አ/ማ | ህዳር 25/2001 | 155 |
| 60 | የጥብቅና ፈቃድን ለማግኘት በህጉ የተቀመጡት መስፈርቶች ራሣቸውን ችለው መታየት ያለባቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 199/92 አንቀጽ 8(1) | 37375 | አቶ ሸምሱ ከድር አህመድ እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር | ህዳር 11/2001 | 158 |
| 61 | በከባድ የወንጀል ጉዳይ የተከሰሱ እና በራሣቸው ወጪ ጠበቃ ለማቆም ያልቻሉ ግለሰቦች በተመለከተ ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት የግለሰቦችን በጠበቃ የመወከል ህገ-መንግሥታዊ መብት መከበሩን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 13 (1) | 37050 | ሻምበል ሁሴን አሊ እና የሱማሌ ክልል ዐ/ሕግ | ታህሣሥ 30/2001 | 160 |
| 62 | ከዘር የወረደ ርስት ነው በሚል የመሬት ባለቤት ለመሆን የሚቀርብ ክስ ህገ-መንግስታዊ ያልሆነና ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 38237 | አቶ በርገና ሽፈራው እና እነ አቶ አብራሃም ሽፈራው(አራት ሰዎች) | ታህሣሥ 21/2001 | 163 |
| 63 | በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በተመሳሳይ ጉዳይ በፍ/ብሔር ለቀረበው ክስ በማስረጃነት ለመወሰድ ብቃትና አግባብነት ያለው ስለመሆኑ | 37184 | የሰሜን ቀጠና ጉምሩክ እና እነ ቄስ ብርሃን ንዋይ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 9/2001 | 166 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 64 | የመንግሥት መሥሪያ ቤት በጨረታ አማካኝነት የሽያጭ ውል አካሄዷል ተብሎ ሊገደድ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1688(2), 3167(1), 1688(2), 3168 | 37163 | የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን እና ህያብ ገ/መድህን ብረታ ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ | ታህሣሥ 23/2001 | 170 |
| 65 | አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ምንነት፣ የሚደረጉበት መንገድና ለአፈፃፀም የሚቀርቡበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3318, 3324, 3325, 3346, 1731<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 315, 319, 350, 357 | 38794 | አቶ ሙክሚል መሐመድ እና አቶ ሚፍታህ ከድር | መጋቢት 24/2001 | 173 |
| 66 | አስተዳደራዊ የሆኑ መስፈርቶች ባልተሟሉበት ሁኔታ ካርታ እንዲሰጥ የሚወሰን ውሣኔ ተገቢ ስላለመሆኑ | 39529 | ቦሌ ክ/ከተማ የመሬትና ልማት አስተዳደር እና እነ ወ/ሮ ግምጃ በዳኔ (ስድስት ሰዎች) | ግንቦት 11/2001 | 176 |
| 67 | ግምቱ ከብር 10,000 ብር በላይ ለሆነ የአፈፃፀም ክስ ሊከፈል የሚገባው ዳኝነት 25 ብር ብቻ ስለመሆኑ<br>የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ. 177/1945 አንቀጽ 2(ሠ) | 40752 | እነ ወ/ሮ ኤክራም መሃመድ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ዘኪ. መሐመድ | ሐምሌ 28/2001 | 179 |
| 68 | ከፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅት ሠራተኞች የሚሰበሰብ የሥራ ግብር ምንም እንኳን ሥራው የሚካሄደው በክልሎች ቢሆንም ወይም ሠራተኞቹ የክልል ነዋሪዎች ቢሆኑም ገቢ የሚደረገው ለፌዴራሉ መንግስት ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 96(3)<br>አዋጅ ቁ. 33/85 አንቀጽ5(2)(ሐ)<br>ደንብ ቁ. 109/96 | 40133 | የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን እና በሶማሌ ብ/ክ/መ የፊደልቱ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ገቢዎች ጽ/ቤት | ሐምሌ 2/2001 | 181 |
| | **አሰሪና ሰራተኛ** | | | | 184 |
| 69 | የግንባታ ዕቃዎች እጥረት አጋጥሟል በሚል የሚደረግ የሥራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 26,28,30 | 41385 | ጊጋ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና እነ ተረፈ ዘርጋው (ስድስት ሰዎች) | ጥቅምት 3/2002 | 185 |
| 70 | የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት አድርጐ ከሚቀርብ ክርክር ጋር በተገናኘ በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሣኔ ሣይሰጥ ከተጠየቁት ዳኝነት መካከል ወደ ሥራ የመመለስ ጉዳይ ላይ ብቻ ውሣኔ ከተሠጠና ሠራተኛው ወደ ሥራ መመለስ ሳይፈልግ ቢቀር ቀድሞ ዳኝነት በጠየቀባቸው ነገር ግን ውሣኔ ባላረፈባቸው ነጥቦች ላይ ዳኝነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(3) | 42361 | ወ/ት ትዕግስት ንጉሴ እና ኤስ.ኦ.ኤስ ኢንፋንት ኢትዮጵያ | ጥቅምት 5/2002 | 187 |
| 71 | በትርፍ ሰዓት በሌላ መሥሪያ ቤት ሰርተሃል በሚል ሠራተኛን ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል የህግ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ 377/96 አንቀፅ 27 | 42818 | አቢሲኒያ ባንክ አ.ማ እና ወ/ር ሙሉታ ገዳ | ጥቅምት 10/2002 | 189 |
| 72 | አሰሪ በግልፅ ባልፈቀደበት ሁኔታ በሁለት ቦታ በተመሳሳይ ጊዜ መስራት ሠራተኛውን የማታለል ተግባር እንደፈፀመ የሚያስቀጥረው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ) | 41767 | የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና አቶ አድማስ ደምሳቸው | ህዳር 8/2002 | 190 |
| 73 | አሰሪ የእድገት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት እና መስኪያ መስፈርቶችን አዘጋጅቶ በሠራተኞቹ መካከል በክፍያ ረገድ ልዩነት ማድረግ ስለመቻሉ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 14(1)(ረ)<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት 42(1)(መ) | 42923 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ሮ ነጃት አባስ | ህዳር 22/2002 | 192 |
| 74 | ሥራውን በገዛ ፈቃዱ የሚለቅ ሰራተኛ የስንብት ክፍያ ለማግኘት የሚችለው ቢያንስ የ5 ዓመት አገልግሎት ያለው እንደሆነ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(ሸ) | 44410 | ወ/ሮ ላይላ ረዲ እና ድሬ ኢንዱስትሪዎች ኃ/የተ/የግል ማህበር | ኅዳር 01/2002 | 195 |
| 75 | በአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ "በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት" ወይም "በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ" በሚል የተቀመጠው ሐረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 95/2/,97,96 | 47807 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ ፈንታው (ሁለት ሰዎች) | ታህሳስ 06/2002 | 198 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 76 | አሰሪ ሠራተኞቹን በማስተዳደር ረገድ የሚፈፅማቸውን ስህተቶች በራሱ አነሣሽነት ሊያርም የሚችል ስለመሆኑ | 45889 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፓሬሽን ደቡብ ሪጅን እና ሳሙኤል ቁለቦ | ታህሣሥ 20/2002 | 201 |
| 77 | በክርስትና ሃይማኖት ተቋም ውስጥ በዲያቆንነት ሥራ ከማገልገል ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የሥራ ክርክር ጉዳዮች በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት ሊስተናገዱ የማይችሉ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 | 47806 | የሆህተሰማይ ቅድስት ማሪያም ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት እና ዲያቆን አያሌው አዲሱ | ታህሣሥ 20/2002 | 203 |
| 78 | በጡረታ የተገለሉና ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ቋሚ ሠራተኞች የሚያገኟቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት መብት የሌላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 10 | 47469 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ስዩም ገብረፃዲቅ(ሃያ ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 15/2002 | 205 |
| 79 | በሥራ ክርክር ጉዳይ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1853 ላይ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 164(3)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1853,1852 | 47784 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>አለምፀሐይ አያና | ታህሣሥ 20/2002 | 208 |
| 80 | በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት የሥራ ግንኙነት በአንቀፅ 30 መሠረት ሲቋረጥ አሰሪ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 30, 28(2) | 49057 | አስመላሽ እና ልጆቹ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ዮሐንስ እሺበል | ጥር<br>5/2002 | 211 |
| 81 | የጡረታ መብት ያለው እና መደበኛ የጡረታ ዕድሜው ደርሶ የተሰናበተ ሰራተኛ የስንብት ክፍያ ለማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2/2(ሰ) እና (ሽ) | 46276 | ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት እናእነ ኃይሌ ይማም<br>(ሁለት ሰዎች) | የካቲት 11/2002 | 213 |
| 82 | • አንድ ድርጅት በመክሰሩ ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቄታው በመዘጋቱ የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኞች የስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው የሚገባ ስለመሆኑ<br>• ድርጅት ለዘለቄታው እንዲቆም የሚያደርግ ሁኔታ ሲከሰት ማስጠንቀቂያ ለሠራተኞች መስጠት ያለበት ስለመሆኑ | 42985 | ውድ መጣስ ኑሮ አስመጪና ላኪ ድርጅት እና እነ አቶ ሁነኛው ሰጠ (አስራ አንድ ሰዎች) | የካቲት<br>25/2002 | 215 |
| 83 | የጠብ አጫሪነት ኃይለ ቃልና ዛቻ አዘል ንግግር በሥራ ቦታ ላይ ማድረግ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብት ጥፋት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)(ረ) | 49958 | ግዩን ትራቭልና ቱርስ<br>ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>አቶ ዳንኤል አስፋው | የካቲት<br>12/2002 | 217 |
| 84 | በሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ ለሠራተኛው ጥገኞች ስለሚከፈል ካሣ፣ ካሣው የሚከፈልበትና የሚሰላበት ሁኔታ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 110 | 40529 | የህፃን ዮናታን ነጋ ተሻገር ጠ/ጥጋቡ ጌጤ<br>እና<br>አቶ ለገሠ አበራ | የካቲት<br>10/2002 | 219 |
| 85 | በአሰሪና ሰራተኛ በኩል በአጠቃላይ ለፕሮጀክት ሥራ በሚል የተደረገ የሥራ ውል በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ አንቀጽ 10(1)(ሀ) መሰረት የተደረገ እንደሆነ ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሀ) | 48648 | የፃልቂ የትምህርትና የተቀናጀ የልማት ማህበር<br>እናእነ አቶ ታጠቅ ደጀኔ<br>(ሁለት ሰዎች) | የካቲት 24/2002 | 222 |
| 86 | ሠራተኞችን ለማበረታታት በሚል የሚደረግ የደመወዝ (ጥቅማጥቅም) ጭማሪን መሠረት በማድረግ ጭማሪውን የሚፈቅደው መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የሥራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ የሚጠይቀው መብት የሌለ ስለመሆኑ | 47825 | የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (አ.ማ) እና እነ አቶ ዘርዓየሁ ሰሜ<br>(ሁለት ሰዎች) | የካቲት<br>25/2002 | 224 |
| 87 | አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ ከሚፈፅመው ጥፋት ጋር በተያያዘ ከሥራ ታግዶ ሊቆይ ስለሚችልበት ሁኔታ በህብረት ስምምነት ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 | 47535 | የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት<br>እና አቶ እንማው ላቀው | መጋቢት 20/2002 | 226 |
| 88 | • የአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ አሰሪና ሰራተኛ ስምምነት ሊያደርጉባቸው የሚችሉበት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ጥፋትንና ጥቅምን በተመለከተ የተለያየ አቋም የያዘ ስለመሆኑ<br>• አሰሪና ሠራተኛ በህብረት ስምምነታቸው ውስጥ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት በሚል የተስማሙበት ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 134(2), 27(1)(ሽ) | 49750 | በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/01 የመዝናኛ ክበብ<br>እና<br>አቶ ማስረሻ ሁሴን | መጋቢት 30/2002 | 228 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 89 | አሠሪ የሠራተኛውን የሥራ ውል ያቋረጠበትን ምክንያት በፅሁፍ አለመግለፁ ብቻ ስንብቱ ህገ- ወጥ ነው ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(2) | 49797 | አልሀበሽ ሹገር ሚልስ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>ተገኔ ገ/ሃዋሪያት | መጋቢት 30/2002 | 230 |
| 90 | በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ውስጥ "እንደ ጥፋቱ ክብደት በሥራው ላይ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር መፈፀም" በሚል የቀረበው አባባል (አነጋገር) ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ) | 50009 | የአዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል<br>እና<br>አቶ ዮናስ ጥላሁን | መጋቢት<br>6/2002 | 232 |
| 91 | አሠሪና ሠራተኛ የሥራ ውል መቋረጥ ጋር በተያያዘ በሥራ ውሉ ላይ የሚያመለክቱት ሁኔታ የአሰሪና ሠራተኛ ህጉን እስካልተፃረረ ድረስ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ | 50205 | የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት<br>እና<br>አቶ ምናለ በሪሁን | መጋቢት 20/2002 | 234 |
| 92 | የሥራ ውል በተቋረጠ ጊዜ አሰሪው ከሠራተኛው በህግ አግባብ የሚፈልገው/ የሚጠይቀው ዕዳ ያለ እንደሆነ ለሠራተኛው የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀት ከመስጠት ባሻገር የሥራ መልቀቂያ (ክሊራንስ) ለመስጠት የማይገደድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀፅ 78 (1),87 | 48476 | የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት እና አቶ ደረጀ መኮንን | ሚያዝያ 12/2002 | 236 |
| 93 | ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የሚደርስበትን ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ወይም ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት በማለት ለመለየት የሚቻልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 101 (2) | 49273 | አቶ ደረጀ ውለታው<br>እና<br>ዋሊያ ሌዘርና ሌዘር ፕሮዳክትስ ኃ/የተ/የግል ማህበር | ሚያዝያ 27/2002 | 238 |
| 94 | • አንድ ሰው በአፈፃፀም ሊገደድ የሚችለው በህግ አግባብ የተፈረደ ፍርድ ሲኖር ብቻ ስለመሆኑ<br>• በግልፅ ፍርድ ያላረፈበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 | 50148 | እነ አቶ ወርቁ ደረጀ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ አባርኪር ሁመድ | ሚያዝያ 4/2002 | 240 |
| 95 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ ከሠራተኛው ጋር ያለው ግንኙነት ሠራተኛው ወደ ሥራ ቢመለስ ችግር ውስጥ እንደሚወድቅ በአሠሪው ስለተገለፀ ብቻ ሠራተኛው ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት በሚል የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/ | 49931 | የጎሽና እርግብ መለስተኛና አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሽ ባለንብረቶች ማህበር<br>እና<br>አቶ ተሰማ ኃይሉ | ሚያዝያ 21/2002 | 242 |
| 96 | የድርጅት መዋቅራዊ ለውጥ ያደረገ ተቋም በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ መሠረት ሠራተኞቹን አዲስ በሚያወጣው የሥራ መደብ ላይ ተመርኩዞ የሥራ ምደባ ሊያከናውን የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 28 | 50838 | ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት እና እነ አቶ አማረ አበራ<br>(ሰባት ሰዎች) | ሚያዝያ 12/2002 | 244 |
| 97 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪ ሠራተኛው የፈፀመውን ድርጊት መሠረት አድርጐ ለማሰናበት የሚችለው የሥራ ውሉን ለማቋረጥ ምክንያት የሆነው ነገር መከሰቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ ሰላሳ ቀናት ውስጥ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(3) | 45746 | ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል/ማህበር<br>እና<br>አቶ በለጠ ጫላ | ሚያዝያ<br>6/2002 | 246 |
| 98 | ሠራተኛ የተረከባቸውን ንብረቶች አላስረከበም ወይም አጉድሏል በሚል የሥራ ውሉ በተቋረጠ ጊዜ የሚጠይቃቸውን ተገቢ ክፍያዎች ሊጠይቅ አይችልም በሚል በአሠሪው የሚቀርብ ክርክር ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 36,37,38 | 44405 | ፊንፊኔ የቢትና የቢሮ ዕቃዎች ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና አቶ ደጃ ደምሴ ጎበና | ግንቦት<br>19/2002 | 248 |
| 99 | ወደ ሥራ እንዲመለስ ፍርድ የተሰጠ እንደሆነና በአሰሪው ችግርም ሆነ በሠራተኛው ፍላጐት በፍርዱ መሠረት ወደ ሥራ ለመመለስ ሠራተኛው ያልፈለገ ከሆነ ሠራተኛው የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ በምትክነት በሰጠው መብት መሠረት በመመለሱ ፈንታ ካሣ እንዲከፈለው አፈፃፀሙን ለያዘው ችሎት ጥያቄውን ባቀረበ ጊዜ ሊስተናገድ የሚገባው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(3) | 53064 | አቶ ደራሳ ኮቱ<br>እና<br>የአምቦ ገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩኒየን | ግንቦት 17/2002 | 250 |
| 100 | በድርጅት ውስጥ የተከሰተ ተጨባጭ ችግርን ለመቅረፍና የድርጅቱን ትርፋማነት ለማስቀጠል በሚል በተመሳሳይ ሙያና ደረጃ ላይ ካሉ ሠራተኞች መካከል ተለይቼ ወደ ሌላ የሥራ መደብ ስለተዛወርኩኝ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ | 50182 | የአዲስ አበባ ቁራዎች ድርጅት እና አቶ አበበ ተፈራ ይልማ | ግንቦት<br>13/2002 | 252 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 101 | የሥራ ውል የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ ነው በሚል ክርክር በቀረበ ጊዜ ይህንኑ የማስረዳት ሸክም የሚኖር ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 9 | 44218 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና<br>እነ አቶ ታጁ አባጋሮ (ሃያ አንድ ሰዎች) | ግንቦት 13/2002 | 254 |
| 102 | አንድ አሰሪ በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበትን ሰራተኛ ወደ ውጭ አገር ልኮ ስለሚያሳክምበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 124,105 | 46363 | ሚሊኒ ኮንስትሩቶሪ ኤስ.ፒ.ኤ<br>እና<br>አቶ ትግሉ ፍሬህይወት | ግንቦት19/2002 | 257 |
| 103 | • ከአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት ጋር በተገናኘ ሁለቱ ወገኖች አዋጅ ቁ. 377/96 "ን" ወደ ጐን በማድረግ በሌላ አገር ህግ ለመዳኘት ስምምነት ያደረጉ በመሆኑ ብቻ ጉዳዩ የግለሰብ አለም አቀፍ ህግ ጥያቄን ያስነሳል በሚል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊስተናገድ የማይገባ ስለመሆኑ<br>• አዋጅ ቁ. 377/96 የውጭ አገር ድርጅት ሆኖ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሚሰራ የበጐ አድራጐት ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/3/ /ለ/ | 50923 | ፋውንዴሽን አፍሪካ<br>እና<br>አቶ አለሙ ታደሰ | ግንቦት 19/2002 | 260 |
| 104 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሚነሣው የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚሰላው የሥራ ቀናትን ብቻ በማስላት ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 163(2) | 51912 | የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እና<br>ወ/ሮ ሶፋኒት አጥናፉ | ሰኔ 7/2002 | 263 |
| 105 | • በአሰሪ የተፈፀመው የሥራ ስንብት ህጉ- ወጥ ቢሆንም ከሥራ ግንኙነቱ ፀባይ የተነሣ ከፍተኛ ችግር የሚፈጠር በሆነ ጊዜ ሠራተኛውን ወደ ሥራ ከመመለስ ይልቅ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ<br>• የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀፅ 43(3) በአንድ በኩል የሠራተኛን የሥራ ዋስትና በሌላ በኩል ደግሞ የኢንዱስትሪን ሰላም በማመዛዘን ትርጉም ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑ | 55189 | አዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል<br>እና<br>አቶ ዘላለም መንግስቱ | ሰኔ 30/2002 | 266 |
| 106 | በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ‹‹… ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱን ካወቀበት…›› በሚል የተመለከተው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(3) | 53358 | የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>አቶ ጥላሁን ኩማ | ሰኔ 18/2002 | 268 |
| 107 | አንድ የሥራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ የተደረገ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 9,10 | 43160 | እነ እንደገና ተሾመ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ኒው ጀኔሬሽን ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ነቀምቴ ቅርንጫፍ | ሰኔ 22/2002 | 270 |
| 108 | በማናቸውም ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኛው ያልወሰደው የዓመት እረፍት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል የሚገባ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 77(5) ,24(2) | 52459 | እነ ወ/ሮ ሙሉ ታደሰ<br>እና አለሙ መራ ኮንስትራክሽን ጠቅላላ ብረታ ብረት ሥራ ድርጅት | ሐምሌ 16/2002 | 272 |
| 109 | በክረምት ወቅት የማስተማር ሥራ እንዲሠራ የሚያዝ ግልፅ ደንብ ወይም መመሪያ የሌለ እንደሆነ ወይም አስተማሪው በክረምት ወራት ለማስተማር የገባው የውል ግዴታ (ስምምነት) በሌለ ጊዜ በክረምት ወቅት ሥራን ለመስራት ፈቃደኛ አልሆነም በሚል ከሥራ ሊሰናበት የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 13(1) | 45170 | የቅድስት ማሪያም አፀደ ህፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት<br>እና<br>መ/ት ሲሳይ ሙሉጌታ | ሐምሌ 8/2002 | 274 |
| | **የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | 276 |
| 110 | በክርክር የግድ ተካፋይ ሊሆኑ የሚገባቸው ወገኖች እና የፍ/ቤት ሚና<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 39,(1),40(2) | 43424 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና<br>እነ አቶ መስፍን /ስምንት ሰዎች/ | ጥቅምት 10/2002 | 277 |
| 111 | የቃል ክርክር እንዲሰማ በተቀጠረበት ዕለት ግራ ቀኝ የሆኑ ወገኖች ያልቀረቡ እንደሆነ መዝገቡ መዘጋት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 69(2) | 43410 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ<br>እና ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል | ህዳር 30/2002 | 280 |
| 112 | አንድን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ተለይቶ የተመለከተ ማስረጃ እንዲቀርብ ህጉ ካላስገደደ በቀር ይህንን ፍሬ ነገር በማንኛውም የማስረጃ ዓይነት ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ | 47551 | ንግድ ማተሚያ ድርጅት እና አቶ ካሱ ሙላት | ታህሣሥ 6/2002 | 282 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 113 | ጣልቃ በመግባት በክርክር ተሳታፊ ለመሆን ጠይቆ የተፈቀደለትና የጣልቃ ገብነት አቤቱታውን ለተከራካሪ ወገኖች ማድረስ ሲገባው ይህን ባለመፈፀሙ መብቱ ከተሰረዘበት በኋላ ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሣኔ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41,358 | 40229 | ወ/ሮ ኸይሮ መሐመድ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መዲና በያን<br>(ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 15/2002 | 284 |
| 114 | በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠበት ተከራካሪ ወገን ፍ/ቤቱ ለጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት አቤቱታው ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70(ሀ), 78,69,72 | 43731 | ሲ..ጂ..ሲ..ኦቨርሲስ ኮንስትራክሽን<br>ኢትዮጵያ ሊሚትድ እና<br>ሰለሞን እንዳለ | ታህሣሥ<br>8/2002 | 286 |
| 115 | • በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280 መሠረት መዝገብ ሊዘጋ የሚችልበት አግባብ<br>• ተከራካሪ ወገኖች በአቤቱታቸው ዳኝነት የሚጠይቁበትን ፍሬ ነገር በአግባቡ ከገለፁ ትክክለኛውን የህግ ድንጋጌ አለመጥቀሳቸው መብታቸውን የሚያስቀር ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280,69(2), 70(መ), 71(2) | 39581 | አቶ ውብሸት ካሣዬ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ማዕድን ሃብት ኮርፖሬሽን | ጥር<br>25/2002 | 288 |
| 116 | ተከራካሪ ወገኖች በአቤቱታቸው ላይ የጠቀሷቸውን የሰው ማስረጃዎች ሊለውጡ (ሊቀይሩ) የሚችሉበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 223/2/,234 | 45984 | ኘሮፌሰር ረዳ ተ/ኃይማኖት እና አቶ ልመንህ ተፈራ | ጥር<br>26/2002 | 290 |
| 117 | የክርክር ጭብጥ የሚመሰረተው ከሳሽ የሚያቀርበውን ክስና ማስረጃ በተከሳሽ የቀረበውን  የመከላከያ መልስና ማስረጃ እንዲሁም ፍ/ቤቱ የቃል ምርመራ ሲያደርግ የሚያገኘውን ፍሬ ጉዳይ መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241,248 | 47252 | ወ/ሮ ፑሽፓላት ጆሴፍ<br>እና<br>አቶ ሠይፈ ጎሣዬ | የካቲት 26/2002 | 292 |
| 118 | ዳኝነት እንደገና እንዲታይ (Review of judgement) በሚል የሚቀርብ አቤቱታ አስቀድሞ በተሰጠ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የተባለበት ነው በሚል ምክንያት ብቻ ውድቅ ሊደረግ የማይገባ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም በሰበር ችሎት የተሰጠው የሕግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)(ሀ),(ለ) | 43821 | ወ/ሮ ትርሃስ ፍስሀዬ እና<br>ወ/ሮ ዘነበች በሪሁን | ጥር 5/2002 | 295 |
| 119 | ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ላይ በተሰጠ ትእዛዝ/ብይን ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6(3)(4) | 42871 | የቀድሞ ወረዳ 07 ቀበሌ 32 አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና ወ/ሮ ጆሮ ዋቅጅራ | ጥር 12/2002 | 301 |
| 120 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 421 መሠረት ክስ ለመመስረት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418,421 | 37214 | አቶ ተስፋዬ አለሙ<br>እና እነ ሐጂ ይማም ሙዘይን(ሦስት ሰዎች) | የካቲት<br>25/2002 | 304 |
| 121 | በፍ/ብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ | 44634 | አቶ ታዬ ሆሳዕና እና ወ/ሮ መሠረት ወልደየስ | የካቲት<br>22/2002 | 306 |
| 122 | ፍ/ቤቶች ለቀረበላቸው ክስ ምክንያት የሆነው ነገር መቋረጡን ወይም ጨርሶ መቅረቱን በክሱ ሂደት በማንኛውም ደረጃ በቂ በሆነ ማስረጃ በተገነዘቡ ጊዜ ክሱን ሊዘጉት የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280 | 45371 | የገነተ-ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ማህበር በኩር ሰንበቴ<br>እና<br>እነ አቶ ማሞ ተሠማ<br>(ሦስት ሰዎች) | የካቲት 8/2002 | 308 |
| 123 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216 መሠረት በድጋሚ ክስ እንዳይቀርብ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216(3) | 36776 | መብራቱ፣ተ/ማሪያም፣ገ/ማሪያም<br>የሸርክና ማህበር እና አቶ መብራቱ ዓንዳይ | መጋቢት<br>7/2002 | 310 |
| 124 | ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር በዋናው ጉዳይ ላይ የራሱን ውሣኔ ካሣለፈና የበላይ የሆነ ፍ/ቤት ደግሞ የይግባኝ ውሳኔውን  ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በደፈናው በማፅናት የሚሰጠው ውሣኔ የተከራካሪ ወገን የይግባኝ መብት የሚያጣብብና የሥነ-ሥርዓት ህግ ደንብን የሚጥስ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341,342,343 | 44545 | ክፍሉ መሓሪ<br>እና<br>በላይ ከመላ | መጋቢት 7/2002 | 312 |
| 125 | የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለሰጠው ብድር በመያዣነት የያዘ ባለገንዘብ ባንክ መብቱ በይርጋ እስካልታገደ ድረስ የያዘውን ንብረት በጨረታ ለመሸጥ የሚገደድበት ተለይቶ በህግ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 97/90<br>አዋጅ ቁ. 216/92 አንቀፅ 2<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 394 - 449 | 44883 | አቶ ፈንታ ምህረቱ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | መጋቢት 8/2002 | 314 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 126 | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 ሊተረጉም የሚችልበት አግባብ | 39799 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ ገነት ስዩም | መጋቢት 21/2002 | 317 |
| 127 | • በተከራካሪ ወገኖች የሚቆጠሩ ማስረጃዎች ሳይሰሙ የሚቀሩት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የሌላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ<br>• ፍ/ቤቶች ተከራካሪ ወገኖች የቆጠሩትን ማስረጃ ሳይሰሙ ወደ ጐን በመተው አቤቱታቸውን በበቂ ማስረጃ አላስረዱም በሚል የሚደርሱበት መደምደሚያ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ | 43845 | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ጌታይዳ ኃ/የተ/የግል ማህበር | መጋቢት 20/2002 | 320 |
| 128 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 208 መሠረት በሥር ፍ/ቤት የተደረገ እርማትን መነሻ በማድረግ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ ለመለወጥ የሚያስችለው የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 208,209,320,(1) ,348(1) | 44931 | ወ/ሮ ሰዓዳ ኢድሪስ<br>እና<br>አቶ ረሺድ ቡባ | መጋቢት 20/2002 | 323 |
| 129 | የፍ/ቤትን ክብርንና የዳኝነት ሥርዓቱን መልካም አመራር ለማስጠበቅ ሲባል የማንኛውም ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ በችሎት ውስጥ በሚገኝ ማንኛውም ሰው ላይ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 480 | 48237 | ወ/ሮ ሰኢዳ ሁሴን ይመር<br>ተጠሪ፡የለም | መጋቢት 6/2002 | 325 |
| 130 | ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት ወደ ጉዳዩ ሥረ-ነገር ገብቶ ተከሳሽ የሆነን ወገን በሌለበት ባለዕዳ የሚያደርግ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ተከሳሹ በአግባቡ ስለመጠራቱ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 97, 95(3) | 50022 | 5 ብራዘርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና ዓብደላ ኢብሮ ዩሴፍ | መጋቢት 29/2002 | 327 |
| 131 | የንብረት ክፍፍል እንዲደረግ በፍርድ ቤት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በውሳኔው ወቅት ንብረቱን በእጁ አድርጐ የሚገኘው ወገን የንብረቱን ስመ ሐብት ወደ ሌላ ሦስተኛ ወገን አዛውሮ ሲገኝ ፍርድ ቤቶች ሊከተሉት ስለሚገባው አካሔድ | 45038 | እነ ወ/ሮ አለሚቱ ጓዱ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና ወ/ሮ አስረስ አህመድ | መጋቢት 23/2002 | 329 |
| 132 | • ሐሰተኛ ቃል ተሰጥቷል በሚል ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 481 መሠረት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ሊሰጥ የሚችልበት አግባብ<br>• በአንድ የወንጀል ድርጊት ነፃ የተባለ ሰው እንደገና ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጐ የሚቀጣበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 481 የወንጀል ህግ ቁ. 452(1) | 43005 | እነ አቶ አውግቸው እርገጤ<br>(ሦስት ሰዎች)<br>ተጠሪ፡የለም | ሚያዝያ 19/2002 | 331 |
| 133 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 መሠረት ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ለሰጠ ፍ/ቤት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 | 45839 | ወ/ሮ ይርጋለም ከበደ እና እነ ወ/ሮ ፅጌ ሚካኤል (አምስት ሰዎች) | ሚያዝያ<br>5/2002 | 333 |
| 134 | በፍ/ብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ መሠረት ተጨማሪ ማስረጃ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 256, 345, 327 | 39853 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና<br>እነ የአፋር ነፃ አውጪ ግንባር (ሁለት ሰዎች) | ሚያዝያ 21/2002 | 335 |
| 135 | አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ ከማስረጃ ምዘና ጋር የተያያዘና የፍሬ ነገር ክርክር ላይ ያተኮረ እንደሆነ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 80(3), አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 10 | 41526 | ትራንስ አፍሪካ ትራንስፖርት አ.ማ<br>እና<br>ሙሉ ኤሌክትሮኒክስ ኢንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር | ግንቦት 2/2002 | 338 |
| 136 | ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በእርቅ ለመጨረስ የተሰማሙና ይሄንኑም ስምምነት ለፍ/ቤት በማቅረብ ያስፀደቁ በሆነ ጊዜ ስምምነቱ እንደ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተቆጥሮ መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277 | 52752 | እነ ከድር ሐጂ ሁሴን (ሁለት ሰዎች)<br>እና እነ አቶ አሚን ዑስማን (ሁለት ሰዎች) | ሰኔ 16/2002 | 340 |
| 137 | ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው አቤቱታ የክስ ምክንያት አለው ወይም የለውም ብሎ ለመወሰን በክስ ላይ የተገለፀው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሽ የሆነው ወገን የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ህግ ይፈቅድለታል ወይስ አይፈቅድለትም የሚለውን ጥያቄ መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ | 45247 | አቶ ደጀኔ በላቸው እና አቶ ነስሩ አወል | ሰኔ 17/2002 | 343 |
| 138 | ሁለት ሰዎች ተጣምረው በተከሰሱ ጊዜ አንደኛው ወገን ጉዳዩ በሌለበት ከታየ በኋላ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተፈቀደለት እንደሆነ ሌላኛው ተከሳሽ አስቀድሞ ያነሳቸውን መቃወሚያዎች በድጋሚ ልታነሣና ልትከራከር አትችልም ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | 49857 | ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ ፋንታ<br>እና<br>ወ/ሮ በላይነሽ ወ/ኪዳን | ሰኔ<br>30/2002 | 346 |
| 139 | በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ ይቆጠራል የሚለው የሥነ- ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ተከሳሽ ቀርቦ ክርክሩን ባሰማ ጊዜ ስለመሆኑና ድንጋጌው የካሣ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 235(2),83 | 48632 | አቶ ሙልሳ በየቻ<br>እና<br>አቶ ደበሌ በየቻ | ሰኔ 14/2002 | 348 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 140 | ክስ የቀረበበት ወገን ክሱን ለማስተባበል የሚቆጥራቸው ማስረጃዎችን ተቀብሎ አለመስማት የመከላከል ህጋዊ መብትን የሚያጣበብ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ5 223, 234, 137, 249, 256 | 49660 | እነ መንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ት/ቤት (ሁለት ሰዎች) እና መምህር ሲሳይ ደጀኔ | ሰኔ<br>22/2002 | 350 |
| 141 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1) መሠረት በድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይቻለው በቀደመው ክርክር የተያዘው ጭብጥና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑና የተከራካሪ ወገኖች አንድነት በመኖሩ ብቻ ሣይሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | 52525 | ወ/ሮ የትምወርቅ ሰብስቤ<br>እና<br>አቶ ሸዋረጋ ደመቀ | ሰኔ<br>29/2002 | 352 |
| 142 | የሥር ፍ/ቤት በመቃወሚያ ላይ የሰጠውን ውሣኔ የሚለውጥ ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠ እንደሆነ በግራ ቀኝ ወገኖችን በኩል የሚቀርቡ የፍሬ ነገር ክርክሮችንና ማስረጃ በአግባቡ ለመስማት ብሎም የተከራካሪዎችን ይግባኝ መብት ላለማጣበብ ሲባል ጉዳዩ ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለስ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341(1) | 43331 | አቶ ገመቹ ቡቻላ<br>እና<br>አቶ በቀለ ኩማ (ቡቻላ) | ሐምሌ<br>19/2002 | 354 |
| 143 | ስልጣን ለሌለው የዳኝነት አካል ክስ ማቅረብና ክርክር ማካሔድ የይርጋ ጊዜን የሚያቋርጥ ስለመሆኑ ( ከዚህ ቀደም የሰበር ችሎት በተቃራኒው የሰጠው የህግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ።)<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 138, 147, 164(1)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9, 23,(1) (ለ) ,231,(1)(ለ), 278(3)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851 (ለ),1852(1)<br>አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀፅ 2(4) | 36730 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>አቶ አማረ ገላው | ሐምሌ 30/2002 | 356 |
| 144 | • በፍ/ብሔር ጉዳይ ተከሣሽ ለሆነ ወገን ከፍ/ቤት የሚላከውን መጥሪያ ለተከሳሹ ሊደርስ የሚችልበትን የተሻለ አማራጭ መንገድ በመለየት ሊላክ የሚገባ ስለመሆኑ<br>• የመኖሪያ አድራሻው በግልፅ ለሚታወቅ ተከሳሽ ፍ/ቤቱ የሚልከውን መጥሪያ በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ብቻ እንዲለጠፍ በማድረግ ተከሳሹ አልቀረበም በሚል በሌለበት ጉዳዩ እዲታይ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>• መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሰው ያልተደረገ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ የተሰጠበት ውሣኔ እንዲነሣለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 105(1), 78, | 50376 | ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ገሰሰ<br>እና<br>በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07/08 አስተዳደር ጽ/ቤት | ሐምሌ<br>12/2002 | 361 |

# ወንጀል

የሰ/መ/ቁ. 35697

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ - ዓቃቤ ሕግ አውግቸው መኮንን ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ከበደ ወርቅነህ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13840 ኅዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ታህሣሥ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በመጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የምዕራብ ጎጃም ዞን ዓቃቤ ሕግ በከሣሽነት ተጠሪ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ የዞኑ ዓቃቤ ሕግ በተጠሪ ላይ፣ መጋቢት 28 ቀን 1998 ዓ.ም. ከምሽቱ በግምት አራት ሰዓት ሲሆን የግል ተበዳይ የመኩሪያው ተጋፋውን ቤት በማቃጠል በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ተኝተው የነበሩት ይታይሽ አለማየሁ፣ አለባቸው መኩሪያውና ፋሲካ መኩሪያው በእሳት ተቃጥለው እንዲሞቱ ያደረገ በመሆኑና ድርጊቱን የፈፀመው በእሳት ቃጠሎ ምክንያት በውስጥ ያሉ ሰዎች ሊሞቱ እንደሚችሉ እያወቀ በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ 539/1/ሀ/ በመተላለፍ የሆነው ይሁን በሚል ተነሳስቶ በመሆኑ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል፤ ይህ የሚታለፍ ቢሆን በአማራጭ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/2/ የተመለከተውን በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል፤ እንደዚሁም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 494 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ግምቱ ከብር 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ በላይ የሆነ ንብረት ሙሉ በሙሉ እንዲወድም አድርጓል የሚሉ ክሶችን አቅርቦበታል፡፡

ተጠሪ ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ክስ የገለፃቸውን የወንጀል ድርጊቶች አልፈፀምኩም በማለት ክዶ በመከራከሩ ዓቃቤ ሕግ ሁለት ምስክሮች አሰምቷል፡፡ ተጠሪ ለወረዳ ፍርድ ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 መሠረት የሰጠውን የዕምነት ቃል በሰነድ ማስረጃነት አቅርቧል፡፡ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቤቱ ከውጭ እንደተቆለፈ በእሳት የተቀጣጠለ መሆኑንና በክሱ ስማቸው የተገለፀው ሰዎች በእሳት ተቃጥለው መሞታቸውን ልዩነት በሌለው ሁኔታ የመሰከሩ መሆኑንና ሁለተኛው የዓቃቤ ሕግ ምስክር በእሳት ተቃጥላ የሞተችው ሴት ተከሣሽ መኩሪያው ተጋፋውን ከነ ቤተሰቦቹ ቆልፌ በእሳት አቃጥላለሁ እያለ ይዝት እንደነበር ከዚያ ቀን በፊት ነግራኛለች በማለት የመሰከረ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ያሣያል፡፡

ሌላው በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው ማስረጃ ተጠሪ በወንጀለኛ መቀጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 መሠረት የሰጠው የዕምነት ቃል ሲሆን መጋቢት 29 ቀን 1998 ሌሊት 4 ሰዓት ሲሆን የመኩሪያው ተጋፋውን ቤት አቃጥየዋለሁ፤ ያቃጠልኩት መጋቢት መባቻ ላይ በዱላ ስለመታኝ ነው፤ ቤቱ ከውጭ ተቆልፎ የነበረ በመሆኑና የቤቱ ባለቤት ወደ ማኀበር ሲሄድ ስላየሁት ቤተሰቦቹም ሄደዋል ብዬ ነው ያቃጠልኩት፤ ቤቱም ከውጪ ተቆልፎ ነበር የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ ተጠሪ በወቅቱ በአካባቢው ያልነበረ መሆኑን ሁለት የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ

ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/3/ የተመለከተውን በመተላለፍ በቸልተኝነት ሶስት ሰዎችን የገደለ ጥፋተኛ ነው፤ እንደዚሁም በወንጀል ሕጉ 691 የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ቅጣቱን በተመለከተ ለመጀመሪያው ጥፋት በሰባት ዓመት ጽኑ እስራትና በአንድ ሺህ አምስት መቶ ብር መቀጮ፣ በሁለተኛው ጥፋት በሁለት ዓመት ጽኑ እስራትና በአምስት መቶ ብር መቀጮ በጥቅሉ በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራትና በሁለት ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በእሳት ተቃጥለው የሞቱትን ሰዎች በተመለከተ ተጠሪ ሊያደርገው የሚችለው ጥንቃቄ አልነበረም፤ የሀሣብ ሁኔታው አልተሟላም በማለት ሙሉ በሙሉ በነፃ እንዲለቀቅ የወሰነ ሲሆን የሁለት ዓመት ጽኑ እስራትና አምስት መቶ ብር ቅጣት በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት አለበት፤ ተጠሪ ቤቱን በማቃጠል የግል ተበዳይ ያደረሰበትን ጉዳት ለመበቀል አስቦ ያደረገው መሆኑ በሰው ምስክርም ሆነ በጽሁፍ ማስረጃ ተረጋግጧል፤ ተጠሪ ከምሽቱ አራት ሰዓት በመሄድ ቤት ያቃጠለው ንብረት ለማውደም ብቻ ሣይሆን ሰዎች የሚተኙበት የእንቅልፍ ሰዓት በመሆኑ የግል ተበዳይን ከነቤተሰቡ በእሳት ለማቃጠል በነበረው ሀሣብ እንደሆነ በማስረጃ አስረድተናል፤ ሆኖም የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአማራጭ የቀረበውን በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ተጠሪን ጥፋተኛ ሲል ዓቃቤ ሕግ ይግባኝ ያልጠየቀ በመሆኑ በከባድ ሰው መግደል ተጠሪ መጠየቅ አለበት ብለን ለመከራከር የሥነ ሥርዓት ገደብ ቢኖርብንም ከዚህ አልፎ የጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል ቸልተኝነት የለም በማለት መወሰኑ ለወንጀል ሕጉ አንቀጽ 59 እና 543/3/ የተዛባ ትርጉም የሰጠና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሰራ መሆኑን ሰለሚያሣይ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ ለአመልካች አቤቱታ መልስ ይዞ እንዲቀርብ መጥሪያ የደረሰው ሲሆን መልሱን ይዞ አልቀረበም፡፡ ስለሆነም በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ ቤቱን ከምሽቱ አራት ሰዓት ያቃጠለው ከግል ተበዳይ መኩሪያው ተጋፋው ጋር ከዚያ በፊት ተጣልተው የግል ተበዳይ በዱላ ስለደበደበው መሆኑን የዓቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የግል ተበዳይን ቤት ከውጭ ቆልፌ ከነቤተሰቡ ነው የማቃጥለው በማለት ይዝት እንደነበር አንደኛዋ ሟች ነግራኛለች በማለት አስረድቷል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱ መመዘን አለበት በማለት የሰጠው ትችት ተቀባይነት ያለው የማስረጃ አመዛዘን መርህ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ሆኖም ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበውን ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱና መልዕክቱ የመዘነ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ዓቃቤ ሕግ የጽሁፍ ማስረጃ አድርጎ ባቀረበው የተጠሪ ዕምነት ቃል የግል ተበዳይ ወደ ማኅበር ሲሄድ ስላየሁት ቤተሰቦቹም ሄደዋል ብዬ በማሰብ ቤቱን አቃጠልኩት የሚል ፍሬ ጉዳይ አለ፡፡ ከዚህም የምንረዳው ተጠሪ በእሳት ቃጠሎ ሕይወታቸው ያለፈው የግል ተበዳይ ቤተሰቦች ወደ ማኅበር ሲሄዱ ያላያቸው መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ ሟቾች ወደ ማኅበር ስለመሄዳቸው እርግጠኛ ባልሆነበት ሁኔታ ማኅበር ሄደዋል ብሎ ስለገመተ ብቻ ቸልተኝነት የለበትም ለማለት አይቻልም፡፡ ወቅቱ ሌሊት ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የግል ተበዳይን ቤትና ንብረት የሚጠብቅ ሰው ከቤት ሊኖር እንደሚችል ማወቅ ሲገባው ወይም እያወቀ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 59 የተደነገገውን ቸልተኝነት የሚያሟላ ነው፡፡ የሟቾች ከቤታቸው ውስጥ ተኝተው መገኘት ከተጠሪው አቅም በላይ የሆነ ኃይል ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈፀመ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 3 ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው ማስረጃ ተጠሪ ከግል ተበዳዩ ጋር በነበረው ጠብ በቂም በቀል ተነሳስቶ የግል ተበዳይን ቤት በእሳት ያቃጠለ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ተጠሪ በለኮሰው እሳት ተቃጥለው ሰዎች ሞተዋል፡፡ ተጠሪ ቤቱን የማቃጠል እንጂ ሟቾቹን የመግደል ሀሣብ አልነበረውም ቢባል እንኳን በቸልተኝነት ሟቾችን በመግደሉ ተጠያቂ የማይሆንበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ ሊያደርገው የሚገባው ጥንቃቄ አልነበረም በቸልተኝነት በሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ መባል የለበትም በማለት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13840 ኀዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም. ተጠሪ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 543/3/ በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ሊጠየቅ አይገባውም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ"ዝገብ ቁጥር 14498 ሀምሌ 23 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገውን በመተላለፍ ሚች ይታይሽ አለማየሁ፣ አለባቸው መኩሪያውና ፋሲካ መኩሪያውን በቸልተኝነት የገደለ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡ ለዚህ ጥፋቱም ከፍተኛው ፍርድ ቤት በወሰነው መሠረት በሰባት ዓመት ጽኑ እስራትና በአንድ ሺህ አምስት መቶ ብር መቀጮ ይቀጣል ብለናል፡፡ ይህንን ቅጣት ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ ለክልሉ ፖሊስ ኮሚሽንና ለክልሉ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ክርክር የወጣውን ወጪ አመልካች በራሱ ይቻል ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 35695

ኀዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አሰማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ - አቃቤ ሕግ አውግቸው መኮንን

**ተጠሪ**፡- አቶ ተመስገን አዲስ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 15071 ታህሳስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ለወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 የሰጠው ትርጓሜና ተጠሪ በዋስ እንዲለቀቅ የሰጠውን ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ተጠሪ 1996 ያወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ንኡስ አንቀጽ 3 በመተላለፍ በቸልተኝነት ያሽከረክር በነበረው አይሱዙ መኪና እማሆይ ሙሉነሽ ደላላ የተባሉትን ገድሏል በሚል ክስ አቅርቦበታል፡፡ ይህ የወንጀል ክስ በሚታይበት ጊዜ ተጠሪ የዋስ መብቴ ተጠብቆ ከውጭ እየቀረብኩ እንድከራከር ይፈቀደልኝ በማለት ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያመለከተ ሲሆን አመልካችን ወክሎ የሚከራከረው አቃቤ ሕግ በበኩሉ በተጠሪ ላይ የተጠቀሰው አንቀጽ እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደረስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ስለሆነ በወንጀሉም የሰው ሕይወት ለሕልፈተሞት የተዳረገ በመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 መሰረት የዋስ መብት የሚያስፈቅድ ባለመሆኑ በእስር ሆኖ እንዲከራከር ትእዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ የዋስ መብት የማያስፈቅድ መሆኑን በመግለጽ የተጠሪን የዋስትና መብት ከጥያቄ ውድቅ አድርጐታል፡፡ ተጠሪ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የዋስትና ጥያቄውን አስመልክቶ የሰጠውን ብይን በመቃወም ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 ሕግ አውጭው የደነገገው ከአስራ አምስት ዓመት በላይ የሚያስቀጡ ሆነ ተብሎ የሚፈጸሙ በሰው መግደል የተከሰሱ ሰዎችን የዋስ መብት ለመከልከል እንደሆነ የሥነ ሥርአት ሕግ ድንጋጌውን በ1949 ዓ.ም ከወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም፣በአዲሱ የወንጀል ሕግ የቅጣቱ መጠን እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ቢሆንም የሥነ ሥርአት ሕጉን ያወጀው ሕግ አውጭ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀሙ ሰዎችን የዋስ መብት የመከልከል ሐሳብ ያልነበረው በመሆኑ ተጠሪ የብር 2000/ሁለት ሺ.ህ ብር/ ዋስ አቅርቦ እንዲለቀቅ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕግ አተረጓጐምና የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ የተከሰሰበት ጉዳይ እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ እያለና በወንጀሉም የሰው ሕይወት ለሕልፈት የተዳረገ መሆኑ በክሱ ውስጥ ተገልፆ እያለ እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች በተሟሉበት ሁኔታ ተከሳሹ በዋስትና ወረቀት እንደማይለቀቅ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 ንኡስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጐ እያለ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል መፈፀም የዋስትና መብት አያስነፍግም የሚል ትርጓሜ በመስጠት ተጠሪ በዋስ እንዲለቀቅ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባዋል የሚል የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በዋናው ጉዳይ ጥፋተኛ ስለተባልኩ አቤቱታው ውድቅ ይደረግ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ደረጃ የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ የተሻሻሉና የተለወጡ ሁኔታዎች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ድንጋጌዎች ጋር ያላቸውን ተፈፃሚነትና ፍርድ ቤቶች ሊከተሉት የሚገባ የሕግ አተረጓጎም ምን መሆን አለበት? የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው የሕግ ትርጓሜ ተገቢ ነው ወይስ አይደም? የሚሉትን ነጥቦች መመርመር ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ መሰረታዊ የይዘታና የቅጣት ለውጥና መሻሻል የተደረገባቸው የወንጀል አይነቶች ያሉ መሆኑ አያከራክርም፡፡ ከወንጀል ሕጉ ጐንለጐን የወንጀል ሥነ ሥርአት ሕግ ተሻሽሎ አለመውጣቱ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያነሳቸውን የመከራከሪያ ሐሳቦችና ጥያቄዎች እንዲነሱ ክፍተት የሚፈጥር ስለመሆኑ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሆኖም ሕግ አውጭው በአዲስ የወንጀል ሕግ ያወጣቸውና ያሻሻላቸው ጉዳዮች ባሉበት ሁኔታ በቀጥታ ከነበረው የሥነ-ሥርአት ሕግ ድንጋጌዎች ጋር ተጣምረው ተፈፃሚ እንዲሆኑና እንዲተረጐሙ ፍላጐትና ሐሳብ አለው ተብሎ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም በአዲሱ የወንጀል ሕግ ቅጣታቸው ከፍ ብሎ የተደነገጉ ወንጀሎች የዋስትና ጥያቄና ተከሳሽ በሌለበት እንዲታይ የሚቀርቡ የሥነ-ሥርአት ጥያቄዎች 1949 ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የነበረውን ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባትና ትርጓሜ መስጠት ሣያስፈልግ የሥነ-ስርአት ህጉን ከአዲሱ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በቀጥታ አጣምሮ በማየት መወሰን ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚህ አንፃር አዲሱ የወንጀል ሕግ ከመውጣቱ በፊት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እስራት ብቻ ያስቀጣ የነበረው በቸልተኝነት ሰው የመግደል ወንጀል በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ንኡስ አንቀጽ 3 እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደረስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ይሕ ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 ንኡስ አንቀጽ 1 የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟላል ወይስ አያሟላም የሚለውን በመመዘን ብቻ መወሰን ሲገባው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት 1949 በወጣው የወንጀል ሕግ የነበረውን ሁኔታ መነሻ በማድረግ የሰጠው የሕግ ትርጓሜ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የተከሰሰበት የሕግ ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርአት ሕግ ቁጥር 63 ንኡስ አንቀጽ 1 የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላና የዋስ መብት የማያስፈቅድ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪ በዋስ እንዲለቀቅ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 15071 ታህሣስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 2077 ኅዳር 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. አመልካች በዚህ ፍርድ ቤት ያወጣውን ወጪ ራሱ ይቻል ብለናል ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ኅዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ.39722

ታህሣሥ 23 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** □ብ□ ልቃ□ር መሐመ□

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** □ርማ ሃ□ሌ -አልቀረቡም

**ተ□ሪ፡-** ዐቃቤ ሕግ - ቀርቧል

□□□፡- ከተመረመረው በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቶበ□ል፤

**□ ር □**

ይህ ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ችሎት በመ/ቁ.37985 ግንቦት 29 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ □ታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

□ዳዩ የይግባኝ ማስፈቀጃ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን፣ ይኸውም አመልካች በወ/መ/ቁ. 21282 በከፍተኛ ፍርድ/ቤት በወንጀል ተከሶ ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም. በሌለበት በ13 ዓመት ፅኑ እስራት ስለተፈረደበት በጉዳዩ ይግባኝ ለማቅረብ □ል□ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ አልፏል በመባሉ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.191(1) መሰረት ይግባኙን ማቅረብ እንዲችል እንዲፈቀድለት ለፌ/ጠቅ/ፍ/ቤት ወንጀል ችሎት ይግባኝ ቢያቀርብም ችሎቱ በወ/ይ/መ/ቁ. 37983 ፣ ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም. በሰጠው ውሳኔ የይግባኝ ጊዜው ያለፈው በአመልካቹ ጥፋት በመሆኑ ጥያቄው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.191(3) መሰረት ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ከላይ የሰፈረውን ውሳኔ በመቃወም አመልካቹ ሐምሌ 26 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱ□ □ቀረበ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም በሌለሁበት የተሰጠውን ፍርድ እንዲሻርልኝ ያቀረብኩት ጥያቄ በ03/07/2000 ዓ.ም. ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ተቀባይነት እንዳጣ እኔም በጉዳዩ ይግባኝ እንደምል በ04/07/2000 ዓ.ም. በማረሚያ ቤት በኩል ለፍ/ቤቱ ማመልከቻዬን ልኬያለሁ፤ይሁን እንጂ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የላከልኝ ቅጣት የተወሰነበት የፍርዱ ግልባጭ ሳይሆን ፍርዱ ተለውጦ ባለሁበት እንደገና እንዲታይልኝ አመልክቼ ፍርዱ አይለወጥም ተብሎ ብይን የተሰጠበት በመሆኑ እንደገና ተመልሼ በ29/07/2000 ዓ.ም. ሊልክልኝ የሚገባው ፍርድ የተሰጠበት ግልባጭ መሆኑ ባመለክተውም በመጀመሪያ በ 04/07/2000 ዓ.ም. ያቀረብኩት ማመልከቻ ትቶ ስህተቱን እንዲያርም ተመልሼ የፃፍኩትን የ29/07/2000 ዓ.ም. ማመልከቻ ብቻ አያይዞ ለጠቅላይ ፍ/ቤቱ በመላኩ ያመለከትኩበትን ጊዜ በአግባቡ ሳይመዘንልኝ አላግባብ ማለትም ከ□ኔ ጥፋት ውጭ በሆነ ምክንያት ጊዜው አልፎበታል ተብያለሁ ፣ ስለሆነም መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለተፈፀመብኝ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

□/ህ□ም በቁ.5 - 2042. ይግባኝ ህዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም. በሰጠው መልስ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የአመልካቹን ቅሬ□ በአግባቡ ለማስተናገድ ሲባል ዋናውን የስር መዝገብ አስቀርቦ ከተመለከተ በኋላ የይግባኝ ጊዜው ያለፈው በአመልካቹ ጥፋት መሆኑ ካረጋገጠ በኋላ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ ስለሆነም የተፈፀመ ስህተት የለም ብሏል፡፡

ይህ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር ከላይ በተቀመጠው መልክ ከተገነዘበና በአመልካችና በተጠሪ መካከል ክርክር የተካሄደበት ዋናው መዝገብ (የወ/መ/ቁ. 21288) ከከፍተኛ □ርድ ቤት አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ አመልካቹ ይግባኝ የማቅረቢያ ጊዜ አልፎበታል ወይስ አላለፈበትም? የሚል መሠረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮ□ል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካቹ በከፍተኛ ፍርድ/ቤት (በወ/መ/ቁ. 21282) በወንጀል ተከሶ ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም. በሌለበት በ13 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ እንደተፈረደበት ነው፤ በሌለበት የተፈረደበትን ፍርድ ተሽሮ እንደገና ባለበት እንዲካሄድለት ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ጥያቄ አቅርቦ እንደነበርና ይህም ጥያቄው መጋቢት 03/2000 ዓ.ም. ተቀባይነት እንደሌለው ከተበየነ በኋላ ለሚቀጥለው ቀን ማለትም መጋቢት 04/2000 ዓ.ም በማረሚያ በኩል ለፍርድ ቤቱ በላከው ማመልከቻ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ እንደሚል ግልባጭ እንዲሰጠው ጠይቆ የተላከለት ቅጅ ጥፋተኛ □ተባለበትና ቅጣት የተሰጠበት የመዝገብ ግልባጭ ሳይሆን ቀደም ብሎ በሌለበት የተሰጠውን ፍርድ እንደገና ባለበት እንዲካሄድለት አመልክቶ የተሰጠውን ብይን የሚያመለክተው ክፍል ብቻ ነው፤ ይህም ስህተት መሆኑ ገልፆ ማለትም ጥቅምት 20 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ውሳኔ የሰጠበትን መዝገብ ተገልብጦ □ንዲላክለት መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ጠይቋል:: ፍርድ ቤቱም ሚያዚያ 03/2000 ዓ.ም. ገልብጦ እንደሰጠና አመልካቹም ሚ□□□ 15/2000 □ም. ቅሬታው በማዘጋጀት ፣ሚያዚያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም. ለፍርድ ቤቱ እንደደረሰ ነው:: የይግባኝ ቅሬታው አመልካቹ ያዘጋጀውና የላከው በዝዋይ ማረሚያ ቤት ሆኖ እንደሆነ ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል:: ከላይ የሰፈሩት ሃቆች ከወ/ስ/ስ/ህ/ቁ 187 (1) (2) ከሰፈረው አሰራር ጋር በማነፃፀር አመልካቹ ፍርዱ በተሰጠ በ 15 ቀናት ውስጥ ይግባኝ እንደሚል አላሳወቀም ተብሎ የይግባኝ ጊዜ አልፎበታል እንደተባለና የይግባኝ ማስፈቀጃ ጥያቄውም በራሱ ጥፋት የተፈፀመ ነው ተብሎ በወ/መ/ሰ/ስ/ህ/ቁ 191 (3) መሰረት ጠቅላይ ፍ/ቤቱ እንዳልተቀበለው ነው፤ ፍርዱን ከሰጠው ከፍተኛ ፍ/ቤት ለጠቅላይ ፍ/ቤቱ የወንጀል ችሎት የተላከው በወ/መ/ቁ 21282 በ15/09/2000 ዓ.ም. የተፃፈው የይግባኝ መሸኛ □ብ□ቤ እንደሚያመለክተው አመልካቹ መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም. ይግባኝ ለማለት እንደሚፈልግ እንዳሳወቀ እንጂ በመጀመሪያ መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚፈልግና ቅጅው ተገልብጦ እንዲሰጠው የገለፀበት ሁኔታ አልተገለፀም:: አመልካቹ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚፈልግ በ04/07 /2000 ዓ.ም. ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ሲያመለክተው የፍርዱን ግልባጭ በጠቅላላው እንደማስተላለፍ የፍርዱ ሂደት እርሱ ባለበት እንደገና እንዲታይለት ላመለከተው ጥያቄ የተሰጠውን ብይን የሚመለከት ብቻ ነጥሎ እንዳስተላለፈ ነው፤ የስር ፍርድ ቤቱ ይህንን ስህተት በመፈፀሙ ምክንያት ደግሞ አመልካቹ በእስር ሆኖ ይህንን ችግር እንዲፈታለት ተመልሶ በ29/07/2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ □ንደጠየቀ ነው:: በአጠቃላይ አመልካቹ በተላለፈበት ፍርድና የፍርድ ሂደት ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚፈልግ በህጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሳያልፍ መጋቢት 04/2000 ዓ.ም. ለፍርድ ቤቱ ጠይቋል ፣ ፍርድ ቤቱም መላክ ያለበትን ግልባጭ በትክክል ገልብጦ እንደመላክ ዋናውን የፍርዱ ቅ□ ሳ□ልክ እንደቀረ ነው፣ ስለሆነም መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም. የፃፈው ደብዳቤ ለሁለተኛ □□ የቀረበ ጥያቄና ቀደም ብሎ የተፈፀመውን የማሳረፍ ፍላጎቱ ለማንፀባረቅ የተጠቀመበት ነው ተብሎ እንደመተርጎም ለመጀመሪያ ጊዜ የይግባኝ ጥያቄ እንደቀረበ ተደርጎ መወሰዱ ተገቢነት የለውም ፣ ከዚያም በኋላ የነበሩት መፃፃፎች አመልካቹ በዝዋይ እስር ቤት ሆኖ በማረሚያ ቤት በኩል ወደ ፍ/ቤቱ ይደረጉ የነበሩ መላላክን አመልካቹ በህጉ መሰረት ይግባኝ ለማቅረብ መዘግየቱ የሚያሳዩ ሆነ□ አይተረጎሙም ፣ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ችሎት ይህንን ሁኔ□ በሚገባ ሳያገናዝብ አመልካቹ ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም. ለተላለፈበት የቅጣት ውሳኔ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚፈልግ የገለፀው በ29/07/2000 ዓ.ም. እንዳመለከተ እና ይህም አመልካቹ የይግባኝ □□□ እንዲያልፍ ያደረገው በራሱ ጥፋት ነው በማለት ጥያቄው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 191 (3) መሰረት ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ሆኖ ተገኝቷል፤ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል::

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ችሎት በወ/ይ/መ/ቁ. 37985 ግንቦት 28/2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 195/2/ መሰረት ተሽሯል፤ ይፃፍ::
2. የአመልካቹ የይግባኝ ጊዜ ያለፈው በአመልካቹ ጥፋት ምክንያት ሳሆን የስር ፍ/ቤቱ በፈፀመው ስህተት ስለሆነ □□ባኙ እንዲያቀርብ ተፈቅዶለታል፤ በማረሚያ ቤት በኩል ይፃፍለት፤ ማረሚያ ቤቱ ትዕዛዝ ባደረሰለት በሃያ ቀናት ውስጥ ይግባኙን እንዲያቀርብ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ . 191 (4) መሰረት □□ል፣ □□□::
3. ይህ ውሣኔ በዛሬው ዕለት 15/05/2001 ዓ.ም. ተሰጥቷል፤ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ:: መዛግብቶቹ ወደ መጡበት ይመለሱ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 33075

ጥር 19 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ብርቁ ገላነው /አቶ/ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- የአማራ ብ/ክ/መ/የስነ- ምግባርና ፀረ- ሙስና ኮሚሽን - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረተውን የወንጀል ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ ማየት እንደተቻለው ተጠሪ በሶስት ወንጀል ድርጊቶች አመልካችን ከሶ የነበረ ሲሆን፣አመልካች በሁለቱ ብቻ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ተወስኖበታል፡፡ ጥፋተኛ የተባለባቸው ክሶች በልዩ ወ/መ/ሕግ አዋጅ ቁ. 214/74 አንቀጽ 23/1//ሀ/ እና አንቀጽ 17/1/ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ አመልካች እነዚህን የወንጀል ድርጊቶች ፈጸመ የተባለው በወረዳ ፍ/ቤት የዳኝነት ስራው ላይ እንዳለ ነው፡፡ ዝርዝሩም በተከፈተው የፍትሐብሔር መዝገብ ተከሣሽ የከነበረችው ግለሰብ ሳትቀርብ ቀርባ መልስ እንደሰጠች አድርጐ በመመዝገብ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ ለፍ/ቤት የተላከውን ሰነድ በመሰረዝ /በመደለዝ/ በሕዝብና በመንግስት ሰነድ ላይ ወንጀል ፈጽሞአል በሚል ሊጠቃለል እንደሚችል ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በዚህ መልክ ክሱ የቀረበለት በአማራ ብ/ክ/መ/የምእራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች ወንጀሎቹን ለመፈጸሙ በምስክሮች አረጋግጫለሁ በማለት የጥፋተኛነት ውሳኔ በመስጠት አመልካች በሰባት አመት ጽኑ እስራት እና በብር 200(ሁለት መቶ) መቀጫ እንዲቀጣ አዞአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማለቱ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በቅጣት ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ ብቻ በማሻሻል አመልካች በሁለት አመት እስራት እና በብር 200(ሁለት መቶ) መቅጫ እንዲቀጣ ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 99 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች የዳኝነቱን ስራ በሚሰራበት ጊዜ በልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አዋጅ ቁ. 214/74 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጐ በስልጣን ያለአግባብ መገልገል ወንጀል ፈጽሞአል በሚል የመከሰሱንና ጥፋተኛ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች የተከሰሰው የዳኝነት ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ በስልጣኑ ያለአግባብ ተገልግሎአል እንደዚሁም የመንግስትና የሕዝብ ሰነዶችን ወደ ሐሰት ለውጦአል ተብሎ ነው፡፡ ወንጀሎቹና ፈጸመ የተባለው የፍትሐብሔር ክርክር በሰማበት መዝገብ እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡ እንደሚታወቀው የፍትሐብሔር ክርክር የሚመራው በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕጉ ነው፡፡ በአንደኛው ክስ እንደተገለጸው ተከሣሽ የነበረችው ግለሰብ ሳትቀርብ እንደቀረበች ተደርጐ ተወስኖ ወይም ተመዝግቦ ሊሆን ይችላል፡፡ እዚህ ላይ በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ነገር እንዳለ ግን ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በእርግጥም በተባለችው ግለሰብ ስም የቀረበ የጽሑፍ መልስ የለም አልተባለም፡፡ በመሆኑም መልሱ ውክልና በሌለው በተሳሳተ/በማይመለከተው/ ሰው ተዘጋጅቶ ቀርቦአል እንኳን ቢባል ይህን መሰል ስህተት ሲከሰት ለማስተካከል በሚል በተደነገጉት የስነ-ስርአት ሕጉ ድንጋጌዎች የሚስተካከል ይሆናል እንጂ የተፈጠረው ስህተት በቀጥታ

ዳኛው/አመልካች/ሆነ ብሎ ስልጣኑን ያለአግባብ በመገለገል የፈጸመው የወንጀል ድርጊት ነው ወደሚለው የሚያደርስ የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነውም ሳትቀርብ እንደቀረበች ተደርጐ ተመዝግባ ውሳኔ ተሰጥቶአል የተባለችው ግለሰብ ወይም በዚህ ሂደት መብቴ ተጐድቶአል የሚል ወገን በፍትሐብሔሩ መዝገብ አቤቱታ አላቀረቡም ወይም አቅርበዋል አልተባለም፡፡ ይህን በራሱ የሚያሳየው በክሱ አመራርም ሆነ ውሳኔ የተጐዳ ወገን አለመኖሩን ነው፡፡ የተጐዳ የለም ከተባለ ደግሞ በተቃራኒው ከሕግ ውጪ ውሳኔ የተሰጠበት ወይም የተጠቀመ ተከራካሪ ወገን የለም ማለት ነው፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካች በተያዘው የፍትሐብሔር ክርክር ከማንኛውም ተከራካሪ ወገን ጥቅም ወይም መደለያ /ጉቦ/ ተቀብሎአል የሚል ክስ አልቀረበም፡፡ በአጠቃላይ በግለሰብዋ አቀራረብ ወይም መልስ አሰጣጥ ረገድ ስህተት ነበር የሚባል እንኳን ቢሆን፣በግለሰብዋ ወይ ጉዳይ ይመለከተኛል በሚል ወገን አግባብ ባለው የስነ-ስርአት ሕጉ መሰረት አቤቱታ ሲቀርብ የሚታይ እንጂ በአቃቤ ሕግ ክስ እንደተነገረው በልዩ ወ/መ/ሕግ አዋጅ ቁ. 214/74 ድንግጌዎች ስር የወንጀል ድርጊት የሚያቋቁም ጥፋት ተፈጽሞአል የሚያሰኝ አይደለም፡፡

በ2ኛ ደረጃ የተጠቀሰው ክስም እንዳየነው ለክርክሩ ምክንያት የነበረው ቤት በተመለከተ ከማዘጋጃ ቤት የተጻፈውን ደብዳቤ ቁጥሩንና ቀኑን ለውጦ ጽፎአል በሚል የቀረበ ነው፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ይህን በሰው ምስክር አረጋግጫለሁ በማለት ነው አመልካችን ጥፋተኛ ያደረገው፡፡ ሁሉም በግልጽ እንደሚያውቀው በአንድ የክርክር መዝገብ ላይ ውሳኔ የሚሰጠው የተሰየመው ዳኛ ቢሆንም፤ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው በዳኛው ቁጥጥር ስር ሆኖ ይቆያል ማለት ግን አይደለም፡፡ ከሁሉም በላይ ግን በተባለው ደብዳቤ ላይ የቁጥር እና በቀን አጻጻፍ ረገድ የተፈጠረ ችግር አለ በመባሉ ብቻ በዳኛ ላይ የወንጀል ክስ መመስረት የሚቻል አይሆንም፡፡ ሲጠቃለል ተፈጠሩ የተባሉት ክስተቶች ካሉም ከዳኝነት ስራ ስነ-ምግባርና ዲሲፕሊን አኳያ የሚታዩ ናቸው፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን አመልካች በወ/መ/ሕግ አዋጅ ቁ. 214/74 በተመለከቱት ድንጋጌዎች ስር ወንጀልን የሚያቋቁም ድርጊት ፈጽሚአል በሚል የቀረበው ክስም ሆነ የተሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ የሕግ መሰረት ያለው ነው የሚባል አይደለም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ ስለዚህም አቤቱታ የቀረበባቸው በአማራ ብ/ክ/መ/ በምእራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 10588 በ14/07/99 ዓ.ም የተሰጠው እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12083 ሰኔ 13 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ ሥ/ሥ/ቁ. 195/2//ለ//1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡ አመልካችም በነጻ ተለቆአል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 38161

የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች ፡-** እነ ጀሚላ መሐመድ ሀጐስ - ጠበቃ እሸቴ ጓንጉል ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** የፌዴራል የመ/ደ/ዓ/ቃህ - ፋሲል ገብሬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ መዝገብ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረምልን ይገባል በማለት ግንባት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ዘርዝረው ስላቀረቡ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካቾች ላይ የመሠረተው ክስ የግል ተበዳይ ወ/ሮ ዘርፌ ጥላሁን በአቶ መሐመድ ሐጐስ ቤት በቤት ሰራተኛነት ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ ግለሰቡ በ1990 ዓ.ም ወደ ኤርትራ ሲባረሩ ቤታቸውን በኃላፊነት እየጠበቁ እንዳለ ሐምሌ 21 ቀን 1997 ዓ.ም አመልካቾች የግል ተበዳይን እቃ ከቤት አውጥተው ግቢ ውስጥ በማስቀመጥ በግብረአበርነት በፈፀሙት ህገ ወጥ በሆነ መንገድ መብትን የማስከበር ወንጀል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1ሀ/ እና 436/1/ሀ/ መሠረት ጥፋተኛ ተብለው ሊቀጡ ይገባል የሚል ሲሆን አመልካቾችም የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ ግን ጥፋተኛ አይደለንም ሲሉ አስመዝግበዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የዓ/ህግን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ አመልካቾች እንዲከላከሉ ትዕዛዝ ሰጥቶ የአመልካቾችን የሰው እና የጽሑፍ ማስረጃዎችን በመስማት ጉዳዩን በመመርመር የአመልካቾች የመከላከያ ማስረጃዎች የዓ/ህጉን ማስረጃዎችን ለማስተባበል በቂ አይደሉም የሚል ምክንያት ይዞ አመልካቾችን በዓ/ህግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጐ እያንዳንዳቸውን በብር 800.00 /ስምንት መቶ/ የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላም አመልካቾች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካቾች ጥፋተኛ መባላቸው ባግባቡ መሆኑን በመግለጽ ድርጊታቸው የሚሸፈንበትን ድንጋጌ ብቻ በማሻሻል ቅጣቱንም በማጽናት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን የጥፋተኛነት ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር ማመልከቻ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት የጥፋተኛነት ውሣኔ የተሰጠበትን አንቀጽ የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦችን የሚያሟላ የወንጀል አላፊነትን የሚያስከትል መሆኑን ያሳያሉ ያሏቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታዩ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርቦ የአመልካቾች ድርጊት ወንጀሉን የሚያቋቁም መሆኑንና ጥፋተኛ መባላቸውም ባግባቡ መሆኑን ጥቅምት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ዘርዝሮ የጥፋተኛነት ውሣኔው ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመረውም አመልካቾች ፈፀሙ የተባለው ድርጊት የወንጀል ድርጊት ያቋቁማል ወይም አያቋቁምም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

አመልካቾች የተከሰሱትና በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የጥፋተኛነት ውሣኔ የተሰጠባቸው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1ሀ/ እና 436/1/ ስር የተመለከተውን ተላልፈዋል በሚል ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካቾች የተሰጠውን የጥፋተኛነት ውሣኔ አንቀፁን በመለወጥ አጽንቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካቾችን ጥፋተኛ ያደረጋቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 436/ሐ/ ስር ነው፡፡

ህገ ወጥ በሆነ መንገድ መብትን ማስከበር ድርጊት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 436/ሐ/ መሠረት ሊያስጠይቅ የሚችለው ማንም ሰው መብት ሳይኖረው ወይም ህግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ በጠቅላላው የሌለውን ወይም በህጉ መሠረት ሊሰራበት የማይችለውን መብት የተጠቀመበት እንደሆነ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የግል ተበዳይ ወ/ሮ ዘርፌ ጥላሁን ቤቱን እንዲለቁ ሲያደርጉ የግል ተበዳይዋ ቤቱን የያዙት በጠባቂነት በነበራቸው ኃላፊነት ስለመሆኑ አንደኛ አመልካች ደግሞ የቤቱ ባለቤት የተባሉት ግለሰብ የአቶ መሐመድ ሐጐስ ልጅ ሁለተኛ አመልካች ደግሞ ድርጊቱ ሲፈፀም በቦታው ላይ የተገኙት ከአንደኛ አመልካች በተሰጣቸው ውክልና መሠረት ስለመሆኑ የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም አንደ1ኛ አመልካች በቤቱ ላይ በጠቅላላው መብት የሌላቸው ወይም በህጉ መሠረት ሊሰሩበት በማይችሉት መብት የተጠቀሙ ሳይሆን በቤቱ ላይ መብት ያላቸው ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁምበት ህጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተጣምረው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 23/2/ ስር አስቀምጧል እጃችን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የአመልካቾች ድርጊት የጥፋተኛነት ውሣኔ የተሰጠባቸው የህግ ድንጋጌ የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦች የተሟሉበት አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 23/2/ እና 436/ሐ/ ስር የተመለከቱትን የህጉን መስፈርቶች ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት መ/ቁ. 35370 ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲሁም በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት መ/ቁ. 64237 መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠ ውሣኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ሐ/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች ፈጽመውታል የተባለው ድርጊት የወንጀል ባህርይ የለውም ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 44594

ሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የፌ/የሥነ-ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ - ዐ/ሕግ ቀረበ

**ተጠሪዎች፡-** እነ ካፍ መሐመድ /4 ሰዎች/ - ጠበቃ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የጉዳዩ አጀማመር የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አቃቤ ሕግ ተጠሪዎች የተጠረጠሩበትን የወንጀል ድርጊት በመጥቀስ በተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 23 መሠረት በማድረግ ተጠርጣሪዎች መዝብረውታል ለተባለው እና ለወደፊቱ ላደረሱት ጉዳት ማካካሻ የሚሆነውን ንብረታቸውን እንዳያሸሹ ወደ ሌላ ወገን እንዳያዛውሩ እና ወደ ጥሬ ገንዘብ ቀይሮ ስለሚያባክኑ መደብሮቹ እንዲታሹጉ እና ጥበቃ እንዲደረግለት በመጠየቁ ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከላይ የተቀጠሱት ተጠርጣሪዎች ዐ/ሕግ ክስ መስርቶባቸው በክርክር ላይ መሆናቸውንና ንብረታቸውን ያሳገደ ቢሆንም ተጠርጣሪዎች የታገደው ንብረት ከደረሰው ጉዳት የበለጠ በመሆኑ ተመጣጣኝ የሆነው ታግዶ ሌላው ሊለቀቅልን ይገባል ያሉትን ክርክር ባለመቀበል ዕግዱ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ /ተጠርጣሪዎች/ በዚሁ ትዕዛዝ ባለመስማማት ክርክራቸውን በማጠናከር የታገደው ንብረትና የደረሰው ጉዳት አይመጣጠንም፣ ደረሰ በተባለው የጉዳት ልክ ብቻ ነው ሊታገድ የሚገባው የቀረው ሊለቀቅልን ይገባል በማለት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የጠቅላይ ፍ/ቤቱም የተሰጠውን ዕግድ እና በተጠርጣሪዎች የተነሣውን ተቃውሞ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁ. 434/97 አንቀፅ 9 መሠረት የታገደው የተጠርጣሪ ንብረት ተፈፅሟል ከተባለው ወንጀል ደርሷል ከተባለው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት በመግለፅ በሥር ፍ/ቤት ዐ/ሕግ ደርሷል የሚለው ከፍተኛ ሲሆን የተጠርጣሪዎችም ንብረቶች በጠቅላላው ከመታገዱ ውጪ የታገዱት ንብረቶች በባለሙያ ተገምተው እንዳልቀረበ ተረድቻለሁ፣ የሥር ፍ/ቤቱም ተመጣጣኝ ነው ያለው በግምት እንጂ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ ስለዚህ የተጠርጣሪዎች /ተጠሪዎች/ የንግድ መደብር ከግለሰብና ከመንግስት ተከራይቶ ሲጠቀሙበት የነበረ ስለሆነ ታሽገው መቆየቱ ተገቢ አይደለም ምክንያቱም በተከራዩም ሆነ በአከራይ ላይ ጉዳት የማያደርስ በመሆኑ ተጠርጣሪዎች በንግድ መደብርነት ሲገለገሉበት የቆዩት ቤቶች ውስጥ የነበሩት ዕቃዎች እንዲወጡ ተደርጐ የንግድ ቤቶቹ ተከፍተው የተለመደው የንግድ ስራ ይከናወን በማለት በማሻሻል ወስኖ የሥር ፍ/ቤት በውሣኔው መሠረት እንዲያስፈፅም አዟል፡፡

በዚህም መሠረት /በጠቅላይ ፍ/ቤት/ የተሰጠውን እንዲያስፈፅም ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ለአፈፃፀም ይረዳ ዘንድ የቀረበውን የግራ ቀኙን የአማራጭ ሃሣብ መሠረት አድርጐ ቢያከራክርም ሊስማሙ ባለመቻላቸው የጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት በመደብሩ ውስጥ የነበሩት ዕቃዎች አሻጊዎች በተገኙበት ተቆጥሮ ወጥቶ

የኮሚሽኑ ዐ/ሕግ በሚያስቀምጥበት ቦታ አሻጊዎች በተገኙት ታሽጐ ይቀመጥ ተጠርጣሪዎች የንግድ ቤቶቹን እንዲረከቡ በማለት አዟል፡፡

የኮሚሽኑም ዐ/ሕግ በዚሁ ትዕዛዝ ባለመስማማት በቀን 22/7/2001 ባቀረበው የሰበር አቤቱታው የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሣኔ እና የሥር ፍ/ቤቱም የይግባኝ ሰሚውን ውሣኔ ተከትሎ የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

እኛም ይህንኑ መሠረት በማድረግ ተጠርጣሪዎችን /ጠበቃ/ እና ዐ/ሕጉን በማስቀረብ የቃል ክርክራቸውን ሰምተናል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተፈለገው የንግድ መደብሮቹ ከነበሩበት የንግድ ቤት ወጥተው አመልካች /ዐ/ሕግ/ በሚያዘጋጀው ቦታ እንዲቀመጡ የተሰጠው የዕግድ ማሻሻያ ትዕዛዝ በማስረጃ ሕጉ ስለ እግዱ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንጻር ለመመርመር ነው፡፡

በዚህም መሠረት ይህን ነጥብ የግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት የቃል ክርክር፣ አቤቱታ ካቀረቡበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበናል፡፡ ለጉዳዩ መነሻ የሆነው የፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ በተጠርጣሪዎች ላይ በመሠረተው ክስ የንግድ መደብራቸውን በማሳገዱ ተጠርጣሪዎች የታገደው ንብረት ከደረሰው ጉዳት የበለጠ በመሆኑ ተመጣጣኙ ታግዶ ሌላው ይለቀቅልን በማለት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱም የተሰጠው ዕግድ ተመጣጣኝ ነው ሲል ዕግድ ይቀጥል ብሎ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠርጣሪዎቹ ተመሣሣይ ክርክራቸውን በማጠናከር ይግባኝ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅረባቸው፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ጥያቄ በመመርመር የታገደው የንግድ መደብርና የደረሰው ጉዳት ይመጣጠናል? አይመጣጠንም? ለሚለው ጥያቄ በሁለቱም ተከራካሪዎች ንብረቱ በባለሙያ ተሰልቶ እንዳልቀረበ ተረድቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ተጠርጣሪዎች የሚነግዱበት የንግድ መደብር ከግለሰብና ከመንግሥት ተከራይቶ ስለሆነ በአከራዩም ሆነ በተከራዩ ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል የንግድ ቤቱ ታሽጐ የሚቀመጥበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በመደብሩ ውስጥ የሚገኙትን ንብረቶችን የኮሚሽኑ ዐ/ሕግ አውጥቶ ሌላ ቦታ ያስቀምጥ ድርጅቶቹ ተከፍቶ አገልግሎታቸውን ይቀጥሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ ውሣኔ /ትዕዛዝ/ መሠረት በማድረግ አፈፃፀም የቀረበለት የሥር ፍ/ቤትም ተከራካሪ ወገኖች በአፈፃፀሙ ላይ ሊስማሙ ባለመቻላቸው በጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሣኔ መሠረት ይፈፀም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የኮሚሽኑ ዐ/ሕግም ተቃውሞ በዚሁ ላይ ነበር፡፡

ለዚህ የሰበር ችሎት ተያይዘው ከቀረቡት መዝገቦች ለመገንዘብ እንደቻልነው ለአሁኑ ክርክር መነሻ የሆነው የአሁኑ መልስ ሰጪዎች በተጠረጠሩበት የወንጀል ጉዳይ ከፍተኛው ፍ/ቤት እንዲታገዱ ያደረጋቸው ንብረቶች በወንጀሉ ምክንያት ደርሷል ከተባለው ጉዳት የበለጠ ዋጋ ያላቸው በመሆኑ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ንብረቶች ብቻ ታግደው ቀሪዎቹ ይለቀቁልን በማለት ለከፍተኛው ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህን ማመልከቻ ውድቅ አድርጐታል፡፡ በትዕዛዙ ቅር ተሰኝተው መ/ሰጪዎች ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሲሉ ግን ጠቅላይ ፍ/ቤቱ በአንድ በኩል የታገደው ንብረት ግምት ደረሰ ከተባለው ጉዳት በላይ ነው ሊባል አይችልም ሲል በሌላ በኩል ግን የታገዱት የመልስ ሰጪ ድርጅቶች ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ፈቅዷል፡፡ በመሰረቱ ከፍተኛው ፍ/ቤት የታገደው ንብረት ደረሰ ከተባለው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ ነው? አይደለም? የሚለውን ሲመዝን ግምት ውስጥ ያስገባው አሁን ሥራ ይስሩ የተባሉትን ድርጅቶች እንደ ድርጅት በመውሰድ ነው ጠቅላይ ፍ/ቤትም በመርህ ደረጃ የታገደው ንብረት ከጉዳቱ አይበልጥም የሚለውን መደምደሚያ ተቀብሎታል፡፡ በከፍተኛ ፍ/ቤት ከተያያዙት ሰነዶች ለመገንዘብ እንደቻልነው የዕግድ ትዕዛዝ የተጠየቀውም ሆነ የተሰጠው በንግድ መደብሮችም ጭምር ነው፡፡ የመደብሮቹ ዋጋ ሲሰላም ግምት ውስጥ የሚገባው የመደብሩ ውስጥ የሚገኙ ሸቀጥ ብቻ ሳይሆን የመደብሩ መልካም ስም (good will) ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም የዕግዱ ዓላማ ደረሰ የተባለውን ጉዳት የሚመጥን ንብረት ይዞ ማቆየት እንደመሆኑ መደብሩ ከሸቀጡ ተነጥሎ እንዲታይ መደረጉ የዕግዱን ዋና ዓላማው የሚያስቀር ነው፡፡ በመሆኑም ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የመደብሩ ዋጋ ደረሰ ከተባለው አደጋ በላይ ነው ሊባል አይቻልም ካለ በኋላ መደብሩ ከዕግድ ትዕዛዙ ውጪ እንዲሆን መደረጉ እርስ በርሱ የሚጋጭ ውሣኔ መስጠቱን የማያመለክት ነው፡፡ መደብሮቹ ታሽገው መቆየታቸው መልስ ሰጪዎች ሊጐዱ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡ ነገር ግን በመልስ ሰጪዎች ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ደረሰ ከተባለው የወንጀል ጉዳት ጋር በማመዛዘን መመልከትም ያስፈልጋል፡፡ በመደብሩ ውስጥ ያሉ ሸቀጦች ተለይተው የተቀመጡም ቢሆን በመልስ ሰጪዎች ላይ የኢኮኖሚ ጉዳት ሊደርስ እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ መደብሮቹን አግዶ ማቆየቱ በአከራይም ሆነ በተከራይ ጉዳት የሚያደርስ ነው በማለት ብቻ ሸቀጡን ከመደብሩ መነጠሉ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ መሻር ያለበት ነው ወደሚል መደምደሚያ ደርሰናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.4180 ጥር 8/2001 በሰጠው ትዕዛዝና የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ ትዕዛዝ ለማስፈፀም የካቲት 12 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ወ/ቁ. 64231 ህዳር 3 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 46382

ሐምሌ 28 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሠ

ታፈሠ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

**አመልካች** ፡- 1. ዳንኤል ገ/ዮሐንስ

2. ሚካኤል ፀጋዬ

3. ሚ/ር አሚት አብዶ

4. ቅዱስ ዓለምሰገድ

} ጠ/ማረን ወንዶ

**ተጠሪ** ፡- ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - ተሾመ አንጂሎ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የወንጀል ክርክር ሲሆን ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስ የወንጀል ሕግ ቁጥር 32/1/ሀ/ እና 692/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ሚያዝያ 16 ቀን 2001 ዓ.ም. ከምሽቱ 4፡45 ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15/16 ክልል የግል ተበዳይ አቶ ኢሳያስ ካሣ ግሮሰሪ በሜድ ውስኪ እንፈልጋለን ብለው መኪና ውስጥ ሆነው አንድ ብላክ ሌብል ውስኪ አዘው እሱን ከተመለከቱ በኂላ ሌላ ብላክ ሌብል ጨምረን ብለው ሲጨምርላቸው ሲሄድ መኪና አስነስተው በማምለጣቸው ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

አመልካቾች ቀርበው ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኂላ በክሱ ላይ መቃወሚያ እንዳላቸው ተጠይቀው ክሱን እንደማይቃወሙ ካረጋገጡ በኂላ የዕምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ድርጊቱን ፈፅመናል ጥፋተኛም ነን ብለዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 134/1/ መሠረት የጥፋተኛነት ውሣኔ ከሰጠ በኂላ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ከሣሽ ዐቃቤ ሕግ በሰጠው የቅጣት አስተያየት ተከሣሾች የወንጀሉን ድርጊት የፈፀሙት ግብረአበር በመሆን ስለሆነ ፍ/ቤቱ ይህንን በቅጣት አወሳሰን ረገድ ከግምት እንዲያስገባልን ካለ በኂላ ተከሣሾች የትምህርት ደረጃቸው ሲታይ የወንጀልን አስከፊነት ከሌላው ሰው በተሻለ መልኩ ሊያውቁና ሊረዱ የሚችሉ መሆኑን መገንዘብ ስለሚቻል ይህንንም ከግምት በመክተት እንደዚሁም ፍ/ቤት ቀርበው ማመናቸውንም ከግምት በማስገባት ፍ/ቤቱ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ቅጣት እንዲወስንባቸው በማለት አመልክቷል፡፡

ተከሣሾችም በበኩላቸው ድርጊቱ በአጋጣሚ የተፈፀመ መሆኑን፣ ወጣቶች እንደሆኑ፣ በድርጊታቸውም እንደተፀፀቱና ከግል ተበዳይም ጋር እንደታረቁ ገልፀው የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች መሆናቸውን ጠቅሰው ቅጣቱ በገደብ እንዲሆን ይወሰንልን በማለት የቅጣት አስተያየት መስጠታቸውን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ መልኩ የቅጣት አስተያየት የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ተከሣሾች የተከሰሱበት ወንጀል እስከ 3 ዓመት በሚደርስ እሥራት የሚያስቀጣ ቢሆንም ተከሣሾች አስቀድሞ ወንጀል የፈፀሙ ስለመሆኑ ሪከርድ ያልቀረበባቸው ስለሆነና ይህንንም ወንጀል ስለመፈፀማቸው ያመኑ በመሆኑ ይህም ሁኔታ በወንጀል ሕግ ቁጥር 82/1/ሠ/ መሠረት

ቅጣት ማቅለያ ተደርጎ ሊወሰድ ስለሚችል ተከሣሾች እያንዳንዳቸው በ6 /ስድስት/ ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሣሾች የጥፋተኛነት ውሣኔውን ተቀብለው ነገር ግን በቅጣት ማቅለያነት ያቀረቡት ምክንያቶች የተወሰነውን ቅጣት በወንጀል ሕግ ቁጥር 192 መሠረት በገደብ ለማቆየት የሚያስችል ሆኖ ሳለ ቅጣቱ ሳይገደብ መቅረቱ ተገቢነት የሌለው ነው በማለት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በአመልካቾች ላይ የተወሰነውን ቅጣት በገደብ ለማቆየት የሚያበቃ ሁኔታ ስለመኖሩ ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ችሎት ይቅረብ ብሎ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ሲሆን በበኩላችንም አቤቱታው ለሰበር ይቅረብ ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በአንድ የወንጀል ተከሣሽ ላይ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ የተወሰነው የእሥራት ቅጣት ሳይፈፀም በገደብ እንዲቆይ ሊደረግ የሚችልባቸው ምክንያቶች በወንጀል ሕግ በቁጥር 192 ላይ ተመልክቶ ይገኛል፡፡ እንደዚሁም የቅጣት ውሣኔ በገደብ ሊቆይ የማይችልባቸው ምክንያቶችም በቁጥር 194 ሥር ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሠረት ከቁጥር 192 አኳያ የተወሰነውን የእስራት ቅጣት በገደብ ለማቆየት የሚቻለው ጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነው ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለጠባዩም መሻሻል አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑን ፍ/ቤቱ ያመነበት ከሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ቀደም ሲል ወንጀል ስለመፈጸማቸው ሪከርድ ያልቀረበባቸው እንደመሆኑ መጠን ያለፈ የሕይወት ታሪካቸው መልካም እንደነበር ይገመታል፡፡ አሁን ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበትንም ወንጀል በየዋህነት ወይም ባልታሰበና ድንገተኛ አጋጣሚ የፈፀሙት ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም ሌላ አመልካቾች ወንጀሉን ከፈፀሙ በኋላ ከግል ተበዳዩ ጋር ወዲያውኑ መታረቃቸው ድርጊቱን በድንገተኛ አጋጣሚ በየዋህነት የፈፀሙት መሆኑና በዚህም መጸጸታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩልም የወንጀል ሕግ ግብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተ ሲሆን ይዘቱም የወንጀል ሕግ ግብ ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ ዕርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወንጀል ሕግ ቁጥር 82 መሠረት ቅጣቱን በማቅለል ከወሰነ በኋላ አመልካቾች ከፍ ብሎ እንደተመለከተው የቀድሞ የወንጀል ሪከርድ ያልቀረበባቸው ከመሆኑ አኳያ ይህንንም ወንጀል የፈፀሙት በድንገተኛ አጋጣሚ በየዋህነትና ባለማስተዋል ከመሆኑ አንፃር በአጠቃላይም ከወንጀል ሕግ ግብ አኳያ ሲታይ አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ ተሰጥቷቸው የተወሰነባቸው ቅጣት ሳይፈፀም ተግዶ ቢቆይ ዳግም ጥፋት ከመፈፀም ሊታቀቡ እንደሚችሉ ከአጠቃላይ የወንጀሉ አፈፃፀምና ከአመልካቾች ሁኔታ መገንዘብ እየተቻለና ቅጣቱንም በወንጀል ሕግ ቁጥር 194 መሠረት በገደብ ላለማቆየት የሚያበቃ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ቅጣቱን ለመገደብ የሚያበቃ በቂ ሕጋዊ ምክንያት እያለ እንዲገደብ ሳያደርግ መቅረቱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ/7933 በ21/8/2001 ዓ.ም. የሰጠውን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ በማጽናት በመ.ቁ. 45568 በ9/9/2001 ዓ.ም. የሰጠውን ውሣኔ በበኩላችንም በማጽናት ነገር ግን በአመልካቾች ላይ የተወሰነው የ6 /ስድስት/ ወር ቀላል እሥራት ከፍ ብሎ በተመለከቱት ምክንያቶች ሳይፈፀም በ2 /ሁለት/ ዓመት ገደብ ይቆይ በማለት በወንጀል ሕግ ቁጥር 192 እና 197/1/ መሠረት ወስነናል፡፡

2. በአመልካቾች ላይ የተወሰነው የእስራት ቅጣት የተገደበ ስለመሆኑ እንዲታወቅ ለሥር ፍ/ቤቶችና ለአ.አበባ ማረሚያ ቤት ይገለጽለት ብለናል፡፡
3. አመልካቾች በዚህ ችሎት ክርክር ሲደረግ እያንዳንዳቸው ለዋስትና በሞዴል 85 ያስያዙት ብር 2000 /ሁለት ሺህ/ እንዲመለስላቸው ለሚመለከተው ይፃፍ ብለናል፡፡
4. መዝገቡን ዘግተን ወደ መ/ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ጽ/ሽ

የሰ/መ/ቁ. 44031

ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ፈለቀች ኃ/ገብርኤል - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ - የዓቃቤ ሕግ አፀዱ ረጋሣ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታው ውድቅ ከተደረገበት ዮሴፍ ከበደ ጋር በጋራ ባቀረበችው የሰበር አቤቱታ በመጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በላሎ አሳቢ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ዓቃቤ ሕግ የሰበር አቤቱታው ውድቅ የተደረገበት ዮሴፍ ከበደ ጋር በመሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አንቀጽ 630/2/ሀ በመተላለፍ ነሐሴ 24 ቀን 1998 ከምሽቱ ሶስት ሰዓት በግል ተበዳይ ወ/ሪት ብርቱካን ዱባለን አስገድዶ መድፈር ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ አቅርቦ የሰውና የጽሁፍ ማስረጃ አሰምቶ የወረዳው ፍርድ ቤት ተከሣሾች መከላከያ ሣያስፈልጋቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 መሠረት በነፃ እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡ ዓቃቤ ሕግ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቦ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ራሱ የአመልካችን መከላከያ ከሰማ በኋላ ከላይ የተሰጠቀሰውን የሕግ ድንጋጌ በተመላለፍ ወንጀል የፈፀመች ጥፋተኞች ናቸው በማለት ዮሴፍ ከበደ በሰባት ዓመት ጽኑ እስራት፣ አመልካች በሶስት ዓመት ጽኑ እስራት እንድትቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት ያቀረበች ሲሆን ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ አመልካች ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ያቀረበችው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች የካቲት 24 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ዮሴፍ ከበደ የግል ተበዳይን እንዲደፍር በመላው ሀሣቤና በድርጊት ያደረግሁት አስተዋጽኦ ስለመኖሩ የቀረበብኝ ማስረጃ ሣይኖር አላግባብ ጥፋተኛ ተብዬ መቀጣቴ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ጠይቃለች፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ዮሴፍ ከበደ የግል ተበዳይን እንዲደፍራት ሁኔታውን በማመቻቸት ተሣትፋለች፡፡ ይህንንም በማስረጃ ያስረዳንበት ስለሆነ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረትዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ሐምሌ 10 ቀን 2001 ዓ.ም. በጽሁፍ ባቀረበው መልስ ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች ዮሴፍ ከበደ የግል ተበዳይን አስገድዶ ሲደፍር አመልካች የወንጀሉ ተካፋይ በመሆኗ ዓቃቤ ሕግ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 33 እና የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 25 ድንጋጌዎች መሠረት በማስረዳት የአመልካችን ጥፋተኛነት አረጋግጧል ወይስ አላረጋገጠም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ዓቃቤ ሕግ ክስ ሲያቀርብ ወንጀሉ የተፈፀመበትን ጊዜና ቦታ እንዲሁም ተከሣሾቹ ከአንድ በላይ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው በወንጀሉ ያላቸውን ተካፋይነት በዝርዝር መግለጽ ያለበት መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 111 ድንጋጌዎች የተደነገገ ሲሆን ዓቃቤ ሕግ ይህንን በክስ የተገለፀውን ፍሬ ጉዳይ አጥጋቢ በሆነ ማስረጃ የማስረዳት ግዴታ ያለበት መሆኑን ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 141 እና 149 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የግል ተበዳይን ወ/ሪት ብርቱካን ዱባለን መድፈሩ ተረጋግጦ በፍርድ የተቀጣው ዮሴፍ ከበደ የአመልካች ባል ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ ዮሴፍ ከበደ ወ/ሪት ብርቱካን ዱባለን የደፈራት ነሐሴ 24 ቀን 1998 ከምሽቱ አራት ሰዓት በአመልካች መኖሪያ ቤት ውስጥ እንደሆነ የገለፀ ሲሆን በጉዳዩ የምስክርነት ቃል የሰጠችው የግል ተበዳይ አመልካች ጊንቢ ከተማ እንሂድ ብላት አብረው ሄደው ዕቃ እንደገዙና ከዚያም በምሽት አመልካች በመኪና ትኬት ቆርጣ ከመኪናው ጋቤና ተቀምጠው እንደመጡና አመልካች እቤቷ አጠገብ ስትደርስ ወርዳ ዕቃውን አያይዥኝ ብላ ጠይቃ እቤት እንደገባችና የአመልካች ባል ዮሴፍ ከበደ ከምሽቱ ስምንት ሠዓት ሲሆን የአስገድዶ መድፈር ወንጀል እንደፈፀመባት የመሰከረች መሆኑን ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የአማርኛ ትርጉም ለመረዳት ችለናል፡፡ ሌሎቹ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የጽሁፍ ማስረጃ አመልካች የወንጀል ተካፋይ ስለመሆኗ የሚያስረዱ አይደሉም፡፡

አመልካች ተካፋይ ሆናበታለች ተብላ የተከሰሰችበት የአስገድዶ መድፈር ወንጀል በወንጀል ሕግ ቁጥር 32 ድንጋጌዎች መሠረት አመልካች ተካፋይ ለመሆን የማትችልበትና ወንጀሉ በተቃራኒው ጾታ (ወንድ) ሊፈጸም የሚቻል በመሆኑ ከጅምሩ ዓቃቤ ሕግ አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና አንቀጽ 630 በመጥቀስ የቀረበው ክስ የአመልካች የወንጀል ተካፋይነት ባግባቡ የሚገልጽ አይደለም፡፡ አመልካች በወንጀሉ ተካፋይ ነበረች ለማለት ዓቃቤ ሕግ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 33 የተነገገውን ሁኔታ በአጥጋቢ ማስረጃ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 33 መሠረት አዷት ሴት ሌላኛዋ ሴት ለተፈፀመባት የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ተካፋይ ሆናለች ብሎ ለመክሰስና ጥፋተኛ ለማሰኘት ሴትዮዋ በሙሉ ፈቃዷና ዕውቀቷ የወንጀሉ ተካፋይ የነበረች መሆኑን ከሣሽ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 33 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ዓቃቤ ሕግ አመልካች ባሏ የግል ተበዳይን አስገድዶ ሲደፍር በሙሉ ፈቃዷና ዕውቀቷ የወንጀሉ ተካፋይ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረበው ብቻኛ ማስረጃ የግል ተበዳይ የሰጠችው የምስክርነት ቃል ሲሆን ምስክሯ አመልካች ጊንቢ ሃኪም ቤት አብራት እንድትሄድ ጠይቃት ቀን ጊንቢ ከተማ አብረው የዋሉ መሆኑን ከምሽቱ ሶስት ሠዓት አካባቢ የተመለሱና አመልካች የገዛችው ዕቃ ስታወርድ ተሣፍራበት የነበረው መኪናው ጥሏት የሄደ መሆኑን ከምሽቱ ሶስት ሰዓት አመልካችና የአመልካች ባል ዮሴፍ ከበደ ከቤታቸው ያስገቧት መሆኑን ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ሲሆን ዮሴፍ ከበደ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል የፈፀመባት መሆኑን የመሰከረች መሆኑን መዝገቡ ያሣያል፡፡ ይህንንም ስንመለከተው አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር ጊንቢ ከተማ ሄዳ የዋለችው እና አምሽተው የመጡት ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት በመነሳት ባሏ ዮሴፍ ከበደ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል እንደሚፈጽምባት ሙሉ እውቀት የነበራትና በሙሉ ፈቃደኝነት በወንጀሉ ስራ ተካፋይ መሆኗን የሚያስረዳ የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃ አይደለም፡፡ ይልቁንም በግል ተበዳይ ላይ ዮሴፍ ከበደ አስገድዶ መድፈር ወንጀል በፈጸመበት ጊዜ ከሌሊቱ 8 ሰአት አመልካች ያደረገችው ተሣትፎ ያለ ስለመሆኑ የግል ተበዳይ ለመመስከሯ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው የአስገድዶ መድፈር ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ማለትም ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት አመልካች የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 33 በሚደነግገው መሠረት በሙሉ ፈቃዷና ዕውቀቷ በወንጀሉ ሥራ ያልተካፈለች መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ ስለሆነም ዓቃቤ ሕግ በቂ ማስረጃ በማቅረብ አመልካች ባለቤቷ በሌሊት ስምንት ሠዓት ኳደኛዋ በሆነችው የግል ተበዳይ ላይ የፈፀመው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል በሙሉ ፈቃዷና ዕውቀቷ ተካፋይ የነበረች መሆኑን ባላስረዳበት ሁኔታ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በወንጀሉ ተካፋይ ልትሆን የምትችልበትን ልዩ ሁኔታና የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 33 ድንጋጌ ሣያገናዝብ አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር ጊንቢ ከተማ ውላ የመጣች መሆኑን የአስገድዶ መድፈር ወንጀሉን ለማመቻቸት ነው የሚለውን ግምታዊ መደምደሚያ በመመልከት ብቻ አመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ከላይ የዘረዘርናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና በስር ችሎት ይህንን ግድፈት ሣያርሙ ማለፋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት ስለ አመልካች የሰጡት ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
3. አመልካች ባለቤቷ አቶ ዮሴፍ ከበደ ጥፋተኛ ሆኖ በተቀጣበት የአስገድዶ መድፈር ወንጀል በሙሉ ፈቃዷና ዕውቀቷ ተካፋይ ስላልሆነች በነፃ ትሰናበታለች ብለናል፡፡
4. አመልካች ላይ ተሰጥቶ የነበረው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ የተሻረ መሆኑ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡ አመልካች በዋስትና ያስያዘችው ገንዘብ ካለ ይመለስ፡፡

   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 42703

ሐምሌ 22 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ፋሲል ብርሃኑ - ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** ዓቃቤ ሕግ /የኦሮሚያ ክልላዊ ብሔራዊ መንግስት/ - አልቀረቡም

## ፍ ር ድ

የሰበር ችሎት አመልካች በተወሰነበት የጥፋተኝነት እና ቅጣት ውሣኔ ላይ ባቀረበው ማመልከቻ መነሻነት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይህን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ለጉዳዩ መነሻ የሆነው ዓቃቤ ሕግ በአመልካቹ ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ በ1/8/2000 ዓ.ም በተፃፈ ክስ አመልካቹ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543(3) በመተላለፍ የካቲት 8 ቀን 2000 ዓ.ም በግምቱ ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ በጂማ ዞን ስኮሩ ወረዳ በቲሮ ቁምቢ ቀበሌ ውስጥ ኬላ ጉሼ በሚባል ቦታ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-42631 አ.አ የሆነ አይሱዚ የሕዝብ ማመላለሻ መኪና ያለጥንቃቄ ሲያሽከረክር መኪናው ተገልብጦ መኪናው ውስጥ ሲጓዙ የነበሩትን ሁለት ሰዎች በቸልተኝነት ገድሏል በማለት የወንጀል ክስ መስርቷል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ሶስት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችን፣ የትራፊክ ኘላንና የመኪናው የቴክኒክ ምርመራ መግለጫ ከተቀበለ በኋላ ተከሣሹ እንዲከላከል በማዘዙ ሁለት የመከላከያ ምስክሮችንም ሰምቷል፡፡

ፍርድ ቤት የቀረቡት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ከጂማ ወደ አዲስ አበባ በመሄድ ላይ እያለ ኩርባ ቦታ ላይ ሲደርሱ መገልበጡን አረጋግጠዋል፡፡ ከእነዚህ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች አንደኛው መኪናው በመካከለኛ ፍጥነት ይጓዝ እንደነበር ሲመሰክር ሁለተኛው የመኪናውን ፍጥነት መገመት እንዳልቻለ ገልጿል፡፡ ሦስተኛው ምስክር ግን ተከሣሹ በፍጥነት ሲያሽከረክር እንደነበርና ፍጥነቱን ሳይቀንስ ኩርባው ላይ በመድረሱ መኪናው መገልበጡን ገልጿል፡፡ ሦስቱም ምስክሮች በዚህ ምክንያት ሁለት ተሳፋሪዎች መሞታቸውንም መስክረዋል፡፡ የተከሣሹ ሁለት የመከላከያ ምስክሮችም እንደዚሁ በመኪናው ተሳፍረው ይጓዙ እንደነበረ ገልፀው በክሱ በተገለፀው ቦታ ላይ ሲደርሱ አንድ በሬና እረኛ ወደ መንገዱ ድንገት ስለገቡበት እነሱን ለማዳን ሲል ተከሣሹ መኪናውን ኩርባው ላይ ከቀኝ ወደ ግራ ሲጠመዝዝ መኪናው ተንሸራትቶ መገልበጡንና በዚህ ምክንያት ሁለት ሰዎች መሞታቸውን መስክረዋል፡፡ ፍጥነቱን በሚመለከት አንደኛው ምስክር በጥሩ ሁኔታ በመጓዝ ላይ እንደነበር ሲመሰክር ሌላኛው ግን በግምት ከ50- 60 ኪ.ሜ በሰዓት ይጓዝ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

ጉዳዩን የያዘው ፍ/ቤት ይህን በግራ ቀኙ የቀረበውን ማስረጃ ከተመለከተ በኋላ ተከሣሹ ኩርባ ላይ ከ50—60 ኪ.ሜ በሰዓት በመጓዙ ድንገት የገቡበትን በሬና እረኛ ለማትረፍ ብሎ ወደጐን ሲይዝ መኪናው ተንሸራቶ አደጋው ሊደርስ እንደቻለ ተረድቻለሁ በማለትና ተሳፋሪዎቹ ሊሞቱ የቻሉትም ተከሣሹ ቀስ ብሎ መንዳት በነበረበት ቦታ ላይ በፍጥነት በማሽከርከሩ ነው በማለት ተከሣሹ የወንጀል ሕጉን 543(3) በመተላለፍ ጥፋተኛ ነው ብሏል፡፡ የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላም በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እና 10,000(አስር ሺህ ብር) እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

ተከሣሹ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅረቡ የጥፋተኝነት ውሣኔን አፅንቶ ቅጣቱን ወደ ሦስት ዓመት ጽኑ እስራትና አምስት ሺ ብር መቀጮ ዝቅ እንዲልለት አድርጓል፡፡ የኦሮሚያ የሰበር ችሎት ጉዳዩ በአቤቱታ ቀርቦለት በድምፅ ብልጫ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተገኘበትም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ በዚህ ሁኔታ ጥፋተኛ ተብሎ የሦስት ዓመት እስር 5,000 ብር (አመስት ሺህ ብር) መቀጮ የተጣለበት ተከሣሽ ታህሣስ 14 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የፍርድ ቤቶቹ ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን በማተት ውሣኔው እንዲሻርለት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚህ ሰበር ችሎት አጥብቆ የሚከራከረው መኪናው የተገለበጠው ድንገት ኩርባ ላይ የገቡትን አንድ እረኛና አንድ በሬ ለማዳን በማሰብ መኪናውን ወደ ግራ አቅጣጫ ስለጠመዘዝኩት ነው፣ በመሆኑም በዚህ ሂደት ህይወታቸው የጠፋው ሁለት ተሳፋሪዎች በአደጋ ምክንያት ሞቱ ከሚባል በስተቀር በኔ ቸልተኝነት ሞቱ ተብሎ እኔ ጥፋተኛ ልሆን አይገባኝም በማለት ነው፡፡ ከዚህ በላይ ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543(3) እግረኛን ገጭቶ ለገደለ እንጂ መኪና ተገልብጦ ሰው ለሞተበት አሽከርካሪ ተፈፃሚ ሊሆን አይገባውም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተሳፋሪዎቹ የሞቱት በአሽከርካሪ ቸልተኝነት ነው ሊባል ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን የሕግ ነጥብ ለማጣራት ጉዳዩ ዓቃቤ ሕግም ባለበት ሁለቱ ባለጉዳዮች የቃል ክርክር እንዲያደርጉበት ተደርጓል፡፡

የሰበር ችሎት ከላይ የተጠቀሰው አጠቃላይ የክርክሩ ሂደት አግባብ ካላቸው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ እና አመልካችና መልስ ሰጪ በዚህ ችሎት ቀርበው ካሰሙት የቃል ክርክር ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል፡፡ ከቀረበው ፍሬ ነገርና ከተወሰነው ውሣኔ አንፃርም አመልካችን በወንጀል ጥፋተኛ ለማለት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 543(3) የተጠቀሱት መስፈርቶች ተሟልቷል? ወይስ አልተሟሉም? የሚለውን ነጥብ አጣርቷል፡፡ አመልካቹ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የተቀጣ በመሆኑ በሕጉ ቸልተኝነት የሚያቋቁሙ መስፈርቶች መሟላት አለመሟላታቸውን አጣርቷል፡፡ ይህ ችሎት በዋናነት የመረመረው የሕግ ነጥቡን ብቻ ቢሆንም የሕጉን አግባብነት በትክክል ለመመዘን በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች በቅድሚያ ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳዩ በሥር ፍ/ቤቶች ሲታይ አመልካች ከጂማ ወደ አዲስ አበባ ሲጓዝ መኪናው መገልበጡና ከተሳፋሪዎች መካከል ሁለቱ መሞታቸው ተረጋግጧል፡፡ መኪናው ሊገለበጥ የቻለው መኪናው ከ 50 — 60 ኪ.ሜ በሰዓት ሲጓዝ ከፊት ለፊት አንድ እረኛ በሬውን ለመመለስ በቅርብ ርቀት ስለገባበት እንደሆነም በስር ፍ/ቤቶች ግንዛቤ ተወስዶበታል፡፡ እረኛው መኪናው መንገድ ውስጥ የገባበትና መኪናው የተገለበጠበት ቦታ ኩርባ እንደሆነም በሂደቱ ተጣርቷል፡፡ መኪናው የቴክኒክ ብልሽት ያልነበረበት መሆኑም ከቀረበው የቴክኒክ ሪፖርት ተረጋግጦአል፡፡ እነዚህ በፍርዱ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ሲሆኑ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ሕግ ይዘት ደግሞ ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

አመልካቹ በዓቃቤ ሕግ ክስ የተመሰረተበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(3)"ን" በመተላለፍ ሁለቱ ሰዎች በቸልተኝነት ገድሏል በማለት ነው፡፡ በመሆኑም የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የተጠቀሰውን ሕግ የሚያቋቁሙ መሆን አለመሆናቸው ለማረጋገጥ ሕጉ ቸልተኝነት አለ የሚለው ምን ምን ሁኔታዎች ሲሟሉ እንደሆነ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 57 በግልፅ እንደሰፈረው "ለድርጊቱ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት አንድ ወንጀል ካላደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ አይሆንም" በአንፃሩ አንድ ሰው "የፈፀመው ድርጊት በሕግ የሚያስቀጣ ቢሆንም ምንም ጥፋት ሳያደርግ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ ነገር የተፈፀመ ወይም የደረሰ ሆኖ ሲገኝ በወንጀል ሕግ ሊፈረድበት አይገባውም በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 57(2) ይደነግጋል፡፡ ከዚህ የሕጉ አጠቃላይ አባባል መገንዘብ የሚቻለው በአንድ ድርጊት ምክንያት አንድን ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት ከሳሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግ ድርጊቱ የተፈፀመው ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት መሆኑን ነው፡፡ ድርጊቱ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የተፈፀመ መሆኑ ማስረጃ ካልቀረበ ወይም ድርጊቱ ከአቅም በላይ ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈፀመ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በተከሣሽ በኩል ከቀረበ የተከሰሰውን ሰው በወንጀል ሕግ ጥፋተኛ ብሎ መፍረድ ከሕጉ መንፈስ ውጪ ነው፡፡ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ቸልተኛ ነበር ወይስ አልነበረም የሚለው ጥያቄ በወንጀል ሕጉ በአንቀፅ 59 የሰፈረውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የሚወሰን ነው፡፡ የዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ አንድ አሁን ለተያዘው ጉዳይ በቀጥታ አግባብነት ያለው በመሆኑም የሕጉን ይዞታ እንዳለ ማስቀመጡ ጠቃሚ ነው፡፡ "59(1) ማንም ሰው በቸልተኝነት የወንጀል ተግባር አድርጓል የሚባለው፡-

(ሀ) ድርጊቱ በወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም የሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን፣ ወይም

(ለ) ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ነው።"

" የእንግሊዘኛው ትርጉም ደግሞ እንደሚከተለው ይደነግጋል Article 59

1) A person is deemed to have committed a criminal act negligently where he acts:
   a) by imprudence or in disregard of the possible consequences of his act while he was aware that his act may cause illegal and punishable consequences; or
   b) by a criminal lack of foresight or without consideration while he should or could have been aware that his act may cause illegal and punishable consequences."

በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው በቸልተኝነት ወንጀል ፈፅሟል የሚባለው ውጤቱን እያወቀ ውጤቱ አይደርስም ከሚል መነሻ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ደግሞ የወንጀል ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ባያውቅም ውጤቱን ማወቅ ነበረበት ወይም ጥረት ቢያደርግ ውጤቱን ማወቅ ይችል ነበር ማለት ሲቻል ነው። በመሆኑም ቸልተኝነት አለ ለማለት ሕጉ የሚጠቀምበት ዋነኛ መስፈርት የተከሰሰው ሰው በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንዛቤ ነው። ድርጊቱን የፈፀመው ሰው የነበረው ዕውቀትና ግንዛቤ ወይም ሊኖረው የሚገባው ዕውቀትና ግንዛቤ የሚመዘነው የሰውዬው ዕድሜ፣ ያለው የኑሮ ልምድ፣ የትምህርት ደረጃው፣ ሥራውና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃው ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነም የሕጉ አንቀፅ 59(1) ይደነግጋል።

አሁን በቀረበልን ጉዳይ አመልካች የሚከራከረው ከላይ የተቀጠሱት መስፈርቶች ስላልተሟሉ በቸልተኝነት ሰው በመግደል ጥፋተኛ ልሆን አይገባም በማለት ሲሆን ዓቃቤ ሕግ በሌላ በኩል የሕግ መስፈርቶች ተሟልተዋል የሚል ሙግት አቅርቦአል። ጉዳዩን መጀመሪያ ያየው የጂማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካችን በቸልተኝነት ሰው በመግደል ጥፋተኛ ያለው ቢሆንም የቀረቡለትን ማስረጃዎች በዝርዝር ሕጉ ካስቀመጠው መስፈርት አንፃር ስለመመዘኑ በፍርዱ በግልፅ ያሰፈረው ነገር የለም።

ከላይ እንደተገለፀው አመልካች ጥፋተኛ ነህ የተባለው ከጂማ ወደ አዲስ አበባ በአመልካች አሽከርካሪነት ሲደረግ በነበረ ጉዞ መኪናው በመገልበጡና ሁለት ተሳፋሪዎች በመሞታቸው ነው። መኪናው ሲገለበጥ ከ50 - 60 ኪ.ሜ በሰዓት ፍጥነት የነበረው መሆኑ ምስክሮች የገለፀ ሲሆን በጉዞ ላይ እያሉ ኩርባ ላይ ሲደርስ አንድ እረኛ ከበሬ ጋር ወደ መንገዱ እንደገቡበትም ተመስክሯል። መኪናው ሊገለበጥ የቻለው ሹፌሩ እረኛውንና በሬውን ላለመግጨት ሲል ወደ ግራ ሲጠመዘዝ መኪናው በመንሸራተቱ ነው። በዚህ ሁኔታ የተከሰተው የሁለት ሰዎች ሞት አመልካችን ሊያስጠይቅ የሚችለው በአሽከርካሪነት ስራው ማድረግ የነበረበትን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 59(1) የተገለፀውን ያሟላ እንደሆነ ነው።

ከማህደሩ ዝርዝር ለመገንዘብ እንደቻልነው ሹፌሩ /አመልካች/ መኪናውን ከ50-60 ኪ.ሜ በሰዓት ያሽከረክር ነበር የሚል ምስክርነት የተሰጠው በባለሞያ አይደለም። መኪናው በዚህ ፍጥነት ይጓዝ ነበር ያሉት መኪናው ውስጥ የነበሩ አንድ የዓቃቤ ሕግ ምስክር እና አንድ የከሳሽ ምስክር ናቸው። በመሰረቱ እነዚህ ሁለት ተሳፋሪዎች መኪናው ይጓዝበት የነበረውን ፍጥነት በትክክል ይናገራሉ ብሎ መገመት የሚቻል አይደለም። በመሆኑም ፍ/ቤቱ መኪናው በዚህ ፍጥነት ይጓዝ ነበር በማለት ለደረሰበት መደምደሚያ የሚያበቃ በቂ ማስረጃ አልቀረበለትም።

ከዚያም በላይ መኪናው ከ50 — 60 ኪ.ሜ በሰዓት ይጓዝ ነበር እንኳን ቢባል ከከተማ ውጪ በነበረ ጉዞ በዚህ ፍጥነት ማሽከርከር በአሽከርካሪው በኩል ጥንቃቄ ጉድለት ነበር ለማለት የሚያስችል አሳማኝ ማስረጃ አልቀረበም መኪናው የሕዝብ ትራንስፖርት በመሆኑ ከጂማ ወደ አዲስ አበባ ሲጓዝ በዚህ ፍጥነት መንቀሳቀሱ ጥፋት ሊባል የሚችል አይደለም። መኪናው በተገለበጠበት ቦታ አካባቢ የፍጥነት ጣሪያ የነበረ መሆኑ አልተረጋገጠም ወይም ከጅማ እስከ አ/አ ባለው መንገድ ወይም በአጠቃላይ ከከተማ ውጪ በሚደረግ ጉዞ ከ50 ኪ.ሜ በሰዓት በላይ መንዳት ክልክላ ስለመኖሩም አልተገለፀም። መኪናው ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ማስረጃ የቴክኒክ ችግር እንዳልነበረበት በመረጋገጡ በመኪናው ልዩ ባህርይ

ምክንያት ተከሳሹ ከ50 ኪ.ሜ በሰዓት በታች መንዳት ይጠበቅበት ነበር ሊባል አይችልም፡፡ ስለሆነም መኪናው ከመገልበጡ በፊት ሹፌሩ መፈፀም የነበረበት የጥንቃቄ እርምጃ አለመወሰዱ የሚያሳይ ነገር የለም፡፡

መኪናው በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ አንድ እረኛ ድንገት ከገባበት አሽከርካሪው ማድረግ የሚጠበቅበትን ፈፅሟልን? የሚለው ጥያቄ መልስ የሚፈልገው ሌላው ነጥብ ነው፡፡ ኩርባው ላይ ሲደርስ በቅርብ ርቀት እረኛና በሬ መኪናው መንገድ ላይ ሲገቡ አሽከርካሪው የተለያዩ አማራጮች እንደነበሩት መገመት ይቻላል፡፡ አንደኛው ዕረኛውንና በሬውን ገጭቶ ማለፍ ነው፣ ሁለተኛው ወደ ቀኝ ለመጠምዘዝ እረኛውን ከነከብቱ ለማዳን መሞከር ነው፡፡ በማስረጃ እንደተረጋገጠው መኪናው ወደቀኝ ቢጠመዘዝ ገደል ውስጥ ይገባ ነበር፡፡ በመሆኑም አሽከርካሪው ይህንን አማራጭ አለመውሰዱ የጥንቃቄ ጉድለት ፈጽሟል ሊያሰኘው አይችልም፡፡ ወደግራ በመጠምዘዝ መንገድ ውስጥ ድንገት የገባውን ሰው ለማዳን መሞከሩና እርግጥም ይህንን ሰው ከሞት አደጋ መታደጉም የጥንቃቄ ጉድለት ሊባል አይችልም፡፡ እንዲያውም ሰውዬውን ለማዳን ምንም ሙከራ ሣያደርግ ፊት ለፊት የሚያየውን ሰው ጨፍልቆ ቢያልፍ ከፍ ያለ ወንጀል ይፈፅም እንደነበረ ግልፅ ነው፡፡ አመልካች የቀረውን የመጨረሻ አማራጭ በመጠቀም መኪናውን ወደግራ ሲጠመዝዝ መኪናው እንደሚገለበጥና ከተሳፋሪዎች መካከል ከፊሎቹ እንደሚሞቱ ያውቅ ነበር? ይህንስ እያወቀ ነው ድርጊቱን የፈፀመው? ለያውቅም ከተባለስ የወሰደው አማራጭ ለሰዎች ሞት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ማወቅ ነበረበት ማለት ይቻላል? የሚሉት ጥያቄዎች ቸልተኝነት ነበረ ወይም አልነበረም ለማለት መመለስ የሚገባቸው ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በመሰረቱ ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት አመልካችን የቸልተኝነት ወንጀል ፈፅሟል ሊያሰኝ የሚችል ማስረጃ ወይም የሞያ አስተያየት በዓቃቤ ሕግ በኩል አልቀረበም፡፡ በበኩላችን ከፊት ለፊት ካጋጠመ አደጋ ለመዳን መኪና ወደ ቀኝ ይሁን ወደግራ ሲጠመዘዝ ሁሌም ይገለበጣል ወይም የመገልበጥ ዕድሉ ሰፊ ነው ለማለት አልቻልንም፡፡ በመሆኑም አሽከርካሪው የመኪናውን መገልበጥ ቀደም ብሎ ያውቅ ነበር ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ መኪናው ሊገለበጥ እንደሚችል ማወቅ ነበረበት ማለትም የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም አሽከርካሪው የመኪናው መገልበጥ በጉዞ ላይ በተፈጠረና ከአሽከርካሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ የዕረኛው ድንገት መግባት የተፈጠረ አደጋ (accident) እንጂ በአሽከርካሪው ቸልተኝነት የተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ነው ማለት አልቻልንም፡፡ ከተሳፋሪዎቹ መካከል የሁለቱ መሞትም የዚሁ አደጋ ውጤት እንጂ የቸልተኛ ድርጊት (negligent act) ውጤት ነው ማለት አልቻልንም፡፡ የሰው መሞት በሕግ ሊያስጠይቅ እንደሚችል ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ውጤት በሕግ ሊያስጠይቅ የሚችለው ለሞቱ ምክንያት የሆነው ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ጥፋተኛ የሚሆነው ደግሞ ድርጊቱ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የተፈፀመ እንደሆነ ነው፡፡ አሁን በቀረበልን ጉዳይ የሁለት ተሳፋሪዎች ሞት የተከሰተው በአሽከርከሪው ቸልተኝነት ሳይሆን በድንገተኛ አጋጣሚ በሆነ የመኪና መገልበጥ አደጋ ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የአሁኑን አመልካች በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ያለው የቀረበለትን ማስረጃ ከሕጉ ጋር በተገቢው ሁኔታ ሳያገናዝብ ነው፡፡ ለውሣኔው መሰረት ያደረገው የመኪናው መገልበጥ ለሁለት ሰዎች ሞት ምክንያት መሆኑን ብቻ ነው፡፡ አመልካቹ ሰዎቹ የሞቱት በአደጋ (accident) እንጂ በቸልተኛ የወንጀል ድርጊት (negligent criminal offence) አይደለም እያለ ከመጀመሪያው ጀምሮ የተከራከረ ቢሆንም ፍ/ቤቶቹ ለዚህ ክርክር ትኩረት በመስጠት በአደጋና በቸልተኛ ድርጊት መካከል ያለውን ልዩነት አልመረመሩም በዚህም ምክንያት በሕጉ መንፈስ ወንጀለኛ መባል ያልነበረበት ሰው ጥፋተኛ በማለት በእስርና በገንዘብ እንዲቀጣ ውሣኔ መስጠታቸው የሕጉን ግልፅ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ስላገኘነው በዚህ ጉዳይ የጂማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትና ሰበር ችሎት የሰጡት የጥፋተኛነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ መሻር አለበት ብለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የጂማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 10769 ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 71726 ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ሰበር ችሎት በወ/ቁ 70164 ታህሣሥ ቀን 2001 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543(3) ተጠቅሶ ከቀረበበት ክስ ነፃ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች በዚሁ ችሎት ትዕዛዝ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ ካለ ይመለስላቸው፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

# ንብረት

የሰ/መ/ቁ. 36320

ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መሰሠ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዘውዴ ገ/ስላሴ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሕይወት ባሕታ - ቀረቡ፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በትግራይ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በሌሎች 4 ተከሣሾች ላይ ባቀረቡት ክስ ተከሣሾች መብት ሣይኖራቸው የሟች አባቴን ቤትና ቦታ ስለያዙ ለቀው ያስረክቡኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ተከሣሾችም ተከራይና አከራይ በመሆናቸው የቤቱ ባለቤት ናቸው የተባሉት የአሁኗ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ተተክተው እንዲገቡ ተደርጎ ተጠሪዋ ቤቱና ቦታው የሣቸው መሆኑንና አመልካች በቤቱ ላይ መብት ያላቸው ለመሆኑ አግባብ ያለው ማስረጃ ስላላቀረቡ ክሱ ውድቅ እንዲደረግባቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮችን ከሠማ በኂላ ቤቱና ቦታው የአመልካች አባትና የሚስታቸው የአሁኗ ተጠሪ የጋራ ንብረት በመሆኑ ተጠሪ የአመልካች አባት ድርሻ የሆነውን ግማሽ ንብረት ለአመልካች ታካፍል  በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤትም የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሣኔ በድምጽ ብልጫ አጽድቆታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ላይ በድጋሚ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ እያከራከረ ያለው የማይንቀሳቀስ ንብረት በመሆኑ ክስ ሊመሠርቱ ይገባ የነበረው የቤትና የቦታውን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ በማቅረብ ነው በማለት ክሱን ለማቅረብ በንብረቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን አላስረዱም ሲል የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተጠሪ ቦታና ቤቱን የያዙት የአባቴ ባለቤት ስለሆኑ እንጂ እራሳቸው ተመርተው አይደለም፤ ቦታውና ቤቱ አሁንም ድረስ በአባቴ የሚጠራ ነው፤ በፈረስ ማይ ከተማ እስካሁን ድረስ ለቤትና ለቦታ የተሰጠ ሰነድ የለም፤ ምክንያቱም ከተማው ራሱ እንደከተማ እየተዋቀረ ያለው አሁን ነው፤ የሚል ነው፡፡ ተጠሪም ለሰበር አቤቱታው መልስ እንዲሰጡ ተደርጎ በሰጡት መልስ አመልካች በንብረቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን አላስረዱም፤ በስር ያልተነሣ ክርክር አሁን ሊነሳ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ክስ በመሠረቱበት ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም ወይ? የሚለው ነጥብ ሊመረመር ይገባል፡፡

አመልካች በክሣቸው የአባታቸውን ቤት ተጠሪ እንዲያስረክቧቸው ጠይቀዋል፡፡ በእርግጥ አንድ ሰው ክስ በሚያቀርብበት ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑን ካላረጋገጠ በስተቀር ክስ ማቅረብ እንደማይፈቀድለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች ክርክር ባስነሣው ቤትና ቦታ ላይ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ንብረቱ የአባታቸው መሆኑን ያስረዱልኛል ያሏቸውን የሰው ምስክሮች አቅርበዋል፡፡ የሰበር ችሎቱ ግን ክርክር የሚደረግበት ንብረት የማይንቀሣቀስ ንብረት በመሆኑ መብት መኖሩ ሊረጋገጥ የሚገባው የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ወይም ሰነድ በማቅረብ ነው በማለት ወስኗል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 ላይ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ምስክር ወረቀቱ ለተሠጠበት ንብረት ባለሃብት ሆኖ እንደሚቆጠር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ለአንድ ቤትና ቦታ የባለሃብትነት ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው

የዚሁ ንብረት ባለቤት ለመሆኑ ሕጉ ግምት ይወስዳል፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች ክርክር የተነሣበት ንብረት የሚገኝበት የፈረስ ማይ ከተማ ለማንኛውም ቤትና ቦታ የሰነድ ማስረጃ ያልሰጠ መሆኑን ጠቅሰው ያቀረቡትን ክርክር ተጠሪም አላስተባበሉም፡፡ ተጠሪም ራሣቸው ቢሆኑ ቦታው የራሣቸው ለመሆኑ ግብር የተከፈለበት ደረሰኝ፣ በሌላ መዝገብ የተሰጠ ውሣኔ እና የሰው ምስክር ከማቅረብ በቀር የቤቱና የቦታው ባለሃብት ለመሆናቸው የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አላቀረቡም፡፡ ይህም የሚያሣየው ክርክር የተነሣበት ቤትና ቦታ የሰነድ /የባለሃብትነት ምስክር ወረቀት/ ያልወጣለት መሆኑን ነው፡፡ ከፍ ሲል የተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 የማይንቀሳቀስ ንብረት የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው የንብረቱ ባለሃብት ለመሆኑ ሕጉ ግምት ይወስዳል ከማለት በቀር ማንኛውም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነት በሌላ መንገድ ሊረጋገጥ እንደማይችል አያመለክትም፡፡ በአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ብዙ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች የባለሃብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አልተዘጋጀላቸውም፡፡ ስለዚህ አመልካች ክርክር የተነሣበት ንብረት ላይ በተመለከተ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ባለማቅረባቸው በንብረቱ ላይ ጥቅም ወይም መብት የላቸውም ሊባሉ አይገባም፡፡

በሌላ በኩል ግን ክርክር የተነሣበት ቤትና ቦታ ያለበት አካባቢ በከተማነት እየተዋቀረ መሆኑ የተገለጸ ስለሆነ ይህ ቦታ ቀደም ሲል የማን እንደነበር፣ በአሁኑ ጊዜ ለማን እንደተሰጠ፣ በአሁኑ ጊዜ በስሙ የተመዘገበው ሰው ቦታውን እንዴት እንዳገኘ ከሚመለከተው የከተማ አስተዳደር ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም መሠረት ጉዳዩ መጀመሪያ የቀረበለት ፍ/ቤት የቦታው ባለሃብት ማን እንደሆነ በሚገባ አጣርቶ ሊወስን ይገባል ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 21523 ታህሣሥ 11 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ክርክር የተነሣበት ቤትና ቦታ ቀደም ሲል የማን እንደነበር፣ በአሁኑ ጊዜ ለማን እንደተሰጠና በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ከሚመለከተው የከተማው አስተዳደር አካል ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 መሠረት ለትግራይ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 35003

ህዳር 9 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መሰሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ አሸናፊ ዓብዱልቃድር - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** እነ ወ/ሮ ሽቶ ኢብራሂም/ 4 ሰዎች/ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ሟች አባታቸው በኑዛዜ ያወረሷቸውን ቤት ተጠሪዎች እንዲያካፈሏቸው ጠይቀዋል አንደኛ ተጠሪ የሟች ሚስት በሕይወት እያሉ የውርስ ንብረት ክፍፍል ሟች በኑዛዜያቸው ስለገለፁ ክፍፍሉ ሊፈፀም አይገባም በማለት ተጠሪዎች መልስ ሰጥተዋል ፍ/ቤቱም የውርስ ንብረት አጣሪ አቋቁሞ የውርሱ ንብረት እንዲጣራ አድርጎ የውርስ ንብረት የሆነው በሻሸመኔ ከተማ ቀበሌ 08 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥር 544 የሆነ በ500 ካ.ሜ. ላይ የሠፈረ ቤት መሆኑን ተረጋግጦ ቀርቦለታል፡፡ ከዚህም በኋላ ይኸው ቤት በባለሙያ ተገምቶ ግምቱ ብር 41,078.77 (አርባ አንድ ሺህ ሰባ ስምንት ብር ከሳሰባት ሳንቲም)መሆኑ ተገልጿል፡፡ ፍ/ቤቱም አንደኛ ተጠሪ የሟች ሚስት በመሆናቸው የቤቱ ግማሽ የሣቸው ድርሻ ነው የግምቱን ግማሽ ግን አመልካችና ቀሪዎቹ ተጠሪዎች ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት በመጀመሪያ ለምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀጥሎም ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኛቸው ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል በመጨረሻም አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ለሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ነው የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ አባቴ ቦታ ላይ በራሴ ገንዘብ የሰራሁት ቤት ግምት ውስጥ አልገባልኝም ቤቱ በገበያ ዋጋ አልተገመተም የሚል ነው ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊጣራ የሚገባው ነጥብ መኖሩን በማመን ተጠሪዎች ቀርበው እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡ ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታውን የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ከተባለው ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው አንደኛ ተጠሪ የሟች ሚስት አመልካችና ቀሪዎቹ ተጠሪዎች ደግሞ የሟች ልጆችና ወራሾች ናቸው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የሟችና የአንደኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት በመሆኑ የቤቱ ግማሽ ለአንደኛ ተጠሪ ይገባል በማለት በሰጠው የውሣኔ ክፍል አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ ባለመኖሩ ውሣኔውን እንደተቀበሉት ይቆጠራል፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች በአባታቸው ቦታ ላይ በራሣቸው ገንዘብ የሠሩት ቤት ከግምት ውስጥ ሣይገባ የክፍፍል ውሣኔ እንደተሠጠ ገልፀዋል፡፡ ይህ ቤት በሟች ስም የተመዘገበና ቤቱ የአመልካች ለመሆኑ ምንም ማስረጃ ያልቀረበ ምስክርም ያልተቆጠረ መሆኑን የሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት በውሣኔው አስፍሯል፡፡ በመሆኑም አመልካች ቤቱ በገዛ ገንዘባቸው የሠሩት መሆኑን ማስረዳት ሣይችሉ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሌላው የአመልካች ቅሬታ የውርስ ንብረት በገበያ ዋጋ ሣይገመት በአነስተኛ ግምት ክፍፍሉ መፈፀሙ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ በሌላ አነጋገር የውርስ ንብረቱ በወራሾች መሃከል እኩል አልተከፋፈለም የሚል ነው፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች ክስ ያቀረቡት የውርስ ንብረቱን በሟች ኑዛዜ መሠረት ለመካፈል ነው፡፡ ፍ/ቤቶቹም የቤቱ ግማሽ የአንደኛ ተጠሪ ድርሻ መሆኑንና ቀሪውን የሟች ግማሽ ድርሻ ልጆቹ እኩል እንደካፈሉ በሰጡት ውሣኔ በግራ ቀኙ የቀረበ ቅሬታ ባለመኖሩ ሟች ንብረቱን በዚሁ መሠረት እንዲካፈሉ የተናዘዙ መሆኑን ችሎቱ ግንዛቤ ወስዷል፡፡ ንብረቱን በዚሁ መሠረት ለመካፈልም የንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የስር ፍ/ቤት የንብረቱ ዋጋ በመሐንዲሶች የቀረበው ግምት ነው በማለት በዚሁ መሠረት ክፍፍሉን መወሰኑን ተረድተናል፡፡ የንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ ነው ማለት የሚቻለው ግን ቤቱን ለመስራት የወጣው ወጪ /book value/ ብቻ ሣይሆን ይልቁንም ቤቱ በወቅቱ ለገበያ በቀረበ ሊያወጣ የሚችለው ዋጋ /market value/ ነው በሥር ፍ/ቤት እንደተደረገው ቤቱ የተሠራበት ዋጋ ብቻ በባለሙያ ተገምቶ በቀረበው ግምት መሠረት ገንዘቡን መከፋፈሉ ንብረቱን የሚያስቀረው ወገን የበለጠ ጥቅም እንዲያገኝና በሌላው ወገን ላይ ጉዳት የሚያደርስ በመሆኑ የእኩልነት መርህን የሚንድ ይሆናል፡፡ ስለሆነም የውርስ ንብረት ክፍፍሉ መፈፀም ያለበት በንብረት የገበያ ዋጋ መሠረት ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ንብረቱ ለመስራት የወጣውን ወጪ መሠረት በማድረግ ክፍፍሉን መወሰናቸው የእኩልነት መርህን የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት የመ/ቁ. ባልተጠቀሰ በ24/6/98 የሰጠው ውሣኔ የምዕ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 09775 በ28/07/98 እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40405 በ4/9/98 የሰጡት ትእዛዞች እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 41006 በ07/04/2000 የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የውርሱ ንብረት በገበያ ዋጋ ተገምቶ በሚቀርበው ግምት መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈፀም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት ጉዳዩ ለሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ 36645

ህዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ረዳት ሳጂን አያኖ አንጀሎ - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** እነ ወ/ሮ ዓለሚቱ ጫሌቦ- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መ/ በወላይታ ዞን በአረካ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ ንብረትነቱ የእራሷና የሟች ባለቤቷ የሆነውን በ270 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተሰራ ቤት በ26/10/94 በተጻፈ ውል ሸጣልኝ ቤቱን አስፋፍቼ ለመሥራት እንስት ለመንቀል ስጀምር አላስነቅልም፣ ቤቱንም ቦታውንም አልሸጥኩም በማለት ሁከት የፈጠረችብኝ ስለሆነ ይሄው ሁከት ይወገድልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አንደኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ቀርበው ሁከት ተፈጥሮበታል የተባለውን ቤት ለከሳሽ እንዳልሸጡና በውሉ ላይም እንዳልፈረሙ ከሳሽ በቤቱ ውስጥ የሚኖረው በተከራይነት መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል ሁለተኛ አመልካችም በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ጠይቀው ተፈቅዶላቸው የሟች አባታቸው ወራሽ መሆናቸውን ገልጸው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በሽያጭ ለከሳሽ እንዳልተላለፈና በቤቱ ውስጥ በኪራይ እንደሚኖሩ ጠቅሰው ከአንደኛ ተከሳሽ ጋር ተመሳሳይ የሆነው ክርክር አቅርበው ክሱ ሊሰረዝ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የአረካ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሳሽ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ከአንደኛ ተከሳሽ የገዙት መሆኑን ቢገልጽም በአስረጂነት ያቀረቡት ሠነድ በአንደኛ ተከሳሽ ያልተፈረመበት መሆኑ ስለተረጋገጠና ከሳሽም እራሱ በሰነድ ላይ ስለመፈረሙ በዚህ ሁኔታ ሁከት ይወገድልኝ ተብሎ የቀረበው ክስ አግባብነት የለውም በማለት አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ለጉዳዮ እልባት መስጠት የነበረበት ሁከት አለ ወይንስ የለም? ከሚለው ጭብጥ አኳያ መሆን ሲገባው የውሉን ሕጋዊነት በጭብጥነት ይዞ ጉዳዮን በመመርመር ውሉ በአግባቡ ስላልተደረገ ሁከት የለም በማለት ውሳኔ መስጠቱ በተገቢው አይደለም ካለ በኋላ ሁከት ስለመፈጠሩ በይግባኝ ባይ ማስረጃ መረጋገጡን መገንዘብ ስለሚቻል የተፈጠረው ሁከት ሊወገድ ይገባል በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም ተጠሪዎች የይግባኝ ቅሬታቸውን በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት አቅርበው ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙ አከራክሮ መልስ ሰጭ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ያቀረቡት በሕግ የማይጸና ውልን መሠረት አድርገው ስለሆነ ጉዳዮን በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣኑ በተመለከተው የአረካ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሉ በሕግ አግባብነት ያልተቋቋመ ስለሆነ የቀረበው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ማለቱ አግባብነት ያለው ሆኖ ሳለ የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ ውሳኔ መሻሩ በአግባቡ አይደለም በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመበትም በማለት የሰበር አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ለዚህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ያቀረቡት ክስ ሁከት ይወገድልኝ የሚል ሆኖ ሳለ የቤት ሽያጭ ውሉ የሚጸና አይደለም ተብሎ መወሰኑ አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ መጠራት እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሑፍ አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብስ አኳያ የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እነደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስበቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በሥር ፍ/ቤት አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ላይ ክስ ያቀረቡት የመኖሪያ ቤት በውል ሸጠውልኝ ይህንኑ ቤት አስፋፍቼ ለስራት በነበረኝ ፍላጐት ሥራውን ስጀምር እንዳልሰራ የከለከሉኝ ስለሆነ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልኝ በማለት ነው፡፡

ይዞታው የተወሰደበት ወይም በይዞታው ላይ ሁከት የተነሳበት ሰው የተወሰደበት ነገር እንዲመለስለት ወይም የተነሳው ሁከት እንዲወገድለት ዳኝነት መጠየቅ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ1149/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይዞታ ማለት ደግሞ አንድ ሰው አንድን ነገር በእጁ አድርጐ በእውነት የሚያዝበት ሆኖ ሲገኝ እንደሆነም በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1140 ላይ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ የሕጉ ድንጋጌ አኳያ አንድ ሰው በአንድ ነገር ላይ ባለይዞታ እንዲባል ነገሩ በእጁ መገኘት እንደሚገባውና የነገሩ በእጁ መገኘትም ይዞታ ያለው ስለመሆኑ በቂ ማረጋገጫ አንደሆነ መገንዘብ ይቻላል እዚህ ላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነጥብ አንድ ሰው ንብረቱ በእጁ አድርጐ በእውነት የሚያዝበት የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡ በእውነት የሚያዝበት የሚለው አባባል የሚያስገነዝበው ንብረቱን በእጁ አድርጐ መገኘቱ ብቻ ሳይሆን በዚህ ንብረት ላይ በእውነት ማዘዝ እንዲችል የንብረቱ አያያዝ ያልተጨበረበረና በማናቸውም መንገድ ሕገወጥ በሆነ ሁኔታ ያልተገኘ መሆን እንደሚገባው ነው፡፡

አመልካች ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ቤቱ የያዙት አንደኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል መነሻነት እንደሆነ  ጠቅሰዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪም በበኩላቸው ቤቱን ለአመልካች እንዳልሸጡና በአመልካች በኩልም የሽያጭ ውል መኖሩን ያረጋግጣል ተብሎ የቀረበው ሠነድ በሕግ አግባብነት ያልተቋቋመ መሆኑን ገልጸው ይልቁንም ከሳሽ በቤቱ ውስጥ የሚገኙት በኪራይ ውል መነሻነት እንደሆነ ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ የተጠሪ ክርክር ሁከት ተፈጥሮበታል የተባለው ቤት በተጭበረበረ አኳኋን አመልካች እጀ ሊገባ እንደቻለ መገንዘብ አይቻልም፡፡ በመካከላቸው ተደርጓል የተባለው ውል ተገቢውን የአጻጻፍ ሥርአት /Form/ ተከትሎ አልተደረገም ቢባል እንኳን ይህ ሁኔታ በእራሱ አመልካች ቤቱን በተጭበረበረ መንገድ እንደያዙትና በእውነት የሚያዙበት እንዳልሆነ የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ የውሉ ተገቢውን የአጻጻፍ ሥርዓት ተከትሎ አለመደረግ ይዞታው በተጨበረበረ መንገድ ስለመያዙ ወይንም በማናቸውም ሕገወጥ ሁኔታ ስለመያዙና አመልካችም በይዞታው በእውነት ሊያዙበት እንደማይችሉ ስለማያረጋግጥ በዚህ ረገድ ውሉ ጉድለት አለበት ከተባለ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1808(2) ላይ እንደተመለከተው ውሉ ፈራሽ ነው እንዲባል የክስ ምክንያት ከሚሆን በስተቀር ሁከት ይወገድልኝ ተብሎ በቀረበ ክስ ላይ ሊስተናገድ የሚችል አይሆንም ከዚሁ ጋር በተያያዘም አንደኛ ተጠሪ አመልካች ቤቱን ይዘው የሚገኙት በመካከላችን በተደረገው የቤት ሽያጭ ውል መነሻነት ነው በማለት የጠቀሱት ቤቱ በአመልካች በተጭበረበረ ሁኔታ እንዳልተያዘና በተገቢው መንገድ እንደተያዘና በእውነትም የሚያዙበት መሆኑን ይበልጥ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዮን በይግባኝ የተመለከተው የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በጭብጥነት ተይዞ መፈታት የሚገባው ጉዳይ ሁከት አለ ወይንስ የለም? የሚለው ነው በማለት በዚህ ጭብጥ ላይ ተመስርቶ ጉዳዮን በመመርመር በአመልካች ይዞታ ላይ ተጠሪ ሁከት ስለመፈጸማቸው የተረጋገጠ ስለሆነ ይኸው ሁከት ይወገድ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ በእኛ በኩልም ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ነገር ግን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የቤት ሽያጭ ውሉ በሕግ አግባብነት ስላልተቋቋመ በዚህ ውል ላይ ተመስርቶ የቀረበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የለውም ሲል የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ውሳኔ ማጽናቱ

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር  ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም በመ/ቁ/21070 የሰጠው ትእዛዝ እንደዚሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 20355 በ2/6/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሽረነዋል፡፡
2. የወላይታ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 06718 በ9/4/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
3. የግራ ቀኙ ወጪና ኪሣሳ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

## የ ሀ ሳ ብ  ል ዩ ነ ት

እኔ በአምስኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አመልካች በተጠሪ ላይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ የማቅረብ መብት የለውም የሚል እምነት ያለኝ በመሆኑ ከሙያ አጋሮቼ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ፍሬ ጉዳይ ከላይ በአጭሩና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ተጠቅሷል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ቤት በውል የገዛ መሆኑንና ቤቱንና ቦታውን ተረክቦ በእጁ ያደረገ መሆኑን ገልጾ የገዛሁትን ቤት አስፋፍቼ ለመሥራት ስሞክርና እንሰት በመንቀል ላይ እያለሁ ተጠሪ ስለ ከለከለችኝ በይዞታዬ ላይ ሁከት እየፈጠረች ነውና ሁከቱ እንዲወገድ ትእዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

ከዚህ በመነሳት አመልካች ከተጠሪው ጋር ባደረገው የቤት ሽያጭ ውል መነሻ ቦታውንና ቤቱን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1140 መሠረት በእጁ አድርጐ የያዘ መሆኑና የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በይዞታው ላይ የተፈጠረ ሁከት እንዲወገድለት የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑ ግልጽና የማያከራክር ጉዳይ ነው፡፡

አከራካሪው ነጥብ አመልካች የቤቱና የቦታው በይዞታ እንጅ ባለቤት አይደለም፡፡ አመልካች ቤቱን በግዥ ውል መሠረት ከተጠሪ ተረክቦ በእጁ ያደረገ ቢሆንም የቤቱ የባለቤትነት መብት ገና አልተላለፈለትም፡፡ ስለዚህ በቤቱና በቦታው ላይ አመልካች የይዞታ መብት ያለው ሲሆን ተጠሪ በበኩሏ የባለቤትነት መብት አላት፡፡ ባለ ሀብትነት በአንድ ግዙፍ ንብረት ላይ ከሁሉ ያሰፋ መብትን የያዘ እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1204 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል ከዚህ አንፃር ስናየው አመልካች የንብረቱ ግል ይዞታ የሆነው ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1204 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የባለቤትነት መብቷን ለማስተላለፍ ባደረገችው ስምምነት ነው፡፡ ሆኖም ይኸ ስምምነት ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ አልሆነም፡፡ የሽያጭ ውሉ ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ ባልሆነበትና ስመ ንብረቱ በአመልካች ባልተዛወረበት ሁኔታ የንብረቱ ባለቤት የሆነችው ተጠሪ የንብረት ባለ ይዞታ ከሆነው አመልካች የሰፋ መብት አላት፡፡ ተጠሪ የንብረቱ ባለቤት በመሆኗም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1206 መሠረት የባቤትነት መብቷን የማስከበርና የመፋለም መብት አላት፡፡ የአንድ ንብረት ባለቤት የሆነ ሰው ሌሎች ሰዎች በንብረቱ ላይ እንዳይደርሱ ወይም የንብረቱን ባለይዞታና ጠባቂ ከንብረቱ እንዲለቁ የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ከዚህ አንፃር የይዞታ መብትን ለማስከበር የሚቀርብ ክስ የአንድን ሀብት ባለቤት የባለቤትነት መብት የሚገድብ ሣይሆን የንብረቱ ባለቤት ሣይሆኑ በይዞታ ጣልቃ የሚገቡ ሌሎች ሰዎችን ለማስቆምና ለመከላከል የሚቀርብ የክስ አይነት ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

አመልካች ተጠሪ በቤቱ ላይ ያላትን የባለቤትነት መብት በህግ የሚፀና የቤት ሽያጭ ውል ለማስተላለፍ ተስማምታለች የሚል ከሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2879 ድንጋጌዎች መሠረት የቤቱን ስመ ንብረት ወደ እሱ ለማዛወር የሚያስፈልጉ ሰነዶችን እንድታስረክብና የቤቱን ስመ ንብረት ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ግዴታዎችን እንድታሟላ

በንብረቱ ግምት ልክ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 215 ንዑስ አንቀጽ 1 የዳኝነት ከፍሎ ከሚጠይቅ በስተቀር የሽያጭ ውልን መነሻ አድርጐ የቤቱና የቦታው ባለይዞታ የሆነው ሰው የንብረቱ ባለቤት የሆነችውን ተጠሪን በይዞታዋ ላይ ሁከት ፈጠረችብኝ ብሎ መክሰሱ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም የቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት በልዩነት ወስኛለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

**ፀ/መ**

የሰ/መ/ቁ. 37297

ታህሣሥ 02 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

በላቸው አንሺሶ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ በላይነህ ዓለማየሁ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ እታለም ተስፋ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኗ ተጠሪ በነቀምቴ ከተማ ቀበሌ 07 ክልል ውስጥ የሚገኘውን በቁጥር 864 የተመዘገበውን የመኖሪያ ቤት ባለቤታቸው አቶ አብሽሩ ብልሃት ከአመልካች ድርጅት ገንዘብ ሲበደሩ ተጠቃሹን ቤት ከተጠሪ እውቅና ውጪ ለብድሩ በዋስትና ያስያዙ ሁኖ አግኝተው በቤቱ ላይ ያላቸው ድርሻ እንዲጠበቅላቸው ዘንድ በፍ/ቤት ክስ መስርተው ክርክር ከተካሄደ በኋላ ፍ/ቤቱ ተጠሪ በቤቱ ላይ ያላቸውን ግማሽ መብት በመጠበቅ ውሣኔ ሰጥቶ ይህ ውሣኔ በበላይ ፍ/ቤት አለመለወጡን፣ በቤቱ ላይ ያላቸው መብት በፍ/ቤት ውሣኔ ተጠብቆላቸው እያለ ግን አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ተጠቃሹን ቤት በሐራጅ ለመሸጥ በጋዜጣ ማስታወቂያ አውጥቶ በዝግጅት ላይ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰው በቀድሞ ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀምላቸው ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካች በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመሰረቱት የአፈፃፀም ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በፊት በተሰጠው ውሣኔ መሠረት በንብረቱ ላይ የመያዝ መብት እንዳለው መረጋገጡን፣ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ንብረቱን በሐራጅ በመሸጥ ለተጠሪዋ በፍ/ቤቱ ውሣኔ መሠረት ለመፈፀም በዝግጅት ላይ ባለበት ጊዜ የቀረበ ጥያቄ መሆኑን በመግለጽ የተጠሪዋ የአፈፃፀም ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ክርክር የተነሣበት ንብረት ላይ ተጠሪዋ መብት እንዳላቸው ከዚህ በፊት በተሰጠው ውሣኔ የተረጋገጠ ስለሆነ የተጠሪዋን መብት ወደ ጎን በመተው ንብረቱን በሐራጅ ለመሸጥ ማስታወቂያ ማውጣቱ የሕግ አግባብነት የለውም የሚለውን ነጥብ በምክንያትነት በመያዝ ንብረቱ በሐራጅ የቀረበበትን ዋጋ የብር 16349.50 /አስራ ስድስት ሺህ ሦስት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር ከሃምሣ ሣንቲም/ ግማሽ ብር 8174.75/ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሰባ አራት ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም/ ተጠሪዋ ለአመልካች ከከፈሉ በኋላ የንብረቱ ስም ወደ ተጠሪዋ እንዲዞር በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ላይ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ይኸው ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፈጅ ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ አመልካች በንብረቱ ግማሽ ላይ የፍርድ ባለመብት ሁኖ እያለ የበታች ፍ/ቤቶች ትዕዛዝ ይህንኑ ሁኔታ ያላገናዘበ መሆኑን፣ እንዲሁም በቤተሰብ ሕጉ ላይ የተመለከተውን የጋብቻ የጋራ ንብረት ክፍፍል አፈፃፀምን መሠረት ያላደረገ መሆኑን፣ የመሐንዲስ ግምት የገበያ ዋጋ የማይወክል መሆኑን፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ አመልካች በግማሽ መብቱ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ማስፈፀም እንደሚችል ተረጋግጦ እያለ በአፈፃፀም ወቅት መሻሩ ያለአግባብ መሆኑን መበዘርዘር የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ ክርክር ያስነሳው ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት በሀራጅ ተሸጦ አመልካችና ተጠሪ

እኩል እንዲካፈሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ሐምሌ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ የመልሣቸው ይዘትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ነጥቦችን ያላግባበነት፣ የበታች ፍ/ቤቶችን ትዕዛዝ ደግሞ ሕጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካችም ሐምሌ 30 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ በመያዣ ንብረት ላይ ያላቸው የድርሻ መብት የሚታሰበው ከሐራጅ የሽያጭ ገንዘብ ሣይሆን በሐራጅ መነሻ ዋጋ መሠረት ነው ተብሎ ተጠሪ የሐራጅ መነሻ ዋጋ ግማሹን ለአመልካች እንዲከፍሉ መወሰኑ ባግባቡ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በክርክሩ ሂደት አመልካች ለክርክሩ መነሻ በሆነው ንብረት የመያዣ መብት እንዳለውና በግማሽ የፍርድ ባለመብት መሆኑ፣ ንብረቱ በዓይነት ሊከፋፈል የማይችል መሆኑ እና ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ የተደረገውም የመሐንዲሱን ግምት ግማሽ ዋጋ መሆኑ የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

የአመልካችና የተጠሪ በቤቱ ላይ ያላቸው የጋራ ባለሀብትነት በፍርድ የተቋቋመ ነው፡፡ በሕጉ መሠረት የተፈጠረ የጋራ ባለሀብትነት ደግሞ የሚገዛው አግባብነት ባለው ሕግ ነው፡፡ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1259-1277 ያሉት ድንጋጌዎች የሚያሣዩትም ይህንኑ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1260/1/ ድንጋጌ የሚገልፀው ደግሞ እያንዳንዱ የጋራ ባለሀብት ድርሻውን ለመሸጥ ወይም በሌሎች መንገዶች የማስተላለፈ ወይም ለማስያዝ መብት ያለው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ስልጣኖች ሌሎች የጋራ ባለሃብቶች እየተቃወሙ ቢሆን እንኳን ባለድርሻው የጋራ ባለሃብት የሚተገብራቸው፣ በሕግ የተጠበቁ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1261፣ 1388 እና 1406 ድንጋጌዎች ይዘት ሲታይ የጋራ ባለሀብቶች ያልተከፈለውን የጋራ ንብረት ከማንኛውም 3ኛ ወገን በፊት፣ ሊሸጥ የታሰበውን ድርሻ አስገድዶ ለመግዛት የቅድሚያ መብት ያላቸው መሆኑን ያስረዳል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት እንዲገዙት መወሰናቸው የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በዚህ ረገድ የቀረበ የሰበር አቤቱታም የለም፡፡

ይሁን እንጂ የተጠሪ የቅድሚያ ግዢ መብት ሲጠበቅ የቤቱ ዋጋ በመሐንዲስ ተገምቶ በቀረበው መሆን አለበት ተብሎ የመወሰኑ አግባብነት የቤቱ ትክክለኛ ግምት ተደርጎ ሊወሰድ ከሚገባው ዋጋ መነሻ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡ የመሐንዲሱ ግምት ቤቱን ለመስራት የወጣውን ወጪ /Book value/ ከሚያሣይ በስተቀር የቤቱ የወቅቱ የገበያ ዋጋን /Market value/ በሚያሣይ የተሠላና በዚህ ግንዛቤ የቀረበ አይደለም፡፡ በመሆኑም የመሃንዲስ ግምት የወቅቱን የገበያ ዋጋ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑ ሣይረጋገጥ የቤቱ ትክክለኛ የወቅቱ ግምት ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ አይደለም፡፡ አመልካችና ተጠሪ የቤቱን የወቅቱ የገበያ ዋጋ የተስማሙበትም አይደለም፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1261/2/ ድንጋጌ ሕጋዊ የሆነ የቀዳማይነት መብት በስራ ላይ የሚውልበት አኳኋን የሚመራው በፍትሐብሔር ሕጉ ሦስተኛ መጽሐፍ አንቀጽ 6 ምዕራፍ አራት በተነገረው ድንጋጌ ደንብ መሠረት ስለመሆኑ ያጣቅሣል፡፡ በዚህ ምዕራፍ የተመለከቱት ስለቀዳሚነት ግዢ ይገባኛል የማለት መብት የሚገዙት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1386-1409 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ደግሞ የሽያጩ አኳኋን በሐራጅ ወይም ያለሀራጅ በሻጭና በገዢ ስምምነት ሊደረግ የሚችል መሆኑን ያሣያሉ፡፡ በመሆኑም የጋራ ንብረቱ ዋጋ ስምምነት ሊቆረጥ ካልቻለ የሽያጭ ሂደቱ በሐራጅ ተከናውኖ የንብረቱ የገበያ ዋጋ ይታወቃል፡፡ በዚህ ሂደት የንብረቱ ዋጋ ሲታወቅ የጋራ ባለሃብቱ የቅድሚያ ግዢ መብት ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ከላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መንፈስ የሳገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11851 ኀዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 60273 ጥር 30 ቀን 2000 በትዕዛዝ የፀናው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በነቀምቴ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥር 864 የሆነ የመኖሪያ ቤት ግልጽ ጨረታ ከወጣበት በኋላ ተጠሪ ቤቱ ያወጣውን ከፍተኛ ዋጋ ግማሹን ለአመልካች ገቢ በማድረግ የጋራ ንብረቷን በቅድሚያ የመግዛት መብቷን ትጠቀም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ቤቱ በግልጽ ጨረታ የሚያወጣውን ዋጋ ግማሹን ለአመልካች ገቢ ለማድረግ ካልቻሉ ቤቱ ለጨረታ አሸናፊው ተሽጦ የቤቱን ግማሽ ዋጋ የማግኘት መብት የተጠበቀ ነው ብለናል፡፡ ግማሹን ለአመልካች ይከፈል ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 37298

ታህሳስ 2 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

በላቸው አንሺሶ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ነገረፈጅ አቶ በላይነህ አለማየሁ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ አለምነሽ ዋቅጅራ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ወለጋ ዞን ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 21938 ታህሳስ 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 60274 የካቲት 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሚያዚያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች በነቀምቴ ከተማ ቀበሌ 02 ቁጥሩ 964 የሆነውን የመኖሪያ ቤት በመያዥያነት በመያዝ ብድር ያበደረ ሲሆን ተጠሪ ይኸ ቤት የአቶ ይማሙ ባቲና የእሷ የጋራ ንብረት መሆኑንና የመያዥያ ውሉ እሷ ሣታውቅና ሳትፈቅድ የተፈፀመ በመሆኑ በእሷ ድርሻ ላይ ውጤት እንደሌለው እንዲወሰንላት ክስ አቅርባ አመልካች በመያዥነት የያዘው ቤት የተጠሪ የጋራ ሐብት እንደሆነና የመያዥያ ውሉም የተጠሪን ድርሻ ውጤት የሌለው መሆኑን በፍርድ አስወስናለች አመልካች ቤቱን ለመሸጥ፣የቤቱን ግምት 28,092/ሃያ ስምንት ሺ ዘጠና ሁለት ብር/ መሆኑን በመግለጽ የጨረታ ማስታወቂያ አውጥቷል፡፡ ተጠሪ አመልካች የጋራ ንብረቷን ለመሸጥ ያወጣው ማስታወቂያ በመቃወም የቤቱ ግማሽ ባሐብት መሆኔና መያዥያው የእኔን ድርሻ የማይመለከት መሆኑ በፍርድ የተረጋገጠ ስለሆነ በዚህ መሰረት ይፈፀምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ የቤቱ ግምት ግማሽ ዋጋ ለአመልካች ከፍላ ቤቱን የግሏ ታድርግ በማለት የአፈፃፀም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ አመልካች ይኸ ትእዛዝ በግማሽ የመያዥያ መብት ያለን መሆኑ የተረጋገጠውን ቤት፣በገበያ ዋጋ በመሸጥ በተሻለ ሁኔታ መብታችንን የማስከበርና እዳችንን የመሰብሰብ መብታችን የሚያሳጣና የቤቱን የመሐዲስ ግምት ግማሽ ዋጋ በመክፈል ተጠሪ ቤቱን እንድትረከብ የሚያደርግ፣ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልን በማለት ያመለከተ ሲሆን ተጠሪ በበኩሏ አመልካች የእኔን ድርሻ ጨምሮ ለመሸጥ የሚፈቀድለት ሕግ የለም፡፡ ስለዚህ የስር ፍርድ ቤቶች የቅድሚያ የመግዛት መብቴን በመጠበቅ የሰጡት ትእዛዝ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ሐምሌ 8 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረበችው መልስ ተከራክራለች፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ የክርክሩ መሰረታዊ ጉዳይ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንዳየነው አመልካች ክርክር በተነሳበት ቤት ላይ ከፊል የመያዥያ መብት ያለው መሆኑና ተጠሪዋ በበኩሏ የንብረቱ የጋራ ባለሐብት መሆኗ አያከራክርም፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የጋራ ሐብቷ የሆነውንና በከፊል የአመልካች ባለመብት የሆነበትን ቤት ቅድሚያ የመግዛት መብት ያላት መሆኑ በፍታብሔር ሕግ

ቁጥር 1261/1/ ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ቤቱን የመግዛት መብት አላት በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ትእዛዝ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡

ሆኖም ተጠሪ ቤቱን በቅድሚያ የመግዛት መብቷን ተጠቅማ የምትገዛውና ለአመልካች ገቢ የምታደርገው የቤቱን የመሐድስ ግምት ዋጋ መሰረት ነው ወይስ ቤቱ በገበያ የሚያወጣውን እርግጠኛ ዋጋ የሚለው ነጥብ የስር ፍርድ ቤቶች በትኩረት አላዩትም፡፡ ተጠሪ ቤቱን የመግዛት የቅድሚያ መብት ያላት ቢሆንም ቤቱን የምትገዛው በመሐድስ ግምትና መነሻ ዋጋ ግማሹን በመክፈል ሣይሆን ቤቱ ለግልጽ ጨረታ ቀርቦ ያወጣውን እርግጠኛ ዋጋ ግማሹን በመክፈል ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ በቶች ተጠሪ የቤቱን የመሐዲስ ግምት ግማሽ ዋጋ በመክፈል ቤቱን የግሏ ታድርግ በማለት የሰጡት ትእዛዝ የአመልካችን ንብረቱን በዋጋው የመሸጥ መብት የሚጋፋት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ወለጋ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ትእዛዝ ተሻሽሏል ይፃፍ፡፡
2. በነቀምቴ ከተማ ቀበሌ 02 የሚገኘውና ቁጥሩ 964 የሆነው መኖሪያ ቤት ለግልጽ ጨረታ ከወጣ በኂላ ተጠሪ ቤቱ ያወጣውን ከፍተኛ ዋጋ ግማሹን ለአመልካች ገቢ በማድረግ የጋራ ንብረቷን በቅድሚያ የመግዛት መብቷን ትጠቀም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ቤቱ በግልጽ ጨረታ የሚያወጣውን ዋጋ ግማሹን ለአመልካች ገቢ ማድረግ ካልቻሉ ቤቱ ለጨረታ አሸናፊው ተሸጦ የቤቱ ግማሽ ዋጋ ለተጠሪ ይከፈላት ብለናል፡፡ ግማሹ ለአመልካች ይከፈለው ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚ ችሎት ታህሣስ 2 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 38228

ታህሣሥ 7 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መሰሠ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሐጂ መሐመድ አወል ረጃ - ጠ/ደሣለኝ አለሙ ክብረት

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ዲኖ በሺር
2. ወ/ሮ ዘይቱ አረጋ
} ጠ/ አምሃ ነጋሽ ቀረቡ፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሁከትን ጉዳይ የሚመለከትን ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ከሣሽ ሲሆኑ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሾች ነበሩ፡፡ አመልካች ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በሰበታ ወረዳ ካራብህርቡ ቀበሌ ገ/ማኀበር ውስጥ ሁለገብ የአረብኛ እና የሙያ ማሠልጠኛ ማዕከል አቋቁመው እየሠሩ ባለበት ወቅት ተጠሪዎች ድንበሩን ለመከላከል የተቆፈረው አፈር በመሙላት፣ የጥበቃውን ቤት በማፍረስና የተማሪዎቹን መኖሪያ በቁፋሮ በማናጋት ሁከት እየፈጠሩ በመሆኑ ሁከቱ ተወግዶ በሁከቱ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍሉ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ሁከት ተፈጠረበት የተባለው ቦታ በአመልካች ይዞታ ስር መሆኑና በዚሁ ቦታ ላይ ተጠሪዎች ሁከት መፍጠራቸው በማስረጃ ስለተረጋገጠ ሁከቱ እንዲወገድ፣ በሁከቱ ምክንያት ለደረሰው ተጠሪዎች ብር 4500.00 /አራት ሺህ አምስት መቶ/ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይዞታ የሚረጋገጠው በፍ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት ከሚመለከተው አስተዳደር መ/ቤት በተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወይም ካርታ ነው፣ አመልካች ይዞታው የራሣቸው መሆኑን ለማስረዳት ይህን መሰል የሰነድ ማስረጃ አላቀረቡም፣ ስለሆነም ባለይዞታ መሆናቸውን ሳያስረዱ ተጠሪዎች ሁከት ፈጥረዋል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈጠረበት ነው በማለት ውሣኔውን ሽሯል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የሁከትን ጉዳይ ለመወሰን አመልካች በፍ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት ከአስተዳደር መ/ቤት የተሰጠ የባለይዞታነት ማረጋገጫ መቅረብ አለበት በማለት የሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ተጠሪዎችም ለቀረበው የሰበር አቤቱታ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ በይዞታቸው ላይ ተጠሪዎች ሁከት እየፈጠሩ በመሆኑ ሁከቱ ተወግዶ በሁከቱ ምክንያት ለደሰረሰው ጉዳት ኪሣራውን ተጠሪዎች እንዲከፍሉ ነው፡፡ በይዞታው የተወሰደበት ወይም በይዞታው ላይ ሁከት የተነሣበት ሰው የተወሰደበት ነገር እንዲመለስለት ወይም የተነሣው ሁከት እንዲወገድለት እንዲሁም ስለደረሰበት ጉዳት ኪሣራ እንዲሰጠው መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 1149/1/ ሥር

ተመልክቷል፡፡ ይዞታ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በፍ/ሕ/ቁ. 1140 ሥር ትርጓሜ ተሰጥቶታል፡፡ ይዞታ ማለት አንድ ሰው አንድን ነገር በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው ባለይዞታ ነው ለማለት በግድ በይዞታው ላይ ባለሃብት መሆን እንደሌለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህም ምክንያት አንድን ነገር በእጁ አድርጎ በእውነት ያዝበት የነበረ መሆኑን ካስረዳ ባለይዞታ መሆኑ ይረጋገጣል ወደ ፍ/ሕ/ቁ. 1195 ስንመለስ ግን ይህ ድንጋጌ የሚገናረው ስለባለሃብትነት /ownership/ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው የማይንቀሣቀስ ንብርት ባለሀብት መሆኑ ከሚመለከተው አስተዳደር ክፍል የሚሰጠውን የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት በማቅረብ ማስረዳት ይችላል፡፡ በእርግጥ መሬት የማይንቀሳቀስ ንብረት ቢሆንም የመሬት ባለሀብት መሆን ባይችልም የመሬቱ የይዞታ ባለሀብት መሆኑን በማረጋገጥ ግን ተመሣሣይ ማስረጃ ማቅረብ ይገባል፡፡ በመሆኑም በፍ/ሕ/ቁ. 1140 እና 1195 መሃከል የሰፋ ልዩነት አለ፡፡ የመጀመሪያው አንድን ነገር ይዞ መገልገል ባለይዞታ የሚያደርግ መሆኑን የሚልጽ ሲሆን ሁለተኛው ግን አንድን ነገር ይዞ መገልገልን ብቻ ሣይሆን ከዛ ባለፈ የዚሁ ነገር ባለቤት መሆንን ለማረጋገጥ የሚያገለግል ድንጋጌው ነው፡፡ ስለሆነም የሁከትን ክስ ለማቅረብ ከሣሽ ማስረዳት ያለበት ሁከት ተፈጠረ የተባለበትን ነገር በእጁ አድርጎ በውነት ያዝበት የነበረ መሆኑን ብቻ እንጂ የዚሁ ነገር ባለሃብት መሆኑን አይደለም፡፡ ስለሆነም የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት አመልካች ባቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ ክስ የፍ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት አድርጎ መወሰኑ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች ሁከት ተፈጠረ የተባለበትን በእጃቸው አድርገው ያዙበት የነበረ ለመሆኑ እና ተጠሪዎችም ሁከት የፈጠሩ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት አይቻልም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58254 በ16/04/2000 የሰጠው ውሣኔ እና በፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35850 በ12/07/2000 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19195 በ04/11/99 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪዎች በአመልካች ቦታ ላይ የፈጠሩት ሁከት ሊወገድ ይገባል፡፡ በሁከቱ ምክንያት በደረሰው ጉዳትም ብር 4500.00 /አራት ሺህ አምስት መቶ ብር/ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 36638

ታህሳስ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** በላይ አበበ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. አበራሽ ዋቅጅራ - ቀረቡ

2. አበበ ኃ/ወልድ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በስር ከሣሽ ተጠሪዎች ደግሞ የስር ተከሣሽ ነበሩ አመልካች ባቀረቡት ክስ አንደኛ ተጠሪ የእንጀራ እናቴ ሁለተኛ ተጠሪ አባቴ ናቸው፡፡ በወረዳ 11 ቀበሌ 15 ክልል በቤት ቁ. 433 ግቢ በራሴ ወጪ ቤት ሰርቼ እንድጠቀም ፈቅደውልኝ 40,000(አርባ ሺ.ህ ብር) አውጥቼ ሰርቼ ይህንንም በህዳር 6 ቀን 1976 በጽሁፍ አረጋግጦልኝ ለ19 ዓመት እየኖርኩበት በሚያዝያ 11 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ መብራትና ውሐ በመቁረጥ ሁከት በመፍጠር ለቅቄ እንድወጣ አድርገውኛል፡፡

ስለዚህ የስራሁትን ቤት እንዲያስረክቡኝ ፍቃደኛ ካለሆኑ ያወጣውትን 40,000 ብር (አርባ ሺ.ህ ብር ) እና የደረሰብኝን ኪሣራ ይከፈለኝ ሲል ጠይቋል፡፡

ፍ/ቤቱም ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ በማዘዝ በመልሳቸውም ተፈረመ የተባለው የስጦታ ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443 መሰረት ያልተፈፀመ ነው ስለዚህ ፈራሽ ነው፡፡ ስጦታ ተቀባዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2436 መሰረት መቀበሉን አላረጋገጠም፣ውል ይፈጸምልኝ ለማለት በ1845 መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው፡፡ የቤቱ መለያ ያልታወቀ ነው፡፡ የመክሰስ መብት የለውም 40,000 ብር (አርባ ሺ.ህ) አውጥቶ አልሰራም በኛ ገንዘብ ነው ቤቱ የተሰራው የውሃና የመብራት አልከፍልም በማለት ነው ሁከት ተፈጠረ የሚለው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አግባብነት ካለው ሕግ በማገናዘብ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1179/1/ መሰረት ባለመሬቱ ሣይቃወም በሌላ ሰው መሬት ሕንፃ የሰራ ሰው የዚሁ ሕንፃ ባለሐብት ነው ይላል፡፡ በዚህም ጉዳይ አመልካች በተጠሪዎች መሬት ቤት ሲሰሩ አልተቃወሙም ይልቁንስ መፍቀዳቸውን በጽሑፍ አረጋግጠዋል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ መታየት ያለበት በስጦታ ውል መስፈርት ሣይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1179/1/ መሰረት ነው ስለሆነም አመልካች በቤቱ ውስጥ ሲኖሩ እንደነበር የተረጋገጠ ስለሆነ አመልካች የቤቱ ባለሐብት ናቸው የተፈጠረው ሁከት ይወገድ አመልካች ወደ ቤቱ ይመለሱ፡፡ ተጠሪዎች ይህን የማይፈልጉ ከሆነ ግምቱን ያልተቃወሙ ስለሆነ 40,000 ብር (አርባ ሺ.ህ ብር) ከፍለው ቤቱን የማስቀረት መብት አላቸው ሲል ውሳኔ፡፡

ይግባኝ ባይም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታቸውን አቅርበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን በማከራከር ካዩ በኋላ የግራ ቀኙ ክርክር የሁከት ይወገድልኝ ጥያቄ ነው አንድ ሁከት ይወገድልኝ የሚል ወገን ሁከት

የተፈጠረበትን ነገር በእጁ አድርጐ በእውነት የሚያዝበት ሆኖ መገኘት እንዳለበት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1140 በግልጽ ተደንግጓል አመልካች ሁከት ተፈጥሮብኛል ሊል የቻለበት በኀዳር 6 ቀን 1976 ዓ.ም የተፃፈ ውል ቤት ሰርቶ እንዲኖር የተሰማሙበትን ነው፡፡ እንደዚህ አይነት የስጦታ ውል ደግሞ በግልጽ በመደረጉ የጉዛዜ ስርአት መደረግ እንዳለበት ሕጉ ያዛል ከዚህ ስርአት ውጪ የሆኑት ስጦታ ፈራሽ ናቸው ሲል የፍ/ሕጉ /ቁ. 2443 ያዛል በመሆኑም የስጦታው ውሉ ፎርማሊትን ያላሟላ ስለሆነ ፈራሽ ነው የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ሽሮታል፡፡

አመልካችም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኙን ቢያቀርብም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ዘግቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም በቀረበው ማመልካቻ በፌደራል ከፍ/ቤት እና በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሲል አመልክቷል፡፡

እኛም በዚሁም መሰረት አቤቱታ የቀረበበትን የስር ውሣኔ እና የአመልካች አቤቱታን አግባብ ካለው ሕግ ለማገናዘብ ተጠሪዎችን በማስጠራት ሰምተናል በመሆኑም ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ የተባለው አመልካች በስጦታ ውል አገኘሁት የሚሉት ቤት ለመስራት ያወጡት ወጪ ሣይከፈላቸው የስር ፍ/ቤቶች የስጦታ ውሉ ፈርሶ አመልካች ቤቱን ያስረክቡ መባሉ በአግባቡ መሆኑን ለመመርመር ነው፡፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የአመልካች ጥያቄ የነበረው በተጠሪዎች ይዞታ ላይ ባገኘው ፍቃድ ቤት ሰርቶ ለ"19" አመት የኖረበት እና ለግንባታውም 40,000 ብር (አርባ ሺህ ብር)እንዳወጣበት እና ተጠሪዎች በ1975 በተፃፈ ጽሁፍ ተስማምተው እንደሰጡት በመጥቀስና ከግዜ በኂላ መብራትና ውሐ አልከፈልክም በማለት ተጠሪዎች ከቤት እንዳስለቀቁት በመጥቀስ ሁከት ተወግዶ ወደ ቤቱ እንዲመለስ ተጠሪ ካለፈቀደ አመልካች ለቤቱ ግንባታ ያወጣውን 40,000 ብር(አርባ ሺህ ብር) እንዲከፍሉት ጠይቋል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም አመልካች በተጠሪዎች ፈቃድ ቤት ገንብተው ለ19 ዓመታት የኖሩበት መሆኑን በመረዳት ጉዳዩ መታየት ያለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1979/1/2/ መሰረት የሚታይ እንጂ በስጦታ ውሉ መሰረት መታየት የለበትም ብሎ ሁከት ይወገድ አመልካች ወደ ቤቱ ይመለስ ተጠሪዎች ካልፈቀዱ ለአመልካች 40,000 ብር(አርባ ሺህ ብር) ይክፈሉ ሲል ሲወስን የከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩ የሚታየው በስጦታው ውል መሰረት ነው በማለት የስር ውሣኔን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ሲሽር የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ዘግቶታል፡፡

በመሰረቱ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ፍ/ቤቱ ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የሕጉን አንቀጽ 1179/1/2/ ነው ይህ አንቀጽ ባለመሬቱ ሣይቃወም በሌላ ሰው መሬት ላይ ህንፃ የሰራ የዚሁ ሕንፃ ባለሐብት ይሆናል በዚህም ጉዳይ አመልካች በቤቱ ውስጥ ለ19 አመት መኖሩ በተጠሪ አልተካደም መብራትና ውሐ ስላልከፈለ ነው የወጣው(የለቀቀው) ሲሉ ተከራክረዋል ይህ ደግሞ ከመጀመሪያውኑ ፍቃድ(ስምምነት) እንደነበረ የሚያመለክት ነው አመልካችም ይህንኑ በግምት በማስገባት ቤቱን ይገነባል ተብሎ ይታመናል በሌላ በኩል ፍ/ቤቱም አመልካች በራሱ ወጪ ቤት ለመስራቱም አረጋግጧል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤትም የስጦታ ውሉን ቢያልፈው (ፈራሽ) ነው ቢል እንኳ አመልካች ያለ ምንም ተቃውሞ ለ19 አመት የኔ ነው በሚል እምነት የኖረበትን እግምት ማስገባት ሲገባው የአመልካች አባት (ወላጅ) ሁለተኛ ተጠሪ አመልካች ቤቱን ሰርቶ መኖር ከጀመረ በኂላ ቤቱን ለልጄ ሰጥቻለሁ ብለው ጽፈው ለሽማግሌዎች ያስፈረሙትን ጽሑፍ መሰረት በማድረግ ሁከት የለም በማለት የስር ውሣኔን መሻሩና የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይህንን ማረም ሲገባው መዝገቡን ጉድለት የለበትም ብሎ መዝጋቱ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገቡ ቁ.44725 በጥር 7 ቀን 2000 ዓ.ም እና በጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35834 በ8/7/2000 የተሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02183 ጥር 4 ቀን 1998 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

3. ተጠሪ አመልካች ወደ ቤቱ እንዲመለሱ ካልፈቀዱ አመልካች ያወጣውን 40,000 (አርባ ሺህ ብር) ይክፈሉ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 36013

ታህሣሥ 21 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዘምዘም ኑሩ - ጠ/በረከት በርሔ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የኢት/ልማት ባንክ - አልቀረቡም፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ያለውን ባለገንዘብ የቀዳሚነት መብት የሚመለከት ነው፡፡

በምዕ/ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ባቀረቡት ክስ፤ በባሕር ዳር ከተማ 04 የቤት ቁጥር 151 የሆነውን ቤት በአፈፃፀም ከሣሽ ባሕር ዳር ልዩ ዞን አገር ውስጥ ገቢ መ/ቤትና በአፈፃፀም ተከሣሽ ሐጂ ኑር ሁሴን ምትኩ መካከል በነበረው የአፈፃፀም ክርክር በወጣው ጨረታ ተሣትፈው በማሸነፍ ቤቱን የገዙ መሆኑን፣ የቤቱን የባለቤትነት ስም በስማቸው ለማዛወር ሲሞክሩ የማዘጋጃ ቤቱ በመያዣነት ተይዟል በማለት የከለከላቸው መሆኑን፣ በዚህ ሂደት ላይ ተጠሪ ቤቱ ያለአግባብ የተሸጠ ስለሆነ ጨረታው ይፍረስ በማለት አመልክቶ ጥያቄው ውድቅ መደረጉን፣ ከዚህ በኋላ የቤቱ ባለቤትነት ስም በስማቸው መዛወሩን በስማቸው ካርታና ፕላን ተሰርቶ የተሰጣቸው መሆኑን፣ ቤቱን በይዞታቸው ሥር አድርገው እየተገለገሉበት እያለ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ ማውጣቱን ገልፀው በንብረታቸው ላይ የፈጠረው ሁከት እንዲወገድላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለቀረበት ክስ በሰጠው መልስም ጉዳዩ በሌላ መዝገብ ክርክር ቀርቦበት ውሣኔ ያገኘ በመሆኑ በድጋሚ ሊታይ አይገባም፣ ተጠሪ ቀደም ሲል በነበረው ክርክር ጣልቃ በመግባት ንብረቱ ላይ ያለው መብት እንዲከበርለት ጠይቆ ፍ/ቤቱ በንብረቱ ላይ ያለውን መያዣ መብት ንብረቱን በመከተል መጠቀም የሚችል መሆኑን በመግለጽ ብይን የሰጠ በመሆኑና ቤቱን ለአቶ ኑር ሁሴን ለሰጠው ብድር በመያዣ የያዘው በመሆኑ የመያዣ መብቱን ንብረቱን ከገዛው ሰው ላይም መጠቀም ይችላል፤ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም አከራካሪ በሆነው ቤት ላይ ተጠሪ የመያዣ መብት ያለው መሆኑን አመልካች አልካዱም በመያዣ የያዘውን ቤት ደግሞ በአ/ቁ. 97/90 መሠረት የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት መሸጥ ይችላል፣ ስለሆነም በጨረታ የያዘውን ንብረት ለመሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ ማውጣቱ ሁከት ፈጥሯል የሚያሰኝ አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኛቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ፤ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠው ተገቢውን ጭብጥ ሣይዝ ነው፣ ተጠሪ ንብረቱን የመከተል መብት የሚኖረው ንብረቱን በዋስትና ካስያዘው ሰው ላይ ገዝቼው ቢሆን ነበር ንብረቱ በሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ከተያዘ በኋላ የተጠሪ መብት ከንብረቱ ሽያጭ ገንዘብ ውስጥ በቅድሚያ ዕዳው እንዲከፈለው መጠየቅ ነው በመያዣ የተያዘው ንብረት በሃራጅ ተሸጦ ገንዘቡ በባለገንዘቦች ከተከፋፈለ

በኋላ የመያዣ መብቱ ቀሪ ይሆናል፣ ተጠሪ ከመንግሥት ግብር በፊት ቅድሚያ መብት የለውም እንጂ አለው ቢባል እንኳን መብት ያለው መሆኑ በማሣወቅ ያቀረበው ጥያቄ የለም፣ በመሆኑም የገዛሁትን ንብረት በሃራጅ በድጋሚ የመሸጥ መብት የለውም የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም አከራካሪው ንብረት በአገር ውስጥ ገቢ ግብር ክፍያ በሃራጅ ከተሸጠ በኋላ በድጋሚ ተጠሪ በሃራጅ ሊሸጠው የሚችል መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ስለተባለ ተጠሪ መልሱን አቅርቧል፡፡

ተጠሪ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ በሰጠው መልስ፣ በአ/ቁ. 97/90 እና 98/90 በተሰጠኝ መብት በመያዣ የያዝኩትን ንብረት ለመሸጥ ማስታወቂያ ማውጣቴ ሁከት አይደለም፣ መያዣው በሕጋዊ መንገድ የተቋቋመና የተመዘገበ በመሆኑ ንብረቱን የመከተል መብት አለኝ፣ ንብረቱ በግብር እዳ ተሸጦ ባለቤትነቱ ለሌላ ሰው የተላለፈ ቢሆን እንኳን ንብረቱን የመከተል መብቴን አያስቀርም፣ ቀደም ሲል በነበረው ክርክር ፍ/ቤቱ ንብረቱን የመከተል መብት ያለኝ መሆኑን አረጋግጧል፣ በመያዣ ውሉ ምክንያት የሆነው እዳ የተሰጠው ለአመልካች አባት ነው ቤቱን ሲገዙ እዳ ያለበት መሆኑን ያውቃሉ፤ በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንዲፀና ጠይቋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ችሎቱ ኅዳር 2/2001 በነበረው ችሎት የግራ ቀኙን የቃል ክርክር አድምጧል፡፡ ከላይ የተመለከተው የግራ ቀኙ ክርክርና የፍ/ቤቶች ውሣኔ ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ መርምሯል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው በዚህ መዝገብ መሠረታዊ የሆነው ጭብጥ ተጠሪ በመያዣነት የያዘው ንብረት በሌላ ገንዘብ ጠያቂ ዕዳ ምክንያት በሃራጅ ከተሸጠ በኋላ የተጠሪ መብት ምንድነው? የሚለው ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ጭብጥ አግባብነት ካላቸው የፍ/ብ/ሕጉ ስለማይንቀሳቀስ ንብረት መያዝ ከተደነገጉት ሕጎች አንፃር መመርመሩ ተገቢ ይሆናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በሐጅ ኑር ሁሴን ምትኩ እና በባሕር ዳር ከተማ ልዩ ዞን አገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት በሃከል በነበረው የአፈፃፀም ክርክር ንብረቱ ከመሸጡ በፊት ተጠሪ ለሐጂ ኑር ሁሴን ምትኩ ለሰጠው ብድር በመያዣ የተሰጠው መሆኑን ተረድተናል፡፡ አንድ ባለገንዘብ በአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በሕጉ መሠረት የተቋቋመ የመያዣ ውል ካለው ውሉ ሁለት ዓይነት መሠረታዊ መብቶችን ያጎናጽፈዋል፡፡ እነዚህም መብቶች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/ እና /2/ ሥር የተመለከቱት ናቸው፡፡ ለውሣኔ ያመች ዘንድ ሕጎቹን በዝርዝር ማስቀመጡ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059

1. "የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ መብት የተሰጠው ገንዘብ ጠያቂ መያዣው የሚመለከተውን የማይንቀሳቀስ መብት፣ ገንዘብ ጠያቂዎች ያስያዙት እንደሆን ከንብረቱ ዋጋ ላይ የሚጠይቀው ገንዘብ ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች በፊት በርሱ በቀዳሚነት እንዲከፈለው መብት አለው"
2. "እንዲሁም የመጀመሪያው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ መብት ከተመዘገበ በኋላ፣ መብቱን ባስመዘገበ በሌላ 3ኛ ወገን ባለዕዳው የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ቢሸጥ ቢያስተላልፍም እንኳን የመያዣ መብቱን ያስመዘገበው ገንዘብ ጠያቂ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ለማስያዝ ይችላል፡፡"

ከእነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች እንደምንረዳው የመያዣ መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣው የሚመለከተው ንብረት በሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ተይዞ ሲሸጥ ከሽያጩ ገንዘብ ላይ በቅድሚያ ገንዘቡን የማግኘት መብት /right of Preference/ እና ንብረት አስይዞ ንብረቱን ለሌሎች 3ኛ ወገኖች ካስተላለፈ መያዣ የተሰጠበትን ንብረት ከማናቸውም 3ኛ ወገኖች ተከትሎ የማስያዝ /right of persuit/ ይኖረዋል፡፡ የመያዣ መብት ያለው ሰው እነዚህ ሁለት መብቶች አሉት ከተባለ መብቶቹን እንዴት ነው የሚገለገልባቸው የሚለውን መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በመጀመሪያ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/2/ ላይ ያለውን መብት እንመልከት፡፡ መያዣ የተሰጠው ባለገንዘብ ባለዕዳው ግዴታውን መፈፀም ሲያቅተው የግዴታውን አፈፃፀም ለማረጋገጥ የሚወስደው እርምጃ ነው፡፡ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ በመሠጠቱ ብቻ ንብረት አስያዡ በንብረቱ ላይ ያለው መብት ቀሪ ይሆንበታል ማለት አይደለም፡፡ በንብረቱ ላይ መያዣ የሰጠ ሰው ይህንኑ ንብረት ለመሸጥ፣ ለመለወጥ መብት ያለው ሲሆን ይህንን በሚቃረን መልኩ ማንኛውንም ስምምነት ማድረግ እንደማይቻል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3084/1/ እና /2/ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን አንድ ንብረት በመያዣ የተሰጠ ቢሆንም አስያዡ ንብረቱን ለሌላ ሰው ለመሸጥ ለመለወጥ ወይም በስጦታ ለማስተላለፍ ይችላል፡፡ ዋናው ባለዕዳም ግዴታውን መፈፀም እስከቻለ

ድረስ ባለገንዘቡ መያዣ በተሰጠው ንብረት ላይ መብት አይኖረውም፡፡ ነገር ግን ባለዕዳው ግዴታውን መፈፀም ሲያቅተው ንብረቱ ለሎች 3ኛ ወገኖች ተላልፎ እንኳን ቢሆን በማስያዝ የመሸጥ መብት አለው፡፡ ይህ ንብረቱን የመከተል መብት ተፈፃሚም የሚሆነው ንብረቱ ለሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ጥያቄ መሠረት ከመያዙ በፊት ነው፡፡

ንብረቱ በሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ከተያዘ በኋላስ መያዣ የተሰጠው ባለገንዘብ መብት ምንድነው ይህ ጥያቄ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/ ሥር ወደተመለከተው የቀዳሚነት መብት ይወስደናል፡፡ የቀዳሚነት መብት /right of preference/ የሚነሣው በመያዣ የተያዘው ንብረት በሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች እዳ ተይዞ ንብረቱ በሃራጅ ከተሸጠ በኋላ የሚገኘው ገንዘብ በሁላችንም ገንዘብ ጠያቂዎች ዕዳ ለመሸፈን የማይበቃ ሲሆን ነው፡፡ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ የተሰጠ ቢሆንም መያዣ በሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ዕዳም ተይዞ ሊሸጥ እንደሚችል ድንጋጌው ራሱ የሚናገር ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1988/1/ ሥር በባለዕዳው ግዴታ አፈፃፀም በሕግ ሊያዙ አይገባውም ተብሎ ክልከላ ካልተደረገባቸው ንብረቶች በቀር ሌሎች የባለዕዳው ንብረቶች ሁሉ ሊያዙ መሆኑ መደንገጉ በፍ/ሕ/ጠ 3059/1/ ሥር የተቀመጠውን ሃሣብ የሚያጠናክር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከአንድ ለበለጠ ዕዳ በመያዣ ሊሠጥ የሚችል መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3088/1/ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በባለዕዳው ላይ መያዣ ያላቸውም ሆነ የሌላቸው ባለገንዘቦች በመያዣ የተያዘውን ንብረት በማስያዝ ለማሸጥ መብት አላቸው፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ መያዣ ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች የመያዣ መብታቸውን ባስመዘገቡበት ቅደም ተከተል ከሽያጩ ገንዘብ ላይ በቅድሚያ ገንዘባቸውን የማግኘት መብት ያላቸው በመሆኑ ንብረቱ በማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ተይዞ ከተሸጠ በኋላ የመያዣ መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ የሚኖረው ብቸኛ መብት ከሽያጩ ገንዘብ ላይ በቅድሚያ ዕዳቸውን መሰብሰብ ነው፡፡ ከዚህ በቀር ንብረቱ ተይዞ ከተሸጠና ከሽያጩ ገንዘብ በቅድሚያ እንዲከፈለው ሣይጠይቅ ቀርቶ ገንዘቡ በሌሎች ባለገንዘቦች መሃከል ከተከፋፈለ በኋላ ንብረቱን የመከተል መብት አለኝ በማለት የሚያነሣው መብት የለም፡፡ ምክንያቱም በመያዣ የተያዘው ንብረት በሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ዕዳ ምክንያት ተይዞና በሐራጅ ተሸጦ ዋጋው ለባለመብቶቹ ከተከፋፈለ በኋላ መያዣው ቀሪ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3110/ሐ/ መገንዘብ ይቻላል፡፡ መያዣው ቀሪ ከሆነ ደግሞ መያዣውን መሠረት በማድረግ የሚያነሣው የመብት ጥያቄ አይኖርም ማለት ነው፡፡ ስለሆነም በንብረቱ ላይ የመያዣ መብት ያለው ባለገንዘብ ንብረቱን የመከተል መብት የሚኖረው ንብረቱ በማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ዕዳ ከመያዙና ከመሸጡ በፊት ነው፡፡

የተያዘውን ጉዳይ ከፍ ሲል ከተዘረዘሩት የሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ ስንመረምርም ተጠሪ ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት በመያዣ የያዘው መሆኑ አላከራከም፡፡ ነገር ግን የዚሁ ቤት ባለቤት በባሕር ዳር ልዩ ዞን አገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ላይ ባለባቸው የግብር ዕዳ ምክንያት ቤቱ ተይዞ በፍ/ቤት በኩል በሐራጅ በአሁኑ አመልካች ተሽጧል፡፡ ቤቱ ከተሸጠ በኋላ ተጠሪ በንብረቱ ላይ የመያዣ መብት ያለው መሆኑን በመግለጽ ሽያጩን ተቃውሟል፡፡ ፍ/ቤቱም ተጠሪ በቤቱ ላይ ባለው የመያዣ መብት መሠረት ንብረቱን ከሚከተል በቀር ሽያጩን ሊቃወም እንደማይችል ገልፆ ጥያቄውን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ በእርግጥ በመያዣ የተያዘ ንብረት በሌላ በማንኛውም ባለገንዘብ ዕዳ ተይዞ ሊሸጥ የሚችል በመሆኑ ፍ/ቤቱ ተጠሪ ሽያጩን በመቃወም ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ አግባብ ነበር፡፡ ሆኖም ንብረቱ በሌላ ሰው ዕዳ ተይዞ በሐራጅ ሲሸጥ ተጠሪ የሚኖረው መብት ከሽያጩ ገንዘብ በቅድሚያ እንዲከፈለው መጠየቅ እንጂ ንብረቱን የመከተል መብት እንዳልሆነ ከላይ ከተመለከትናቸው የመያዣ ሕግ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ንብረቱ በአገር ውስጥ ገቢ እዳ በሐራጅ ሲሸጥ ሽያጩን መቃወም ሣይሆን ከሽያጩ ገንዘብ ቅድሚያ እንዲከፈለው ሊጠይቅ ይገባ ነበር፡፡ ፍ/ቤቱም ንብረቱን የመከተል መብቱን ጠብቆ ሲያሰናብተው በዚሁ ላይ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኙን አቅርቦ የቀዳሚነት መብቱ እንዲጠበቅለት ማድረግ ሲገባው ይህንን አላደረገም፡፡ በመሆኑም በክርክር ላይ ያለው ንብረት በባህር ዳር ልዩ ዞን አገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ዕዳ ተይዞ በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡ ለባለገንዘብ ከተከፈለ በኋላ ተጠሪ ንብረቱን የመከተል መብት ስላለኝ በሃራጅ ሽያጩ ላይ ተወደደረው ከገዙት የአሁኗ አመልካች ላይ ይገፔ መሸጥ እችላለሁ በማለት ያቀረበው ክርክርና ፍ/ቤቶችም ይህንኑ ክርክር ተቀብለው የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የምዕ/ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 17072 በ30/01/2000 የሰጠው ውሣኔ እና የአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14659 በ19/05/2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. በባሕር ዳር ከተማ ቀበሌ 04 የቤት ቁጥር ዲ 151 የሆነውን ቤት በባሕር ዳር ልዩ ዞን አገር ውስጥ ገቢ እዳ ምክንያት ተይዞ በሐራጅ የተሸጠ ስለሆነ ንብረቱን የመከተል መብት ስለሌለው ንብረቱን በጨረታ ለመሸጥ አይችልም ሁከቱ ይወገድ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 39940

ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ነጂባ ነጋሽ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ዚያዳ ጼታሞ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ሁከት ይወገድልኝን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኗ ተጠሪ ነሐሴ 15 ቀን 1998 ዓ.ም. በፃፉት ማመልከቻ ሟች አቶ አብዶ ናስር ሼህ ጀቤር ከተባሉት ባለቤታቸው ጋር በአዲስ አበባ ከተማ አራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11/12 የቤት ቁጥር 1638 የሆነውን ከመንግሥት ተከራይተው ሲኖሩ እንደነበር፣ ተጠሪ ያላግባብ የቤቱን ኪራይ ቀበሌው በስማቸው አድርጎላቸው ቤቱን መያዛቸውን በመዘርዘር ተጠሪ የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድ ይወስንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኗ አመልካችም የቤቱ ኪራይ በስማቸው የዞረላቸው የሟቹ ሚስት በመሆናቸው መሆኑን፣ ተጠሪ በወቅቱ በቤቱ ያልነበሩ መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የቀበሌው አስተዳደር ተጠሪ በቤቱ ላይ ከአመልካች ጋር እኩል መብት ያላቸው መሆኑን እያወቀ ተጠሪን በማስታወቂያ ሣይጠራና የቤት ኪራይ ስም ዝውውሩን መፈፀሙና ከአመልካች ኪራይ መቀበሉ በተጠሪ ላይ ሁከት መፍጠር ነው በማለት አመልካችና ተጠሪ በቤቱ ላይ በጋራ እንዲገለገሉበትና በጋራ ኪራይ እንዲከፍሉ እንዲደረግ ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የከተማው ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ የከተማው የሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተገኘም ሲል የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 09 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት 2 /ሁለት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የተጠሪ የሁከት ይወገድልኝ ጥያቄ በጊዜ ያልቀረበና የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1149 ድንጋጌን ያላገናዘበ ሆኖ እያለ በተከራይነት ባገኘሁት የይዞታ መብትን እንዳካፍል መወሰኑ ሕጋዊነት የሌለው በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ኀዳር 03 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የአመልካችን ቅሬታ ለመንቀፍ፣ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ተገቢነት በመዘርዘር ውሣኔው ሊፀና ይገባል ሲሉ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ሁከት ፈጥረዋል መባሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የቀበሌው አስተዳደር የሚያስተዳድረው የመንግሥት ንብረት መሆኑን፣ ቤቱን ሟቹ ተከራይተውት ይኖሩበት እንደነበር፣ ከሟች ሕይወት ማለፍ በኋላ በወቅቱ ይዘውት በነበረው የሚስትነት ማስረጃ መሠረት አመልካች የቤቱን የተከራይነት መብት ቀበሌው ያስተላለፈላቸው መሆኑን፣ በዚህ ጊዜ ተጠሪ ከቤት ያልነበሩና ሕጋዊ ጠባቂም ያልነበራቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው ይዞታው ለመንጠቅ ወይም በይዞታው ላይ ሁከት ለመፍጠር የሚፈፀምን ማንኛውንም ድርጊት እንዲቆም ወይም ተገቢው መብት እንዲመለስለት ሕጉ ከዘረጋላቸው መንገዶች አንዱ የይዞታ ክስ /Possessory action/ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1149/1/ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ንብረት ላይ በቀጥታ ወይም በጠባቂ ይዞታ ሲኖረውና ይህንኑ ሁኔታ በኃይል ሲነጠቅ ነው፡፡ እንዲሁም የይዞታ ክስ የሚቀርበው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት በወቅቱ ለመያዝ ምንም ዓይነት መብት የሌለው ሰው ሲይዝ ስለመሆኑም ተጠቃሹ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ በመሆኑም የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ አቅራቢ ማረጋገጥ ያለበት ንብረቱ በሕግ አግባብ በይዞታው የነበረና የሁከት ድርጊት ፈፃሚው የኃይል ተግባር በመጠቀም ወይም በሚስጢር ንብረቱን የወሰደበት መሆኑን ነው፡፡ ይህ የድንጋጌው መንፈስ የሚያስረዳው የሁከት ተግባር የሚኖረው ባለይዞታ የሆነው ሰው በይዞታው ሥር በሚገኘው ንብረት እንዳይገለገልበት ሌላ ሰው ጣልቃ ገብቶበት መሰናክል ሲፈጥርበት ወይም ረብሻ ሲፈጥርበት መሆኑን ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1140 እና 1149 ድንጋጌዎች ይዘት የሚያሣዩትም ይህንኑ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ከላይ ከተገለፀው ነጥብ በተጨማሪ የሚያስገነዝቡት ነጥብ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅራቢ የተሻለ የይዞታ መብት ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጥ ያለበት መሆኑን ነው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በቤቱ ላይ ከአመልካች የተሻለ መብት የሌላቸው መሆኑ፣ አመልካች ቤቱን የያዙት በቀበሌው ስምምነት የተከራይነት መብት አግኝተው እንጂ በኃይል አለመሆኑ የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እንዲህ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1140 እና 1149 ድንጋጌዎች የተመለከቱት ሕጋዊ መሥፈርቶች አለመሟላታቸውን በቀላሉ ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡ በመሆኑም የአመልካች ተግባር ሁከት ሊባል የሚችልበትን ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. አራ-03095 ጥቅምት 27 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ፣ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05585 መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የዚሁ ፍ/ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት በመ/ቁ. 06753 ሐምሌ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2/ አመልካች በተጠሪ ላይ የፈጠሩት ሁከት የለም ብለናል፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በጋራ የሚገለገሉበት ወይም እኩል ተካፍለው የሚከራዩበት ሕጋዊ ምክንያትም የለም ብለናል፡፡

3/ ለክርክሩ የተደረገውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 38169

ግንቦት 12 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ.ፈ. ሂሩት አስራት

**ተጠሪ፡-** የወ/ሮ ንጋቷ ዘለቀ ወራሽ አቶ እሸቱ ቦጋለ - ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የሥር ከሣሽ ተጠሪ የሥር ተከሣሽ ነበሩ አመልካች ባቀረቡት ክስ በወረዳ 17 ቀበሌ 24 ቁጥር 360 የሆነውን ቤት ወ/ሮ ንጋቷ ዘለቀ ከ1973 ጀምሮ በመያዝ ክራይ ሣይከፍሉና የኪራይ ውል ሣይሞሉ እስከ የካቲት 1990 ድረስ ሲገለገልበት ከቆየ በኋላ ከዚህ አለም በሞት በመለየታቸው የተጠሪ ወራሽ የሚች ወራሽነኝ በማለት ቤቱን በመያዝ ክራይ ሣይከፍሉ ይገለገሉበታል የሥር ሁለተኛ ተከሣሽም የሚች ዘመድነኝ በማለት ቤቱን እየተገለገሉበት ስለሆነ ሁለቱም ተከሣሽ ኪራይ ሣይከፍሉ ከውል ውጭ በሕገ ወጥ መንገድ ቤቱን በመያዛቸው አመልካች አከራይቶ ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም አጥቷል፡፡ ስለዚህ ያለ አግባብ የበለፀጉበትን እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 1994 የቤቱን ኪራይ በወር 54 እያከራየ ሊያገኝ የሚገባውን ብር 14,193.76(አስራ አራት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ሦስት ብር ከሰባ ስድስት ሣንቲም) ከወለድ ጋር 150,628.55 በአጠቃላይ(አንድ መቶ ሃምሣ ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ስምንት ብር ከሃምሣ አምስት ሣንቲም) ብር 164,817.41 (አንድ መቶ ስልሳ አራት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሰባት ብር ከአርባ አንድ ምንቲም) በአንድነትና በነጠላ ከፍለው ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ሲል ጠይቋል፡፡

(ተጠሪ) ተከሣሽ ለቀረበበት ክስ መልሱን ሲሰጥ አመልካች የጠቀሰው የኪራይ ግምት የተጋነነ ነው፡፡ አመልካች በቤቱ ላይ ያለውን መብትና ጥቅም ባለማረጋገጡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2)(3) መሠረት ክስ ማቅረብ አይችልም ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለውም፡፡ በይርጋ ይታገዳል ካሉ በኋላ በአማራጭም መልሳቸውን ሲሰጡ አውራሻችን ወ/ሮ ንጋቷ እና እኔ በአንድነት ስንኖርበት ቆይተናል ቤቱ የተሰጠን በቀድሞ የደርግ መንግሥት የከተማ ልማት ቤት ምንስተር ትዕዛዝ መሠረት የቤተ መንግሥት አካባቢ በራሳችን ወጪ ሠርተን ስንጠቀምበት ለነበረው ቤታችን በልዋጭነት ነው፡፡ አመልካች በራሱ ተምኖ ያቀረበው ገንዘብ መጠን ሕጋዊ አይደለም ስለዚህ አመልካች ያቀረበው ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባዋል ሲል መልሱን ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የቀረበውን ክስ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ ውሣኔ ሰጥቷል በውሣኔውም የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ውስጥ በፍ/ሥ/ሥ/ቁ 33(2)(3) መሠረት አመልካች መብትና ጥቅም ስለሌለው ሊከሰን አይገባም ያሉትን ነጥብ ብቻ መርምረዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪ ቤቱን ያስረክቡኝ የሚል ነው ይሁን እንጂ አመልካች ለተጠሪም ሆነ ለሌላ ሰው እያከራየ የሚያስተዳድር መሆኑን ወይም ቤቱ መወረሱን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም በቤቱ ላይ አለኝ የሚለውን መብት ወይም ጥቅም ምን እንደሆነ አላረጋገጠም ስለዚህ መቃወሚያውን በመቀበል ክሱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33(2)(3) መሠረት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር አመልካች ይህን ቤት በሥሩ ይዞ የሚያስተዳድረው የገነባው ወይንም በመንግሥት የተወረሰ ለመሆኑ አላስረዳም በተጨማሪም የቀረበው ማስረጃም ቤቱን እንዲያስተዳድር መብት ሊሰጡ የሚችሉ አይደሉም ከቤተ መንግሥት ተፅፏል የተባለው ደብዳቤም ቢሆን ቤቱ የቤተ መንግሥት መሆኑን አያረጋግጥም። ስለዚህ አመልካች ክስ በቀረበበት ቤት ላይ መብት የለውም ሲል የሥር ውሣኔን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348(1) አፅንቷል።

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው።

አመልካች በ29/9/2000 ፅፎ ባቀረበው ማመልከቻ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው። ሲል እንዲታረምለት ጠይቋል። ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪውን አስቀርቦ ክርክራቸውን ሰምቷል። ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች መብት ወይም ጥቅም የለውም በማለት የተሰጠውን ውሣኔ ለመመርመር ነው።

በዚህም መሠረት ይህንን ነጥብ ግራቀኙ ካቀረቡት ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

እና የክርክሩን አመጣጥ ባጭሩ ስናይ አመልካች ለክርክሩ መንስኤ የሆነውን ቤት ተጠሪ ወራሽ ነኝ በማለት ብቻ መብት ሣይኖራቸው ክራይ ሣይከፍሉ በሕገ ወጥ መንገድ እየተገለገሉበት ነው በማለት ውዝፍ ኪራይ ከፍለው ቤቱን እንዲለቁ በመጠየቁና ተጠሪም በበኩሉ ቤቱ የአመልካች እንዳልሆነና ቤቱን በደርግ ትዕዛዝ የከተማ ልማት በራሱ ወጪ ለሰራሁበት ቤት በልዋጭ ያገኘሁት ነው። ሊከሰኝ አይችልም ሲል በመከራከሩ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም እንዳለው አላስረዳም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል።

እኛም አመልካች በተጠቀሰው ቤት ላይ ክስ የማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የለህም የተባለው አስመልክቶ በመዝገቡ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ፅሑፍ (ደብዳቤ) ሆነ የግራ ቀኙ በሰበር ችሎት ያካሄዱትን የቃል ክርክር በጥልቀት እንደመረመርነው የተጠሪ አውራሽ (ሟች) የቤተ መንግሥት አገልጋይ የነበሩና የቤተ መንግሥት አስተዳደር በሰጣቸው ቤት ውስጥ ሲኖሩ የነበረ በመሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር ለመረዳት ተችሏል። በመሆኑም ይህ ክርክር የተነሳበት ቤት በጉርናፍ ምክንያት በመፍረሱ ለቤተ መንግሥት አስተዳደር ቤቱን በጊዜያዊነት የተጠሪ አውራሽ በሕይወት እስካሉ እንዲገለገሉበት የተፈቀደላቸው እንጂ በልዋጭ የተሰጣቸው እንዳልሆነ  ፍ/ቤቱ ተረድቷል ቤቱም በወቅቱ በነበረው የከተማ ልማትና የቤት ሚንስተር ትዕዛዝ ነው እንዲኖሩበት የተደረገው ይህ ማለት ደግሞ ቤቱ የመንግሥት መሆኑን ያስረዳል። ቤቱ የመንግሥት ከሆነ ስለ ቤቱ የመከራከር መብቱ መንግሥትን የወከለው ተቋም ነው እሱም አመልካች (የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ) ነው ወደሚለው ድምዳሜ ያደርሰናል።

ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ሳያገናዝቡ አመልካች ለመክሰስ መብት ወይም ጥቅም የለውም ሲሉ የሰጡት ውሣኔ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.33(2) መንፈስ ውጪ በመሆኑ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም።

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 21285 በቀን 20/1/98 እና የፌ.ከ/ፍ/ቤት በመቁ 43105 መጋቢት 2/2000 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል።
2. አመልካች የመክሰስ መብት አለው ብለናል።
3. የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍሬ ነገሩ ላይ በማከራከር ሕጋዊ ውሣኔ ይስጥበት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሠረት መዝገቡን መልሰናል።
4. የወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 39539

ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ ስአማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የአዲስ አበባ አስተዳደር ግብርና ቢሮ - ነ/ፈጁ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** እነ አቶ አበበ ዓባይ ዘጠኝ ሰዎች - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ሁከት ይወገድልንን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪዎች በቂሌንጦ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ክልል ከ26 ዓመታት በላይ ግብር እየገበሩ በቦታው ከ6000(ስድስት ሺህ) ዛፎች በላይ ተክለው ከብቶቻቸውንም የሚያቆሙበትን ቦታ የአሁኑ አመልካችና ሦስት ሰራተኞቹ በኃይል ያስለቀቋቸውና ሁከት የፈጠሩባቸው መሆኑን ገልጸው ሁከቱ ተወግዶ ይዞታቸው እንዲመለስላቸው ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካችና ሰራተኞቹ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ መሬቱ የመንግስት እንጅ የተጠሪዎች አለመሆኑን፣ቦታው ለምለም ቦታ የተከለለ መሆኑን ገልፆ የተጠሪዎች ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረና ተጨማሪ ማስረጃም ተገቢ ነው ካለው አካል ከጠየቀ በኋላ ቦታው ለደን ቦታ ተብሎ የተተከለ ቢሆንም ባለይዞታነቱ ግን የተጠሪዎች መሆኑ መረጋገጡ፣ የደን ክልልም በመንግስት ብቻ የሚከለል ሣይሆን በቀበሌ ማህበረሰብና በግለሰብ ሊከናወን እንደሚችል ከደን አዋጅ መረዳት የሚቻል መሆኑን በምክንያትነት ይዞ አመልካች ከሰራተኞቹ ጋር ሁኖ የፈጠረው ሁከት አለ በማለት ሁከቱ እንዲወገድ፣በቁጥር ብር 1000.00(አንድ ሺህ) ለተጠሪዎች እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርቦ ይኸው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ ከዚህ በኋላም አመልካች ለዚሁ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታው አቅርቦ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፈጅ ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 4/አራት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪዎች ለክርክሩ መነሻ በሆነው ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ያላቀረቡ መሆኑን፣ቦታው የመንግስት ስለመሆኑ ሕገ-መንግስቱና አግባብነት ያላቸው አዋጆች እየደነገጉ ከእነዚህ ህግ ጋር አኳያ ጉዳዩ አለመታየቱን፣ደን በቦታው ላይ ለማልማት ስልጣንና ኃላፊነቱ የተሰጠው ለአመልካች ሆኖ በአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ላይ በጸደቀው መሰረት የደን ልማት ስራ ማከናወን የሚችል መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ አለመግባቱን ዘርዝሮ ሁከት ይወገድ ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪዎች እንዲቀርቡ ተደርጐ መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ 4/አራት/ ገጽ ማመልከቻ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ቅሬታ ነጥቦች እውነት የሌላቸው፣የፈራጅን ህሊና ሊያሣምን በሚችል መልኩ ተቀነባብረው መቅረባቸውን፣ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቦታ ከ35 ዓመታት በላይ ይዘው የሚጠቀሙት ስለመሆኑና የአመልካች እርምጃ ከሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 40/4/ ስር ጥበቃ ከተደረገው መብት ጋር ተቃራኒ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ የሕግ ስህተት የለውም ተብሎ ሊፀና

ይገባል በማለት ተከራክረዋል። የአመልካች ነ/ፈጅም ሚያዝያ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት 2/ሁለት/ ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረውም አመልካች ሁከት ፈጥሯል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቦታ ተጠሪዎች ለበርካታ ዓመታት በይዞታችን ስር አድርገን እየተጠቀምንበት የሚገኝ ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን፣ፍ/ቤቱ ባደረገው ማጣራትም መሬቱ ለተጠሪዎች በ1991 ዓ.ም ለግጦሽ መሬት ተብሎ የተሰጠ መሆኑን ቀበሌው ያረጋገጠው መሆኑን፣በ1991 ዓ.ም ቦታው የደን ቦታ ተብሎ የተከለለ መሆኑን የስር ፍ/ቤት አረጋግጦ የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው ደን በመንግስት ብቻ የሚከለል አይደለም በማለት ስለመሆኑ ነው።

በመሰረቱ የአመልካች ክርክር ዋቢ ያደረገው የአዲስ አበባ ከተማ መሪ ፕላን ማጽደቂና የአፈፃፀም አዋጅ ቁጥር 7/1986 "ን" ነው። ይህ አዋጅ በአንቀጽ 2/5/ ስር የመሪ ፕላን ትርጉምንና የሚያዛቸውን ካርታዎች ዓይነት አስቀምጧል። ለዚህ ክርክር አግባብነት ያለው የካርታ ዓይነትም የለምለም ክልል ካርታ ሲሆን አዋጁ በአንቀጽ 2/5/ሸ/ ስር የተደነገገው ነው። የአዋጁ አንቀጽ 21 ስለለምለም ክልል ካርታ ይዘት፣አንቀጽ 22 የለምለም ክልል ማለት ጥበቃና እንክብካቤ፣አንቀጽ 23 ደግሞ የዛፎችና እጽዋቶች ልማትና እንክብካቤ ከደነገጉ በኂላ በአንቀጽ 24 የክልል መስተደደሩ በለምለም ክልል ካርታው ላይ የተመለከቱትን ክልሎች የመጠበቅ፣ የመንከባከብ፣ ወይም እንዲጠበቁ የማድረግ፣ እንዲለሙ የታቀዱትን የለምለም ክልሎች ስለሚለሙበት፣ ስለሚጠበቁት ሁኔታ አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ ተመልክቷል። አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቦታ ለደን የተከለለ ስለመሆኑ ማረጋገጡን፣ሰራተኞች ጉድጓድ አስቆፍረው በቦታው ላይ ችግኝ ያስተከሉትም ከቢሮው በተሰጠው መመሪያ ስለመሆኑ አረጋግጧል። በመሆኑም አዋጁ አመልካች ተግባርና ኃላፊነት ያለው ስለመሆኑ ያሣያል።

ተጠሪዎች ላቀረቡት ክርክር የማስረዳት ብቃት ያለው ማስረጃ ያላቀረቡ ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ያሣያል። ፍ/ቤቱ ተጠሪዎች ያቀረቡት ማስረጃ የማስረዳት ብቃት የሌለው መሆኑን አምኖም ተገቢ ነው ካለው አካል ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያቀርብ አድርጓል። ይሁን እንጂ ተጠሪዎች ቦታው ላይ የተደረገውን የአመልካች እንቅስቃሴ ሁከት ነው ለማለት የቻሉት በ1991 ዓ.ም በተደረገው የግጦሽ መሬት ክፍፍል ተሰጥቷቸዋል የሚል ማረጋገጫ ከቀበሌ ገብሬ ማህበር ስለተላከላቸው እንጂ በህጉ አግባብ የይዞታ ማረጋገጫ በማቅረብ አይደለም። ከሁሉም በላይ የተጠሪዎች ህጋዊ የሆነ የይዞታ መብት ያላቸው መሆኑ ከተረጋገጠም ከፍ/ቤት የሚጠይቁት ዳኝነት የሁከት ይወገድልኝ ሣይሆን የካሣ ጥያቄ ስለመሆኑ የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 40/8/ እና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የወጣው አዋጅ ቁጥር 455/1997 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ነው። እንደሚታወቀው የአንድ ንብረት ባለ ይዞታ የሆነ ሰው ይዞታውን ለመንጠቅ ወይም በይዞታው ላይ ሁከት ለመፍጠር የሚፈጸምን ማንኛውንም ድርጊት እንዲቆም ወይም ንብረቱ እንዲመለስለት ሕጉ ከአስቀመጣቸው መንገዶች አንዱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1149/1/2/ ስር የተመለከተው ነው። በዚህ አንቀጽ መሰረት የሁከት ይወገድልኝ ክስ መቅረብ የሚችለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ነገር በቀጥታ ወይም በጠባቂ ይዞታ ሲኖረው ነው። እንዲሁም የይዞታ ክስ የሚቀርበው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት በወቅቱ ለመያዝ ምንም ዓይነት መብት በሌለው ሰው ስለመሆኑም የተጠቃሹ ድንጋጌ መንፈስ ያስገነዝባል። በሌላ አገላለጽ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅራቢ ከተከሣሹ የተሻለ የይዞታ መብት ያለው ስለመሆኑ ማሣየት ይጠበቅበታል። ሆኖም ይህንኑ ያስረዳ ከሣሽ ጥያቄው ተቀባይነት የሚያገኘው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1140 እና 1149 ድንጋጌዎች የተመለከቱትን መብቶች የሚገድብ ሌላ ሕግ በሌለበት ሁኔታ ነው። የይዞታ መብት ፍጹም አይደለም። በሕጉ አግባብ ሌላ መፍትሔ ሊሰጥበት የሚችል ነው። ከእነዚህ መፍትሔዎች መካከልም ይዞታው ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ሲወሰድ ካሣ የሚከፈልበት ስለመሆኑ አንዱ ነው።

የአመልካች ጥያቄም ተጠሪዎች በቦታው ላይ ህጋዊ የባለይዞታነት የላቸውም ከሚል በተጨማሪ በአዲስ አበባ ከተማ መሪ ፕላን ማጽደቂያና አፈፃፀም አዋጅ ቁጥር 7/1986 መሰረት ድርጊቱ ሁከት ሊባል የሚገባ አይደለም የሚል ነው። ተጠሪዎች በቦታው በዚህ አዋጅ መሰረት የደን ተብሎ አለመከለሉን አላረጋገጡም። ይልቁንም ቦታው ለደን ተብሎ የተከለለ ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤትም አረጋግጧል።

እንግዲህ የአዋጅ ቁጥር 7/1986 አንዱ ዓላማ በአዲስ አበባ መስተዳድር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች መሰረት የከተማው እድገት ስርአት እንዲይዝና እንዲፋጠን ማድረግ ስለመሆኑ በመግቢያው ላይ ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም የክልል መስተዳደሩ በለምለም ክልል ካርታው ላይ የተመለከቱትን ክልሎች እንደሚጠብቅ እንደሚንከባከብ፣ወይም እንዲጠበቁ የማድረግና እንዲለሙ የታቀደበትን የለምለም ክልሎች ስለሚለሙበት፣ስለሚጠበቁበት ሁኔታ አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ኃላፊነት ያለው ስለመሆኑ ተጠቃሹ አዋጅ በአንቀጽ 24 ስር በግልጽ አስፍሯል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ቦታው በደን የተከለለ መሆኑ ከተረጋገጠ አመልካችና ሰራተኞቹ ጉድጓድ በማስቆፈር ችግኝ ማስተከላቸው በሕጉ የተፈቀደ ተግባር ነው ከሚባል በስተቀር ሁከት ሊባል የሚቻልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ተጠሪዎች ቦታውን በሕጉ አግባብ የያዙትና ያለሙት ዛፍ ካለም በሕጉ አግባብ ካሣ የመጠየቅ መብት ይኖራቸዋል እንጂ ይዞታውን ልንለቅ አይገባም፣ሁከቱ ሊወገድ ይገባል በማለት ሊከራከሩ የሚችሉ አይደሉም፡፡ አመልካች ሁከት ፈጥሯል በማለት በማስተር ፕላኑ መሰረት ቦታውን ለአረንጓዴ ክልል በማዋል እንዳይንከባከብና እንዳይጠበቅ ማድረግ ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ሕጋዊ ምክንያት የሚሰጠው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ የአመልካች አድራጎት ሁከት ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1140 እና 1149 ድንጋጌዎችን ከአዲስ አበባ ከተማ መሪ ፕላን ማጽደቂና የአፈፃፀም አዋጅ ቁጥር 7/1986 አንቀጽ 2/5/፣21፣22፣23 እና 24 ድንጋጌዎች ጋር ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 319/92 ሰኔ 08 ቀን 1996 ዓ.ም ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው በመ/ቁ. 01595 ሐምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም፣እንዲሁም በሰበር ችሎቱ በመ/ቁ. 05481 ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪዎች ላይ የፈጠረው ሁከት የለም ብለናል፡፡
3. ተጠሪዎች በሕጉ አግባብ የሚያቀርቡትን ሌላ ህጋዊ ጥያቄ ይህ ውሣኔ አያስቀርም ብለናል፡፡
4. ለክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 38666

ሐምሌ 9 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ ታምራት አባተ

**ተጠሪ** ፡- ባላንባራስ ተስፋዬ ገ/እየሱስ - ጠበቃ ገ/እግዚአብሄር ተስፋዬ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን አመልካች በተጠሪ ላይ በትግራይ ብ/ክ/መ/በመቀሌ ዞን ማዕከላዊ ፍ/ቤት ባቀረበው አቤቱታ ለአቶ ተስፋዬ ፍትዊ ለሰጠው ብድር መያዣ የሆነ በመቀሌ ከተማ ደቡብ ወረዳ ኩሃ ቀበሌ የሚገኝ በ35259 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የሠፈረ መጋዘንን ዕዳው ሳይከፈል በመቅረቱ ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 97/90፣ 98/90 እና 216/92 መሠረት አመልካች ከተበዳሪው ላይ ተረክቦ በማስተዳደር ላይ እያለ ተከሣሽ ከዚሁ ባለዕዳ ላይ ለሚፈልጉት ገንዘብ ይሄው ንብረት እንዲሸጥ ጠይቀው በሐራጅ ባለመሸጡ ምክንያት ንብረቱን እንዲረከቡ በፍ/ቤት ትዕዛዝ በመስጠቱ ንብረቱን መረከባቸው ተገቢ እንዳልሆነ በመጥቀስ ይመለስልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽም ቀርበው በሰጡት መልስ ንብረቱን የተረከቡት ዕዳው ሳይከፈል በመቅረቱ ምክንያት የተጠቀሰው መሬትና መጋዘን ባለዕዳው በባለይዞታነት የሚጠቀምበት መሆኑን በመግለጽ ይሄው ንብረት እንዲሸጥ ተጠይቆ ሁለት ጊዜ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ወጥቶ ገዢ ባለመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/428/2/ መሠረት የፍርድ ባለመብቱ እንዲረከበው ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሠጥቶ በዚሁ መሠረት የተረከብኩት ስለሆነ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሽ የብድር ዕዳው ሳይከፈለው በመቅረቱ ምክንያት ንብረቱን ተረክቤያለሁ ቢልም ንብረቱን ስለመረከቡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1723/1/ መሠረት ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ከመሆኑም በላይ ተከሣሽ ንብረቱን በሐራጅ የሚገዛ በመጥፋቱ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/428/1/ በሚፈቅደው መሠረት የተረከበ ስለሆነ ንብረቱን ሊመልስ አይገባም በማለት የከሣሽን አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለትግራይ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው ሲል በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/337 መሠረት ይግባኙን ሠርዟል፡፡

የሠበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች በመያዣ ይዞት የነበረውን ንብረት አግባብ ባለው አካል ከማስመዝገብ አልፎ በስሙ በርስት መዝገብ አላስመዘገበም ተብሎ በመያዣ የያዘውን የተረከበውን ንብረት ለተጠሪ እንዲያስረክብ መባሉ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥና ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችንም አቤቱታው ለሰበር ይቅረብ ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

አመልካች አቶ ተስፋዬ ፍትዊ የተባሉ ግለሰብ የተበደሩትን ገንዘብ ባለመክፈላቸው ምክንያት በመያዣ የያዘውንና ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነውን መሬትና መጋዘን አዋጅ ቁጥር 97/90፣ 98/90 እና 216/92 በሚፈቅደው መሠረት ገዢ በመጥፋቱ ምክንያት ተረክቦት እንደነበር መረጋገጡን ተገንዝበናል በሌላ በኩልም የአሁን ተጠሪ በዚሁ ባለዕዳ በአቶ ተስፋዬ ፍትዊ ላይ አስፈርደው አመልካች በመያዣ ይዞት የነበረውና በኋላም የተረከበው መጋዘን በሐራጅ እንደሸጥ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሲሰጥ አመልካች ንብረቱን በመያዣ ይዞት እንደነበረና ዕዳው ባለመከፈሉ ምክንያትም ንብረቱ በሐራጅ ለመሸጥ ተሞክሮ ገዢ በመጥፋቱ ምክንያት ከፍ ብሎ በተጠቀሱት አዋጆች መሠረት ንብረቱን እንደተረከበ በመግለጽና በንብረቱም ላይ መብት እንዳለው በመጥቀስ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/444 መሠረት ሽያጩን በመቃወም አመልካች አቤቱታ አቅርቦ እንደነበረና ፍ/ቤቱም አቤቱታው የቀረበው ዘግይቶ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ ማድረጉንም ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

በዚህ መልኩ አቤቱታው ተቀባይነት ሳያገኝ ከቀረ አመልካች በዚህ ጉዳይ ላይ ክስ ከማቅረብ እንደማይታገድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/421 እና 455 ላይ ተመልክቷል፡፡

አመልካች በዚሁ መሠረት አቤቱታውን ሲያቀርብ የከፍተኛው ፍ/ቤት አቤቱታውን ሳይቀበለው የቀረው ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ንብረቱን ስለመረከቡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1723/1/ መሠረት ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ስላልተደረገ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡

ይሁንና የንብረት ባለሀብትነት ከሕግ ወይም ከውል የሚያመነጭ ሲሆን አመልካች በዚህ ንብረት ላይ ባለሀብትነትን አቋቁሜያለሁ የሚለው ከውል ሳይሆን ከሕግ ነው፡፡ ይሄውም አመልካች በመያዣ የያዘው ንብረት ዕዳው ባለመከፈሉ ምክንያት በሐራጅ መሸጥ ካልቻለ ንብረቱን መረከብ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 98/90 ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚሁ መሠረትም ይህንኑ ንብረት የተረከበው ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደመሆኑ መጠን አመልካች የንብረቱ ባለሀብት መሆን የቻለው ከሕግ በመነጨ መብት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ/1723 ተፈፃሚነቱ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብትነት በውል ማስተላለፍ በተፈለገ ጊዜ ስለሆነ የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ለጉዳዩ ዕልባት መስጠቱ አግባብነት በሌለው ሁኔታ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡

አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬትና መጋዘን በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መረከቡ ከተረጋገጠ ይህንኑ ንብረት በሌላ ዕዳ ምክንያት ተጠሪ እንዲረከቡት ትዕዛዝ ሲሰጥ የተረከበውን ንብረት በአመቺው መንገድ በመሸጥ ገንዘቡን ገቢ የማድረግ መብቱን የሚጋፋ ነው፡፡

ስለሆነም ተጠሪ የፍርድ ባለመብት የሆኑበት ጉዳይ አመልካች በሕግ አግባብነት የንብረቱ ባለቤት በሆነበትና ለዚህ ክርክር ምክንያት በሆነው መሬትና መጋዘን ላይ አፈፃፀም ሊቀጥል የማይገባው ሆኖ ሳለ የመቀሌ ዞን ማዕከላዊ ፍ/ቤት ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለውን ድንጋጌ በመጥቀስ የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የመቀሌ ዞን ማዕከላዊ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 05134 በ24/6/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 24088 በ8/9/2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በመቀሌ ከተማ ደቡብ ወረዳ ኩሃ ቀበሌ የሚገኘው 35259 ካ.ሜትር ቦታ ላይ የሠፈረውን መጋዘን አመልካች በሕግ አግባብነት የተረከበው ስለሆነ ተጠሪ መልሰው ለአመልካች እንዲያስረክቡ ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ መሠረትም እንዲፈጽም የፍርዱ ግልባጭ ለመቀሌ ዞን ማዕከላዊ ፍ/ቤት ይተላለፍ ብለናል፡፡
4. የግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሽ

# ከውል ውጭ ኃላፊነት

የሰ/መ/ቁ. 34544

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን- ነገረ ፈጅ አቶ መስፍን ሃብቴ ይመር - ቀረበ

**መልስ ሰጭ፡-** ወ/ሮ ፋጤ ዓሊ - በሌሉበት የሚታይ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር መዝገብ ተከፍቶ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ጉዳይ በይግባኝ ተመልክቶ በኮ.መ.ቁ. 48755 ታህሳስ 07 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝቶ የሰበር አቤቱታውን በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡ የአሁን መልስ ሰጭ በጋምቤላ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሳሽ በመሆን በባለቤቷ ሞት ምክንያት በእራሷ እና የሞግዚትነት ሥልጣን ባገኘችባቸው ልጆቿ ስም ደረሰ ያለችውን ጉዳት አስልታ የጉዳት ካሣ ገንዘብ በአሁን አመልካች ላይ ከውል ውጭ በሚደርስ ኃላፊነት የተነሳ የክስ አቤቱታ አቅርባለች፡፡

የአሁን አመልካችም በዚህ አኳኋን ለቀረበበት ክስ ጉዳቱ ደርሷል ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ድረስ ያለው ጊዜ ሲታሰብ ሁለት ዓመት ያለፈው በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይቋረጣል የሚለውን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ካቀረበ በኋላ ስለ ፍሬ ጉዳዩም ያለውን የመከራከሪያ ነጥቦች በመዘርዘር ተከራክሯል፡፡

ክሱ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር አገናዝቦ ከመረመረ በኋላ ክሱ ለጉዳቱ ምክንያት የሆነው ድርጊት ከተፈፀመ ሁለት ዓመት ካለፈው በኋላ  የቀረበ መሆኑ ቢታወቅም ጉዳቱ ሞት ነው፤ የደረሰው ጉዳት ሞት በሆነ ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2143 የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም የሚለውን ምክንያት አስፍሮ ክሱ በይርጋ ሊቋረጥ አይችልም የሚል ዳኝነት ሰጥቶ በአሁን አመልካች ላይ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ጠቅሶ የካሣ ገንዘቡን በሚመለከት ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ ብር) በርትእ እንዲከፈል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረቡ ይኸው ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ ሙሉ ክርክር ካደረገ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ውሳኔውን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውንም ሆነ የኃላፊነቱን ነጥብ በሚመለከት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነው፡፡

መልስ ሰጭ በዚሁ የሰበር አቤቱታው መነሻነት ቀርባ መልስ እንድትሰጥበት ቢታዘዝም ጥሪ ደርሷት ያልቀረበች በመሆኑ ጉዳዩ በሌለችበት ታይቷል፡፡

እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ በዚህ ጉዳይ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተገኘው ይርጋን አስመልክቶ ለቀረበው ክርክር የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ትርጉም የሕግ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡

ምንም እንኳ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ ነጥብ በሚመለከት ዳኝነት ያልሰጠበት ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ ቢያስረዳም የአሁን አመልካች ለዚሁ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያቀረበውን የይግባኝ ማመልከቻ ቅጅ እንዳየነው የይርጋ ጉዳይ በመቃወሚያነት በመጀመሪያ ደረጃው ፍ/ቤት እንስቶ የተከራከረበት መሆኑን ገልፆ ክሱ በመቃወሚያው ክርክር መቋረጥ የሚገባው ሆኖ እያለ ያለአግባብ መታለፉ ቅሬታ የፈጠረበት መሆኑን ጠቅሶ በይግባኝ የተከራከረበት ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ከክርክር አቀራረብ ሥርዓት አንፃር ይህ የሰበር አቤቱታ ደረጃውን ሳይጠብቅ የቀረበ ነው ማለት አይቻልም፡፡

ወደ ተያዘው አከራካሪ ነጥብ ስንመለስ ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክስ ጉዳቱ ደረሰ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ የቀረበ ለመሆኑ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የክሱም ምክንያት ከውል ውጭ በሚደርስ ኃላፊነት ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ ይህም ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2143 እንደተደነገገው ማናቸውም የጉዳት ካሣ ክስ ካሣ የሚጠየቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ካልቀረበ በቀር ክሱ በይርጋ የሚቋረጥ ነው፡፡ ካሣ የሚጠየቅበት ጉዳት ሲባል ደግሞ ሞትንም እንደሚያካትት ይኸው ሕግ በማያሻማ አኳኋን ደንግጐ እያለ፤ ክሱ የቀረበለት የጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከዚህ በግልጽ ከተደነገገው ሕግ በመራቅ የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ጉዳት ሞት ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል አይደለም በማለት የይርጋውን ክርክር ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ቀድሞውንም ቢሆን ስለኃላፊነቱ ከማከራከሩ በፊት ክሱ በይርጋ ይቋረጣል በማለት መዝገቡን መዝጋት ሲገባው በተሳሳተ የሕግ አተረጓጐም የተነሣ የተሟላ የክስ መስማት ሂደት ማከናወኑ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## **ው ሳ ኔ**

1. የጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛው ፍ/ቤት በፍት/መ/ቁ. 6/95 ግንቦት 06 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 48755 ታህሳስ 07 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የአሁን መልስ ሰጭ በአመልካች ላይ ያቀረበችው የጉዳት ካሣ ክስ ከውል ውጭ በሚደርሰው ኃላፊነት ሕግ እንደተመለከተው በሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ የተቋረጠ ነው ብለናል፡፡

ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 33201

ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ የሺጥላ ተሾመ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ሼል ኢትዮጵያ - ጠበቃ አጥናፉ ቦጋለ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሣን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ አመልካች ንብረትነቱ የተጠሪ በሆነው የነዳጅ ማደያ ላይ በደረሰው የቃጠሎ አደጋ መንስኤነት አመልካች የሚያስተዳድረው አድራሻው ወረዳ 18 ቀበሌ 27 የቤት ቁጥር 303 የሆነው ቤት ተቃጥሎ ጉዳት የደረሰበትን ቤት ተጠሪ በማደስ ለአመልካች ቢያስረክብም በእድሣቱ ምክንያት ቤቱ በመዘጋቱ አመልካች የኪራይ ገቢ ማጣቱን በመግለጽ አመልካች ከኪራይ ገቢ ያጣውን ብር 6375.00 /ስድስት ሺህ ሦስት መቶ ሰባ አምስት ብር/ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር እንዲከፍለው ይወሰንለት ዘንድ በአሁኑ ተጠሪ ላይ ነሐሴ 26 ቀን 1997 ዓ.ም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረተው ክስ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በፍ/ቤቱ ጥሪ መሠረት ቀርቦ የአመልካችን ቤት ያሣደሰው የነዳጅ ማደያው ስራ እንዳይቆም እንጂ ኣላፊነትን በመቀበል አለመሆኑን፣ ለጉዳት አላፊነት ያለበት አካልም በወቅቱ የነዳጁ አንጓዥ የነበረው ኢነርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የወከለው ቴዲ ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ ሹፌር መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም ተጠሪ ለደረሰው ጉዳት አላፊ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ሲል የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚልበትን ምክንያቶች በ15/01/2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ዘርዝሯል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የተቃጠለው የነዳጅ ማደያም ሆነ ለቃጠሎው መንስኤ የሆነው በወቅቱ በመራገፍ ላይ የነበረው ነዳጅ ባለቤት ሼል ኢትዮጵያ ሊሚትድ እንጂ ሌላ ባለመሆኑ ከአላፊነት ነፃ መባሉ ያላግባብ ስለሆነ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊሻር ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን ሠጥቷል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ አመልካች በሰበር ባላነሣው የሕግ ነጥብ የበታች ፍ/ቤቶች ስህተት ፈጽመዋል ሊባል ስለማይገባ የሠበር አቤቱታው ውድቅ ሆኖ ይወሰንልኝ በማለት መከራከሩን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ በበታች ፍ/ቤት የሕግ ድንጋጌ ተጠቅሶ ክርክር አለመቅረቡ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በመለየት ውሣኔ መስጠት የፍ/ቤት የስራ ድርሻ ከመሆኑ አኳያ በስር ያልተነሣ የክርክር ነጥብ ሊባል አይችልም በማለትና የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር መጋቢት 01 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ

መርምሮታል እንደመረመረውም ለአመልካች የተቋረጠ የኪራይ ገቢ ይከፈለኝ ጥያቄ ተጠሪ ኣላፊነት የለበትም ተብሎ ውድቅ መደረጉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን? በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በክርክሩ ሂደት ተጠሪ የቃጠሎ አደጋ የደረሰበት ነዳጅ ማደያ ባለቤት መሆኑ ቃጠሎውን ያስነሣው መኪና ባለቤት ከተጠሪ ጋር የአጓጓዥነት ስራ የተዋዋለ ሰው መሆኑ፣ በቃጠሎው የአመልካች ቤት መጎዳቱና ተጠሪ ይህንኑ በቃጠሎው የተጎዳውን ቤት በማሣደስ ለአመልካች ማስረከቡ የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የተቋረጠውን የኪራይ ገቢ እንዲከፍል በአመልካች በኩል የቀረበበት ክስ ውድቅ የሆነው ቃጠሎውን ያስነሣው መኪና ሹፌር በፈፀመው ስለሆነ እና ሹፌሩ የተጠሪ ተቀጣሪ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት ነው፡፡

ይሁን እንጂ ነዳጁ ሲራገፍ የነበረው ተጠሪ ስራውን በሚያከናውንበት የነዳጅ ማደያ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ የተጠሪ ኣላፊነት የሚመነጨው ከሚያከናውነው ስራ አደገኝነት አኳያ ታይቶ ነው፡፡ ማንም ሰው ስራው በሚያደርሰው ጉዳት ምክንያት ጥፋት ባይኖርበትም ከውል ውጪ ኣላፊነት ሊከተልበት እንደሚችል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2066 - 2089 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ያስረዳሉ፡፡

በእጃችን ላለው ጉዳይ አግባብነት የሚኖረው ድንጋጌም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2069/1/ ሲሆን ተጠሪ በሚያከናውነው የነዳጅ ማደያ ስራ ለሚከሰተው አደጋ ኣላፊነቱን ሊወስድ እንደሚገባ ያስገነዝባል፡፡ ምክንያቱም የነዳጅ ማደያ ስራ ጥንቃቄ የሚያስፈልገውና በቀላሉም የመቀጣጠል ወይም የመፈንዳት ባህርይ ስላለው የአደገኛ ስራ ባህርይነት ኑሮት አጥፊ ሣይሆን ኣላፊ መሆንን የሚያስከትል ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ኣላፊነት የለብኝም የሚል ክርክር ሣያቀርብ በስር ፍ/ቤት ተነስቶ ክርክር ያልተደረገበት ነው በሚል ምክንያት ብቻ በዚህ ችሎት በሰጠው መልስ ተከራክሯል፡፡ ይሁን እንጂ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ መጥቀስ የፍ/ቤት የስራ ድርሻ ከመሆኑ አኳያ የተጠሪ ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329/1/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ባገናዘበ መልኩ ያልቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ የአመልካች ቤት በቃጠሎው ከወደመ በኋላ አድሶ ማስረከቡን ሣይክድ ይኸው ተግባሩ ኣላፊነቱን መቀበሉን አያሣይም የሚል ክርክር ማቅረቡ አሣማኝነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የአሁኑ ተጠሪ ከኣላፊነት ነፃ የተደረገው የግራ ቀኙን ክርክር እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2069/1/ ድንጋጌን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1/ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57875 ጥቅምት 06 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 51136 ሠኔ 27 ቀን 1999 የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ ተጠሪ በሚያከናውነው ስራ አደገኛነት የተነሣ በአመልካች ንብረት ላይ ባደረሰው ቃጠሎ ምክንያት የተቋረጠውን የኪራይ ገቢ የመተካት ኣላፊነት አለበት ብለናል፡፡

3/ ተጠሪ ለአመልካች ብር 7968.75 /ሠባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሣ ስምንት ብር ከሰባ አምስት ሣንቲም/ ይክፈል ብለናል፡፡

4/ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

5/ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 31721

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ብዙነሽ ኃ/ዮሐንስ - ጠበቃ መድሕን መሐሪ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ስንታየሁ እሸቱ - በሌለችበት

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ከውል ውጪ የደረሰ ኃላፊነትን መሠረት አድርጎ የቀረበ የካሣ ክፍያ ጥያቄን /ክርክር/ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሶማሌ ብ/ክ/መ/ በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ ስትሆን በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችውም የምትወልደው ልጅዋ ሦስት ሕፃናት ልጆቼን አርዶ ስለገደለብኝ በእናትነትዋ ካሣ ልትከፍለኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠችው መልስ ጉዳዩ በፈጸመው ድርጊት ኃላፊ የምሆንበት የሕግ ምክንያት የለም፤ መከሰሴም ያለአግባብ ነው፡፤ በማለት ስለመከራከርዋ ከመዝገቡ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ ተከሣሽ ላደረሰው ጉዳት ኃላፊ ናት በመሆኑም በጠቅላላው ብር 35000(ሰላሳ አምስት ሺህ) ካሣ ለከሣሽ ትክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ይህን ውሣኔ በመቃወም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማለትዋ በዚህ ይግባኝ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ በከፍተኛው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሣኔ በማሻሻል አመልካች ብር 78000(ሰባት ሺህ ስምንት መቶ) ካሣ እንድትከፍል ወስኖአል፡፡ በጨረሻም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ከአመልካች በቀረበለት አቤቱታ መነሻነት ክርክሩን ከሰማ በኋላ በጠ/ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የአሁኑ አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሐምሌ 6 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪ በተደረገላት ጥሪ መሠረት ባለመቅረብዋ ክርክሩ የተሰማው እሷዋ በሌለችበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊ የምትሆንበትና ካሣ የምትከፍልበት የሕግ ምክንያት አለ ወይ? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ ባጭሩ እንደተመለከተው አመልካች የተከሰሰችው እና በመጨረሻም ኃላፊ ነሽ የተባለችው እርስዋ በፈጸመችው ድርጊት ጉዳቱን አድርሳለች በሚል አይደለም፡፡ ጉዳቱን አድርሷል የተባለው የእሷ ልጅ የሆነው ሰው ነው፡፡ እርሱም ልጆቹን ከገደለ በኋላ ራሱንም እንዳጠፋ በተጠሪ ክስ ተገልጾአል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሰውየው አካለ መጠን የደረሰና ዕድሜውም ከ40 ዓመት በላይ እንደነበረ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ተጠሪ ክሱን የመሠረተችው በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2125 የተመለከተውን ድንጋጌ በመጥቀስ ሲሆን ይህ ድንጋጌ የሚያመለክተው በአባት አላፊነት ምትክ ሆነው ስለሚጠየቁት ሰዎች ነው፡፡ ድንጋጌው የሚገኘው “ለሌላ ሰው ተግባር አላፊ ስለመሆን” በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 13 በምዕራፍ 1 /ከውል ውጪ ስለሚደርስ አላፊነት/ በሚለው በክፍል 4 ስር ነው፡፡ ከቁጥር 2125 በፊት ያለው ቁ. 2124 አካለ መጠን ያላደረሰ ልጅ አላፊነትን የሚያስከትል ሥራ የሠራ እንደሆነ በፍትሐብሔር በኩል ለተሠራው ሥራ አላፊ የሚሆነው አባት እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ቁጥር 2125 ደግሞ አባት በሌለ ጊዜ በሱ ምትክ ኃላፊ የሚሆኑትን በተመለከተ

የሚደነግግ ነው፡፡ ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዷ የልጁ እናት እንደሆነችም በዚሁ ቁጥር 2125/ሀ/ ተመልክቶአል፡፡ እንግዲህ እንደተጠሪ ክስ አመልካች ኃላፊ ልትሆን ትችል የነበረው ጉዳቱን አድርሷል /የተጠሪን ልጆች ገድሎአል/ የተባለው ሰው አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ቢሆን ነበር፡፡ ይህ ግን በተጠሪ በኩል አልተረጋገጠም፡፡ ጉዳት አድራሹ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ነው የሚል በተጠሪ ክስም ሆነ ክርክር አልተነሳም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ ጉዳት አድራሹ ሰው ዕድሜው ከ40 ዓመት በላይ የነበረ እና በኔም ስር የሚተዳደር ያልነበረ ነው የሚለውን የአመልካችን ክርክር ከመመዝገብ አልፈው በእርግጥ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ነበር አላሉም፡፡ ይህም የሚያመለክተው ፍ/ቤቶቹ አመልካችን ኃላፊ ያደረጉዋት ኃላፊ የምትሆንበት የሕግ ምክንያት ሳይኖር እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በሶማሌ ብ/ክ/መ/ በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ እና በዚህ ውሣኔ ላይ በቀረበው ይግባኝ እና አቤቱታ ማስረጃነት በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት እና ሰበር ችሎት በመ/ቁ. **GM**181/98 ሰኔ 28 ቀን 98 ዓ.ም. እና በመ/ቁ. 09/99 ሚያዝያ 13 ቀን 1999 ዓ.ም. የተሰጡት ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1 መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊ የምትሆንበትም ሆነ ካሣ የምትከፍልበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ወስነናል፡፡
   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 31171

ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አብልሃሚድ የሱፍ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የምሥራቅ ቀጠና ጉምሩክ ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ አጥሉ ሀብታሙ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንብረት ግምት ጥያቄ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ አመልካች ጥር 05 ቀን 1997 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ በአወዳይ ከተማ ውስጥ የንግድ ስራ በሕጋዊ መንገድ እያካሄዱ ባሉበት ሁኔታ ተጠሪ የጉምሩክ ፖሊስ እና ሌላ የፖሊስ ኃይል በማስተባበር የሱቁን ቁልፍ በመስበር በሱቁ ውስጥ የነበረውን የንግድ ዕቃ በሙሉ አውጥተው በጭነት መኪና ጭነው በመውሰድ በተጠሪ መጋዘን ማስገባቱን፤ የተወሰዱ ንብረቶችን ተጠሪ ይመልስላቸው ዘንድ ጥያቄ ቢያቀርቡም ተጠሪ ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘቱን፤ የተወሰዱባቸው በሱቁ ውስጥ የነበሩት ንብረቶች ዓይነታቸውና ብዛታቸው እንዲሁም ግምታቸው ምን ያሕል እንደሆነ በመዘርዝር ግምቱ ብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ የሆነ ንብረት እንዲመለስላቸው፣ ንብረቶቹ ተሸጠው ይገኝ የነበረውን ትርፍ እንዲከፍሉ፣ ንብረቶቹን ካልመለሱ ግምቱን እንዲከፍሉ እና የተለያዩ ወጪዎችንም ጭምር እንዲከፍሉ ይወስንላቸው ዘንድ የአሁኑን ተጠሪ አንደኛ ተከሣሽ ሌሎች ሁለት የፖሊስ አባላትን ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሣሽ በማድረግ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በአመልካች በኩል ተዘርዝረው የቀረቡትን የንብረት ዓይነቶች በፍ/ቤት የብርበራ ትዕዛዝና በሕብረተሰቡ ትብብር የኮንትሮባንድ ንግድን ለመቆጣጠር እና ለመያዝ በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የወሠደ መሆኑን በመግለጽ ተጠያቂነት እንደሌለበት፤ በአመልካች በኩል የቀረቡት ማስረጃዎችም ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑንና ሌሎች የመከራከሪያ ነጥቦችን በማንሣት ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት በ27/07/97 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ የተጠሪን መከራከሪያ ነጥቦች ውድቅ በማድረግ ተጠሪንና በስር ሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩትን የጉምሩክ ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ኃላፊን ለድርጊቱ ኣላፊ አድርጎ የአመልካችን ንብረት በክሱ በቀረበው ዝርዝር መሠረት በእራሣቸው ወጪ ከወሰዱበት ቦታ ከአመልካች ሱቅ እንዲመልሱ ይህን ካልፈፀሙ ግምቱን ብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ፣ ወጪና ኪሣራ ዝርዝር የማቅረብ መብት ለአመልካች በመጠበቅ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የተለያዩ ምክንያቶችን ከዘረዘረ በኋላ በአሁኑ አመልካች በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች ንብረቶቹ የአመልካቹ ለመሆናቸው ለማስረዳትና ለማረጋገጥ የማይችሉ አጥጋቢና አሣማኝ አይደሉም ወደሚል ድምዳሜ በመድረስ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር ተጠሪን በነፃ በማሠናበት ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ያሉባቸውን ምክንያቶች ሰኔ 03 ቀን 1999 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ዘርዝረዋል፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ

ሊታይ ይገባል በመባሉ ተጠሪ ጥር 01 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን አቅርቧል፡፡ አመልካችም በተጠሪው መልስ ላይ የካቲት 06 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ተጠሪ የወሰዳቸው ከአመልካች ሱቅ ነው እየተባለ ንብረቶቹ የአመልካች መሆናቸው አልተረጋገጠም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በክርክሩ ሂደት ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ተጠሪ የወሰዳቸው ከአመልካች ሱቅ መሆኑ፣ የአመልካች ሱቅ ቁጥር የለውም ቢባልም በብር 10,000.00 /አስር ሺህ/ ካፒታል ልዩ ልዩ ዕቃዎችንና ሸቀጦችን ለመነገድ ከተገቢው አካል ፈቃድ አውጥተው የሚሠሩበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ሱቅ ንብረቶቹን መወሰዱን ሣይክድ ተግባሩን የፈፀመው በሕጉ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሆኑንና ንብረቶቹ የአመልካች ስለመሆናቸው ተቀባይነት ያለው ማስረጃ አለመቅረቡን በመጥቀስ የሚከራከር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የተጠሪ መ/ቤት ስልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር 60/1989 በአንቀጽ 6 እና 58 ስር ተዘርዝሯል፡፡ እነዚህ የአዋጁ ድንጋጌዎች የሚያሣዩት የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር የጉምሩክ ባለስልጣንና ሹም የተሰጣቸው ስልጣንና ተግባራት በዝርዝር መቀመጣቸውን ነው፡፡ የጉምሩክ ባለስልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 368/1995 ደግሞ ኮንትሮባንድ ማለት ሕጎችንና በሕግ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ወደ ጉምሩክ ክልል ዕቃዎችን በማስገባት ወይም ከጉምሩክ ክልል በማስወጣት፣ በሕጋዊ መንገድ የመጡትን በሕገ ወጥ መንገድ መልሶ ማስባት፣ መያዝ፣ ማከማቸት፣ ማዘዋወር ማስተላለፍ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ ለማድረግ መሞከር እና ከእንደዚህ ያሉ ድርጊቶች መተባበርን እንደሚጨምር በአንቀጽ 2/28/ ትርጓሜ ሠጥቶበታል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ተጠሪ ተግባሩን ሕጋዊ ነው ብሎ ሲከራከር በተለይ መሠረት ያደረጋቸው የአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 6/5/ እና 58/1/ለ/ ድንጋጌዎችን ነው፡፡ አንቀጽ 6/5/ ሙሉ ይዘቱ ሲታይ ባለስልጣኑ "በኮንትሮባንድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን ዕቃዎች እንቅስቀሴ ይቆጣጠራል፣ ይከላከላል፣ በዚሁ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን ይይዛል፣ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል" በማለት ሲደነግግ አንቀጽ 58/1/ለ/ ደግሞ ወደ አገር እንዳይገቡ ወይም ከአገር እንይወጡ የተከለከሉ ገደብ የተደረገባቸው ወይም ቀረጥ እንዳይከፈልባቸው በማሠብ የተደበቁ ዕቃዎች በፍተሻ ሲገኙ ዕቃዎችን የመያዝ እንዲሁም እንደሁኔታው ማጓጓዣውን የማጓጓዣውን ኃላፊ ወይም የዕቃውን ባለቤት ይዞ ለምርመራ በጥበቃ ሥር የማቆየት ስልጣንና ኃላፊነት የጉምሩክ ሹም ያለው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የጉምሩክ ባለስልጣን በኮንትሮባንድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን ዕቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ፣ በሕገ ወጥ መንገድ መገልገያ የሆኑ መጓጓዣዎችን ጭምር ይዞ ለምርመራ በጥበቃ ስር የማቆየት ስልጣን በሕጉ የተሰጠው መሆኑን ነው፡፡ እነዚህን ተግባራት የሚያከናውነው ግን ኮንትሮባንድ ተብሎ በሕግ የተሰጠው ትርጓሜ ተሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡ ማንኛውም የዕቃ እንቅስቃሴ ኮንትሮባንድ ስለመሆኑ አሣማኝ እና በቂ ምክንያት ሣይኖረው ባለስልጣኑ መ/ቤት እንዲይዝና እንዲቆጣጠር ሕጉ ስልጣን ሠጥቶታል ተብሎ አይታሰብም፡፡ የአንድን ሰው መኖሪያ ቤት ወይም የንግድ ቤት የኮንትሮባንድ ዕቃ የተደበቀበት ስለመሆኑም ባስልጣኑ ጥርጣሬ ሲኖረው ሰብሮ በመግባት ዕቃዎችን እንዲይዝ ሕጉ ይፈቅድለታል ወደሚለው ድምዳሜ መድረስ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26/1/ ስር ጥበቃ የተደረገለትን የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት ዋስትና የሚያሣጣ ነው፡፡ በመሆኑም የጉምሩክ ባለስልጣን ተግባር ሕጋዊ ነው ሊባል የሚችለው በሕጉ መሠረት ሊሟሉ የሚችሉትን ሁኔታዎች አሟልቶ ሲገኝ ብቻ እንጂ በማንኛውም ጥርጣሬና ምክንያት ሁሉ የግለሰብን ንብረት በመያዝ ሊሆን አይችልም፡፡

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስ በተጠሪ ተወሰዱ የተባሉ ንብረቶች በአመልካች ይዞታ ስር የነበሩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1193/1/ ሥር በተደነገገው አኳኋን አመልካች የንብረቶቹ ባለሀብት መሆናቸውን ሕጉ ግምት ይወስዳል፡፡ ይህ ሕጋዊ ግምት ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1193/2/ ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለይዞታነት የሰው ወይም የጽሁፍ ማስረጃ በማቅረብ ካልፈረሰ በቀር ባለይዞታው የንብረቱ ሕጋዊ ባለሀብት ስለመሆኑ ግምት የሚወሰድበት እና ባለሀብትነትን የማስረዳት /proof of ownership/ አንዱ ዘዴ ነው፡፡

ተጠሪ ንብረቶቹ የአመልካች አለመሆናቸውንና በኮንትሮባንድ ስራ ወደ አመልካች እጅ የገቡ ናቸው በማለት የሚከራከረው በአመልካች በኩል የቀረቡትን ደረሰኞች፣ የንግድ ፈቃድ ካፒታል መጠንና የንግድ ዓይነትን መሠረት በማድረግ እንጂ ያላግባብ ወደ አገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ መሆኑን በማስረዳት አይደለም፡፡ በተለይም ተጠሪ የአመልካችን ንብረቶች ያዘኩ የሚለው በፍ/ቤት የብርበራ ትዕዛዝ ቢሆንም ይኸንኑ ትዕዛዝ ብርበራው ከተፈፀመ በኋላ ፍ/ቤቱ ማንሣቱ መረጋገጡ የተጠሪን ተግባር ሕጋዊነት ቀሪ ማድረጉን ከሚጠቁም በስተቀር አመልካች የንብረቶቹ ሕጋዊ ባለቤት አለመሆናቸውን የማያሣይ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የአመልካች ንብረቶች ኮንትሮባንድ ስለመሆናቸው አላስረዳም፡፡ በአንፃሩ ንብረቶቹን በይዞታቸው በማድረግ ይጠቀሙባቸው የነበረ ስለመሆኑ አመልካች ያረጋገጡ በመሆኑ በማስረጃ ምዘና መርህ ረገድ ሲታይ የተሻለ ማስረጃ ያቀረቡትም አመልካች ናቸው፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ያቀረቡትን ማስረጃዎች የመዘነበት መንገድ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1193 /1/እና /2/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ባላገናዘበ ሁኔታ ነው፡፡

ስለሆነም የአመልካች ዕቃዎች ከአመልካች ሱቅ መወሰዳቸው ተረጋግጦ እያለና ንብረቶቹ በኮንትሮባንድ ተግባር ወደ አመልካች ዕጅ የገቡ መሆናቸውን ተጠሪ ባላስረዳበት ሁኔታ ተጠሪ ተጠያቂነት የለበትም መባሉ ባግባቡ ሆኖ ስላልተገኘ ውሣኔው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1193፣ የአዋጅ ቁ. 60/1989 አንቀጽ 6/5/ እና 58/1/ለ/ እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 368/1995 አንቀጽ 2/28/ ድንጋጌዎችን መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ የአመልካችን ንብረቶች መወሰዱ በበቂ ሁኔታ ስለተረጋገጠ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2027፣ 2035 እና 2054 ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት አላፊ ሊባል የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የካሣውን መጠን በተመለከተም አመልካች ከጠየቁት ዳኝነትና ካቀረቡት ማስረጃ እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2118 አኳያ ሲታይ ተጠሪ ተዘርዝረው የቀረቡትን ንብረቶች በዓይነት እንዲመልስ ወይም ግምታቸውን እንዲከፍል መወሰኑ ፍትሐዊነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32974 ሰኔ 08 ቀን 1998 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26383 መጋቢት 19 ቀን 1999 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02282 ሐምሌ 07 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ከአመልካች ይዞታ ያላግባብ የወሰዳቸው መሆኑ ስለተረጋገጠ ንብረቶቹን በዓይነት እንዲመልስ ወይም ግምታቸውን ብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
4. በዚህ የሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 35034

ጥቅም 06 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

አሊ መሐመድ

**አመልካቾች**:- እነ ወ/ሮ ጥሩቀለም ደሴ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች**:- እነ ወ/ሮ ጽጌ ከፍያለው - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ክርክሩ ከውል ውጪ አላፊነትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የስር ከሣሾች የነበሩት የአሁኑ አመልካቾች ሲሆኑ መጋቢት 28 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ ክስ ንብረትነቱ የአንደኛ ተጠሪ የሆነ ታክሲ በሁለተኛ ተጠሪ ሲሽከረከር ተማሪ እየሩሣሌም ስሙር የተባለች የአስራ አንድ ዓመት እድሜ ያላት ሕፃን ልጃቸውን በመግጨት በቀኝ ታፋዋ ላይ ጉዳት በማድረስ አጥንቷ ተሰብሮ እያነከሰች እንደምትገኝ እና በጉዳቱ ምክንያትም ወደፊት ተምራ ልትጦራቸው በማትችልበት ሁኔታ እንደምትገኝ በመጥቀስ ለአካል ጉዳትና ለሞራል ካሣ በድምሩ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ የአሁኑ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችም ሰኔ 27 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ የመከላከያ መልስ ማመልከቻ ለአደጋው ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑንና የተቋረጠ ጥቅምም አለመኖሩን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ተገቢ ናቸው ያላቸውን ጭብጦችን በመመስረት ተከሣሾች አደጋው የደረሰው በክሱ ላይ በተጠቀሰው ተሽከርካሪ መሆኑን አምነው መከራከራቸውንና የከሣሾች ማስረጃም ጥፋቱ የአሽከርካሪው መሆኑን ማረጋገጡን ገልፆ ለጉዳቱ ተከሣሾች አላፊ ናቸው ካለ በኂላ የጉዳት መጠኑን በተመለከተ ግን ተጎጂዋ ትምህርቷን በመከታተል ላይ እንደምትገኝ መረጋገጡን፣ የህክምና ማስረጃውም መካከለኛ የሆነ ማነከስ ቢኖርባትም መራመድ እንደምትችል መግለፁን ጠቅሶ ተጎጂዋ ከሣሾችን ወደፊት ልትረዳ የማትችል እና ራሷም ሊቀርባት የሚችል ጥቅም ስለመኖሩ አጠራጣሪ ነው በማለት የአካል ጉዳት ካሣ ጥያቄን ውድቅ አድርጎ የህሊና ጉዳትን በተመለከተ ግን ብር 800.00 /ስምንት መቶ/ ሁለተኛ ተጠሪ ከወጪና ኪሣራ ጋር እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም አመልካቾች በእርግጠኝነት በአደጋው ምክንያት በልጅቷ ላይ የደረሰውን የአሁንና የወደፊት ቁሣዊ ጉዳት አላስረዱም ሲል ይግባኙን ሣይቀበል ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ሲሆን አመልካቾች ጥር 08 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሠበር አቤቱታ የቅሬታ ነጥቦችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የስር ፍ/ቤት ጉዳት የደረሰባት ልጅ መካከለኛ ማነከስ ያለባት እንደሆነ በህክምና ተረጋግጧል እያለ በሌላ በኩል ወደፊት ተጎጂዋ ሊቀርባት የሚችል ጥቅም ስለመኖሩ አጠራጣሪ ነው በማለት የጉዳት ካሣ ክፍያ አይገባትም በሚል መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪዎች መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን ሲያቀርቡ አመልካቾች በበኩላቸው ሚያዝያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡

እኛም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ተጠሪዎች የአካል ጉዳት ካሣ ለመክፈል ይገደዳሉ ወይስ አይገደዱም? የሚለው ነጥብ የችሎቱ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በክርክሩ ሂደት አንደኛ ተጠሪ የታክሲው ባለቤት ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ በተጎጂዋ ጉዳት አደረሰ የተባለውን ታክሲ በወቅቱ ሲያሽከረክሩ የነበሩ መሆኑ እና ለጉዳቱ መድረስ አንደኛ ተጠሪ የታክሲው ባለቤት በመሆናቸው ብቻ ያለጥፋት ሁለተኛው ተጠሪ ደግሞ በጥፋቱ አላፊነት ያለባቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካቾችን የአካል ጉዳት ካሣ ጥያቄ ያለፈው ተጎጂዋ ወደፊት ሊቀርባት የሚችል ጥቅም ስለመኖሩ እና አመልካቾችንም ልትረዳ የማትችልበት ሁኔታ መኖሩ አጠራጣሪ ሆኖ ተገኝቷል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተጎጂዋ መካከለኛ የሆነ ማነከስ ያለባት መሆኑ በሐኪም ከመረጋገጡ አኳያ እና የካሣ አከፋፈልና ልክ ከሚደነግጉት የፍትሐብሔር ሕጋችን ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ የስር ፍ/ቤት ድምዳሜ ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

በመሠረቱ በፍትሐብሔር ሕጋችን ከውል ውጪ አላፊነትን በሚመለከት የተቀመጡ ድንጋጌዎች ጉዳት የደረሰበት ሰው የሚካስበትን ሥርዓት የዘረጉ ናቸው፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ዓይነተኛ ግባቸውም ጉዳትን የመካስና የጥፋት ባህርይን የመግታት ስለመሆኑ በድንጋጌዎቹ ላይ ማብራሪያ ጽሑፍ ያበረከቱት በቀድሞ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርስቲ የሕግ ትምህርት ክፍል አስተማሪ የነበሩት  ቺቺኖቪች ገልፀውታል፡፡

ከውል ውጪ አላፊነትን በተመለከተ የሚገዙት የፍትሐብሔር ሕጋችን ድንጋጌዎች መንፈስ የጉዳትን ጠቅላላ ባህርይና የካሣ ልክ አተማመን ሁኔታዎችን ያስገነዝቡናል፡፡ በዚህም መሠረት ጉዳት በሰው ጥቅም ላይ ችግር ማድረስ መሆኑን፣ ይህም ጥቅም ማቴሪያላዊ /በሰው አካል ወይም ንብረት የደረሠ/ ወይም ሞራላዊ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጎዳ ሰው ደግሞ መካስ እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ የካሣውን አተማመን በተመለከተም መጠኑ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የጉዳት ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ ሲመዘንም በተጎጂው ላይ በእርግጠኝነት መድረሱ የታወቀ /actual damage/ ወይም ወደፊት ሊደርስ የሚችል /future damage/ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የግድ የሚል መሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2090/1/ እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል፡፡ ለእነዚህ ጉዳዮች ካሣ ሊተመን የሚገባ መሆኑን ሕጉ በግልጽ ከማስቀመጡም በተጨማሪ የአተማመኑ ሥርዓትም እንደጉዳቱ ዓይነትና ማስረጃ አቀራረብ ውስብስብና ሊለያይ የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሁኖ በሕጉ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት የጉዳት ካሣ መጠን አጥጋቢና በቂ ማስረጃን  ወይም ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን የካሣ አከፋፈልን ልክ በሚደነግገው የሕጉ ክፍል የተቀመጡ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በሌላ በኩል የካሣ አተማመን ሥርዓት ጠቅላላ የመሥራት አቅም /General utility/ ሣይሆን ልዩ ጠቀሜታ/specific utility/ መርህን ቢከተል ፍትሐዊነት ያለው  አሠራር መሆኑ ይታመናል፡፡ ይህም አሠራር በተጨባጭ የደረሰው ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ የካሣውን ልክ ያላግባብ ከማጋነንና ከመቀነስ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም ጉዳት መድረሱ በማስረጃ ከተረጋገጠና ጉዳቱም በተጎጂው የወደፊት ሕይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሣደሩ እንደማይቀር ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለ መሆኑ ከተረጋገጠ ካሣ መወሰን ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ አኳያ አግባብነት ያለው ነው፡፡ መጠኑን በተመለከተ በሕጉ ለዳኞች በተሰጠው ሥልጣን ወይም በጉዳዩ ላይ በቀረበው ማስረጃ መሠረት በመተመን ለተጎጂው መፍረድ የሚቻልበት ሁኔታ መኖሩን ከላይ ተመልክተናል፡፡ ከዚህ ውጪ ጉዳቱ መድረሱ እየታወቀ የአሁንና የወደፊት ቁሣዊ ጉዳት /material damage/  ስለመኖሩ ተጎጂው አላስረዳም ተብሎ የመካስ መብት ማጣት ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማ ያፈነገጠ ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም የአመልካቾች ልጅ በደረሰባት የመኪና አደጋ በቀኝ እግሯ ላይ መካከለኛ ማነከስ የደረሰባት መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳቱ ወደፊት ሊጠፋ የሚችል ስለመሆኑም የተገለፀ ነገር የለም፡፡ ተጠሪዎች ጉዳት የደረሰባት ሕፃን ትምህርት እየተማረች ትገኛለች በማለት ከመከራከራቸው ውጪ ከጉዳቱ ሙሉ በሙሉ ስለመዳኗ ያስረዱት ነገር የለም፡፡ ስለሆነም በተጎጂዋ ላይ የደረሰው ጉዳት በወደፊት ሕይወቷ አሉታዊ ተጽእኖ ማሣደሩ የማይቀር ስለመሆኑ የነባራዊው ዓለም ሁኔታዎች ያስገነዝቡናል፡፡ በእርግጥ በተጎጂዋ ላይ የወደፊት ሕይወት ጉዳቱ የሚያደርሰውን የካሣ መጠን በትክክል መገመት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ የጉዳት ካሣ መጠኑን በተመለከተ በሕጉ ለዳኞች በተሰጠው ስልጣን መሠረት መተመን የሚቻልበት ሁኔታ ስለመኖሩ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2102 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በልጃቸው ላይ ጉዳት መድረሱን በሚገባ አስረድተው እያለና ይህ ጉዳትም በተጎጂዋ የወደፊት ሕይወት አሉታዊ ተጽእኖ ማሣደሩ የማይቀር መሆኑን በምክንያታዊ እርግጠኝነት ከነባራዊው ዓለም መገንዘብ እየተቻለ፣

እንደዚሁም የካሣ አተማመኑም ርትዕን መሠረት ሊያደርግ የሚገባ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች የአመልቾችን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው ከውል ውጪ አላፊነቱን በተመለከተ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች አጠቃላይ ዓላማም ሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2090፣2091፣2092 እና 2102 ስር የተመለከቱትን መርሆዎች ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1/ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33351 ግንቦት 03 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57181 ታህሣሥ 16 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2/ አመልካቾች በልጃቸው ላይ ጉዳት የደረሰባት ስለመሆኑ በማስረጃ ያረጋገጡ ከመሆኑም በላይ ጉዳቱም በወደፊት ህይወቷ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ (Negative impact) ማሣደሩ እንደማይቀር ምክንያታዊ እርግጠኛነት ያለው ስለመሆኑ ስለተረጋገጠ የካሣ አተማመኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2102 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ በርትዕ ሊወሰን የሚገባው ነው ብለናል፡፡

3/ የካሣ መጠኑን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ከርትዕ አኳያ በመመልከት እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት መልሰናል፡፡

4/ በዚህ ችሎት ትእዛዝ መሠረት ተጠሪዎች ለጉዳት ካሣው በአንድነትና በነጠላ አላፊነት ያለባቸው መሆኑን ተገንዝቦ መጠኑን በመተለከተ ይወስን ዘንድ የውሣኔው ግልባጭ ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ይተላለፍ ብለናል፡፡

5/ በዚህ ችሎት ለተደገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአመስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 34314

ኀዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ግምጃ ጎበና - ጠበቃ እንዳልካቸው ይላቅ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ወንድወሰን ወልዴ - በሌለበት

2. ወ/ሮ ላይላ አህመድ- ወኪል አብዱልቃድር ቀረቡ፡፡

3. አቶ ተስፋዬ ተሾመ - በሌሉበት

4. አቶ ደረሠ ለገሠ - በሌሉበት

5. አቶ ጋሪሣ ዶረራ - በሌሉበት

6. ናይስ ኢንሹራንስ ኩባንያ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከውል ውጪ አላፊነትን መሠረት አድርጎ የቀረበ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች ሟች ልጃቸው አዱኛ ደበሌ ዕድሜው 30 /ሠላሣ/ ዓመት የሆነው መጋቢት 14 ቀን 1995 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት 1፡00 በሚሆንበት ጊዜ የአሁኑ አንደኛ ተጠሪ ንብረት የሆነውና በአሁኑ ሦስተኛ ተጠሪ ይሽከረከር የነበረው መኪና እና የአሁኗ ሁለተኛ ተጠሪ ንብረት የሆነውና በአሁኑ አራተኛ ተጠሪ ይሽከረከር የነበረው፣ በአሁኑ 6ኛ ተጠሪ የመድን ሽፋን የተሰጠው መኪና ባደረሱት ግጭት ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱን፤ በሕይወት እያለም በግብርና ስራ ተሠማርቶ በዓመት የተለያዩ ሠብሎችን በማምረት ገቢ ያገኝ እንደነበር፤ በዚህ ገቢውም አመልካችን ይረዳቸውና ያስተዳድራቸው የነበረ መሆኑን ዘርዝረው የመኪናዎቹ ባለንብረቶችና አሽከርካሪዎች ለሟች መሞት አላፊ ተብለው ሟች ወደፊት ለ10 /አስር/ ዓመታት ቢኖር ያገኝ ነበር ብለው ያሠሉትን ብር 104000.00 /አንድ መቶ አራት ሺህ ብር/ የተቋረጠ ጥቅም፣ ከዳኝነትና ጠበቃ አበል ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ጥቅምት 02 ቀን 1996 ዓ.ም. በተፃፈ የክስ ማመልከቻ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ በፍ/ቤቱ ጥሪ መሠረት ተከሣሾች ቀርበውም አለን ያሉትን የመከራከሪያ ነጥብ አቅርበዋል፡፡ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ የተጠየቁ ተከራካሪዎችም ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር በአላፊነትና በጉዳት ካሣ መጠን ክርክር ላይ በተለያዩ የክርክር ደረጃዎች ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አላፊነትን በተመለከተ ውሣኔ የተሰጠው መጋቢት 20 ቀን 1998 ዓ.ም. ሲሆን በዚህ ጊዜም የአሁኑ አንደኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ለጉዳቱ አላፊነት የሌለባቸው መሆኑ ተገልፆ በነፃ ሲሰናበቱ የአሁኑ አንደኛ እና አራተኛ ተጠሪዎች ግን ለጉዳቱ አላፊነት አለባቸው ተብለው የጉዳት ካሣ መጠኑን በተመለከተ የአመልካች ምስክሮች ተሠምተዋል፡፡ ከዚህም በኂላ የአመልካች ምስክሮች ቃል በጉዳዩ ላይ ከቀረበው ክርክር አንጻር መመርመሩ ተገልፆ አመልካች ሟች ልጃቸው ምን ያሕል ይረዳቸው እንደነበረ ያላስረዱና ወደፊት ሊኖሩ የሚችሉት ዕድሜም ምን ያሕል እንደሆነ አልገለፁም የሚል ምክንያት መሠረት ተደርጎ የካሣ ጥያቄውን የስር ፍ/ቤት ውድቅ አድርጎ

ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኗ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ይኸው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥቅምት 12 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ አመልካች ከሟች ልጃቸው ጋር እየኖሩ ይጦሩ እንደነበር ተረጋግጦ እያለ አመልካች ምን ያሕል ዓመት ወደፊት እንደሚኖሩ ዕድሜአቸውን ገልፀው አልቀረቡም ተብሎ የካሣ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ተቀባይነት የሌለው ምክንያት መሆኑንና ሟች ከናዝሬት ወደ አዲስ አበባ ተሣፍሮ ይጓዝበት የነበረው የአንደኛ ተጠሪ መኪና በሆነው በሦስተኛ ተጠሪ ይሽከረከር በነበረው ሆኖ እያለ ተገቢው ውሣኔ ሣይሰጥ መታለፉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሮ በስር ፍ/ቤት የተጠየቀውን የመተዳደሪያና የመጦሪያ ካሣ ገንዘብ ተጠሪዎች ባልተነጣጠለ አላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት አንደኛ፣ ሦስተኛ እና አምስተኛ ተጠሪዎች በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን 4ኛ ተጠሪም የፍ/ቤቱን መጥሪያ ተቀብለው ያልቀረቡ መሆኑ ስለተረጋገጠ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ 2ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች ግን ቀርበው ጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የሟች ሕይወት ያለፈው በሁለተኛ ተጠሪ መኪና ተሣፍሮ ሲሄድ ባለመሆኑ አላፊነቱ የአጓጓዥ እንጂ የሁለተኛ ተጠሪ ባለመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊሆን እንደሚገባ፣ ይህ የሚታለፍ ከሆነም አመልካች በስር ፍ/ቤት በልጃቸው ሞት ምክንያት የተቋረጠባቸው ገቢ መኖሩን ገልፀው ያላቀረቡና በሰውም ማስረጃ አስደግፈው ያላቀረቡ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ ውሣኔው ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው መጋቢት 03 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ ይዘትና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች በልጃቸው ሞት ምክንያት ተቋርጧል ያሉትን ጥቅም ሊያገኙ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በክርክሩ ሂደት ለሟች ሕይወት ማለፍ አላፊነት አለባቸው ተብሎ ውሣኔ ያረፈባቸው ወገኖች የአሁኑ ሁለተኛ እና አራተኛ ተጠሪዎች ናቸው፡፡ የአሁኑ አንደኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ለጉዳቱ አላፊነት የለባቸውም ተብሎ መጋቢት 20 ቀን 1998 ዓ.ም. ውሣኔ መስጠቱን የስር ፍ/ቤት የውሣኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም በአመልካች የሰበር አቤቱታ በአንደኛ እና በሦስተኛ ተጠሪዎች ላይ የስር ፍ/ቤት ተገቢውን ውሣኔ ሣይሰጥ አልፏል ተብሎ የቀረበው ቅሬታ እውነትነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ሥነ ሥርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው ብለናል፡፡

በሌላ በኩል የአሁኑ ስድስተኛ ተጠሪ ለሟች ሕይወት ማለፍ አላፊነት ያለበት አጓጓዡ እንጂ ሁለተኛ ተጠሪ ናቸው ሊባል አይገባም በማለት ያቀረበው የሰበር መከራከሪያ ነጥብ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ከውል ውጪ አላፊነትን በሚመለከት ሕግ ተመልክቶ ለአደጋው አላፊነት የሚወስዱት የአሁኑ ሁለተኛ እና አራተኛ ተጠሪዎች ናቸው በማለት ውሣኔ የሰጠበት እና በበላይ ፍ/ቤትም የተለወጠ ካለመሆኑም በላይ በይዘቱ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በመሆኑ የስድስተኛ ተጠሪ ክርክር በሰበር ችሎቱ የሚስተናገድበት ሥርዓት አልተገኘም፡፡

በመቀጠል የስር ፍ/ቤት ሁለተኛ እና አራተኛ ተጠሪዎች ለሟች ሕይወት ማለፍ አላፊ ናቸው ካለ በኂላ፣ የአመልካችን የጉዳት ካሣ ጥያቄ ውድቅ የማድረጉን አግባብነት መመልከቱ የግድ ይሏል፡፡ ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው በአመልካች በኩል የቀረቡት ሁለት ምስክሮች ሟች የአመልካች ልጅ መሆኑን፣ በግብርና ሥራ ይተዳደር እንደነበር፣ በዓመት ከአርባ እስከ ሃምሣ ኩንታል እህል ያመርት እንደነበር፣ አትክልት በማልማት ደግሞ በዓመት እስከ ብር 10,000.00 /አስር ሺህ ብር/ ያገኝ እንደነበር፣ ልጅና ሚስት ያልነበረውና 6/ስድስት/ ቤተሰብ ያስተዳድር የነበረ ስለመሆኑ መመስከራቸውን ነው፡፡ ከዚህም በላይ የአመልካች ልጅ የሆነው ሟች አመልካችን በቤቱ ውስጥ ይዞአቸው ይጦራቸው እንደነበር በአመልካች በኩል የቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ ይጠቁማል፡፡ ይህንኑ የአመልካችን ማስረጃ ተጠሪዎች ለማስተባበል ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በሟች ልጃቸው እርዳታ ይጦሩ የነበሩ ስለመሆኑ ከተጠሪዎች በተሻለ

ሁኔታ አስረድተዋል፡፡ ጉዳዩ የፍትሐብሔር እንደመሆኑ መጠንም የማስረጃ ምዘናው የትኛው ተከራካሪ ወገን የተሻለ ማስረጃ አቅርቧል? የሚለው መመዘኛ መሠረት ተደርጎ የሚስተናገድ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የስር ፍ/ቤት የማስረጃ ምዘናም መርሁን ያላገናዘበ ነው፡፡

አመልካች በሟች ልጃቸው ስር ይተዳደሩ የነበሩና ሟች ልጃቸውም ገቢ የነበረው ስለመሆኑ ካስረዱ ደግሞ የራሣቸውን የወደፊት ዕድሜ በማመልከቻቸው አለመጥቀሣቸውና ሟች በትክክል ይሰጣቸው የነበረው የመጦሪያ ገንዘብ መጠን አለመታወቁ የጉዳት ካሣ ጥያቄአቸውን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል የሕግ መሠረት የሌለው ምክንያት ነው፡፡ ይልቁንም አመልካች ልጃቸው ገቢ የነበረውና በስሩ አድርጎ ያስተዳድራቸው የነበረ መሆኑን ማስረዳታቸው የጉዳት ካሣ መጠኑን በርትዕ ለመወሰን መነሻ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ የጉዳት ካሣ መጠኑን በተመለከተ በርትዕ መተመን የሚቻልበት ሁኔታ ስለመኖሩም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2102 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የጉዳት ካሣ መጠኑን በሕጉ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መተመን እየቻለ አመልካች በማስረጃ አላስረዱም በማለት ጥያቄአቸውን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ማድረጉ ከውል ውጪ አላፊነቱን በተመለከተ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች አጠቃላይ ዓላማም ሆነ የካሣ አተማመኑን በተመለከተ በሕጉ የተቀረጹትን ሥርዓቶች ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33149 መስከረም 29 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 49878 ጥቅምት 08 ቀን 2000 ዓ.ም. በፀናው ውሣኔ የአመልካችን የጉዳት ካሣ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው የውሣኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ሁለተኛ ተጠሪ በተሽከርካሪ ባለቤትነታቸው፣ አራተኛ ተጠሪ በአሽከርካሪነታቸው፣ ስድስተኛ ተጠሪ ደግሞ ለተሽከርካሪው በሰጠው የመድን ሽፋን ዋስትና መሠረት በአመልካች ላይ በልጃቸው መሞት ምክንያት ለተቋረጠው የመተዳደሪያ ገቢ ባልተነጣጠለ ሁኔታ አላፊነት አለባቸው ብለናል፡፡
3. የስድስተኛ ተጠሪ የአላፊነት መጠን በመድን ዋስትና ውሉ የተመለከተውን ያሕል ነው ብለናል፡፡
4. አንደኛ፣ ሦስተኛ እና አምስተኛ ተጠሪዎችን በተመለከተ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
5. በአመልካች ላይ የደረሰው የጉዳት ካሣ መጠን በርትዕ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ ስለተገኘ ብር 25,000.00 /ሃያ አምስት ሺህ ብር/ ሁለተኛ፣ አራተኛ እና ስድስትኛ ተጠሪዎች ለአመልካች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ብለናል፡፡
6. በዚህ ጉዳይ ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
7. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

ሰ/መ/ቁ. 31704

ጥር 29 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ አማረ መጃ - ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** የድሬዳዋ ለጋር ጉምሩክ - ነ/ፈጅ አቶ ታደሰ ጎለንዴ ቀርበዋል

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 02 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግንቦት 10 ቀን 1999 ዓ.ም በፍ/ይ/መ/ቁ. 24665 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይሻርልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የድሬዳዋ ምድብ ችሎት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሣሽ የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ስር ከሣሹ ሐምሌ 21 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ ክስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም የሰሌዳ ቁጥሯ 3-05884 የሆነች ኢሮቶዮታ መኪናዬ ኮንትሮባንድ ጭናለች በሚል ምክንያት ታህሣሥ 09 ቀን 1996 ዓ.ም ተከሣሹ በድሬዳዋ ከተማ በቁጥጥር ስር አውሏት ስትፈተሽ አንድ ቦንዳና 10 ሜትር ብትን የመጋረጃ ጨርቅ ጭና ስለተገኘች መኪናዋ ልትለቀቅልኝ ባለመቻሏ ባቀረብኩት አቤቱታ መነሻነት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በየደረጃው ያሉት ኃላፊዎች ለተያዘው ዕቃ ሊከፈል የሚገባው 36.83 ብር የጉምሩክ ቀረጥ ተመን ተከፍሎ መኪናዋ እንዲለቅ በተደጋጋሚ ደብዳቤ ለተከሣሹ ቢጽፍለትም ሊለቅልኝ አልቻለም፤በመሆኑም ከመኪናዋ አገኝ የነበረው በቀን ብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ ሂሣብ ሆኖ ከታህሣሥ 09 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ሰኔ 16 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ ያለውን የተቋረጠ ገቢ ብር 608,000 /ስድስት መቶ ስምንት ሺህ ብር/ ከነወለዱ ይከፈለኝ የሚል ነው፡፡

ስር ተከሣሹ በ23/02/1998 ዓ.ም በተፃፈ መልሱ መኪናው መስከረም 04 ቀን 1998 ዓ.ም ተለቋል፤ መኪናዋን የያዝኩት በአዋጅ ቁጥር 60/1989 ዓንቀጽ 6 በተሰጠኝ ስልጣን መሠረት ነው፡፡ በመኪናዋ ከተጫነው 190 ጣቃ ጨርቅ 10 ሜትር የመጋረጃ ጨርቅ አደባልቆ በራሱ እየነዳ ነው በቁጥጥር ስር የዋለችው፤ የመጨረሻ ውሣኔ እስኪያገኝ ድረስ መኪናዋን በቁጥጥር ስር አውሎ ማቆየት ሕግ ይፈቅድልኛል፤ በተለይም የጉምሩክ ባለሥልጣን ባወጣው መመሪያ ሲያሽከረክር የተገኘው የመኪናው ባለቤት ከሆነ የመጨረሻ የፍ/ቤት ውሣኔ ይጠብቃል ይላል፤ ስለሆነም መኪናው በሕግ አግባብ የተያዘ ነው ብሏል፡፡

የስር ፍ/ቤቱም በመ/ቁ. 01735 መጋቢት 20 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ተከሣሹ መኪናዋን እንዲለቅ በተደጋጋሚ ከበላይ የመዋቅሩ አካላት ደብዳቤ በተደጋጋሚ እየተፃፈለት እምቢተኛ ሆኖ ከሣሽን ለኪሣራ የዳረገ በመሆኑ ከ11/06/96 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 21 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ ያለውን የመኪናዋን የተቋረጠ ገቢ ከሣሹ ለመንግሥት ሪፖርት ባደረጉት ብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ ብር/ ሂሣብ ብር 36,111.11 /ሰላሣ ስድስት ሺህ አንድ መቶ አስራ አንድ ብር ከአስራ አንድ ሣንቲም/ ሊከፍላቸው ይገባል ብሏል፡፡

ክርክሩ በይግባኝ ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ ፍ/ቤቱ በፍ/ይ/መ/ቁ. 24665 ግንቦት 10/1999 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ አዋጅ ቁጥር 60/89 ዓንቀጽ 6 እና 58 መሠረት ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ ኮንትሮባንድ ጭኖ የተያዘን መኪና ይ/ባይ በቁጥጥሩ ስር አድርጎ የማቆየት ስልጣን ስላለው ካሣ ክፈል ሊባል አይገባም በማለት ከላይ የተጠቀሰውን የከፍተኛ ፍ/ቤቱ ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/መሠረት ሽሮታል፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት፣ ይግባኝ ችሎት ውሣኔ በመቃወም አመልካች ሐምሌ 02 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም መኪናዋ በክሱ የተመለከተውን ሕጋዊ ያልሆነ እቃ ጭና የተያዘችው የመኪናው ባለቤት የሆንኩት እያሽከረከርኩ እያለሁ አይደለም፤ ሌላ ሹፌር ነበር ሲያሽከረክራት የነበረው፤ ሕጋዊ ያልሆነ ወይም ኮንትሮባንድ ነው የሚባል እቃ የተጫነበት መኪና ተይዞ እንዲቆም የሚደረገው አሽከርካሪው የመኪናው ባለንብረት ሲሆን ነው፤ ለዚህም የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በቁጥር 10/መ352/201/18/123 በ18/08/1996 ዓ.ም ግልጽ መመሪያ ያስተላለፈበት ነው፤ መኪናው እንዲለቅ ተደጋጋሚ ትእዛዝ ተጽፎለት እያለ ተጠሪ መኪናዋ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ገቢዬ አላግባብ እንዲቋረጥ አድርጓል፤ይሁን እና ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከዚህ ነጥብ አኳያ እንደማጤን ተጠሪው በአዋጅ ቁጥር 60/89 ዓንቀጽ 6 እና 58 መሠረት የመኪናዋን በቁጥጥር ስር የማዋልና ችግሩ እልባት እስኪያገኝ ድረስ በቁጥጥር ስር አድርጎ ማቆየት ይችላል ብሎ ፍርድ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ሊሻርልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

ተጠሪም ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም አመልካች መኪናው በሌላ ሹፌር ይሽከረከር ነበር ከማለት ውጭ የዛ ሹፌር ማንነት በስር ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አልጠቀሱም መኪናው ሲያሽከረክሩ የነበሩት ራሣቸው አመልካች ናቸው፤ ኮንትሮባንድ ጭኖ የተገኘን መኪና ችግሩ እልባት እስኪያገኝ ድረስ በቁጥጥር ስር አድርጌ ማቆየት እንደምችል አዋጅ ቁጥር 60/89 ዓንቀጽ 6/5/፣ 58/1/ለ/፣61 እና 78 ይፈቅድልኛል፤ መኪናዋ ኮንትሮባንድ ጭና መገኘቷ አያከራክርም፤ ስለሆነም የጠቅላይ ፍ/ቤት የፈፀመው የሕግ ስህተት ስለሌለ ፍርዱ ይጽናልኝ የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እየተገለፀ እንደመጣው ሆኖ ይህ ፍርድ ቤትም ተጠሪው የአመልካችን መኪና ይዞ በማቆየቱ የተቋረጠ ገቢ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚል መሠረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክር አመጣጥ መረዳት የሚቻለው የአመልካቹ መኪና በሕጋዊ መንገድ ጭናው ከነበር 190 ጣቃ ጨርቅ ውስጥ አንድ ቦንዳና 10 ሜትር ብትን የመጋረጃ ጨርቅ ሕግን ባልተከተለ መንገድ ተደብቆ እንደተገኘና በዚህ ምክንያም መኪናዋ በተጠሪ በቁጥጥር ስር እንደዋለች ነው በወቅቱ መኪናዋ በአመልካች ሣይሆን በሌላ ሾፌር ትሽከረከር እንደነበር ነው፡፡ በግራና ቀኙ ክርክር ጉዳይ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ለውሣኔያቸው መሠረት ያደረጉት ጭብጥ ልዩነት ያለው ይመስላል የሸውም የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ አስተሳሰብ በኮንትሮባንድ ጭና የተገኘት መኪና በአዋጅ ቁጥር 60/89 መሠረት በቁጥጥር ማዋልና ችግሩ መፍትሄ እስኪያገኝ ድረስ ይዞ ማቆየት አይቻልም የሚል አይደለም፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በውሣኔው ያስመረበት መሠረታዊ ነገር መኪናዋ በሌላ ሾፌር ስትሽከረከር ከላይ የተጠቀሱት ንብረቶች ይዛ መገኘቷ ታውቆ መኪናዋ መለቀቅ እንዳለባት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን የበላይ አመራሮች ወደ ተጠሪው በተደጋጋሚ ደብዳቤዎች ጽፈው እያለ /በቁ.ዘ40/ቀ64/640/05/15 መጋቢት 09/1996፣ በቁ.ዘ30/ቀ64-16/06 መስከረም 28/1997 ዓ.ም፣ በቁጥር ዘ40/ቀ 64-6/03 ነሐሴ 27/1997 ዓ.ም/ ተጠሪው ይህንን ትእዛዝ ወደጎን በመተው የአመልካችን መኪና ጉዳዩን ለማጣራት ከሚገባው ጊዜ በላይ በቁጥጥር ስር አውሎ አመልካችን ለተጨማሪ ወጪ ዳርጓል የሚል ሲሆን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ውሣኔ ደግሞ ከላይ የተመለከተውን የደብዳቤዎች ልውውጥ ግምት ውስጥ ባለማስገባት በአጠቃላይ በኮንትሮባንድ የተጠረጠረች መኪና በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ የማቆየት ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 60/1989 መሠረት ያለው መሆኑን ነው፡፡ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የጠቀሰው አሰራር በሕጉ የተመለከተ ሃቅ ቢሆንም ሁኔታውን በሚባ ተገንዝቦና የጉምሩክ መመሪያን መሠረት በማድረግ የባለስልጣኑ የበላይ አመራሮች መኪናዋ በወቅቱ ትሽከረከር የነበረው በሌላ ሹፌር እንጂ የመኪናዋ ባለቤት በሆኑት በአመልካች ባለመሆኗ በአስቸኳይ እንድትለቀቅ በተደጋጋሚ እያዘዙት ተጠሪው መኪናዋን በወቅቱ ወይም ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ ሣይለቅ በቀረበት ሁኔታ ከላይ የተጠቀሰው አዋጅ የያዘው ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ነው ማለቱ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በተጠሪው ጥፋት ምክንያት በአመልካቹ ላይ የገቢ መቋረጥ ሲደርስ አዋጅ ቁጥር 60/1989 ሽፋን በማድረግ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተጠሪው ያቀረበው ክርክር መሠረት ያለው አይደለም፤ አዋጁ የጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች ወይም ቅርንጫፎቻቸው

በጥፋታቸው ምክንያት በባለንብረቶች ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት ተጠያቂ እንዳይሆኑ ሽፋን የመስጠት ዓላማ የለውም፤ ስለሆነም በአሁኑ ጉዳይ መኪናዋ ስትሽከረከር የነበረው በሹፌር እንጂ በአመልካቹ አለመሆኗ ተገልፆለትና እንዲህ በሆነ ጊዜም መኪናዋ በቁጥጥር ስር አድርጎ ለረጅም ጊዜ ማቆየት በጉምሩክ መመሪያ መሠረት እንደማይፈቀድ ተጠሪው በግልጽ እያወቀ ሆን ብሎ መኪናዋን አለቅም በማለት በአመልካቹ ላይ ጉዳት ማድረሱ የተረጋገጠ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2028፣2031/1/ መሠረት ለደረሰው የገቢ መቋረጥ ጉዳት ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ተጠሪው በተጠቀሰው አዋጅ መሠረት መኪናዋን በቁጥጥር ሥር አውሎ የማቆየት ስልጣን ስላለው ሊጠየቅ አይገባም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፤ ሥለሆነም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 24665፣ ግንቦት 10/1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፤ ይፃፍ፡፡

2/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የድሬዳዋ ምድብ ችሎት በመ.ቁ. 01735፣ መጋቢት 20 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፤ ይፃፍ፡፡

3/ ተጠሪው ጥፋት መፈፀሙ ስለተረጋገጠ በአመልካቹ ላይ ለደረሰው የገቢ መቋረጥ ኃላፊነት አለበት፤ ሥለሆነም ብር 36,111.11 /ሰላሣ ስድስት ሺህ አንድ መቶ አስራ አንድ ብር ከአስራ አንድ ሣንቲም/ ለአመልካቹ ይክፈል ብለናል፡፡

4/ ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ችሎት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

ጉዳዩ በውሣኔ የተቋጨ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ/ወ

የሰ/መ/ቁ 38457

ሰኔ 2 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን - ነ/ፈጅ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ተመኘሁ እንደሻው - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በመኪና አደጋ ደረሰ የተባለውን ጉዳት መሠረት በማድረግ የተጠየቀውን የካሣ ክፍያ ጥያቄ /ክርክር/ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በአመልካች ሹፌር ሲሽከረከር በነበረው መኪናው ተሳፍሬ ስጓዝ በነበረበት ጊዜ መኪናው በመገልበጡ በእግሬ ላይ ጉዳት ደርሶአል፡፡ ስለዚህ ካሣ ይከፍለኝ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ መኪናው ለመንግስት ሥራ የተሰማራ እንጂ ሰዎችን ለማጓጓዝ የተዘጋጀ የንግድ መኪና አይደለም፡፡ ከሣሽ በመኪናው ላይ የተሳፈረው ያለአግባብ እና ለከሣሽ ጥቅም በማይሰጥ ሁኔታ ስለሆነ በሕግ ረገድ ኃላፊነት የለብኝም በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም አመልካች ለደረሰው ጉዳት ሃላፊነት አለበት በማለት ካሣ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሰኔ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በተጠሪው ላይ ለደረሰው ጉዳት አመልካች ኃላፊ ነው የተባለበትን አግባብ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2089(1) አንፃር ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ሊመረመር እና ትርጉም ሊሰጠው የተፈለገው ሕግ የፍ/ብ/ሕግ ቁ 2089(1) የሚገኘው ከውል ውጪ ስለሚደርስ አላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልፀግ በሚለው በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 13 ሥር ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችን የከሰሰውም ከውል ውጪ ደረሰ የሚለውን ኃላፊነት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በስር ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ እንደተረጋገጠው ተጠሪ የተባለውን ጉዳት የደረሰበት በአመልካች መኪና በመገጨቱ ሳይሆን፣ በመኪናው ላይ ተሳፍሮ ሲሄድ መኪናው በመገልበጡ ምክንያት ነው፡፡ በእርግጥ መኪናው የአመልካች ንብረት ነው፡፡ ሆኖም ለመንግስት ሥራ የተሰማራ እንጂ ገንዘብ በማስከፈል ሰዎችን የሚያጓጉዝ የንግድ መኪና አይደለም፡፡ ተጠሪ በመኪናው ስለመሳፈሩ እንኳን አመልካች አያውቅም፡፡ ተጠሪን በማሳፈር ያገኘው ጥቅምም የለም፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ እነዚህን ሁኔታዎች ከተረጋገጡ ቀጥሎ መታየት ያለበት አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ የሚሆንበት የሕግ አግባብ አለ ወይስ የለም የሚለው ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕግ ቁ 2081(1) እንደተደነገገው የመኪናው ባለቤት መኪናው በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ የሚሆንበት አግባብ አለ፡፡ ይህ እንግዲህ በአጠቃላይ የተቀመጠ የኃላፊነት መርህ ሲሆን፣ በቁጥር 2089 ደግሞ ልዩ ሁኔታ ማለትም የመኪናው ባለቤት ኃላፊ የማይሆንበትን ሁኔታ ተደንግጎአል፡፡ ከድንጋጌው ርእስ መገንዘብ እንደሚቻለው

ጉዳቱ የደረሰው ጥቅም በሌለው ግንኙነት ጊዜ ሲሆን፣ የመኪናው ወይም ጉዳቱን ያደረሰው ንብረት ባለቤት ኃላፊነት አይኖርበትም። ከላይ እንዳመለከትነው ተጠሪ በአመልካች መኪና የተገለገለው ለአመልካች ጥቅም በማያስገኝ ሁኔታ ነው። ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካች በዚህ ረገድ ጥፋት ፈጽሞአል አልተባለም። በመሆኑም አመልካች ኃላፊ የሚሆንበት የሕግ አግባብ የለም። የስር ፍ/ቤቶችም በዚህ አግባብ ሕጉን ባለመተርጐማቸው የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል።

## ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መ የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 03066 ህዳር 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 63179 ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል።
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊነት የለበትም ብለናል። ስለዚህም በሥር ፍ/ቤቶች የተወሰነውን ካሣ አይከፍልም በማለት ወስነናል።
3. ወጪና ኪሣራ በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ። መዝገቡ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ራ/ታ

# የዳኝነት ሥልጣን

የሰ/መ/ቁ. 35657

ጥቅምት 06 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች፡-** እነ ወ/ሮ እመቤት መክብብ - ጠበቃ አስቴር አርአያ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ በድሉ መክብብ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ አመልካች፣የአሁኑ አመልካቾችና ወ/ሮ አልታየወርቅ መክብብ ደግሞ ተጠሪዎች ነበሩ፡፡

የስር አመልካች አቤቱታ ይዘት ሲታይም የሟች ወንድማቸው የአቶ መሉጌታ መክብብ ተተኪ ወራሽ መሆናቸውን፣ ከስር ተጠሪዎች ጋር በመሆን የውርስ ሐብቱን ለማጣራት ቢፈልጉም ተጠሪዎች ፈቃደኛ ሆነው ውርሱን ለማጣራት ያልቻሉ መሆናቸውን በመግለጽ ውርሱ ይጣራ ዘንድ ፍ/ቤቱ የውርስ አጣሪ እንዲሾምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚገልጽ ነው፡፡ የስር ተጠሪዎችም በፍ/ቤቱ ጥሪ መሰረት ቀርበው ፍ/ቤቱ የውርስ አጣሪ ለመሾም በሕግ የተሰጠ ስልጣን የሌለው መሆኑን፤ የውርስ አጣሪን መሾም የማያስፈልግ መሆኑን የሚያሣዩ ምክንያቶች መኖራቸውን በመዘርዘር የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊሆን እንደሚገባ ተከራክረዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የስር ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር በማድመጥ እና አግባብነት አላቸው ያላቸውን ጭብጦች በመመስረት ፍ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41(1)(ሸ) መሰረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን እንዳለው በመዘርዘር የተጠሪዎችን ተቃውሞ ካለፈ በኋላ የውርስ አጣሪ በመሾም የውርስ ሐብቱ ተጣርቶ ሪፖርቱ ሊቀርብ ይገባል በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች በዚህ የስር ፍ/ቤት ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን እና የሰበር አቤቱታቸውን እንደየቅደም ተከተሉ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሣያገኙ ቀርተዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍ/ቤቶች ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

አመልካቾች የካቲት 12 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የቅሬታ ነጥቦችንና በበታች ፍ/ቤቶች ተፈፀሙ ያሏቸውን የህግ ስህተቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአዋጁ የተሰጠው ስልጣን የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለመስጠት እንጂ ውርስ አጣሪ ለመሾም አይደለም፤ የሚልና የውርስ አጣሪ መሾም ለጉዳዩ አስፈላጊ አለመሆኑን በመዘርዘር የበታች ፍ/ቤቶች ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ተብሎ በሰበር ችሎቱ ተሽሮ በቂ ወጪና ኪሣራ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮም የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የውርስ ክርክርን አስመልክቶ በቀረበ ጉዳይ ላይ የውርስ አጣሪ የመሾም ስልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ ተጠሪ እንዲቀርቡና መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት በሕግ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን በመዘርዘር የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ ሆኖ የበታች ፍ/ቤቶች ትእዛዝ ሊፀና ይገባል በማለት

መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካቾች የተጠሪ መልስ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመጥቀስና የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ ከሕጉ ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 39 ስር የከተማው አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶችና የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች የሚኖሩት ስለመሆኑ፤ በአዋጁ አንቀጽ 41 መሰረትም የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን መዘርዘሩን ተገንዝበናል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 41(1)(ሸ) ድንጋጌም የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታን የማየት የዳኝነት ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን መሆኑን በማያሻማና ግልጽ በሆነ ቋንቋ ይገልፃል፡፡ የስር ፍ/ቤት የውርስ አጣሪን የመሾም ስልጣን አለኝ ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ከላይ የተጠቀሰውን አዋጅና የፍ/ብ/ሕ/ቁ.996/1/ ድንጋጌን መሰረት በማድረግ የውርስ ሐብቱ ሣይጣራ የወራሽነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላይ የወራሽ ድርሻ ሊገለጽ አይችልም በሚል ምክንያት ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ትርጓሜ አዋጁ ላይ የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ ከመሆኑ እና የወራሽነት የምስክር ወረቀት ከውርስ ማጣራት ሂደት ጋር ተያያዥነት ያለው ቢሆንም ሊያስነሣ ከሚችላቸው ሕጋዊ ክርክሮች አኳያ ሲታይ ከውርስ ማጣራት ሂደት ያነሰ የውስብስብነት ባሕርይ ያለው መሆኑን ያላገናዘበ ነው፡፡

በመሰረቱ የተፃፈ ሕግ የሚተረጐመው ግልጽነት ሲጐድለው ነው፡፡ ህጉ ግልጽ በሆነበት ሁኔታ ግን ትርጉም አላስፈላጊ ስለመሆኑ የሕግ አተረጓጐም መርሆዎች ያስገነዝቡናል፡፡ ግልጽ ህግን መተርጐም ፍ/ቤት በትርጉም ሰበብ የሕግ አውጪውን ስልጣን ተክቶ እንደሰራ የሚያስቆጥር ነው፡፡ ስለሆነም የወራሽነት የምስክር ወረቀት የማግኘትና የውርስ ማጣራት ሂደት ሁለት የተለያዩ ሂደቶች መሆናቸው እየታወቀ፣ ህግ አውጪውም የምስክር ወረቀት የማግኘት አቤቱታን በሚመለከት ብቻ ለአስተዳደሩ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን በግልጽ ለይቶ ሰጥቶ እያለ፣ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ማግኘትና የውርስ ማጣራት ተያያዥነት አላቸው በሚል ምክንያት ብቻ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ማየቱ የሕግ አተረጓጐም መርህን በተከተለ መንገድ ሣይሆን ይህንኑ ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 678/99 የካቲት 08 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ በአስተዳደሩ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 04083 ሐምሌ 12 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት፣እንዲሁም በአስተዳደሩ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 04951 ጥር 16 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት በትእዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41(1(ሸ)) መሰረት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታን በተመለከተ እንጂ የውርስ አጣሪ የመሾም የዳኝነት ስልጣን አይደለም ብለናል፡፡
3. በአዲስ አበባ መስተዳድር ውስጥ የውርስ አጣሪ ይሾምልኝ ጥያቄ የማየት የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

## ልዩነት ውሣኔ

እኔ ስሜ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫው ድምጽ በሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ ባለመስማማት በሚከተለውን በልዩነት ወስኛለሁ፡፡

1. በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 ንኡስ አንቀጽ 1(ሸ) የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታን መርምሮ የመወሰን ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ

ቤቶች መሆኑ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በፍርድ ቤት የሚሰጥ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ወይም ማረጋገጫ ወራሽ የሆነው ሰው ለሟች ወራሽ መሆኑንና ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ የሚያመለክት እንደሚሆን በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 996/1/ ድንጋጌ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የወራሽነት የምስክር ወረቀት ወይም ማረጋገጫ ለመስጠት ሁለት መሰረታዊ ነገሮችን ማጣራት አለባቸው፡፡ የመጀመሪያው አቤቱታ አቅራቢው የሟች የኑዛዜ ወይም ያለኑዛዜ ወራሽ መሆኑን ማጣራት ሲሆን 2ኛው የሟች የውርስ ንብረት ምን እንደሆነና ወራሽ ድርሻ ያለው መሆኑን የድርሻውንም መጠን ማጣራት አለባቸው፡፡ ይህንን ለማድረግ የውርስ አጣሪ መሾም የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የውርስ አጣሪ የመሾም ስልጣን ያላቸው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41/1/ሽ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 996 ንኡስ አንቀጽ 1 ጋር አጣምሮ በመተርጐም ለመረዳት ስለሚቻል የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ውርስ አጣሪ የመሾም ስልጣን የላቸውም መባሉ ተገቢ አይደለም የሚል እምነት አለኝ፡፡

2. ውርስ አጣሪ የመሾም ጉዳይ በራሱ እንደ ትልቅ ነገር የሚታይና የሥረ ነገር ስልጣኑ የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ነው ወይም የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚለውን ክርክር የሚያስነሣ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የፍትሀብሔር ህጉ የሟች ውርስ የማጣራት ስልጣን ያላቸውን ግለሰቦች በቅደም ተከተል የሚዘረዝር ሲሆን እነርሱም፡-
   - ሟች በኑዛዜ የውርስ አጣሪ ሆኖ ውርሱን እንዲያጣራ የሾመው ሰው ካለ በመጀመሪያ የውርስ አጣሪ እንደሆነ የፍትሀብሔር ህጉ 948/1/ የሚደነግግ ሲሆን፣
   - ሟች በውርስ አጣሪነት በኑዛዜ የሾመው ሰው ከሌለ ጠቅላላ የኑዛዜ ተቀባይ የሆነው ሰው የሟችን ውርስ የማጣራት ስልጣን እንዳለው የፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር አንቀጽ 948 ንኡስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡
   - ሟች በኑዛዜ የመረጠው የውርስ አጣሪ ወይም ጠቅላላ የኑዛዜ ተቀባይ የሌለ በሆነ ጊዜ ሁሉ የሟች ያለ ኑዛዜ ወራሾች ያላንዳች ፎርማሊቲ የውርስ አጣሪነት ስልጣን እንዳላቸው በፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 947 ተደንግጓል፡፡

በፍርድ ቤት የውርስ አጣሪ የሚሾመው የሟች ወራሾች የማይታወቁ ሲሆን ወይም የሟች ወራሾች ውርሱን ለማጣራት ፈቃደኛ በማይሆኑበት ጊዜ እንደሆነ ከፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 850 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ይህንን ሕጉ በቅደም ተከተል ያስቀመጣቸውን ነገሮች የሚፈጽም የውርስ አጣሪ የመሰየም ስልጣን የወራሽነት አቤቱታን ተቀብሎ የማስተናገድ ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የሚፈጽሙት እንጂ የተለየ አቤቱታና ክስ ቀርቦበት ውሣኔ የሚሰጥበት ራሱን የቻለ የዳኝነትና የሥረ ነገር ስልጣን የሚጠይቅ ጉዳይ ተደርጐ መታየት የለበትም፡፡ ውርስ ማጣራትና የውርስ ንብረት መካፈል የተለያዩ ሒደቶች እንደሆኑ በጥልቀት ሊታይ ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

3. ሕግ አውጭው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታን መርምሮ የመወሰን ስልጣን ለከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ሲሰጥ ሰዎች የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ከተማ ነክ ፍርድ ቤት፣ የውርሱ ንብረት እንዲጣራላቸው ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አንድ ላይ ሊታይና ሊፈፀም የሚችለውን ጉዳይ ከተለያዩ ሁለት ፍርድ ቤቶች እንዲጠይቁና አገልግሎት እንዲያገኙ በማሰብ ነው ብሎ ለመደምደም አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም አዋጅ ቁጥር 361/1995 በሚወጣበት ጊዜ መንግስት በፖሊሲ ደረጃና የተለያዩ የማሻሻያ ፕሮንራሞችን በመንደፍ ሰዎች አንድን ጉዳይ የሚመለከት ማናቸውም አገለግሎት ከአንድ መስሪያ ቤት በተቀላጠፈ መንገድ የሚያገኙበትን ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ በሚንቀሣቀስበት ወቅት ነው፡፡ ስለሆነም ከዚህ የመንግስት ፖሊሲና የማሻሻያ ፕሮግራም አንጻር የአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41/1/ሽ/ ድንጋጌ መታየትና መተርጐም ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ አብላጫው ድምጽ የሰጠው ትርጓሜ ተገልጋዩ ሕብረተሰብ አንድ እና ተያያዥነት ያለውን ጉዳይ ለማስወሰን ሁለት ቦታ ማለትም የውርስ ሰርተፍኬት ለማግኘት አዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት፣ ውርሱ እንዲጣራ ለማመልከት ለፌደራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው ጊዜውን፣ ገንዘቡንና ጉልበቱን እንዲያባክን የሚያደርግ ነው፡፡ ስለሆነም ከላይ በዘረዘርኳቸው ምክንያቶች አብላጫው ድምጽ በሰጠው ውሣኔ ባለመስማማቴ የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ውርስ አጣሪ የመሾም ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/1/ሽ እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 996/1/ መሰረት አላቸው በማለት በልዩነት ወስኛለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 36338

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ገ/መስቀል ደመወዝ - ቀረበ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ አፀደ መኰንን - ቀረበች፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በሁከት ይወገድልኝ የክስ መነሻነት የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረውም የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተው ከቀበሌ ተከራይቼ የምኖርበትን ቤት ማእድ ቤት ለማደስ ያደረግሁት እንቅስቃሴ እንዳይሳካ ሁከት ስለፈጠረችብኝ ሁከቱ ይወገድ ዘንድ ይታዘዝልኝ በማለት ነው፡፡ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ ተጠሪን በማስቀረብ ክርክሩን ከሰማ በኂላ የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቹ ውሳኔውን በመቃወም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ እንደገና ተሰምቷል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በማህበራዊ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናቱ አመልካች አሁንም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ ክርክሩ እንዲሰማ አድርጓል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከመረመረ በኂላ በአብላጫ ድምጽ በሰጠው ውሳኔ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች የካቲት 5 ቀን 2000 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ጉዳዩ በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆን አለመሆኑ ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው አመልካች ለቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ክስ ያቀረበው ተጠሪ የማእድ ቤቱ እድሳት እንዳይካሄድ በመከልከል የፈጸመችው ድርጊት ሕገ ወጥ ነው ተብሎ እንዲወገድ እና እድሳቱን እንዲያካሂድ እንዲወሰንለት በመጠየቅ ነው፡፡ የክሱ ምክንያት ሕገ ወጥ ነው የተባለው ድርጊት እንዲወገድ የሚጠይቅ ከመሆን አልፎ የገንዘብ ጥቅም ወይም በገንዘብ ሊተመን የሚችል መብት የሚጠይቅ አይደለም፡፡ ጉዳዩ በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ የቻለውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

በግልጽ እንደሚታወቀው ማንኛውም ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ ተቀብሎ ሊያስተናግድ የሚችለው በክልልም ሆነ በስረ-ነገር ረገድ የዳኝነት ስልጣን ሲኖረው ነው፡፡ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣንን በሚመለከትም ሕጉ ጥብቅ የሆነ ድንጋጌ አስቀምጦአል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.9/1/ እንደተመለከተው በስረ-ነገሩ ለመዳኘት ስልጣን የሌለው ፍ/ቤት የክስ ማመልከቻውን በፍ/ብ/ሕግ ቁ.231 በተደገገው መሰረት ተቀባይነት የለውም ብሎ መመለስ አለበት፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን እርምጃ መውሰድ ያለበት ተከራካሪ ወገን መቃወሚያ እንዲያቀርብለት ሳይጠብቅ በራሱ አነሳሽነት እንደሆነም በዚሁ ቁ.9/2/ በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ የተቀመጠውን አስገዳጅ መርህ ለማስከበር ሲባል የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ነበረው ወይ? የሚለው ጭብጥ መያዙ ተገቢ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየቀበሌው የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች እንዳሉና የመዳኘት ስልጣንም እንደተሰጣቸው በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 39 ተመልክቷል፡፡ የፍ/ቤቶቹን የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን በተመለከተ በሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 50/1/ እንደተመለከተውም ግምታቸው ከብር 5000(አምስት ሺህ) ባልበለጡ የንብረትና የገንዘብ ክርክሮች ብቻ የተወሰነ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ነው ያላቸው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ክስ በገንዘብ የሚተመን አይደለም፡፡ በገንዘብ የማይተመኑ ወይም የገንዘብ ግምት የሌላቸው፣ ነገር ግን መሰረታዊ የሆነ የመብት ጥያቄ የሚያስነሱ ክሶች የሚታዩበትን ሁኔታ ሕጉ በተለየ ሁኔታ ደንግጓል፡፡ በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች የስረ- ነገር የዳኝነት ስልጣን ስር እንዲወድቁ ግን አልደነገገም፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አነስተኛ ድምጽ የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የለውም በማለት ከአብላጫው ድምጽ የተለየውም በዚህ ምክንያት እንደሆነ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በበኩላችንም ትክክለኛ ሆኖ ያገኘነው በአነስተኛው ድምጽ የተሰጠው የሕግ ትርጉም ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም በአብላጫው ድምጽ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02188 ታሕሣሥ 3 ቀን 1998 ዓ.ም ተሰጥቶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 02897 ታሕሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የማይወድቅ በመሆኑ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ ክሱን ያስተናገደው ከሕግ ውጪ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 34440

ጥቅምት 06 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** መንበረ ፓትሪያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ቀሲስ መሠረት አፈወርቅ

**ተጠሪ፡-** መጋቢ ሚስጢር መዝገቡ በላይነህ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የአሁኑ ተጠሪ ተከሣሽ ደግሞ የአሁኑ አመልካች ነበር፡፡

የሥር ከሣሽ ጥር 26 ቀን 1999 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የክስ ይዘት ሲታይም ከ1957 ዓ.ም ጀምሮ በቅኔ እና አቋቋም መምህርነት ሲያገለግሉ ቆይተው የተከሣሽ መ/ቤት አስተዳደር ጉባዔ ሰኔ 29 ቀን 1986 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት ይሠሩበት ከነበረው ከደቡብ ወሎ ሀገረስብከት ወደ አዲስ አበባ ተዛውረው እየሰሩ መሆናቸውን፤ ሆኖም ከሐምሌ 01 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ የተቋረጠ ደመወዝ መኖሩን በመግለጽ የተቋረጠው ደመወዝ ከኪሣራ ጋር እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የስር ተከሣሽም በፍ/ቤቱ ጥሪ መሠረት ቀርቦ መጋቢት 14 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመከላከያ መልሱን አቅርቧል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ሲታይ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለው መሆኑንና የከሣሽ የክፍያ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ የሚሆን መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥብነት አንስቶ በፍሬ ነገር ረገድም ከሣሽ አዲስ አበባ መጥተው በሌላ ቤተክርስቲያን አገልግሎት እየሠጡና ደመወዝ እየተከፈላቸው ከመሆኑም በላይ ቀድሞ ይሠሩበት ከነበረው ቦታም ሌላ ሰው ተተክቶ ደመወዝ እየተከፈለ መሆኑን በመጥቀስ የከሣሽ ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መከራከሩን የሚያስረዳ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን በቃል ከአከራከረና ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በተከሣሽ በኩል የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦች በከፊል ውድቅ በማድረግ የከሣሽን ጥያቄ በከፊል በመቀበል የተቋረጠ ደመወዝ ሊከፈለው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የሠበር አቤቱታው የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ባለመስማማት በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች ነገረፈጅ ታህሣሥ 15 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ የበታች ፍ/ቤቶች ፈፀሙ ያሏቸውን የሕግ ስህተቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለው መሆኑን፣ ይኸው ቢታለፍ እንኳ የደመወዝ ጥያቄው ከአስራ ሁለት ዓመታት በኋላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚገባው መሆኑን በመዘርዘር የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ መጋቢት 01 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው መሆኑንና የደመወዝ ጥያቄውም ውዝፍ ደመወዝ ይከፈለኝ ባለመሆኑ በይርጋ የሚታገድበት የሕግ አግባብ አለመኖሩን በመዘርዘር እና የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ ተገቢነት በመግለጽ ሊፀና ይገባል ሲሉ መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረፈጅ

በበኩላቸው የተጠሪን መልስ በመንቀፍና የሠበር አቤቱታ ይዘቱን ተገቢነት በማጠናከር መጋቢት 30 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ከሕጉ ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ በመደበኛ ፍ/ቤት መታየቱን በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የተቋረጠው የደመወዝ ክፍያ ጥያቄን ሊያቀርቡ የቻሉት በአመልካች መ/ቤት ከ1957 ዓ.ም ጀምሮ በቅኔ መምህርነት ተቀጥረው ሲያገኙት የነበረው ደመወዝ ከ1/11/86 ዓ.ም ጀምሮ ተቋርጧል በሚል ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ የቅኔ መምህር በመሆናቸውና አገልግሎቱም መንፈሣዊ በመሆኑ በስራ ክርክር ሰሚ ሊታይ እንደማይገባው በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤት ይህንኑ የአመልካች መከራከሪያ ነጥብ ያለፈውም የተጠሪ አገልግሎት ከኃይማኖት ተቋሙ ጋር የተያያዘ ቀጥተኛ መንፈሣዊ ስራ አይባልም በሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ የተጠሪ ስራ ለተማሪዎች አገልግሎት የሚሰጥ የቅኔ መምህርነት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ለዚህ ለሰበር ችሎቱ በሰጡት መልስም የቅኔ መምህርነት ከኃይማኖት ተቋሙ ጋር የተያያዘ ቀጥተኛ መንፈሣዊ ስራ አይደለም በማለት ያነሱት ክርክር የለም፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የቅኔ መምህርነት ስራ ቀጥተኛ የሆነ መንፈሣዊ ስራ መሆኑ የሚያከራክር ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ የግራ ቀኙን ክርክር ያላገናዘበ ነው፡፡

ይህ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 18419 ግንቦት 04 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የኃይማኖት ድርጅት ሠራተኞችን በሁለት ከፍሎ በማየት የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ተፈፃሚነትን ወስኗል፡፡ በዚህም መሠረት ከኃይማኖት ድርጅቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለውና ከእምነት ተነጥሎ ሊታይ የማይችል ስራ የሚሠሩ ሠራተኞች እንደ ቄስ፣ ካህን፣ ዲያቆን --- ወዘተ ከኃይማኖት ድርጅታቸው ጋር የሚያነሡት ክርክር በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ሊዳኝ የማይገባው መሆኑ ተወስኗል፡፡ ሠበር ችሎቱ ወደዚህ ድምዳሜ የደረሰውም መንፈሣዊ ስራ የሚሠሩት ግለሰቦች ቀጥተኛ ከእምነቱ ወይም የኃይማኖት ድርጅቱ ከሚከተለው እምነት የሚመነጭና ከእምነቱ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው በመሆኑ፣ መንፈሣዊ አገልግሎቱን ለመስጠት ብቁ ሆኖ ለመገኘትም በእምነቱ መሠረት መሟላት የሚገባቸው ልዩ ነጥቦች መኖራቸው ይታወቃል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ከዚህም የምንገነዘበው ተጠሪ የቅኔ መምህር ሆነው ሊቀጠሩ የቻሉት የአመልካች እምነት የሚጠይቀውን ልዩ መመዘኛ አሟልተው በመገኘታቸውና ይህንኑ መንፈሣዊ አገልግሎት ለተማሪዎች ለመስጠት ነው፡፡ ተጠሪ የሚሠጡት አገልግሎት በባህርይው ቀጥተኛ የሆነ መንፈሣዊ ትስስር ያለው መሆኑ እየታወቀ በኃይማኖት ተቋሙ እንደሚሠሩ ሌሎች እንደ ሂሣብ ሠራተኛ፣ ንብረት ክፍል ሠራተኛ የስታትስቲክስ ሠራተኛ --- ወዘተ ተቆጥሮ የቅኔ መምህርነት ቀጥተኛ መንፈሣዊ አገልግሎት ሊባል አይገባም መባሉ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የተጠሪ ስራ ቀጥተኛ የሆነ መንፈሣዊ አገልግሎት ነው ከተባለ ደግሞ ከአመልካች ጋር የሚኖሩት አለመግባባት በስራ ክርክር ሠሚ ቀርቦ ሊታይ የማይገባ፣ ይልቁንም በኃይማኖት ተቋሙ አለመግባባቶች በሚፈቱበት መንገድ ሊታይ የሚገባው መሆኑን ከላይ የተጠቀሰው የሰበር ችሎት ውሣኔ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1/ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20228 ግንቦት 08 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 55548 ህዳር 25 ቀን 2000 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348 /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2/ የተጠሪ ጥያቄ በኃይማኖት ተቋሙ አለመግባባቶች በሚፈቱበት መንገድ ከሚታይ በስተቀር በስራ ክርክር ሠሚ አካል ቀርቦ የሚዳኝበት የሕግ መሠረት የለም ብለናል፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

4/ መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 33841

ጥቅምት 6 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ አስጨናቂ ረጋሣ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- 1. አቶ ገዛኸኝ ነጋሽ ወኪል ሙሉመቤት - ቀረቡ

2. ወ/ሪት ሙሉእመቤት ነጋሽ - ቀረቡ

3. ወ/ሪት አሰገደች ነጋሽ - አልቀረበችም

4. አቶ ዘላለም ነጋሽ

5. አቶ ዳኛቸው ነጋሽ ወኪል - ቀረቡ

6. አቶ ኤፍሬም ነጋሽ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥሰናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01973 ግንቦት 10 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03392 ጥቅምት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይሻርልኝ በማለት ኅዳር 9 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ያልተወረሰና አባታችን ከአዋጁ በፊት በወለድ አግድ አስይዞት የነበረ፤እንዲሁም በቅጽ 004 የተመዘገበ የአባታችን አቶ ነጋሽ መንገሻ ንብረት የሆነ ቁጥሩ 668/669 ቤት አመልካችና የወረዳ 4 ቀበሌ 28 አስተዳደር ጽ/ቤት በፍርድ ተገድደው እንዲያስረክቧቸው ለአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችና ሁለተኛ ተከሳሽ የነበረው የወረዳ 4 ቀበሌ 28 አስተዳደር ጽ/ቤት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሰ ነው፤ በማስረጃነት የቀረበው ቅጽ 004 በሚመለከተው የበላይ አካል ያልፀደቀና በቀበሌ ደረጃ ብቻ የተሞላና አስተያየት የተሰጠበት ሰነድ በመሆኑ ቤቱ ያልተወረሰ መሆኑን ለማስረዳት አይቻልም የሚል ክርክር አቅርበዋል፤ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት የተወረሰ ነው በማለት የተጠሪዎችን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪዎች ይግባኛቸውን ለከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ቤቱ በቅጽ 004 የተሞላ ተጠሪዎች አውራሽ የምርጫ ቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያለ በመሆኑ ለተጠሪዎች መመለስ አለበት በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለከተማ ነክ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም የከተማ ነክ ሰበር ሰሚ ችሎት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህ ውሣኔ መሰረታዊ ስህተት አለበት፤ በመጀመሪያም የከተማ ነክ ፍርድ ቤት ይህንን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው የሥረ-ነገር ስልጣን የለውም፤ ቤቱ የተወረሰ ነው፤ ቅጽ 004 የተባለው በሚመለከተው አካል የፀደቀ ባለመሆኑ ቤቱ ለተጠሪዎች አውራሽ በምርጫ ቤትነት እንዲይዙት የተወሰነ መሆኑን ለማስረዳት ብቃት የለውም፤ የሚል ክርክር ያቀረበ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው፤ ቤቱ በቅጽ 004 በወቅቱ ሕጋዊ ስልጣን ባለው አካል ለአውራሻችን በምርጫ ቤትነት የተሰጠ ነው ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ስህተት የለበትም የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የከተማ ነክ ፍርድ ቤት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት የተወረሰ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለማየትና ቤቱን በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ያልተወሰረ በመሆኑ ለተጠሪዎች ይመልስ በማለት የመወሰን የዳኝነት ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውመሰረታዊ የህግ ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመረምረው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ስልጣንና ሐላፊነት በአዋጅ ቁጥር 361/1995 በአንቀጽ 41 የተዘረዘረ ሲሆን የከተማ ነክ ፍርድ ቤት ንብረትነቱ የከተማው አስተዳደር የሆነ ቤት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን አይቶ የመወሰን ስልጣን እንዳለው በአዋጅ አንቀጽ 41(1)(ረ) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህም የምንረዳው የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ንብረትነታቸው የከተማ አስተዳዳር ለመሆናቸው ክርክር በማይቀርብባቸው ቤቶች ላይ የሚነሱ የይዞታ የኪራይ እና ሌሎች ክርክሮችን አይተው የመወሰን ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

ሆኖም ክርክር የተነሳበት ቤት የከተማው አስተዳደር ነው ወይስ የሌላ ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚል መሰረታዊ ክርክር ያለበት ከሆነ የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ይህንን የቤት ባለቤትነት ጥያቄ አስመልክቶ በከተማው አስተዳደርና በሌሎች ሰዎች መካከል የሚደረግ ክርክር በዳኝነት አይተው ለመወሰን የሚያስችል የሥረ-ነገር ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 (1) (ረ) ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የቤቱን ባለቤትነት አስመልክቶ በተጠሪዎች በኩል ክርክር እያቀረቡበትና የጉዳዩም መሰረታዊ ጭብጥ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት ተወርሷል ወይስ አልተወሰረም የሚል በመሆኑ ይህንን ጉዳይ ሰምተውና አከራክረው ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችላቸው የሥረ-ነገር ስልጣን ሣይኖራቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ውሣኔ ሰጥተውበታል፡፡ ስለሆነም በየደረጃው ያሉ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት የስረ-ነገር ስልጣን ሣይኖራቸው ጉዳዩን ሰምተውና አከራክረው የሰጡት ውሣኔ ህጋዊ አስገዳጅነት የሌለውና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 0455 ጥር 5 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01973 ግንቦት 10 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከተማ ነክ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03392 ጥቅምት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የሥረ-ነገር ስልጣን ሳይኖራቸው የተሰጡ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪዎች ሥልጣኑ ለሚፈቅድለት ፍርድ ቤት ወይም አካል አቅርበው የመጠየቅ መብታቸውን ይህ ውሣኔ አይገድብባቸውም ብለናል፡፡
3. በትውስት የመጣው መዝገብ ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር ይመለስ፡፡
4. በዚህ መዝገብ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ጉዳዩ በውሣኔ የተቋጨ ስለሆነ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 6 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 33368

ህዳር 9 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ሻምበል አሰፋ በላይ ዘገየ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ**፡- ወታደራዊ ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የወንጀል ክርክርን ይሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ነው ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በ1949 ዓ.ም በወጣው የወ/መ/ሕ በቁ. 386 እና 642 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ስለፈጸመ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት ይገባል በማለት ነው፡፡ ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤቱም አመልካችን አስቀርቦ ከአከራከረ በኂላ አመልካች በተጠቀሱበት የሕግ ድንጋጌዎች የተመለከቱትን የወንጀል ድርጊቶች ለስመፈጸሙ በማስረጃ አረጋግጫለሁ የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በመቀጠልም በአመልካች ላይ የስድስት (6) ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ የተሰማ ሲሆን በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው ቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 30 ቀን 99 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካች ተፈጽሞአል የተባለው ወንጀል በወታደራዊ ፍ/ቤት የስረ - ነገር የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ለጉዳዮ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው በዚህ ሰበር ችሎት አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ጭብጥ በአመልካች ላይ የተመሠረተው ክስ በወታደደራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ ጉዳዮ የፍ/ቤቶችን የዳኝነት ስልጣን ምንጭ (በአጠቃላይ) ምንድነው? አንድ ፍ/ቤት ከስልጣኑ ውጪ ጉዳይ ተቀብሎ ዳኝቷል ማለት ምን ማለት ነው? የዳኘው ከስልጣኑ ውጪ ሆኖ ከተገኘስ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች የሚያስነሳ በመሆኑ በጥንቃቄ ለመመርመር የሚገባው ነው፡፡

እንደሚታወቀው ፍ/ቤቶች በሕግ የሚቋቋሙ እንደመሆናቸው የዳኝነት ስልጣናቸው የሚመነጨውም ከሕግ ነው፡፡ ከዚህ እንግደህ መገንዘብ የሚቻለው የማንኛውም ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን በሕግ ተወስኖ የተሰጠ (የሚሰጥ) መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ (ክስ) ተቀብሎ ከማስተናገዱ በፊት በጉዳዮ (ክሱ) ላይ በሕግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፡፡ በሕግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የሚሰጥ ውሳኔ የሕግ መሠረት ያለው ነው ወይም ሕጋዊ ውሳኔ ነው ለማለት እንደማይቻልም በአግባቡ መገንዘቡ ተገቢ ነው የሚሆነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የወታደራዊ ፍ/ቤቶች እንደ ሌሎቹ ፍ/ቤቶች በሕግ የተቋቋሙ እና የዳኝነት ስልጣናቸውም በሕግ ተወስኖ የተሰጠ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ በመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁ.27/1988 በአንቀጽ 25 እንደተመለከተው ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ተቋሙ-መዋል ለፍ/ቤቶቹ የተሰጠ የዳኝነት ሥልጣን በተመለከተም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 26፣27 እና 28 በዝርዝር ተገልጿአል፡፡ በ1949 ዓ.ም በወጣው የወ/መሕግ ከቁ.296 እስከ ቁ.331 በተዘረዘሩት ወንጀሎች ተጠያቂ የሚሆኑ ሰዎች ላይ በግዳጅ ላይ ያለ ወታደር በሚፈጽማቸው በማናቸውም ወንጀሎች ላይ በውጪ አገር በጦር ሜዳ ግዳጅ ላይ ካለ ወታደር ጋር አብረው በሚዘምቱ ሲቪሎች ላይ እና በጦር ምርኮኞች ላይ ከተፈፀመ ወንጀል ላይ የወታደራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው አንቀጽ 26 በግልጽ ያመለክታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተከሣሹ ከቀረቡበት ክሶች መካከል አንዱ በወታደራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ወንጀል በሆነ ጊዜ ሁሉም ክሶች የሚቀርቡት ለወታደራዊ ፍ/ቤቶች እንደሆነ በአንቀጽ 28 ተመልክቶአል፡፡

በአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር ስንመለከት ፍ/ቤቶቹ በዚህ ጉዳይ አመልካች በተከሰሰበት የዳኝነት ስልጣን የላቸውም ለሚለው ክርክሩ በዋቢነት የጠቀሰው ከላይ በተመለከተው አንቀጽ 26/1/ የተቀመጠው ድንጋጌ ነው፡፡ በእርግጥም ይህ ንዑስ አንቀጽ ለብቻው ተወስዶ ሲታይ በወ/መ/ሕጉ ከቁ.296 እስከ ቁ.331 ድረስ ያሉትን ድንጋጌዎች ብቻ ስለሚጠቅስ በአመልካች ላይ በቀረበው ክስ የተጠቀሱትን ቁ.386 እና ቁ. 642 አያካትትም፡፡ ከዚህ የተነሣም የአመልካቹ ክርክር ተገቢነት ያለው ነው ሊባል ይችላል፡፡ በአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)፣(3) እና (4) የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ስንመለከት ግን ለወታደራዊ ፍ/ቤቶች የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በንዑስ አንቀጽ /1/ ከተመለከተው የሰፋ እንደሆነ ነው መገንዘብ የሚቻለው፡፡ በንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከተውን ድንጋጌ እንኳን ወስደን ስናየው በንዑስ አንቀጽ /1/ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በግዳጅ ላይ ያለ ወታደር በሚፈጽማቸው በማናቸውም ወንጀሎች ላይ ጭምር ፍ/ቤቶቹ የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው ነው የምንገነዘበው፡፡ የአመልካቹ ክርክር በጽሑፍ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል ብሎ መደምደምያ የማይቻለውም (ትክክል የማይሆነውም) በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ‹‹ ግዳጅ›› የሚለው ቃል በአዋጁ ባለመተርጐሙ እና አመልካችም የተከሰሰው ከፋይናንስ አስተዳደር ጋር በተያያዘ ወንጀል በመሆኑ አመልካቹ በአዋጁ አንቀጽ 26 (2) አባባል በግዳጅ ላይ እንዳለ በፈጸመው ወንጀል ነው የተከሰሰው ወይም የተከሰሱበት ወንጀል የተፈጸመው በግዳጅ ላይ ሳለ ለማለትም ይቻላል ወይ የሚለው ነጥብ አከራካሪ ይሆናል፡፡

የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁ.27/88 በመከላከያ ሠራዊት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁ.343/95 ተሻሽሎአል፡፡ ይህ አዋጅ በግልጽ ካሻሻላቸው አንቀጾች መካከል የቃላትን ትርጓሜ በተመለተ የተደነገገ ነው አንቀጽ 2 እና የወታራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን የሚመለከተው አንቀጽ 26 ይገኙበታል፡፡ በዚህም በቀድሞው በትርጓሜ ውስጥ ተካቶ ያልነበረው ‹‹ግዳጅ›› የሚለው ቃል ‹‹ማንኛውም የሠራዊት አባል ከተቀጠረበት ጊዜ አንስቶ ከሠራዊቱ እስኪሰናበት ጊዜ ድረስ በመከላከያ ውስጥ የሚያከናውነው የውትድርና ተግባር ነው›› በሚል በማሻሻያው አዋጁ ቁ.343/95 አንቀጽ 2(9) ተተርጉሞአል፡፡ አንቀጽ 26(2)ም በትርጓሜ ክፍሉ በተተረጐመው ‹‹ግዳጅ›› ከሚለው ቃል በሚስማማ መልኩ ተሻሽሎአል፡፡ በዚህም የወታራዊ ፍ/ቤቶቹ የዳኝነት ስልጣን ከቀድሞው የበለጠ ሰፍቶአል፡፡ አዋጅ ቁ.27/88‹ን› ማሻሻል ካስፈለገበት ምክንያቶች አንዱም በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ በወታደርነት በማገልገል ላይ ያለ የሠራዊቱ አባል የሚፈጽማቸው ወንጀሎች በወታደራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር እንዲወድቁ በመታሰቡ እንደሆነ ከአዋጁ ማሻሻያ አዋጅ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች የተከሰሰበትን ወንጀል ፈጸመ በተባለበት ጊዜ ሠራዊቱ አባል (ወታደር) ሆኖ ይሠራ እንደነበረ ተረጋግጦአል፡፡ ይህም ማለት በማሻሻያው አዋጅ ቁ.343/95 አንቀጽ 2(9) እንደተደነገገው በግዳጅ ላይ ነበር ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ፈጸመው የተባለው የወንጀል ድርጊት በአዋጁ አንቀጽ 26/1/ በተመለከቱት የወ/መ/ሕጉ ድንጋጌዎች ስር የማይወድቅ ቢሆንም በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ተቀጥሮ (በውትድርና) የሚያከናውነውን የውትድርና ተግባር ሲሰራ በነበረበት ጊዜ የፈጸመው በመሆኑ ክሱ ለወታደራዊ ፍ/ቤት መቅረቡ ትክክል ነው፡፡ ሲጠቃለል የወታደራዊ ፍ/ቤቶች ይህን ክስ ለማስተናገድ በሕግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን አላቸው፡፡ ስለዚህም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልቻልንም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት ይግባኝ ሰሚ ወታራዊ ፍ/ቤት የመቁ.014/99 መጋቢት 18 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ክሱ ለወታደራዊ ፍ/ቤት መቅረቡ በሕጉ መሠረት ሆኖ ስላገኘነው የአመልካችን ክርክር አልተቀበልንም፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

የሰ/መ/ቁ. 34788

ኅዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- የሟች አቶ ሰለሞን ሳሙኤል ወራሾች -ቀርቧል

እነ ወ/ሮ ማረታ ሰለሞን(ሁለት ሰዎች) - ጠበቃ ታደሰ ጉርሙ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡-ኑረዲን  መሐመድ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ጣልቃ ገቦች ተጠሪ የሥር ከሣሽ ነበሩ፡፡

የአሁን ተጠሪ በሥር ተከሣሾች በነበሩት አንደኛ ንግድ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ቢሮ፣ ሁለተኛ የወረዳ 5 አስተዳደር፣ ሦስተኛ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ላይ ባቀረበው ክስ በድርጅት ቤት፤ የሆቴል ንግድ ሕጋዊ ፈቃድ አውጥቼ በየዘመኑ ፈቃዴን እያሳደስኩ ከኪራይ ቤቶች ተከራይቼ በምሰራው ሆቴል ቤት እየሰራሁ እያለሁ፤የሥር ተከሣሾች ቤቱን ያለአግባብ እንዳልሰራ አሽገውብኛል፡፡ ስለዚህ አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሣሾች ቤቱን እንዲያስረክቡኝ ሦስተኛ የሥር ተከሣሽ ከእኔ (ተጠሪ) ጋር የነበረውን ውል ሣያቋርጥ(ሳያፈርስ) ሌላ ውል በመፈፀም ያስገባቸውን ግለሰቦች እንዲያስወጣ ውላቸውንም እንዲሰርዝ፣ የቀረብኝን ጥቅምና የደረሰብኝ ጉዳት የመጠየቅ መብቴ ተጠብቆ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

አንደኛ እና ሁለተኛ የሥር ተከሣሾች ለቀረበባቸው ክስ መልስ ሲሰጡ፡- የአሁን ተጠሪ ፍቃዳቸውን ያላደሱ በመሆኑ የጸና የንግድ ፍቃድ የላቸውም ፍቃዳቸው ተሰርዟል፡፡

ከተጠሪ ጋራ ያለን ግንኙነት ስለተቋረጠ የሚጠይቁት ጥቅም ሆነ መብት የላቸውም ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ሲመልስ፤ሁለተኛ የሥር ተከሣሽ በበኩሉ የተባለውን ቤት በጋራም ሆነ በተናጥል አላሸግኩም ሲል መልሷል ሦስተኛ የስር ተከሳሽም በተመሣሣይ መልኩ ድርጊቱን እንዳልፈፀመ ክዶ ተከራክሯል፡፡

በዚሁ ጉዳይ የሥር ጣልቃ ገብ የአሁን ተጠሪ ይህን ቤት በሕጋዊ መንገድ ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር ተረክበው በውላቸው መሰረት ይዘውት እንዳሉ ገልጸው የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲሆን በመቃወም ተከራክረዋል፡፡

የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ጉዳዩን ከሕግ ጋር በማገናዘብ ከመረመረ በኂላ ተጠሪ የንግድ ፈቃድ ባለማደሳቸው እና በወቅቱ የቤት ኪራይ ክፍያ ባለመፈፀማቸው ምክንያት በኪራይ ይዘውት የነበረውን ቤት ሕግና ደንብ በሚያዘው መሰረት መብታቸውን አጥተዋል፡፡ ስለዚህ ይህን ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 33(2) መሰረት የመክሰስ መብት የላቸውም ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪም በተሰጠው ውሳኔ ባለመስማማት ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅሬታውን አቅርቦ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን አስቀርቦ በማከራከር ካየ በኂላ የሥር አንደኛ ተከሣሽ የአሁን ተጠሪን የንግድ ድርጅት ያሸገው ያለ አግባብ ነው፣ ሦስተኛ የሥር ተከሣሽ ከአሁን ተጠሪ ጋር ያደረገው የቤት ክራይ ውል ፀንቶ ባለበት ሁኔታ ከአሁን አመልካቾች ጋር

በውል ላይ ውል በመፈፀም ቤቱን ያስረከባቸው በአግባቡ አይደለም፣ የአሁን ተጠሪ እና የሥር ሦስተኛ ተከሣሽ የኪራይ ውላቸውን መቀጠል ይገባል በማለት የሥር ውሳኔን በመሻር ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡

በዚህም መሰረት የአሁን አመልካቾች በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለከተማው ሰበር ሰሚ ስሆነው ፍ/ቤት ቅሬታቸውን በማቅረባቸው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በፍ/ቤቱ ውስጥ ጉዳዩን የማየት ስልጣንን አስመልክቶ የሐሳብ ልዩነት በመፈጠሩ በልዩነት ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አብላጫው ድምጽ ምክንያቱን ሳያስቀምጥ "ምንም እንኳን የፌዴራል መንግስት አካል የሆነው የኪ.ቤ.አ.ድ በዚህ መዝገብ ተከራካሪ ቢሆንም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ነገር የመስተዳድሩ አካላት በነበራቸው የአስፈፃሚነት ስልጣን በመሆኑና እነርሱ የወሰዱትን እርምጃን ተከትሎ የኪ.ቤ.አ.ድ በወሰደው እርምጃ የተከሰሰና ይህም አንድ ድርጊት በመሆኑ ጉዳዩ የዚህ ፍርድ ቤት ሥልጣን ነው" በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ስህተት የለም በማለት የሰበር አቤቱታውን ሰርዞታል፡፡

አነስተኛ ድምፁም በጉዳዩ የተለየበትን ሐሳብ ሲያስቀምጥ፡- "በክርክሩ ጭብጥ ውስጥ ይህንን ቤት በባለቤትነት የሚያስተዳድረው የኪራይ ቤቶች ድርጅት ቤቱን አላግባብ ለሦስተኛ ወገን አከራየብኝ የሚል በመሆኑ በአዋጅ 25/88 መሰረት መዳኘት የሚኖርበት በፌዴራል ፍርድ ቤት ከመሆኑም በላይ የክርክሩ መነሻ የሆነው ቤትም በአዋጅ 36/95 አንቀጽ 41/1/ረ ላይ መስተዳድሩ በባለቤትነት ከሚያስተዳድራቸው ሥር የማይሸፈን በመሆኑ በከተማው ፍ/ቤት መታየቱ ከሥልጣን አኳያ አግባብ አይደለም" ሲል ልዩነቱን አስፍረዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች ጥር 1 ቀን 2000 ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ በከተማው ይግባኝ ሰሚና በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሣኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አቤቱታቸውን አቅርቧል፡፡

ይህ የፌዴራል ሰበር ችሎትም አቤቱታውን ምክንያት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምተዋል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የወሰነው የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህም መሰረት ይህን ነጥብ ከተነሳው ክርክር፣ በአቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ክሱን ሲመሰርት የሆቴል ቤቱ ያለአግባብ በመስተዳድሩ አካላት እና በቱሪዝም ቢሮ የታሸገበት መሆኑን ብቻ ሳይሆን የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት የሆነውን የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ኪራይ እየከፈልኩ የምሰራበትን የሆቴል ቤት ነጥቆኝ ለሦስተኛ ወገን አከራይቶታል በሚል ምክንያት ነው፡፡

እኛም ተሻሽሎ የወጣውን የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁ. 24/1/ረ ስናይ የከተማው ፍ/ቤት ማየት የሚችለው የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮችን ነው፡፡ ሕጉ ይህን እያለና ዋና **የቤት** አስተዳደር (ባለቤት) ከተጠሪ ጋራ የውል ግንኙነት እያላቸው በፌዴራሉ ሥልጣን ክስ የሚወድቀውን ክርክር በከተማው ፍ/ቤት መታየቱ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለዚህ በሥር ፍ/ቤት በአበላጫ ድምጽ የተሰጠው ውሳኔ ተሽሮ በአናሳው ደምጽ ጉዳዩ የከተማው ፍ/ቤት ሥልጣን አይደለም ያለው ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የአ.አ.ከተማ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት መ/ቁ. 2633/91 ሐምሌ 22 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02703 ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የከተማው ሰበር በመዝገብ ቁ. 05360 በ4/4/2000 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ ተሽሮአል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የአ/አ/ከተማ መስተዳድር ፍ/ቤቶች ይህን ክርክር የማየት ስልጣን የላቸውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪ እና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 31906

ኀዳር 4 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ሒሩት አሥራት

**ተጠሪ፡-** የአቶ መርስኤ መንበሩ ወራሾች - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ለዚሁ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ሟች አባታችን በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 3 ቀበሌ 53 ክልል ቁጥር 849 የሆነውን ቤት በ1957 ዓ.ም. ከቀድሞ ባለ ርስት በጭሰኝነት ተመርተው ተገቢው ኪራይ እየከፈሉ ሲገለገሉ የቆየ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 47/67 ሲታወጅ የባለርስትና የጭሰኛ ግንኙነት በመቋረጡ የአፈር ግብር ለመንግሥት እየከፈሉ የቆዩ ቢሆንም የቤት ባለቤትነት ደብተር ለማውጣት በቦታው ላይ ይዞታ እንደነበራቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከፍ/ቤት አስመስክረንና አረጋግጠን እንድንቀርብ የተጠየቅን በመሆኑ የቤት ባለቤትነት ደብተሩን ማግኘት እንድንችል በቦታው ላይ ይዞታ ያለን ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጠን በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች በተጠሪነት ያጣመሩት ባለመኖሩ ፍ/ቤቱ የአመልካቾችን ምስክሮች ሰምቶ የአመልካቾች አባት ቦታውን በ1959 ዓ.ም. ከልዕልት ተናኘ ወርቅ ላይ በጭሰኝነት ተመርተው ውሃና መብራት በማስገባት ቤት ሠርተው የጋራዥ ድርጅት አቋቁመው ሲሰሩበት እንደበር አዋጅ ቁጥር 47/67 ከታወጀ በኋላ የቦታና የቤት ግብር ለመንግሥት ሲከፍል እንደነበር በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ይሄው ተገልጾ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍላቸው በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካች የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ በወቅቱ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት አመልካቾች በይዞታቸው ሥር እንደሆነ ተገልጾ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ትዕዛዝ የተሰጠበት ድርጅት በአዋጅ 47/67 መሠረት የተወረሰና የሚያስተዳድረው መሆኑን ገልጾ በሌለበት የተሰጠው ትዕዛዝ መብቱን እንደነካ በመግለጽ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት በተቃዋሚነት ወደ ክርክሩ ለመግባት ጠይቆ በተፈቀደለት መሠረት ወደ ክርክሩ በመግባት ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ክርክር የተነሳበት ድርጅት በአዋጅ 47/67 መሠረት ተወርሷል አልተወረሰም የሚለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር መወረሱ ስለተረጋጠ አመልካቾች ከአዋጅ 47/67 መንፈስ ውጭ ተወስዶብናል የሚሉ ከሆነ ይህንኑ ጥያቄያቸውን በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ከሚያቀርቡ በስተቀር በተያዘው መዝገብ እንደማይስተናገድ ጠቅሶ አስቀድሞ ለአመልካቾች ይዞታ ያላቸው መሆኑ ተጠቅሶ እንዲፃፍላቸው የተሰጠው ትዕዛዝ ሊነሳ ይገባል በማለት አንስቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኝ አከራክሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ድርጅት በይግባኝ ባዮች ይዞታ ሥር እንደነበርና በአዋጅም እንዳልተወረሰ የቀረቡት ማስረጃዎች የሚያረጋግጡ እንደመሆኑ መጠን መልስ ሰጭው ድርጅቱ መወረሱን ባላረጋገጠበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት ድርጅቱ መወረሱ ተረጋግጧል በማለት አስቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ ማንሣቱ በአግባቡ አይደለም ሲል በመሻር የቀድሞው ትዕዛዝ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

የከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ሰበር ችሎትም ይሄው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመበትም በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ሳይቀረበለው ቀርቷል፡፡

ለዚህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ በሚያከራክረው ንብረት ላይ ተጠሪዎች የይዞታ ማስረጃ እንዲሰጣቸው በፍ/ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ ነው ተብሎ የአመልካች መቃወሚያ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውድቅ መደረጉ ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን ጠርቷል፡፡ ሆኖም ተጠሪዎች በአድራሻቸው ሊገኙ ባለመቻላቸው በጋዜጣ ተጠርተው ስላልቀረቡ በጽሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡ በቃል ክርክርም ጊዜ ስላልቀረቡ ችሎቱ የአመልካችን የቃል ክርክር ብቻ አዳምጧል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በቅድሚያ ችሎቱ የተመለከተው አመልካቾች አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ለፍ/ቤት ሊቀርብ የሚችልና ዳኝነት የሚያፈልገው /Justicable/ መሆኑን በተመለከተ ነው፡፡

ተጠሪዎች በከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ለክርክሩ ምክንያት በሆነው የንግድ ድርጅት ላይ የይዞታ መብት ያለን መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጠን በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች የዚህ ዓይነቱ ማስረጃ ከፍ/ቤቱ እንዲሰጣቸው የጠየቁትም የቤት ባለቤትነት ደብተር ከሚመለከተው መንግሥታዊ ተቋም ለማግኘት እንደሆነም በአቤቱታቸው ላይ ጠቅሰዋል፡፡

የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 ላይ የተመለከተ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን በማወቅ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት የሚሰጠው በመንግሥት የአስተዳደር መ/ቤት በኩል እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

እንደዚሁም የምስክር ወረቀት የሚሰጥበት ሥርዓት የአስተዳደር መስሪያ ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት እንደሚወሰንም በዚሁ ድንጋጌ ሥር ተመልክቷል፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም ሰው በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ማግኘት የሚችለው ከሚመለከተው የመንግሥት አስተዳደር መስሪያ ቤት በኩል ሲሆን የሚመለከተው የመንግሥት አስተዳደር መ/ቤት የምስክር ወረቀት አሰጣጡን አስመልክቶ በሚያወጣው የምስክር ወረቀትም እንደሚሰጥ መረዳት ይቻላል፡፡

ሕጉ በዚህ መልኩ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት እንደሚሰጥ ከደነገገ የምስክር ወረቀቱን ለማግኘት እንዲቻል የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲሰጥ ፍ/ቤትን መጠየቅ ከነመነሻውም ቢሆን ጉዳዩ በፍ/ቤት ቀርቦ ዳኝነት የሚያስፈልገው /Jusciable matter/ እንዳልሆነ ተገንዝበናል፡፡

ስለሆነም የዚህ ዓይነቱ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት በፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ቤት ሊስተናገድ እንደማይችል ግልጽ በመሆኑ ከመነሻውም ቢሆን ፍ/ቤቱ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት መመለስ ሲገባው ጉዳዩን ማስተናገዱ አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ ሲያቀርብ ፍ/ቤቱ የቀድመውን ትዕዛዝ መሰረዙ ከውጤት አኳያ ተቀባይነት ነበረው፡፡ ሆኖም ግን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይህንኑ ትዕዛዝ ምክንያቱን ለውጦ ሊያጸናው ሲገባ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ድርጅት መወረሱ አልተረጋገጠም በማለት መሻሩ ጉድለት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ሰበር ችሎትም መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት ይህንኑ ጉድለት ሳያርም መቅረቱ በአግባቡ ሆኖ አላገኘነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 01998 ሚያዝያ 19 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እንደዚሁም ይግባኙ ችሎቱ በመ/ቁ. 00682 በ30/3/97 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት በአብላጫ ድምጽ ሽረነዋል፡፡
2. ተጠሪዎች የቤት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት እንድችል የይዞታ መብት ያለን መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከፍ/ቤቱ ይሰጠን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ለፍ/ቤት ቀርቦ ዳኝነት ሊሰጥበት የማይችል ጉዳይ

/Justicable matter/ ስላልሆነ አቤቱታው ከመነሻውም ቢሆን ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ነበር በማለት ወስነናል፡፡

3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መ/ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የሀሣብ ልዩነት

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ በመጀመሪያ ተጠሪዎች ክርክር የተነሳበትን ቤትና ቦታ በከፍተኛ 3 ቀበሌ 53 ፍርድ ሸንጎ ውሣኔ መሠረት መያዛቸውን አንስተው የተከራከሩ በመሆኑና አመልካችም በበኩሉ ተጠሪዎች ኪራይ እንዲከፍሉ ሚያዝያ 5 ቀን 1981 ዓ.ም. በቀበሌ ሸንጎ አስወስኛለሁ የሚል ክርክር ያለው በመሆኑ የቀበሌ ፍርድ ሸንጎ ጥር 26 ቀን 1973 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና ሚያዝያ 5 ቀን 1981 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት ይህ ሰበር ችሎት በተደጋጋሚ ትዕዛዝ ሰጥቶ ተደጋጋሚ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በትዕዛዙ መሠረት መዝገቡ አልተገኘም የሚል ምላሽ የቀረበ ሲሆን እነዚህን አመልካችም ሆነ ተጠሪዎች የፍርድ ባለ መብት ሁነንባቸዋል የሚላቸውን ውሣኔዎች በማግኘት የሚያስችል ሌላ ተለዋጭ ትዕዛዝ መስጠቱን በአዋጅ ቁጥር 47/1967 በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የቀበሌ ሸንጎዎች የሰጡት አስገዳጅ ውሣኔ መኖር አለመኖሩን በማጣራት ለጉዳዩ እልባት መስጠት ይገባ ነበር፡፡ ይህ ሣይደረግ መዝገቡ አሁን ባለበት ሁኔታ መርምሮ ውሣኔ መስጠቱ፣ ተገቢ አይደለም የሚል ዕምነት አለኝ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የአንድ ቦታና ንብረት ሕጋዊ ባለይዞታ መሆኔ በፍርድ ይረጋገጥልኝ የሚል ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም ወይም በፍርድ ቤት ክስ ሊቀርብበት ውሣኔ ሊሰጥበት የሚችል /Justicable/ አይደለም የሚለውና የአብላጫው ድምጽ መደምደሚያ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ምክንያቲም ይዞታን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት የመስጠት ስልጣን የአስተዳደር አካላት መሆኑ የማይካድና የይዞታ የምስክር ወረቀትም በአስተዳደር ደንብ መሠረት መከናወን ያለበት መሆኑ ያማያከራክር ቢሆንም የሕጉን ሥርዓትና ደንቡን ያሟላ ባይዞታዎች በአስተዳደር በኩል የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው ጠይቀው አላግባብ ቢከለከሉ ይህንንም እስከ መጨረሻው አስተዳደራዊ እርከን ድረስ ለማሣረም ሞክረው የይዞታ የምስክር ወረቀት አታገኙም ተብሎ ቢወስንባቸው ይህንን አስተዳደራዊ ውሣኔ በመቃወም ሕጉንና ደንቡን አሟልተው በቦታው ላይ የሚገኙ ሕጋዊ ባለይዞታዎች መሆናቸውን በፍርድ እንዲረጋገጥላቸው ከመጠየቅ የሚገድባቸው ሕግ የሌለ በመሆኑ ጉዳዩ የክስ ምክንያት የለውም በሚለው መደምደሚያ ባለመስማማት ከሙያ አጋሮቼ በሀሣብ ተለይቻለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረትና ቦታ ሕጋዊ ባለይዞታ መሆኔ በፍርድ ይረጋገጥልኝ የሚለው ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም የሚባል ከሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አንድ የማይነቀሳቀስ ንብረት በይዞታቸው ሥር በማድረግ ለአስራ አምስት ዓመት ግብር እየገበሩ የኖሩ ሰዎች አስተዳደሩ ለአስራ አምስት ዓመት የቦታውና የንብረቱ ባለይዞታ መሆናቸውን እና በስማቸው ግብር መክፈላቸውን የሚያረጋግጥ የይዞታ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ባይቀርብላቸው ይህንን በማስረጃ በማጣራት ፍርድ ቤቱ የንብረቱ ባለይዞታ ብቻ ሣይሆኑ የንብረቱ ባለቤት መሆናቸውን በፍርድ እንዲያረጋግጥላቸው የሚያቀርቡትን ጥያቄ በፍርድ ቤት ሊወሰን አይችልም በሚል መንገድ፣ የሚዘጋበት የሕግ አተረጓጎም እና መደምደሚያ የሚያስከትል ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ሰዎች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168 ንዑስ አንቀጽ 1 የተረጋገጠላቸውን መብት በአስተዳደር አካላት ቢጣስ በፍርድ ቤት ክስ አቅርበው መብታቸውን እንዲያረጋግጡ የሚያደርግ በመሆኑ በጥንቃቄ መታየት አለበት የሚል ሀሣብ አለኝ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ከዚህ በፊት ስልጣን ባላቸው አካላት ታይቶ የተወሰነ መሆኑን ተከራካሪዎቹ ካደረጉት ክርክር ለመረዳት የሚቻል ሲሆን፣ ይህ ችሎትም እነዚያን ውሣኔዎች ይዘትና ምንነት በመመርመር ለመወሰን የሚያስችለውን ሥርዓት መከተል ነበረበት፡፡ በሌላ በኩል የይዞታ መብት ጥያቄና ይዞታን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የማግኘት ጥያቄ በባሕሪው በፍርድ ቤት የማይታይና ክስ የማይቀርብበት ጉዳይ አይደለም፡፡ አስተዳደሪዊ መፍትሔዎችን አሟጥጦ የጨረሰ ሰው እስከመጨረሻው እርካን ድረስ ባለው አስተዳደራዊ መዋቅር የተሰጠው ውሣኔ ሕጋዊ የይዞታ መብቱ እውቅና የማይሰጥና መብቱን የሚሸራርፍ ነው ብሎ ሲያስብ በበቂ ማስረጃ ለፍርድ ቤቶች ክስ ማቅረብና የቦታውና የነብረቱ ሕጋዊ ባለ ይዞታ መሆኑን፣ በፍርድ እንዲረጋገጥለት መጠየቅና ፍርድ

ቤቶችም ጉዳዩን አይተው ለመወሰን የዳኝነት ስልጣን አላቸው በማለት አብላጫው ድምጽ ከሰጠው የሕግ ትጉምና ከደረሰበት መደምደሚያ በሀሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 37281

ታህሳስ 16 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ አበበ ዓሊ - ቀርበዋል

**ተጠሪዎች**፡- 1. የ08 ቀበሌ ገ/ማህበር - አልቀረቡም

2. አቶ ዓሊ ሰይድ - አልቀረቡም

3. ወ/ሮ ገዛሽ ስዩም - አልቀረቡም

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኂላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ አቤቱታ የቀረበው አመልካች ሚያዝያ 07 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጠ/ፍ/የፍ/ይ/መ/ቁ. 336/2000፣ ጥር 21/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲሻርላቸው በመጠየቃቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን፣ በቃሉ መረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሳሽ፣የአሁኑ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ክስ የመሰረታዊ ይዘቱ ክርክር የተነሳበትን ቤቴን አንደኛ ተከሳሽ (አከራይ) ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ደግሞ (ተከራዮች) በመሆን አላግባብ ይዘው ስለሚገኙና ቤቴን ሊያስረክቡኝ ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ከመስከረም 1998 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 100(አንድ መቶ) ሂሳብ ክስ እስከ ቀረበበት ጊዜ ድረስ ታስቦ በጠቅላላ ብር 500(አምስት መቶ ብር) ከፍለው ተገደው እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ክስ የቀረበለት ወረዳ ፍርድ ቤትም በፍ/መ/ቁ.02127/98 ጥር 18 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አከራካሪው ቤት በመንግስት እጅ የሚገኝ በመሆኑና በመንግስት እጅ የሚገኝ የተወረሰ ቤት ደግሞ በአዋጅ ቁ. 110/1987 መሰረት የመወሰን ስልጣን ያለው የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ ፍርድ ቤቶች አይደሉም በማለት የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ሥራና ከተማ ልማት ቅ/ጽ/ቤት ጥር 08/1999 ዓ.ም ደብዳቤ እንደፃፈ በመግለጽ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም ብሏል፡፡ የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት በፍ/ይ/መ/ቁ. 14649 ካከራከረ በኂላ ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ ያጸናው ሲሆን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ጉዳዩ በይግባኝ ቢቀርብለትም በጠ/ፍ/የፍትሐብሔር ይግባኝ መ/ቁ 336/2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ሚያዝያ 07 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ወደዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም ተጠሪዎቹ በውርስ ያገኘሁትን ቤት አላግባብ ይዘዋል፤ቤቱ በመንግስት የተወረሰ አይደለም፤ ይህ አከራካሪ ቤት እንዲመለስልኝ ለቃሉ ወረዳ ምክር ቤት አመልክቼ ምክር ቤቱም መፍትሄ እንዲሰጠኝ ወደ የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ደብዳቤ ጽፎልኝ ኤጀንሲውም በበኩሉ ጳጉሜ 03 ቀን 1996 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ በአዋጁ ከተሰጠው ስልጣን አኳያ ተገናዝቦ ሲታይ በስልጣኑ ስር እንደማይወድቅና የማየት ስልጣን እንደሌለው በግልጽ ወስኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶቹ ያቀረብኩትን ክርክር በአግባቡ ሳይመረምሩ በደፈናው ስልጣን የለንም ማለታቸው ተገቢ

አይደለም፤የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አከራካሪውን ቤት የመመለስ ጉዳይ በተሰጠው ስልጣን ውስጥ እንደማይካተት በግልጽ አስቀምጦ እያለ ፍ/ቤቶቹ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው ማለታቸው የፍትህ ጥያቄን ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡

አንደኛ ተጠሪም በቁጥር ፍ/ደ/ማ 19/421/2000 ሐምሌ 03 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ሰጥቷል፤ይዘቱም አከራካሪው ቤት በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን፣ኮምቦልቻ ከተማ 08 ቀበሌ ገበሬ ማህበር ክልል ልዩ ስሙ ሚጢቆሎ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኝ በምስራቅ የአቶ አብዱ ረዲ ቤት፣በምእራብ የ08 ቀ/ገ/ማህበር ጽ/ቤት፣ በደቡብና በሰሜን የመኪና መንገድ የሚያዋስናው ከእንጨትና ከጭቃ የተሰራ ሁለት ክፍል ቤት ሲሆን የአቶ ዓሊ ሙሄ እንደነበር ይታወቃል፣ ቤቱ በአዋጅ ቁ. 47/67 የተወረሰ ነው፣የቤቱ ባለቤት የነበሩት አቶ ዓሊ ሙሄ ቤቱ እንዲመለስላቸው ጥረት እያደረጉ የነበረ ቢሆንም ቤቱ እንደማይመለስላቸው በወቅቱ ተነግሯቸዋል፤የአሁኑ አመልካችም ይህንን ጠንቅቀው ያውቃሉ፤አቶ ዓሊ ሙሄ በሞት የተለዩት በ1971 ዓ.ም ስለሆነ አመልካች ከ33 ዓመታት በኋላ አሁን ያቀረቡት ክስ በይርጋ እንደሚታገድ ተቃውሞ አቅርቤበት እያለሁ የስር ፍ/ቤቱ ምንም አይነት ብይን ሳይሰጥበት አልፏል፣ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶቹ በአከራካሪው ቤት የሰጡት ፍርድ ተገቢ ስለሆነ ይጽናልኝ የሚል ሲሆን፡፡ ሁለተኛ ተጠሪም ሐምሌ 16 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው አከራካሪው ቤት በመንግስት የተወረሰ ሆኖ እኔ በኪራይ ይዤዋለሁ፤ተጨማሪ ወጪ አድርጌበታለሁ፤ አመልካች ይህንን ክስ ጊዜውን ጠብቆ ያቀረበው ባለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000 በይርጋ ይታገዳል ብለዋል፤ሦስተኛ ተጠሪ ስላልቀረቡ የሰጡት መልስ የለም፡፡

አመልካችም በመሰረቱ ከአቤቱታቸው ያልተለየ የመልስ መልስ ያቀረቡ በመሆኑ ደግሞ መዘርዘር ሳያስፈልግ ታልፏል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የክርክሩ አመጣጥ ከላይ በሰፈረው መልኩ ከተገነዘበ በኋላ የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አከራካሪውን ቤት የማየት ስልጣን የለኝም እያለ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም ማለት ነበረበት ወይስ አልነበረበትም? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤቱ ባቀረቡት የቤት ይመለስልኝ ክስ የቃሉ ወረዳ ፍ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው ቤቱ በመንግስት የተወረሰ ነው የሚል ክርክር በመቅረቡና የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከተማ ልማት በመንግስት የተወረሱ ቤቶች አይቶ መወሰን የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሰረት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ መደበኛ ፍርድ ቤቶች አይደሉም ያለውን ነው፡፡ በእርግጥ በአዋጅ ቁ. 47/1967 የተወረሱ ቤቶች እንዲሁም ከዚህ አዋጅ ውጭ በደርግ ጊዜ በቀላጤ የተወረሱ ቤቶችን መደበኛ ፍርድ ቤቶች አከራክረው የመወሰን ስልጣን የላቸውም፣ በሚመለከተው የአስተዳደር አካል እንዲሁም በቀላጤ የተወረሱ ከሆነ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 110/1987 መሰረት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ይታያሉ እንጂ በመደበኛ ፍ/ቤቶች አይደለም፡፡ አሁን ክርክር የተነሳበት ቤት በሚመለከት ግን ቤቱ የተወረሰ ነው ከሚል ግምት ውጭ የግራ ቀኙ ወገኖች ማስረጃዎች በዝርዝር አልተመዘኑም፣ የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አከራካሪውን ቤት የማየት ስልጣን የለኝም ብሎ ደብዳቤ ጽፏል የተባለው በተገቢው ሁኔታ ተገናዝቦና ተተንትኖ ፍርድ ያረፈበት አይደለም፤የዞኑ የስራና ከተማ ልማት ቅ/ጽ/ቤት ደብዳቤ ስለፃፈ የሚለው ምክንያት በማስቀመጥ ክርክሩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የተሰጠው ፍርድ የተሟላ አይደለም፤ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁ. 47/1967 የተወረሰ ቤት ወይም ከዚሁ አዋጅ ውጭ በደርግ ስርአት ጊዜ በቀላጤ የተወረሰ ቤትን በሚመለከት አከራክሮ የመወሰን ስልጣን የለኝም ለማለት ይህ መሆኑ በተከራካሪ ወገኖች ወይም በሌላ አካል ስለተጠቀሰ ብቻ ሳይሆን የቀረቡለት ማስረጃዎችና አጠቃላይ የክርክር አቅጣጫዎች በመመዘን ይህ መሆኑ የሚያመላክቱ ሆነው ሲያገኛቸው ነው፤በአሁኑ ክርክር ግን የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ጉዳዩ ስልጣኑ እንዳልሆነ ገልጿል እየተባለ ነው፤በአጠቃላይ የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞዎች ሳይመዝኑና ሳይበይኑ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የተሰጠው ፍርድ በመሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የቃሉ ወረዳ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 02127/98 ጥር 18 ቀን 1999 ዓ.ም የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 14649፣ጥቅምት 15 ቀን 2000 እንዲሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በጠ/ፍ/ይ/መ/ቁ.

336/2000 ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጧቸው ፍርዶች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፤ይፃፍ፡፡

2. የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክርና የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ ከማስረጃዎቻቸው አኳያ በተገቢው ሁኔታ ሳያገናዝብ አመልካች ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁ. 110/87 መሰረት የኢትዮጵያ ፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስልጣን ነው በማለት የቃሉ ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገቡን መዝጋቱ የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ተቀብለው ማጽደቃቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፤ስለሆነም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክርና የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ ካቀረቡት ማስረጃና የህግ ይዘት አኳያ አገናዝቦ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 መሰረት ለቃሉ ወረዳ ፍርድ ቤት ተመልሶለታል፤ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍርድ ቤት ላደረጉት ክርክር ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፤ጉዳዩ ያለቀ ስለሆነ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 37339

ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ንግሥት ኃይሌ - ተወካይ አቶ ኃይሌ በልሁ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ለገሠ ዓለሙ ጠበቃ - አቶ ብስራት መኰንን ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለመርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57224 ታህሣሥ 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35533 መጋቢት 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች በከፍተኛው ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርባና ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሣሥረው ሲኖሩ በአገር ውስጥና በአሜሪካን ሀገር የጋራ ሀብት ያፈሩ መሆኑን በመግለጽ፣ ጋብቻችን በፍች ፈርሶ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአገር ውስጥ ያለንን የጋራ ሀብት አስመልክቶ ክርክራችንንና ማስረጃችን በመመርመር ውሣኔ የሰጠ ሲሆን በአሜሪካን አገር የሚገኘው ንብረት በተመለከተ ስልጣኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው በማለት ጥያቄን ያልተቀበለኝ ለመሆኑ በውጭ ያለንን የጋራ ንብረት አስመልክቶ አከራክሮ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርባለች፡፡ ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ የሁለታችንም በዜግነት ኢትዮጵያዊያን ነን፡፡ ንብረቱ በአሜሪካን አገር መኖሩ የዓለም አቀፍ የግል ሕግ ጥያቄ የማያስነሣና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የሥረ-ነገር ስልጣን የማያሣጣ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ጉዳዩ የዓለም አቀፍ የግል ሕግ ጥያቄ አያስነሣም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው ከገለፀ በኋላ በአሜሪካን አገር የተገኘ ንብረት ብቻ ተነጥሎ በዚህ ፍርድ ቤት የሚያስተናግድበት ሥርዓት የለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን ይግባኝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባታል፡፡ አመልካች ያቀረብነው የጋራ ንብረት ጥያቄ በተመለከተ በአገር ውስጥ የሚገኘውን ሀብት በተመለከተ አከራክሮ ከወሰነ በኋላ በአሜሪካን አገር የተጠራቀመውን 9713.12 ዶላር /ዘጠኝ ሺ ሰባት መቶ አስራ ሶስት ዶላር ከአስራ ሁለት ሣንቲም/ የክፍፍል ጥያቄ በተመለከተ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ ጥያቄ የሚያስነሣ በመሆኑ ስልጣን ባለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይታይ በማለት መዝገቡን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልኳል፡፡ ሆኖም ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን የተላከለትን የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በመዝጋት ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ አድርጓል፡፡ እኔም አዲስና ራሱን የቻለ ክስ ውጭ ያለውን ገንዘብ አስመልክቶ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ሣቀርብ አላግባብ ውድቅ ሆኖብኛል፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ ያቀረብኩትን የመብት ጥያቄ ውሣኔ ሣይገኝ እየተጉላላሁ ያለሁ በመሆኑና ይኽም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ጠይቃለች፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡትን መዝገብ ዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ሲመልስ ይግባኝ ማቅረብ ሲገባት እንደ አዲስ ክስ ማቅረቧ ተገቢ አይደለም ሕጋዊ ሥርዓትን የተከተለ አይደለም፡፡ ስለዚህ

የመጨረሻ ውሣኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ እንደገና ክስ ማቅረቧ ተገቢ ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ፍርድ ቤቶቹ ሥልጣኑ የአንተ ነው እየተባባሉ ጉዳዩን አንጠልጥለው ከማስቀረታቸው ውጭ በጉዳዩ ላይ የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ የለም፡፡ እንደ አዲስ ክስ ማቅረቤ ተገቢ ነው በማለት በመልስ መልሱ ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ መነሻና አመጣጥ በሰበር አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው :

1.ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ነው ወይስ አይደለም?

2. የአመልካች ክስና ጥያቄ በሥር ፍርድ ቤት ሊታይና ሊስተናገድ የሚገባው ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ የአመልካችና የተጠሪ ጋብቻ በፍች እንዲፈርስ የወሰነው የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ በአገር ውስጥ ያላቸውን የጋራ ሀብት አስመልክቶ ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሣኔ የሰጠ ሲሆን በአሜሪካን አገር አለ ስለተባለው ሀብት ሥልጣኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ ውሣኔ ይሰጥበት በማለት መዝገቡን ወደ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ልኮታል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በበኩሉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የላከለትን መዝገብ አመልካችን ሣይጠራ በከፊል በሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ያገኘ ጉዳይ ተቀብዬ የማስተናግድበት ሥርዓት የለም በማለት መዝገቡን ዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት የመለሰው መሆኑ ፍርድ ቤቱ ጥር 16 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በውጭ አገር አለ ያሉትን የጋራ ሀብት አስመልክቶ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 በተሰጠው ስልጣን መሠረት እንዲወስንላቸው አዲስ ክስ ያቀረቡ ሲሆን ይህንንም ፍርድ ቤቱ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በግማሽ ጉዳይ ላይ አይቶ ውሣኔ የሰጠ በመሆኑ እኔ ከፊሉን ጉዳይ አይቼ የምወስንበት ሥርዓት የለም በማለት ዘግቶታል፡፡

ከዚህም የምንረዳው አመልካች በአሜሪካን አገር ያለው የጋራ ሀብት እንዲካፈል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበችው ክስና ጥያቄ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ዓለም አቀፍ የግለሰብ ሕግ ጥያቄ ሊያስነሣ ስለሚችል ይህንን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን የላከው መሆኑንና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ በአገር ውስጥ ስላለው ሀብት ውሣኔ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የተሰጠ በመሆኑ በውጭ አገር የሚገኘውን ሀብት ብቻ አይቼ በከፊል የምወስንበት ሥርዓት የለም በማለት በመወሰኑ ጉዳዩ በእንጥልጥል ላይ ያለና የመጨረሻ ውሣኔ ያላገኘ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሆኑም ተጠሪ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ነው በማለት የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች በውጭ አገር ያለው የጋራ ሀብት እንድትካፈል ያቀረበችው ጥያቄ አይቶ የመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን እንደሌለው የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ብይን ከሰጠ በኋላ የአመልካችንና የተጠሪን ክርክር የተሰማበትን የመዝገብ ቁጥር 00289 ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ልኮለታል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህንን የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥሩ 54637 በሆነ ፋይል ከሸፈነ በኋላ በአመልካች ጥያቄ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ትእዛዝ የተላለፈለትን ጉዳይ አመልካችን ሣይጠራ ጉዳዩ የሚያስተናግድበት ሥርዓት የሌለ መሆኑን በመግለጽ የሥር ፍርድ ቤትን መዝገብ የራሱ መዝገብ አካል በማድረግ ወደ መዝገብ ቤት እንዲመለስ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ሒደት ያልተጠራችው ተጠሪ ያቀረበችውን ክስም ውድቅ አድርጓል፡፡

ከዚህም የምንረዳው ሁለቱ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን እኔ አላየውም የሚሉበትን የተለያዩ ምክንያቶች በመጥቀስ በሰጡት ትእዛዝ የአመልካች ጥያቄ በእንጥልጥል የቀረ መሆኑን ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በዳኝነት ሊወሰን የሚገባው ጉዳይ በዳኝነት እንዲታይለትና ፍትህ የማግኘት መብት ያለው መሆኑ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 37 ተደንግጓል፡፡ አመልካች በውጭ አገር አለ የምትለው የጋራ ሀብት ጥያቄ በዳኝነት እንዲታይለትና ፍትህ እንዲሰጣት የመጠየቅ ሕገ-መንግሥታዊ መብቷ ነው፡፡ ሆኖም የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን አንደኛው ለሌላው

በመግፋት ይህንን ሕገ-መንግሥታዊ መብቷን የሚጥስ ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች ያቀረበችው የዳኝነት ጥያቄ ምላሽ ማግኘትና መስተናገድ ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የአመልካች ጥያቄ በየትኛው ፍርድ ቤት ይስተናገድ የሚለውን ነጥብ በተመለከተ ጉዳዩ የዓለምአቀፍ የግል ሕግ ጥያቄ የሚያስነሣ መሆኑን የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57234 ታህሣሥ 17 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ብይን አረጋግጧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበችው ክስ የዓለም አቀፍ የግል ሕግ ጥያቄ የሚያስነሣ ነው የሚለው መደምደሚያ ላይ ከደረሰ፣ አመልካች ተጠሪ በአገር ውስጥ ያፈሩት የጋራ ሀብት ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አከራክሮ መወሰኑን እንደከፍተኛ ስህተት በመቁጠር ጉዳዩ በከፊል ለመጀመሪያ ፍርድ ቤት የታየ ስለሆነ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ በሕገ-መንግሥቱ የተረጋገጠውን የአመልካችን ፍትህ የማግኘት መብትና ለፍርድ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 4 የተሰጠውን ሥልጣን የሚጥስ ስህተት ያለበት ሆኖ እያለ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማጽናቱ ተገቢነት የሌለውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57224 ታህሣሥ 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 35533 መጋቢት 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በውጭ አገር አለ የሚሉትን የጋራ ሀብት ጥያቄና ማስረጃ የተጠሪን መልስና ማስረጃ ሰምቶ እንዲወስን ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል ይፃፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ራሣቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
5. በትውስት የመጣው የከፍተኛው ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 54637 ይመለስ፣ ይፃፍ፡፡

   ይኽ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጥር 28 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 37016

የካቲት 3 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ተስፋዬ ማሞ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በተከሣሽ ድርጅት በበላይ ገንዘብ ያዥነት /senior teller/ በማገልገል ላይ ሳለሁ በ10ኛው ኅብረት ስምምነት መሠረት የሥራ መደቡ መጠሪያ ስያሜ ተለውጦ ኦፊሻል 3 የሚል መጠሪያ በመሰጠቱ ምክንያት ለሥራ መደቡ ማግኘት የሚገባኝን ልዩ ጭማሪ ብር 219 /ሁለት መቶ አሥራ ዘጠኝ ብር/ ተከሣሽ ከልክሎኛል፡፡ ስለሆነም ተከሣሽ ከ24/5/99 ዓ.ም. ጀምሮ ማግኘት የሚገባኝን ልዩ ጭማሪ በመክፈል ወደ ቀድሞው የበላይ ገንዘብ ያዥነት የሥራ መደብ እንዲመልሰኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሽም /የአሁን አመልካች/ ቀርቦ በሰጠው መልስ ከሣሽ የሚሠሩበት የሥራ ደረጃ 14 ሲሆን በዚህ ደረጃ የሚከፈለው ደመወዝ አሁን እየተከፈላቸው ካለው ደመወዝ የሚያንስ ሲሆን የተሻለ ደመወዝ እየተከፈላቸው ባለበት ሁኔታ ልዩነት ብር 219(ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር) ሊከፈለኝ ይገባል ያሉት በተገቢው አይደለም፡፡ በከሣሽ ላይ የሥራ ለውጥ ያልተደረገ ሲሆን ተደርጓል ቢባል እንኳን የከሣሽ የትምህርት ዝግጅት ማነስ የሥራ አፈፃፀም ዝቅተኛነት፣ የደንበኞች ቅሬታና የቅርብ ኃላፊዎች ግምገማ ተጨምሮበት በባንኩ የአደረጃጀት የአሠራር ለውጥ /BPR/ መሠረት ከሣሽ እንዲሠሩ የታመነበት አሁን እየሠሩ ያሉበት የሥራ መደብ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ማስረጃ ሠምቶ በተከሣሽ መ/ቤት ሥራ የተቋቋመው የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ /BPR/ ኮሚቴ አባላት ቀርበው በሰጡት የምስክርነት ቃል ከሣሽ ለነበሩበት የሥራ መደብ ብቃት እንደሌላቸው የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ቢሆንም የግል ማኅደራቸውን ፍ/ቤቱ አስቀርቦ እንደተመለከተው መልካም የሥራ አፈፃፀም እንደነበራቸው ስለሚያሳይ የኮሚቴው ውሣኔ በበቂ ማስረጃ የተደገፈ ባመሆኑ ከሣሽ ወደ ቀድሞ ከፍተኛ ገንዘብ ያዥነት የሥራ መደብ ሊመለሱ እና የመደቡ የደመወዝ ልዩነትም ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በሚሉት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪ ወደ ቀድሞው የሥራ መደብ ሊመለሱ ይገባል ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ አግባብነቱ ተጠሪ ባሉበት ሊጣራ እንደሚገባ በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በቅድሚያም ችሎቱ የተመለከተው የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው መሆኑን በተመለተ ነው፡፡

ተጠሪ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በክስ አቤቱታቸው ዳኝነት የጠየቁት ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ቀድሞ ስሰራበት ወደነበረው የሥራ መደብ እንድመለስና ለመደቡም የተሰጠው ልዩ ጭማሪ እንዲከፈለኝ በማለት ነው፡፡

የአሠሪና ሠራተኛን ግንኙነት በሚገዛው በአዋጅ ቁጥር 377/96 ለወልም ሆነ ለግል የሥራ ክርክር የተሰጠ ትርጉም ባይኖርም ነገር ግን አንድ የሥራ ክርክር የወል የሥራ ክርክር ወይንም የግል የሥራ ክርክር ነው ለማለት የሠራተኛው ቁጥር እንደ መለያ መስፈርት ሊያገለግል እንደማይችል ከአዋጁ አንቀጽ 138 እና 142/1/ ዝርዝር ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ክርክሩ የወል ነው ለማለት የጋራ የሆነን የሠራተኞችን መብትና ጥቅም ጋር ግንኙነት ያለው ማለትም የደመወዝም ሆነ የሌላ ጥቅም፣ የቅጥርም ሆነ የዕድገት አሰጣጥ፣ የዝውውርም ሆነ የሥልጠና ከመሣሰሉት ጋር ግንኙነት ኖሮት በጋራ በሆነ ሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤት በሚያስከትል ጊዜ እንደሆነ ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው አንቀጽ 142/1/ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ ጥያቄ ወደ ቀድሞ የሥራ መደቤ እንድመለስና ለመደቡም የተሰጠው ልዩ ጭማሪ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ የሚል እንደመሆኑ መጠን የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ በአንቀጽ 142/1/ሀ/ እና /ለ/ ሥር የሚሸፈንና የወል የሥራ ክርክር ተብሎ የሚመደብ ነው፡፡ ክርክሩ የወል ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ የሚታየው በአስማሚ ወይም በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አማካኝነት እንጂ በፍ/ቤት በኩል ስላልሆነ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በዚህ ሁኔታ ጉዳዩን ተቀብሎ ውሣኔ መስጠቱ በአንቀጽ 138/1/ ሥር ከተሰጠው የሥረ-ነገር ሥልጣን ውጭ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል፡፡

ስለሆነም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በዚህ መልኩ የሰጠው ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 21652 በ5/5/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 63054 በ26/7/2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 39085

የካቲት 3 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን - ነ/ፈጅ አቶ ዳንኤል ጥበቡ ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- እነ ወ/ር አስረሳች ወርቅነህ (87 የጉምሩክ ፖሊሶች)

ጠበቃ ሙሉጌታ ወንድማገኝሁ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው የጉምሩክ ፖሊሶች ወደ ስራ እንመለስ የሚል ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሳሾች የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ሲሆኑ አመልካች ተከሳሽ ነበር፡፡ እሱም በድርጅቱ ከተራ ወታደርነት እስከ መኮንንነት ተመድበን ከምንሰራበት በማይታወቅ ሁኔታ ሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ ያሰናበተን ከጉምሩክ ፖሊሶች መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 4/96 ውጪ በመሆኑ ሕገ-ወጥ ነው እንዲባልና ወደ ስራ እንድንመለስ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ አመልካች በሰጠው መልስ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለውም በጉምሩክ አዋጅ የመዋቀር ማስተካከያ በማድረግ የሰው ኃይል ለመጨመርም ሆነ ለመቀነስ ስልጣን ተሰጥቷል፡፡ መመሪያው የዲስፒሊን እርምጃን የሚመለከት እንጅ የመዋቀር ማስተካከልን የሚከለክል አይደለም በማለት ስንብቱ ሕጋዊ መሆኑን በማስመልከት የመቃወሚያና በአማራጭ የፍሬ ነገር ክርክር በማቅረብ ተከራክሯል፡፡ ግራ ቀኙን ያከራከረው የመጀመሪያ ፍ/ቤት ወደ ቀድሞ ስራቸውና ደመወዛቸው እንዲመለስ ሲል ወስኗል፡፡ ከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ/ቁጥር 64577 ሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የመጀመሪያ ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 7 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው አቤቱታ መሰረት በማድረግ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ስልጣን አለው ወይንስ የለውም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ታዝዞ ተጠሪዎች ቀርበው እንዲከራከሩ ተደረጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ ክርክር አካሄደዋል፡፡

እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

የአመልካች ዋና ክርክር በአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀጽ 8/2/መ እና በአዋጅ ቁጥር 368/1995 በተሻሻለው መሰረት የጉምሩክ ፖሊሶች የሚተዳደሩት የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በሚተዳደርበት አኳኋን ነው፡፡ በዚህ ዓይነት በተሰጠው ውሳኔ ላይ ፍ/ቤት ማየቱ ተገቢ አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ ለሚደርሰው የመብትና የፍትህ መጓደል አቤቱታ የሚቀርብበት በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል ባለመኖሩ መብትና ጥቅማችን የሚያስከብርና ሕጐችን በመተርጐም የሚወሰንልን መደበኛ ፍ/ቤት ብቻ ስለሆነ ክሱን ተቀብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአዋጁ ቁጥር 368/95 እንደተመለከተው የጉምሩክ ፖሊስ ኃይል የሚተዳደረው የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን አዋጅና ደንብ ተከትሎ በሚወጣው መመሪያ መሰረት እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች በግልጽ ባልተመለከቱ ጉዳዮች ስንብት ቢፈፀም በፍ/ቤት እንደሚታይም አልተመለከቱም፡፡ የበታች ፍ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው በመመሪያ ቁጥር 4/1996 ከተመለከተው የጉምሩክ ፖሊስ አገልገሎት ከሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ውጪ በሆነ ሁኔታ ከመዋቅር ማሻሻያ ጋር ተያይዞ ከመጣው የጉምሩክ ፖሊስ ኃይል አደረጃጀትን የሚመለከት ጉዳይ እንጂ

በመመሪያው ላይ ስለስንብት የተመለከተውን ምክንያት የሚሽር ባለመሆኑ ስንብቱ ከመመሪያው ውጪ ነው በማለት ነው፡፡ በመመሪያው ከተመለከቱ ምክንያቶችም ሆነ በመመሪያው ከተመለከቱ ምክንያቶች ውጪ የጉምሩክ ፖሊስ የስራ ስንብት ጉዳይ ሊታይ የሚችለው የፌዴራል ፖሊስ በሚተዳደረው ስርአት እንደሆነ በአዋጁ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ የጉምሩክ ፖሊሶች የስንብት፣በስራ ላይ ማስማራትም ሆነ የዲስፒሊን ውሳኔ ጉዳዮች በቀጥታም ሆነ በይግባኝ በፍ/ቤት በዳኝነት ሊታይ የሚችልበት ስርአት በአዋጅ ወይም በመመሪያው ባልተመለከተበት ስንብቱ ሕጋዊ ነው ወይንስ ከሕግ ውጪ ነው በማለት በፍ/ቤት ጭብጥ ተይዞ ክርክር ሊካሄድበትና ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

በመሆኑም የበታች ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ብቸኛ ስልጣን ያለው ፍ/ቤት ነው በማለት ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክስና ክርክር ተቀብሎ ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው ወደ ስራ መልሷቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ በአዋጅ በግልጽ የፌዴራል ፖሊስ በሚተዳደረው ስርአት (executive provocative) የሚታየውን ጉዳይ ያለስልጣኑ ለጥጦ በመተርጐም በፍ/ቤት የሚታይ ጉዳይ በማድረግ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ የተመለከተው የከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ማረም ሲገባው በማጽናት የሰጠው ውሳኔ ከላይ በተመለከቱ ምክንያቶች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 98010 በ14/5/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 64527 በ1/11/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጡ ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም ብለናል፡፡
3. ተጠሪዎች ወደ ስራ ሊመለሱም ሆነ ደመወዝ ሊከፈላቸው አይገባም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የቻቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 38745

መጋቢት 10 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

ዓልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች፡-** 1. ወ/ሮ ሳሊያ ኢብራሂም - ወኪል 2ኛ አመልካች

2. አቶ ሙሐዲን ጀማል - ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** ሐጂ ሰማን ኢሳ- በሌሉበት

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሚተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ይህ ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26/98 ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም እና ሚያዝያ 08 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጣቸው ውሳኔዎች መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆናቸው ይሻሩልን በማለታቸው ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በኢሊባቡር ዞን ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ሲሆን በዚሁ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካቾች ተከሳሾች፣የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን፣የስር ከሳሹ ነሐሴ 09 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘቱ አንደኛዋ ተጠሪ ሚስቴ ሆና እያለች ሁለተኛው ተጠሪ የሸሪዓን ህግ በመጣስ ስላገባት በጋብቻ ላይ ጋብቻ በመፈፀም ጥፋት ስለፈፀመ በህግ ፊት ቀርቦ የጥፋተኝነት ውሳኔ ይሰጠው የሚል ነው፡፡ ስር ተከሳሾች በቀነ ቀጠሮው ባይቀርቡም የስር ፍ/ቤቱ ሐምሌ 6 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ብይን ጉዳዩ ወንጀል ነክ በመሆኑ አከራክሬ የመወሰን ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ስር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪም በስር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ላይ ቅሬታ በማሳደር ጉዳዩን በይግባኝ እንዲታይላቸው ለኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበውት ፍ/ቤቱም ተከሳሾቹ በሌሉበት በመ/ቁ 26/98፣ሚያዝያ 08/1999 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ አቶ ሙሒዲን ጀማል ወ/ሮ ሳሊያ ኢብራሂም የሐጂ ሰማን ኢሳ ህጋዊ ባለቤት መሆኗን እያወቀ ስላገባት በጋብቻ ላይ ጋብቻ በመፈፀም ጥፋት ፈጽሟል በማለት ስር ተከሳሾቹ ለከሳሹ ብር 1700 (አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር) እንዲከፍሉትና በሚመለከተው አካል በወንጀል የመክሰስ መብቱ በመጠበቅ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላም የአሁኑ አመልካቾች ታህሳስ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78/1/2/ መሰረት ባሉበት ክርክሩ እንደገና እንዲካሄድ ፍርዱን ለሰጠው የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት አመልክተው ከተፈቀደላቸው በኋላ ያቀረቡት ክርክር በጋብቻ ላይ ጋብቻ እንዳልፈፀሙ፣አቶ ሙሐዲን ወ/ሮ ሳሊያን ያገባት ቀደም ብሎ ከሐጂ ሰማን ኢሳ ጋር የነበራትን ጋብቻ /ኒካ/ ከፈረሰ በኋላ እንደሆነና ማስረጃም እንዳላቸው የሚገልጽ ሲሆን ይግባኝ ባዩ ሐጂ ሰማን ደግሞ ከወ/ሮ ሳሊያ ጋር የነበረኝ ጋብቻ በሸሪዓ ፍ/ቤት አልፈረሰም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤቱም በኦ/ጠ/ሸሪዓ ፍ/ቤት መ/ቁ. 26/98፣ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ተከሳሾቹ በጋብቻ ላይ ጋብቻ አልፈጸምንም በማለት ያቀረባቸው የጽሁፍ ማስረጃዎች ማለትም የዘመድ ዳኞች በ27/08/1990 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና የኢልባቦር ዞን የእስልምና ጉዳዮች ጉባኤ በ01/02/1993 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ሲታዩ እነዚህ አካላት ጋብቻውን የማፍረስ ስልጣን የላቸውም በማለት ተከሳሾቹ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ፈጽመዋል በማለት ቀደም ብሎ ማለትም በመ/ቁ. 26/98፣ሚያዚያ 08/1999 ዓ.ም ሰጥቶት የነበረውን ውሳኔ ተመልሶ አጽድቆታል፡፡

ከላይ የሰፈረውን ውሳኔ በመቃወምም የአሁኑ አመልካቾች ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም በጋብቻ ላይ ጋብቻ አልፈፀምንም፤ጋብቻችንን የፈጸምነው በአንደኛ አመልካችና በተጠሪው መካከል የነበረው ጋብቻ በህጋዊ አካል ከፈረሰ በኂላና ይህንን መሰረት በማድረግ የኢልባቦር ዞን የእስልምና ጉዳዮች ጉባኤ በቁጥር DHIIL 62/3/3-1/93 ጥቅምት 01/1993 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ወ/ሮ ሳሊያ ኢብራሂም ጋብቻዋ የፈረሰ በመሆኑ የፈለገችውን ማግባት እንደምትችል ማረጋገጫ ከሰጠ በኂላ እንደሆነ፤በጋብቻ ላይ ጋብቻ ፈጽማችኂል በማለት በብር 1700 (አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር) በወንጀል እንድንቀጣ መወሰኑ መዝገቡን በጥልቀት ሳይመረምር ከስልጣኑ ውጭ እንደሆነ በመግለጽ በኦ/ጠ/ሸሪዓ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይሻርልን የሚል ነው፡፡

ተጠሪው ለቃል ክርክር ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ መጥሪያው ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ፍ/ቤቱ ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ አዞ የተካሄደ ያለ በመሆኑ ተጠሪው መልስ አልሰጡም፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እየተዘረዘረ በመጣው መልኩ ከተገነዘበ በኂላ አመልካቾቹ ጋብቻ የፈፀሙት አንደኛዋ አመልካችና ተጠሪው መስርተውት የነበረው ጋብቻ በህጋዊ መንገድ ሳይፈርስ በነበረበት ሁኔታ ነው ወይስ አይደለም? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ አንደኛዋ ተጠሪ ከእርሳቸው ጋር ያላት ጋብቻ በሸሪዓ ህግ ሳይፈርስ ሁለተኛው ተጠሪ እንዳገባትና ይህ አድራጐትም በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈጸም ስለሆነ አመልካቾች እንዲቀጡለት የሚጠይቅ ሲሆን አመልካቾቹ ደግሞ ቀደም ብሎ በተጠሪው እና በአንደኛ አመልካች መካከል የነበረው ጋብቻ በአግባቡ ከፈረሰ በኂላ እንጂ ጋብቻው ሳይፈርስ እንዳልተጋቡ መልሰዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያከራከረው የኢልባቦር ዞን ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የወንጀል ክርክር ስለሆነ ስልጣን የለኝም ቢልም ጉዳዩን በይግባኝ ያስተናገደው የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ግን በአንደኛዋ አመልካችና በተጠሪው መካከል ቀደም ብሎ የተመሰረተው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሁለተኛው ተጠሪ አንደኛዋን ተጠሪ በማግባት በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈፀሙን በማስመር በብር 1700(አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር) እንደቀጣቸው ነው፡፡ ሽማግሌዎች አፋትተውናል ፍርድ ቤትም ተቀብሎታል፣ቀጥሎም የኢልባቦር ዞን የእስልምና ጉዳዮች ጉባኤ አንደኛዋ አመልካች የፈለገችውን ማግባት እንደምትችል በደብዳቤ ገልፆላታል የሚል ክርክር ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ስልጣን የላቸውም በማለት አልፎታል፡፡ ይሁን እንጂ ቀደም ብሎ በተጠሪውና በአንደኛዋ አመልካች መካከል የነበረው ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ የቀረበለት የዲዱ ላሎ ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩ ወደ ሽማግሌዎች መርቶት ሽማግሌዎቹ ተጋቢዎቹን ለማስታረቅ ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ በመቅረቡ ጋብቻው እንዲፈርስ አስተያየታቸውን ተመልሰው ለወረዳ ፍ/ቤቱ ካቀረቡለት በኂላ የተጠቀሰው ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 48/94፣ሚያዚያ 28 ቀን 1990 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሽማግሌዎቹን አስተያየት ተቀብሎ ፍቺውን እንዳፀደቀ መዝገቡ ያስረዳል፤የመጀመሪያው ጋብቻ የፍቺ ሂደት በዚህ መልክ ከተጠናቀቀ በኂላ እና የኢልባቦር ዞን እስልምና ጉዳዮች ጉባኤ በቁ. DHIILU 62/3/3-1/93 ጥቅምት 01/1993 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ አንደኛዋ አመልካች ከዚህ በኂላ የፈለገችውን ሰው ማግባት እንደምትችል ገልጿል፡፡ የአሁኑ ሁለተኛው አመልካች እነዚህ ሂደቶች ማለትም የመጀመሪያው ጋብቻ ስልጣን ባለው የወረዳ ፍ/ቤት አማካኝነት መፍረሱን አረጋግጠው አንደኛዋ አመልካች እንዳገቡ ነው፡፡ የእስልምና ተከታይ የሆኑ ተጋቢዎች ጋብቻቸው እንዲፈርስ ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ወይም ሁለቱም ከፈቀዱ ደግሞ ወደ ሸሪዓ ፍ/ቤት አስቀርበው እንደምርጫቸው ሊያፈርሱት እንደሚችሉ እየታወቀ የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት የዲዱ ላሎ ወረዳ መደበኛ ፍ/ቤት ቀደም ብሎ የሰጠውን የፍቺ ውሳኔ ወደ ጐን በመተው በአንደኛዋ አመልካችና በተጠሪው መካከል የነበረው ጋብቻ አልፈረሰም፤አመልካቾች በጋብቻ ላይ ጋብቻ ፈጽመዋል ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፤ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 26/98፣ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካቾቹ ጋብቻ የፈጸሙት ቀደም ብሎ በአንደኛዋ አመልካችና በተጠሪው መካከል የነበረው ጋብቻ በዲዱ ላሎ ወረዳ ፍ/ቤት በአግባቡ ከፈረሰ በኂላ በመሆኑ አመልካቾቹ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ባለመፈጸማቸው የተላለፈባቸው የገንዘብ ቅጣት ተገቢ አይደለም ብለናል፡፡
3. ግራና ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍ/ቤት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም የተላለፈው እግድ ተነስቷል፤ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ያለቀ በመሆኑ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 36677

ሚያዝያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሻምሺ ዩኑስ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ኑሪያ ማሚ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 16/99 የካቲት 27 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በድሬዳዋ ናኢባ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በድሬደዋ ናኢባ ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርባ ሟች አባቴ በድሬደዋ ከተማ ቀበሌ 08 በአምስት መቶ ካሬ ሜትር ባለው ቦታ ላይ አመልካች ቦታውን እንድትለቅ ስትጠየቅ ለመልቀቅ ተስማምታ ትንሽ ቤት ሠርታ ትኖር ነበር፤ ቦታውን የያዘችው የዛሬ ሰባት ዓመት ሲሆን ወላጅ አባቴ ከሞተ በኂላ በቦታው ላይ ግንባታ ለማካሄድ ቦታውን እንድትለቅልኝ ስጠይቃት እንቢ ስላለችኝ ቦታውን እንድትለቅ እንዲወሰንልኝ በማለት ክስ ያቀረበች ሲሆን፣ የአሁን አመልካች በተጠሪነት ቀርባ፣ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሠረት የመደበኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ የይግባኝ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በፍሬ ጉዳይ እረገድ ቦታው በአዋጅ ቁጥር 47/1967 የተወረሰ ነው የሚሉና ሌሎች ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡

የናኢባ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበችውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማለፍ የፍሬ ጉዳይ ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኂላ አመልካች ይዞታውን ለተጠሪ እንድትለቅ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለድሬዳዋ ፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ከተከራከሩ በኂላ የከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤቱ የሥረ ነገር ሥልጣንን በተመለከተ የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ በማለፍ በፍሬ ጉዳይ በኩል አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 መሠረት መልሶ ልኮለታል፡፡ ሆኖም በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርባ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ የናኢባ ፍርድ ቤት ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የማያንስ ስልጣን አለው ካለ በኂላ በፍሬ ጉዳይ ረገድ፣ የድሬደዋ ፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የናኢባ ወረዳ ፍርድ ቤትን ውሣኔ በማጽደቅ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህ የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፤ ተጠሪ ያቀረባቸው ክስ የወላጅ አባቴን ይዞታ ታስረክበኝ የሚል ሲሆን እኔ ደግሞ 1982 ዓ.ም. ጀምሮ በቦታው ላይ ቤት ሰርቼ እየኖርኩ ያለሁ መሆኔን ገልጬ የናኢባ ፍርድ ቤት ይዞታን አስመልክቶ የሚነሳ ክርክርን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት ያቀረብኩትን መቃወሚያ አላግባብ አልፎና በይዞታ ጉዳይ አከራክሮ ወስኗል፤ ስለዚህ ያለበቂ ማስረጃ አከራክሮ ውሣኔ የሰጠ በመሆኑ፣ የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤትም የተፈፀመውን የሕግ ስህተት ያላረመ በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሏ ክርክሩ በሸሪዓ ፍርድ ቤት የተደረገው በአመልካች ፈቃደኝነት ነው፤ ስለዚህ የሸሪዓ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች በጽሁፍ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታዋን የሚያጠናክር ክርክር አቅርባለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥ ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን፣ እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የሸሪዓ ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተፈጠረውን የይዞታ መብት ጥያቄ አይቶ የመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከድሬደዋ ናኢባ ፍርድ ቤት፣ ከከፍተኛ ሸረዓ ፍርድ ቤትና ከጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የውሣኔ ግልባጭ ለመረዳት እንደቻልነው ጉዳዩ ይዞታ ክርክር ነው፡፡ ተጠሪ ቤቱ የሟች ወላጅ አባቷ መሆኑንና አመልካች ቤት የሰራችው በአባቷ ፈቃድ ልቀቂ ስትባል ለመልቀቅ ተስማምታ መሆኑን በመግለጽ የምትከራከር ሲሆን፣ አመልካች በበኩሏ ከ1982 ዓ.ም. ጀምሮ ይዞታው የእሷ መሆኑን በመግልጽ የይዞታ ክርክርን የናኢባ ፍርድ ቤት ማየት የለበትም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርባለች፡፡

የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት የወል የዳኝነት ስልጣን በምን ጉዳዮች ላይ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 188/1992 በአንቀጽ 4 ተደንግጓል፡፡ በዚህ የሕግ ድንጋጌ መሠረት በፌዴራል በማናቸውም ደረጃ የሚገኙ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን አይተው የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን የሚኖራቸው፡-

-በማንናቸውም የጋብቻና የፍች፣ የቀለብ አወሳሰን፣ አካለ መጠን ያልደረሱ ሕፃናት ሞግዚትነት እና የቤተሰብ ተዛምዶ ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን አስመልክቶ ጥያቄ ያስከተለው ጋብቻ በእስልምና ሀይማኖት ሥርዓት መሠረት የተፈፀመ የሆነ እንደሆነ ወይም ባለጉዳዮቹ በእስልምና ሀይማኖት ሥርዓት ለመዳኘት አቅደው እንደሆነ፤

- የእውቅና ስጦታ /ሂባ/፣ ውርስ ወይም ኑዛዜ ጉዳዮችን በተመለከተ አውራሹ ወይም ስጦታ አድራጊ ወይም ተናዛዥ ሙስሊም የሆነ እንደሆነ ወይም ሟች በሞተበት ሰዓት ሙስሊም ሆኖ የሞተ እንደሆነ፤
- ከላይ በተገለጹት ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ ክሶችን ኪሣራ የሚመለከት ሲሆን እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ለመረዳት እንችላለን፡፡

ከዚህ ውጪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የናኢባ ፍርድ ቤት፣ የከፍተኛው ሸሪዓ ፍርድ ቤትም ሆነ የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ክርክር የመስማትና ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የላቸውም፡፡ የያዝነው ጉዳይ የይዞታ ክርክር ጉዳይ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ የአንድ ሰው ወራሾች በመሆናቸው ምክንያት የቀረበ የውርስ ንብረት ክፍያ ጥያቄ አይደለም፡፡ ስለሆነም ቦታው የማን ይዞታ ነው የሚለውን ጉዳይ አከራክረው የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሠረት መደበኛ ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የድሬደዋ ናኢባ ፍርድ ቤት ቦታውን አስመልክቶ ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያላነሰ ሥልጣን አለው በማለት መወሰኑ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣው አዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱትን መሠረታዊ ድንጋጌዎች ባለማገናዘብ የተሰጠ ሆኖ ስላገኘነው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት እና የድሬዳዋ ናኢባ ፍርድ ቤት የይዞታ ጉዳይ አከራክረው የመወሰን የዳኝነት ስልጣን የሌላቸው በመሆኑ ውሣኔያቸው ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. ይህ ውሣኔ ተጠሪ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ አቅርባ ከመጠየቅ የሚገድባት አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሚያዝያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 37866

ግንቦት 19 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሙሉጌታ አባይ - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን - ኑሪዬ አብተው /ነገረ ፈጅ/ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በፌዴራል የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጀመረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ አከፋፈል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ለጉባኤው በይግባኝ የቀረበው አመልካች ሲሆን፣ ቅሬታውም በተጠሪ የተጣለብኝ መቀጫ ያለአግባብ ስለሆነ ይነሳልኝ የሚል ነው፡፡ ጉባኤው ከተጠሪ የቀረበውን ክርክር ከሰማ በኂላ፣ የመቀጮውን መጠን ዝቅ በማድረግ ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ የጉባኤውን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በዚህ ደረጃም የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ መቀጮን በተመለከተ በሚቀርበው ክርክር /ይግባኝ/ ላይ ስልጣን የለውም የሚል ምክንያት በመስጠት የጉባኤውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት አመልካች ያቀረበለትን ይግባኝ ውድቅ አድርጎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

የሰበር ችሎቱ አመልካች ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረቡለትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀጮ ላይ በሚነሳው ክርክር ላይ ስልጣን የለውም በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡

እንደምንመለከተው አከራካሪው ነጥብ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በዋናው ግብር ላይ የሚጣለውን መቀጫ በመቃወም በሚቀርበው ይግባኝ ላይ ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡ በሰበር መ.ቁ 34691 በቀረበው ክርክር በአሁኑ በተያዘው መዝገብ የተነሣው ጭብጥ አከራካሪ ስለነበር የሰበር ችሎቱ ለሕጉ ትርጉም በመስጠት የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀጮ እና ወለድ ላይ የሚቀርበውን ይግባኝ አይቶ የመወሰን ስልጣን አለው በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በዚህ አይነት የሰበር ችሎቱ የሚሰጠው ውሳኔ (የሕግ ትርጉም) በችሎቱ እስካልተለወጠ ድረስ አስገዳጅ እንደሚሆን የፌዴራል ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ 454/97 በአንቀጽ 2(4) ተደንግጎአል፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 46438 ጥቅምት 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 34888 የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀጮ እና ወለድ ላይ የሚቀርበውን ይግባኝ የማየት ስልጣን አለው ብለናል፡፡ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 41608

ሐምሌ 22 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**:- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካቾች**:- እነ ሙላቱ አንበርብር - ቀርቧል

**ተጠሪ**:- ወ/ት ታመነች ዮሴፍ መና ወኪል - ቀርቧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ የቀበሌ 06 አስተደደር ማሕበራዊ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች የስር ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ ነበሩ አመልካቾች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ በተጠሪ የመኖሪያ ቤት የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የሆኑ ግለሰቦች ከፍተኛ የድምጽ ማጉያ በመጠቀም በሚያካሂዱት ጩኸት አካባቢውን በማወካቸው በመኖሪያችን ልናርፍ አልቻልንም በሚፈጠረው የድምጽ ብክለት በጤናችን ላይ ጉዳት እያደረሰብን ስለሆነ የድምጽ ብክለቱ ይወገድልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ ይህ የሐይማኖት ጥላቻ በመሆኑ በአድማ የቀረበ ክስ ነው፡፡ የማንንም መብት ሣንጋፋ መንግስት ለሐይማኖትና ለእምነት ነፃነት የሰጠው ሕገመንገስታዊ መብት እንዲከበርልን ተደርጐ የማምለክ መብታችን ተጠብቆ እያለ ድንጋይ እየተወረወረብን በደል እየደረስብን ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የማህበራዊ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ በመመርመር አመልካቾች ያቀረቡትን አቤቱታ አስመልክቶ ሁከት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ሲል የመሰረት ልማት ቴክኒሻን(ባለሙያ) ወደ ስፍራው በመላክ ሁከት እንዳለ በማረጋገጥ ተጠሪዎች በሌላው ሰው ላይ ሁከት እየፈጠሩ ህገ-መንግስታዊ መብታችን እየተጠቀምን ነው ማለቱ ሕጉን በተሣሣተ መተርጐም ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህ በአዋጅ ቁ. 12/96 አንቀጽ 5/3/ መሰረት፣በወንጀል ሕግ 815/1/ የሌሎችን ስራና ሰላም ማወክ ሆኖ ስላገኘው ተጠሪዎች 100 ብር (መቶ ብር) ይቀጡ መኖሪያ ቤቱ ለተፈቀደለት አላማ ብቻ ይዋል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለአ/አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ጉዳዩ የቀረበለትም ፍ/ቤት የግራ ቀኙን በማከራከር በጭብጥነት የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ መወሰን ስልጣን አለው ወይ? የሚለውን በማየት ሲወስን የክልል 14 መስተዳደር ደንብ ቁጥር 1/1986 አንቀጽ 10/2/ በመጥቀስ ይህን ደንብ የጣሰ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የመንግስት አካል ተገቢውን አስተደደራዊ ውሣኔ እንደሚወሰድበት ከተጠቃሹ ደንብ አንቀጽ 17/1/ሀ/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ ተጠቃሹን ደንብ የጣሰ በቅድሚያ አስተዳደራዊ ውሣኔ እንዲሰጥበት ማድረግ እንጂ በቀጥታ ክስ በፍ/ቤት ክስ የማይመሰረትበት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይም አመልካቾች ይህን ለማድረጋቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም በአስተዳደር አካል ውሣኔ ካልተሰጠ ደግሞ የስር ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን የለውም በመሆኑም የስር ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ በማለት ሲወስን የአሁን አመልካቾችም በዚሁ ውሳኔ ባለመስማማት ለአ/አበባ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ጉዳዩ የቀረበለትም ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ሣይሰማ አመልካቾች

በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የፍ/ብሔር ክርክር በመሆኑ በስር ፍ/ቤት በተወሰነው መሰረት በቅድሚያ የሚመለከተው አስተዳደራዊ አካል ውሳኔ መስጠት ይገባል መባሉ በአግባቡ ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 ዘግቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

አመልካቾች ህዳር 24 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በአ/አ/ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና በከተማው የከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጽመበት በመሆኑ ሊታረምልን ይገባል በማለት አመልክቷል፡፡

በዚህም መሰረት የተጠሪን እና የአመልካችን የቃል ክርክር በችሎት ሰምተናቸዋል፡፡ ጉዳዩ በሰበር እንዲታይ የቀረበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ መስተናገድ ያለበት በአ/አ/አስተዳደር አዋጅ ቁ. 12/96 አንቀጽ 5/3/ አንፃር ሣይሆን በአስተዳደር ደንብ ቁጥር 1/86 አንቀጽ 10/2/ እና 17/1/ሀ ነው በማለት የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የማህበራዊ ፍ/ቤትን የመሻራቸውን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ የግራ ቀኙ ካሰሙት ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር ማገናዘብ መርምረናል፡፡

በመሆኑም የጉዳዩን አመጣጥ ጠቅለል ባለ መልኩ ስናይ የአሁን አመልካቾች በስር ክሣቸው የፕሮቴስታንት ተከታዮች በተጠሪ መኖሪያ ቤት ከፍተኛ የድምጽ ማጉያ በመጠቀም በሚያካሄዱት ጩኸት አካባቢውን በማወክ በድምጽ ብክለት በጤናችን ላይ ጉዳት እያደረሱብን ነው፡፡ ይህ ድምጽ ይወገድልን በማለታቸው ምክንያት፡፡ የማህበራዊ ፍ/ቤቱም እንደተባለው የድምጽ ብክለት አለ በማለት ተጠሪ (100) ብር (መቶ ብር) እንዲቀጡ ሲወስን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን በማከራከር ጉዳዩ በፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት በመስተዳደር አካል መታየት ነበረበት ስለዚህ የዳኝነት ስልጣን የለህም በማለት የማህበራዊ ፍ/ቤትን ውሳኔ ሲሽር የከተማው የከፍተኛው ፍ/ቤትም በተመሣሣይ ምክንያት የከተማውን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት አጽንቷል፡፡

እንግዲህ በዚህ ጉዳይ በዋናነት ሊታይ የሚገባው የስር ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለው ሆኖ አግኝተነዋል በመጀመሪያ ደረጃ የቀበሌ የማህበራዊ ፍ/ቤቱ አዋጅ ቁ. 12/96 በአዋጅ ቁ. 31/99 መሻሻሉን ከግንዛቤ ሣያስገባ እና ይህ አዋጅ ቁጥር 31/99 ስልጣን ባልሰጠው ሁኔታ ውሣኔ ሰጥቷል የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ይህን በጥልቀት ሣያጤነው ምንም እንኳ የስር ፍ/ቤት ስልጣን የለውም ቢልም ምክንያት ያደረገው የግራ ቀኙ ክርክር መጀመሪያ በአስተዳደራዊ አካል መታየት ነበረበት በሚል ነው፡፡ የከፍተኛውም ፍ/ቤት ይህንኑ አጽንቷል፡፡ በመሰረቱ ለክርክሩ መንስኤ አመልካቾች በተጠሪ ድርጊት የጽምጽ ብክለት ጉዳት አድርሶብናል የሚል ሲሆን ጉዳዩም የፍትሐብሔር ክርክር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ሊስተናገድ የሚገባውም በፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 1225 መሰረት ነው፡፡ ይህንንም ጉዳይ ለማየት ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ አስተዳደራዊ አካል እና የአ/አ ከተማ ፍ/ቤቶች ስልጣን አይደለም፡፡

በመሆኑም ይህ ታልፎ በስር ፍ/ቤቶች መታየቱ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአስተዳደሩ ማህበራዊ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0207 በቀን 2/5/2000 የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 877/00 በቀን 01/9/2000 እና የከተማው ይግባኝ ሰሚ በመ/ቁ. 08015 ቀን 12/2/2001 የተሰጡት ውሣኔዎች ተሽሯል፡፡
2. የማህበራዊ ፍ/ቤትም ሆነ ከአ/አ/ከተማ ፍ/ቤቶች ስልጣን የላቸውም፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

# ባንክና ኢንሹራንስ

የሰ/መ/ቁ. 42139

ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት- ክንፈ ታደለ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ብያን ኡመር- ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሣ ክፍያን መሰረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ በምእራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ ክስ የመሰረተው ጉዳት አደረሰ በተባለው መኪና ባለንብረት እና በሹፌሩ ላይ ነው፡፡ አመልካች ለመኪናው የመድን ዋስትና ግዴታ ገብቷል ስለተባለ ጣልቃ እንዲገባ ተጠይቆ ነው የክርክሩ ተካፋይ የሆነው፡፡ በዚህ አግባብ መሰረት ቀርቦ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የስረ-ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊ ሊሆን እንደማይገባው በመግለጽም ተከራክሯል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ተከሣሾቹ እና አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ናቸው፤ የጉዳት ካሳውን ይክፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህን ውሳኔ በመቃወም በአሁኑ አመልካች ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም ብሏል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች ታሕሣስ 14 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጸመ የሚለውን መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ በበኩላችንም ጉዳቱ የደረሰው በተጠሪው ጥፋት ነው እየተባለና አመልካችም የመድን ሽፋን ባልሰጠሁበት ተግባር ላይ ተሰማርቶ በነበረው መኪና ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በማለት መከራከሩ እየታወቀ የጉዳት ካሣ እንዲከፍል መወሰኑ አግባብ ነው ወይ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ግራ ቀኝ ወገኖቹን አከራክረናል፡፡

ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች የሰ/ቁ. 3-29779 ኢ.አ ለሆነው የጭነት (የእቃ) ተሽከርካሪ የመድን ዋስትና ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ጉዳት ደረሰብኝ የሚለው በዚህ መኪና ላይ ተሳፍሮ ሲሄድ በነበረበት ጊዜ ነው፡፡ የአመልካች ክርክርም ከዚህ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የቀረበ ነው፡፡ የመድን ዋስትና የሰጠሁት በሕዝብ ማመላለሻነት ለተሰማራ መኪና ሳይሆን፣ እቃዎችን ለሚያጓጉዝ የጭነት መኪና በመሆኑ ከገባሁት ውል ውጪ ኃላፊ የምሆንበት ምክንያት የለም በማለት ነው የተከራከረው፡፡ በተጠሪ በኩል አመልካች ባቀረበው የፍሬ ነገረ ክርክር ላይ ምንም አይነት ማስተባበያ አልቀረበም፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች ክርክሩ ውስጥ የገባው የመኪናው ባለንብረት ጣልቃ እንዲገባለት በመጠየቁ ነው፡፡ ባለመኪናው የጣልቃ ይግባልኝ ጥያቄ ያቀረበው ደግሞ የመድን ዋስትና ውል አለኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች እንግዲህ በውልህ ትገደዳለህ ከተባለ የውሉን ይዘት ማየቱ የግድ ይሆናል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ውሉ ዋስትና በተገባለት የጭነት መኪና ላይ ተሳፍረው በሚጓዙ ሰዎች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት የሚሸፍን አይደለም፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለጸው ተጠሪ እንደማንኛውም መንገደኛ በመኪናው ተገጭቶ አይደለም ጉዳት የደረሰበት፡፡ በመሆኑም በማንኛውም ሁኔታ፣

የደረሰበት ጉዳት አመልካች በነበረው ውል የሚሸፈን አይደለም፡፡ ሲጠቃለል አመልካችን ኃላፊ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/የምእራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08797 መስከረም 26 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 71528 ኀዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ አመልካችን በሚመለከት ያለው የውሳኔው ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 384/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የስር አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሣሾች በነበሩት ላይ የተሰጠው ውሳኔ አልተሻረም፡፡ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ የሚሆንበት የሕግም ሆነ የውል ምክንያት የለም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 42309

ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን - ሳሙኤል ተገኑ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የመድን ዋስትና ውልን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ለአመልካች መኪና የመድን ዋስትና ሰጥቶአል፡፡ መኪናው ሲሽከረከር በነበረ ጊዜ በመገልበጡ ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ተጠሪም የገባውን የመድን ዋስትና ግዴታ መሠረት በማድረግ ገንዘቡን ወጪ አድርጎ መኪናው የተገለበጠው በሹፌሩ ሳይሆን በብልሽት ምክንያት አገልግሎት መስጠት አቁሞ በነበረበት ጊዜ የተበላሸውን ፍሬን እያስተካከለ የነበረው መካኒክ ሥራውን ሲሞክር መሆኑን ስለደረስኩበት ኃላፊነት ሳይኖርብኝ ለጥገና ያወጣሁት ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በማለት በአመልካች ላይ ክስ መስርቷል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ክሱ በንግድ ሕግ ቁ 674(1) ወይም (2) መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦአል፡፡ የስረ-ነገር ክርክር በማንሳትም ተከላክሎአል፡፡ ክሱን ያስተናገደው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከመረመረ በኋላ የተጠሪን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ በመቀበል ክስ የቀረበበትና ገንዘብ ከነወለዱ እና የጠበቃ አበል ጋር እንዲከፈለው ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች ታሕሣሥ 23 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጸመ ያለውን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም የአመልካችን የይርጋ ክርክር የታለፈው በአግባቡ ነው ወይ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡

እንደምንመለከተው በዚህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው የክርክር ጭብጭ ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ወይስ አልሆነም? የሚለው ነው፡፡ ይህ ጭብጥ ግራቀኝ ወገኖችን ያከራከረ ወይም ግራቀኝ ወገኖች የተለያዩት የሕግ አግባብ /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.246(1)/ በመሆኑ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር ተገናዝቦ የሚታይ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ግን ወደሕጉ ከመኬዱ በፊት ከዚህ የተያያዘው የፍሬ ነገር አግባብ መመርመሩ ተገቢ ይሆናል፡፡

በግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንደተመለከተው ተጠሪ ክሱን ያቀረበው ሚያዝያ 3 ቀን 1999 ዓ.ም ሲሆን ለክሱ መነሻ የሆነው ጉዳት ደረሰ የተባለው ደግሞ ግንቦት 12 ቀን 1994 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ ጊዜ ማለትም ጉዳቱ በደረሰበት እና ክሱ በቀረበበት መሃል ያለው ሲታሰብ አራት ዓመት ከአስር ወር በላይ ነው፡፡ ይህ እንግዲህ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው እውነታ ሲሆን፣ እውነታው ከየትኛው ሕግ ጋር ሲገናዘብ ነው ለይርጋው ክርክር አወሳሰን አግባብነት የሚኖረው የሚለውን ደግሞ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተጠሪ ገንዘቡ ሊመለስልኝ ይገባል በማለት ወደክስ ሊያመራ የቻለው የመድን ሽፋን ባልሰጠሁበት ሁኔታ የወጣ ነው የሚል ምክንያት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች ሁለት የፍሬ ነገር አግባቦችን በመጠቀስ ክሱ በንግድ ሕግ ቁ 674 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ተከራክሮአል፡፡ የፍሬ ነገር አግባቦቹም የመጀመሪያው አደጋው ከደረሰበት ቀን አንስቶ ክሱ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ያለውን ጊዜ የሚመለከት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ተጠሪ የአደጋውን መንስኤ ካወቀበት ግንቦት 26 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ ክሱ እስከ ቀረበበት ቀን ድረስ ያለውን ጊዜ የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ክሱ በንግድ ሕግ ቁ 674(1) ወይም (2) መሠረት በይርጋ ቀሪ ነው ሊባል ይገባል ብሎአል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ክርክር የተጠቀሱት የፍሬ ነገር አግባቦች ትክክል አይደሉም የሚል ክርክር የለውም፡፡ የሚከራከረው ያቀረብኩት ክስ ያለአግባብ የተከፈለን ገንዘብ እንዲመለስ የሚጠይቅ በመሆኑ ተጠሪ በጠቀሰው ሕግ መሠረት በይርጋ ቀሪ አይሆንም፡፡ ሕጉ ለተያዘው ክርክር አግባብነት የለውም በማለት ነው፡፡

ተደጋግሞ እንደተገለጸው የግራቀኝ ወገኖች ግንኙት መነሻው የመድን ዋስትና /የኢንሹራንስ/ ውል ነው፡፡ ተጠሪ መኪናውን ያስጠገነው የውል ግዴታ እንዳለበት በማመን ነው፡፡ በኋላ ግን የጉዳቱን አደራረስ ወይም ሁኔታ ባውቅ ኖሮ መኪናውን አላስጠግንም ነበር፡፡ ጉዳቱ የደረሰው በመድን ዋስትና ውሉ ባልተሸፈነ ሁኔታ ነው የሚል ምክንያት አንስቶአል፡፡ ይህ አይነቱ የተጠሪ ክርክር ከተገባው ውል ውጪ በተሸሸገ ምክንያት ወይም በሐሰት በቀረበ ጥያቄ መሠረት እኔም ልሳሳት ችያለሁ ከሚል ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ በተሸሸገ ወይም በሐሰት ቃል የቀረበ ጉዳይ ያጋጠመ ሲሆን፣ የይርጋው ዘመን የሚታሰበው ኢንሹራንስ ሰጪው የተሸሸገውን ወይም በሐሰት የቀረበውን ቃል ካወቀበት ቀን ጀምሮ እንደሆነ በንግድ ሕግ ቁ. 674(2) ተደንግጎአል፡፡ የይርጋው ዘመን ሁለት ዓመት እንደሆነም በዚሁ ቁጥር ንኡስ ቁ (1) ተመልክቶአል፡፡ተጠሪ ክሱን ያቀረበው የተደበቀ ነገር መኖሩን ካወቀ ከሁለት ዓመት በላይ ቆይቶ እንደሆነም በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል፡፡ በመሆኑም አመልካች የንግድ ሕጉን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መከራከሩ ተገቢ ሲሆን የተጠሪ ክርክር ግን የሕግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ሲጠቃለል ተጠሪ ክሱን ያቀረበው በሕጉ በይርጋ ቀሪ ከሆነ በኋላ በመሆኑ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.86581 ታሕሣሥ 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 63225 ህዳር 23 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ በይርጋ ቀሪ በመሆኑ አመልካች ገንዘቡን እንዲመልስ የሚገደድበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

# ውክልና

የሰ/መ/ቁ. 38289

ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ነጂሃ ድዋሌ ዋይስ - አልቀረበችም፡፡

**ተጠሪ፡-** አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማ - ነ/ፊጅ ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03497 መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም. በሰጠው ትእዛዝ ላይ ነው፡፡ በመዝገቡ እንደተመለከተው ጉዳዩ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበችውን የገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ልትመሠርት የቻለችው ድሬዳዋ በሚገኘው ቅርንጫፉ በኩል ተገቢውን የአገልግሎት ኮሚሽን በመክፈል አዲስ አበባ በሚገኘው ሲዳሞ ተራ በሚባለው ቅርንጫፉ አቶ ሽሪፍ ከዲር ለተባለ ሰው እንዲሰጥ የላከችውን ብር 45,000 (አርባ አምስት ሺህ) ለማይመለከተው ሰው ከፍያለሁ በማለት አደራውን አልተወጣም በማለት ነው፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ ገንዘቡ አመልካች በገለጸችው ሁኔታ መላኩንና የደረሰው መሆኑን ሳይክድ ነገር ግን ገንዘቡ የተላከልኝ ሰው እኔ ነኝ በማለት መታወቂያ ይዞ ለመጣ ሰው መክፈሉን በመግለጽ ከክሱ በነፃ ይሰናበት ዘንድ እንዲወሰንለት ጠይቆአል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም በዚህ መልክ የቀረበውን የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ ክሱን ውድቅ በማድረግ ተጠሪን በነፃ አሰናብቶአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበል ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሰኔ 3 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጭበርብሮ ገንዘቡን ለማይገባው ሰው የከፈለው ተጠሪ መሆኑ እየታወቀ ገንዘቡን ለአመልካች ለመተካት አይገደድም በሚል የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች ተገቢውን ኮሚሽን በመክፈል ገንዘቡን ለባንኩ አስረክባለች፡፡ ገንዘቡን ለባንኩ የሰጠችውም ለተላከለት ሰው እንዲያደርስላት ነው፡፡ በእርግጥም ባንኩ የተሰጠው አደራ ገንዘቡን ለተላከለት ሰው ማድረስ እንደመሆኑ የማድረስ ግዴታ አለበት፡፡ ነገር ግን ባንኩ /ተጠሪ/ ገንዘቡን ለተላከለት ሰው አላደረሰም፡፡ ይልቁንም ለማይመለከተው /ላልተላከለት/ ሰው መክፈሉ ተረጋግጦአል፡፡ በተጠሪ ክርክር እንደተገለጸው ገንዘቡን የከፈለው የተላከልኝ ሰው እኔ ነኝ የሚል መታወቂያ ደብተር የያዘ ሰው ስለቀረበ ነው፡፡ ይህ ሰው ግን በእርግጥም አመልካች ገንዘብ የላከችለት ሰው አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ሁኔታ የተጭበረበረው ተጠሪ /ባንኩ/ እንጂ አመልካች አይደለችም፡፡ አጭበርባሪውን ሰው ከሶ ገንዘቡን ማስመለስ የሚችለውም ተጠሪ እንጂ አመልካች ልትሆን አትችልም፡፡ ግልጽ ሆኖ እንደሚታየው በአመልካች እና አጭበርብሮ ገንዘቡን ከተጠሪው ባንክ በወሰደው ሰው መካከል ምንም አይነት ግንኙነት የለም፡፡ ተጠሪ ስለተጭበረበረ አመልካችም እንደተጭበረበረች ይቆጠራል ወደሚለው መደምደሚያ የሚደርስ ሁኔታ የለም፡፡ በዚህ መዝገብ

የተያዘው አከራካሪ ሆኖ የተነሣው ነጥብ ባንክ ሂሣብ /ገንዘብ/ ባላቸው ሰዎች ስም ሌሎች ሰዎች አጭበርብረው ገንዘብ ከሚያወጡበት ሁኔታ ተለይቶ የሚታይ ነው፡፡ ባንክ ገንዘብ ያስቀመጡትን ሰዎች ሰነዶች እና ፊርማ አጭበርብሮ በማግኘት ገንዘብ የሚወስዱ ሰዎች በባለሂሣቦቹም ሆነ በባንኩ ሊጠየቁ የሚችሉበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች ባንኩን አጭበርብሮ ገንዘብ የወሰደውን ሰው በመጠየቅ ገንዘቡን የምታስመልስበት አግባብ የለም፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ተጠሪ ገንዘቡን ለተላከለት ሰው ለመስጠት ከአመልካች ሲቀበል የአደራውን ሃላፊነት ወስዶአል፡፡ አደራ ተቀባይ የሆነው ወገን በአደራ ያስቀመጠውን /የተቀበለውን/ ዕቃ መመለስ ያለበት ለአደራ ሰጪው ወይም አደራ ሰጪው ይቀበልልኝ ብሎ ላመለከተው ሰው እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2792/1/ በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ ተጠሪ ከእነዚህ ግዴታዎቹ አንዱንም አልተወጣም፡፡ ስለዚህም ገንዘቡን ለአመልካች አልከፍልም የሚልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔም ከዚህ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 21113 ኅዳር 20 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03497 መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለአመልካች ይመልስ ብለናል፡፡ በሥር ፍ/ቤቶች እና በዚህ ሰበር ችሎት አመልካች የከፈለችው የዳኝነት ገንዘብም ተጠሪ ይተካላት ብለናል፡፡
3. ሌሎች ወጪና ኪሣራ በተመለከተ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   የውሣኔው ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 43875

ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** በወላይታ ዞን የቦዲቲ ከተማ ማዘጋጃ ቤት - ነ/ፈጅ አረታ ቶሩ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ወንድሙ ኃይሌ - ጠበቃ ዳንኤል ገ/ጊዮርጊስ ቀርበዋል፡፡

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## <u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቹ የካቲት 24 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታው የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/ር ሰበር መ/ቁ. 22624፣ ታህሣሥ 17 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረምለት በመጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በወላይታ ዞን በቦዲቲ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ በአፈፃፀም ከሳሽነት እንዲሁም የአሁኑ አመልካች በአፈፃፀም ተከሣሽነት ተከራክረዋል፤ የአሁኑ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤቱ ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘቱ በቦዲቲ ከተማ ምዕራብ ክፍል በ600 ሜ.ካ ያረፈውን ቤትና ቦታ ከወላጅ አባታቸው አቶ ኃይሌ መርሻ እና ከአክስቶቼ ወ/ሮ የሺ መርሻና ወ/ሮ ተዋበች መርሻ በስጦታ አግኝቼ ስጦታው በቦዲቲ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፀደቀልኝ ሲሆን በዚሁ ውሣኔ መሠረት የቦዲቲ ማዘጋጃ ቤት ወደ ስሜ እንዲያዞርልኝ ብጠይቀውም ፍቃደኛ ባለመሆኑ በፍርድ ቤቱ ተገድዶ ይፈጽምልኝ የሚል ሲሆን፣ ሥር ተከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ወደ ሥር ፍ/ቤቱ ቀርቦ በአከራካሪው ቦታ የመንግሥት ቤት ስላለና ጉዳዩ በቤቶች ኤጀንሲ መታየት ያለበት ነው ብሎ መልስ ሰጥቷል፤ ክርክሩ በመጀመሪያ የቀረበለት የቦዲቲ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 00446 ጥቅምት 14/2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ ጉዳዩ በቤቶች አጀንሲ መታየት ያለበት እንጂ በቀጥታ ማስፈፀም አይቻልም ያለውን የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 8618፣ ሰኔ 18 ቀን 2000 ዓ.ም. ጉዳዩን በይግባኝ አከራክሮ የሥር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቶታል፡፡

ከላይ የሰፈረውን የሥር ፍርድ ቤቶቹ ውሣኔ በመቃወም የአሁኑ ተጠሪ ጉዳዩን ወደ ደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዳቀረቡትና ፍ/ቤቱም የመንግሥትና የግለሰቡ ይዞታዎች ለይቶ መፈፀም ሲገባ የግለሰቡ /የአሁን ተጠሪ/ መብት በደፈናው መዝጋት አግባብነቱ ለመመርመር ብሎ ጉዳዩን ካቀረበው በኋላ ተከሣሹ ተቋም መልስ እንዲሰጥ ባዘዘው መሠረት ውክልናቸው በተከሣሹ መስሪያ ቤት በሚገባ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የተቋሙ የፕሮቶኮል ቁጥርና ፊርማ በሌለበት ኀዳር 12/2001 ዓ.ም. በተፃፈ ነገረ ፈጁ የተባሉት በሰጡት መልስ የግለሰቡ ቤት ከመንግሥት የውርስ ቤቶችና ቦታ ነጥለን ለማስረከብ ዝግጁ ነን ብለዋል በማለትና መልሱ የተቋሙ የፕሮቶኮል ቁጥርና ፊርማ ባይኖረውም የሚታመን ነው በማለት በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም በመወሰን የሥር ፍ/ቤቶቹ የሰጡትን ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ሽሮታል፡፡

ከላይ የሰፈረውን የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/ር ሰ/መ/ቁ. 22624 ታህሣሥ 17/2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት የአሁኑ አመልካች የካቲት 24/2001 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታቸው ውሣኔው እንዲሻርለት ጠይቋል፤ ያቀረበው ምክንያትም ተገቢው ውክልና

ባልተሰጠው ነገረ ፈጅ የቀረበው የፕሮቶኮል ቁጥርና ፊርማ የሌለበትን መልስ መሠረት አድርጎ ውሣኔ መስጠቱ ተገቢነት የለውም የቀረበው መልስ የአመልካች አይደለም፤ ከአዋጅ ውጭ የተወረሱትን ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት አጣርቶ የመወሰን ስልጣን የቤቶች ኤጀንሲ እንጂ የፍ/ቤቱ አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም የአመልካች ስምና ፊርማ እንዲሁም የፕሮቶኮል ቁጥር የሌለውን ደብዳቤ መሠረት በማድረግ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ መሻሩ አግባብነቱን ለመመርመር ብሎ ጉዳዩን በማቅረብ ተጠሪው መልሱን እንዲሰጥ አዟል፤ ተጠሪውም መጋቢት 30 ቀን 2001 የተፃፈ መልስ ሰጥተዋል፤ አጭር ይዘቱም የአመልካች ነገረ ፈጅ ለመሆናቸው ማረጋገጫ የላቸውም የተባሉት አቶ መሠለ ማሞ በትክክል የተቋሙ ነገረ ፈጅ ናቸው፤ እኚህ ነ/ፈጅ ባቀረቡት መልስ ለምን የፕሮቶኮል ቁጥርና ፊርማ የለውም ተብለው ሲጠየቁ ከቦታው ርቀት አኳያ ትራንስፖርት እንዳያመልጠኝ ብዬ በመቸኮሌ እንጂ የጽሁፉ /የመልሱ/ ይዘት በትክክል የአመልካቹ መሆኑ ስላስረዱና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም በዚህ አባባላቸው እምነት በማሳደሩና ይህን ማድረጉም ተገቢነት ያለው ነው፤ አመልካቹ ቤቶቹ የተወረሱ ናቸው ይበል እንጂ የተወረሱ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥለት ማስረጃ አላቀረበም፤ ስለሆነም የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ፍርድ ይጽናልኝ የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ወገኖች የክርክር አመጣጥ ከላይ እየተገለፀ እንደመጣው በመገንዘብ ይህ ፍርድ ቤት የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር የመጨረሻ እልባት የሰጠው <u>ከአመልካች ተገቢውን ፎርማሊቲ የጠበቀ መልስ ከቀረበለት በኋላ ነው ወይስ አይደለም?</u> የሚል መሠረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በዚህ ክርክር ለመገንዘብ እንደተቻለው የአመልካቹ ቁልፍ ቅሬታ የሚያተኩረው በደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተላለፈብኝ ፍርድ በተገቢው ነገረ ፈጅ ሳልወክልና ነገረ ፈጅ የተባሉት ግለሰብ የሰጡት መልስም የአመልካች የፕሮቶኮል ቁጥርና ፊርማ በተገቢው መንገድ ያላሟላና በዚህ መልስ መሠረት ተደርጎ የተሰጠ ውሳኔም የአመልካች ክርክር በአግባቡ ያካተተ ስላልሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ሲል ተጠሪው ደግሞ ይህንን አይቀበልም፡፡ አመልካች መንግስታዊ ተቋም ሲሆን የመንግስት ተቋም በሚከስበትም ሆነ በሚከሰስበት ክርክር ወክሎ የሚከራከር ነገረ ፈጅ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 59 መሠረት በሚመለከተው የመንግስት ተወካይ መወከል አለበት፡፡ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ ዓንቀፅ 80፣92 እና 93 እንደሚገልፁትም ማንኛውም አቤቱታ በዋናው ባለጉዳይ ወይም በጠበቃው መፈረም እንዳለበት ነው፤ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 92(3) በተለይ እንዳስፈረው ደግሞ መንግስት በሚከስበትም ሆነ በሚከሰስበት ጊዜ አቤቱታውን የሚፈርመው ስለዚህ ጉዳይ በተለይ የተወከለ ወይም ስልጣን ያለው ሰው ነው፤ የፅሁፉ ትክክለኛነት የሚያረጋግጠው ደግሞ ጉዳዩን በተለይ የሚያውቀውና ለዚህም የተለየ ስልጣን የተሰጠው ክፍል ሃላፊ እንደሆነ ነው፡፡ በእጃችን ወዳለው ክርክር ስንመጣ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንደ የአመልካች መልስ በመቁጠር ለውሳኔው ግብአት ያደረገው የፅሁፍ መልስ የፕሮቶኮል ቁጥር የሌለውና በሚመለከተው የአመልካች ወኪል ያልተፈረመ ሆኖ እያለ ነገረ ፈጅ ነኝ ብለው የቀረቡት ሰው ትራንስፖርት እንዳያመልጠኝ በመቸኮሌ በሚመለከተው ኃላፊ አላስፈረምኩም ያሉትን ሃሣብ በማመን ብቻ ተመስርቶ የቀረበው መልስ የአመልካቹ ነው ብሎ መውሰዱ ከላይ ከተጠቀሱት ህጎች አኳያ ተገናዝቦ ሲታይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ፈፅሟል፤ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደቡብ ብ/ብ/ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ር ሰበር መ.ቁ 22624 ታህሳስ 17 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፤ ይፃፍ፡፡
2. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎቱ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔን የሻረው የአሁኑ አመልካች መልስ መሆኑ በተገቢው መንገድ ባላረጋገጠው ፅሁፍ ተመስርቶ ስለሆነ ተገቢውን ፎርማሊቲ ያሟላ የአመልካች መልስ ተቀብሎ ለጉዳዩ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት ተመልሶለታል፤ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍ/ቤት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
4. የካቲት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተላለፈው እግድ ተነስቷል፤ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡
   ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 37799

ሐምሌ 29 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የባህርና ትራንዚት አግልግሎት ድርጅት - ነ/ፈጅ በዛብህ አመዴ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ሰናይት በዳሣ

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ተጠሪ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የመሰረተው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረበው ክስ ደንበኛው የሆነው አዋሽ ወይን ጠጅ አ/ማ ለፋብሪካው አገልግሎት የሚውል የጠርሙስ ማጠቢያ ማሽን በጉዞ ላይ ለሚደርስበት ጉዳትና ውድመት የመድን ሽፋን ሰጥቷል፡፡ የተጠሪ ደንበኛ የጉምሩክ አስተላላፊነት ውክልና ቀጥሎም የማጓጓዝ ትእዛዝ ለአመልካች የሰጠ ሲሆን ማሽኑን በስር ሁለተኛ ተከሣሽ በነበሩት ግለሰብ መኪና አስጭኖ ሲያመጣ ተሽከርካሪው ተገልብጦ በማሽኑ ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡ ማሺኑም ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ በመሆኑ ብር 2,200,856.43(ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ስድስት ከአርባ ሦስት ሳንቲም) ለደንበኛው ስለከፈለ አመልካች በገባው የውክልናና የማጓጓዝ ውል መሰረት፣በንግድ ሕግ ቁጥር 590 ባለበት ሃላፊነት፣ሁለተኛ ተከሣሽም የተሽከርካሪው ባለንብረት በመሆናቸው ሁለቱም ገንዘቡን ሊተኩ ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ተመልክቶ አመልካች እቃውን ያጓጓዘው በውክልና ስልጣን በመሆኑ ሊጠየቅ አይገባም በማለት ሁለተኛው ተከሣሽ ብቻ ገንዘቡን እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ አመልካች እቃውን ያጓጓዘው ራሱን ችሎ እንጂ በውክልና ስላልሆነ ለጉዳቱ ኃላፊ ሊሆን ይገባል በማለት ከስር ሁለተኛ ተከሣሽ ጋር ክስ የቀረበበትን ገንዘብ በአንድነትና በነጣላ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም አመልካች ማሽኑን ያጓጓዘው በውክልና ነው ወይስ እራሱን ችሎ ነው? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት ግራ ቀኙ ቀርበው ክርክራቸውን በቃል አሰምተዋል፡፡ ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ ተመክቷል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው የተጠሪ ደንበኛ ያስመጣውን የጠርሙስ ማጠቢያ ማሽን አመልካች ያጓጓዘው መሆኑ አከራካሪ አልሆነም፡፡ አከራካሪ የሆነው ነጥብ አመልካች ማሽኑን ያጓጓዘው እራሱ አጓጓዥ ሆኖ ነው? ወይስ በውክልና ነው? የሚለው ነው፡፡

አመልካች እቃ አስተላላፊ ለመሆኑ ተጠሪም በክሱ ገልፆታል፡፡ እቃ አስተላላፊ ምን ማለት እንደሆነ እና ምን ምን ስራዎችን እንሚሰራ ስለእቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ስራ ፈቃድ አስመልክቶ የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 37/90 ያመለክታል፡፡ በዚሁ በተጠቀሰው ደንብ አንቀጽ 2/1/ ስር እቃ አስተላላፊ በአገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ እቃ ተቀባይነት ወይም እቃ ላኪን በመወከል የጉምሩክ፣የወደብ ወይም ሌሎች ስርአቶች አስፈጽሞ ገቢ ወይም የወጪ እቃዎችን ወደብ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ የሚያደርግ ሲሆን እቃን የማጓጓዝና የማስረከብን ስራም ይጨምራል፡፡ ይህ ድንጋጌ በጥቅሉ ሲታይ እቃ አስተላለፊው ስራውን የሚያከናውነው እቃ ላኪዎችን ወይም ተቀባዮችን

በመወከል በውክልና ስልጣን መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ በእርግጥ የእቃ ማጓጓዝ ተግባሩን እንዴት ሊያከናውን እንደሚችል በደንቡ አንቀጽ 3/6/ እና /7/ ስር ተለይቶ ተቀምጧል፡፡ በአንቀጽ 3/6/ ስር እቃ አስተላላፊው የራሱ የትራንስፖርት አገልግሎት ካለው የእቃ ማጓጓዙን ተግባር የሚያከናውነው እንደ አጓጓዥ ሆኖ እንጂ በውክልና ስልጣን አለመሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህም በአንቀጽ 2/1/ ስር የተመለከተው የውክልና ስልጣን ልዩ ሁኔታ(exception) ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን የራሱ ትራንስፖርት ከሌው ወይም ባለእቃው የራሱን ማጓጓዣ ካላቀረበ እቃ አስተላላፊው ማጓጓዣ ተከራይቶ  እቃውን እንደሚያጓጉዝ በንኡስ አንቀጽ 7 ስር ተመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ በንኡስ አንቀጽ 6 ስር በግልጽ እንደተመለከተው የማጓጓዝ ስራውን እንደ አጓጓዥ ሆኖ እንደሚሰራ አያስቀምጥም፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸው ደግሞ እቃ አስተላላፊ ስራውን ሁሉ የሚያከናውነው በውክልና በመሆኑ በእራሱ ስም ስለራሱ ሆኖ ይሰራል ተብሎ በንኡስ ቁጥር 7 ስር ልዩ ሁኔታ (exception) ስላልተመለከተ የማጓጓዝ ተግባሩን የሚያከናውነው በውክልና መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች የማጓጓዝ ውሉን በራሱ ስም መፈጸሙ የማጓጓዝ ተግባሩን የፈፀመው እንደ አጓዥ ሆኖ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ግን እቃ አስተላላፊው እቃውን በወደብ ማስተላለፍ፣የወደብና የጉምሩክ ስርአቶችንና የእቃ ማጓጓዝ ተግባርን በሙሉ የሚፈጽመው በውክልና ነው፡፡ እንደ አጓዥ ሆኖ የሚቆጠረው የማጓጓዙን ስራ በራሱ ማጓጓዣ ካጓጓዘ ብቻ ነው፡፡ የማጓጓዣ ውሉን በስሙ መፈረሙ ብቻ ስራው በውክልና ያልተሰራ መሆኑን አያመለክትም በእርግጥ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2251 የተገለጸው የእቃ አስተላላፊ በደንብ ቁጥር 37/90 ስር ከተመለከተው ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሣሣይ ተግባር የሚፈጽም ባይሆንም እቃ አስተላላፊው ስራውን የሚያከናውነው በራሱ ስም ሆኖ ለወካዩ ጥቅም መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የእቃ አስተላላፊ በራሱ ስም የሚያደርጋቸው ተግባሮች ለወካዩ ጥቅም በውክልና ስልጣን የሚፈጸሙ ናቸው ማለት ነው፡፡

አመልካች ወኪል ነው ከተባለ ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው የውክልና ስራው በክፋት ያደረገ መሆኑ ከተረጋገጠ ብቻ እንጂ ጉዳት ስለደረሰ ብቻ በኃላፊነት ተጠያቂ እንደማይሆን በንግድ ሕግ ቁጥር 683/3/ ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ደግሞ አመልካች  ስራውን በክፋት በማከናወኑ ጉዳት ያደረሰ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ለደረሰው ጉዳት በኃላፊነት የሚጠየቅበት የሕግ መሰረት የለም፡፡

ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶችም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች ኃላፊ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 28225 በ07/08/2000 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40949 በ5/3/99 የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
3. አመልካች የማጓጓዝ ስራውን የሰራው በውክልና ስልጣን በመሆኑ ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 34621

ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ኒያላ ኢንሹራንስ አ/ማ - ጠበቃ አቶ በረከት በርሄ ቀረበዋል

**ተጠሪ፡-** አቶ ሐጐስ ገ/ድህን - ጠበቃ አቶ ገ/ሄር ተስፋይ ቀርበዋል

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመር በኂላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ታህሳስ 22 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 41455 መስከረም 23 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ግድፈት የተፈጸመበት ነው በማለት እንዲሻርለት ስለጠየቀ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች በስር ከሳሽነት፣የአሁኑ ተጠሪ እና ሌሎች በዚህ ሰበር ችሎት ተከራካሪ ያልሆኑ ሁለት ሰዎች ተከሳሾች በመሆን የተከራከሩ ሲሆን የስር ከሳሹ (የአሁኑ አመልካች) መስከረም 14 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ ያቀረበው ክስ አጭር ይዘቱ ደንበኛዬ ከጣሊያን ሃገር ገዝቶ ለሚያስገባቸው የጫማ ሶል መስሪያ ኬሚካሎች በጉዞ ላይ እንዳሉ ለሚደርስባቸው ጉዳት የመድን ሽፋን የሰጠሁ ሲሆን እነዚህ የመድን ሽፋን የሰጠኂቸውን ንብረቶች ከጅቡቲ ወደብ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ለማጓጓዝ የተባበሩት የጭንት ማመላለሻ ባለንብረቶች ማህበር(አንደኛ ተከሳሽ) ግዴታ በመግባት ተረክቦ በአቶ ሐጐስ ገ/መድህን(ሁለተኛ ተከሳሽ) ንብረት በሆነችው እና በአቶ ፋሲል ሐጐስ(ሦስተኛ ተከሳሽ) ንብረት በሆነችው እና ቁጥሯ 3-37484/3-04254 በሆነች መኪና ተጭኖ በመጓጓዝ ላይ እንዳለ የመኪናው ተሳቢ በመገለበጡ ግምቱ ብር 129,333.93(አንድ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ ሦስት መቶ ሰላሳ ሦስት ብር ከዘጠና ሦስት ሳንቲም) በሆነ 42 በርሜል እና 4 ጀሪካን ኬሚካል ላይ ጉዳት በመድረሱ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ለደንበኛዬ መድህን ከፍያለሁ እና ተከሳሾቹ ይህንን የገንዘብ መጠን ከነወለዱ ይክፈሉኝ የሚል ነው፡፡

ተከሳሾቹም ለቀረበባቸው ክስ መልስ እንዲሰጡ በታዘዘው መሰረት፣

አንደኛ ተከሳሽ በሰጠው መልስ ከሳሹና ደንበኛዬ የሚለው ባለንብረት የፈጸሙት የኢንሹራንስ ውል ተገቢውን የአፃፃፍ ፎርም ያላሟላ በመሆኑ ለከሳሹ የመዳረግ መብት አይፈጥርለትም፤ለከሳሹም የመዳረግ መብት በባለንብረቱ አልተሰጠውም፤እንዲሁም ክሱ በይርጋ ይታገዳል፤በኢንሹራንስ ውሉ የተዋዋይ ወገኖችና የምስክሮች ፊርማ የሌለ በመሆኑ ውጤት የለውም ብሏል፤

ሁለተኛ ተከሳሽ ደግሞ እኔ የማጓጓዙ ውል ተዋዋይ አይደለሁም፤እቃው የተጫነበት ንብረት የእኔ ስለመሆኑም የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም፤አደጋው በደረሰ በ7 ቀናት ውስጥም ያልቀረበ ጥያቄ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብሏል፤

ሦስተኛ ተከሳሽም የተባለው እቃ አልጫነኩም፤ክሱም በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት መልሷል፡፡

የስር ፍርድ ቤቱም በግራ ቀኙ ወገኖች መካከል የቃል ክርክር ካካሄደ በኋላ ከላይ ላቀረቡት ክርክሮች እንደሚከተለው ወስኗል፣ይኸውም የስር ከሳሽ የመዳረግ መብት አለኝ በማለት ክሱን ያቀረበው ወይም መብቱ መነጨ የሚለው ኢንሹራንሱን ከከፈለው ደንበኛው ጋር ካደረገው የኢንሹራንስ ውልና ይህ ደንበኛው በሱ መብት ተዳርጐ ክሱን በተከሳሾቹ ላይ ማቅረብ እንደሚችል ከፃፈለት ደብዳቤ በመሆኑና ተደረገ የተባለው የኢንሹራንስ ውል በሚመለከት በንግድ ሕግ አስገዳጅ የሆነ የተለየ ፎርማሊቲ ያልተቀመጠለት በመሆኑ የኢንሹራንሱ ውል የፎርማሊቲ ጉዳይ የሚታየው በፍትሐብሄር ሕጉ በተቀመጠው በጠቅላላ ውል ዓንቀፆች 1725፣1727 እና 1720(1) መሰረት ተደርጐ በመሆኑና ከሳሹ ከደንበኛው ጋር ያደረገው የኢንሹራንስ ውል በግራ ቀኙ ወገኖችና በምስክሮች ያልተፈረመ በመሆኑ ህጋዊ እውቅና የለውም፣አይጸናም፤ ስለሆነም የከሳሹ ደንበኛ በሌለ የኢንሹራንስ ውል ተመስርቶ ለከሳሽ የፃፈለት የመዳረግ መብት ህጋዊ ውጤት የለውም፣ ሁለተኛው ተከሳሽም የንብረቶቹ አጓዥ ተብለው በማጓጓዣ ሰነድ እስካልተጠቀሱ ድረስ የመኪናው ባለቤት በመሆናቸው ብቻ አጓዥ ሊባሉ ስለማይገባ በውልም ሆነ ከውል ውጭ መሰረት ያደረገ ክስ ሊቀርብባቸው አይገባም የሚል ነው፡፡

ከላይ የሰፈረውን የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም የአሁኑ አመልካች ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኋላ በኮ/መ/ቁ. 41455፣መስከረም 23 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት አጽንቶታል፡፡

በስር ፍ/ቤቶቹ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት አመልካቹ ታህሳስ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበ ሲሆን፤አጭር ይዘቱም፡- ከደንበኛዬ ጋር ህጋዊ የሆነ የኢንሹራንስ ውል በማድረግ እቃዎቹ በተጠሪው መኪና ከወደብ ተጭኖ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ላይ እያለ አደጋ በመድረሱ ለደንበኛዬ በክስ የቀረበውን ገንዘብ መክፈሌ ተረጋግጦ እያለ፣የመኪናዋ ባለቤት ተጠሪው መሆናቸው እና የጭነት ውሉ የተደረገው ከወኪላቸው (የስር አንደኛ ተከሳሽ) ጋር በመሆኑ በንግድ ህጉ መሰረት የእቃው አጓዥ መባል ሲገባቸው አጓዥ መሆናቸው በሰነዱ አልተጠቀሱም ስለሆነም አጓዥ አይባልም፤የመኪናዋ ባለቤት ቢሆንም ጉዳዩ የተያያዘው ከውል ጋር በመሆኑ ከውል ውጭ መሰረት በማድረግ ሊጠየቁ አይገባም በማለት የተሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻረልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

ተጠሪውም ነሐሴ 07 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው በስር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ማህበር የእኔ ወኪል አይደለም፤ እኔ የፈጸምኩት የእቃ አጓዥነት ውል የለም፤አመልካች ገንዘቡ ከስር ሦስተኛ ተከሳሽ እንዲያገኝ ተፈርዶለት እያለ አላግባብ በእኔ ላይ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡

ይህ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር ከላይ እየተገለፀ በመጣው መልኩ ከተገነዘበ በኋላ፣

1. አመልካች ከደንበኛው ጋር የፈጸመው ህጋዊ የኢንሹራንስ ውል አለ ወይስ የለም?
2. አመልካች ለደንበኛው ተክቶ ወይም ተዳርጐ በስር ተከሳሾች (በእነ ተጠሪ) ክስ ሊመሰረት ይችላል ወይስ አይችልም?
3. ተጠሪው የእቃው ማጓዝ ውል ወስደዋል ወይስ አልወሰዱም? በሌላ አባባል ተጠሪው በዚህ ጉዳይ አጓዥ ናቸው ወይስ አይደሉም?

የሚሉ መሰረታዊ ጭብጦችን በማውጣት ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡-

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ የስር ፍርድ ቤቶቹ የሰጡት ትርጉም በተጠሪውና በደንበኛው መካከል በሕግ የሚጸና የኢንሹራንስ ውል የለም የሚል ለዚህም የሰጡት ምክንያት በውሉ ላይ ተዋዋይ ወገኖቹና ምስክሮች ስላልፈረሙበት በሕግ የሚፈለግበትን ተገቢ ፎርማሊቲ አላሟላም፤የንግድ ሕጉ የኢንሹራንስ ውል ይዘት ከሚዘረዝር በስተቀር ስለውሉ ፎርማሊቲ የሚለው ነገር ስለሌለ የኢንሹራንስ ውል ፎርማሊቲ በሚመለከት በፍትሃብሄር ሕግ ውስጥ በጠቅላላ ውሉ ዓንቀጽ 1725 እና 1727 በተመለከተው መሰረት መከናወን እንዳለበት ማለትም ውሉ የግድ በጽሁፍ መዘጋጀት ያለበትና ተዋዋይ ወገኖችና ምስክሮች የግድ ሊፈርሙት እንደሚገባ፣ይህ ሳይሟላ ከቀረ ግን በፍትሃብሄር ሕግ ቁጥር ዓንቀጽ 1720(1) መሰረት ውሉ እንደረቀቀ የሚቆጠርና ምንም አይነት ውጤት የማያስከትል ነው፤በመሆኑም አመልካች ከደንበኛው ጋር ያደረገው የኢንሹራንስ ውል በተከሳሾቹ ላይ ግዴታ ሊያስከትል አይችልም የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የንግድ ሕጉ ስለ የኢንሹራንስ ውል ፎርማሊቲ ምንም ነገር አላለም የተባለው ተገቢነት የለውም፡፡ ምክንያቱም የንግድ ሕግ አንቀጽ 657 ስለ ውሉ ፎርማሊቲ የሚደነግግ ሃሳብ አስፍሯል፤ ይኸውም የኢንሹራንስ ውል በኢንሹራንስ

ውል ፖሊሲ በሚባል ጽሁፍ እንደሚደገፍና የመድህን ገቢው ጥያቄ መሰረት በማድረግ በፖሊሲው ላይ መድህን ሰጭው ከፈረመ ህጋዊ የሆነ የኢንሹራንስ ውል ግንኙነት በመድህን ሰጭው እና በመድህን ገቢው መካከል እንደሚመሰረት ነው፤ይህ ሁኔታ ደግሞ የንግድ ሕጉ ልዩ የሆነ የኢንሹራንስ ውል አፈፃፀም የሰፈረ እንጂ ጉዳዩ በጠቅላላ የውል ሕግ የሚመራ ግንኙነት አይደለም፤ይህ ሰበር ችሎትም የኢንሹራንስ ውል አለ ለማለት ተመሳሳይ ትርጉም በሰ/መ/ቁ. 24703 ሚያዝያ 09 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶቹ በአመልካችና በደንበኛው መካከል የተደረገው ውል ሁለቱ ወገኖች እና ምስክሮች የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1725 እና 1727 በሚያዙት መሰረት ባለመፈረማቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1720/1/ መሰረት የኢንሹራንስ ውል ግንኙነት የለም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ ሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በመሆኑም በአመልካችና በደንበኛው መካከል ህጋዊ የሆነ የኢንሹራንስ ውል ግንኙነት አለ ብለናል፡፡

ሁለተኛው ጭብጥ በተመለከተ የአመልካች ደንበኛ ሐምሌ 17 ቀን 1995 ዓ.ም የተፃፈ ሰነድ አዘጋጅቶ አመልካቹ በእርሱ እግር ተተክቶ መብቱን የማስከበር ወይም የመዳረግ መብት እንዳለው ቢያረጋግጥም፣የስር ፍ/ቤቶቹ በሰጡት ፍርድ ይህ የመዳረግ መብት ሕጋዊ ከሆነ የኢንሹራንስ ውል የመነጨ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡ ይሁን እንጂ በአመልካችና በደንበኛው መካከል ሕጋዊ የሆነ የኢንሹራንስ ውል ግንኙነት እንዳለ በላይኛው ጭብጥ የተረጋገጠ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካቹ ን/ሕ/ቁ. 683 መሰረት በደንበኛው እግር ተዳርጐ በተከሳሾቹ ላይ ክስ ማቅረብ የሚያስችለውን መብት ከደንበኛው አግኝቶ እያለ የስር ፍ/ቤቶቹ ሳይቀበሉት መቅረታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡

ሦስተኛውን ጭብጥ በሚመለከት አመልካቹ ተጠሪው የመኪናዋ ባለንብረት በመሆናቸው አጓዥ ናቸው፤በስር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው የተባበሩት የጭነት ማመላለሻ ንብረቶች ማህበር ለተጠሪው ጥቅም ሲባል የሚጫን ነገር ከማፈላለግ ውጭ ጥቅሙ ለተጠሪው የሚውል በመሆኑ በን/ሕ/ቁ. 566/የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2251 መሰረት የትራንስፖርት ስራው በውክልና የሚያስተዳድር አካል ነው፤ስለሆነም ተጠሪው አጓዥ መባል አለበት ሲል ተጠሪው ደግሞ አጓዥ እንዳልሆኑ በመግለጽ የአመልካቹ አባባሉን የሚደግፍለት ማስረጃ አላቀረበም በማለት ይከራከራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳት ያደረሰችውን የአሁኑ ተጠሪ መኪናን በሚመለከት ከአመልካቹ ደንበኛ ጋር የአሁኑ ተጠሪ የመጓጓዣ ውል በቀጥታ የፈጸመው በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው (የተባበሩት የጭነት ማመላለሻ ባለንብረቶች ማህበር) ቢሆንም ይህ አካል ያደረገው ውል ተጠሪውን በመወከል ነው፤ምክንያቱም የዚህ አካል የስራ ድርሻ በማህበሩ የታቀፉት መኪኖች የጭነት ስራ እንዲያገኙ ከማድረግ አልፎ የእያንዳንዱ መኪና የጭነት ኪራይ ገቢ የባለቤቱ ነው፣በአሁኑ ክርክርም ተጠሪው መኪናቸው በተባበሩት የጭነት ማመላለሻ ማህበር ከመታቀፏ ውጭ የመኪናው ገቢ በቀጥታ ተጠቃሚ ናቸው፤ስለሆነም በንግድ ሕ/ቁ. 566 እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2251 መሰረት ተጠሪው ከአመልካቹ ደንበኛ ጋር የጭነት ማጓዝ ውል የነበራቸው ሆነው እያለ የስር ፍ/ቤቶቹ ተጠሪው አጓዥ አይደሉም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43650፣ሰኔ 16 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 41455፣መስከረም 23/2000 ዓ.ም የሰጧቸው ፍርዶች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪው ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 129,333.93(አንድ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ ሦስት መቶ ሰላሳ ሦስት ብር ከዘጠና ሦስት ሣንቲም) እንዲሁም ክሱ ከቀረበበት ከመስከረም 14/1997 ዓ.ም ጀምሮ 9% ወለድ ተከፍሎ እስኪያልቅ ለአመልካች እንዲከፍለው ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

# የንግድ ሕግ

የሰ/መ/ቁ. 33954

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መሰሠ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ዘውዱ ቢረዳ - ከጠበቃቸው አቶ ፍቅሩ ታደሰ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 30404 ሐምሌ 19 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 59124 ጥቅምት 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ህዳር 16 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በመጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ባልና ሚስት የነበሩት አመልካችና ተጠሪ በፍቺ ጋብቻቸው መፍረሱን ተከትሎ የቀረበው የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ነው፡፡ አመልካች በመርካቶ የገበያ አዳራሽ በቁጥር 209 እና 210 በተሰጣቸው ብር 100,000 /መቶ ሺ ብር/ የሚገመት የተዘጋጁ የሴት ልብሶችና ጫማ የያዙ የሱቅ የንግድ ድርጅቶች የጋራ ንብረት በመሆኑ ፍርድ ቤቱ እንዲያካፍላት የጠየቀች ሲሆን ከላይ ከተገለፁት የሱቅ የንግድ ድርጅቶች በተጨማሪ ሌሎች ንብረቶችም እንዲያካፍላት ጠይቃለች፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በሱቅ የንግድ ድርጅቶቹ ውስጥ ያለው ሸቀጥ ለብቻው ተቆጥሮ አመልካችና ተጠሪ እንዲካፈሉ የወሰነ ሲሆን በቁጥር 209 እና 210 ያለው የንግድ ድርጅትን በተመለከተ ቤቶቹ የኪቤአድ ንብረት በመሆናቸው በጋራ ንብረትነት የሚካፈሉበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ምክንያት የለም በማለት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ አመልካች የሥር ፍርድ ቤቶች በቁጥር 209 እና 210 ያለውን የንግድ ድርጅት በጋራ ንብረትነት ለመካፈል ያቀረቡትን ጥያቄ ባግባቡ አልመዘኑም፤ የሥር ፍ/ቤት የሰጠውም ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፤ የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ አስደግፌ ያቀረብኩትን ሌሎች የጋራ ንብረት ክፍያዎች አላግባብ ያለፈብኝ ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ለሰበር ባቀረቡት አቤቱታ ጠይቀዋል፡፡

ይኸ የሰበር ችሎትም የሥር ፍርድ ቤት በቁጥር 209 እና 210 የሚንቀሣቀሰው የንግድ ድርጅት የሚከናወንባቸው ክፍሎች የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ንብረት በመሆናቸው በጋራ ንብረትነት ለማካፈል አይቻልም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ተገቢነት ለማጣራት ብቻ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ለተጠሪ እንዲደርሰው አድርጓል፡፡ ተጠሪ በቁጥር 209 እና 210 ያለው የንግድ ድርጅትና የመከራየት መብት ከጋብቻ በፊትም ሆነ በኋላ የእኔ የግል ንብረት በመሆኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በቁጥር 209 እና 210 ይከናወን የነበረው የንግድ ድርጅት በእሣት ቃጠሎ ምክንያት ከወደመ በኋላ እንደገና በጋራ ሀብታችን የተቋቋመና የተደራጀ ስለመሆኑ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ክዶ ያልተከራከረ በመሆኑ በሰበር ደረጃ ይህንን ነጥብ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም የሚል የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና የሰበር ችሎት በጭብጥነት የያዘው ነጥብ፣ አመልካችና መልስ ሰጭ በሰበር ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በመጀመሪያ ደረጃ አመልካች የጋራ ንብረት ስለሆነ ድርሻዬ ተከፍሎ ሊሰጠኝ ይገባል በማለት የጠየቁት ንብረትነታቸው የመንግሥት የሆኑ የንግድ ማከናወኛ ክፍሎችን አይደለም፡፡ አመልካች ለመካፈል የጠየቁት በመርካቶ የገበያ አዳራሽ ውስጥ በቁጥር 209 እና 210 የሆነውን የጫማና የተዘጋጁ የሴት ልብሶች መሸጫ የንግድ ድርጅት ግምታቸው 100,000 /አንድ መቶ ሺ ብር/ የሆነ ሸቀጦችን እንደያዘ እንደሆነ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሣኔው በግልጽ አስፍሮታል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አመልካች በጋራ ንብረትነት ለመካፈል ጥያቄ ያቀረቡት በሱቅ የንግድ ድርጅት ውስጥ የሚገኙ ሸቀጦችን ለብቻ ንግድ የሚከናወንባቸውን ክፍሎች ደግሞ ለብቻ በመነጣጠል ፍርድ ቤቱ እንዲያካፍላቸው አይደለም፡፡

አመልካች በጋራ ንብረትነት ፍርድ ቤቱ እንዲያካፍላቸው የጠየቁት በመርካቶ የገበያ አዳራሽ በቁጥር 209 ያለውን የንግድ ድርጅትና በቁጥር 210 ያለውን የንግድ ድርጅት የንግድ ሕግ ቁጥር 124 በሚደነግገው መሠረት በንግድ ድርጅትነቱ ከውስጡ ካሉ ሸቀጦች ጋር በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ይህንን በማለፍ አመልካች ሸቀጦቹ ለብቻ ቆጠራ ተደርጎ እንዲካፈሉ የንግድ ሥራ የሚከናወንባቸው ክፍሎች ግን የጋራ ንብረት ሣይሆኑ ንብረትነታቸው የመንግሥት ስለሆነ ጥያቄሽ ተገቢነት የለውም በማለት መወሰኑ አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የሥር ፍርድ ቤት በቁጥር 209 እና 210 ያለው የንግድ ድርጅቶች በንግድ ድርጅትነታቸው ሣይሆን ነጣጥሎ በማየት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ከንግድ ሕግ ቁጥር 127 ድንጋጌዎች ለመረዳት እንደሚቻለው የአንድ የንግድ ድርጅት መሠረታዊ አካል የንግድ ድርጅቱ መልካም ዝና ስምና በደንበኞቹ የተለመደ መሆኑ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ነገሮችን አካትቶ የሚይዝ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ንግዱ የሚከናወንበትን ክፍል የመከራየት መብት የንግድ ድርጅት አንደኛው ክፍል እንደሆነ በንግድ ሕግ ቁጥር 127 ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም አመልካች በዚህ የሕግ ድንጋጌ መሠረት በመርካቶ የገበያ አዳራሽ በቁጥር 209 እና 210 በጋራ ንብረትነት አመልካችና ተጠሪ ያላቸውን የንግድ ድርጅት የንግድ ሥራው የሚከናወንበትን ክፍል የመከራየት መብት ጭምር ፍርድ ቤቱ እንዲያካፍላትና እንዲወስንላት ያቀረበችውን ሕጋዊ ጥያቄ የንግድ ሥራ የሚከናወንባቸው ክፍሎች የመንግሥት ንብረቶች ናቸው በሚል ምክንያት ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በመርካቶ የገበያ አዳራሽ በቁጥር 209 እና 210 ያሉት የሱቅ የንግድ ሥራ ድርጅቶች የተጠሪ የግል ንብረት ናቸው በማለት ሣይሆን የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ቤት የመንግሥት የልማት ድርጅት ንብረት በመሆኑ በጋራ ንብረትነት ለማካፈል አይችልም በማለት በመሆኑ ተጠሪ የሱቅ የንግድ ድርጅቱ የግል ንብረቴ ነው በማለት በሰበር ደረጃ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሆኑም አመልካች በጋራ ንብረትነት ለመካፈል የጠየቀችው በመርካቶ የገበያ አዳራሽ በቁጥር 209 እና 210 ያሉትን የሱቅ የንግድ ድርጅቶች በንግድ ድርጅትነታቸው ባሉበት በንግድ ሕግ ቁጥር 124 እና 127 ድንጋጌ መሠረት ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ እነዚህን የሕግ ድንጋጌዎች እና የንግድ ሕግ ቁጥር 145 ንዑስ አንቀጽ 1ን ሣያገናዝብ፣ አመልካች የሌላ ሰው ንብረት የሆነ የንግድ ማከናወኛ ቤት ለመካፈል መጠየቅ አትችልም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ በመርካቶ ገበያ አዳራሽ በቁጥር 209 እና 210 ያሉት የሱቅ ንግድ ድርጅቶች አመልካች ለመካፈል ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ይህንን ነጥብ በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ስህተት የለበትም በማለት የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ አመልካች በመርካቶ የገበያ አዳራሽ በቁጥር 209 እና 210 ያሉት የሱቅ የንግድ ድርጅቶች የንግድ ሥራ የሚከናወንበትን ክፍል ከመከራየት መብት ጭምር በጋራ ንብረትነት የመካፈል፣ መብት አላት ብለናል፡፡ በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም የውሣኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡

3/ በሰበር ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 33470

ኅዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ወ/ሮ እጅጋየሁ ታደሰ - ቀረበች

**ተጠሪ**፡- መገርሳ ጉደታ - ከጠበቃ ሻለቃ ሃይሉ ቦረና ጋር ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የሽርክና ውልን መሰረት ያደረገ የንብረት እና የገንዘብ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች ናት፡፡ በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተችውም በሞት የተለየው ባልዋ እና ተጠሪ በጋራ አቋቁመው ሲሰሩበት ከነበረው ጋራዥ ከተገኘው ገቢ ድርሻዋን እንዲከፍላት ወይም የጋራዡን ግማሽ እንዲሰጣት በመጠየቅ ነው ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ ጋራዡ የግሉ እንደሆነ፣ከአመልካች ባል ጋር አድርገውት የነበረው ውል የሽርክና ሳይሆን የደባልነት እንደሆነ በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ ክሱን የሰማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪ እና በአመልካች ባል መካከል የተደረገ የሽርክና ውል የለም በማለት ወስኖ የነበረ ቢሆንም፤ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሽርክና ውል መኖሩን በማረጋገጥና በመወሰኑ በጉዳዩ ስረ- ነገር ላይ ክርክሩ ቀጥሎአል፡፡ በመጨረሻም የእሽሙር ሽርክና ውል ተደርጐ ነበር ቢባልም፤በአመልካች ባል ሞት ምክንያት ፈርሶአል፡፡ የሽርክና ውሉ ተዋዋዮቹ ይዘውት የመጡትን ንብረት እንጂ ጋራዡን አይመለከትም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ፍ/ቤቱ አመልካች ያቀረበችውን የገቢና የጋራዥ ድርሻ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበበት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም ብለዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መስከረም 30 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የሽርክና ውል አለ እየተባለ የአመልካች የገንዘብ ክፍያ እና የንብረት ጥያቄ ውድቅ የተደረገው በሕግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በተጠሪ እና በአመልካች ባል መካከል የእሽሙር የሽርክና ውል እንደነበር በፍ/ቤት ተረጋግጦ የተወሰነ በመሆኑ ይህን በተመለከተ በአሁኑ ደረጃ የሚባል ነገር የለም፡፡ በዚህ ደረጃ ሊወሰን የሚገባው ነጥብ የዚህ ውጤት ምንድነው የሚለው ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በውሳኔው እንደገለፀው ተዋዋዮቹ ውሉን ሲያደርጉ በየግላቸው የነበሩዋቸውን መሣሪያዎች ይዘው መግባታቸውን በውሉ ላይ በግልጽ በማስፈር ነው፡፡ ከዚህ ባለፈም የጋራዡን ንግድ ሥራ በጋራ ለማቋቋም ውል አላደረጉም፡፡ በየግላቸው የነበሩዋቸውን መሣሪዎች በመያዝ ሥራ የሚሰሩበት ጋራዥ በተጠሪ ይዞታ ስር እንደሆነና የሚታወሰውም በሱ ስም ብቻ እንደሆነም አላከራከረም፡፡ በንግድ ሕግ ቁ.271 እንደተመለከተው የእሽሙር ማህበር ማህበርተኞቹ እንደፈቃዳቸው የውላቸውን ሁኔታዎች ወስነው የሚያቋቁሙት እንደመሆኑ በተያዘው ጉዳይም ተዋዋዮቹ በሚያመቻቸው መንገድ ወስነው እንዳቋቋሙት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በንግድ ሕግ ቁጥር 273 እንደተደነገገው ደግሞ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር እያንዳንዱ ማህበርተኛ ገቢ ላደረገው መዋጮ ባለሃብትነቱን እንደያዘ

ነው የሚቆየው፡፡ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እንደሚታየው ውሉ ከተደረገ በኋላ በጋራ የተገዛ ንብረት ወይም የተደረገ መዋጮ የለም፡፡ ይልቁንም የጋራዥ ንግዱ በተጠሪ ስም ብቻ እንደተመዘገበ ነው የቀጠለው፡፡ የንግድ ፈቃዱም በተጠሪ ስም ነው፡፡ በመሆኑም የአመልካች ባለቤት የጋራዡም የጋራ ባለሃብት ነው የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ሲጠቃለል አመልካች በጋራዡ ላይ የጋራ ባለሐብትነት መብት እንዳለ በመቁጠር ያቀረበችው ክርክር በስር ፍ/ቤቶች ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው፡፡

ቀጥለን የተመለከትነው ሌላው ነጥብ ሟች እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ያለውን የትርፍ ክፍያ እና የሽርክና ውሉ በተደረገበት ጊዜ ይዘዋቸው መጣ የተባሉትን መሣሪያዎች በሚመለከት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን የውሳኔውን ክፍል ነው፡፡ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበችው አቤቱታ ጭምር እነዚህን ነጥቦች በማንሳት ተከራክራለች፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ እንደተመለከተው አመልካች በትርፉም ሆነ በመሣሪያዎቹ ላይ መብት እንዳላት ግንዛቤ ተወስዶአል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን በጠየቀችው ዳኝነት መሰረት ይህ ይገባሻል ወይም አይገባሽም የሚል ውሳኔ አልተሰጠም፡፡ ስለዚህም በዚህ ረገድ ሊታረም የሚገባው ስህተት እንዳለ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ስህተቱ ይስተካከልም ዘንድ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05140 ሰኔ 26 ቀን 1998 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 48762 ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. አመልካች ከባለቤትዋ ሞት በኋላ ያለውን ትርፍ እንድትካፈል ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ ጋራዡን ግማሽ ልካፈል በማለት ያቀረበችውም እንደዚሁ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. የሽርክና ውሉ በሟች ምክንያት እስከፈረሰበት ቀን ድረስ ለነበረው ጊዜ የተገኘ ትርፍ ካለ አመልካች የመካፈል መብት አላት፡፡ ሟች ለሽርክና ማህበሩ በመዋጮነት ገቢ ያደረጋቸው መሣሪያዎች ካሉም ሊመለሱላት ይገባል፡፡ ተጠሪ በእነዚህ መሣሪያዎች በመጠቀም ያገኘው ገቢ ካለም እንደዚሁ ተጣርቶ ለአመልካች ሊከፈል ይገባል፡፡ ስለዚህ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩ በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ በእነዚህ ሦስት ነጥቦች ግራ ቀኝ ወገኖችን ካከራከረ በኋላ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መቁ 34945

ህዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ፡- ወ/ሮ መስታወት በላቸው - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ፡- አቶ ለገሠ ሣህሉ - ጠ/መከተ ዳኜ ቀረቡ

**ፍ ር ድ**

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የንብረት ክፍፍሉ ጉዳይ በቤተ ዘመድ ሽምግልና ጉባኤ ሲታይ ቆይቶ ጉባኤው በ06/21/1998 ውሣኔ ሠጥቷል፡፡ ይህንኑ ውሣኔ እንዲያጸድቅላቸው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ሲያመለክቱ አመልካች ግን ጉባኤው ክርክሩን በአግባቡ ለመምራት መሠረታዊ የህግ ግንዛቤ የሌለው በመሆኑ የተሠጠውም ከፊል ውሣኔ ከጉባኤው ስልጣን ውጪ በመሆኑና የህግ ስህተቶችም ስላሉበት ጉዳዩን ፍ/ቤቱ ተረክቦ ውሣኔ ይስጥበት በማለት አስተያየታቸውን ሠጥተዋል፡፡ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ግን የአመልካችን መቃወሚያና ክርክር ወድቅ አድርጎ ውሣኔውን በማጽናት የጋራ ናቸው ተብለው ውሣኔ የተሠጠባቸው ንብረቶችን ከተስማሙ በአይነት እንዲካፈሉ ካልተቻለ አንደኛው ለሌለኛው ልዩነቱን እንዲከፍል በማድረግ እንዲካፈሉ በዚህ ካልተስማሙ ንብረቶቹ በሐራጅ ተሸጠው ገንዘቡን እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው አመልካች ለተጠሪ ብድር ብር 700,000 (ሰባት መቶ ሺ.ህ)ስለከፈልኩ ግማሹን ተጠሪ ይክፈሉ በማለት አቅርበውት የነበረውን የዳኝነት ጥያቄ ጉባኤው ሣይቀበል እንዲሁም አመልካች ለተጠሪ የዚህን ገንዘብ ግማሽ እንዲከፍሉ በማለት የሠጠውን ውሣኔ ብቻ በመሻር የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አፅንቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ የረር ሃላፊነቱ የተወሠነ የግል ማህበር የራሱ የህግ ሠውነት ያለው በስሙ መከሠስና መክሠስ የሚችል ድርጅት መሆኑ እየታወቀ እንዲካፈሉት መወሠኑ ለተጠሪ የግል ዕዳ ከጋራ ገንዘብ የተከፈለ ገንዘብ ለመሆኑ ምስክር ሣይሠማ ጥያቄው ውድቅ መደረጉ እንዲሁም ሌሎች የቤት ቁሣቁሶች በተመለከተ ማስረጃ ሣይሰማ መወሠኑ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎታም የአመልካች አቤቱታ በሠበር ችሎት ሊጣራ የሚገባው መሆኑን በማመን ተጠሪ ቀርበው እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ስህተት ተፈጽሞበታል ከተባለው ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

በዚህ መሠረት ራሱን ችሎ የህግ ሠውነት ያለው ድርጅት በቤተ ዘመድ ሽምግልና ጉባኤ እንዲከፋፈል መወሠኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑን እንዲሁም ማስረጃ ሣይሠማ ውሣኔ ተሠጥቶበታል የተባለው የንብረት ክፍፍል አግባብ መሆን አለመሆኑን ችሎቱ መርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ የረር ኃላፊነቱ የተወሠነ የግል ማህበር በንግድ ህጉ መሠረት የተቋቋመ እና የህግ ሠውነት ያለው መሆኑ ግራ ቀኙ አልተካካዱበትም፡፡ የንግድ ማህበሮች የሚቋቋሙበት እና የሚፈርሱበት ሁኔታ ደግሞ በንግድ ህጉ ውስጥ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት የተወሠነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር ሊፈርስ የሚችልበት ምክንያቶች በንግድ ህግ ቁጥር 542 ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ በዚህ የንግድ ህጉ ድንጋጌ ሥር የተመለከቱት ምክንያቶች ሲኖሩ ማህበሩ በፍ/ቤት አማካኝነት ይፈርሣል፡፡ ከዚህ ውጪ የንግድ ማህበሩ አባላት የህጉን ሥርዓት ሣይከተሉ በራሣቸው

ወይም በሌላ አካል አማካኝነት ሊፈርስ የሚችልበት የህግ መሠረት የለም፡፡ በፍ/ቤት አማካኝነት ከፈረሠና ሂሣቡ ተጣርቶ የመጨረሻው ውጤት በሂሣብ አጣሪዎች ከታወቀ በኂላ ማህበሩ ከንግድ መዝገብ ተሠርዞ በህግ የተሠጠው መብቱ ቀሪ የሚሆንበትን ሥርዓት የንግድ ህጉ አስቀምጧል ሃላፊነቱ የተወሠነ የግል ማህበር የህግ ሠውነት ያለውና በራሱ ስም ህጋዊ ተግባራትን ሊፈፅም የሚችል ሊከስና ሊከሠስ የሚችል በመሆኑ የሠራቸው ህጋዊ ተግባራትም የተለያዩ ውጤቶች የሚያስከትሉ በመሆኑም ህጉ በተለየ ሁኔታ እንዲስተናገዱ አድርጓል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን የማህበሩ ብቸኛ የአክስዮን ባለድርሻ ባልና ሚስቱ ቢሆኑ እንኳን እንደሌላ የባልና ሚስት  የጋራ ንብረት ማህበሩን በዓይነት የሚካፈሉት ወይም በሃራጅ ተሸጦ ገንዘቡን ሊከፋፈሉ የሚችሉበት የህግ መሠረት የለም፡፡ ስለሆነም የሽምግልና ጉባኤው እንደሌላ ንብረት ማህበሩን እንዲከፋፈሉ የሠጠው ውሣኔ የንግድ ህጉን ያላገናዘበ ነው፡፡

የቀረውን ነጥብ በተመለከተ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች የመኖሪያና የጀምናዝየም ዕቃዎች ከቤቶቹ ጋር አብረው የተሸጡ መሆኑ በአግባቡ ሣይጣራ ተወስኖብኛል ያሉ ሲሆንም ከሽምግልና ጉባኤው ውሣኔ ቤቶቹ መሸጣቸውን የሚያረጋግጠው  የፁሁፍ ማስረጃ ከቤቶቹ ጋር የቤትና የጅምናዝየም ዕቃዎች አብረው መሸጣቸውን የማያመለክት በመሆኑ በቂ ማስረጃም ያልቀረበበት መሆኑን በማረጋገጥ ውሣኔ መስጠቱን ተመልክተናል፡፡

በሌላ በኩል ግን አመልካች እነዚህ የቤት እቃዎችና የጅምናዝየም ዕቃዎች ቤቱን የገዙት ግለሠብ ከቤቱ ጋር አብረው የገዟቸው ስለመሆናቸው ቀርበው እንዲመሠክሩላቸው በማስረጃነት የቆጠሯቸው መሆኑን ከሽምግልና ጉባኤ ውሣኔ ላይ ተገንዝበናል፡፡ እነዚህ ንብረቶች የሚንቀሣቀሱ ንብረቶች በመሆናቸው የንብረቶቹ ሽያጭ የግድ በፁሁፍ መደረግ ያለበት መሆኑ ወይም ንብረቶቹ ለመሸጣቸው ሊረጋገጥ የሚገባው በፁሁፍ /በሠነድ ማስረጃ/ ብቻ ለመሆኑ በህግ ተለይቶ የተመለከተ ነገር የለም፡፡ በህግ በተለይ ሁኔታ እንዲረጋገጥ ካልተመለከተ በቀር አንድን ጉዳይ በማንኛውም አይነት ማስረጃ ማረጋገጥ እንደሚቻል ከፍ/ብ/ህ/ቁ.2002 እና 1677(1) መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች የቤትና የጅምናዝየም እቃዎቹ ስለመሸጣቸው በሰው ምስክር ለማስረዳት እየጠየቁ ጉባኤው በቤት ሽያጭ ውሉ ላይ እነዚህ ንብረቶች ስለመሸጣቸው አልተገለፀም በማለት ክርክራቸውን ውድቅ ማድረጉ የአመልካችን የመከላከል መሠረታዊ መብት የማያጣብብ ሆኖ አግኝተዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የረር ሃላፊነቱ የተወሠነ የግል ማህበር እና የቤትና የጅምናዝየም ዕቃዎችን በተመለከተ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ሚያዝያ 22/1999 ዓ.ም. በመ/ቁ 55299 የሠጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ህዳር 12/2000 ዓ.ም. በመ/ቁ 55333 የሠጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡
2. የረር ኃ/የተ/የግ/ማ በንግድ ህጉ በተመለከተው መሠረት የሚፈርስና ሂሣቡ የሚጣራ ካልሆነ በቀር እንደሌሎቹ የባልና ማስት የጋራ ንብረቶች ተገቢዎቹ በዓይነት የሚካፈሉት ወይም ተሸጦ ገንዘቡን የሚካፈሉት ንብረት አይደለም ብለናል፡፡
3. የቤትና የጅምናዝየም ዕቃዎችን በተመለከተ አመልካች በማስረጃነት የቆጠሯቸው ምስክር ቀርበው ከተሠሙ በኂላ ተገቢው ውሣኔ እንዲሠጥ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343 (1) መሠረት ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡
4. ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

የሰ/መ/ቁ. 31264

ጥር 5 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች** ፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

31264

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ እመቤት መኰንን- ጠበቃ ነቃጥበብ በየነ፡፡

**ተጠሪ**፡- ወረዳ 20 ቀ. 29 አ/ጽ/ቤት ነ/ፈጅ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪና በሥር ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሣሾች ላይ ባቀረቡት ክስ በወረዳ 20 ቀበሌ 29 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 449 የሆነውን ቤት ከቀበሌው አስተዳደር አንደኛ ተከሣሽ ላይ ተከራይቼ በቤቱ የሆቴል የንግድ ድርጅት በማቋቋም ስጠቀምበት የነበረ ሲሆን ይህንኑ የንግድ ድርጅት ለማስፋፋት ከቤቱ ፊት ለፊት በነበረው 67 ካሬ ሜትር ባዶ ቦታ ላይ ግንባታ ፈጽሜ የድርጅቱ አካል አድርጋ ለመጠቀም ለቀበሌው ጥያቄ አቅርቤ ተፈቅዶልኝ ብር 300,000(ሦስት መቶ ሺ.ህ) ወጭ አድርጌ ገንብቻለሁ፡፡ ከዚህ በኋላም ለሁለተኛ ተከሣሽ /ለአሁን ተጠሪ/ እና ለሦስተኛ ተከሣሽ አውራሽ ወ/ሮ የሻሐረግ ገዳሙ የሆቴል ንግድ ድርጅቱን ከሙሉ የሆቴል ቤት መገልገያዎች ጋር በ3/10/87 ዓ/ም በተደረገ ውል ያከራየሁ ሲሆን ነገር ግን የውሉ ማለቂያ ቀን በሆነው በ2/10/89 ዓ/ም ተከራይ ወ/ሮ የሻረግ ገዳሙ ለከሣሽ መመለስ ሲገባት ከአንደኛ ተከሣሽ ጋር በመተባበር ከሐምሌ ወር 1998 ዓ/ም ጀምሮ ድርጅቱን ቀበሌው ወርሶታል ከዚህ በኋላ የድርጅቱ ሕጋዊ ተከራይ ወ/ሮ የሻረግ ገዳሙ ነች በማለት ለማስረከብ ፈቃደኛ ያልሆኑ ስለሆነ ይህንኑ ድርጅት ሶስቱም ተከሣሾች በአንድነትና በነጠላ ለከሣሽ እንዲያስረክቡ ከሣሽ ማግኘት የሚገባኝን የተቋረጠ ኪራይ በድምሩ ብር 342,000 (ሦስት መቶ አርባ ሁለት ሺ.ህ) በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ፡፡

የድርጅቱን ግንባታ ለማከናወን ወጭ ያደረግሁትንም ብር 300,000(ሦስት መቶ ሺ.ህ) በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ እንደዚሁም የወ/ሮ የሻረግ ገዳሙ ወራሾች የሆኑት ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሣሾች በኪራይ ውሉ ላይ የተመለከተውን ብር 4000(አራት ሺ.ህ) የገደብ መቀጫ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሾችም በየበኩላቸው የመከላከያ መልስ ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ የክርክር ነጥባቸውም በከሣሽና በቀበሌው አስተዳደር መካከል ተደርጎ የነበረው የኪራይ ውል መንግስት ባወጣው የተከራይ አከራይ መመሪያ መሠረት ተቋርጦ በአንደኛ ተከሣሽና በወ/ሮ የሻረግ ገዳሙ መካከል የኪራይ ውል የተደረገ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ለክሱ መነሻ የሆነውን የንግድ ቤት አንደኛ ተከሣሽ የቀበሌው አስተዳደር ለከሣሽ ማከራየቱን ያልካደ ሲሆን ውሉን ለማቋረጥ ያቀረበው ምክንያት ከሣሽ የቤቱን ኪራይ በወቅቱ ስትከፍል ያልነበረች ከመሆኑም በላይ ለሌላ ሰውም አሳልፋ አከራይታለች በማለት ሲሆን ነገር ግን ይህ ሁኔታ ውሉን በአንድ ወገን በእራሱ ሥልጣን ለማቋረጥ እንደሚያስችለው ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ ስለሌለ በመካከላቸው የነበረው ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው ካለ በኋላ በከሣሽና በሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሣሾች አውራሽ በወ/ሮ የሻረግ ገዳሙ መካከል የተደረገው ውል ጊዜው ያላለቀ ስለሆነ ይህንኑ የንግድ ድርጅት ሦስቱም ተከሣሾች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ለከሣሽ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የኪራይ ክፍያ ጥያቄውን በተመለከተም ከሳሽ ከድርጅቱ ኪራይ ያጣቸው ብር 54,000(ሃምሣ አራት ሺህ) ስለሆነ ይህንኑ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ተከሣሾች ለከሣሽ እንዲከፍሉ የንግድ ቤቱን ለማስፋፋት ለግንባታ ወጭ ሆኗል የተባለውና ከሣሽ እንዲተካላቸው የጠየቁት የብር 300,000(ሦስት መቶ ሺህ) ክፍያ በተመለከተ በንግድ ቤቱ ላይ ከተከራይነት ያለፈ መብት እንዳላት ከሣሽ ያላስረዳች ስለሆነ የክፍያ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡ የሥር አንደኛ ተከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም ይግባኙን መርምሮ መ/ሰጪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሮ መልስ ሰጭ ልከራየው የምትለው ቤት ንብረትነቱ የቀበሌው አስተዳደር /የይግባኝ ባይ/ ሲሆን ንብረቱ በመሆኑም ከመልስ ሰጭዋ ጋር የነበረውን የኪራይ ውል በመተው ለሌላ ሰው አከራይቶታል፡፡ በእርግጥ ቤቱ የንግድ ሥራ የሚሰራበት በመሆኑ መልስ ሰጭ የይግባኝ ባይን ፈቃድ ሣትጠይቅ በኪራይ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ እንደምትችል በንግድ ሕግ ቁጠር 145/1/ ላይ ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን ይህ ድንጋጌ የቤቱ ባለሀብት የሆነውን ይግባኝ ባይን ከመልስ ሰጭ ጋር አድርጐት የነበረውን የኪራይ ውል እንዳያቋርጥ የሚያግደው ነው በሚል የሚተረጐም እንዳልሆነ ተገንዝበናል፡፡ ይግባኝ ባይ ከፈቃዱ ውጭ ከማይፈልገው ሰው ጋር የኪራይ ውል አድርግ የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ባይ ቤቱን ለመልስ ሰጭ አስረክብ ኪራይም ክፈል መባሉ ትክክል አይደለም በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔውን ሽሯል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪ ከማይፈልገው ሰው ጋር የኪራይ ውል አድርግ የሚባልበት ምክንያት የለም ተብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ አግባብነቱ ከንግድ ሕግ ቁጥር 145 አንፃር ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን በቃል አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ተጠሪ በወረዳ 20 ቀበሌ 29 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 449 የሆነውን ቤት ለአመልካች እንዳከራየና አመልካችም በቤቱ የሆቴል ንግድ ድርጅት በማቋቋም ሲሰሩ እንደነበር ከተጠሪ ባገኙት ፈቃድ መሠረትም የሆቴል ድርጅቱን አስፋፍተው እንዲሰሩና በኋላም ይህንኑ የሆቴል ድርጅት ለሥር ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሣሾች አውራሽ ለወ/ሮ የሻሐረግ ገዳሙ በ3/10/87 ዓ/ም በተደረገ የንግድ መደብር ኪራይ ውል እንዳከራዩ ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩልም ተጠሪ ከአመልካች ጋር አድርጐት የነበረውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ በምክንያትነት የጠቀሰው አመልካች የቤቱን ኪራይ በወቅቱ አትከፍልም ነበር፡፡ ቤቱንም ለሌላ ሰው አሳልፋ አከራይታለች በማለት ሲሆን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ መልኩ የቀረበውን የተጠሪን ክርክር ሳይቀበለው የቀረው ይህ ድርጊት በከሣሽ /በአሁን አመልካች/ ተፈጽሟል ቢባል በዚህ ድርጊት መነሻነት ውሉን በአንድ ወገን በእራሱ ሥልጣን ለማቋረጥ ከውሉ ወይም ከሕግ የመነጨ መብት ያለው ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ከሣሽ ውሉን የጣሰ ድርጊት ፈጽማለች ቢባል እንኳን ተከሣሽ በሕጉ አግባብ መብቱን ማስከበር ከሚችል በስተቀር በእራሱ ሥልጣን ውሉን ለማቋረጥ በሕግ የተሰጠው መብት የለም በማለት ሲሆን፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረውን ውል በማቋረጥ ከሌላ ሰው ጋር የተዋዋለ ስለሆነና ሁለተኛውን ውል አቋርጦ ከአመልካች ጋር እንዲዋዋል ሊገደድ የማይችል ከመሆኑም በላይ ቤቱ የንግድ ሥራ የሚሰራበት በመሆኑ አመልካች የተጠሪን ፈቃድ ሣታገኝ በኪራይ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ እንደምትችል በንግድ ሕግ ቁጥር 145/1/ ላይ የተደነገገ ቢሆንም ይህ ድንጋጌ የቤቱ ባለቤት የሆነውን ተጠሪን ከአመልካች ጋር አድርጐት የነበረውን የኪራይ ውል እንዳያቋርጥ የሚያግደው ባለመሆኑ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች እንዲያስረክብና ኪራይም ክፈል መባሉ ተገቢነት የለውም በሚል ነው፡፡

በበኩላችንም ጉዳዩን አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነውም ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ከተጠሪ የተከራዩትን የንግድ ቤት አሳልፈው ለሦስተኛ ወገን በማከራየታቸው ተጠሪ ውሉን በማቋረጥ ከውል ወይንም ከሕግ የመነጨ መብት አለው ወይንስ የለውም? የሚለው በመሆኑ ከዚህ ጭብጥ አኳያ የሰበር አቤቱታው ተመርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የንግድ ሕግ ቁጥር 145/1/ ላይ የንግድ መደብርን የተከራየ ወገን ይህንኑ የንግድ መደብር 3ኛ ወገንን የተከራይ ተከራይ አድርጐ ማስተላለፍ እንደሚችል ይህንንም ሲያደርግ የንግድ መደብሩን ባለቤት ፈቃድ እንደማያስፈልገውና የንግድ መደብሩን ለ3ኛ ወገን አሳልፎ ለማከራየት የባለቤቱ ፈቃድ

ያስፈልጋል የሚል የውል ቃል ቢኖርም እንኳን የዚህ አይነት የውል ቃል/term/ፈራሽና? ዋጋ እንደሌለው እንደዚሁም የማይንቀሣቀስ ንብረትን ለ3ኛ ወገን አሳልፎ ለማከራየት የባለቤቱ ፈቃድ አስፈላጊ እንደሆነ በውል ሊወሰን ይችላል ተብሎ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2959 ላይ የተደነገገው ለንግድ መደብር ኪራይ ተፈጻሚነት እንደሌለው ተደንግጐ እናገኛለን፡፡

ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለውም የንግድ መደብር የተከራየ ሰው የንግድ መደብሩን ለሌላ 3ኛ ወገን አሳልፎ ላለማከራየት ከንግድ መደብሩ ባለቤት ጋር የውል ግዴታ ቢገባም እንኳን የዚህ ዓይነቱ ስምምነት ውጤት እንደሌለው ስለሚቆጠር አሳልፎ ማከራየት እንደሚችልና የንግድ መደብሩ ባለቤት ይህ ተግባር በመፈጸሙ ምክንያት ውሉን ማቋረጥ እንደማይችል ሲሆን ነገር ግን የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይህ ድንጋጌ የቤቱ ባለቤት የሆነውን ወገን ውሉን ከማቋረጥ አያግደውም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ለድንጋጌው የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪ ከአመልካች ጋር ለክርክሩ ምክንያት በሆነው የንግድ ቤት ላይ አድርጐት የነበረውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ ከውልም ሆነ ከሕግ የመነጨ መብት እንደሌለው መገነዝብ የሚቻል በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪና የሥር ተከሣሾች የንግድ ቤቱን ለአመልካች እንዲያስረክቡ አመልካችም ከንግድ ድርጅቱ ያጡትን ኪራይም እንዲከፍሉ በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት ያለው ሆኖ ሳለ ነገር ግን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ከላይ በተመለከተው አኳኋን ይህንኑ ውሣኔ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27048 ሚያዝያ 19 ቀን 1999 ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 15978 ሰኔ 27 ቀን 1998 ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ ፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ ፊርማ የአምስት ዳኞች አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 34586

ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ ያለው ድልነሳው - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- 1. ወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረግ - አልቀረቡም ከተባለበኋላ ቀረቡ

2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር - ነ/ፈጅ ቀረቡ

3. ወረዳ 22 ቀበሌ 04 አስተዳደር - አልቀረበም

4. አቶ ወሰን ፀጋ - ተቋርጧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአንደኛ ተጠሪ ከሳሽነትና ከሁለተ እስከ አራት በተጠቀሱት ተጠሪዎች ተከሳሽነት የነበረውን ክርክር መርምሮ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/358 መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አንደኛ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሁለት እስከ አራት በተጠቀሱት ተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ ቤት መንግሥት ስለ ንግድ ቤቶች መግለጫ ካወጣም በኋላ በስሜ ውል ተዋውዬ ባለሁበት ሁኔታ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ከአራተኛ ተጠሪ ጋር በውል ላይ ውል በማድረግ የንግድ ቤቱን አሳልፈው የሰጡ ስለሆነ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልኝ በማለት ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ከሳሽ ንግድ ቤቶችን አስመልክቶ መንግሥት መመሪያ ካወጣ በኋላ በስማቸው ተከራይተው በይዞታቸውም ሥር አድርገው በንግድ ቤቱ ሲጠቀሙበት የነበረ ስለሆነና ተከሳሾች መመሪያው ከወጣ በኋላ ከከሳሽ ጋር የተደረገው ውል በስህተት እንደተደረገ ከማንሳት ውጭ ውሉ የጸና ሊሆን እንደማይችል ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ ስለሌለ በዚህ ሁኔታ በተከሳሾች የተፈጸመው ድርጊት በሕግ የተፈቀደ መብትን ተከትሎ የተፈጸመ ባለመሆኑ አድራጎቱ ከሁከት ስለሚፈረጅ ባለይዞታ ለሆኑት ለከሳሽ ቤቱ ሊመለስላቸው ይገባል በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካች በወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 የተመዘገበውን የንግድ መደብር የካቲት 16 ቀን 1992 ዓ.ም በንግድ ቤቱ ላይ እዳና እገዳ እንደሌለበት አጣርቼ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ ከሦስተኛ ተከሳሽ /ከአሁን ሦስተኛ ተጠሪ/ ላይ ገዝቼ ሽያጩም ሕጋዊ መሆኑ በቀበሌው አተዳደር በኩል ታምኖበት የኪራይ ውሉ በስሜ ተዛውሮ ኪራይ የምከፍል ከመሆኑም በላይ የንግድ ፈቃድም አውጥቼ በመስራት ላይ እንዳለሁ የንግድ ቤቱን አስቀድሞ በተሰጠ ፍርድ መነሻነት ለከሳሽ ለአሁን አንደኛ ተጠሪ እንዳስረክብ የተገደድኩ ስለሆነ ይሄው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/360(2) መሠረት ይሰረዝልኝ በማለት አመልክተው ፍ/ቤቱም ውሳኔ ከሳሽና ተከሳሾች የነበሩት

በመጥራት ካከራከረ በኋላ በቀድሞው ውሳኔ ክርክር ያስነሳው የንግድ ቤት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስለ ንግድ ቤቶች መግለጫ ከማውጣቱ በፊትም ሆነ በኋላ ከአንደኛ እና ሁለተኛ ተከሳሾች ተከራይተው ይጠቀሙበት እንደነበርና ይዞታቸው እንደሆነ የተረጋገጠ ከመሆኑም ሌላ ከሳሽ መመሪያው ከወጣ በኋላ ከአንደኛ እና ሁለተኛ ተከሳሾች ጋር ያደረጉት ውል ፈራሽ ነው ሳይባል ከሦስተኛ ተከሳሽ ጋር ያደረጉት ውል መብትና ግዴታን ሊያቋቁም እንደማይችል ስለተወሰነና ከዚህም ውሳኔ ሦስተኛ ተከሳሽ አንዳችም መብት እንደሌላቸው መገንዘብ ስለሚቻል የመቃወም አመልካችም የንግድ ቤቱን ገዛሁ የሚሉት መብት ከሌላቸው ከሦስተኛ ተከሳሽ ላይ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ የቀድሞው ውሳኔ ይሰረዝልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢነት የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ይሄው ውሳኔም የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ጉድለት የለውም ተብሎ እስከ አዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ እንደፀና ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ለዚህ ችሎት የቀረበውም የሰበር አቤቱታ ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ በየደረጃው የሚገኙ የሥር ፍ/ቤቶች ሳይቀበሉ የቀሩበት ምክንያት ተጠሪዎች ባሉበት ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሁፍ አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የዚህን ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ፡፡

አመልካች ባቀረቡት መቃወሚያ መነሻነት አስቀድሞ የተሰጠው ፍርድ ሊሰረዝ ይገባል ወይንስ አይገባም? የሚለው ነው፡፡ ከዚሁ ጭብጥ አኳያም የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አንድ ፍርድ በአንድ ፍ/ቤት ከተሰጠ በኋላ ይሄው ፍርድ በዚያው ፍ/ቤት በድጋሚ ከሚታይባቸው ሥርዓቶች መካከል አንዱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/358 መሠረት መቃወሚያ በሚቀርብበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረትም በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና እንደዚሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማንኛም ሰው ተካፋይ ባልሆነበት የተሰጠው ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያውን ማቅረብ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበትንና ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ ቤት አመልካች  በስማቸው የንግድ ፈቃድ አውጥተው ሲሰሩበት ከነበረው የሥር ሦስተኛ ተከሳሽ የአሁን አራተኛ ተጠሪ ላይ የካቲት 16 ቀን 1992 ዓ.ም በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ ስለመግዛታቸውና በኋላም የኪራይ ውሉን በስማቸው በማዛወርና የንግድ ፈቃድም በስማቸው በማውጣት የንግድ ሥራ ሲሰሩበት እንደነበር ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ የቀድሞው ውሳኔም መብቱን የነካ ስለሆነ ሊሰረዝ /Set aside/ ይገባል በማለት መቃወሚያ ያቀረቡትም ይህንኑ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ጉዳዩን በየደረጃው የተመለከቱት የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካች መቃወሚያ ሳይቀበሉት የቀሩት ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው አንደኛ ተጠሪ ከሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የኪራይ ውል ቀሪ ባልሆነበት ሁኔታ ሌላ ውል ከአራተኛ ተጠሪ ጋር መደረጉ ተገቢነት የሌለውና ውጤትም ሊኖረው ስለማይችል በዚሁ ውጤት በሌላው ውል ላይ ተመስርቶ በአራተኛ ተጠሪና በመልካች መካከል የተቋቋመው የንግድ መደብር ሽያጭ ውል የመብትም ሆነ የግዴታ ምንጭ ስለማይሆን መቃወሚያው ተገቢነት የለውም በማለት ነው፡፡

ይሁንና አመልካች ይህንኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የንግድ መደብር ከአራተኛ ተጠሪ ሲገዙ ከላይ እንደተጠቀሰው አራተኛ ተጠሪ ንግድ መደብሩን በስማቸው ባደረጉት ውል ይዘውት እንደሚገኙ እንደዚሁም በስማቸው የንግድ ፈቃድ በማውጣት እየሰሩ እንደሚገኙ በማረጋገጥ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ የሽያጩን ውል ከአራትኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉ እንደመሆኑ መጠን ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች አስቀድሞ ከአራተኛ ተጠሪ ጋር ያደጉት የኪራይ ውል ተገቢነት የሌለው ነው ቢባል እንኳን አመልካች ውሉን በቅን ልቦና ያደረጉት በመሆኑ ሕጉ ለቅን ልቦህና ተዋዋዩች ከሰጠው ጥበቃ አኳያ ጉዳዩ የማይታይበት ምክንያት አይኖርም በዚህም መሠረት የቅን ልቦና ባለይዞታነትን አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ባለሀብት ለመሆን በቅን ልቦና ዋጋ ሠጥቶ ውል የተዋዋለ ሰው የተባለውን ተንቀሳቃሽ ነገር  በእጁ ሲያደርግ በቅን ልቦናው ምክንያት የዚህ ንብረት ባለሀብት እንደሚሆን ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የንግድ መደብር ግዙፍነት ባይኖርም ነገር ግን ግዙፍነት የሌለው ተንቀሳቃሽ ንብረት /Incorporeal

movable/ እንደሆነ የንግድ ሕግ ቁጥር 124 ላይ ስለተመለከተ ስለቅን ልቦና ባለይዞታነት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/1161 ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነው፡፡

አመልካች ይህንኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የንግድ መደብር ይዘው የሚገኙት በቅንልቦና በተደረገ ውል መነሻነት ነው ከተባለ አስቀድሞ አንደኛ ተጠሪ ከሁለት እስከ አራት በተጠቀሱት ተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት የንግድ መደብሩን ለከሳሽ ለአንደኛ ተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ አመልካች በክርክሩ ተካፋይ ባልሆኑበት መብታቸውን የነካ ውሳኔ አንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በመሆኑም አመልካች የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/358 በሚፈቅደው መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/1161 አኳያ ታይቶ አስቀድሞ የተሰጠውና የአመልካችን መብት የነካው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/360(2) መሠረት መሰረዝ ሲገባው ከአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እስከ አዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ አቤቱታው ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመቁ 2901/91 ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ.ቁ 414/93 እንደዚሁም ሰበር ሰሚው ችሎት በመ/ቁ 01424 በ20/3/2000 ዓ.ም  የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348 (1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 2901/91 የሰጠው ውሳኔ አመልካች የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆኑ መብታቸው የነካ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/360(2) መሠረት ተሰርዟል፡፡
3. አመልካች በወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ መደብር ከአራተኛ ተጠሪ ላይ የገዙት በቅንልቦና ስለሆነ ሊያስረክቡ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

የሰ/መ/ቁ. 43315

ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ብራንድ ኒው የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ማዕከል ኃ/የተ/የግ/ማኀበር ጠበቃ አቶ ቸርነት ወርዶፋ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- አቶ መስፍን ታደሰ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሆኖ ተጠሪ ከሳሽ ሲሆኑ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ የክሱ ምክንያት መጋቢት 7 ቀን 2000 ዓ.ም. የሚመነዘር ቼክ ቁጥር ኤኤ 187877 የሆነ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ/ የያዘ ቼክ ሰጥተውኝ ለክፍያ ባንክ ስቀርብ ሂሣቡ ታግዷል በሚል ምክንያት ቼኩ ሳይከፈል ተመልሷል፡፡ ስለዚህ በቼኩ የተመለከተውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፈል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 286 መሠረት በአጭር ሥነ-ሥርዓት ታይቶ እንዲወሰን በማለት ክስ ቀረበ፡፡

አመልካችም ቼኩ የተሠጠው የካቲት 13 ቀን 2000 ዓ.ም. ለተደረገው እስከቫተር ሽያጭ ውል ስምምነት መነሻ ሆኖ ከሽያጩ ገንዘብ ውስጥ 200,000 ብር በዕለቱ ተከፍሎ ቀሪው 100,000 ብር መጋቢት 12 ቀን 2000 የሚመነዘር ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቼክ መስጠታቸውን በማስመልከት ለመከላከል እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡

ግራ ቀኙን ያከራከረው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 123416 በሆነው በ12/2/2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ለመከላከል እንዲፈቀድ የቀረበለትን ጥያቄ ባለመቀበል ክስ የቀረበበትን በቼኩ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ/ቁጥር 74146 በ26/5/2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎች ውሣኔውን አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ፍ/ቤትም አመልካች የግል ግንኙነት ያላቸው መሆኑን በመጥቀስ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ጥያቄ አቅርቦ የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ለሰበር እንዲቀርብ ታዞ መጋቢት 9 ቀን 2001 ዓ.ም. የግራ ቀኙን ክርክር አድምጧል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ በአጭሩ የተመዘገበው ሲሆን እኛም ክርክራቸውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 284 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት በአጭር ሁኔታ በሚወሰኑ ክርክሮች ላይ ስለሚፈፀም ሥነ-ሥርዓት በሕጉ የተመለከቱ ሥርዓቶችን መሠረት በማድረግ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመሠረቱ በአጭር ሥነ-ሥርዓት ዳኝነት ታይቶ እንዲወሰን ክስ የሚቀርብበት ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 285/1/ እንደተመለከተው ከሕጉ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ቁጥር 2 መሠረት ተከሣሽ የሆነው ሰው መጥሪያ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በአሥር ቀናት ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ክሱን ለመከላከል እንዲፈቀድለት ፍ/ቤቱን ፈቃድ እንዲጠይቅ መደረግ እንዳለበት በሕጉ መሠረት ቼኩ የተሠጠበት ምክንያት የኤክስካቬተር ሽያጭ ውል ምክንያት እንደሆነ በመጥቀስ ለመከላከል እንዲፈቀድለት በቃለ መሐላ የጠየቀ መሆኑን ከክርክሩ መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡ የተጠሪ ዋና ክርክር በቼኩ

ላይ ሐተታ ወይም ገደብ የለበትም በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ በሽያጩ ውል ላይ የቼክ ቁጥር ተጠቅሶ ውል የተገባ መሆኑን በመግለጽ የሚከራከር ሲሆን በዚህ ፍ/ቤት የቃል ክርክር ጊዜ ተጠሪም ይህ የውል ግንኙነት በመካከላቸው እንዳላቸው አልካዱም፡፡ በመከላከያ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ላይም ይህ ግንኙነት መኖሩ እስከተገለፀ ድረስ ምንም እንኳን ቼክ እንደ ገንዘብ ለተለያዩ ሰዎች በቀላሉ ሊተላለፍ የሚችል ባሕርይ ያለው የገንዘብ ሰነድ በመሆኑ ቼክ አከፋፈል ላይ ማንኛውም መቃወሚያ ሊቀርብበት እንደማይችል በንግድ ሕጉ የተደነገገ ሲሆን ሕጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር የቼክ ክፍያ በማናቸውም ምክንያት ሊቆምና ሊታገድ የማይችል መሆኑ አካከራካሪ አይደለም፡፡ ነገር ግን በባለ ጉዳዮቹ መካከል ግልጽ የሆኑ ሁኔታዎች ወይም ግንኙነቶች በተፈጠሩ ጊዜ ብቻ ይህን መቃወሚያ ለማድረግ እንደሚቻል በን/ሕ/ቁ. 717/1/ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ይህን መሠረት በማድረግ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ያልተቀበለው የቼክ ክርክር በመሆኑ ብቻ የቼክን ባህርይ መሠረት ለማድረግ ነው፡፡ ሆኖም በዚህ የፈቃድ ጥያቄ ደረጃ ላይ የቼክ ባሕርይ ሳይሆን መታየት ያለበት አመልካች ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበው ምክንያት ፈቃድ የሚያሰጥ መሆን አለመሆኑን ነው፡፡ ሌላ የፍሬ ነገር ክርክር ከፈቃድ በኋላ የሚታይ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የሽያጭ ውል ግንኙነት መሠረት በማድረግ ለመከላከል እንዲፈቀድ ፍ/ቤቱን ለመጠየቅ ሕጋዊ ምክንያት አለው፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ በአጭር ሥነ-ሥርዓት እንዲታይ የሚቀርቡ ክሶች አመራር ሥርዓትን ሳይሆን የተከተለው የቼክ ባሕርይን መሠረት በማድረግ ውሣኔ መደምደሚያ ላይ መድረሱ አግባብ ሆኖ አላገኘንም፡፡ ምክንያቱም ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት በፍ/ቤቱ አግኝቶ የተጠየቀውን ገንዘብ ላለመክፈል በቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑ የሚታወቀው ፍ/ቤቱ ከአጭር ሥነ-ሥርዓት ወደ መደበኛ የክርክር ሥነ-ሥርዓት ውስጥ በመግባት ግራ ቀኙን በአግባቡ በማስረጃ ካከራከረ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 123416 ጥቅምት 12 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 74146 ጥር 26 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ያለውን መከላከያና ማስረጃ አቅርቦ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በመደበኛ የክርክር ሥርዓት አከራክሮና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341 መሠረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡን ዘግተናል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

# የአእምሯዊ ንብረት

የሰ/መ/ቁ. 42253

ሐምሌ 8 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** መምህር ሙሉ ኃይለሥላሴ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ዘመናዊ ማተሚያ ቤት ጠበቃ አቶ ዓለሙ ወ/አረጋይ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው መቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆኖ አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ ክሱም ተጠሪ መጽሐፍት እንዲያትምልኝ ውል ፈጽሜ በድርጅቱ ሰራተኛ ተሠርቆ በተሸጡት 9 መጽሐፍት ምክንያት ኪሣራ ደርሶብኛልና በአዋጅ ቁጥር 410/96 የተመለከተውን የሞራል ካሣና ሳይሸጡ የቀሩ መጽሐፍት ዋጋ በድምሩ 260,000 /ሁለት መቶ ስድሳ ሺ ብር/ እንዲከፍለኝ የሚል ሲሆን ተጠሪም በሰጠው መልስ ተሰርቋል የተባለው 7 መጽሐፍት እንጂ ሌላውን ለመክፈል አንገደድም ሰረቀ የተባለው ሰው ጣልቃ እንዲገባ ይታዘዝልን ስርቆት ግላዊ ባህርይ በመሆኑ ካሣውን ሊከፍል የሚገባው የሰረቀው ሰው ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ግራ ቀኙን ያከራከረው ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱንና ማስረጃውን በማገናዘብ ተሰርቆ ተሸጠ የተባለውን የ9 መጽሐፍት እያንዳንዱን በ20 ብር ግምትና በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34(4) የተመለከተውን የሞራል ካሣ ጭምር 100,180,00 /አንድ መቶ ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ብር/ ለአመልካች ተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ውሣኔውን በአብላጫ ድምፅ በማጽናቱ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ችሎቱም ተጠሪ ድርጊቱን ሊያውቅ የሚችልበት በቂ ምክንያት በሌለበት የሞራል ካሣ 100,000 /መቶ ሺህ ብር/ እንዲከፍል መወሰኑ ስህተት ነው፤ ተሰርቋል የተባለውን የ7 መጽሐፍት ብቻ መሆኑን በማረጋገጥ የ7 መፅሐፍት ዋጋ 140,00 /አንድ መቶ አርባ ብር/ እንዲከፍል በማሻሻል ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

አመልካች ታህሣሥ 4 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው ቅሬታ፡-

ተጠሪው ስርቆቱን ቢያውቅም ባያውቅም በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34/(4) የተመለከተውን አነስተኛ የሞራል ካሣ 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ የሚያስቀር አይደለም በማለት ውሣኔው እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡

ይህ ችሎትም የውሳኔውን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ታዞ መጋቢት 2 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ግራ ቀኙ ቀርበው ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡

ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር በሕግ ረገድ እንደሚከተለው ተመልክቶታል፡፡

የተከራካሪዎቹ ግንኙነት ተጠሪ 5,000(አምስት ሺህ) መጽሐፍት አትሞ ማስረከብ ሲሆን አመልካች ደግሞ ቀሪውን በውል የተመለከተውን ገንዘብ መክፈል ነው፡፡ ከዚህ ግንኙነት አንፃር የግራ ቀኙ ክርክር ሊታይ የሚገባው በውል ነው ወይንስ ከውል ውጪ ነው? የሚለውን ስንመለከተው፡- አንድ ጉዳይ ከውል ውጪ ነው ሊባል የሚችለው አንድ ሰው በራሱ በኩል ምንም የገባው ግዴታ ሳይኖር በራሱ ጥፋት ላደረሰው ጉዳት ኣላፊ እንደሚሆን ከውል ውጪ የሆኑ የኃላፊነት ምንጮችን ከሚደነግገው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2027 መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ ወገኖች ግልጽ

ስምምነት አድርገው የውል ግዴታ ገብተዋል፡፡ ይኸው የውል ግዴታ ከመፈፀሙ በፊት በስምምነቱ ውስጥ የተካተተው መጽሐፍ በተጠሪ ድርጅት ሠራተኛ ተሰርቆ ገበያ ላይ በመዋሉ ምክንያት ግዴታው በተባለው ሁኔታና ጊዜ አለመፈፀም ምክንያት ሆነ ከሚባል በቀር ጉዳዩን የውል ውጪ (extra contractual) አያደርገውም፤ ይልቁንም ውሉ ከሚመለከተው የሕትመት ሥራ አንፃር ውሉ ሳይፈፀም የተወሰኑ መፃሕፍት በሕትመት ሰራተኛ መሠረቅ የውል መጣስ (breach of contract) የነበረ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ የውል መጣስ ወይም ውሉ በታሰበው አኳኋን አለመፈፀም ጉዳይ የሚታየው በውል ሕግ እንጂ ከውል ውጪ የሚሆንበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ይህን ጉዳይ በየደረጃው ያዩ ፍ/ቤቶች ግዴታውን ከውል የመነጨ ሆኖ እያለ ውሉም ባልተካደበት በድርጅቱ ሰራተኛ በመሰረቁ ብቻ ከውል ውጪ ኃላፊነት ተደርጐ መታየቱ ስህተት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩ ከውል ውጪ መሆኑን ተቀብሎ ለውሣኔው መሠረት ያደረገው በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34(5) መሠረት ተጠሪው ድርጊቱን ያላወቀ ከሆነ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት በቂ ምክንያት የሌለው ከሆነ የሚለውን ትርጉም መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 34(5) የተጠቀሰው " - - ያላወቀ ከሆነ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት በቂ ምክንያት የሌለው ከሆነ - - -" የሚለው የሕጉ ትርጉም መጽሐፍን እንዳለ መሰረቅን የሚመለከት ሳይሆን የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 410/96 መሠረት ጥበቃ የተደረጉ የአዕምሮ መብቶች ሲጣሱ ማለትም ከመፃሐፉ ውስጥ እንደ ቅጅ፣ ማባዛትና ሌሎች ተመሣሣይ ድርጊቶችን ሳያውቅ የጥሰት ተግባር በተፈፀመ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆን እንጂ አሁን በተያዘው ጉዳይ ዓይነት ማተሚያ ቤቱ ሚስጥራዊነቱን ጠብቆ እንዲታተም በተገባው ውል ስምምነት መሠረት አትሞ በመስጠት ሂደት ላይ በማተሚያ ቤቱ ሰራተኛ መጽሐፍት ተራ በሆነ ስርቆት ወጥቶ ቢሸጥ ማተሚያ ቤቱ ሊያውቅ ወይም ማወቅ የሚችልበት በቂ ምክንያት አለመኖሩን የሚመለከት አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለሕጉ የሰጠው ትርጉም የተሳሳተ ነው፡፡ ተጠሪ ስርቆት ግላዊ ባርይ በመሆኑ መጽሐፍትን የሰረቀው ሰው ካሣውን ሊከፍል ይገባል የሚለውን ክርክር በተመለከተ ሰረቀ የተባለው ሰው ግንኙነቱ በአሰሪነት ከተጠሪ ጋር ነው እንጂ ከአመልካች ጋር አይደለም፡፡ የውል ግንኙነቱ ከተጠሪ ጋር በመሆኑ ይህ ተዋዋይ ወገን እንደውሉ ግዴታውን ያልፈፀመበትን በቂ ምክንያት ካላስረዳና ይህም ምክንያት ከአቅም በላይ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የውሉ አለመፈፀም ከሚያመጣው ኃላፊነት ሊድን እንደማይችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1791(2) ተመልክቷል፡፡ መጽሐፉን የሰረቀው ከውጪ የመጣ ዘራፊ አይደለም፡፡ የድርጅቱ ሰራተኛ በሆኑ የመቆጣጠር ኃላፊነት የተጠሪ ሲሆን ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1792(1) መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይችሉ ኃይል ነው የሚያሰኝ አይደለም፡፡ እንዲያውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1792(2) መሠረት በአዕምሮ ግምት መጽሐፉ ሊሰረቅና ወይም ተደብቆ ሊወጣ ይችላል በሚል ተጠሪው ቀደም ብሎ ሊያስብበት የሚችል ከመሆኑ አንፃር ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ነው ተብሎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ይልቁንም በውሉ አለመፈፀም ምክንያት አመልካች የደረሰበትን የጉዳት ኪሣራ እንዲጠይቀው የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1771(1) መብት የሚሰጠው ሲሆን ተጠሪ ምንም ጥፋት ባያደርግ እንኳ በውሉ መሠረት ባለመፈፀሙ ምክንያት ብቻ የጉዳት ኪሣራውን መክፈል እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.791(1) ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ የጉዳት ኪሣራ ከውልም ሆነ ከውል ውጪ ሊከሰት የሚችል ሲሆን ቁሣዊ ጉዳት ብቻ ሣይሆን የህሊና ወይም የሞራል ጉዳትንም የሚጨምር ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1790(2)እና 2090 — 2123 ከተመለከቱ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የመብቱ ባለቤት ከሆነው ከአመልካች ፈቃድ ውጪ የአዕምሮ ሃብቱ የሆነው መጽሐፍት አመልካች ከመረከባቸው በፊት መሠረታዊ የውል ዓላማ ተጥሶ በውል ተቀባይ ድርጅት ሰራተኛ መጽሐፍት ገበያ ላይ መዋላቸው በፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ በሕጉ የመብቱ ባለቤት መብቶች ናቸው የተባሉት ኢኮኖሚያዊና የሞራል መብቶች ሲሆኑ በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 7 የተመለከቱ ኢኮኖሚያዊ መብቶች አንዱ ተጥሶ በተገኘ ጊዜ የሞራል ጉዳት ጥሰት ይኖራል ማለት ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 7 የተመለከቱ ኢኮናሚያዊ መብቶች እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 9 እስከ 19 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሥራ አመንጪ ወይም የአንድ ሥራ ባለቤት የሚከተሉትን ለመፈፀም ወይም ሌላ ሰው እንዲፈፅማቸው ለመፍቀድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል፡፡
   ሀ/ ሥራን የማባዛት፣

   ለ/ ሥራን የመተርጐም፣

   ሐ/ ሥራን የማመሳሰል፣ የማቀናበር ወይም ወደ ሌላ አይነት የመቀየር፣

   መ/ በሽያጭ ወይም በኪራይ ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን የማከፋፈል፣

   ሠ/ ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን ከውጭ ሃገር የማስገባት፣

ረ/ ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን ለሕዝብ የማሣየት፣

ሰ/ ሥራን በይፋ የመከወን፣

ሸ/ ሥራን ብሮድካስት የማድረግ፣

ቀ/ ሥራን በሌላ መንገድ የማሰራጨት፣

እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በፊደል "ረ" የተመለከተው ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጅውን ለህዝብ ማሳየት የሚለው ድንጋጌ በተጠሪ ተጥሷል፡፡ ይኸውም መጸሐፉ ከአመልካቹ ፈቃድ ውጪ ገበያ ላይ ውሎ በሕዝብ መነበቡ ነው፡፡ አንድ ፊልም ከባለቤቱ ፈቃድ ውጪ ኦርጅናሉ ወይም ቅጅው ለሕዝብ ቢታይ የአመንጪው ኢኮኖሚያዊ መብቱ እንደሚጣስ ሁሉ አንድ መጽሐፍም እንዲሁ ከአመልካቹ ፈቃድ ውጪ ገበያ ላይ ውሎ ቢነበብ ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጅውን ለሕዝብ ማሳየት (public display of original or copies of the work) የሚለው በሕጉ የተመለከተው የአመልካች መብት ተጥሷል ማለት ነው፡፡ ይህ መብት ተጥሶ የሞራል ጉዳት በደረሰ ጊዜ የካሣው መጠን በአዋጁ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34(4) መሠረት ከ100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ የማያንስ የገንዘብ ካሣ ሊከፍል እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት በአመልካች ላይ የደረሰውን የህሊና ጉዳት ሞራል ካሣ ተጠሪው በተጠቀሰው አዋጅ መሠረት 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

የከፍተኛ ፍ/ቤትና የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከላይ እንደተጠቀሰው የግራ ቀኙ ግንኙነት ውል ሆኖ ሳለ ሠራተኛ መጽሐፍ በመሥረቁ ብቻ ከውል ውጪ አድርገው ትርጉም በመስጠት የተመለከቱት በአግባቡ ባይሆንም በውጤት ረገድ ግን በአግባቡ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በአጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ድርጊቱን ያላወቀ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት በቂ ምክንያት የሌለው ከሆነ የሚለውን ከሕጉ መንፈስ ውጪ የሆነውን ትርጉም መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሣኔ ከፍ ሲል ከተመለከቱት ምክንያቶች አንፃር መሠረታዊ የሕግ ትርጉም ስህተት የተፈፀመበት ውሣኔ ነው ብለናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. ከትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 25/99 በ11/3/2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ በውጤት ረገድ በአግባቡ ነው ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት በማፅናት አመልካች የሞራል ካሳ 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ እና የሰባት መፃሕፍት ዋጋ ብር 140 /አንድ መቶ አርባ ብር/ በድምሩ 100,140 /አንድ መቶ ሺ አንድ መቶ አርባ ብር/ ይከፈለው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተናል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

# ልዩ ልዩ

የሰ/መ/ቁ. 21214

ህዳር 4 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - አልቀረቡም

**ተጠሪዎች፡-** 1/ አቶ ለማ ኩማ - አልቀረቡም

2/ አቶ አዲሱ ታመነ - አልቀረቡም

3/ አቶ ሺግዛው አስራት - አልቀረቡም

ጉዳዩን ከመረመርን በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የሃረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 00627 ሐምሌ 14/1997 ዓ.ም የሰጠውን ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበትና ይታረምልኝ በሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በሐረሪ ክልል የአሰሪና ሰራተኛ ወሣኝ ቦርድ ሲሆን በዚሁ አካል በተደረገ ክርክር የአሁኑ ተጠሪዎች በከሣሽነት የአሁኑ አመልካች ደግሞ በተከሣሽነት እንዲሁም በሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁኑ አመልካች ይግባኝ ባይ የአሁኑ ተጠሪዎች ደግሞ መልስ ሰጭዎች ነበሩ፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ስር ከሣሾች የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች የካቲት 11/1997 ዓ.ም በተፃፈ ወደ ቦርድ ያቀረቡት ክስ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም በተከሣሽ ድርጅት /የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ሃረር ዲስትሪክት/ ውስጥ በቴክኒክ ሠራተኛነት እየሰሩ ያሉ መሆናቸውን ገልፀው ካላቸው አገልግሎትና የትምህርት ደረጃ ጋር በማይመጣጠን ደረጃ 03 ተመድበው እየሰሩ እንደሆነና ተከሣሽ በሚመጥናቸው / በሚገባቸው /ደረጃ/ ግሬድ 06 እንዲመድባቸው ቢጠይቁትም ለመመደብ ፍቃደኛ ባለመሆኑ በቦርድ ውሣኔ እንዲስተካከልላቸው የሚጠይቅ ነው፡፡

ስር ተከሣሹም ከላይ ለቀረበበት ክስ የካቲት 29/1997 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ሰጥቷል፤ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጭብጥ አግባብነት ስለሌለው ዝርዝሩን ማስቀመጥ ሣያስፈልግ ታልፏል፤ ይሁን እንጂ መሠረታዊ ይዘቱ ክርክሩ በአስማሚ አካል ሣይታይ ቦርዱ የማየት ስልጣን እንደሌለው የሚገልጽ ነው፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያከራከረው ቦርድ ሰኔ 03/1997 ዓ.ም ውሣኔ የሰጠ ሲሆን ስር ተከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች በዚሁ የቦርድ ውሣኔ ቅሬታ በማሣደር ወደ ሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍርድ ቤቱ በመ.ቁ. 00627 ሐምሌ 14/1997 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ በአዋጅ ቁ. 377/1996 ዓንቀጽ 139/1/ለ/ መሠረት የተጠቀሰው ቦርድ የሰጡውን ውሣኔ ተከትሎ ይግባኙን የማየት ስልጣን ለክልል ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ማለትም ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንጂ ስልጣኑ የሱ እንዳልሆነ በመግለጽ የቀረበለትን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9/2/ መሠረት ውድቅ አድርጓል፡፡

የአሁኑ አመልካችም ነሐሴ 17/1997 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም በሃረሪ ክልል የአሰሪና ሰራተኛ ወሣኝ ቦርድ በቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ በአስማሚ አካል ሣይታይ ቦርዱ ጉዳዩን ተቀብሎ በቀጥታ ማከራከር እንደሌለበትና ጉዳዩም በይርጋ ቀሪ እንደሆነ ገልፆ ተከራክሮ እያለ ቦርዱ ሕጉን ሣያገናዝብ በመወሰኑ ተከትሎ የቀረበለትን ይግባኝ የሃረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስልጣኔ አይደለም በማለት ይግባኙን መሠረዝ የለበትም፤ አዋጅ ቁ. 377/1996 ዓንቀጽ 154 እንዲሁም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት ዓንቀጽ 80 መሠረት በማድረግ ሲታይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን ይግባኝ ማስተናገድ የነበረበት ሆኖ እያለ ስልጣኔ አይደለም ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነው፤ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ቢታዘዙም ሊቀርቡ ባለመቻላቸው ጉዳዩ በሌሉበት እየተካሄደ ነው፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ እየተገለፀ እንደመጣው ሆኖ ይህ ፍርድ ቤትም የሃረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበለትን ይግባኝ የማየት ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚል ጭብጥ በመመሥረት ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ ይህ የሥራ ክርክር የተጀመረው በሃረሪ ክልል የአሰሪና ሰራተኛ ወሣኝ ቦርድ ሲሆን ይህ አካል ለቀረበለት ክርክር የመጨረሻ እልባት/ ውሣኔ/ ከሰጠ በኂላ የይግባኝ አቀራረቡ ሥነ-ሥርዓት ምን እንደሚመስል በአዋጅ ቁ. 377/1996 ዓንቀጽ 154/1/ በግልጽ እንደተመለከተው በሕግ በኩል ውሣኔው ተዛብቷል የሚል ወገን ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት ይግባኝ የማቅረብ መብት እንዳለው ነው፤ ቦርድ ያረጋገጣቸው የፍሬ ነገር ክርክሮች በተመለተ ግን የመጨረሻና ክርክር የማይነሣባቸው ነጥቦች በመሆናቸው በአዋጁ ዓንቀጽ 153 ተመልክቷል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኑ ወቅት መዋቅሩ በእያንዳንዱ ክልል ያልተዘረጋና በዚሁ የፍርድ ቤት የስልጣን እርከን የሚጠቃለሉ ጉዳዮች በክልሎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ በስልጣን ደረጃ ተመሣሣይ የሆነው የእያንዳንዱ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ወክሎ /ተክቶ/ ክርክሮችን እያስተናገዱ የሚገኙበት ነው፤ ከዚህ አኳያም የሃረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡለትን ይግባኝ በአዋጅ ቁ.377/1996 ዓንቀጽ 140 እና 154 መሠረት ተቀብሎ ማስተናገድ ሲገባው የዓንቀጽ 139/1/ለ/ ይዘት በመውሰድ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የሃረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 00627 ሐምሌ 14/1997 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ ተሽሯል፡፡

2/ በተከራካሪ ወገኖች መካከል የተደረገው ክርክር ከሃረሪ ክልል አሰሪና ሠራተኛ ወሣኝ ቦርድ የጀመረ በመሆኑ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁ. 377/1996 ዓንቀጽ 140 እና 154/1/ መሠረት ተቀብሎ ይግባኙን የማየት ስልጣን አለው፤ ስለሆነም ይግባኙን ተቀብሎ አከራክሮ እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሠረት ተመልሶለታል፤ ይፃፍ፡፡

3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ በት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊረማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 35391

ኅዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ፈርተውሐል ወ/ጊዮርጊስ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አንበሣ ጫማ አ/ማ - ጠበቃ መኮንን ኪዳኔ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጡረታ አዋጅን የተመለከተውን የጡረታ መዋጮ ክፍያን በወቅቱ ገቢ ያለማድረግን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ጥቅምት 24 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ የአሁኑ ተጠሪ የጥር ወር 1992 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ብር 39,974.35(ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አራት ብር ከሰላሣ አምስት ሣንቲም) ለአመልካች ድርጅት ገቢ ያደረገው ከሦስት ዓመታት በኋላ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም መሆኑን በመግለጽ ለዘገዬበት 2%(ሁለት በመቶ) ተጨማሪ ክፍያ የመክፈል ህጋዊ ግዴታ ያለበት በመሆኑ የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 ስራ ላይ ከዋለበት ከሰኔ 01 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ድረስ ብር 41,573.32(አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰባ ሦስት ብር ከሠላሣ ሁለት ሣንቲም)፣ ከሐምሌ 01 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ብር 8,474.56(ስምንት ሺህ አራት መቶ ሰባ አራት ብር ከሃምሣ ስድስት ሣንቲም) በድምሩ ብር 50,047.88 (አምሣ ሺህ አርባ ሰባት ብር ከሰማኒያ ስምንት ሣንቲም) ከነ ህጋዊ ወለድ እና በቂ ወጪና ኪሣራ ጋር ተጠሪ እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሣሽነቱ ቀርቦ አዋጁ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ነው፣የክፍያ ጥያቄውም ሁለት ዓመት ያለፈበት በመሆኑ እንደተከፈለ የሚቆጠር ስለመሆኑ የሚሉትን ነጥቦችን በመቃወሚያነት፣ለአመልካች በአዋጅ የተሰጠው ስልጣን ገቢ ባልሆነው የመዋጮ ገንዘብ ላይ ብቻ በመሆኑ እና ተከሳሽም የተጠየቀውን እዳ ስለከፈለ ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ ጥያቄ መቅረቡ ከአዋጁ ዓላማ ውጪ መሆኑን የተጠየቀው የጡረታ መዋጮ ተጨማሪ ክፍያ ይመለከተዋል ቢባልም ስሌቱ ተገቢነት የሌለውና በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በፍሬ ነገር መከራከሪያ ነጥብነት በማንሣት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የተጠሪን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን በመመርመር አመልካች የሚጠይቀው መብት በጥር ወር 1992 ዓ.ም እንደመሆኑ መጠን ይህ በ1998 ዓ.ም የተከፈለው እንኳን ቢሆን ከአዋጁ በፊት የተገኘው መብት በአዋጁ መሰረት ሊገዛ ስለማይችል አዋጁ ወደ ኋላ ተመልሶ ተፈፃሚ ሊሆንበት የማይችል ነው በሚል ምክንያት የአመልካችን ክስ ወድቅ አድርጐ ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፈጅ ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የ1992 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ገቢ የተደረገው ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም መሆኑና ክፍያ የተጠየቀውም አዋጁ ስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ

ጀምሮ እንጅ ወደ ኋላ አለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ ሕጉ ወደ ኋላ ሄዶ አይሰራም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባል በመባሉ ተጠሪ ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡ በመልሱ ላይም የአመልካች ጥያቄ የህግ ድጋፍ የሌለው ስለመሆኑ ያሣያሉ ያላቸውን መከራከሪያ ነጥቦች በማንሣት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩሉ ሰኔ 16 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 7/3/ መሰረት የጡረታ መዋጮ ለዘገየበት 2%(ሁለት በመቶ) ተጨማሪ ክፍያ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ድርጅት የጥር ወር 1992 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ብር 39,974.35(ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አራት ብር ከሰላሣ አምስት ሣንቲም) ለአመልካች ድርጅት ገቢ ያደረገው ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው የአዋጅ ቁጥር 345/95 ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም፣ይሰራል ከተባለም የሁለት ዓመት ጊዜ ያለፈ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/ሠ/ መሰረት እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው፣ስሌቱም የተሣሣተ ነው የሚሉትን ነጥቦችን በማንሣት ነው፡፡ እኛም እነኚህን የመከራከሪያ ነጥቦች ከህጉ ጋር አገናዝበናል፡፡

በዚህ መሰረት የአመልካች ድርጅት ዳኝነት የጠየቀበት መብት የበሰለው በጥር ወር 1992 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ በዚህ ወቅት በተጠሪ ዓይነት አካላት ተፈፃሚነት የነበረው ሕግ የመንግስት የሆኑ ድርጅቶች ሰራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 49/1967 ሲሆን በዚህ አዋጅ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ተጨማሪ ክፍያ የሚከፈልበት ስለመሆኑ የሚያመላክት ድንጋጌ አልነበረም፡፡ ይህንኑ አዋጅ የሻረው አዋጅ ቁጥር 345/1995 ዓ.ም በአንፃሩ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ የ2% /ሁለት በመቶ/ ተጨማሪ ክፍያ እንደሚከፈልበት በአንቀጽ 7/3/ ስር ደንግጓል፡፡ ይህ አዋጅ ስራ ላይ የዋለው ከሰኔ 01 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን የመሸጋገሪያ ድንጋጌም ይዟል፡፡ የአዋጁ መሸጋገሪያ ድንጋጌ አንቀጽ 52/1/ የሚያሣየውም አዋጁ ከመጽናቱ በፊት ለተፈጠሩ ህጋዊ ሁኔታዎች /legal situations/ ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩ ህጐችና መመሪያዎች ተፈፃሚነት ያላቸው ስለመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ የድንጋጌ መንፈስ በግልጽ መገንዘብ ከሚቻለው የአዋጅ ቁጥር 345/1995 ዓ.ም ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑን ነው፡፡ አዋጁ ተፈፃሚነቱ ከሰኔ 01 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑ በአንቀጽ 56 ስርም በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ የአዋጁ አቀራረጽ መረዳት የሚቻለው መብቶቹ በነባር ህጐችና መመሪያዎች የተፈጠሩ ከሆነ የሚፈፀሙትም በነባሮቹ ህጐችና መመሪያዎች መሆኑን ሲሆን አሁን በተያዘው ጉዳይ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ የመጠየቅ መብት በነባሮቹ ህጐች የተፈጠረ በአዲሱ አዋጅም ቀሪ ስለመሆኑ ያልተመለከተ ሁኖ በዚህ ውዝፍ መዋጮ ተጨማሪ ክፍያ የማስከፈል መብት የተፈጠረው በአዲሱ አዋጅ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪን መጠየቅ የማይችለው ከጥር ወር 1992 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ውስጥ ያለውን ተጨማሪ ክፍያ እንጂ በአዲሱ አዋጅ መጽናት በኋላ ላሉት ጊዜያት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ተጨማሪ ክፍያን ሊባል አይገባም፡፡ የአመልካች ጥያቄም ከሰኔ 01 ቀን 1995 ዓ.ም በኋላ ያሉትን ጊዜያትን መሰረት ያደረገ መሆኑን አቤቱታው በግል ያሣያል፡፡ ተጠሪ የመክፈል ግዴታ የሚኖረው ውዝፍ የጡረታ መዋጮውን ብቻ ነው፡፡ ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የአመልካች ጥያቄ ከአዋጅ ቁጥር 345/1995 በፊት የተገኘ መብት በመሆኑ በአዋጁ አይገዛም ተብሎ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ አዋጁ ተፈፃሚነት አለው ከተባለ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/ሠ/ መሰረት ተጨማሪ ክፍያው እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው በማለት የሚያቀርበውን ክርክር ስንመለከተው ተጠሪ ዋናውን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ወዲያውኑ አለመክፈሉን እያመነ ተጨማሪ ክፍያው እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት መከራከሩ ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በላይ አመልካች ድርጅት ተጧሪ ባለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/ሠ/ አግባብነት ሊኖረው አይችልም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከሰኔ 01 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ገቢ ላላደረገበት ጊዜ ተጨማሪ ክፍያ(2%) ሁለት በመቶ የማይከፈልበትን ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ አመልካች ህጋዊ ወለድ ሊታሰብ ይገባል የሚለው የዳኝነት ጥያቄ ግን ህጉ

የ(2%) ሁለት በመቶ ተጨማሪ ክፍያ ይከፈላል ከሚል ውጪ በድጋሚ እንዲታሰብ የሚፈቅድበት ሁኔታ ምክንያት ባለመኖሩ የምንቀበለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 345/1995 ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም የሚለውን ምክንያት ብቻ በመያዝ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት አዋጁ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ተግባራዊ መሆን የሚኖረበት ስለመሆኑ ባላገናዘበ መልኩ ሆኖ ስለተገኘ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 77477 ግንቦት 10 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 56348 ጥር 15 ቀን 2000 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሸሯል፡፡
2. ተጠሪ ከሰኔ 01 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 30 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ የጡረታ መዋጮውን ገቢ ያላደረገ በመሆኑ ገቢ ባላደረገው የጥር ወር 1992 ዓ.ም ገንዘብ ብር 39,974.35/ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አራት ብር ከሰላሳ አምስት ሣንቲም/ ላይ በየወሩ ሁለት በመቶ (2%) ታስቦ በተጨማሪ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
3. አመልካች ክስ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ወደፊት ከሚያስከትለው ተጨማሪ ክፍያና ይህ ገንዘብ ገቢ ሊሆን ከሚችልበት ጊዜ ጀምሮ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ እንዲከፈል ያቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ አልተቀበልነውም፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷ፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 37375

ኅዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ ሽምሱ ከድር አህመድ - ቀርበዋል፡፡

**ተጠሪ፡-** የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር - አልቀረቡም

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ አቤቱታ የቀረበው አመልካች ሚያዝያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻቸው እንደገለፁት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር በቁ. 12 ጥ/2029/2037 ታሕሳስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ለአመልካች ባሳወቀው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢቀርብም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ. 62758 የካትት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 ይግባኙን በመሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟልና ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች መስከረም 9 ቀን 2000 ዓ.ም ለተጠሪ በፃፉት ማመልከቻ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ መግቢያ ፈተና ለመውሰድ እንዲፈቀድላቸው ቢያመለክቱም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአመልካች ጥያቄና ማስረጃ በማገናዘብ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ነሐሴ 10 ቀን 1998 ዓ.ም በሕግ ዲፕሎማ ከተመረቁ በኋላ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 8/1/ መሰረት በሙያው 5 ዓመት ያላገለገሉ ናቸው በማለት የአመልካች ጥያቄን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅሬታ በማሳደር ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ በመ/ቁ. 62758 የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 ሰርዞታል፡፡

አመልካችም ሚያዝያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም አግባብነት ባለው የሕግ ሞያ ከ12 ዓመት በላይ ማለትም ከሰኔ 01 ቀን 1981 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 1985 ዓ.ም በአውራጃ አቃቤ ሕግነት፣ ከሐምሌ 01 ቀን 1985 ዓ.ም እስከ መጋቢት 1988 ዓ.ም ድረስ በወረዳ አቃቤ ሕግ ሐላፊነት እንዲሁም ከጥቅምት 01 ቀን 1989 ዓ.ም እስከ ግንቦት 14 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በነገረ ፈጅነት ያገለገልኩና በ1981 ዓ.ም ለአውራጃ አቃቤ ሕግነት የተሰጠውን ስልጠና በመከተታል የሕግ ስርተፍኬት እንዲሁም ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በሕግ ዲፕሎማ ያሉኝ ማለትም የኢትዮጵያ መሰረታዊ ሕጐች የማወቅ ነኝ፤ ይህ ሁኔታ ደግሞ አዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 8/1/ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፍቃድ ለማግኘት ወደ ፈተና ለመቀመጥ የሚያበቃኝ ሆኖ እያለ ተጠሪው እና የስር ፍርድ ቤቱ ሕጉን አላግባብ በመተርጐም ዲፕሎማው ካገኝሁበት ጊዜ ወዲህ ቢያነስ 5 አመት ማገልገል ይጠበቅብሐል ማለታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል፤ በተጠቀሰው አንቀጽ የተመለከተው መስፈርት በተለይም ደግሞ በሞያው 5 ዓመትን የማገልገል ሁኔታ በህግ ዲፕሎማ ከተመረቅኩ ወዲህ ብቻ ሳይሆን ከመመረቁ በፊት የሰጠኋቸውን አግባብነት ያላቸውን አገልግሎቶቹም የሚጨምር ነው፤ስለሆነም የፈፀሙት የሕጉን የአተረጓጐም ስህተት ታርሞልኝ የጠየቀኩትን የጥብቅና ፈቃድ ለማግኘት የሚያስችሉኝን ፈተና እንድወስድ ሆኖ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪም ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የሰጠ ሲሆን ይዘቱም አመልካች የሕግ ዲፕሎማውን ካገኙ በኂላ የ5 ዓመት ግልጋሎት ስለሌላቸውና ከዚያ በፊት የነበሯቸው አገልግሎቶች ለተፈለገው የጥብቅና ፍቃድ ብቃት ስለሌላቸው ቦርዱ በአዋጁ አንቀጽ 8/1/ መሰረት የተመለከቱትን መስፈርቶች ያልተሟሉ ሆኖ ስላገኘው የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ በመሆኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጡ ከላይ እንደተገለፀው ሆኖ ፍርድ ቤቱም አመልካች ላቀረቡት የጥብቅና ፈቃድ ጥያቄ የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ያሟላሉ ወይስ አያሟሉም? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡-

ከላይ እንደተጠቀሰው የአመልካች ጥያቄ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፍቃድ ማግኘት ሲሆን ይህ የጥብቅና ደረጃ የሚመለከቱ መስፈርቶች በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 8/1/ በግልጽ የተዘረዘሩ ሲሆኑ እነዚህም በሕግ ዲፕሎማ ያለው፣ የኢትዮጵያ መሰረታዊ ሕጐችን ማወቅ እንዲሁም አግባብነት ባለው ሞያ ቢያንስ 5 ዓመታትን ማገልገል የሚሉ ናቸው፣ የአመልካች ጥያቄ ከእነዚህ መስፈርቶች አኳያ ሲታይ ደግሞ ቀደም ብሎ የሕግ ሰርተፍኬት (በ1981 ዓ.ም የተሰጠ) የነበራቸውና ነሐሴ 10 ቀን 1998 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በሕግ ዲፕሎማ ማግኘታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች የትምህርቱን መስፈርት ያሟሉና የኢትዮጵያ መሰረታዊ ህጐች እንደሚያውቁ ነው፡፡ የሰጡት ግልጋሎትም ሲታይ በአውራጃ አቃቤ ህግነት ለ4 ዓመታት፣ በወረዳ አቃቤ ሕግ ሐላፊነት ለ2 ዓመት ከዘጠኝ ወራት እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ ነገረ ፈጅነት ለ6 ዓመት ከ8 ወራት አካባቢ በጠቅላላ ወደ 13 ዓመታት መስራታቸውን ስለሚያሳይ ከዚሁ ውስጥም ለጠየቁት የጥብቅና ደረጃ ከ5 ዓመታት በላይ ማገልገላቸው ያሳያል፤ ቀጥሎ መታየት ያለበት ነጥብ በተጠቀሰው አንቀጽ የሰፈረው የ5 አመታት አገልግሎት የግድ መቆጠር ያለበት ዲፕሎማ ካገኙበት ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡ ሕጉ በግለጽ እንደሚያሳየው የ5 አመታት አገልግሎት የግድ በዲፕሎማ ከተመረቁ በኂላ የሰጡት መሆኑ አያሳይም፣ እነዚህ መስፈርቶች ራሳቸውን ችለው የተቀመጡ እንጂ የአገልግሎት ዘመኑ መቆጠር ያለበት የሕግ ዲፕሎማ ካገኙበት ጊዜ ጀምሮ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ለጠየቁት የጥብቅና ፈቃድ ደረጃ በሕጉ የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟሉ ሆነው እያሉ ተጠሪው ሚኒስቴርም ሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መስፈርቱን እንዳላሟሉ በማድረግ ያስቀመጡት የሕጉ አተረጎጐም መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. ተጠሪ በቁ. 12 ጥ/2029/2037 ታህሳስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ለአመልካች ያሳወቀው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 62758፣የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ ተሽረዋል፤ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች ለጠየቁት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የጥብቅና ፈቃድ በአዋጅ ቁ. 199/1992 አንቀጽ 8/1/ የተዘረዘሩትን የትምህርት ደረጃ፣ የአገልግሎት ዘመንና የሕግ እውቀት የሚያሟሉ ስለሆነ ተጠሪው ፈተና ሊፈትናቸው ይገባል፤ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ ጉዳዩ ያለቀ ስለሆነ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 37050

ታህሣሥ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሊ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ሻምበል ሁሴን አሊ - ጠበቃ መድህን መሐሪ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ሱማሌ ክልል ዐ/ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከባድ የሆነ የሰው ግድያ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የጅጅጋ ዞን ዐ/ሕግ መስከረም 02 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፈው የክስ ማመልከቻ የአሁኑ አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1ሀ/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ነሐሴ 26 ቀን 1998 ዓ.ም ከጠዋቱ 4:00 ሲሆን በጅጅጋ ዞን ፖሊስ ጽ/ቤት ፊት ለፊት የሱፍ መሐመድ ሰሊም ይባል የነበረውን ግለሰብ ታጥቆት በነበረው ሽጉጥ አንድ ጥይት በመተኮስ ራሱ ላይ በመምታት ለህልፈት የዳረገው በመሆኑ ሊቀጣ ይገባል በማለት በመሠረተው ክስ መነሻ ሲሆን የአሁኑ አመልካች በተከሣሽነታቸው ቀርበው ክሱ ከተነበበላቸው በኋላ ፍ/ቤቱ ለክሱ የሚከራከርለትን ጠበቃ እንዲፈቅድላቸው ጠይቀው ፍ/ቤቱም ተከሣሹን የክሱ ማመልከቻ የሚለውንና የተነበበው የገባቸውና የተረዱት መሆኑን ጠይቋቸው ተጠሪም የተረዱት መሆኑን ለፍ/ቤቱ ከገለፁ በኋላ የድርጊት አፈፃፀሙን በተመለከተ ግን በዐ/ሕግ የክስ ማመልከቻ በተከሠሡበት ዓይነት አልፈፀምኩም ሲል የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ለጥቅምት 08 ቀን 1999 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ የዐ/ሕግ ምስክሮች እንዲቀርቡ አመልካች ጠበቃቸውን ይዘው እንዲቀርቡ ተደርጎ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ሊቀርቡ አለመቻላቸው የአመልካች ጠበቃም ያልቀረቡ መሆኑ ተረጋግጦ ተለዋጭ ቀጠሮ ተይዞ የዐ/ሕግ ምስክሮች ሲቀርቡ የአመልካች ጠበቃ በሌላ ቦታ ላይ በነበራቸው ቀጠሮ ምክንያት ያልቀረቡ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ ቀጠሮው በአዳሪ /ለተከታዩ ቀን/ እንዲለወጥላቸው ቢጠይቁም በዐ/ሕግ በኩል ነገሩን ያጓትተዋል የሚል ተቃውሞ ቀርቦ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኝ አዳምጦ ጠበቃው የበለጠ ጊዜ ሊጠበቅ አይቻልም፣ ግራ ቀኙም ተስማምተውበታል በማለት የአመልካች ጠበቃ ሣይቀርቡ ወይም ሌላ ጠበቃ ሣይተካ የዐ/ሕግ ምስክሮች እንዲሰሙ ተደርጓል፡፡ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀማቸውን ዐ/ሕግ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በፀዳ ሁኔታ አረጋግጦባቸዋል ተብሎ እንዲከላከሉ ከተደረገ በኋላ መከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብታቸውን መተዋቸውን ገልፀዋል ተብሎ ከታለፈ በኋላ የዐ/ሕግ ተጨማሪ ምስክሮች እንዲሰሙ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በኋላ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ አመልካችን በዐ/ሕግ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ በሞት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡ ከዚያም የአሁኑ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኝ እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ ይኸው ፍ/ቤትም በአመልካች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሚያዚያ 04 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 7/ሰባት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ጠበቃ የመወከል መብታቸው ያልተጠበቀላቸው መሆኑን፣ የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈፀማቸው በማስረጃ ያልተጋጠባቸው መሆኑን መከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብታቸው የታለፈውም በቂ ጊዜ ሣይሠጣቸው መሆኑን፣ የተጨማሪ ማስረጃ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓቱን ያልጠበቀ መሆኑን የጥፋተኛነት ውሣኔ የተሰጠበት ድንጋም አግባብነት እንደሌለው እና የሞት ቅጣት ፍርዱም ተገቢነት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ይሻርላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ የክልሉ ዓ/ሕግ ሐምሌ 09 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመለከቻ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ህዳር 10 ቀን 2001 ዓ.ምበተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሱን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች የተከሱበት ጉዳይ ከባድ መሆኑ እየታወቀ በጠበቃ ሣይወከሉ ክርክሩ መካሄዱና ውሣኔ መሰጠቱ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከመዝገቡ የክርክር ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በስርፍ/ቤት የቀረቡትና የእምነት ክህደት ቃል የሰጡት መስከረም 04 ቀን 1999 ዓ.ም ሁኖ በዚህ ዕለት ጠበቃ ያልተወከለላቸው መሆኑን፣ ጥቅምት 08 ቀን 1999 ዓ.ም የዐ/ሕግ ምስክሮች እና የአመልካች ጠበቃ እንዲቀርቡ ተገልጾ ቀጠሮ በተያዘበት ቀንም የአመልካች ጠበቃ አለመቅረባቸው፣ በተከታዩ ቀነ ቀጠሮም የዐ/ሕግ ምስክሮች ቀርበው የአመልከች ጠበቃ ሣይቀርቡ የቀሩበትን ምክንያት አመልካች ለፍ/ቤት ገልፀው የዐ/ሕግ ምስክሮች ጠበቃቸው በበነጋው ሲቀርቡ እንዲሰሙላቸው ቢያመለክቱም ተቀባይነት በማጣት የዐ/ሕግ ምስክሮች አመልካች በጠበቃ ባልተወከሉበት ጊዜ የተሰሙ መሆኑ መረጋገጡን ነው፡፡

በመሠረቱ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር የተያዙና የተከሰሱ ሰዎችን በተመለከተ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት የተካተቱትን መብቶችን የሚገልፁት ድንጋጌዎች አቀራረፅና ይዘታቸው ሲታይ በተቻለ መጠን ወዲያውኑ ሊተገበሩ የሚገባ መሆኑን ያስገነዝቡናል፡፡ ከዚህም በላይ በወንጀል ፍትህ አስተደደር የተያዙና የተከሠሡ ሠዎች ሕገ- መንግሥታዊ መብታቸውን የዳኝነት አካሉ የማክበርና የማስከበር ሕገ መንግሥታዊ ግዴታ ያለበት መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 13/1/ ስር በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም የተያዙና የተከሠሡ ሰዎች ሕገ መንግሥታዊ መብት የማክበርና የማስከበር ግዴታ በዳኛው ትከሻ የወደቀ ስለመሆኑ ሊስተዋል ይገባል፡፡ በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ዳኞች ይህንኑ ግዴታ ሲወጡ ደግሞ ማህበረሰቡ የሂደቱን ፍትሃዊነት ከማክበሩም በተጨማሪ የሂደቱን ውጤትም በአክብሮት እንዲቀበል ያደርጋል፡፡ የሕግ ሥርዓቱ በሕገ-መንግሥቱ ጥበቃ የተደረገላቸውን የዜጎች መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ ካልተወጣ ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ተቀባይነትና አክብሮት እንደሚቀንስ ይታመናል፡፡ ስለሆነም በሕገ-መንግሥቱ የተመለከቱት ሠብአዊ መብቶች ማክበርና ማስከበር የግድ ይሏል፡፡

አንድ በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ የተያዘና የተከሰሰ ሰው ከሂደቱ መጀመሪያ እስከ ፍፃሜ ድረስ በሕገ-መንግሥቱ ከተረጋገጠለት ሠብአዊ መብቶች መካከል አንዱ በጠበቃ የመወከል መብት ነው፡፡ ይህ መብት ተከሣሹ በራሱ የሚፈልገውን ጠበቃ በማቆም ሊጠቀመው የሚችለው ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣቱ ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም በመንግሥት ወጪ ጠበቃ በማቆም ሊከበርለት የሚገባው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 20/5/ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ከድንጋጌው መንፈስ የምንገነዘበውም ተከሣሹ ራሱ በመረጠው ጠበቃ የመወከል ሕገ-መንግሥታዊ መብቱን እንዲጠቀም በቂና አሣሣኝ ጊዜ ከመስጠት በተጨማሪ ይኸው መብት እንዳለውም በችሎቱ ሊገለጽለት የሚባው መሆኑን ነው፡፡

ይህ ብቻ ሣይሆን ተከሣሹ ብቃት ባለው ጠበቃ መወከሉም ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ይህ ሁሉ የፍ/ቤቱ የስራ ድርሻ ነው፡፡ ስለሆነም በጠበቃ የመወከል መብት ትልቅ ሕገ- መንግሥታዊ መብት መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡

እጃችን ወደአለው ጉዳይ ስንመለስም የአሁኑ አመልካች ከሂደቱ መጀመሪያ ጀምሮ እስከመጨረሻው በፈለጉት ጠበቃ የመወከል ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው በቂና አሣማኝ ጊዜ ተሰጥቷቸው በስር ፍ/ቤት የተከበረላቸው አለመሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የአመልካች ሕገ-መንግሥታዊ መብት ሣይከበር የተሰጠ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 001/99 በቀን 01/02/1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ በሶማሌ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም. የፀናው የጥፋተኛነትና የሞት ቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ1/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል ይፃፍ፡፡
2. አመልካች በመረጡት ጠበቃ የመወከል ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው ሊከበር ይገባል ብለናል፡፡
3. አመልካች በመረጡት ጠበቃ የመወከል ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው ተከብሮ ጉዳዩ ከዚህ በፊት ባላዩት ዳኞች እንደገና ታይቶ ተገቢው ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን ለጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 38237

ታህሣሥ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ በርገና ሽፈራው - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ አብርሃም ሽፈራው
2. አቶ መስፍን ሽፈራው
3. ወ/ሮ ታሪኳ ሽፈራው

(1–3) ወ/ነ/ፈጅ አቶ አብረሃም ሽፈራው ቀረቡ፡፡

4. ወ/ሮ ሽታዬ ሽፈራው - በሌለችበት የሚታይ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ለዚህ ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 20032 በሆነው መዝገብ ግንቦት 1 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪዎች በወረዳ ፍ/ቤት ከሣሾች ሲሆኑ አመልካች ተከሣሽ ነበር፡፡ የክሱም ምክንያት የሚች አባታችን ንብረት የሆነውን የውርስ መሬት ይዞ ስለሚገኝ ድርሻችንን ያካፍለን የሚል ሲሆን አመልካችም በዚሁ መሬት ከዚህ በፊት ታላቅ ወንድማቸው ክስ አቅርቦ ተከራክረን በመ/ቁ. 32/94 በሆነው መዝገብ በ12/9/94 ዓ.ም. የዋለው ችሎት ውሣኔ የሰጠ በመሆኑ ሌሎች ወንድሞቹ ተመሣሣይ ክስ ቢያቀርቡም በተመሣሣይ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ደግሞ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም፡፡ አባታችን የሞቱት በ1973 ዓ.ም. በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ መሠረት ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ የተከራከረ ስለመሆኑ መዝገቡ የስረዳል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ያከራከረው የምዕራብ አባያ ወረዳ ፍ/ቤት ከዚህ በፊት ውሣኔ ያገኘ ጉዳይ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5/1/ መሠረት እንደገና ክስ ሊቀረብበት አይገባም አመልካች ከ15 ዓመት በላይ ግብር እየገበረበት የሚጠቀምበት ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክርን መሠረት በማድረግ የከሳሾችን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የጋሞ ጎፋ ዞን የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤትም የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ አጽንቷል፡፡ ግራ ቀኙን ያከራከረው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ወንድማቸው አቶ በለጠ ሽፈራው ስለራሱ ተከራከረ እንጂ ከሣሾችን ወክሎ አልተከራከረም፡፡ ስለዚህ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5/1/ መሠረት በማድረግ የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ አይደለም በማለት የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመሻር ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 3 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፎ ያቀረበው ቅሬታ፡-

- እኔ ከጦር ሜዳ እንደተመለስኩ እንደ እኔ ከጦር ሜዳ ግዳጃቸውን ፈጽመው ለተመለሱ ሲሰጣቸው የተሰጠኝን ይዞታ መሬት አርሼ ለ19 ዓመታት ከተጠቀምኩ በኂላ የተጠሪዎች ታላቅ ወንድም በ1993 ዓ.ም. ክስ መስርቶ ተከራክረን በተወሰነው ጉዳይ እንደማያውቁ ሆነው ክስ ማቅረባቸው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5/1/ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፣

- ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ መሠረት በይርጋ እንደሚታገድ በማስመልከት ያቀረብኩትን ክርክር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሳያጣራ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሣኔ በመሆኑ ተሽሮ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንዲፀና እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡
- ቅሬታውን መሠረት በማድረግ ለማጣራት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዞ መስከረም 22 ቀን 2001 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ ከ1-3 ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተጠሪዎች መልስ አቅርበዋል፡፡ የመልሱም ፍሬ ሀሣብ አቶ በለጠ ሽፈራው ያቀረበው የይዞታ ክርክር እንጂ የውርስ ንብረት ክርክር አይደለም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5/1/ ለክርክሩ አግባብነት የለውም፡፡
- የይርጋ ክርክም በሥር ፍ/ቤት ስላልተነሳ በሰበር ሰሚ ችሎት ማንሳት አይቻልም በማለት በወኪላቸው አማካይነት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አራተኛ ተጠሪ በቀበሌው የማይታወቁና በወረዳውም የሌሉ መሆኑን ከቀበሌው አስተዳደር በመግለጹ መጥሪያው በፍ/ቤት ቅጥር ግቢ ተለጥፎ ያልቀረቡ በመሆኑ በሌለችበት እንዲታይ ታዟል፡፡

አመልካችም በ5/3/2001 በተፃፈው የመልስ መልስ ወንድማቸው ያቀረበው ክስ የውርስ ጥያቄ ነው፡፡ የይርጋ ክርክርም ቢሆን ከበታች ፍ/ቤቶች ጀምሮ የተከራከርኩበት መዝገብ ያስረዳል በማለት ተከራክሯል፡፡

እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች አግባብነት እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ግራ ቀኙ የሚከራከሩት የሟች አባታቸው ይዞታ የነበረ ሙዝና ቋሚ ሰብል ያለበት በውርስ ሊደርሰን የሚገባንን አመልካች ለብቻው ይዞ ይጠቀማልና ድርሻችንን ያካፍለን በማለት ነው፡፡ የአመልካች ክርክር ደግሞ ለ19 ዓመታት በእጄ አድርጌ የምጠቀምበት ነው፡፡ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ይከራከራል፡፡ አባታቸው የሞቱት በ1973 ዓ.ም. መሆኑን ግራ ቀኙ አልተካካዱም፡፡ ለተጠሪዎች በአመልካች ላይ መሬቱን እንዲያካፍላቸው ክስ ያቀረቡት ሰኔ 6 ቀን 1999 ዓ.ም. ነው፡፡

በመሠረቱ ከሣሽ መብቱንና የውርስ ንብረቶች በተከሣሹ መያዛቸውን ካወቀ ሦስት ዓመት ካለፈ በኋላ ስለወራሽነት የሚያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት እንደማይኖረው አመልካች ጠቅሶ በሚከራከረው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ ሥር ተደንግጓል፡፡ አባታቸው ከሞቱበት ከ1973 ዓ.ም. ጀምሮ ይህ ክስ እስከቀረበበት ሰኔ 6 ቀን 1999 ዓ.ም. ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ 26 ዓመታት ያሕል አስቆጥሯል፡፡ በሕጉ አነጋገር ተጠሪዎች የአባታችን መሬት በዚህ ጊዜ ነው በአመልካች መያዙን ያወቀነው በማለት የይርጋው ጊዜ ሊያሳጥርላቸው የሚችልበትን ለይተው የተከራከሩበት ወይም መያዙን አላወቅንም ሲሉ የተከራከሩበት ወይም በሌላ ምክንያት ይርጋው ሊቋረጥ የሚችልበትን ምክንያት መሠረት በማድረግ ያደረጉት የሕግ ክርክር የለም፡፡ የመሬት ባለቤትነት የኢትዮጵያ ሕዝብና የመንግሥት ከመሆኑ አንፃር ከዘር የወረደ ርስት ነው ተብሎ የሚጠየቅ አይደለም፡፡ ይህ ባልሆነበት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከሌሎች የክርክር ነጥቦች በቀዳማይነት ሊታይ የሚገባውንና አመልካችም ከወረዳ ፍ/ቤት ጀምሮ በጥብቅ የሚከራከርበትን የመቃወሚያ ክርክር ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት በሌለበት በዝምታ በማለፍ የወረዳውንና የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ሲል የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ መሠረት በወራሾች መካከል የሚደረግ የውርስ ጥያቄ ክርክር ከ3 ዓመት በኋላ ሊቀርብ እንደማይገባ የተደነገገውን ሕግ ትርጉም የልጠበቀና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 20032 በቀን 01/09/2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የተጠሪዎች ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል ብለናል፡፡
3. የምዕራብ አባያ ወረዳ ፍ/ቤት አመልካች በመሬቱ መሠረት አድርጎ የሰጠው ውሣኔና የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤትም የፀናው በአግባቡ ነው ብለን ውሣኔዎቹን አጽንተናል፡፡

4. ወጪና ኪሣራ የዚህ ፍ/ቤትን ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡
ውሣኔው ዛሬ በ22/04/2001 በንባብ ተሰማ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁጥር 37184

ታህሣሥ 09 ቀን 2001

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የሰሜን ቀጠና ጉምሩክ - የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪ፡-** 1. ቄስ ብርሃነ ንዋይ - አልተጠራም

2. ሐጂ ዓብዱልቃድር መሐመድ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በኮንትሮባንድነት የተያዘ 71/ሠባ አንድ/ ኩንታል በአደራ ተጠምጦ ከቆየ በኋላ ባለመመለሱ ዋጋው ይከፈለኝ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ አመልካች የአሁኑ አንደኛ ተጠሪ በመረብለኸ ወረዳ በራማ ከተማ በኮንትሮባንድ ወንጀል የተያዘ ሠባ አንድ ኩንታል ቡና በአደራ በመጋዘን ለማስቀመጥና እንዲሁም አቅርብ በተባለበት ጊዜ ለማስረከብ ካልቻሉ ግን እጥፍ አድርገው 142 /አንድ መቶ አርባ ሁለት/ ኩንታል ቡና አድርገው ለመመለስ የውል ግዴታ መግባታቸውን፣ ሁለተኛ ተጠሪ በበኩላቸው ደግሞ ለአንደኛ ተጠሪ ዋስ ሆነው ተጠሪው ቡናው ካልመለሱ ሰባ አንድ ኩንታል ቡና ለመመለስ ውል መፈረማቸውን በመዘርዘር አንደኛ ተጠሪ በውሉ መሠረት 142 ኩንታል ቡና ዋጋ ብር 340,800.00 /ሦስት መቶ አርባ ሺህ ስምንት መቶ ብር/፣ ይህንኑ መክፈል የማይችሉበት ምክንያት ካለ ደግሞ ሁለተኛ ተጠሪ በገቡት የዋስትና ውል መሠረት የሰባ አንድ ኩንታል ቡና ዋጋ ብር 170,400.00 /አንድ መቶ ሰባ ሺህ አራት መቶ ብር/ እንዲከፍሉ ይወስንለት ዘንድ ዳኝነት በመጠየቅ በተጠሪዎች ላይ በመሠረተው ክስ ነው፡፡ ተጠሪዎችም ቀርበው አለን ያሉትን መከላከያ መልስ አቅርበዋል፡፡ አንደኛው ተጠሪ ባቀረቡት የመከላከያ መልስ በጉዳዩ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡት የፊርማ ሠነድ ባለመመርመሩ እንጂ ተመስክሮባቸው አለመሆኑን፣ ውልም አለመኖሩን፣ ቡናው የሌላ ሰው መጋዘን በጉምሩክ ፖሊሶች ተከራይቶ የተቀመጠ እንጂ ተጠሪ የተረከቡት አለመሆኑን በመዘርዘር የተከራከሩ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ በበኩላቸው ዋስ የሆኑት አንደኛውን ተጠሪ ለማቅረብ እንጂ ሰባ አንድ ኩንታል ቡና ለመክፈል አለመፈረማቸውን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ማዕከላዊ ዞን ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር፣ የምስክሮችን ቃል ከሠማና በውሉ ላይ አለ የተባለው ፊርማ የተጠሪዎች ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት እንዲቀርብ ከአደረገ በኋላ ተገቢ ነው ያለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር በመልካች በኩል የቀረበ ማስረጃ ዝቅተኛ ነው በማለት ተጠሪዎችን በነፃ አሠናብቶ ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፈጅ ሚያዝያ 09 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነው በኮንትሮባንድ ተያዘ የተባለው ቡና አንደኛ ተጠሪ በአደራ ስለመረከባቸው በዚሁ መሠረት መልሰው ባለማስረከባቸው በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው ተቀጥተው ያሉ፣ ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ ዋስ ሁነው

መፈረማቸውን የሚያሣዩ ሰነዶች ቀርበው እያለ ተጠሪዎች ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ሊታረም ይገባል በማለት የቡናውን ዋጋ እንዲከፍሉ ይወስን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው ሰኔ 26 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓቱንና ጥንካሬውን በተመለከተ ምክንያቶችን በመዘርዘር ክርክሩ በበታች ፍ/ቤቶች በሚሠማበት ወቅት የቀረቡት ጭብጦችና የማስረጃዎች ሁኔታ ተጠሪዎችን ኃላፊ ለማድረግ ብቃት ያላቸው ስላልሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ነ/ፈጅ በበኩላቸው የተጠሪዎችን የመልስ ማመልከቻ ነጥቦችን አንድ በአንድ በማንሣት ተገቢነት የሌላቸው መሆኑን በመዘርዘር እና የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ሐምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም የሰነድ ማስረጃዎችን ይዘት ተመልክቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር፣ የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ተጠሪዎች ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሲሆን የአላፊነት መጠኑም ተያይዞ ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ሀ/ አላፊነትን በተመለከተ</u>

አመልካች ክሱን ሊመሰርት የቻለው በኮንትሮባንድ ወንጀል የተያዘ ቡና አንደኛ ተጠሪ በአደራ አስቀምጠው እንዲያቆዩ፣ ሲጠየቁም በተጠየቀበት ጊዜ ለማስረከብ፣ ይህ ካልሆነ እጥፍ አድርገው ለመክፈል ኅዳር 17 ቀን 1989 ዓ.ም. በተፃፈ ሰነድ ስምምነት አድርገው በስምምነቱ መሠረት ሊፈፀምለት ባለመቻሉ ነው፡፡ ይህንኑ ፍሬ ነገር ለማስረዳትም የውሉን ሰነድ፣ አንደኛ ተጠሪ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ ስለመሆኑ የሚያሣይ የፍ/ቤት ውሣኔ፣ ለአንደኛ ተጠሪ የተሰጠ ማስጠንቀቂያና የሰው ምስክሮችን አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎች በውሉ ላይ ያለውን ፊርማ በመካዳቸው ምክንያትም ፊርማቸው እንዲመረመር ተደርጎ የተጠሪዎች መሆን አለመሆኑ ሊለይ አለመቻሉን በግለጽ መርማሪው አካል በደብዳቤ ገልጿል፡፡ በውሉ ነበሩ የተባሉ ምስክሮች እንደሰሙ ተደርጎም ሁለቱ ምስክሮች ውሉን እንማያውቁና ያልፈረሙበት መሆኑን፣ ቀሪው ምስክር ግን ውሉ መኖሩን በመግለጽ መስክረዋል፡፡

የበታች ፍ/ቤቶች ለእነዚህ የአመልካች ማስረጃዎች ክብደት ያልሰጡት ፊርማው ተመርምሮ ሊለይ አለመቻሉና ሁለት ምስክሮች ውሉን የማያውቁ መሆናቸው ተረጋግጧል በማለት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1726፣ 1727፣ 2709፣ 2787፣ 2802 እና 1922/3/ ድንጋጌዎችን በመጥቀስ የአመልካች ማስረጃ ዝቅተኛ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

በአመልካችና በአንደኛ ተጠሪ መካከል የተቋቋመው ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2779 ሥር የተመለከተውን ትርጓሜ ሊያሟላ የሚችል የአደራ ውል ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት በግልጽ ያሣያል፡፡ በግራ ቀኙ መካከል ያለው ውል የአደራ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ መታየት የሚገባው በዚህ ረገድ የተመለከቱት የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ሊተው የሚችሉት ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት የማያስችሉ ሆነው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ የሕግ አተጓጎም መርህ ያስገነዝባል፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ከአደራ ውል አኳያ የተመለከቱት ስለመሆኑ የውሣኔ ይዘት ቢያሳይም በዚህ ረገድ በዋቢነት የተጠቀሱት ድንጋጌዎችም ሆነ ከጠቅላላ የውል ክፍል የተጠቀሱት ድንጋጌዎች የማስረጃውን ዝቅተኛነት ለማሣየት አግባብነት የሌላቸው መሆኑን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡ ለአንድ ውሣኔ በዋቢነት ሊጠቀስ የሚገባው ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው እንጂ ተዛማጅነት የሌለው ሊሆን አይገባም፡፡

አመልካች በክሱ ላይ የተገለፀውን ፍሬ ነገር እርግጠኛነት ለፈራጅ ለማሣመን ያቀረባቸው የሰነድ እና የሰው ምስክሮች ናቸው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ከቀረቡት የአመልካች ማስረጃዎች መካከል አንደኛ ተጠሪ በጉዳዩ በወንጀል ተከሠው ጥፋተኛ የተባሉበትና የተቀጡበትን የፍ/ቤት ውሣኔ ለጉዳዩ ያለውን አግባብነት ወይም ብቁነት ሳይገልጽ ስለማለፉ የውሣኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ የተቆጠረው ወይም የቀረበው ማስረጃ ለክርክሩ መነሻ ከሆኑት ፍሬ ነገሮች ጋር ግንኙነት እያለው እና ፍሬ ነገሮችን ለማረጋገጥ በሕጉ ክልከላ ያልተደረገበት የማስረጃ ዓይነት እስከሆነ ድረስ በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ሁሉም ማስረጃዎች መመዘን አለባቸው በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ሁሉን ማስረጃዎች በአንድነት ሣይመዘኑ የተወሰኑትን ብቻ ነጥሎ በመወሰድ የሚሠራ ምዘናም ሆነ ውጤት ፍትሐዊነት አይኖረውም፡፡

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስ አንደኛ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ በወንጀል ተከሰው በፍ/ቤቱ ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ መሆኑንና በበላይ ፍ/ቤትም አለመለወጡ ተረጋግጦ እያለ ይህ የአመልካች ማስረጃ በሰበር ፍ/ቤት በዝምታ ታልፏል። ይህም የማስረጃ አቀባበል ሥርዓትን ያልተከተለ ነው። የዚህን ማስረጃ አግባብነት እና ብቁነት ስንመለከተውም ለጉዳዩ በማስረጃነት ሊቀርብ ወይም ክብደት ሊሰጠው አይገባም የሚባልበትን የሕግ ምክንያት አላገኘንም። በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በዚያው ጉዳይ በፍትሐብሔር በማስረጃነት አግባብነት እና ብቃት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ ሕ/ቁ. 2149 ተቃራኒው ንባብ ያስገነዝባልና። በዚህ ድንጋጌ መሠረት በወንጀል የተሰጠ ውሣኔ በፍትሐብሔር ለቀረበው ክስ በማስረጃነት አግባብነት የሚኖረው በወንጀል ክሱ በወንጀል ፍ/ቤት ተከሣሹ ጥፋተኛ ተብሎ ከተወሰነ ስለመሆኑ እና ለዚህም የሚሰጠው ምክንያት የወንጀል ክስ ማስረጃ አመዛዘን መርህ ከፍትሐብሔሩ የበለጠ ጠንካራና የማያሻማ ማስረጃ የሚጠይቅ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም። የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ማስረጃ ክብደት የመዘነው ከፎረንሲክ ምርመራ ውጤት መግለጫና ከተሰሙት ምስክሮች ቃል አንፃር እንጂ በወንጀል ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ ከሕጉ ጋር አገናዝቦ አይደለም።

በመሠረቱ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት በውሉ ሰነድ ላይ የተመለከተው ፊርማ የተጠሪዎች አይደለም በሚል የማይገልጽ፣ ይልቁንም ለመለየት ያልተቻለ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። በመሆኑም በዚህ መልኩ የተገለፀውን የባለሙያ አስተያየት በውሉ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪዎች አይደለም ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ማስረጃ /conclusive evidence/ አይደለም። በመሆኑም የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ ምክንያት የለም። ከተሰሙት የአመልካች ምስክሮች ውስጥም አቶ ኀይቶኦሞ ገ/ሕይወት የተባሉት በ17/03/1989 በተፈረመው የውል ሰነድ ላይ የፈረሙ መሆናቸውን የውሉ ሰነድ የሚያሣይ ከመሆኑም በላይ በወንጀል ችሎት በዓቃቤ ሕግ ምስክርነት ቀርበው የአደራ ውሉን መኖር መመስከራቸው ከመረጋገጡ አኳያ በፍትሐብሔር ክስ ጊዜ ውሉን አላውቀውም፣ አልፈረምኩም ማለታቸው የምስክሩን ቃል ተዓማኒነት በመቀበል የውል ሰነዱንና የወንጀል ችሎት ውሣኔ ሰነድ የማስረጃነት ተገቢነት /admissibility/ ሊያስቀር የሚችል አይደለም ሁለተኛ ተጠሪም በወንጀል ችሎት የመሠከሩ ከመሆናቸውም በላይ በውሉ ሰነድ ላይ መፈረማቸውን ሣይክዱ የፈረሙበት ምክንያት አንደኛ ተጠሪን ለማቅረብ ብቻ ነው ማለታቸውን፣ የውሉ ይዘት ይኸው የነበረ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2006/1/ በሚያዝዘው መሠረት መቃወሚያ ማስረጃ ሣያቀርቡ የሚከራከሩ በመሆኑ ክርክራቸው የሕግ መሠረት የሌለው ነው። ሌላው ሁለተኛ ተጠሪ የዋስትና ውሉን በተመለከተ ያቀረቡት የሕግ መከራከሪያ ሲታይም በውሉ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው አንደኛ ተጠሪ የተረከቡትን ቡና ካልመለሱ 71 /ሰባ አንድ/ ኩንታሉን ቡና ለአመልካች ለማስረከብ የተጠቀሰ በመሆኑ ዋሱ እዳውን አውቀው እንደፈረሙ የሚያሣይ ነው ከሚባል በስተቀር የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1922/3/ ድንጋጌን መስፈርት እያሟላም ሊባል የማይገባ ሆኖ በመገኘቱ በዚህ ረገድ የቀረበው መከራከሪያ ነጥብ ተቀባይነት የለውም ብለናል።

ተጠሪዎች የአመልካች ማስረጃ አቀራረብም ሥርዓቱን ያልጠበቀ፣ በስር ፍ/ቤት ሣይቀርብ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የማይገባ ነው በማለት የተከራከሩ መሆኑንም ይህ ችሎት ተገንዝቧል። ሆኖም በአመልካች በኩል የተጠቀሱት ማስረጃዎች በስር ፍ/ቤት ተዘርዝረው የቀረቡ መሆናቸውን የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የሚያሣይ በመሆኑ የማስረጃው አቀራረብ ሥርዓቱን ያልጠበቀ ነው ለማለት አልተቻለም።

በመሆኑም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች የበታች ፍ/ቤቶች በተጠሪዎች አላፊነት ላይ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ የተገኘ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔ ተሽሮ ተጠሪዎች በአደራ ተቀምጦ ለአመልካች ላልተመለሰው ቡና አላፊ ሊባሉ የሚገባ ነው ብለናል።

__ለ/ የአላፊነትን መጠን በተመለከተ፡-__ ጉዳዩ በአደራ ውል ድንጋጌዎች መገዛት ያለበት መሆኑ ከላይ ተገልጿል። በመሆኑም የተጠሪዎች የሃላፊነት መጠን መታየት ያለበትም አደራ ይዘት ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም መሠረት አንደኛ ተጠሪ በአደራ የተረከቡትን ቡና ሲጠየቁ ካልመለሱ እጥፍ አድርገው ለመመለስ በሕዳር 17 ቀን 1989 ዓ.ም. ተደረገ በተባለው ውል የተስማሙ ቢሆንም ይኸው ግዴታቸው በጠቅላላ የውል ድንጋጌዎች መገዛት የሌለበት በመሆኑ፣ የአደራ ተቀባዩ በአደራ የተቀመጠውን ዕቃ እንዲመልስ ሲጠየቅ ያለበት ሕጋዊ ግዴታ በአደራ የተቀመጠውን ዕቃ መመለስ እንጂ ሊመለስ የሚገባው ዕቃ ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅምና ሌላ ተያያዥነት ያለው ትርፍ ጋራ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2779 — 2799 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች መንፈስ ስለማያሣይ፣ አመልካች የአንደኛ ተጠሪ የአላፊነት መጠን እጥፍ ሊሆን ይገባል በማለት የጠየቀው ዳኝነት ከአደራ ውል ድንጋጌዎች ጋር ተዛምዶ የማይሄድ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም፣ የአንደኛ ተጠሪ የአላፊነት መጠን በአደራ ውሉ የተገለፀውን 71 /ሰባ አንድ/ ኩንታል ቡና በዓይነት ለአመልካች መመለስ፣ ወይም

ይኸው ብዛት ያለው ኩንታል ቡና በወቅቱ ገበያ በነበረው ዋጋ ብር 170,400.00 /አንድ መቶ ሰባ ሺህ አራት መቶ/ ተብሎ በአመልካች ተገልፆ በተጠሪ በኩል የቀረበ የተቃውሞ ነጥብ የሌለ በመሆኑ አንደኛ ተጠሪ ይህንኑ የገንዘብ መጠን ለአመልካች በአማራጭ የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡

ሁለተኛ ተጠሪ በአላፊነት መጠኑ ላይ ያቀረቡት ክርክር የዋስትናው ግዴታ መጠን በገንዘብ ያልተጠቀሰ ነው ከሚል ይዘት ውጪ አንድ ኩንታል ቡና በወቅቱ የነበረውን የገበያ ዋጋ መሠረት አድርጎ የቀረበ ባለመሆኑ የአላፊነታቸው መጠን በአንደኛ ተጠሪ አላፊነት መጠን ውጪ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ተጠሪ የገቡት ግዴታ ተራ ዋስትና ዓይነት በመሆኑ እና በዚህ የዋስትና ዓይነት ደግሞ ዋሱ ለባለገንዘቡ የሚገደድበት ባለዕዳው ግዴታውን መወጣት ያልቻለ የሆነ እንደሆነ በመሆኑ ሁለተኛ ተጠሪ አንደኛ ተጠሪ መክፈል ካልቻሉ ብቻ 71 /ሰባ አንድ/ ኩንታል ቡና በዓይነት ለአመልካች የመመለስ ወይም በአማራጭ የ71 /ሰባ አንድ/ ኩንታል ዋጋ ብር 170,400.00 /አንድ መቶ ሰባ ሺህ አራት መቶ ብር/ የመክፈል ግዴታ አለባቸው ተብሎ ሊወሰን የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም ለክርክሩ መነሻ የሆነው በኮንትሮባንድ ወንጀል ተያዘ የተባለው ቡና አንደኛ ተጠሪ በአደራ ስለመረከባቸው እና በዚህ መሠረት መልሰው ባለማስረከባቸው በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሠው ጥፋተኛ የተባሉበት የፍ/ቤት ውሣኔ በሰነድ ማስረጃነት አመልካች አቅርቦ እያለ የሰው ምስክሮችን ቃል እና ሙሉ በሙሉ መደምደሚያ ላይ ሊያደርስ የማይችል የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት መግለጫ ብቻ ነጥሎ በመመዘን በ17/03/1989 ዓ.ም. ተደረገ የተባለውን የአደራ ውል ሰነድ ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎች ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ የማስረጃ አቀባበልና አመዛዘን ሥርዓትን ያልተከተለ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በዞኑ ማዕከላዊ ፍ/ቤት ጥቅምት 20 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጥቶ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22296 ጥር 28 ቀን 2000 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች 71 /ሰባ አንድ/ ኩንታል ቡና እንዲያስረክቡ ወይም በአማራጭ ብር 170,400.0000 /አንድ መቶ ሰባ ሺህ አራት መቶ ብር/ እንዲከፍሉ ብለናል፡፡
3. ሁለተኛ ተጠሪ ለባለገንዘቡ አመልካች የሚገደዱት ባለዕዳ አንደኛ ተጠሪ ግዴታቸውን መወጣት ያልቻሉ እንደሆነ ብቻ ነው ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 37163

ታህሳስ 23 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን - ነ/ፈጅ ዘመድ ገ/አምላክ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ህያብ ገ/መድህን ብረታ ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ - ጠበቃ ሰሞን ባርናባስ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ጨረታን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ኀዳር 04 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ የአሁኑ አመልካች የተገለገለባቸውን ብረት ነክ የሆኑ የተለያዩ ንብረቶችን ለፈላጊዎች በጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ በአወጣው የጨረታ ማስታወቂያ መሰረት ዝርዝር መመሪያውን በማንበብ በጨረታ የሚሸጡትን ንብረቶች በጠቅላላ የሚገዛበትን ዋጋ በማቅረብ እና ድርጅቱ በተለየ መልኩ በድርድር ንብረቶችን የመሸጥ ሐሣብ ካለው በመደራደር ለመግዛት ፍላጐት ያለው መሆኑን በመግለጽ በተጠሪ ስም በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ ለጨረታው በተከፈተው ሣጥን ማስገባቱን ጨረታው በይፋ በተከፈተበት ቀንም በመደራደር ተጠሪ የተሻለ ዋጋና የድርድር ሃሣብ በማቅረብ ተመርጦ ከጨረታው ኮሚቴ ጋርም በመደራደር ለጨረታው የቀረቡትን ንብረቶች በብር 200.000/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ለመግዛት ስምምነት ተደርሶ ኮሚቴው ቃለ ጉባኤ ይዞ ግኘው ፀድቆ ለስራ አስኪያጅ ለፊርማ ከቀረበ በኂላ ጨረታው ውድቅ ነው ተብሎ እንደገና እንዲካሄድ በማለት ስራ አስኪያጁ የጨረታ ውጤቱን መሰረዛቸውን ዘርዝሮ የጨረታው ኮሚቴ በወሰነው መሰረት የተጫረተውን፡፡ ንብረት አመልካች እንዲሸጥና ኪሣራና ወጪ እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ የዳኝነት ጥያቄ በዞን ሦስት ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በፍ/ቤቱ በተደረገለት ጥሪ መሰረት ቀርቦ ህዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በዋና ዳይሬክተሩ አማካኝነት መከላከያ መልሱን አቅርቧል፡፡ በመከላከያ መልሱም በጨረታው ላይ የተከሰቱት ጉድለቶች ምን እንደሆኑ በመዘርዘር በእነዚህ ምክንያቶች ጨረታው የተሰረዘ መሆኑንና በስራ አስኪያጁ ባልፀደቀ የጨረታ ውጤት ክስ ሊቀርብ የማይችልበት ስለመሆኑ ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ተጠቃሹ ፍ/ቤትም የጨረታ ኮሚቴ አባላትንና የአመልካችን መ/ቤት የሕግ ክፍል ባልደረባን በምስክረነት ከሰማ በኂላ ለጨረታ የቀረበው ንብረት ለተጠሪ በድርድር መሸጡን ኮሚቴው ገልጾ ያቀረበው የውሣኔ ሐሣብ በአመልካች መ/ቤት ስራ አስኪያጅ ባይፀድቅም ሽያጩ ተግቢነት ያለው ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት በኮሚቴው በተሰጠው የውሣኔ ሐሣብ የአሁኑ አመልካች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተጠሪ ብሩን ከፍሎ ንብረቶችን እንዲያነሣ ወጪና ኪሣራ በድምሩ ብር 5850.50(አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ብር ከሃምሳ ሣንቲም) እንዲከፈለው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ቅሬታውን ለአፋር ቤሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሚያዝያ 13 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልባቸውን ምክንያቶች ዘርዝሯል፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል

በመባሉ ተጠሪ እንዲቀርብ ተደርጐ ግንቦት 22 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልስ ተሰጥቷል፡፡ አመልካችም ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልስ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር ተጠናቅቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የጨረታ ኮሚቴ ተጠሪን የጨረታ አሸናፊ በማድረግ የወሰኑት የውሳኔው ሐሣብ በአመልካች መ/ቤት ስራ አስኪያጅ ሣይፀድቅ እንደ በመጨረሻ ውሣኔ ተደርጐ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ የሚለው ጭብጥ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ተጠሪ የጨረታ ዋጋ ሣይገልጽ የጨረታው ተሣታፊ ሆነው ጨረታው በኋላ ግን ከባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የጨረታ ኮሚቴ ጋር በመደረራደር ጨረታውን በብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ እንደአሸነፈ ተገልጾ የጨረታው ኮሜቴ የውሣኔ ሐሣብ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ቀርቦ አለመጽቁን ነው፡፡

በመሰረቱ ማንም ሰው ሐብቱን በሐራጅ የሚሸጥ መሆኑን ባስታወቀ ጊዜ ውል ተፈፀመ ለማለት የሚቻለው በመጨረሻው ሐራጅ ለጨረታ የቀረበው ሐብት ለዋጋ አቅራቢው የተሰጠ ጊዜ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1688/2/ የተደነገገ ሲሆን የጨረታ ሥነ ሥርአትን በሚደነግግት የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ አስራ ዘጠኝ ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መካከልም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3167/1/ አሸናፊ የሆነውን ተጫራች ለጊዜው ጽ/ቤቱ ቢመረጥ ውሉ እንደተፈጸመ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1688/2/ ድንጋጌ ከፍ/ህ/ቁ. 3168 ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲታይም የጨረታውን ሥርአት ያስፈፀመው ያስተዳደር መ/ቤት የጨረታውን ውጤት በመቀበል ውሉን ፈጽሟል ሊባል የሚችለው የማጽደቅ ሥራ ከተደረገ በኋላ ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የመንግስት መ/ቤት እንደመሆኑ መጠን የግዥ፣ የሽያጭና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮችን የመንግስት የፋይናንስ አዋጅ ፣ደንብና መመሪያን መሰረት በማድረግ የሚፈጽም መሆኑ የግድ ነው፡፡ የመንግስትን የፋይናንስ አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት አድርጐ ተፈፀመ የሚባል የግዥም ሆነ የሺያጭ ስራ ስራውን እንዲያከናውን የተቋቋመው ኮሜቴ የራሱን የውሳኔ ሐሳብ ገልጾ ለመ/ቤቱ የበላይ አላፊ አቅርቦ ተገቢ ከማስወሰን ባለፈ የጨረታን ውጤቱን በተመለከተ የመጨረሻ ውሣኔ መስጠት አይችልም፡፡ የጨረታውን ውጤት በተመለከተ የመጨረሻ ውሣኔ የመስጠት ሕጋዊ ስልጣን የመ/ቤቱ የበላይ ሐላፊ ነው፡፡ የጨረታ ኮሚቴ የሚያቀርበው የውሣኔ ሐሣብ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሊሰረዝ፣ ሊሻሻል ወይም ሊፀድቅ ይችላል፡፡ በመሆኑም የኮሚቴው የውሣኔ ሐሣብ ውል እንደተፈፀመበት የሚቆጠረው በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተቀባይነትን አግኝቶ አሸናፊው ተጫራች ተለይቶ ሲጸድቅ ብቻ ነው፡፡ ህግም ጥበቃ የሚያደርገው በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የፀደቀውን የጨረታ ውጤት እንጂ የኮሚቴውን የውሳኔ ሐሣብ አይደለም፡፡ የኮሚቴው የውሣኔ ሐሣብ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ከመጽደቁ በፊት ለጊዜው ለተለየው አሸናፊ መብትና ጥቅም ሊያሰጥ አይችልም፡፡

በያዝነው ጉዳይ የጨረታው ኮሚቴ ባቀረበው የውሣኔ ሐሣብ ተጠሪን የጨረታው አሸናፊ አድርጐ ተጠሪ የተመረጠበትን ምክንያት ጭምር በመግለጽ ለመ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ቢያቀርብም ሥራ አስኪያጁ በጨረታው ላይ የተከሰቱ ጉድለቶ አሉ በሚል ምክንያት የኮሚቴውን የውሣኔ ሐሣብ አለማጸደቃቸው ተረጋግጧል፡፡ እንዲህ ከሆነ የስራ አስኪያጅ ስራ ተገቢ አይደለም ከተባለ ለሚመለከተው የበላይ የአስተደደር አካል ጥያቄ በማቅረብ ተገቢውን ምላሽ ከማግኘት በስተቀር መብትና ጥቅም ሊሰጥ የሚችል ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግንኙነት ሣይኖር መደበኛ ክስ በፍ/ቤት የሚቀርብበት አግባብ የለም፡፡ ሥራ አስኪያጁ በህጉ አግባብ አልሰሩም ከተባለ የመንግስት የፋይናንስ አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት ተገቢውን አስተዳደራዊ መፍትሔ ከመጠየቅ በስተቀር ከወዲሁ የፍትሐብሔር ክስ የሚቀርብበት ሥርአት አለ ለማለት ስለማይቻል ተጠሪ የስራ አስኪያጁ አድራጐት ሥርአት የለሽ አሰራርን ያሰፍናል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ የጨረታው ኮሚቴ የውሣኔ ሐሣብ እንደመጨረሻ ውሣኔ ታይቶ አመልካችን ለመክሰስ የሚያስችል ከህግ ወይም ከውል የመነጨ መብት የማይሰጥ በመሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠ ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በዞን ሦስት ከፍተኛ ፍ/ቤት ታህሳስ 03 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በአፋር ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 1017 ሚያዝያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ ጋር በህጉ አግባብ የፈፀመው የጨረታ ውል ስለሌለ ለጨረታ የቀረቡትን ንብረቶች ለተጠሪ እንዲያስረክብ የሚገደድበት ህጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 38794

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ ሙከሚል መሐመድ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ሚፍታህ ከድር - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ አመልካች ታህሣሥ 03 ቀን 1994 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ ከአሁኑ ተጠሪ ጋር የንግድ ግንኙነት እንደነበራቸው፣ በመካከላቸው የተፈጠረውን ያለመግባባትም በስምምነት ለመፍታት ተስማምተው ሽማግሌዎችን መምረጣቸውንና የተመረጡት ሽማግሌዎችም ህዳር 08 ቀን 1990 ዓ.ም ውሣኔ መስጠታቸውን፣ በውሣኔው መሠረትም የጋራ ንብረት ክፍፍል ተፈጽሞ ቀሪ ብር 170,122.75 /አንድ መቶ ሰባ ሺህ አንድ መቶ ሃያ ሁለት ብር ከሰባ አምስት ሣንቲም/ ከአሁኑ ተጠሪ የሚፈለግና ለአመልካች የሚከፈል መሆኑ ተገልፆ በሽማግሌዎች ቢወሠንም ተጠሪ ሊከፍሉ አለመቻላቸውን በመዘርዘር ተጠሪ እንደውሣኔው እንዲፈጽሙላቸውና ወጪና ኪሣራ የመጠየቅ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ዳኝነት ጠይቀው በተጠሪ ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት የአፈፃፀም ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በፍርድ ተከሣሽነት ቀርበው ከአመልካች ጋር በግልግል ወይም በሽምግልና ዳኝነት ለመዳኘት የተደረገ የግልግል ስምምነትም ሆነ የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ያለመኖሩን፣ የተደረገውም ስምምነት የእርቅ ውል ስምምነት መሆኑን፣ የእርቅ ስምምነቱ ውሣኔ ከተባለም የግልግል ቃሎችን በጽሑፍ ስላላረጋገጡ የማይገደዱ መሆኑን፣ አስታራቂ ሽማግሌዎችንም የማያውቋቸው፣ የእርቅ ስምምነቱም ጉድለት ያለበት መሆኑን እንዲሁም በ23/02/90 ዓ.ም በተደረገው ስምምነት ባለጉዳዮችን ለማስታረቅና ለማግባባት ተገልፆ እያለ ወደ ግልግል ወይም የሽምግልና ዳኝነት መሄዱ ሕጋዊነት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው ሊፈፀም የሚችል ውሣኔ የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመርና ምስክሮችን በመስማት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ስምምነት እርቅ /conciliation/ መሆኑንና የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3322/2/ በሚያዘው መሠረት የግልግል ቃሎችን የሚያረጋግጥ የጽሑፍ ግዴታ አለመኖሩን ጠቅሶ የአፈፃፀሙን ክስ ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔን አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 3 /ሦስት/ ገጽ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የቤተዘመድ የሽምግልና ጉባዔው ያከናወነው ስራ በግራ ቀኙ በ23/02/90 ዓ.ም በተደረገው ስምምነት መሠረት የግልግል ሁኖ እያለ የእርቅ ስራ ነው መባሉ ስለእርቅና ግልግል የተደነገጉ ድንጋጌዎችን ባላገናዘበ መልኩ መሆኑን የሽምግልና ዳኝነቱ የተሰጠውም የግራ ቀኞችን ማስረጃ መሠረት አድርጎ ሁኖ እያለና ይኸው አካል በጥብቅ የፍ/ቤቶችን የዳኝነት አሠጣጥ ሥርዓት እንዲከተል የሚያዝ ሕግ ሣይኖር የሽምግልና ዳኝነቱ የፍ/ቤቶችን የዳኝነት አካሄድ ያልተከተለ ነው የተባለው ያላግባብ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሸሮ በቤተዘመድ ሽምግልና ጉባዔ ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀም ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተደምጧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበትና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረውም አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ ውድቅ የተደረገው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ጥቅምት 23 ቀን 1990 ዓ.ም የተደረገ ስምምነት መኖሩን፣ ከዚህ ስምምነት በኋላም ህዳር 08 ቀን 1990 ዓ.ም የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባዔ ውሣኔ መስጠቱን ነው። ስምምነቱ መኖሩን በተመለከተ የስር ፍ/ቤትም ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን ከውሣኔው ግልባጭ ተመልክተናል። የስር ፍ/ቤት የጥቅምት 23 ቀን 1990 ዓ.ም ስምምነት እና የህዳር 08 ቀን 1990 ዓ.ም በሽምግልና ጉባዔ አባላት ተሰጠ የተባለ ውሣኔ መኖሩን አምኖ ለጉዳዩ እልባት የሰጠው በሽማግሌዎች ተሰጠ የተባለው ውሣኔ የግልግል ስምምነት /arbitration/ ሣይሆን የግልግል እርቅ /conciliation/ ሆኖ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2322/2/ የተመለከተውን ድንጋጌ ያላሟላ ነው በሚል ምክንያት ነው።

በመሠረቱ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ተብለው በአብዛኛው ከሚታወቁት መንገዶች መካከል ድርድር /conciliation/፣እርቅ /mediation/ ግልግል /arbitration/እና ስምምነት /Negotiation/ የሚጠቀሱ ሲሆን በሀገራችን ከሚሠሩት የሽምግልና ዓይነቶች ውስጥ ድርድር፣ ግልግልና እርቅ ይገኙበታል። የስር ፍ/ቤት ለጉዳዩ እልባት ሲሰጥ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባቸው የሽምግልና ዓይነቶች ድርድር /conciliation/ እና ግልግል /arbitration/ ስለሆነ እነዚህ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች በፍትሐብሔር ሕጉና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ያላቸውን ትርጉምና አፈፃፀም መመልከቱ ተገቢነት አለው።

ድርድር /conciliation/ የሚባለው የሽምግልና ዘዴ 3ኛ ወገን ባለበት ግራ ቀኙ ወገኖች የሚደራደሩበት መንገድ ሲሆን 3ኛ ወገን ከመታዘብ በስተቀር በድርድሩ ጣልቃ አይገባም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 3318 - 3324 የተመለከቱት ድንጋጌዎችም የሚገዙት ይህንኑ ነው ግልግል /arbitration/ የሚባለው የሽምግልና ዘዴ ደግሞ ግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን ለ3ኛ ወገን አቅርበው የግልግል ዳኛው የሚሰጠውን ውሣኔ የሚቀበሉበት መንገድ ነው። በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3325 - 3346 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎችና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315 - 319 እና 350 - 357 የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ስለግልግል አደራረግና አፈፃፀም የሚገዙ ናቸው ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ በሕጉ አግባብ የተደረጉ የግልግል ስምምነቶች ሊፈፀሙ የሚችሉ ስለመሆኑ ነው። በፍ/ብ/ህ/ቁ. 3325- 3346 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በተለይ ሲታዩም የግልግል ስምምነቶች እንደ ልዩ ውሎች ሊታዩ የሚገባ መሆኑን ያስገነዝባሉ።

ስለግልግል ትርጉም የሚያስቀምጠው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3325 ግልግል ውል ስለመሆኑ ያሣያል። ውል ግዴታዎች የሚቋቋሙበት፣ የሚለወጡበት ወይም ቀሪ የሚሆኑበት ስምምነት እንደመሆኑ መጠን ውል ስለመኖሩ መሟላት የሚገባቸው ነገሮች /elements/ በግልግል ስምምነትም /arbitral submission/ ተሟልተው ሊገኙ ይገባል በመሆኑም የግራ ቀኙ ወገኖች ችሎታ፣ የግልግሉ ጉዳይ ሕጋዊነት እና በሕጉ የሚፈለግ ከሆነ ፎርም ተሟልተው መገኘት የግልግሉን ስምምነት መኖሩን የምናረጋግጥባቸው ጉዳዮች ናቸው ስለሆነም በግልግል የሽምግልና ዘዴ ቀዳሚው እርምጃ ግራ ቀኙ በሕጉ ፊት የሚፀና /valid/ የግልግል ስምምነት ገብተው መገኘት ነው።

በሕጉ አግባብ በተደረገ የግልግል ስምምነት መሠረት የግራ ቀኙን ጉዳይ ክርክር የግልግል ዳኛ መመልከት ከጀመረ በኋላ ሊከተል የሚገባውን ሥነ ሥርዓት በተመለከተ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.3345 ድንጋጌ ያሣያል። የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 317/1/ ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ የግልግል ዳኛ ክርክሩን መምራት ያለበት በተቻለ መጠን የመደበኛ ዳኝነት አካሄድን ተከትሎ መሆኑን ይገልፃል። በዚህ ድንጋጌ መሠረት ተከራካሪ ወገኖች የመስማት፣ ማስረጃዎቻቸውን የማቅረብና የመጠየቅ መብታቸው ሊጠበቅ እንደሚገባ እና የዳኝነት አሠጣጥም በዚህ ረገድ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ሊከተል የሚገባው መሆኑን እንገነዘባለን። ይሁን እንጂ የግልግል ዳኛ የዳኝነት አካሄድ የመደበኛ ፍ/ቤት የዳኝነት አካሄድን መከተል ያለበት ቢሆንም እንደ መደበኛ ፍ/ቤት የዳኝነት አካሄድ እጅጉን የጠበቀ እንዲሆን የማይጠበቅ መሆኑን የተጠቃሹ ድንጋጌ መንፈስ ያስረዳል። በግልግል ዳኛ የሚሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 350 እና ተከታዮቹ መሠረት በበላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ቀርቦ እስካልተለወጠ ድረስ በመደበኛ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በሚፈፀምበት ሥርዓት ቀርቦ ሊፈፀም የሚችል መሆኑንም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3345/2/ ድንጋጌ ያስገነዝባል። በመሆኑም በግልግል ዳኛ የሚሰጥ ውሣኔ የመጨረሻ ነው የግልግል ውሉም ውል እንደመሆኑ መጠን በአግባቡ

እስከተቋቋመ ድረስ ተዋዋይ ወገኖችን የሕግን ያህል የሚያስገድድ፣ በቃላቸው እንዲታሠሩ የሚያደርግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3325' ን' ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731 ጋር አጣምረን ስንመለከት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የግልግል ውል አላደረግኩም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሌለና በግልጽ ያልተካደ ስለመሆኑና ይኸው ውል ስለመኖሩ የበታች ፍ/ቤትም ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ የግልግል ውሉ ጥቅምት 23 ቀን 1990 ዓ.ም ስለመደረጉና በአመልካች፣ በተጠሪና በአቶ ሱልጣን ሽኑሪ መካከል ንብረትንና ገንዘብን አስመልክቶ የተነሣውን አለመግባባት ለማስታረቅ ጉባዔዉ መቋቋሙን፣ ጉባዔው ያየውንና የወሰነውን ለመቀበል ተዋዋይ ወገኖች የተስማሙበት እንዲሁም ተዋዋይ ወገኖችና ሽማግሌዎቹ ፊርማቸውን ያኖሩበት ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ ህዳር 08 ቀን 1990 ዓ.ም የተሰጠው የግልግል ዳኞች ውሣኔም መሠረት ያደረገው ይህንኑ ውል ሁኖ ገንዘብና ንብረትን በተመለከተ ግራ ቀኙን ተዋዋይ ወገኖች በማስተማመንና በማጣራት የተዋዋይ ወገኖች ድርሻ ተለይቶ የተወሰነ መሆኑን ይገልፃል፡፡የስር ፍ/ቤት በ23/2/1990 ዓ.ም የተደረገው ሰነድ የእርቅ ስለመሆኑ አሽማጋይ የተባሉት ግለሰቦች መስክረዋል በማለትና የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3322/2/ ስር የተመለከተውን በመጥቀስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3318-3324 ስር በተመለከቱት የሚገዛ ሣይሆን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3325-3346 ባሉት ድንጋጌዎች የሚገዛ ስለመሆኑ በ23/2/1990 ዓ.ም የተደረገው የግልግል ውል ይዘቱ ያሣያል፡፡ የህዳር 08 ቀን 1990 ዓ.ም ውሣኔ የተሰጠውም ተዋዋይ ወገኖችን በማስተማመንና ተገቢው ማጣራት ተደርጎ መሆኑ የግልግል ዳኝነት በጥብቅ የፍ/ቤቶችን የዳኝነት ሥርዓት እንዲከተል ሕጉ የማይጠብቅ መሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 317 ከተመለከተው ድንጋጌ አኳያ ተዳምሮ ሲታይ ጉዳዩ በግልግል / arbitration / አልታየም ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም በአመልካችና በተጠሪ መካከል በ23/02/1990 ዓ.ም በተደረገው የግልግል ውል ሠነድ ላይ ግራ ቀኙ ያስሚሟቸው ሽማግሌዎች የሚወስኑትን እንደሚቀበሉ መስማማታቸውና ውሣኔ የማሣለፍ ሥልጣኑም ለሽማግሌዎች የሰጡ መሆናቸው ተገልፆ እያለ የስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው እርቅ /conciliation/ እንጂ ግልግል /arbitration/ አይደለም በማለት ተጠሪ በሽማግሌዎቹ የተወሰነውን ገንዘብ ለአመልካች ሊከፍሉ አይገደዱም ሲል የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 3325- 3346 እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315-319 እንዲሁም ከቁጥር 350-357 ድረስ የተመለከቱትን ለማስረጃነት ከቀረበው ሰነድ ይዘት ጋር ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1/ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00136 መስከረም 30 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 60538 ሚያዝያ 09 ቀን 2000 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ ተጠሪ በሽማግሌዎቹ የተወሰነውን ገንዘብ ብር 170,122.75 /አንድ መቶ ሰባ ሺህ አንድ መቶ ሃያ ሁለት ብር ከሰባ አምስት ሣንቲም/ ለአመልካች እንዲከፍሉ ሊገደዱ ይገባል ብለናል፡፡

3/ የፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔውን እንዲያስፈጽም ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

4/ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ 39529

ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሀጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ቦሌ ክ/ከተማ የመሬትና ልማት አስተዳደር ነ/ፈ ደረጀ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ ግምጃ በዳኔ - በራሳቸውና ሞግዚት በሆኑላት በህፃን ብሩክ ባጫ ስም ወኪል ብርቱካን ባጫ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሮማን ባጫ

3. ወ/ሮ ብርቱካን ባጫ

4. አቶ አሸናፊ ባጫ

5. ወ/ሪት መቅደስ ባጫ

6. ወ/ሮ ፋንቱ ባጫ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር አንደኛ ተከሣሽ ተጠሪ ከሣሽ ነበሩ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ አንደኛ አመልካች በተጠሪዎች እና በስር ሁለተኛ ተከሣሽ ሥም ካርታ ሰርቷል ተጠሪዎች ካርታውን ለመውሰድ ሲፈርሙ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ለመፈረም ፍቃደኛ አልሆኑም፡፡ በመሆኑም አመልካች ተሰርቶ የተቀመጠውን ካርታ ይስጠን፣ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ቀርበው እንዲፈርሙ ይወሰንልን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

አንደኛ አመልካች በቀጠሮ ቀን መልሳቸውን ባለማያያዛቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፎ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ መልስ ሲሰጡ (በፍሬ ጉዳዩ) በግሌ የሰራሁት የቤት ቁጥር 2026ን በቤት ቁጥር 443 ጋር ካርታው ስለተሰራ ለመፈረም አልገደድም፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር አግባብ ካለው ሕግና ከቀረበለት ማስረጃ አንፃር መርምሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በውሣኔውም የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ቀርበው የመፈረም ግዴታ እንዳለባቸው ተጠሪዎች በማስረጃ አላቀረቡም ስለዚህ ጥያቄውን ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም፡፡

አመልካች በሕግ ካርታ የመስጠት ሥልጣንና ግዴታ አለበት በዚህም የተነሣ ካርታ የሚጠይቀውን ወገን መብት አረጋግጦ ሲቀርብ አጣርቶ ካርታ የመስጠትም ሆነ የመከልከል ግዴታ የአመልካች ነው ተጠሪዎች የሟች ሚስትና ወራሽ መሆናቸውን በሟች ንብረት ላይ መብት እንዳላቸው አረጋግጠው ካርታ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን ጥያቄ በመቀበል ተጠሪዎች መብት ያላቸው መሆኑን አጣርቶ ካርታ ሊሰጣቸው ወይም የማይፈቀድበትን ምክንያት በመግለፅ ውሣኔ ሊሰጥ ይገባል ስለዚህ አመልካች የተጠሪዎችን ጥያቄ ተቀብሎ ክስ በቀረበበት ቤት ላይ መብት ካላቸው ካርታ እንዲሰጣቸው ሲል ወሰነ፡፡

አመልካችም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 18/2000 ባቀረበው አቤቱታ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ እና በፌዴራሉ ከ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል ሲል ጠይቋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ላይ መብት ካላቸው አመልካች ካርታ ይሠጣቸው ተብሎ የመወሰኑ አግባብነት በመመርመር ነው፡፡

በዚህም መሠረት ይህን ነጥብ የግራ ቀኙ ወገን ካሰሙት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ ባጭሩ ስናይ ተጠሪዎች በተሠጣቸውና በሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ስም በአመልካች ካርታ ተሰርቶላቸው እያለ ተጠሪዎች ካርታውን ፈርመው ለመውሰድ ፍቃደኛ ሲሆኑ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ካርታው የእኔ የግሌ የሆነውን ቤት አካቶ የተሰራ ስለሆነ ልፈርም አልገደድም ሲሉ ፍቃደኛ ያለመሆናቸውን በመግለፃቸው ምክንያት በቀረበው ክስ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ካየ በኋላ ተጠሪዎች መብት ካላቸው አመልካች ካርታ ይስጣቸው በማለት ወስኗል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤትም ጉድለት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

በእኛም በኩል ከሥር ፍ/ቤት የውሣኔ ሐተታ ልንገነዘብ እንደቻልነው አመልካች መብታቸውን አረጋግጦ የቀረቡለትን ወገኖች በእኩል የማስተናገድና አግባብ ያለው ምላሽ ሊሰጥ እንደሚገባው ገልጿል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ አመልካች በሕግ የተቋቋመ አስተዳደራዊ ተቋም በመሆኑ በሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ሐላፊነት መሠረት አገልግሎት የሚሠጥ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

እንግዲስ ከዚህ የአመልካች ሥልጣንና ተግባር ስንነሳ ሁለት መብት አለን ብለው የሚቀርቡለትን ወገኖች ሊያስተናግድ የሚችለው ባለው ሕጋዊ አሠራር ብቻ መሆኑን እንረዳለን በዚህ በተያዘው ጉዳይም ተጠሪዎች መብት አለን በማለት ካርታው እንዲሠጣቸው ጠይቀዋል፡፡ በተነጻጻሪ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽም በጉዳዩ መብት አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ የተሰራው ካርታ መጠን የግሌን ቤት አካቷል በማለት ቀርበው ሊቀበሉ (ሊፈርሙ) ፍቃደኛ አልሆኑም በመሆኑም በአመልካች በኩል እነዚህን ወገኖች አለን በሚሉት መብት ለማስተናገድ ይህ የጋራቸው የሆነውን ንብረት መቀበል የሚችሉት ፈቅደው በአመልካች መ/ቤት ቀርበው ፈርመው ሲቀበሉ ብቻ ነው፡፡ አመልካች እነዚህን ወገኖች አስተዳደራዊ ተግባሩን ከመወጣት ባሻገር ሊያስገድዳቸው የሚያስችለው አሰራር የሌለው መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡ አመልካችም በክርክሩ እንደገለፀው በውሣኔ ተለይቶ ያልቀረበለትንና ሁለት ወገኖች መብት አለን ብለው ያቀረቡለትን ጉዳይ ሌላኛው ባለመብት ባልቀረበበትና ባልተስማማበት ለተጠሪዎች ብቻ አስፈርሞ መስጠቱ ሌላ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ተግባር ሊሆን ይችላል፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የሥር ሁለተኛ ተከሣሽን መብት ሣያገናዝቡ ተጠሪዎች መብት ካላቸው ካርታ ይሠጣቸው በማለት አመልካችን ማስገደዱ እና የፌ.ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ሣያርመው ማለፉ የአመልካችን አስተዳደራዊ ሥራ ላይ ጫና መፍጠር ነው፡፡

ባጠቃላይ ፍ/ቤቱም በጉዳዩ ስልጣን የለኝም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231 መሠረት መዝገቡን መዝጋት ነበረበት፡፡

በመሆኑም የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 99300 በቀን 27/5/2000 እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 65637 ቀን 24/08/2000 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ፍ/ቤቶች አመልካችን ካርታ እንዲሠጥ ሊያስገድዱ የሚችሉበት ሥልጣን የላቸውም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ይቻቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 40752

ሐምሌ 28 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሠ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች** ፡- እነ ወ/ሮ ኤክራም መሃመድ /2 ሠዎች/ - ጠ/አብደላ አሊ ቀረበ

**ተጠሪ** ፡- አቶ ዘኪ መሐመድ - አልተጠሩም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው በአፈፃፀም ጉዳይ ሊከፈል የሚገባውን የዳኝነት ገንዘብ የሚመለከት ነው፡፡

አመልካችና ተጠሪ በነበራቸው የውርስ ንብረት ክፍፍል ክርክር ጉዳያቸው በቤተ ዘመድ ሽምግልና ጉባኤ ከተወሰነ በኋላ አፈፃፀሙን በተመለከተ በፌ/ከፍተኛ ሸሪአ ፍ/ቤት አንስቶ እስከ ፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት ድረስ ደርሶ ውሣኔ አግኝቷል፡፡ ነገር ግን በፍ/ቤት በተሠጠው የአፈፃፀም ውሣኔ መሠረት ሊፈፀም ባለመቻሉ ግራ ቀኙ አፈፃፀሙን በተመለከተ ስምምነት አድርገው ስምምነቱን እንዲመዘግብላቸው የፌ/ከፍተኛ ሸሪአ ፍ/ቤት ጠይቀው ፍ/ቤቱ ጥያቄያቸውን ውድቅ በማድረግ የፌ/ጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤት በሠጠው ውሣኔ ኋላም የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ችሎት ባፀናው ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀምና የዳኝነት ብር 23,886(ሃያ ሦስት ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ስድስት) እንዲከፈል ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ለፌ/ጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤት ይግባኝ ጠይቀው ፍ/ቤቱም የፌ/ከፍተኛ ሸሪአ ፍ/ቤት ዕርቁን የማይመዘግብበት ምክንያት የለም በማለት ዕርቁን እንዲመዘግብ ሲወስን የዳኝነት እንዲከፈል የተሠጠውን ውሣኔ ግን አፅንቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካቾች ጥያቄም በህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 177/1945 አንቀፅ 2/ሠ/ መሠረት ግምቱ ከብር 10,000(አስር ሺህ) በላይ ለሆነ አፈፃፀም ጉዳይ ዳኝነት መከፈል ያለበት ብር 25.00(ሃያ አምስት) ብቻ ሆኖ ሣለ 23,886(ሃያ ሦስት ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስድስት) ብር እንዲከፈል መወሠኑ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም ለቀረበው የአፈፃፀም ክስ እንዲከፈል የተወሠነው ገንዘብ ህግን መሠረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሠበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ የቀረበው ጥያቄም የዳኝነት ገንዘብ አከፋፈልን በሚመለከት በመሆኑ ተጠሪው በተከራካሪነት መቅረብ የሚያስፈልጋቸው ሆኖ ባለመገኘቱ መዝገቡ ባለበት ሁኔታ ተመርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት እንደተረዳነው ለሠበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው የውርስ ንብረት ክፍፍልን አስመልክቶ የግልግል ዳኞች የሠጡት ውሣኔ እንዲፈፀም በቀረበ የአፈፃፀም ክስ ነው፡፡ ስለፍ/ቤቶች ዳኝነት ገንዘብ አከፋፈል የወጣው የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 177/1945 አንቀፅ 2/ሠ/ እንደሚያመለክተው ከብር 10,000 /አስር ሺህ/ በላይ ለሆነ የአፈፃፀም ክስ ሊከፈል የሚገባው በዳኝነት ገንዘብ ብር 25.00 /ሃያ አምስት/ ብቻ መሆኑን በግልፅ

ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ለቀረበላቸው የአፈፃፀም ክስ የፍ/ቤት ዳኝነት ገንዘብ አከፋፈል አስመልክቶ ከወጣው ህግ ውጪ ከፍተኛ ገንዘብ እንዲከፈል የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/ከፍተኛ ሽሪዓ ፍ/ቤት በመ/ቁ 1210/93 በ15/07/2000 ዓ.ም. እንዲሁም የፌ/ጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26/2000 በ7/11/2000 ዓ.ም. የዳኝነት ገንዘብ አከፋፈልን አስመልክቶ የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የአፈፃፀም ክስ ሲቀርብ የፍርድ ባለመብቱ ተገቢውን የአፈፃፀም ዳኝነት የከፈሉ በመሆኑ አመልካቾች ብር 23,886 /ሃያ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስድስት/ በድጋሚ ሊከፍሉ አይገባም ብለዋል፡፡
3. አመልካቾች የከፈሉት በተ.ቁ. 2 ሥር የተጠቀሰው ገንዘብ ለአመልካቾች ሊመለስላቸው ይገባል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሽ

የሰ/መ/ቁ. 40133

ሐምሌ 2 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት - አቶ ግሩም ሙላት - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** በሶማሌ ብ/ክ/መንግሥት የፊልቱ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ገቢዎች ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ አሊኑር አቤክር - ቀርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 20/2000 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታው የሶማሌ ብሔራዊ ክልልዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 145/99 ግንቦት 26/2000 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ የሊበን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. M105/02/07/99፣ ሰኔ 18/1999 ዓ.ም. የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተቀብሎ በማጽደቁ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለፈፀመ ፍርድ ይሻርልኝ በማለቱ ነው፡፡

በሥር ፍ/ቤቱ በተካደው ክርክር የአሁኑ ተጠሪ ከሣሽ፣ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ የነበሩ ሲሆን፣ ሥር ከሣሹ ያቀረበው ክስ አጭር ይዘቱ ተከሣሹ በፊደልቱ መጠጥ ውሀ ፕሮጀክት ስለሚያካሂደው ሥራ መክፈል የነበረበት ብር 183,744 /አንድ መቶ ሰማኒያ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ አርባ አራት ብር/ የሥራ ግብርና ሌሎች ተቀናናሽ ክፍያዎች ባለ መክፈሉ የልማት መስተጓጎል በማድረሱ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን በማስረጃነትም ተከሣሹ ቀደም ብሎ የተጠቀሰው የግብር አይነት ለወረዳው እየከፈለ እንደነበር የሚያሳዩ ደረሰኞች አቅርቧል፡፡ ሥር ተከሣሹም በበኩሉ በሰጠው መልስ የተጠቀሰው የግብር ዓይነት ለወረዳው /ለክሳሹ/ እየከፈለ ቢቆይም የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ለክልሉ ባስተላለፈው ትእዛዝ መሠረት ግብሩን መክፈል ያለብኝ ለአገር ውስጥ ገቢ እንጂ ለከሣሽ እንዳልሆነ በማወቁ መክፈሉን አቋርጫለሁ፤ ስለሆነም ከሣሽ ያቀረበብኝ ክስ በማይመለከተው ጉዳይ ስለሆነ ውድቅ ይደረግልኝ ብሏል፡፡ ከመልሱ ጋር በማያያዝም ጉዳዩን በሚመለከት የተፃፉ የተለያዩ ደብዳቤዎችና የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ አቅርቧል፡፡

የሥር ፍ/ቤቱም ከላይ በተቀመጠው መልኩ ለቀረበለት ክርክር እልባት ለመስጠት አከራካሪው የሥራ ግብር ለማን መከፈል አለበት የሚል ጭብጥ በመያዝ በሰጠው ፍርድ ምንም እንኳ ተከሣሹ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት እንደሆነና በአዋጅ ቁጥር 33/1985 አንቀጽ 5/2/ሐ/ መሠረትም የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶች አከራካሪውን ግብር ለአገር ውስጥ ገቢ መክፈል እንዳለባቸው ቢገልጽም ድንጋጌው በፌዴራል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 96/3/ም በአዋጅ ቁጥር 33/85 አንቀጽ 4 የተቀመጡትን መርሆዎች መሠረት ባደረገ ሁኔታ የተቀረፀ አይደለም፤ ማለትም ግብሩ ገቢ መሆን ያለበት የገቢው ምንጭ ለሆነው ወረዳ ስለሚገልጹ በአዋጅ ቁ. 33/85 አንቀጽ 5/2/ሐ/ የተመለከተው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከሣሹ የተከሰሰበትን ጠቅላላ ብር 183,744 /አንድ መቶ ሰማኒያ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ አርባ አራት ብር/ የሠራተኞች የሥራ ግብር እንዲሁም ብር 7000 /ሰባት ሺህ/ የዳኝነት ገንዘብ በአጠቃላይ ብር 190,744 /አንድ መቶ ዘጠና ሺህ ሰባት መቶ አርባ አራት ብር/ ለከሣሹ መክፈል እንዳለበት ወስኗል፡፡

ሥር ተከሣሹም የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት መሆኑ በመግለጽ የሰበሰበውን የሥራ ግብር በአዋጅ ቁ. 33/85 አንቀጽ 5 መሠረት ገቢ ማድረግ የሚገባው ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ መሆኑ በግልጽ እየታወቀና የሶማሌ ክልል

የገቢዎች ቢሮ በቁ. ኤክስኦ/ ኦኦጀ/3442/3002 በቀን 09/5/99 ዓ.ም. የፃፈውን ደብዳቤ ወደ ጎን በመተው ተገቢ ያልሆነ ትርጉም በመስጠት ግብሩ ለከሳሹ እንድከፍል መወሰኑ ተገቢነት የለውም በማለት ለሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢልም ፍ/ቤቱ በፍ/ይ/መ/ቁ. 145/99፣ ግንቦት 26/2000 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ ግብሩን እንዲከፍሉ የተደረጉት የይግባኝ ባይ ሠራተኞች የሶማሌ ክልል ተወላጆች በመሆናቸው፣ በጀቱም የክልሉ በመሆኑ እና የሥራ ቦታውም በሶማሌ ክልል ውስጥ በመሆኑ የሚሉትን ምክንያቶች በማስቀመጥ አከራካሪው የሥራ ግብር ገቢ መሆን ያለበት ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ሳይሆን ለክልሉ /ለከሣሹ ወረዳ/ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቶታል፡፡

ከላይ የሰፈረውን ፍርድ በመቃወምም አመልካች ሰኔ 20/2000 ዓ.ም. የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፤ መሠረታዊ ይዘቱም አመልካች በፌዴራል የልማት ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ቁ. 109/96 የተቋቋመ የልማት ድርጅት መሆኑ እና የሠራተኞችን ደሞዝና ሌሎች ተቀናናሾች ግብር ለፌዴራል ሃገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን የሚከፈለውን ክፊያ በሶማሌ ክልላዊ መንግሥት ለፊደልቱ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ገቢዎች ቢሮ ክፍያውን እንዲፈፀም የሥር ፍ/ቤቶቹ ውሣኔ መስጠታቸው የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 96/3/ እና አዋጅ ቁ. 33/85 አንቀጽ 5/2/ሐ/ ያሰፈሩትን መርህ በመፃረር ስለሆነና ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የሕግ ስህተቱን ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ ፍ/ቤትም አከራካሪው የሠራተኞች ግብር መከፈል ያለበት ለማን መሆኑ አከራክሮ ለመወሰን ሲል ጉዩን ወደ ሰበር ችሎት ያስቀረበው ሲሆን ግንቦት 13/2001 ዓ.ም. ግራ ቀኙ ወገኖች የቃል ክርክር አድርገዋል፣ በተጨማሪም ተጠሪው ግንቦት 14 ቀን 2001 ዓ.ም. የተፃፈ የጽሁፍ መልስ እንዲያቀርብ ተደርጓል፤ አመልካቹ በቃል ክርክሩ ያሰፈረው ሃሣብ በሰበር አቤቱታው ከዘረዘረው የተለየ ባለመሆኑ ደግሞ መዘርዘር ሳያስፈልግ ታልፏል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪው በቃልም ሆነ በጽሁፍ በሰጠው መልስ አመልካቹ የፌዴራል ተቋም ስለመሆኑ ያስረዳበት ሁኔታ የለም፤ የሥር ፍ/ቤቶቹ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 96/3/ ይዘት አላዛቡም፤ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 97/1/ መሠረት ግብርና ቀረጡ የመሰብሰቡ ስልጣን የእኔ ነው፤ ሕገ-መንግሥቱም ሆነ አዋጅ ቁ. 33/1985 እንዲሁም መመሪያዎች ከወረዳው ሠራተኞች የተሰበሰበው የሥራ ግብር መከፈል ያለበት ለወረዳው እንደሆነ የሚደግፉ እንጂ የሚፃረሩ አይደሉም፤ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 100/1/ እና አዋጅ ቁ. 33/85 እራስን በራስ ከማስተዳደር ትርጉምና ዓላማ ጋር ተያይዘው ሲታዩ የክልሎች ሕልውና መሠረቱ የክልሉን ገቢ መሰብሰብና ማስገባት በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶቹ የሰጡት ትርጉም ተገቢ ነው፤ የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ለሶማሌ ክልል፣ ለፊደልቱ ወረዳ ፋይናንስ ቢሮ አስተላለፈ የተባለው መመሪያ ሕገ-መንግሥታዊ ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ ሊቀበለው አይገባም፤ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶቹ ውሣኔ ይጽናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

እንግዲህ የግራ ቀኙ ወገኖች የክርክር አመጣጥ ከላይ ተዘርዝሮ የተቀመጠውን ሲመስል፣ ይህ ፍ/ቤትም፣

1. አመልካቹ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት ነው? ወይስ አይደለም?
2. አመልካቹ ከሠራተኞቹ የሰበሰበው የሥራ ግብር ገቢ መሆን ያለበት ለፌዴራል መንግሥት አገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ነው? ወይስ ለተጠሪው?

የሚሉትን መሠረታዊ ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪው በዚህ ሰበር ችሎት ባደረገው ክርክር አመልካቹ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት መሆኑን የሚያስረዳለት ማስረጃ አላቀረበም ብሏል፡፡ ይህ ክርክር የተነሳው አሁን እንጂ በሥር ፍ/ቤቶቹ ባካሄዱት ክርክር ያልተነሣ ነው፤ ይሁን እንጂ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 109/1996 አመልካቹ የፌዴራሉ መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ እንደ ተቋቋመ በግልጽ የሚታወቅ ነው፤ ስለሆነም አመልካቹ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረበም በማለት ተጠሪው በዚህ ችሎት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

ሁለተኛው ጭብጥ በሚመለከት ደግሞ ተጠሪው በአመልካቹ ላይ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ቀደም ብሎ ሲያደርገው እንደነበር አመልካቹ ከሠራተኞቹ የሚሰበስበውን የሥራ ግብር ለእኔ ገቢ ሊያደርግልኝ ይገባል ሲል አመልካቹ በሰጠው መልስ ደግሞ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት መሆኑን በማስመር በአዋጅ ቁጥር 33/1985 አንቀጽ 5/2/ሐ/ መሠረት የሰራተኞቹ የሥራ ግብር ገቢ የማድረግ ግዴታው ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ እንጂ ለተጠሪው እንዳልሆነ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪውም አዋጅ ቁጥር 33/1985 አንቀጽ 5/2/ሐ/ ከሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 97 እና 100

ከሰፈሩት የክልሎች ሥልጣንና መርሆዎች የማይጣጣም ነው በማለት በወረዳ ውስጥ ለሚከናወን የክልል ፕሮጀት እንዲሁም የወረዳው ነዋሪ ከሆኑ የአመልካቹ ሠራተኞች የሚሰበሰብ የሥራ ግብር ገቢ ማድረጉ ሕገ-መንግሥታዊ መብቱና የፌዴራል ሥርዓቱ መሠረት መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ አዋጅ ቁጥር 33/1985 አንቀጽ 5/2/ሐ/ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶች ከሠራተኞቹ የሚሰበስበው የሥራ ግብር ለፌዴራል መንግሥቱ ገቢ መሆን እንዳለበት በግልጽ አስፍሯል፤ ተጠሪው በዚህ ሰበር ችሎት ያደረገው ክርክር ሲታይም የዚህ አዋጅ /አንቀጽ/ ይዘት ካለመገንዘብ የሚመነጭ አይመስልም፤ የተጠቀሰው የአዋጁ አንቀጽ ከሕገ መንግሥቱ ጋር ተስማሚ አይደለም የሚል እንድምታ ያለው ክርክር እንደቀረበ ነው፤ የሥር ፍ/ቤቶቹም የተጠሪውን ክርክር እንዳለ በመውሰድ አዋጁ ተጠሪው ከመልካቹ አከራካሪውን ግብር እንዳይሰበስብ የመከልከል ብቃት የለውም በማለት ወስነዋል፡፡ ይሁን እንጂ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 97 የክልሎች የታክስና ግብር ስልጣን የሚመለከት ሲሆን በዚህ አንቀጽ ከሰፈሩት የክልሎች ስልጣናት ውስጥ የፌዴራል መንግሥቱ የልማት ድርጅቶች ከሰራተኞቻቸው የሚሰበስቡት የሥራ ግብር ገቢ የማድረግ መብት እንዳለባቸው አላሰፈረም፤ በአንፃሩ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 96/3/ እንደደነገገው ይህ አይነቱ ገቢ የፌዴራል መንግሥት ገቢ እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶች የሥራ ቦታ አድማስም የግድ የፌዴራል መንግሥቱ ከተሞች በሆኑት በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን እንዳግባብነቱ የሥራ አድማሱ በክልሎችም ውስጥ ሊከናወን የሚችል ነው፡፡ የሚቀጥሯቸው ሰራተኞችም የግድ በተጠቀሱት ከተሞች ብቻ የሚወሰን ሳይሆን እንደ ሁኔታው በተለያዩ ክልሎች ነዋሪና ተወላጅ የሆኑ ሠራተኞች ሊኖሯቸው እንደሚችል ነው፡፡ በሕገ- መንግሥቱ አንቀጽ 96/3/ እና በአዋጁ ቁጥር 33/1985 አንቀጽ 5/2/ሐ/ የተመለከተው ቁልፉ ነገር ሠራተኛው በፌዴራል የልማት ድርጅቱ ውስጥ የተቀጠረ ነው? ወይስ አይደለም? ከሚል ነጥብ አኳያ መታየት ያለበት ነው፡፡ የሠራተኛው የትውልድ ወይም የነዋሪነት ቦታ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በየትኛውም ክልል ወይም ከተማ ቢሆን ሠራተኛው የፌዴራል መንግሥቱ የልማት ተቋም በሆነ አካል ተቀጣሪ ከሆነ ከዚህ ሠራተኛ የሚሰበሰበው የሥራ ግብር በአዋጅ ቁ. 33/1985 አንቀጽ 5/2/ሐ/ መሠረት ገቢ የሚደረገው ለፌዴራል መንግሥቱ እንጂ ለክልሎች አይደለም፡፡ ይህ የገቢ ክፍፍል ስርዓትም በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 97 እና 100 ከተዘረዘሩት ስልጣናት መርሆዎች የሚጋጭ አይደለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶቹ አመልካቹ የሚያከናውነው ፕሮጀክት በተጠሪ ውስጥ በመሆኑ እና ሠራተኞቹም የወረዳው ነዋሪዎች ናቸው በማለት በአዋጅ ቁጥር 33/1985 አንቀጽ 5/2/ሐ/ የሰፈረውን ድንጋጌ በሚመለከት የሰጡት ትርጉምና የደረሱበት ድምዳሜ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፤ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 145/99፣ ግንቦት 26/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የሊበን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. M105/02/07/99 ሰኔ 18 1999 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፤ ይፃፍ፡፡
2. አመልካቹ የፌዴራሉ መንግሥት የልማት ተቋም በመሆኑ ከሠራተኞቹ የሚሰበስበውን የሥራ ግብር ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ለፌዴራሉ መንግሥት እንጂ ለተጠሪው አይደለም ብለናል፡፡
3. ኀዳር 17 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተላለፈው እግድ ተነስቷል፣ ይፃፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
5. ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፤ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

# አሰሪና ሠራተኛ

የሰ/መ/ቁ. 41385

ጥቅምት 3 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- ጊጋ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር - ሰላማዊት አስደግድግ

**ተጠሪዎች**፡- 1. ተረፈ ዘርጋው - ቀረበ

2. ፀጋዬ ደበበ - ቀረበ

3. ገመቹ ኡርጋ - ቀረበ

4. በቀለ መኰንን - አልቀረቡም

5. ዑመር መሐመድ - ቀረበ

6. ተስፋዬ ገረመው - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኞች መካከል የተነሳውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩት ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት አመልካች በሚያካሂደው የሕንፃ (ኮንስትራክሽን) ስራ በአናፂነት፣ በብረት ስራ እና በፌራዮ ስራ ሲሰሩ መቆየታቸውን ገልጸው አመልካች ከሕግ አግባብ ውጪ የስራ ውላቸው ስላቋረጠባቸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው በመጠየቅ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው በአገሪቱ ባጋጠመው የግንባታ እቃዎች (ብረትና ሲሚንቶ) እጥረት መሆኑን በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ ተጠሪዎችን ሲያሰናብት የጥሬ እቃው ሲገኝ ተመልሰው እንዲሰሩ በማስታወቂያ በመግለጽ እንደሆነም በመልሱ ላይ አመልክቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ስንብቱ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 30 መሰረት የሚደገፍ እንደሆነ ገልጾ መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡

ክሱን የሰማው ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ፣የግንባታ እቃዎች እጥረት አጋጥሞአል በሚል የተደረገ ስንብት በመሆኑ እርምጃው ሕገ-ወጥ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ተጠሪዎች የጠየቁትን ክፍያ በሙሉ እንዲያገኙ ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ህዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት የቀረቡት አንደኛ፣ሁለተኛ፣ ሦስተኛ እና ስድስተኛ ተጠሪዎች በተገኙበት ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አራተኛ እና አምስተኛ ተጠሪዎች በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ባለመቅረባቸው ክርክሩ እነሱ በሌሉበት ተሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጪ በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡

በግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እንደተገለጸው አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ስራ ተጠናቆአል በሚል ሳይሆን፣ለህንፃው ስራ አስፈላጊ የሆኑት የግንባታ እቃዎች እጥረት አጋጥሞአል በማለት ነው፡፡ ምክንያቱ ይህ በመሆኑም የግንባታ እቃዎቹ ተሟልተው ሲገኙ ተጠሪዎች ተመልሰው ሊሰሩ እንደሚችሉ በማስታወቂያ የገለጸላቸው ስለመሆኑ ተመልክቶአል፡፡ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የግራ ቀኝ ወገኖች ምስክሮች የተሰሙ ሲሆን፣ምስክሮቹ በሰጡት ቃልም በእርግጥ የተባሉት የግንባታ እቃዎች እጥረት ስለማጋጠሙ ተረጋግጦአል፡፡ በመሆኑም እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ይህን መሰል ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ አሰሪ ሰራተኞችን ቢያሰናብት እርምጃው ሕገ-ወጥ ነው የሚባልበት አግባብ ምንድነው? የሚለው ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው አምልካች የስንብት እርምጃ የወሰደው ከህንፃው ስራ ጠባይ በመነሳት የተወሰኑ ስራዎች ተጠናቅቀዋል በሚል አይደለም፡፡ ይህም ሆኖ ግን የህንፃውን ስራ ለማስቀጠል የማይችልበት ደረጃ ላይ ስለመገኘቱ አልተካደም (አላከራከረም)፡፡ በመሆኑም ስንብቱ በአዋጁ አንቀጽ 30 በተመለተው ድንጋጌ የሚሸፈን ነው የሚለው የአመልካቹ ክርክር መቀበል የሚቻል ባይሆንም፤ስራው በእርግጥ የለም(ቆሞአል) እየተባለ አመልካች የስንብቱን እርምጃ መውሰድ አልነበረበትም? የሚለው በስር ፍ/ቤቶች የተደረሰው ድምዳሜ ግን ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

በአሰሪ አነሳሽነት ስለሚደረግ የስራ ውል መቋረጥ በሚመለከት በአዋጁ ከአንቀጽ 26 እስከ 30 ባሉት ድንጋጌዎች በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ አሰሪው ማስጠንቀቂያ በመስጠት የስራ ውሉን የሚያቋርጥባቸው ሁኔታዎች በአንቀጽ 28 የተቀመጡ ሲሆን፣ከእነዚህም ውስጥ ከድርጅቱ ድርጅትዊ አቋም ወይም የስራ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የተቀመጠ ንኡስ አንቀጽ /2/ ይጠቅሳል፡፡ ሰራተኞች የተሰማሩባቸውን ስራዎች በከፊልም ሆነ በሙሉ በቀጥታና ለዘላቂታው የሚያስቆም የሰራተኞች ቅነሳ የሚያስከትል ሁኔታ ሲከሰት አሰሪው በማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል (ሁኔታው የስራ ውሉን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ተደርጐ እንደሚወሰድ) በተጠቀሰው ንኡስ አንቀጽ/2/ /ሀ/ ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች ባጋጠመው የግንባታ እቃዎች እጥረት የተነሣ የጀመረው የህንፃ ስራ ማስቀጠል አልቻለም፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በአናፂነት፣በብረት እና በፌራዮ ስራ ቀጥሮ ሲያሰራቸው የነበሩትን ተጠሪዎችን ይዞ የሚጓዝበት ሁኔታ የለም ማለት ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም ያለውን ብቸኛ አማራጭ ማለትም የስራ ውሉን የማቋረጥ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ እርምጃውን መውሰድ ያለበት ግን በሕጉ የተቀመጠውን ግልጽ ስርዓት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ሥርአቱ አስቀድሞ ማስጠንቀቅያ መስጠት ሲሆን፣አመልካች ግን ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ አልሰጠም፡፡ ስለዚህም አመልካች የስራ ውሉን ማቋረጡ ተገቢ ቢሆንም፤ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ የተነሣ ሊኖርበት ከሚገባ ሐላፊነት ግን የሚድን አይደለም፡፡ ሲጠቃለል አመልካች አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ መስጠት ከነበረበት የሚለው እንደተጠበቀ ሆኖ የግንባታ እቃዎች እጥረት አጋጥሞአል በሚል የተደረገ የስራ ስንብት ሕገ ወጥ ነው የሚለው የስር ፍ/ቤቶች ድምዳሜ ግን ሕጉን ያላገናዘበ በመሆኑ በዚህ ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39571 ሐምሌ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 70771 ኅዳር 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የነበረው የሥራ ውል ያቋረጠው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ እንዲከፍል የተወሰነበት ገንዘብ ይክፈል፡፡ ሌሎቹን ክፍያዎች ግን አይከፍልም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 42361

ጥቅምት 05 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ወ/ሪት ትዕግስት ንጉሴ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ኤስ.ኦ.ኤስ.ኢንፋንት ኢትዮጵያ - ነ/ፈጅ አያንቱ ግርማ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ የአሁኗ አመልካች ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ የስራ ውሉን አቋርጧል በማለት የመሰረቱት ክስ ከታየ በኂላ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ እርምጃው ሕገ-ወጥ በመሆኑ አመልካችን ወደ ስራ እንዲመልሳቸው በመ/ቁ 38316 ከወሰነላቸው በኂላ አመልካች ወደ ስራ ቢመለሱ ከተጠሪ ጋር መልካም የሥራ ግንኙነት እንደማይኖራቸው ገልፀው ለሕገ-ወጥ ስንብት የሚከፈሉ ክፍያዎችንና የፕሮቪደንት ፈንድ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት የአፈፃጸም ማመልከቻ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የካሳ፣ ስንብትና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ትዕዛዝ ሠጥቶ የፕሮቪደንትና ክፍያ ለዘገየበት ክፍያን ግን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘትም አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ታህሣስ 24 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት 4(አራት) ገፅ የሠበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የፕሮቪደንት ፈንድ ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሠበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪም በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሱን ሠጥቷል፡፡

እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው አመልካች በስር ፍርድ ቤት በመሰረቱት ዋና ክስ ላይ የፕሮቪደንት ፈንድ ጥያቄ ማንሳታቸውን ተጠሪ ደግሞ በድርጅቱ ውስጥ ፕሮቪደንት ፈንድ ያለመኖሩንና ከሠራተኛው ደመወዝ ላይ ለፕሮቪደንት ፈንድ የተቆረጠ ምንም ገንዘብ ያለመኖሩን በመግለፅ መከራከሩን ነው፡፡ በዚህ በግራ ቀኙ ክርክር ማስረጃ ተመርምሮ ተገቢው ዳኝነት አልተሠጠበትም፤ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ የአሳረፈው የስራ ውል መቋረጡ ሕገ-ወጥ በመሆኑ ላይ ሲሆን፤ የሠጠውም መፍትሔም (Relief) አመልካች ወደ ስራቸው እንዲመለሱ የሚል የነበረ መሆኑንም ተረድተናል፡፡ አመልካች በፍርድ ቤቱ ውሣኔ መሠረት ወደ ስራ መመለሱን በመተው በምትኩ የተለየዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ የአፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡

በመሠረቱ ወደ ስራ እንዲመለስ የሚል ውሣኔ ያገኘ ሠራተኛ ከዚህ ውሣኔ በኂላም ቢሆን ወደ ስራ ለመመለስ ፍላጎት ከሌለው ካሣ ተከፍሎት ከስራ እንዲሰናበት በማድረግ የሥራ ክርክሩን የሚወስነው አካል ሊወሰን እንደሚችል

አዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 43(3) ስር አስቀምጧል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለውም ቀድሞ የተወሰነ ውሣኔ ከመፈጸሙ በፊት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ወደ ስራ ሊመለሱ ይገባል ተብሎ የተወሰነው ውሣኔ ከመፈፀሙ በፊት በምትኩ የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍለውኝ ልሰናበት የሚል የአፈፃፀም ማመልከቻ ማቅረባቸው ግራ ቀኙን ያከራከረ ነጥብ አይደለም፡፡ አከራካሪው ነጥብ የፕሮቪደንት ክፍያ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች ጥያቄውን ያልተቀበሉት ወደ ስራ የመመለስ አማራጭ ቀርቶ በአዋጁ አንቀፅ 43/3/ መሰረት በካሳ ሠራተኛው እንዲሰናበት ሲደረግ በአፈፃፀም ሊጠየቅ የሚችለው በዋናው የፍሬ ነገር ክርክር ውሳኔ ያላገኘ ክፍያ አይደለም በሚል ነው፡፡ በእርግጥ በአፈፃፀም ሊጠየቅ የሚገባው ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓቱ ከቁጥር 371 ጀምሮ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ሆኖም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(3) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሳኔ ሳይሰጥ ከተጠየቁት ዳኝነቶች መካከል ወደ ስራ የመመለስ ጥያቄ ላይ ብቻ ውሳኔ ከተሠጠ እና ሰራተኛው ወደ ስራ መመለስ ሳይፈልግ ሲቀር ቀድሞ ዳኝነት በጠየቀባቸው ነገር ግን ውሳኔ ባላረፈባቸው ነጥቦች ላይ ዳኝነት ሊጠይቅ እንደሚችል ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ ጥያቄው ሲቀርብ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የቀረበ ማስረጃ በተገቢው መንገድ ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ነው፡፡ የአመልካች የፕሮቪደንት ፈንድ ጥያቄ በተጠሪ በኩል ክርክር የቀረበበት ነው፡፡ ወደ ስራ እንዲመለስ ለተወሰነለት ሰራተኛ የፕሮቪደንት ፈንድ እንዲከፈል የሚወሰንበት የሕግ አግባብም የለም፡፡ እንዲሁም የፕሮቪደንት ፈንድ እንደሌሎች ከአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የሚመነጩ የመብት ጠያቂዎች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ስር በተመለከቱት የይርጋ ጊዜ ገደቦች የሚታገድ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 ድንጋጌ ስር በተመለከተው የአስር ዓመት የጊዜ ገደብ የሚታገድ ስለመሆኑ ይህ ችሎት በሠ/መ/ቁ 32545 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አመልካች የፕሮቪደንት ክፍያ ጥያቄ በአፈፃፀም መዝገብ ሳይሆን ሌላ የዋና ክርክር መዝገብ ከፍተው ተገቢ ክርክር ተደርጎበት ውሳኔ የሚሰጥበት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 42459 ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ እና በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 68296 መስከረም 10 ቀን 2001 ዓ.ም የተሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 42818

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቢሲኒያ ባንክ አ.ማ - ነገረ ፈጅ ወልደማርቆስ በጋሻው

**ተጠሪ፡-** ወ/ር ሙስታ ገዳ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ተጠሪ በሌላ መስሪያ ቤት በትርፍ ሰአት ተቀጥሮ መስራቱ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 እንደተሻሻለ እና በአመልካች የሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል በቂ ምክንያት ባለመሆኑ አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበተው አላግባብ ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ሐምሌ 19 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ያለ አሰሪው ፈቃድና እና እውቅና በሌላ መስሪያ ቤት ተቀጥሮ መገኘቱ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 27 ንኡስ አንቀጽ 1/ሐ/ እና በሰራተኛ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ያለ ማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት የሚችል ምክንያት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ጥፋቱ ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል አይደለም ብለው መወሰናቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል ተጠሪ በበኩላቸው በትርፍ ሰአት ሌላ ስራ ለመስራት የአሰሪው ፈቃድ መጠየቅ አያስፈልግም፡፡ በአመልካች ሰራተኛ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል ጥፋት ስለመሆኑ አልተደነገገም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በጽሑፍ ተከራክሯል፡፡ ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪን ከስራ ለማሰናበት የሰጠው ምክንያት በትርፍ ሰአት ሌላ መስሪያ ቤት መስራቱ ሰራተኛውን ያለ ማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል ጥፋት ስለመሆኑ በአመልካች የሰራተኛ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ያልተደነገገ መሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የሰራተኛ መተዳደሪያ ደንብ በማስቀረብ አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች ተጠሪን ለማሰናበት የሰጠው ምክንያት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 በግልጽ የተደነገገ ምክንያት አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅና የአመልካችን የሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ሲተረጉሙ የፈጸሙት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያላገኘን በመሆኑ በፍታብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 348 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት አጽንተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 41767

ኀዳር 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ነ/ፈጅ ተካ ገ/መድህን ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ አድማስ ደምሳቸው የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ታህሣሥ 15 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ከጥር 25 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ለአመልካች በጉዳይ አስፈፃሚነት ሲያገለግሉ መቆየታቸውን ገልፀው ለስንብት የሚያበቃ ምክንያት ሳይኖር ወይም ቢኖርም እንኳ ከታወቀ ከአንድ ወር በኋላ ያሰናበታቸው በመሆኑ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ተብሎ ወደ ስራ እንዲመለሱ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እና የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸው እንዲሰናበቱ በጠየቁት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ ስንብቱ የተፈፀመው ተጠሪ ሌላ ቦታ በመስራታቸው መሆኑንና ይህንንም እንደአወቀ የስንብቱ እርምጃ መፈፀሙን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካች ተጠሪን ባሰናበተበት ጊዜ በቂ እና ሕጋዊ ምክንያት ያልነበረው መሆኑን በመግለጽ ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው በሚል ምክንያት ተጠሪ የስድስት ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራቸው ሊመለሱ ይገባል፣መመለስ ካልፈለጉ ተገቢ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይደረግ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ስንብቱ የተፈፀመው ለስንብቱ ምክንያት የሆነው ድርጊት ከተፈፀመ ሰላሳ የስራ ቀናት ከአለፉ በኋላ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3/ በይርጋ ይታገዳል፣የአመት እረፍት የሁለት ዓመቱ ለተጠሪ ሊከፈላቸው አይገባም ሲል ምክንያቱን ለውጦ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ኀዳር 30 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ የሰበር ማመልከቻ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም፡- ስንብቱ ጊዜውን ጠብቆ የተደረገ አይደለም ተብሎ ሕገ-ወጥ ነው መባሉ በጉዳዩ ላይ የቀረበውን ማስረጃ ባግባቡ ባለመመልከቱና ጊዜ አቆጣጠሩም ግልጽነት በሌለው ሁኔታ ተሰልቶ በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አመልካች ተጠሪን በመጀመሪያ ከሥራ ያሰናበተበት ምክንያቱን ተመርኩዞ ለስንብት የሚያበቃ ምክንያት የለም ተብሎ እና በተጨማሪም የስንብት ምክንያቱ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለው በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩላቸው ሐምሌ 24 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው በአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3/ መሰረት በሰላሳ የስራ ቀናት ውስጥ አይደለም ተብሎ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የአመልካች መስሪያ ቤት ሰራተኛ ሆነው በሚሰሩበት ወቅት በሌላ ቦታ መስራቱ ሲታወቅ አመልካች የስራ ውሉን በማቋረጥ ያሰናበታቸው መሆኑንና ተጠሪም ይህንኑ ፍሬ ነገር ሳይክዱ የሚከራከሩት ስንብቱ የተፈፀመው ሰላሳ የስራ ቀናት ከአለፉ በኋላ ነው በሚል መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪም ሆነ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የድርጊቱን መፈፀም ያወቀበት ጊዜ በማለት የሚቀበሉት ነሐሴ 16 ቀን 1999 ዓ.ም ሲሆን የስንብት ደብዳቤ ተሰጠ የሚባለው ደግሞ መስከረም 21 ቀን 2000 ዓ.ም ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ አጥብቀው የሚከራከሩት ይህ ጊዜ ቢያዝ እንኳ የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ አላለፈም በማለት ነው፡፡ እኛም ይህንኑ መሰረት በማድረግ ጊዜውን ስናሰላው ከነሐሴ 16 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጳጉሜ 06 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ አስራ አምስት፣ከመስከረም 01 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የስንብት ደብዳቤ አስከተፃፈበት እስከ መስከረም 21 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ ደግሞ 13 ተከታታይ የስራ ቀናት መኖራቸውን አረጋግጠናል እነዚህ ቀናት በጠቅላላው 28 ናቸው በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27/3 መሰረት አንድ አሰሪ ህጉ በተፈቀደው ምክንያት መሰረት የሥራ ውሉን የሚያቋርጥበት ጊዜ የስራ ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱ ካወቀበት ከሰላሣ የስራ ቀናት በኋላ ከሆነ በይርጋ እንደሚታገድበት ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ከላይ እንደተመለከተው ሰላሳ ተከታታይ የሥራ ቀናት ከማለፋቸው በፊት አመልካች እርምጃውን ወስዷል፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ድምዳሜ ጊዜውን በተመለከተ ካላንደሩን ባግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የአመልካች እርምጃ በሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ የሚታገድበትን ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ስንብቱ መሰረት ያደረገበትን ምክንያት በቂ መሆን ያለመሆኑን ስንመለከተው ተጠሪ አመልካች የማታለል ተግባር ፈጽሟል በማለት የሚያቀረበውን ክርክር ጉዳዩን አመልካች ያውቅ ነበር ከማለት ውጪ ድርጊቱ መፈፀሙን የካዱት ነጥብ አይደለም፡፡ አንድ ሰራተኛ በአሰሪው ላይ የማታለል ተግባር መፈጸሙ ከተረጋገጠ አሰሪው የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ ሕጋዊ መብት ያለው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሐ/ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ አሰሪ ግልጽ የሆነ ፈቃድ እስካልሰጠ ድረስ ሰራተኛው በሁለት ቦታ በተመሳሳይ ጊዜ መስራቱ ከታወቀ አድራጎቱ በስራ ላይ የተፈፀመ የማታለል ተግባር ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይሆንም፡፡ በምርትና ምርታማነት ላይም አሉታዊ ተጽእኖ የሚያስከትል በመሆኑ የስራ ውሉን ለማቋረጥ ሕጋዊ እና በቂ ምክንያት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 39185 ሰኔ 13 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጠቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 68366 ኅዳር 22 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበተው በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰበር መ/ቁ 42923

ህዳር 22 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. ታፈሰ ይርጋ

5. አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ነጃት አባስ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሰረት ያደረገ የደመወዝ ማስተካከያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ናቸው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘት፤ የሁለት ዓመት የሥራ ልምድ የሚጠይቅ በሙሉ ስታትስቲሺያን የሥራ መደብ ተቀጥረው በወር ብር 1971.00 (አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አንድ ብር) ደመወዝ እየተከፈላቸው በመስራት ላይ የሚገኙ መሆኑን፣ አነስተኛ የሥራ ልምድ ያላቸው እና ተመሳሳይ ስራ የሚሰሩ ሌሎች ሠራተኞች ከፍ ያለ ደመወዝ እንደሚከፈላቸው ገልፀው ድርጊቱ ለአንድ ሥራ እኩል ክፍያ የሚለውን መርህ የሚጥስ በመሆኑ አመልካች የወር ደመወዙን ብር 2366.00(ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ስልሳ ስድስት ብር) እንዲያደርግላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካችም በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሠጠው መልስ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑንና ጥያቄአቸውም በይርጋ የታገደ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት፣ በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ የደመወዝ ልዩነት የተደረገው መመሪያውን መሰረት በማድረግ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኂላ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 14(1/ረ) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በዋቢነት በመጥቀስ የአመልካች አሰራር ህገ-ወጥ ነው በማለት ለተጠሪ የደመወዝ ማስተካከያ በማድረግ በፔሮል ላይ ሊተክል ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ሠርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥር 19 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የስር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የአዋጅ ቁጥር 337/96 አንቀፅ 14(1/ረ) አሰሪው መመሪያውን መሰረት በማድረግ ለፈፀመው ተግባር አግባብነት የሌለው በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የስር ፍርድ ቤት አመልካች መስሪያ ቤት ከዘረጋው የእድገት አሰጣጥ ሥርዓት አልፎ ለተጠሪ የወሰነው የደመወዝ መጠን መነሻን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ ጉዳዩ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ሐምሌ 22 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በተመሳሳይ ደረጃ በሚገኙ ሠራተኞች መካከል የሚፈጠር የደመወዝ ልዩነት (Equal Pay Discrimination) የተከለከለ ነው የሚለውንና ኢትዮጵያ ያፀደቀችውን ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽንን መሰረት ያደረገ ስለሆነ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለውም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩላቸው ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ ሊመረመር ይገባዋል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በስታትስቲሽያንነት ተቀጥረው የሚሰሩ መሆኑን፣ ቅጥሩም በሙሉ ስታትስቲሽያን የስራ የማዕረግ መፈፀሙን በተጠሪና በሌሎች ሠራተኞች መካከል የደመወዝ ልዩነት የተፈጠረው እነዚህ ሠራተኞች ምንም የስራ ልምድ በማይጠይቅ በመለስተኛ ስታትሺያን የስራ መደብ ተቀጥረው ከቆዩ በኋላ በዚህ የስራ መደብ የተቀጠሩ የዲግሪ ምሩቃን ሰራተኞች ወደሚቀጥለው የስራ መደብ የሚያድጉበትን ሁኔታ አመልካች በመመሪያ መወሰኑንና በዚህ መመሪያ መሰረትም ከተጠሪ ጋር ተመሳሳይ ስራ የሚሰሩ የዲግሪ ምሩቃን ከተጠሪ የተለየ ደመወዝ የሚከፈላቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 42(1/መ) ድንጋጌ የሚያሳይ ሲሆን ኢትዮጵያ የተቀበለችው አለም አቀፍ ኮንቬንሽንም ይህንኑ ያስገነዝባል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ሲያደርግ መሰረት ያደረገው የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14(1/ረ) ሲሆን የዚህ ድንጋጌ ይዘት ሲታይ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በሐይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት እና በሌሎችም ሁኔታ በሠራተኞች መካከል ልዩነት ማድረግ ለማንኛውም አሠሪ ሕገወጥ ድርጊት ነው የሚል ነው፡፡ የድንጋጌው እንግሊዘኛ ትርጉሙም “discriminate between workers on the basis of nationality, sex, religion, political outlook, or any other conditions shall be unlawful for an employer.” በሚል ተቀምጧል፡፡

ከድንጋጌው ውስጥ “…በሌሎችም ሁኔታ…” ወይም “…. Any other conditions….” የሚለው ሐረግ ጠቅላላ ቃል መሆኑ ግልጽ ሲሆን እንዲህ በሆነ ጊዜ ቃሉን ህግ አውጪው የተጠቀመው ምንን ለማመላከት ነው የሚለው ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ሲሆን የህግ አተረጓጎም መርሆዎችን መሰረት በማድረግም ምላሹን ማግኘት ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት ከጠቅላላው ቃል በፊት የተዘረዘሩት የቃላት ዝርያ የሚያሳዩትን ሁኔታ በመመልከት ጠቅላላ ቃል ሌሎች ያልተዘረዘሩትን ተመሳሳይ ዝርያ ያላቸውን ቃላት ለመጠቀም ታስቦ የተቀመጠ ነው በሚል እንደሚተረጎም ተቀባይነት ያላቸው የህግ አተረጓጎም መርሆዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14(1/ረ) ድንጋጌ ስር “በሌሎች ሁኔታም” የሚለው ቃል ከቃሉ በፊት የተቀመጡትን የልዩነት ማድረጊያ ድርጊቶችን ዓይነት የሚመለከት እንጂ አሰሪው የእድገት አሠጣጥ ሥርዓቱን በመመሪያ ዘርግቶ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ሠራተኞች መስፈርቱን ካላሟሉ ሰራተኞች የተለየ ክፍያ እንዲከፈል የሚያደርግበትን አሰራር የሚመለከት አይደለም፡፡ መመሪያው በሕገ-መንግስቱ፣ በዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14(1/ረ) ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ በተጠሪና በሌሎች ሰራተኞች መካከል የደመወዝ ልዩነት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ መመሪያው መድሎን ለመከላከል የማያስችል ነው ሊባል የሚችልበትን ሕጋዊ ምክንያትም አላገኘንም፡፡ ሲጠቃለልም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ህጋዊ ምክንያቶች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 23005 ሐምሌ 28 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 70763 ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች በተጠሪና በሌሎች ሠራተኞች መካከል ለተመሳሳይ ሥራ የደመወዝ ልዩነት ያደረገው በሕግ የተከለከሉ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ባለመሆኑ ለተጠሪ ብር 2366.00 /ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ስልሳ ስድስት ብር/ በፔሮል እንዲተክል የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 44410

ኅዳር 01 ቀን 2002

**ዳኞች፡-** አቶ ሐጎስ ወልዱ

ወ/ት ሒሩት መለሠ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አቶ አልማው ወሌ

አቶ ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ላይላ ረዲ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ድሬ ኢንዱስትሪዎች ኃ/የተ/የግል ማኅበር - በሌለበት የሚታይ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸው የሥራ ውል ከሕግ ውጪ መቋረጡን ገልፀው የካሣ ክፍያ፣ የስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ ክፍያ የዘገየበት ክፍያ፣ የታህሣሥ ወር 2000 ዓ.ም. ደመወዝ፣ ያልተጠቀሙት የ29 ቀናት የዓመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው እንዲሁም የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀት እንዲሠጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሳሽነቱ ቀርቦ አመልካች በታህሣሥ ወር 2000 ዓ.ም. ለ28 ቀናት በመደዳው ቀርተው ማስረጃ ባለማቅረባቸው ደመወዝ ያልተከፈላቸው መሆኑን፣ ወደ ሥራም በሀዘኔታ የመለሳቸው መሆኑን፣ ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም. አመልካች ለተጠሪ የስንብት ደብዳቤ ጽፈው ሥራቸውን በራሳቸው ፈቃድ ለቀው መሄዳቸውንና በዚህም ምክንያት ሊከፈላቸው የሚገባ ካሣ አለመኖሩን፣ የሥራ ስንብት ክፍያም አገልግሎታቸው ከአምስት ዓመት በታች በመሆኑ ሊያገኙ እንደማይችሉ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያም በገዛ ፈቃዳቸው ሥራውን ስለለቀቁ እንደማይገባቸው፣ የዓመት እረፍትም በወቅቱ መውሰዳቸውንና ያልወሰዱት ካለም ቀርበው መተሳሰብ እንደሚችሉ ክፍያው ለዘገየበት ለተባለው ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ ኖሮ ያልተከፈላቸው ባለመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት እንደሌለው፣ እንዲሁም የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን በመግለጽ የአመልካች ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን የቃል እና የጽሁፍ ክርክር መርምሮ አመልካች ስራቸውን በፈቃዳቸው መልቀቃቸው ተረጋግጧል፣ የታህሣሥ ወር 2000 ዓ.ም. ደመወዝም አመልካች ሥራውን ያልሠሩ መሆኑ ተረጋግጦ ከሥራ ላይ የቀረበትን ሕጋዊ ምክንያት ተገቢውን የሕክምና ማስረጃ በማቅረብ አላስረዱም በማለት በአመልካች የተጠየቁትን ክፍያዎችን ውድቅ አድርጎ አመልካች ያልወሰደችው የዓመት ፈቃድ ከጥቅምት 1999 ዓ.ም. እስከ ጥር 29 ቀን 1999 ላለው ጊዜ ታስቦ በገንዘብ ተለውጦ ተጠሪ እንዲከፍላቸው፣ የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀትም እንዲሠጣቸው ብቻ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሠርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት መጋቢት 14 ቀን 2001 ዓ.ም. በፃፉት አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የሥር ፍርድ ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም. ተፃፈ የተባለውን ደብዳቤ ይዘቱም ባግባቡ ሳያገናዝብ አመልካች የሥራ ውላቸውን በገዛ ፈቃዳቸው መልቀቃቸው ተረግጧል ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው በስህተት በመሆኑ ታርሞ ሕጋዊ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ለተጠሪ መጥሪያ ተልኮለት የቃል ክርክር ሊሰማ ቀነ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የአመልካችን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጦችንም አመልካች ሥራቸውን የለቀቁት በገዛ ፈቃዳቸው ነው /ባግባቡ ነው/? ወይስ አይደለም? አይደለም ከተባለስ አመልካች ሊከፈላቸው የሚገባቸው ክፍያዎች የትኞቹ ናቸው? የሚሉት ናቸው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ስራውን በገዛ ፈቃዳቸው መልቀቃቸው ተረጋጋጧል ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የአመልካችን የምስክሮች ቃል እና በተጠሪ በኩል የቀረበውን አመልካች ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም. ፃፉ የተባለውን ደብዳቤ በመመርኮዝ ስለመሆኑ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩትም የምስክሮች ቃልም ሆነ የደብዳቤው ይዘት ሥራውን በገዛ ፈቃዳቸው የለቀቁ መሆኑን የማያሳይ ሳይሆን በተጠሪ ድርጅት የአመልካች የቅርብ ኃላፊያቸው በተደጋጋሚ በሚደርስባቸው በደል እና ከሥራቸውም እንዲወጡ በቃል በታዘዙት ምክንያት ከሥራቸው የወጡ መሆኑን ገልፀው ተገቢ ክፍያ እንዲፈፀምላቸው ጥያቄ ማቅረባቸውን የሚያሳይ ነው በማለት ነው፡፡ ይህ ችሎትም ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም. በአመልካች ተፃፈ የተባለውን ደብዳቤ ይዘት ተመልክቶታል፡፡ እንደተመለከተውም አመልካች በሥራቸው ቦታ ላይ በቅርብ ኃላፊያቸው የሚደርስባቸውን በደል በመዘርዘር የቅርብ ኃላፊያቸው በራሳቸው ፍላጎት ከሥራቸው ያስወጣቸው መሆኑ ግንዛቤ አግኝቶ ጥቅማ ጥቅማቸው ተጠብቆ የስራ ልምድ እንዲሰጣቸው ለተጠሪ ድርጅት ፐርሶኔል አስተዳደር መፃፋቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታ የቀረበለት የተጠሪ ድርጅት የክፍሉ ኃላፊም በሠራተኛው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እንዲስተናገዱ በሚል ለድርጅቱ አስተዳደር አገልግሎት ክፍል ደብዳቤውን መምራቱን የደብዳቤው ይዘት ያሳያል፡፡ እንግዲህ የደብዳቤው ይዘት አመልካች ስራቸውን የለቀቁት የቅርብ ኃላፊያቸው ከስራቸው ስለአስወጧቸው መሆኑን በመግለፅ ተገቢ ክፍያዎችን የጠየቁ መሆኑን ከሚያሳይ በስተቀር የስር ፍርድ ቤት በመዘገበው አይነት አለመሆኑን ይህ ችሎት ከውሣኔው ግልባጭ አረጋግጧል፡፡ በጉዳዩ ላይ የቀረበውን ማስረጃ ይዘት ባግባቡ ባለመመዝገብ የሚደረሰው ድምዳሜ ደግሞ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን በስነ-ስርዓቱ ሕጉ የተመለከተውን የዳኝነት አካሄድ የሚፃረር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ስራቸውን በገዛ ፈቃዳቸው መልቀቃቸው ተረጋግጧል በማለት የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ብለናል፡፡

ቀጥለን የሕገ-ወጥ ስራ ስንብት ውጤት ከሆኑት ክፍያዎች መካከል ለአመልካች የሚገባቸው የትኞቹ እንደሆኑ ተመልክተናል፡፡

አመልካች ከጠየቁት ክፍያ መካከል ካሣ አንዱ ሲሆን አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/4/ መሠረት ካሣ ሊከፈላቸው የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሌላው አመልካች ዳኝነት የጠየቁት የሥራ ስንብት ክፍያ ሲሆን ተጠሪ ይህንኑ ክፍያ አመልካች አይገባቸውም በማለት በሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክርክር የአመልካች አገልግሎት ጊዜ አምስት ዓመት አልሞላቸውም የሚል ነው፡፡ ሆኖም የአምስት ዓመት አግልግሎት እንደመመዘኛ የሚወሰደው ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለሚለቅ ሠራተኛ የስንብት ክፍያ ሲጠየቅ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/ሸ/ ድንጋጌ መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39/1/ለ/ ድንጋጌ ሲታይም የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ሠራተኛ ሕግ ከደነገገው ውጪ በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ሠራተኛው ከአሠሪው የስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም የአመልካች የሥራ ውል ከሕግ ውጪ መቋረጡ እና የሙከራ ጊዜያቸውን አመልካች የጨረሱ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የሥራ ስንብት ክፍያ የማያገኙበትን ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 40 መሠረት ታስቦ ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 41 መሠረትም የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡ አመልካች በተገቢው ጊዜ ክፍያ ጥያቄ አቅርበው ያልተከፈላቸው በመሆኑ በተጠቃሹ አዋጅ አንቀጽ 38 መሠረት ሊከፈላቸው የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሲጠቃለልም የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ በሚከተለው መልኩ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12978 ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 73958 የካቲት 06 ቀን 2001 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/4/፣ 40፣41 እና 38 መሠረት ካሣ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና ክፍያው ለዘገየበት ክፍያ እንዲከፍል ወስነናል፡፡
3. የሥር ፍርድ የታህሣሥ ወር 2000 ዓ.ም. ደመወዝን፣ የዓመት እረፍት ክፍያንና የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀትን በተመለከተ የሰጠው ውሣኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ፡- 47807

6/4/2002

*ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ*

*ሐጎስ ወልዱ*

*ሂሩት መለሰ*

*ታፈሰ ይርጋ*

*አልማው ወሌ*

*አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ እሌኒ እሸቱ*

*ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ፀሐይነሽ ፊንታው - ቀረቡ*

2. ሜታ አቦ ቢራ ፋብራካ አ/ማ - ነ/ፈጅ ሰለሞን ዘገየ

***መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡***

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ ከሥራ ውል ጋር በተያያዘ የካሳ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን አንደኛ ተጠሪ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ሟች ባለቤቴ አቶ አሸንጋ ዩታ በተከሳሽ ድርጅት ከሰኔ 24 ቀን 1974 ዓ.ም ጀምሮ ተቀጥረው ሲሰሩ ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም በመ/ቤቱ የሥራ ሰዓት ለድርጅቱ ስፖርት ክለብ ውጤት መሳካት ሲባል የስፖርት ልምምድ እንዲያደርጉ ታዘው በልምምድ የተነሳ ወድቀው እራሳቸውን የሳቱ በመሆኑ ሕይወታቸው ሊያልፍ ችሏል፡፡ የባለቤቴ ሕይወት በስፖርት ልምምድ እንዳሉ በመውደቃቸው ምክንያት ሊያልፍ እንደቻለ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በጽሁፍና በቃል በነገሩኝ መሰረት የሕይወት ካሳ እንዲከፈለኝ የጠየቅሁ ቢሆንም ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡

ስለሆነም በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት የሕይወት ካሳ፣ የቀብር ሥነ -ሥርዓት ማስፈጸሚያ እና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ክፍያዎች እንዲከፈሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽ ቀርቦም በሰጠው መልስ ተከሳሽ ድርጅት በሰራተኞች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት የመድን ዋስትና ሽፋን የገባ ስለሆነ መድን ሰጭው ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ይታዘዝልን በማለት አመልክቷል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅትም የአሁን አመልካች በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ተደርጎ በሰጠው መልስ የሟች ሕይወት ያለፈው በነበረባቸው አጣዳፊ የልብ ሕመም ምክንያት ስለመሆኑ በአስከሬን ምርመራ ተረጋግጧል፡፡ ይህም ሟች የሞቱት በበሽታ እንጂ በሥራ ላይ በመጣ አደጋ እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ የሟች ሥራም ስፖርተኛ ሳይሆን ጽዳት የነበረ ሲሆን በትርፍ ሰዓታቸው በስፖርት ሜዳ ተገኝተው ከሆነም የነበረባቸው ሕመም ለሞት አበቃቸው እንጂ በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ሕይወታቸው አላለፈም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በኃላፊነት ልንጠየቅ ስለማይገባ ክሱ ከበቂ ኪሳራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ከዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል የቀረበው የሟች አስከሬን ምርመራ ውጤት ሟችን ለሞት ያበቃቸው አጣዳፊ የሆነ የልብ ጡንቻ ቁስለት እንደሆነ ያሰረዳል፡፡ ከሳሽ ሟች የሞቱት በመ/ቤቱ የሥራ ሰዓት ለድርጅቱ ስፖርት ክለብ ውጤት መሳካት ሲባል የስፖርት ልምምድ እንዲያደርጉ ታዘው በልምምድ ላይ እንዳሉ ወድቀው እራሳቸውን ስተው ሞተዋል ቢሉም በዚህ አካኋን ሟች ስለመሞታቸው ያላስረዱ ከመሆኑም በላይ ሟች በተከሳሽ ድርጅት የፅዳት ሰራተኛ እንጂ ስፖርተኛ

አይደሉም፡፡ ስለሆነም ሟች የሞቱት በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ሳይሆን በተፈጥሮ ምክንያት እንደሆነ ከቀረበው የሐኪም ማስረጃ መረዳት የተቻለ ስለሆነ ከሳሽ ሟች ባለቤቱ በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ሕይወታቸው አልፏል በማለት ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 97 ሥር የሚሸፈን ባለመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ተከሳሽ አንደኛ መ/ሰጭ ለሁለተኛ መ/ሰጭ በጻፈው ደብዳቤ ሟች በሥራ ላይ ከድርጅቱ ስፖርተኞች ጋር ልምምድ ሲያደርጉ ሕይወታቸው ማለፉን ጠቅሶ በመድን ውሉ መሰረት የካሳ ክፍያ እንዲፈጽምላቸው የጠየቀ ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 95/2/ መሰረት በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ማለት እንደሆነ የተመለከተ ስለሆነ ሟችም ከድርጅቱ ስፖርተኞች ጋር ሥልጠና ሲወስዱ ስለሞቱ ይህም በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ምክንያት እንደሞቱ ስለሚያረጋግጥ የሥር ፍ/ቤት ተከሳሽ ለደረሰው አደጋ ኃላፊ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም በማለት ውሳኔውን በመሻር አንደኛ እና ሁለተኛ መ/ሰጭዎች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ስለሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110/1/ /ሀ/ እና /ለ/ እንደዚሁም በንዑስ አንቀጽ /2/ መሰረት ካሳ ሊከፈሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በአመልካች በኩል የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት የሞቱት በሥራ ላይ እንዳሉ በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት ነው ተብሎ ካሳ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ አግባብነቱን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ይቅረብ ብሎ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥና ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት የሞቱት በሥራ ላይ በደረሰባቸው አደጋ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 95/2/ መሰረት በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ /occupational injury/ ወይም በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ /occupational disease/ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ማለት ደግሞ በአንቀጽ 97 ላይ ትርጉም የተሰጠው ሲሆን ማንኛውም ሰራተኛ ሥራውን በማከናወን ላይ ሳለ ወይም ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሱ ውጭ በሆነ ምክንያት ወይም ሥራውን ለማከናወን ባደረገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ ማንኛውም ክፍል ተፈጥሮዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

በዚህ የአዋጁ ድንጋጌ መሰረት የካሳ ክፍያ ጥያቄ የሚያቀርበው ወገን ጉዳቱ የደረሰው በአንቀጽ 97 በተመለከተው አኳኋን በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ምክንያት መሆኑንና እንደዚሁም በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ቅርብና ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት መኖሩን /proximate cause and effect relation ship/ ማስረዳት እንደሚጠበቅበት ይታመናል፡፡

በሌላ በኩልም የአሰሪው ኃላፊነት በጥፋት ያልተመሰረተ ጥብቅ /strict/ ስለሆነ ካሳ ጠያቂው ወገን ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ማሳየት ብቻ እንጂ ከዚህ አልፎ የጉዳት አድራሹን ወይንም የአሰሪውን የአእምሮ ሁኔታ /state of mind/ ማስረዳት እንደማይጠበቅበት ከአንቀጽ 96 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ በተገለፀው አኳኋን አንደኛ ተጠሪም ሟች ባለቤታቸው ሕይወታቸው ያለፈው በአንቀጽ 97 በተመለከተው መሰረት ሥራቸውን በማከናወን ላይ ሳሉ ወይንም ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሳቸው ውጭ በሆነ ምክንያት በድንገት በደረሰባቸው ጉዳት ሳቢያ ሕይወታቸው ማለፉን ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ ሟች ባለቤቴ ሕይወታቸው ሊያልፍ የቻለው ለድርጅቱ ስፖርት ክለብ ውጤት መሳካት የስፖርት ልምምድ እንዲያደርጉ በአሰሪው ታዘው ልምምድ ሲያደርጉ ወድቀው ሕይወታቸው ያለፈ ስለሆነ ይህም በሥራ ላይ የደረሰ አደጋ ስለሆነ ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ሆኖም ግን ሟች የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት የተቀጠሩበት የሥራ መደብ በስፖርተኛነት ሳይሆን በፅዳት ሰራተኛነት የሥራ መደብ እንደሆነ ከመረጋገጡም በላይ አንደኛ ተጠሪ እንደሚሉትም በአሰሪው በኩል ለድርጅቱ ስፖርት ክለብ

ውጤት መሳካት ሲባል የስፖርት ልምምድ እንዲያደርጉ በአሰሪው ታዘው የስፖርት ልምምዱን ሲያደርጉ ሕይወታቸው ስለማለፉም አላሰረዱም፡፡

ከዚህም ሌላ ሟች የስፖርት ልምምድ እንዲያደርጉ በአሰሪው ትዕዛዝ ተሰጥቷቸው ነበር ቢባል እንኳን በስፖርት ልምምድ ላይ እንዳሉ ሕይወታቸው ማለፉ በአንቀጽ 97 ላይ እንደተመለከተው በስራ ላይ በደረሰባቸው አደጋ /accident/ ሳቢያ ሕይወታቸው እንዳለፈ የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የአዋጁ አንቀጽ 95/2/ እና 97 ድንጋጌዎች በጣምራ ሲተረጎም በሥራ ላይ ጉዳት ደርሷል ለማለት በአደጋ ምክንያት በሰራተኛው አካል ላይ ጉዳት መድረሱ መረጋገጥ እንደሚገባው መገንዘብ ስለሚቻል ነው፡፡ በዚህ መልኩም በሟች ላይ በአደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰ ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ ሲሆን ይልቁንም የቀረበው የሟች አስከሬን ምርመራ ውጤት ሟች ለሕልፈት የበቁት አጣዳፊ በሆነ የልብ ጡንቻ ቁስለት ምክንያት መሆኑን ስለሚያረጋግጥ ሟች በሥራ ላይ እንዳሉ በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት ለሞት እንዳልበቁና በተፈጥሮ ምክንያት /Natural cause/ እንደሞቱ የሚያሳይ ነው፡፡

ሲጠቃለልም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 95 እና 97 በተደነገገው አግባብ አንደኛ ተጠሪ ሟች ባለቤታቸው በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ምክንያት ሰለመሞታቸው በማስረዳት የካሳ ክፍያ ጥያቄውን ማቅረብ ሲጠበቅባቸው ይህንን የማስረዳት ግዴታቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሟች ለሞት የበቁት በሥራ ምክንያት በተፈጠረ አደጋ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር የሥር ተከሳሹ /ሁለተኛ ተጠሪ/ ለጉዳቱ ኃላፊ ነው ብሎ በክስ የተጠየቀውን ካሳ ተከሳሹና ጣልቃ ገቡ የአሁን አመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 75634 ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የፌዴራል መጀመሪያ ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13539 በ6/4/2001 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ አጽንተናል፡፡

2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

3.መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ወ/ነ

የሰበር መ/ቁ 45889

ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ደቡብ ሪጅን

- ነገረ ፈጅ ቢንያም እስጢፋኖስ - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** ሳሙኤል ቁልቦ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አስቀድሞ በተሰጠኝ የደረጃ እድገት መሠረት ይከፈለኝ የነበረው ተጨማሪ ደመወዝ ያለአግባብ ስለተቋረጠብኝ ይኸው ሕገ ወጥ ድርጊት ተወግዶ ጭማሪው ደመወዝ እንዲከፈለኝ ይደረግልኝ በማለት ተጠሪ በመሠረተው ክስ መነሻነት የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ከአመልካች የቀረበውን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ጭማሪው በእድገት ሳይሆን በስህተት ተሰጥቶ የነበረ ለመሆኑ በማስረጃ ማረጋገጡን በመግለጽ የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ አመልካች አንዴ የሰጠውን ውሳኔ በራሱ የሚሽርበት አግባብ የለም የሚል ምክንያት በመስጠት በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ግንቦት 13 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ አቤቱታ ባቀረበበት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቀርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

የተጠሪ የክስ ምክንያት በተሰጠኝ የደረጃ እድገት መሠረት ሲከፈለኝ የነበረው የደመወዝ ጭማሪ ያለአግባብ ተቋርጦብኛል የሚል ሲሆን፣ አመልካች ደግሞ ተጠሪ ቀደም ሲል ሲሠራበት ከነበረው የሃዋሳ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅነት ተመሣሣይ ደረጃ ወደሆነው የሪጅን ምክትል ሥራ አስኪያጅነት ነው የተዛወረው፡፡ ሁለቱም ሥራዎች እኩል ደረጃ ያላቸው ሲሆኑ ዝውውሩ ሲደረግ የደመወዝ ለውጥ ማዘዣው በስህተት በመሠራቱ ነው ችግሩ የተፈጠረው፡፡ የተሠራው ስህተት እንደታወቀም የእርምት እርምጃ ተወስዶአል በማለት እንደተከራከረ ከመዝገቡ ለማየት ችለናል፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎትም አመልካች ያቀረበው የፍሬ ነገር ክርክር ትክክል ሆኖ በማግኘቱ ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረው የደመወዝና የደረጃ እድገት የተነሳው (የተሰጠው) በአግባቡ ነው እሚል መደምደሚያ ደረሶአል፡፡ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ የሻረው በፍሬ ነገር ረገድ ያረጋገጠው የተለየ ነገር አግኝቶ ሳይሆን፣ አመልካች እራሱ የሰጠውን ውሳኔ ያለምክንያት መልሶ መለወጥ የሚችልበት አግባብ የለም፣ "እንደ ፍ/ቤት እራሱ የወሰነውን ውሳኔ መከለስ /Review of judgment/ ማድረግ የማይችል ከመሆኑም በተጨማሪ ውሳኔው የሚመረመረው ለመመርመር ስልጣን ባለው በሌላ አካል በjudicial review ነው፡፡" የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት እንደሆነ ከውሳኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

እንደምንመለከተው የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ ቀድሞ ከነበረው የተለየ ደመወዝና ጥቅም ወደሚያስገኝ ከፍያለ ደረጃ ወዳለው ቦታ አልተዛወረም እሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ ክሱን ውድቅ ያደረገ ሲሆን፣ ተጠሪ ግን አንዴ የተሰጠኝ ደመወዝ ልነጠቅ አይገባም ከማለት አልፎ በእርግጥም በኋላ የተመደበበት ቦታ ከቀድሞው የተለየ እና ከፍ ያለ ደመወዝ የሚያስገኝ ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ ይግባኙን የሰማው ጠ/ፍ/ቤትም አመልካች ቀደም ሲል በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት ሲከፈል የነበረውን ደመወዝ በተገቢው የእድገት አሰጣጥ መሠረት የተገኘ አይደለም በማለት የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይችላል ወይስ አይችልም? በሚለው ነጥብ ላይ በመወሰን ውሳኔ ከመስጠት አልፎ በከፍተኛው ፍ/ቤት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር እውነት አይደለም እሚል መደምደሚያ ላይ ሊያደርስ የሚችል ማስረጃ አግኝቻለሁ አላለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ሰበር ችሎት ሊወሰን የሚገባው ጭብጥ አመልካች የቀድሞ ውሳኔህን መለወጥ ወይም ማረም አትችልም የሚባልበት የሕግ አግባብ አለ ወይ? የሚለው ነው፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ነው፡፡ አመልካች በአሠሪነቱ ተጠሪንም ሆነ ሌሎች ሠራተኞቹ የሚያስተዳድረው፣ የደረጃ እድገት አሰጣጥም ሆነ የደመወዝ አከፋፈል ወይም አመዳደብ የሚወሰነው ባለው አሠራር እና ድርጅታዊ መዋቅሩ መሠረት እንደሆነ ይገመታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በኋላ የተመደበበት የሥራ ቦታ ቀድሞ ከነበረበት የሥራ ቦታ ተመሣሣይ በመሆኑ ተጨማሪ ደመወዝ የሚያገኝበት አግባብ እንደሌለ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ የፍሬ ነገር መሠረት ስለሌለው ስህተት ነው ማለት ነው፡፡ ተጠሪ ተጨማሪ ደመወዝ እንዲከፈለው የሚያዘው ደብዳቤም የተጻጻፈው በተሳሳተ ውሳኔ ላይ በመመስረት በመሆኑ አመልካች ስህተቱን በማረም ተለዋጭ ውሳኔ ከመስጠት የሚያግደው የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት የለም፡፡ አመልካች በሥራው መሪነቱ (በአሠሪነቱ) ትክክል ነው ብሎ በሚያምነው መሠረት የመወሰን ሥልጣን ያለው እንደመሆኑ ስህተት መስሎ የታየው የራሱንም ውሳኔ ማረም ያለበት እራሱ እንጂ የተሳሳተ ውሳኔ ሰጥቻለሁና አርምልኝ ብሎ ለሌላ አካል አቤቱታ የሚያቀርብበት የህግ አግባብ የለም፡፡ አግባብ የሚሆነው በውሳኔው ተጎድቻለሁ የሚለው ወገን (ሠራተኛ) የውሳኔ ሕጋዊነት ይታይልኝ (ይመርመርልኝ) በማለት ሥልጣን ላለው አካል አቤቱታ ሲያቀርብ ነው፡፡ ተጠሪም ያደረገው ይኸው ሲሆን፣ አመልካች ውሳኔውን ያረመው በአግባቡ ሆኖ በመገኘቱ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ክሱን በሰማው ፍ/ቤት ተወስኖአል፡፡ በመሆኑም የጠ/ፍ/ቤቱ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው የJudicial Review መርህ በመጥቀስ የሰጠው ውሳኔ ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ውሳኔው በሕግ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 24637 የካቲት 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት በመ.ቁ 5223 ህዳር 9 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቶአል፡፡ በዚህ መሠረትም አመልካች የቀድሞውን ውሳኔ ያረመው በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸው ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 47806

ታህሣሥ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- የሆህተሰማይ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት - ሻምበል አሰፋ ወልዴ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ዲያቆን አያሌው አዲሱ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የሥራ ውሌ ከሕግ አግባብ ውጪ ተቋርጦብኛል በማለት ተጠሪ የመሰረተውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው ከሥራዬ ያላአግባብ አግዶኛል በማለት ሲሆን፣ ሲያገለግል የነበረውም በዲቁና እንደሆነ በክሱ ላይ ገልጾአል፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ ከሥራው ሊሰናበት የቻለው የቤተክርስቲያንዋ ስሞነኛ ቁልፍ ያዥ ሆኖ በሰራበት እለት ከቤተመቅደስ ሙዳየ ምጽዋቶች ተሰብረው ተዘርፈዋል፡፡ ከዚህ የተነሣም ተጠሪ በወንጀል ተከሶአል፡፡ የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ክሱ ውድቅ እንዲደረግለት ጠይቆአል፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን ከሰማ በኂላ፣አመልካች ተጠሪን ወደ ሥራው እንዲመልስ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኙን ሰርዘናል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 27 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደምናየው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት ሃይማኖታዊ ግንኙነት ነው፡፡ አመልካች በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት መሰረት የተቋቋመ ሃይማኖታዊ ተቋም ሲሆን፣ተጠሪ ደግሞ በዚህ ተቋም ውስጥ የሃይማኖት አገልግሎት እንዲሰጥ አባል ወይም ሰራተኛ የሆነ ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ሙዳየ ምጽዋቶች ተዘረፉ በተባለበት እለት ተጠሪ ቤተመቅደሱን መክፈቱንና በመቀጠልም ቅዳሴ እንደገባ በክርክሩ ገልጾአል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለውም በሐይማኖቱ ሥርአት መሰረት የሐይማኖቱ አገልጋይ በመሆኑ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ ክርክር ቀርቦለት በሰበር መ/ቁ. 18419 ግንቦት 4 ቀን 98 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የሐይማኖት ወይም መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጥ ሰራተኛ ከተቋሙ ጋር ያለው የሥራ ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ የሚሸፈን አለመሆኑን በመግለጽ የሕግ ትርጉም ሰጥቶአል፡፡ ከዚህ በኂላም በተመሣሣይ ጉዳዮች ቀርበው ቀደም ሲል በተሰጠው የሕግ ትርጉም እንደተሸፈኑ እየተገለጸ ሲወሰን ቆይቶአል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ ሥልጣን ሳይኖራቸው ክርክሩን ተቀብለው ማስተናገዳቸው አግባብ አልነበረም፡፡ የሰጡት ውሳኔም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቶአል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27517 ሰኔ 10 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04821 ሐምሌ 13 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረተው ክስ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሰረት የሚታይ ባለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ክርክሩን የሰሙት ስልጣን ሳይኖራቸው ነው ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡
   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 47469

ታህሳስ 15 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. አልማው ወሌ

5. ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** እነ አቶ ሥዩም ገብረፃዲቅ (22 ሰዎች)

- ወኪል ወንድምአገኝ ጌታሁን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ ሕዳር 20 ቀን 2000 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ላልተወሰነ ጊዜ ተቀጥረን ስንሰራ ሌሎች ሠራተኞች የሚያገኙትን የበረሃ አበል፣ ቦነስ፣ የሳምንት ዕረፍት ቀን ክፍያ፣ የኤሌክትሪክ ፍጆታ በነፃ መጠቀም፣ የዝናብ ልብስ፣ ጥቅማ ጥቅም የማግኘት መብት እንዲከበርላቸው እና የደመወዝ እርከንና ማሻሻያ ከሌሎች ጋር እኩል እንዲደረግላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሳሽነቱ ቀርቦ የተጠሪዎች ጥያቄ በይርጋ የታገደ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ውል ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ በሚል የተፈረመ ሆኖ አመልካች ግዴታውን እየተወጣ የቆየ መሆኑን፣ ተጠሪዎች በሳምንት የሚሰሩት የስራ ሰዓት ብዛትም በቀን ከስምንት ሰዓት በታች የሚሰሩ መሆኑን፣ የሚያሳይ በመሆኑ የሳምንት የእረፍት ጊዜ ክፍያ ተቀባይነት እንደሌለው ለቋሚ ሰራተኞች የሚከፈሉ ክፍያዎችም ለተጠሪዎች ሊከፈሉ እንደማይገባ ገልጾ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በአመልካች በኩል የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ውድቅ ካደረገና የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የስራ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ አንደተደረገ የሚቆጠር ነው በማለት አመልካች ለተጠሪዎች የሣምንት እረፍት ቀን ክፍያ፣ የበረሃ አበል ክፍያ፣ ነጻ የኤሌክትሪክ፣ ቦነስ ይከፈላቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይኸው ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሐምሌ 08 ቀን 2001 ዓ.ም በአምስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሁነው እያለና ቋሚ እንሁን የሚለው ጥያቄም የክስ ምክንያት የሌለው መሆኑ እየታወቀ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ ይቆጠራል ተብሎ ለቋሚ ሠራተኞች የሚገባቸው ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች እንዲከፈላቸው መወሰኑ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን የቅጥር ውል፣ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 10(1/ሀ)"ን"፣ የድርጅቱን የህብረት ስምምነት እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 18832 የሠጠውን አስገዳጅ ውሳኔ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪዎች በጡረታ የተገለሉና ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ መሆኑ እየታወቀ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ ይቆጠራል በማለት አመልካች ድርጅት ለተጠሪዎች ቋሚ ሠራተኞች የሚያገኛቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን

ይክፈላቸው በማለት የሠጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መስከረም 20 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሠምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር ይገባል ተብሎ ሲታዘዝ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች ድርጅት አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ናቸው በማለት ነው፡፡ ለዚህም መሰረት የሚያደርገው ተጠሪዎች በጡረታ የተገለሉና የስራ ውሉ በጊዜ ተገድቦ በግራ ቀኙ መካከል ውል የተፈፀመበትን ሰነድ ነው፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው በጡረታ ተገልለው የቆዩ መሆኑን ሳይክዱ በአመልካች ድርጅት ሥራ የጀመሩት የጡረታ ደብተሩን በመመለስና በማስያዝ ስለመሆኑና ይህም በስር ፍርድ ቤት በሚመለከታቸው አካላት የተረጋገጠ መሆኑን፣ እንዲሁም የስራ ውሉ በየጊዜው እየታደሰ ለበርካታ አመታት በአመልካች ድርጅት ሲሰሩ መቆየታቸው የስራ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ያስቆጥራል በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ የቅጥር ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ ለአንድ አመት እየተባለ ጊዜው ሲያልቅ እንደገና እየታደሰ እንደ አዲስ የሚታይ መሆኑ ይታመናል፡፡ በዚህም መሰረት ጊዜው ሲያልቅ ውሉን ማቋረጥ የሚቻል መሆኑን ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 11924 አግባብነት ያላቸውን የአሰሪና ሰራተኛ ሕግ ድንጋጌዎችን በመመርመር አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም የሠጠበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰራተኛ ከአሰሪ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቆጠረ ሊቆጠር እንደሚገባ ሕጉ ግምት እንደሚወስድ፣ በዚህ የሕግ ግምት የስራ ውሉ ያልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ነው በማለት የሚከራከረው ሠራተኛ ተጠቃሚ በሆኑ ይህን ክርክሩን የሚደግፍለት ማስረጃ በቅድሚያ ያቀርብ ዘንድ እንደማይጠበቅበት፣ ይልቁንም በሕግ በተወሰደለት ግምት ክርክሩን ከማስረዳቱ ግዴታው ነፃ እንዲሆን እንደሚያደርገው፣ በውጤቱም በቅድሚያ የማስረዳት ሸክም የስራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ የተደረጉ ውሎች በአንቀፅ 10 ስር የሚሸፈኑ ናቸው ሲል በሚከራከር በአሰሪው ላይ የሚወድቅ መሆኑን በመዘርዘር ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ከእዚህ የሰበር ችሎት ውሳኔ መገንዘብ የሚቻለው ሰራተኛው በየዓመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሰራ መቆየቱና የሰራተኛው የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻውን ሰራተኛን ለተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠረ ሊወሰድ የማይገባ መሆኑን ነው፡፡ ዋናው ሰራተኛው የተቀጠረበት ሥራ ቀጣይነት ያለው መሆኑ ነው፡፡ አሰሪው ይህንኑ ለማስተባበል የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 10 ስር የተመለከቱት ምክንያቶች የስራ ውሉ መፈፀሙን በማስረዳት ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለማሳያነት ያቀረበው ማስረጃ በሦስተኛ ተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገ የስራ ውል ሆኖ ውሉ ከሀምሌ 01 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ሀምሌ 01 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ ስለመሆኑ የሚያሳይ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 10 ስር በተመለከተው ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ ለጥበቃ ሥራ የተቀጠሩ መሆኑን በመግለፅ የተፈፀመ ነው፡፡ ተጠሪዎች ሁሉም ለአንድ አይነት ሥራ የተቀጠሩ አለመሆናቸውንም የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ቢያሳይም የቅጥሩ ዓይነት ለተወሰነ ጊዜ መሆኑን ግን ተጠሪዎችም ያልካዱት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የስራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ስለመሆኑ የማስረዳት ግዴታውን የተወጣ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አመልካች ተጠሪዎች በጡረታ የተገለሉ ሆነው በቋሚነት ሊቀጠሩ አይችሉም በማለት ያቀረበው ክርክርም ተጠሪዎች በዕድሜ ጣሪያ በጡረታ የወጡ መሆኑን በዚህ ችሎት በተደረገው የክርክር ሂደት አረጋግጠዋል፡፡ ተጠሪዎች የሚከራከሩት የጡረታ ደብተራቸውን በመያዝ የመብቱ ተጠቃሚ ሆነው እያለ በአመልካች ድርጅት በመስራት ላይ የሚገኙ ባለመሆኑ ቅጥሩ እንደቋሚ የሚቆጠር፤ ሕጋዊ ነው በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንድ አሰሪ በጡረታ የተገለለን ሠራተኛ በድጋሚ ላልተወሰነ ጊዜ ቀጥሮ ያሰራል ለማለት የማይቻል መሆኑን ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 18832 አስገዳጅ የሆነ የህግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡ ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ከመሆናቸውም በላይ እድሜያቸው በጡረታ ደርሶ ከስራ ከተሰናበቱ በኂላ በአመልካች ድርጅት ውስጥ የተቀጠሩ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ሆኖ አግኝተናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት እንዲወሰኑላቸው ያቀረቧቸው የክፍያ ጥያቄዎች ለቋሚ ሠራተኞች የሚሠጡ መሆኑን ተጠሪዎችም በክርክራቸው ገልፀው የሚከራከሩት ነጥብ በመሆኑ ተጠሪዎች ቋሚ ሠራተኞች ካልሆኑ ክፍያዎቹ የሚገባቸው አይሆንም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በጡረታ የተገለሉና ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ መሆኑ እየታወቀ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ ይቆጠራል በማለት አመልካች የተጠሪዎች ቋሚ ሠራተኞች የሚያገኟቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን ይክፈላቸው በማለት መወሰኑ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ

10“ን” የአመልካች ድርጅት የሕብረት ስምምነትንና ከላይ የተጠቀሱትን የሰበር ችሎት ውሳኔዎችን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 19930 የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03718 ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች በእድሜ ጡረታ ተገልለው ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች በመሆኑ አመልካች ለቋሚ ሰራተኞች የሚከፍላቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን የሚያገኙበት ወይም ሊከፍላቸው የሚገባ ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 47784

ታህሣሥ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነገረፈጅ እሸቱ በቀለ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ዓለምፀሐይ አያና - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በኦሮሚያ ክልል የጊንቢ ወረዳ ፍርድ ቤትና የምእራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርባ ሐምሌ 23 ቀን 1984 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ወደ ተላላኪነት የሥራ መደብ አሳድጕኝ ደመወዝና የማነቃቂያ አበል ከፍሎኝ ከጉሊሶ ወደ ጊንቢ ሲያዛውረኝ የቤት ኪራይ አበልና የዝውውር አበል በህብረት ስምምነቱ መሰረት ሊከፍለኝ ሲገባ ያልከፈለኝ በመሆኑ ከተዛወርኩበት ጊዜ ጀምሮ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልካች ላይ ያቀረበችው ክስ ነው አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ የተጠሪ ክስ በይርጋ ይቋረጣል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ተጠሪ በራሷ ፍላጐትና ጥያቄ ከጉሊሶ ወደ ጊንቢ የተዛወረች በመሆኑ የቤት አበልና የዝውውር አበል የማግኘት መብት የላትም፡፡ አመልካች ለተጠሪ ከምትሰራበት ቦታ በመዛወሯ ምክንያት (disturbance allowance) ብር 300/ሦስት መቶ/ተከፍሏል፡፡ ከዚህ ውጭ ያቀረበችው ጥያቄ በሕግም ሆነ በህብረት ስምምነቱ መሰረት የቀረበ አይደለም በማለት የበኩሉን ክርክርና ማስረጃ አቅርቧል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ የካቲት 12 ቀን 1995 የተፃፈ ማስጠንቀቂያ የሰጣት በመሆኑ ይርጋው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 መሰረት በተጠሪ ላይ አይቆጠርባትም በማለት የወሰነ ሲሆን ተጠሪ ያቀረበችውን የጥቅማ ጥቅም በተመለከተ ከየካቲት 12 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች እንዲከፈላት በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ የተጠሪ ጥያቄ ከአስራ አምስት ዓመት በኋላ የቀረበ ሆኖ አያለ ጥቂው በይርጋ አይታገድም ብለው አግባብነት የሌላቸውን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር በመጥቀስ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሰራተኛ በራሱ ጠያቂነት ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ ከተዛወረ ከእቃ ማጓጓዣ ወጭ በስተቀር ሌላ ነገር እንደማይከፈለው በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 20(16) እና(17) ተደንግጐ እያለ ለተጠሪ የዝውውር አበልና የቤት አበል እንዲከፈላት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሏ የበታች ፍርድ ቤቶች ይርጋው የተቋረጠ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1852 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 ድንጋጌዎች በመጥቀስ መወሰናቸው ተገቢ ነው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በጠበቃዋ በኩል የቃል ክርክር አቅርባለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የተጠሪ ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም? የተጠሪ ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ከሆነ እስከ መቼ

ድረስ ያለው ጥያቄዋ ነው በይርጋ የሚታገደው? የሚለውና አመልካች ለተጠሪ የቤትና የዝውውር አበል የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? የሚሉት ጭብጦች ውሳኔ ማግኘት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪ ያቀረበችው የዝውውር አበልና የቤት አበል ጥያቄ መጠየቅ ከሚገባው ጊዜ ውስጥ እስከ ስድስት ወር ባለው የጊዜ ገደብ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ንኡስ አንቀጽ 3 ተደንግጓል፡፡ የቤትና የዝውውር አበል በአዋጅ አንቀጽ 162 ንኡስ አንቀጽ 3 "ሰራተኛው የሚያቀርበው የደመወዝ የትርፍ ሰአትና ሌሎች ክፍያዎች ጥያቄ መጠየቅ ከሚገባው ጊዜ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል" በማለት በደነገገው "ሌሎች ክፍያዎች" በሚለው ውስጥ የሚሸፈኑ ክፍያዎች ናቸው፡፡ የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት የወሰኑት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1852 መሰረት ይረጋው የተቋረጠ መሆኑንና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 መሰረት ተጠሪ ክስ ያላቀረበችው አመልካች ካላት ፍርሐትና ታዛዥነት ምክንያት ነው በማለት ነው፡፡

በመሰረቱ የወረዳውና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የይርጋው መቋረጥ በምክንያትነት ያቀረቡት አመልካች ተጠሪ የቤትና የዝውውር አበል የማይገባት መሆኑን በመግለጽ የካቲት 12 ቀን 1995 ዓ.ም የፃፈውን የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ነው፡፡ ይህ ደብዳቤ አመልካች ተጠሪ የቤትና የዝውውር አበል ያላት መሆኑን በሙሉም ሆነ በከፊል በማመን የፃፈው ደብዳቤ ባለመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 164 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት ይርጋውን ለማቋረጥ የሚችል አይደለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ይርጋውን ሊያቋርጥ የሚችልና በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 164 ድንጋጌዎች የሚሸፈን ምክንያት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሣይቀርብላቸው በጥቅሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1852 በመጥቀስ ይርጋው ተቋርጧል በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ለተጠሪ የፃፈውን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ያላቀረበችው አመልካችን ስለፈራችና በታዛዥነት ስሜት ነው በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 በመጥቀስ የሰጡት ውሣኔ የህጉን ድንጋጌ አቀራረጽ ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበ ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ላለው ግንኙነት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 ድንጋጌ አግባብነትና ተፈፃሚነት የሌለው ድንጋጌ በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህንን ድንጋጌ አላግባብ በመጥቀስ አመልካች ከየካቲት 12 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የቤትና የዝውውር አበል እንዲከፍል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ የጠየቁት ቀጣይነት ያለውና ተከታታይነት ባለው ጊዜ ውስጥ ሊከፈላቸው የሚገባ የቤትና የዝውውር አበል ነው፡፡ ተጠሪ ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት የካቲት 6 ቀን 1999 ዓ.ም መሆኑ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህ በመሆኑ ተጠሪ ከነሐሴ 6 ቀን 1998 ዓ.ም በፊት አመልካች የቤት አበልና የዝውውር አበል እንዲከፈላት ያቀረበችው ጥያቄ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 163 ንኡስ አንቀጽ 3 በይርጋ ቀሪ የሚሆን በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ከየካቲት 12 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ነሐሴ 5 ቀን 1998 ዓ.ም ለተጠሪ የቤትና የዝውውር አበል እንዲከፍል የወሰኑት የይርጋ የጊዜ ገደቡ ያለፈበትን ጥያቄ አላግባብ ተቀብለው በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ከነሐሴ 6 ቀን 1998 ዓ.ም በፊት ያለው የቤት አበልና የዝውውር አበል ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. ተጠሪ ካቀረቡት ጥያቄ ውስጥ ከነሐሴ 6 ቀን 1998 ዓ.ም ወዲህ ላለው ጊዜ የቤትና የዝውውር አበል እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ይህንን ቀሪ ለማይሆነው ጊዜ ለተጠሪ የቤትና የዝውውር አበል የመክፈል ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ጭብጥ ውሣኔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ ከጉሊሶ ወደ ጊንቢ ከተማ የተዛወሩት በራሳቸው ፍላጐትና ጥያቄ አቅራቢነት መሆኑ ክርክር ያስነሳ ፍሬ ጉዳይ ካለመሆኑም በላይ አመልካች ተጠሪ በዝውውሩ እንዲፈቀድላት ጠይቃ መዛወሯን የሚያስረዳ ማስረጃ ያቀረበ መሆኑ ከወረዳው ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ እንደዚሁም በአሰሪኛው የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 16 (መ) እና አንቀጽ 17 ማንኛውም ሰራተኛ ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ በተመሣሣይ የሥራ መደብ ለመዛወር ጠይቆ ከተፈቀደለት ከዝውውር ጋር ተያይዞ የሚሰጠው ጥቅም የማያገኝ መሆኑን እንደሚደነግግ የወረዳው ፍርድ ቤት በውሣኔው ገልፆታል፡፡ ተጠሪ ከጉሊሶ ወደ ጊንቢ የተዛወረችው በራሷ ፍላጐትና ጥያቄ እንጅ መሣሪያ ቤቱ በዝውውር ስለመደባት አይደለም፡፡፡ አመልካች ለተጠሪ የቤትና የዝውውር አበል እንዲከፍል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ከላይ የተገለፀውን የሕብረት ስምምነት

ድንጋጌ የሚጥስ ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ከላይ የተጠቀሰውን ግልጽ የህብረት ስምምነት ድንጋጌ በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን ሲወስን የተጠሪን ወደ ተላላኪ የሥራ መደብ ማደግ መጥቀሱ ተገቢነት የሌለው እና የድንጋጌውን መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም በይርጋ ቀሪ ለማይሆነውም ጊዜ ቢሆን አመልካች ለተጠሪ የቤትና የዝውውር አበል የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት ሆኖ እያለ የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ላይ የሰጡት ውሣኔ የሕግ ወይም የሕብረት ስምምነቱ መሰረት የሌለው ነው፡፡

በአጠቃላይ የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የይርጋ ክርክር ውድቅ በማድረግና የሕብረት ስምምነቱ የተዛባ ትርጉም በመስጠት አመልካች ለተጠሪ ከየካቲት 6 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የቤትና የዝውውር አበል እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ ከላይ የተዘረዘሩትን የሕግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የጊንቢ ወረዳ ፍርድ ቤትና የምእራብ ወለጋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ ለሙሉ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የቤትና የዝውውር አበል የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 49057

ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መሰሰ

ብርሃኑ አመነው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አስመላሽ እና ልጆቹ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር - የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪ**፡- ዮሐንስ እሺበል - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሰረት የቀረበ የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ሲሆን፣አመልካችን የከሰሰው የሥራ ውሌ ከሕግ አግባብ ውጪ አቋርጦብኛል በማለት ነው፡፡ ክሱን መሰረት በማድረግም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉት ጠይቆአል፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ ተቀጥሮ ሲሰራበት የነበረው የህንፃ ግንባታ ተጠናቅቆአል፡፡ ይሰራ የነበረው በአናጺት ሙያ ሲሆን፣ሥራው የለም፡፡ በመሆኑም የሰራተኛ ቅነሳ ሥርአት መከተል ሳያስፈልገኝ ያለማስጠንቀቂያ አሰናብቻዋለሁ በማለት ስለመከራከሩ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ወገኖቹን ክርክር ከሰማ በኋላ፣የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በዚህ መሰረትም ለተጠሪ ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉት ወስኖለታል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መስከረም 7 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30 መሰረት የሥራ ግንኙነት በተቋረጠ ጊዜ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታን ያስከትላል ወይስ አያስከትልም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጭብጥ ላይ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ተጠሪ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ እንደገለጸው ተቀጥሮ ይሰራ የነበረው በአናጺነት የሥራ መደብ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ክርክርም የተመሰረተው በዚህ ላይ ሆኖ የአናጺነት ሥራ በመጠናቀቁ የሥራ ውሉ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30 መሰረት ተቋርጦአል የሚል ምክንያት ሰጥቶአል፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ ስለነበረው ሁኔታ አመልካች እና ተጠሪ ልዩነት የላቸውም፡፡ በመሆኑም አከራካሪው ነጥብ ውሉ የተቋረጠው ሕጉ ከደነገገው ውጪ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ ጭብጡ የሕግ በመሆኑ ሊመለስ የሚችለው ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የአዋጁ ድንጋጌ አንፃር በማየት ነው፡፡

አመልካች የተሰማራበት የሥራ ዘርፍ ኮንስትራክሽን ሲሆን፣ ተጠሪ ተቀጥሮ ይሰራ የነበረውም አመልካች ሲያካሂደው በነበረው የህንፃ ግንባታ ነው፡፡ በህንፃው ግንባታ ሂደት የሚከናወኑ ብዙ የተለያዩ ሥራዎች (የሥራ አይነቶች) እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ተጠሪ ተመድቦበት የነበረው የሥራ አይነትም ከብዙዎች ሥራዎች አንዱ በሆነው የአናጺነት ሥራ ነው፡፡ ሥራዎች ሁሉ በአንድ ጊዜ የሚያልቁ እንዳልሆኑም ከሥራው ባህርይ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረትም የአናጺናነት ሥራው በመጠናቀቁ ተጠሪ ተቀንሶአል፡፡ የዚህ አይነት የሰራተኞች ቅነሳ በሚያጋጥሙበት ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆነው በአዋጁ አንቀጽ 30 የተመለከተው ድንጋጌ ነው፡፡ ድንጋጌው ልዩ ሁኔታን በማስቀመጥ አሰሪው በአዋጁ

የተመለከቱትን የሰራተኞች ቅነሳ ሥነ-ሥርአት መከተል የለበትም ብሎአል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 28/2/ መሰረት ማስጠንቀቂያ እንዲሰጥ አይገደድም ማለት ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከአንቀጽ 30 ውጪ በማየቱ አመልካች በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስጠት ነበረበት እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ውሳኔ ሰጥቶአል ለማለት ችለናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 42790 ሰኔ 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 82438 ነሐሴ 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡ አመልካች ማስጠንቀቂያ መስጠት አያስፈልገውም ነበር፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 46276

የካቲት 11 ቀን 2002 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት - አንዳርጋቸው በየነ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች**፡- 1. ኃይሌ ይማም - ቀረበ፡፡

2. ዓሊ ሐሰን - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኞች መካከል የተነሳውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በዱብቲ ዱአር ወረዳ ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩት ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱት ሥራችንን በገዛ ፈቃዳችን ለመተው የፈለግን ስለሆነ የአገልግሎት ካሣ ከፍሎና ምስክር ወረቀት በመስጠት እንዲያሰናብተን ይወሰንልን በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪዎች በጡረታ የሚገለሉ ከመሆናቸው በተጨማሪ የአገልግሎት ካሣ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ግን ክርክሩን ውድቅ በማድረግ የተጠየቀውን የአገልግሎት ካሣ እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት በአፋር ብ/ክ/መ/የአውሲ ረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤትም እንደዚሁ ክርክሩን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ተጠሪዎች የአገልግሎት ካሣ /የስንብት ክፍያ/ ይከፈላቸው የመባሉን አግባብነት ከመመርመር አንፃር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በሥር ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክር ያልተካደው ወይም የተረጋገጠው ተጠሪዎች የክፍያ ጥያቄን እና ስንብትን መሠረት በማድረግ ክስ የመሠረቱት በጡረታ የሚገለሉበት ጊዜ እንደደረሰ ነው፡፡ አመልካች የክፍያ ጥያቄውን ከሥር ጀምሮ ሲቃወም የመጣውም ተጠሪዎች መደበኛ የጡረታ ዕድሜ የደረሱና የጡረታ አበልም የሚከፈላቸው ናቸው በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎችም በዚህ መልክ ከአመልካች የቀረበውን ክርክር የሚያስተባብል ክርክርም ሆነ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ ተጠሪዎች በአመልካች ዘንድ ማገልገላቸውን ብቻ በማየት ወሰኑ እንጂ በሕጉ የተቀመጠውን ድንጋጌ ከቀረበላቸው የፍሬ ነገር ክርክር ጋር አላገናዘቡም፡፡

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96"ን" ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2/2/ሰ/ እና /ሸ/ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39 እንደተደነገገው የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈለው ሠራተኛው የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት የሌለው ከሆነ እንደዚሁም ሥራውን ሲለቅ መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ያልደረሰ ሲሆን ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪዎች ሥራችንን በገዛ ፈቃዳችን ለቀናልና የስንብት ክፍያ እንዲከፈለን ይወሰንልን በማለት ክስ የመሠረቱት የጡረታ መውጫ እድሜያቸው ሳይደርስና ተገቢውን ዝግጅት እንዲያደርጉ አመልካች ካስታወቃቸው በኋላ እንደሆነ በአመልካች ክርክር ተመልክቶአል፡፡ ተጠሪዎች ይህ እውነት

ላለመሆኑ ያሳዩት ነገር የለም፡፡ ከዚህ እንግዲህ መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪዎች የጡረታ መብት ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ መደበኛ የጡረታ ዕድሜም የደረሱ መሆናቸው ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም የስንብት ክፍያ የሚያገኙበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጠው ውሣኔም ከዚህ አንፃር ሲታይ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በአፋር ብ/ክ/መ/ የዱብቲ ደአር ወረዳ ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ. 0956/2000 ሐምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የአውሲ ረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 1279 ግንቦት 10 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪዎች ያቀረቡት የሥራ ስንብት ክፍያ ሊያገኙ አይችሉም በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 42985

የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ኂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ውድመጣስ ኑሮ አስመጪና ላኪ ድርጅት - የቀረበ የለም

**ተጠሪ**፡- እነ አቶ ሁኝኛው ሰጠ (11 ሰዎች) - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪዎች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ አመልካች ያለአግባብ ከስራ ያሰናበታቸው በመሆኑ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ መልስ ሲሰጥ የተጠሪዎች የስራ ውል የተቋረጠው ድርጅቱ ለዘለቄታው ስራ በማቆሙ ስለሆነ የተጠየቀው ክፍያ ሊከፈል እንደማይገባና ተጠሪዎችም የቀን ሰራተኞች በመሆናቸው የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ እንዲሆን አመልክቷል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች ከስራ የተሰናበቱት ድርጅቱ ለዘለቄታው በመዘጋቱ ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት አመልካች የስራ ስንብት ክፍያና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ይህንን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ በቅሬታውም አመልካች ድርጅት የተዘጋው በባንክ እዳ ምክንያት ባንኩ ተረክቦት በመሆኑ ማስጠንቀቂያ መስጠት አስፈላጊ አይደለም እንዲሁም ተጠሪዎች በአዋጁ አንቀጽ 10/ሰ/ መሰረት የተቀጠሩ የቀን ሰራተኛ በመሆናቸው ስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ ይህ ችሎት የተጠሪዎች የስራ ስንብት ህጋዊ ከሆነ የስራ ስንብትና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈላቸው መወሰኑ አግባብ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪዎችም ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ መዝገቡም ተመርምሯል፡፡

አመልካች ድርጅት ለዘለቄታው በመዘጋቱ ተጠሪዎች ከስራ መሰናበታቸውን የስር ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች በክርክር ድርጅቱ የተዘጋው በባንክ እዳ ምክንያት ባንኩ ድርጅቱን በመረከቡ ስለሆነ የማስጠንቀቂቃ ጊዜ ሊከፈል አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ ነገር ግን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28/2/ሀ/ ሰራተኞች የተሰማሩባቸውን ስራዎች በከፊልም ሆነ በሙሉ በቀጥታና ለዘለቄታው የሚያስቀም የሰራተኛ ቅነሳ የሚያስከትል ሁኔታ ሲከሰት የስራ ውሉ በማስጠንቀቂያ ሊቋረጥ እንደሚችል ይገልፃል፡፡ ድንጋጌው የድርጅቱ ስራ በከፊል ብቻ ሳይሆን በሙሉ ለዘለቄታው ሲቆም ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ እንደሚገባው የሚያሳይ ነው፡፡ ድርጅቱ በሙሉ ስራ ካቆመ የቅነሳ ጥያቄ ሊነሳ አይችልም፡፡ ይልቁንም ሰራተኞች በሙሉ የሚሰናበቱበትን ሁኔታ ነው የሚያስከትለው፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ድርጅቱ ስራውን በሙሉ ለዘለቄታው የሚያስቆም ሁኔታ በመከሰቱ አመልካች የስራ ውሉን ሲያቋርጥ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ ይገባዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ የሚገባው ቅነሳ ሲደረግ ብቻ እንጂ ድርጅቱ እንዳለ ሲዘጋ አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪዎች የአመልካች ድርጅት ሰራተኞች መሆናቸው በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ አመልካች ተጠሪዎች የቀን ሰራተኞች ናቸው በማለት ይከራከር እንጂ የስር ፍ/ቤቶች ክርክሩን አልተቀበሉትም፡፡ የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ሰራተኛ ድርጅቱ በመክሰሩ ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቄታው በመዘጋቱ የስራ ውሉ ሲቋረጥ የስራ ስንብት ሊከፈል እንደሚገባ የአዋጁ አንቀጽ 39/1/ሀ/ ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ድርጅቱ ለዘለቄታው በመዘጋቱ ለተጠሪዎች የስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለውም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 34121 መስከረም 28 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 70887 ኀዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 49958

የካቲት 12 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ግዮን ትራብልና ቱርስ ኃ/የተ/የግ/ማ - ነ/ፈጅ ዳንኤል ወርቅዬ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ዳንኤል አስፋው - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሥራ ውል ማቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ ያለአግባብ ከሥራ መሰናበቱን ጠቅሶ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ በአመልካች በኩል ሥር ፍ/ቤት የቀረበው ክርክር ተጠሪው የሥራ ሃላፊው ላይ አላስፈላጊ አምባጓሮ፣ ፀብ፣ ዛቻ፣ ስድብ በመፍጠሩ ተሰናብቷል የሚል ነው ጉዳዩን በመ/ደረጃ የተመለከተው የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ሥራ አስኪያጅ ላይ እንደዛተ እንጂ አምባጓሮ ወይም ፀብ ስለፍጠሩ አልተረጋገጠም በሚል ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ሲል ፈርዷል፡፡ አመልካች የአምስት ወር ደመወዝ ለተጠሪ ከፍሎ ወደ ሥራ እንዲመለስ ሲልም ወስኗል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው የአመልካች ነ/ፈጅ ጥቅምት 21/2002 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው አቤቱታ ይዘት ተጠሪው የነዳጅ ያቀረበው ደረሰኝ የተጋነነ እና ታማኒነት የጐደለው በመሆኑ በሥራ አስኪያጁ ሲጠየቅ በአግባቡ ማስረዳት ሲገባው ጠብ አጫሪነት በመፍጠር ወይ አንተ ወይ እኔ እንኖራለን በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ ሪ መሰረት ጥፋት ስለመፈፀሙ መረጋገጡን

ስንብቱ ሕጋዊ ስለመሆኑ በአማራጭ ተጠሪው በአዋጁ አንቀጽ 43/1/ መሰረት ካሣ ተከፍሎት ሊሰናበት እንደሚገባ ራሱ የጠየቀው ዳኝነት የሥር ፍ/ቤቶች ማለፋቸው የሕግ ስሕተት መሆኑን ጠቅሶ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ትሎትም በተጠሪ ተፈጽሟል የተባለው ድርጊት ከአዋጁ አንቀጽ 27/1/ረ አንፃር ለመመርመር የሚገባው ሆኖ ስላገኘው ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት አድርጓል ተጠሪ የካቲት 12 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ የሕግ ስሕተት የለውም ሲል እንዲጸና ጠይቋል፡፡

እኛም የቀረበውን አቤቱታ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት የተቻለው ተጠሪው የአመልካች ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ላይ የዛቻ ኃይለ ቃል እንደተናገረው ተመስክሯል፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው የተጠሪ ድርጊት የአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ረ የተደነገገውን ጥፋት ያሟላል የሚል ክርክር በአመልካች በኩል ቀርቧል፡፡ ይህንኑ ለመመረመር የተጠቃሹን ድንጋጌ ይዘት በዝርዝር መመልከት ይገባል፡፡ አንቀጽ 27/1/ረ እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

“እንደጥፋቱ ክብደት በሥራው ቦታ አምባጓሮ ወይም ጠብ አጫሪነት ተጠያቂ መሆን” ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ለማቋረጥ ከሚያስችሉ ምክንያቶች ሥር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የሥራ አስኪያጅን “ወይ አንተ ወይ እኔ እንኖራታለን” በማለት የዛተበት ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር መሆኑ ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡ ይህ የተጠሪው ድርጊት ከተጠቀሰው ድንጋጌ አንፃር ሲታይ የጠብ አጫሪነት ኃይለቃል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የተጠሪው የድርጊት ዛቻ ነው ካለ በኋላ ይህ ድርጊት ፀብ ድርጊት ሊባል እንደማይችል ጠቅሶ ይህ ክብደት ሊሰጠው አይገባም ብሏል፡፡ በኛ በኩል ስንመረመረው አንድ ሰራተኛ የአሰሪው ወይም የሥራ ኃላፊው ትእዛዝ ከሕግ ውጪ እስካልሆነ ድረስ ማክበር እና መፈጸም እንዳለበት ልብ ሊባል ይገባል፡፡ አንድ ሰራተኛ አሰሪው ወይም የሥራ ኃላፊው የሚሰጠውን ሕጋዊ ትእዛዛት መፈጸም እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13/2/ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ ስለሥራው አካሄድ በሥራ አስኪያጅ ሲጠየቅ አግባብ ባለው ሥርአት ማስረዳት ሲገባው ለምን ተጠየቅኩ በሚል ስሜት ኃይለ ቃል እና ዛቻ ማድረጉ የጠብ አጫሪነት ድርጊት መባል የሚገባው ስለመሆኑ ተረድተናል፡፡

ድርጊቱም የተፈፀመው በአመልካች ድርጅት የሥራ አስኪያጅ ላይ መሆኑ የተጠሪን ድርጊት ጥፋት ከባድነት አመልካች ነው፡፡ ስለሆነም የተጠሪው ድርጊት የአዋጁን አንቀጽ 27/1/ረ የተመለከተውን ጥፋት አያሟላም ሲል የሥር ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ሕግ ያስቀመጠውን የሰራተኛውን ግዴታ የሚመለከተውን ድንጋጌ እና የጥፋቱን አደገኛነት ከተጠቃሹ ድንጋጌ አንፃር በአግባቡ ሳያገናዝብ መሆኑን ስለተረዳን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40658 የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 83563 የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ረ መሰረት በመሆኑ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ሊባል አይገባም ብለናል፡፡

ግራ ቀኝ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 40529

የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የሕፃን ዮናታን ነጋ ተሻገር ሞግዚት - ጠ/ጥጋቡ ጌጤ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ለገሰ አበራ - ጠ/ወርቁ መንገሻ ቀረቡ

መዝገቡን መርመረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ ለሰራተኛው ጥገኞች ስለሚከፈል ካሣ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110 አተረጓጐምን የሚመለከት ነው፡፡

የአመልካች አባት አቶ ነጋ ተሻገር በተጠሪ ተቀጥረው ለሥራ ሲንቀሳቀሱ ሕይወታቸው በማለፉ ያልተከፈለ ደመወዝ ብር 6,500 /ስድስት ሺህ አስምት መቶ/፣ ያልተከፈለ አበል ብር 9,750 /ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ/፣የቀብር ማስፈጸሚያ ወጪ ብር 2000 /ሁለት ሺ.ህ/ እና ሟች ሌላ ጥገኛ ስላልነበራቸው የሞት ካሣ ክፍያ ብር 60,000 /ስልሳ ሺህ/ እንዲከፈል አመልካች በሞግዚቱ አማካይነት ክስ መሰረተ፡፡ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ያቀረቡትን የመጠን ክርክር በማስረጃ አጣርቶ ከካሣ ገንዘብ በተቀረ ሌሎቹን እንደ ክሱ አቀራረብ ወስኗል የሞት ካሣ አከፋፈል አስመልክቶ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110/3/ /ለ/ እድሜያቸው 18 ዓመት ያልሞላቸው ልጆች የእያንዳንዳቸው ድርሻ 10% ብቻ ነው በሚል ከተጠየቀው ብር 60,000 /ስልሳ ሺ.ህ/ ውስጥ 10,000 (አስር ሺ.ህ) ብቻ እንዲከፈል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤትም ተጠቃሹ ድንጋጌ የአንዱን ጥገኛ ድርሻ ለሌላኛው እንዲከፈል ሕጉ በግልጽ አልደነገገም የሚል ምክንያት ሰጥቶ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የአዋጁን አንቀጽ 110/3/ በአግባቡ አልተረጐመም፣የሟች ብቸኛ ወራሽ እና ጥገኛ አመልካች ነው፤እንዲሁም ሟች ሚስት አልነበረውም፤የሚስትም ድርሻ ጭምር ታስቦ ለአመልካች ሊከፈል ይገባል አመልካችም የተወለደው ከጋብቻ ውጪ ነው የአመልካች ሞግዚት አክስቱ ናቸው በሚሉ ፍሬ ነገሮች መነሻ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲታረም አመልክተዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤት የአዋጁን አንቀጽ 110 አተረጓጐም አግባብነት ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩ ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የአመልካች ወላጅ አባት በተጠሪ ተቀጥረው ሥራ ላይ እያሉ ሕይወታቸው ማለፉ አላከራከረም፡፡ የአመልካች አባት በሥራ ላይ በሞት የተለዩ ስለመሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የሞት ካሣ ለጥገኞች ስለሚከፍልበት ሁኔታ በዝርዝር የተደነገገው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 110 እንመለከታለን፡፡

በተጠቀሰው አንቀጽ 110/1/ የተመለከተው ሊከፈል የሚገባው የክፍያ ዓይነት ነው፡፡ ይህም አንዱ ለጥገኞች የሚከፈል ካሣ ነው፡፡ ለጥገኞች የሚከፈል ካሣ መጠን እና ጥገኞች የሚባሉት እነማን እንደሆኑ ድንጋጌው በቀጣይ ንኡስ አንቀጾች አመልክቷል፡፡ የሟች ጥገኞች ብሎ ሕጉ የዘረዘራቸው የሟች ልጆች ሆነው 18 ዓመት በታች የሆኑ፣የሟች

ሕጋዊ ባል ወይም ሚስት እና በሟች ሰራተኛ ድጋፍ ይረዱ የነበሩ የሟች ወላጆች መሆናቸውን አንቀጽ 110/2/ ዝርዝር ያመለክታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከአመልካች ሌላ የቀረበ የሟች ጥገኛ ነኝ ባይ የሌለ መሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ቀጥሎ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ የካሳ ስሌት እና የአከፋፈሉ ሁኔታ ነው፡፡ ሊከፈል የሚገባው ካሳ መጠን አስመልክቶ የአዋጅ አንቀጽ 110/3/ የመጀመሪያው አረፍተ ነገር ይገልፃል፡፡ ይኸውም "የሰራተኛው የዐመት ደመወዝ በአምስት ተባዝቶ የሚገኘው" የገንዘብ መጠን ነው፡፡ ስለሆነም የክፍያው መጠን ጣሪያ በሕጉ በግልጽ ተወስኗል፡፡ ከዚህ ተከትሎ የሚታየው ይህንን ገንዘብ በጥገኞች መካከል የሚከፋፈልበት ሥርአት የሚያመለክት ድንጋጌ ነው፡፡ ለዚህም የሟች ጥገኞች ናቸው ተብለው ከላይ የተዘረዘሩት የእያንዳንዳቸው ድርሻ መጠን በመቶኛ በአንቀጽ 110/3/ ሀ-ሐ ተዘርዝሯል፡፡ ከፍ ሲል የተመለከትነው የጥገኞች ማንነት፣ሊከፈል የሚገባው ካሣ መጠን ጣሪያው እና የስሌቱ አወሳሰን እንዲሁም የጥገኞች ድርሻ መጠን አስመልክቶ በሕጉ የተዘረዘሩትን መሰረተ ሐሳቦች ነው፡፡

ከተያዘው ጉዳይ አንፃር አከራካሪው ሟች አንድ ጥገኛ ብቻ ያለው መሆኑ በታወቀ ጊዜ ሊከፈል የሚገባው የካሳ መጠን ጣሪያው የተወሰነው (100%) ወይንስ ከላይ በዝርዝር በተመለከተው መሰረት የጥገኛው ማንነት ተከትሎ የተቀመጠው መቶኛ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን አከራካሪ ጭብጥ መልስ ለማግኘት የአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌ አንቀጽ 110/4/ በዝርዝር መመርመር ተገቢ ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘት እንዲህ ይነበባል፡፡

> "በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 የክፍፍል መጠን መሰረት ተሰልቶ የክፍፍሉ መጠን በድምር (100%) (መቶ በመቶ) የሚበልጥ እንደሆነ የክፍፍሉ ድምር መጠን 100%(መቶ በመቶ) እስኪሆን ከእያንዳንዱ ጥገኛ ላይ ጥገኛ በየመጠኑ ይቀነሳል፡፡ እንዲሁም የክፍፍሉ መጠን መከፈል ከሚገባው አጠቃላይ መጠን የሚያንስ የሆነ እንደሆነ የክፍፍሉ መጠን መቶ በመቶ እስከሚሆን ለእያንዳንዱ ጥገኛ ድርሻ እንደመጠኑ የጨመራል" ይላል፡፡
>
> አንቀጽ 110/4/ ይመለከታል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር መገንዘብ የሚቻለው የእየንዳንዱ ጥገኛ ድርሻ ተዳምሮ ሊከፈል ከሚገባው ጣሪያ (ወሰን) በላይ የሚሆን ከሆነ የእያንዳንዱ ጥገኛ ድርሻ በመቶኛ በሕጉ ከተሰጠው ሊቀነስ እንደሚገባ ነው፡፡

የዚህ ድንጋጌ መንፈስ ሟች ሰራተኛ በርካታ ጥገኞች ቢኖሩት በአዋጁ አንቀጽ 110/3/ ሀ-ሐ በተቀመጠው መጠን ለእያንዳንዱ እየተሰላ የአሰሪውን ሃላፊነት መጠን ከጣሪያው(ወሰን) እንዳያልፍ ወይም የአሰሪው ሃላፊነት በአንቀጽ 110/3/ የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ከተቀመጠው የሥሌት መጠን እንዳያልፍ ለመከላከል ነው፡፡ ይህ የሕጉ ሐሳብ ተፈፃሚነት የሚኖረው ሟች ሰራተኛ በርካታ ጥገኞች ኖሮት የእያንዳንዳቸው ድርሻ በመቶኛ ድምር ከጠቅላላው መቶኛ ድምር በላይ ሆኖ ሲገኝ ነው ማለት ነው፡፡ አንቀጽ 110/4/ ሁለተኛው ዐረፍተነገር ይዘት ደግሞ ሲታይ ሟች ሰራተኛ ያለው ጥገኛ ቁጥር አነስተኛ ሆኖ የእያንዳንዳቸው ድርሻ ስሌት ተደምሮ አሰሪው ሊከፈል ከሚገባው በታች ሆኖ ሲገኝ ቀሪውን መቶኛ ገንዘብ ሌሎቹ ጥገኞች እንዲያገኙት ለማድረግ እንደሚቻል የታሰበ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ማለት ሟች ሁለት ልጆች ብቻ ቢኖሩት እና ሚስት ባይኖረው በአንቀጽ 110/3/ /ለ/ መሰረት የልጆቹ ድርሻ 20% ሲሆን ቀሪው 80% ተጠቃሚ (ባለመብት ጥገኛ) የለውም ተብሎ የሚቀር ሳይሆን ለእነዚሁ ልጆች እንደየድርሻው በመቶኛ ሊጨመርላቸው እንደሚገባ የሚያመላክት ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ መንፈስ የጥገኞች ቁጥር አነስተኛ ከሆነ የአሰሪ ሃላፊነት ጣሪያ ወሰን ድረስ ያሉት ጥገኞች ተጠቃሚ እንዲሁኑ ለማድረግ ያሰበ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ሟች አቶ ነጋ ተሻገር ከአመልካች ሌላ ጥገኛ ስለመኖሩ የቀረበ የለም፡፡ በሥር ፍ/ቤት የተወሰደው አቋም አመልካች ድርሻ 10% ብቻ ነው የሚል ነው፡፡ ነገር ግን የአንቀጽ 110/4/ ድንጋጌ ሁለተኛው ዐረፍተ ነገር እንደሚያስገነዝበው አመልካች ብቸኛ የሟች ጥገኛ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የተጠሪ የሃላፊነት መጠን ጣሪያ ድረስ ካሳው ሊከፈለው ይገባል፡፡ ይህም ማለት የአመልካች ድርሻ 10%(አስር በመቶ) ሳይሆን መቶ በመቶ(100%) ነው፡፡

ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንን በአግባቡ ሳይገናዝቡ የአመልካች ድርሻ 10% ብቻ ነው በማለት የአዋጁን አንቀጽ 110/3/ለ በመጥቀስ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

የአመልካች ድርሻ መቶ በመቶ ነው ከተባለ ስሌቱ ምን ያህል ነው ለሚለው የሥር ፍ/ቤት የአመልካች አባት ደመወዝ በወር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ መሆኑን መሰረት አድርጐ የሰጠው ፍርድ ተጠሪ ስላልተቃወሙ በአንቀጽ 110/3/

መሰረት በሞት ምክንያት ሊከፈል የሚገባው የካሣ መጠን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ብር 60,000 (ስልሳ ሺህ ብር) መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22962 የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 66031 የሰጠው ውሳኔ የአመልካች የካሣ ድርሻ አስመልክቶ የሰጡት የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሎ ተከታዩ ተወስኗል፡፡
2. አመልካች የሟች አቶ ነጋ ተሻገር ብቸኛ ጥገኛ መሆኑ ስለተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110/4/ መሰረት ካሣ ሙሉ ለሙሉ ሊከፈለው ይገባል ብለናል፡፡ ስለሆነም በሟች ደመወዝ ተሰልቶ የቀረበው ብር 60,000 (ሥልሳ ሺህ ብር) ይከፈለው ብለናል፡፡ የሥር ፍ/ቤት በዚሁ መሰረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡

የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁጥር 48648

የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የዓልቂ የትምህርትና የተቀናጀ የልማት ማህበር - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ታጠቅ ደጀኔ
2. አቶ ተፈሪ በርቤ } ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት የቀረበውን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ ሚያዚያ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ አንደኛ ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ታህሳስ 13 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በፕሮግራም ማናጀርነት፣ ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ ከጥቅምት 03 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በኮሚኒቲ ወርከር የስራ መደብ ተቀጥረው እንደሰሩና የስራ ውሉ ያላግባብ ሚያዚያ 08 ቀን 2001 ዓ.ም መቋረጡን ገልፀው ካሳ፣ የስራ ስንብት፣ ክፍያ ለዘገየበት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የሚያዚያ ወር ደመወዝ እና የዓመት እረፍት ክፍያ ከወጪና ኪሳራ ጋር ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚይሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ድርጅትም ለክሱ በሠጠው መልስ፣ ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች ሆነው የስራ ቅጥር ውላቸውም ለማህበሩ በለጋሽ ድርጅቶች የሚሠጠው እርዳታ በመቆሙ ፕሮጀክቱ የተዘጋ ስለሆነ መቋረጡን ገልፆ የስራ ውል የተቋረጠው በሕጉ አግባብ በመሆኑ የተጠየቁት ክፍያዎች ሊከፈሉ አይገባም ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ክርክሩንና ማስረጃዎችን መርምሮ የስራ ውሉ ለአንድ ፕሮጀክት ተጠሪዎች የተቀጠሩ ስለመሆኑ የማያሳይ፣ ተጠሪዎች ለተወሰነ ስራ የተቀጠሩ ሰራተኞች ናቸው ስለማይባሉ፣ በአንድ ፕሮጀክት መዘጋት ምክንያት ተጠሪዎችን ማሰናበቱ ህጋዊ አይደለም የሚል ምክንያት በመያዝ የአመልካችን ክርክር ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ ተጠሪዎች ካሳ፣ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የሚያዚያ ወር ደመወዝ እና የዓመት ፈቃድ ክፍያ አመልካች ሊከፍላቸው ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ስንብቱ ሕገ-ወጥ ተብሎ ውጤቶቹን በተመለከተም የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ነሐሴ 01 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪዎች ለተወሰነ ስራ የተቀጠሩና የተቀጠሩበት ፕሮጀክት የተዘጋ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ተብሎ ተጠሪዎች የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የተጠሪዎች የስራ ውል ለተለየ ፕሮጀክት የተቀጠሩ መሆኑን የሚያስረዳ ባለመሆኑ ተጠሪዎች ይሰሩበት የነበረው ፕሮጀክት ተቋርጧል በሚል የስራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው መባሉ እና የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪዎች ቀርበው ታህሳስ

13 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለጠቅላላ ፕሮጀክት በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ቅሬታ ነጥቦች ተገቢነት የሌላቸው መሆኑን፣ በአንፃሩ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትን ውሳኔ ተገቢነት ያለው መሆኑን በመዘርዘር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተፈፀመም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም ታህሳስ 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ የመልስ መልስ ሠጥተዋል፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሮ ግራ ቀኙን ጥር 12 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ያነጋገረ ሲሆን ግራ ቀኙ የስራ ውል ለጠቅላላ ፕሮጀክት የተደረገ መሆኑንና አመልካች ድርጅትም በአሁኑ ወቅት ስራውን እየሰራ እንደሚገኝ ተማምነዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካች እርምጃ ሕገ-ወጥ ተብሎ ተጠሪዎች የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ የተወሰነው ባግባቡ ነው ወይም አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ተጠሪዎችን አሰናበትኩ የሚለው ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ፕሮጀክት በመዘጋቱ ነው የሚል ምክንያት ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ቅጥሩ ለተዘጋው ፕሮጀክት ሳይሆን ለጠቅላላ ፕሮጀክት ሆኖ ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ ይገኛል በማለት የሚከራከሩ ሆኖ ቅጥሩ ለጠቅላላ ፕሮጀክት ስለመሆኑ በዚህ ችሎት በተደረገው ማጣራት መረጋገጡን ነው፡፡ ይህ ፍሬ ነገር ከተረጋገጠ ደግሞ በተጠሪዎች እና በአመልካች መካከል ያለው ግንኙነት መገዛት ያለበት በመካከላቸው በተቋቋመው ውል በመሆኑ ተጠሪዎች በአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 10(1ሀ) መሰረት ለአንድ ለተለየ ፕሮጀክት የተቀጠሩ ሰራተኞች አለመሆናቸውን መገንዘብ አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 30005 ሰኔ 03 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 52383 ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም በከፊል የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## <u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

በዚህ ችሎት ነሐሴ 29 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 47825

የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ አ.ማ - ነ/ፈጅ አስቴር በቀለ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ዘርዓየሁ ስሜ
2. አቶ ሽፈራው አራጋው } ጠበቃ ክፍሌ ታደሠ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ከአመልካች ጋር የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት እንደነበራቸው፣ ይህ ግንኙነታቸው የተቋረጠው በተጠሪዎች ፈቃድ መሆኑን፣ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ሊከፈላቸው የሚገባው ደመወዝ ሳይከፈላቸው የቀረ መሆኑን፣ ልዩነቱ መከሰቱን ያወቁት መንግስት የደመወዝ ጭማሪ ወይም ማስተካከያ ማድረጉን የካቲት 28 ቀን 2000 ዓ.ም ከጻፈው ደብዳቤ መሆኑን፣ የደመወዝ ማስተካከያው ከሕዳር 01 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን መወሰኑን፣ በዚህም መሰረት አንደኛ ተጠሪ ሊከፈላቸው ከሚገባው ደመወዝ ብር 6338.84(ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሰማንያ አራት ሳንቲም)፣ ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ ብር 14430.93(አስራ አራት ሺህ አራት መቶ ሰላሳ ከዘጠና ሶስት ሳንቲም) መሆኑን ገልፀው ይኸው በልዩነት የመጣውን ገንዘብ አመልካች እንዲከፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር መከራከሪያ ነጥቦችን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረባቸውን የመከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ ከማድረጉም በላይ ለተጠሪዎች ክስ ኃላፊነት አለበት በማለት የክሱን ገንዘብ ለተጠሪዎች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሐምሌ 24 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር ማመልከቻ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የስር ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የቀረቡትን የአመልካችን መከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ ያደረገው ያላግባብ መሆኑን፣ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የነበራቸው የስራ ግንኙነት በገዛ ፈቃዳቸው ከተቋረጠ በኋላ መንግስት ያደረገው የደመወዝ ማስተካከያ እንዲከፈላቸው የተወሰነው ከመመሪያው ዓላማና መንፈስ ውጪ መሆኑን ዘርዝረው ውሳኔው ሊሻር ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ተጠሪዎች ከአመልካች ድርጅት ስራ ከለቀቁ በኋላ ተፈቀደ የተባለው የደመወዝ ስኬል ጭማሪ ተጠሪዎችን ይመለከታል ወይስ አይመለከታቸውም? የሚለውን እና ሌሎችን ነጥቦች ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የተጠሪዎች ጠበቃ ሕዳር 23 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተገቢነት አለው የሚሉባቸውን ምክንያቶች

ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩላቸው ሕዳር 25 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረው የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት በተጠሪዎች ፈቃድ ከጥር 03 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ መቋረጡን፣ በዚህ ወቅት ተጠሪዎች ከአመልካች ድርጅት ሲሰናበቱ በወቅቱ ሊከፈላቸው ይገባል የተባለው የተለያየ ክፍያ መከፈሉን፣ ተጠሪዎች ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ በአመልካች ላይ ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት የካቲት 28 ቀን 2000 ዓ.ም የደመወዝ ጭማሪ መመሪያው ተፅፎ ከህዳር 01 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ጭማሪው ተግባራዊ እንዲሆን ከተወሰነ በኋላ መሆኑን ነው፡፡ እንግዲህ ተጠሪዎች የመብት ጥያቄው ምንጭ ነው የሚሉት የስራ ውሉ ከመቋረጡ በፊት ለሰሩበት ስራ በደመወዝ ጭማሪ መመሪያው መሰረት ሊከፈለን የሚገባው የደመወዝ ልዩነት አለ በማለት ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰራተኛ ከአሰሪው ጋር በሚፈጥረው የስራ ግንኙነት መሰረት ሕጉ የሚፈቀደው ማንኛውም መብት የሚጠበቅለት መሆኑ አከራካሪ አይሆንም፡፡ የአንድ መብት ወይም ግዴታ መሠረት ደግሞ ሕግ ወይም ውል መሆኑ ይታወቃል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ተጠሪዎች የጠየቁትን ክፍያ የሚያገኙበት የሕግ መሰረት አለ ወይስ የለም? የሚለው ነው፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የደመወዝ ስኬል ማስተካከያ መመሪያው ከመውጣቱ በፊት ተጠሪዎች በገዛ ፈቃዳቸው ስራቸውን ስለለቀቁ መመሪያው በስራ ላይ ያሉትን ሰራተኞች ለማበረታታት የወጣ እንደመሆኑ መጠን ሊከፈላቸው የሚገባ ቀሪ ደመወዝ የለም በማለት ነው፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት አለው የተባለው መመሪያም የወጣበት መሰረታዊ ዓላማ ሲታይ የፋይናንስ ድርጅቶች ሰራተኞች የሆኑት በጭማሪው ተነቃቅተው ከፍተኛ ውጤት ለማስመዝገብ ስለመሆኑ በመግቢያው ላይ የተገለፀ መሆኑን የስር ፍርድ ቤትም ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ የመመሪያው መሰረታዊ ዓላማ ይህ ከሆነ መመሪያው ከመውጣቱ በፊት ስራውን በገዛ ፈቃዱ የለቀቀ ሰራተኛ ወደኋላ ተመልሶ ማስተካከያውን መሰረት አድርጎ ቀሪ ደመወዝ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግም ሆነ የስነ አመክንዮ(ሎጂክ) አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች የተጠሪዎችን የዳኝነት ጥያቄ ከመመሪያው ዓይነተኛ ዓላማ ጋር በማዛመድ መመልከት ሲገባቸው ይህንኑ ሳያደርጉ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ ለተጠሪዎች በቀሪነት የሚፈለጉት ደመወዝ ይከፈል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35175 መጋቢት 30 ቀን 2001 ዓ/ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 80204 ሐምሌ 06 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የነበራቸውን የስራ ግንኙነት በገዛ ፈቃዳቸው ከለቀቁ በኋላ በወጣው የደመወዝ ጭማሪ ማስተካከያ መመሪያ መሰረት የሚከፈላቸው ቀሪ ደመወዝ የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 47535

መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት - ነ/ፈጅ ታደለ ገ/ወልድ

**ተጠሪ**፡- አቶ አንማው ላቀው - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በደብረ-ማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ድርጅት ያለአግባብ ከስራና ከደሞዝ ስላገዳቸው ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ካልቻለ የስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ድርጅት ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ የፈፀሙት ድርጊት በዲሲፒሊን ታይቶ ተጠሪ ለአንድ ወር በታገዱበት ላለው ጊዜ ደሞዝ ሳይከፈላቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ስለተወሰነ ደሞዝ ሊከፈላቸው አይገባም ብሏል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን መርምሮ አመልካች ተጠሪን ያገደው ያለአግባብ መሆኑን አምኖበት ወደ ስራ ስለመለሳቸው የመስከረምና የጥቅምት ወር ደሞዛቸው ይከፈላቸው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለምስ/ጐጃም አስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ተጠሪን ሳይጠራ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ በድምጽ ብልጫ አቤቱታው ውድቅ ተደርጐበታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው ተጠሪ ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው የመጨረሻ የፁሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው መሆኑ ተገልፆ እያለ ከስራ የታገዱት ያለአግባብ መሆኑ ታምኖበት ወደ ስራ ስለተመለሱ ደሞዛቸው ይከፈላቸው መባሉ ስህተት ነው፣አሰሪ ሰራተኛው ጥፋተኛ ሆኖ ካገኘው ለ30 ቀናት ከደሞዝና ከስራ አግዶ ለማቆየት እንደሚችል አዋጁ ስልጣን ስለሚሰጠው ለታገዱበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፈላቸው የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት አለበት ብሏል፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ በቀረበበት የዲሲፒሊን ክስ ምክንያት ለታገደበት ጊዜ ደሞዝ ይከፈላቸው የመባሉን አግባብነት ለመመረመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም ለቀረበባቸው አቤቱታ መልሳቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ በመልሳቸውም አመልካች ጥፋት ሳይፈጽሙ ለአንድ ወር ከስራና ከደሞዝ ታግደው የመጨረሻ ደረጃ የፁሁፍ ማስጠንቀቂያ የሰጣቸው ያለአግባብ መሆኑን በመግለጽ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ እንደሚከተው መርምሯል፡፡

ተጠሪ ከስር ፍ/ቤት ክስ የመሰረቱት አመልካች ያለአግባብ ከስራና ከደሞዝ ስላገዳቸው ለታገዱበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፈላቸውና ወደ ስራ እንዲመልሳቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ለፈፀሙት ጥፋት ጉዳዩ በዲሲፒሊን እስከሚታይ ድረስ ከደሞዝና ከስራ ማገድ ስለሚችል ጥያቄው ውድቅ እንዲሆንለት አመልክቷል፡፡ አመልካች ለክርክሩ መሰረት ያደረገው አ/ቁ. 377/1996 እና የድርጅቱን ህብረት ስምምነት ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ተጠሪ ከስራና ከደሞዝ ለታገዱበት ጊዜ ደሞዝ ሊከፈላቸው የሚገባ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ ይህንንም ጭብጥ ለመመለስ ችሎቱ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁንና በወቅቱ በስራ ላይ የነበረውን የድርጅቱን ህብረት ስምምነት ተመልክቷል፡፡ በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 27/4/ ስር ያለማስጠንቀቂያ የሰራተኛውን የስራ ውል እንዲቋረጥ ከመደረጉ በፊት ሰራተኛውን ከስራ አግዶ ማቆየት ስለሚቻልበት ሁኔታ በህብረት ስምምነት ሊወሰን እንደሚችልና የእገዳው ጊዜ ግን ከ30 ቀናት እንደማይበልጥ ተደንግጓል፡፡ አመልካች የሚከራከረው የድርጅቱ ህብረት ስምምነት ጥፋት የፈፀመ ሰራተኛ ጉዳዩ በዲሲፒሊን እስከሚታይ ለ30 ቀን ከስራና ከደሞዝ አግዶ ማቆየት እንደሚቻል ተደንግጓል በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ጥፋቱን ፈጽመዋል ተብለው ከስራ የታገዱት ከመስከረም 2001 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ ችሎቱ በወቅቱ በስራ ላይ የነበረውን

የድርጅቱን የህብረት ስምምነት ተመልክቷል፡፡ በዚህ ህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 51 ስር ማንኛውም ሰራተኛ ከባድ ጥፋት በመፈፀሙ ምክንያት ጥፋቱ ተጣርቶ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ ከ30 ቀናት ሳልበለጠ ጊዜ ከመደበኛ ሥራው ያለደሞዝ እንዲታገድ ማድረግ እንደሚቻልና ለውሳኔው መዘግየት ሰራተኛው ራሱ ምክንያት መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ከ30 ቀናት በላይ ላለው ጊዜ ደመወዝ እንደሚከፈለው ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሰራተኛው ጥፋት ሲገኝበት ጉዳዩ እስከሚጣራ ለአንድ ወር ከስራና ደሞዝ ሊያግደው እንደሚችል የአመልካች ድርጅት ህብረት ስምምነት ይፈቅዳል፡፡ ይህ ደግሞ አዋጁን መሰረት አድርጐ የወጣ የስምምነት ቃል በመሆኑ ተጠሪ ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ በመሆኑ አመልካች ተጠሪ ፈጸሙ ያለውን ጥፋት እስከሚያጣራ ከስራና ላገደበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፍል አይገደድም፡፡ የስር ፍ/ቤት አዋጅንና የህብረት ስምምነቱን ድንጋጌዎች ሳይመረመር ተጠሪ ከስራ ለታገዱበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፈል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ከስራ የታገዱት ለሁለት ወራት መሆኑና የሁለት ወር ደሞዝ ያልተከፈላቸው ስለመሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ነገር ግን ከፍ ሲል እንደተመለከተነው ሰራተኛው ከስራና ደሞዝ ሊታገድ የሚችለው ለ30 ቀናት ብቻ ነው፡፡ የህብረት ስምምነቱ ከ30 ቀን ደሞዝ የማይከፈለው ውሳኔው የዘገየው በሰራተኛው ምክንያት ከሆነ ብቻ እንደሆነ ቢደነግግም አመልካች ውሳኔው በተጠሪ ምክንያት ስለመዘግየቱ ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለሁለት ወራት ከስራና ከደሞዝ መታገዳቸው አዋጁንም ሆነ የሕብረት ስምምነቱን የሚቃርን በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ የመስከረም ወር እንዲከፈላቸው መወሰኑ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደብረ-ማርቆስ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 5852 ታህሣሥ 21 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን፣ምስ/ጐጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 96588 ጥር 4 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 00973 ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ከስራ ለታገዱበት አንድ ወር ጊዜ ደሞዝ ሊከፈላቸው አይገባም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ያልተከፈላቸው የመስከረም ወር 2001 ዓ.ም ደሞዛቸው እንዲከፈል የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 49750

መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/01 የመዝናኛ ክበብ -

ጠበቃ አሰፋ ዝቅአርጋቸው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ማስረሻ ሁሴን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ ክሳቸውም ሰኔ 01 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ ሁኖ ይዘቱም ባጭሩ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከነሐሴ 01 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ተቀጥረው በወር ደመወዝ ብር 314(ሦስት መቶ አስራ አራት) እየተከፈላቸው በመስራት ላይ እንዳሉ ያላግባብ ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም ከስራ የተሰናበቱ መሆኑን በመግለፅ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለክሱ በሠጠው መልስ፤ ስንብቱ የተከናወነው ተጠሪ የድርጅቱን ትዕዛዝ ባለማክበራቸው ስለመሆኑ በመግለፅ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት አመልካች ድርጅት ለተጠሪ የስራ ስንብት፣ የካሣ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ እንዲከፍላቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥቅምት 06 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ የተሰናበቱት የአመልካችን ትዕዛዝ ሊያከብሩ ባለመቻላቸው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት ለሕብረት ስምምነቱ አፈፃፀም የተዛባ ትርጉም በመስጠት ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ጥር 25 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃም የካቲት 09 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የአመልካች ሰራተኛ ሆነው በሚሰሩበት የስራ ሠዓት ወቅት አመልካች የድራፍት በርሜል እንዲረከቡ ትዕዛዝ ሲያስተላልፍላቸው ሊቀበሉ ያልቻሉ መሆኑ የስር ፍርድ ቤት አረጋግጦ ይህ

የተጠሪ ድርጊት ከስራ ለመሰናበት ሕጋዊ ምክንያት አይደለም ለማለት የቻለው በሕብረት ስምምነቱ እንደጥፋት ቢጠቀስም ሰራተኛው ትዕዛዙ ሕገ-ወጥ እስከሆነ ድረስ ለመቃወም የሚችል ስለመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13(2) ድንጋጌ መረዳት ይቻላል በሚል ነው፡፡ በእርግጥ አንድ ሰራተኛ በስራ ውሉ ላይ የተጣለውን ግዴታ የመወጣት ኃላፊነት ያለው ስለመሆኑ ይኸው የተጠቀሰው ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል በአዋጁ በአንቀጽ 27(1/ሸ) ድንጋጌ ሕጉ ካስቀመጣቸው በተጨማሪ በሕብረት ስምምነቱ ላይ ከስራ ሊያስባርሩ የሚችሉ ጥፋቶችን መወሰን እንደሚቻል ተመልክቷል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ተጠሪን ከስራ ሊያሰናብታቸው የቻለው በሕብረት ስምምነቱ መሆኑን በመጥቀስ የሚከራከር ሲሆን የህብረት ስምምነቱ አለመታዘዝ ከማስጠንቀቂያ በኂላ ከስራ ሊያስባርር እንደሚችል ተቀምጧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህ የሕብረት ስምምነቱ ክፍል በዚህ መልኩ መቀመጡ የተረጋገጠ ቢሆንም ተቀባይነት የለውም ያለው ለሰራተኛው ከሕጉ ከተቀመጠው ጥቅም ያነሰ ያስገኛል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሕጉ ከሕጉ ከተቀመጡት ጥፋቶች ውጪ በሕብረት ስምምነቱ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያስባርሩ ይችላሉ ተብሎ መደንገግ የሚቻል መሆኑን ከማስቀመጡም በላይ በአዋጁ አንቀፅ 134(2) መሰረት የሕብረት ስምምነቱ ለሰራተኛው ሕጉ ካስቀመጠው ጥቅም ያነሰ የሚያስገኝ ሆኖ ከተገኘ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ጥፋትና ጥቅምን በተመለከተ ሕጉ የተለያየ አቋም የያዘ መሆኑን እንጂ አሰሪና ሰራተኛ በሕብረት ስምምነቱ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት በማለት የተስማሙበት ድርጊት ተቀባይነት የለውም የሚለውን ነጥብ አይደለም፡፡ አንድ ሰራተኛ የአሰሪውን ትዕዛዝ ማክበርም ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 13(7) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ህጋዊ መሰረት የሌለው ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ቤትም ይህንኑ ሳያርም ማለፉ ተገቢነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፤ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 56547 ሐምሌ 09 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 83500 ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የስራ ውል ያቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከፕሮቪደንት ፈንድ ውጪ የሚከፈላቸው ክፍያ የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 49797

መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አልሀበሽ ሹገር ሚልስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር -

ተወካይ አቶ ተካልኝ መለሰ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ተገኔ ገ/ሄዋርያት - ከጠበቃ አብዱራህማን መሐመድ ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 54585 ሀምሌ 17 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ጥቅምት 2 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡

ክርክሩ የታየው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርቦ በወር ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) እየተከፈለው በአመልካች ድርጅት ሢሠራ እንደነበር ገልፆ አመልካች መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም ከሥራ አላግባብ ያሰናበተኝ ስለሆነ ወደ ሥራ እንድመለስ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሉኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ተጠሪን ያሰናበተው መኪናና ሹፌር ተመድቦለት እየተገለገለ እያለ ታህሣሥ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የድርጅቱን መኪና ቁልፍ ከሹፌሩ በመረከብ በማሽከርከር ላይ እያሉ የድርጅቱን መኪና በማጋጨት ጉዳት አድርሷል፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህጉን መሠረት ያደረገ በመሆኑ የከሳሽ (ተጠሪ) ጥያቄ ተገቢነት የለውም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ለመደገፍ ያቀረቡትን ማስረጃ ሣይሰማና ሣይመረምር አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው የሥራ ስንብት ደብዳቤ ፅፎ ሣይሆን በቃል በመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት አመልካች ለተጠሪ የአምስት ወር ደመወዝ በመክፈል ወደሥራው እንዲመልሰው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ከሥራ የተባረረው በጥፋቱ ነው፡፡ ተጠሪን የጥፋቱ ተጠቃሚ የሚያደርግ ውሣኔ መሠጠቱ የህግ ስህተት ያለበት ውሣኔ ነው፡፡ ተጠሪ ከሥራ የተባረረው የሥራ ውሉ ሊጠናቀቅ አንድ ወር ሲቀረው በመሆኑ የአምስት ወር ደመወዝ ከፍላችሁ ወደሥራ መልሱ በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ችሎት ማስረጃችንን በመቀበል ውሣኔ ይሰጥልን በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እኔ የተቀጠርኩት ላልተወሰነ የሥራ ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች የሥራ ውሉ ሊጠናቀቅ አንድ ወር ሲቀረው ነው ያሰናበትኩት በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች በህጉ የተመለከተውን ሥርዓት ሣያሟላ ከሥራ ማሰናበቱ ህገ-ወጥ ስለሚያደርገው የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የቀረበው ክርክርና በሰበር ያቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው በፅሑፍ ሣይሆን በቃል መሆኑ ብቻ

ስንብቱ ህገ-ወጥ መሆኑን ያሣያል በማለት አመልካች ተጠሪን የአምስት ወር ደመወዝ ከፍሎ እንዲመልስ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ለዚህ ጭብጥ እልባት ለመስጠት በመጀመሪያ የሥር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበትን መሠረታዊ ጭብጥ በመለየትና በመመሥረት ለክርክሩ እልባት የሰጠ መሆኑን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ አንድ ጭብጥ የሚመሰርተው ከሳሽ በክሱ የገለፀውን ተከሳሹ ክዶ የሚከራከር ሲሆን እንደሆነ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 247 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ አመልካች አላግባብ ከሥራ ያሰናበተው መሆኑን ገልፆ ክስ ያቀረበ ሲሆን አመልካችም ተጠሪን ከሥራ አላሰናበትኩትም የሚል ክርክር አላቀረበም፡፡ አመልካች ተጠሪን ከሥራ አሰናብቸዋለሁ በማለት በግልፅ መልስ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል ማቋረጡ ግራቀኙ የሚተማመኑበት ነጥብ በመሆኑ ስንብቱ በፅሑፍ ነው ወይስ በቃል የሚል ማጣሪያ ማድረግ የሚያስፈልገው አይደለም፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት አሠሪው ለሠራተኛው የሥራ ውሉ ያቋረጠበትን ምክንያት በፅሑፍ አለመግለፁ ብቻውን ስንብቱን ህገ ወጥ የሚያደርግ አይደለም፡፡ አሠሪው ይህንን ሣይፈፅም ቢቀርና በፅሑፍ ሣይሆን በቃል ወይም በድርጊት የሥራ ውሉን ቢያቋርጥ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ምክንያት ያለው መሆኑን ከመከራከርና ማስረጃ ከማቅረብ የሚገድብ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሣይሰማና ግራቀኙ የሚከራከሩበትን ጭብጥ ሣይመሰርት ስንብቱ በፅሑፍ ያልተደረገ በመሆኑ ብቻ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል አላግባብ አሰናብቷል በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአንድ ጉዳይ ጭብጥ የሚመሠረተው ከሳሽ ያቀረበውን ክስና ማስረጃ ተከሳሽ የሚሰጠውን የመከላከያ መልስና ማስረጃና ፍርድ ቤቱ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሠረት በሚያደርገው የቃል ምርመራ የተሰጠ መልስ መሠረት በማድረግ መሆን እንዳለበት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ይደነግጋል፡፡ በዚህ ጉዳይ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል ማቋረጡ አከራካሪ ጭብጥ አይደለም፡፡ አከራካሪው ጭብጥ አመልካች በድርጅቱ መኪና ላይ ጉዳት በማድረሡና ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ለማሰናበት የሚችል ጥፋት በመፈፀሙ ስንብቱ ህጋዊ ነው የሚል ክርክር ያቀረበና ይህንን ለማስረዳት የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ያቀረበ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ የሚካካዱበትን ይህንን ጭብጥ በመመሥረትና በማስረጃ በማጣራት ውሳኔ መስጠት ሲገባው የሥራ ስንብቱ በቃል የተደረገ መሆኑ ብቻውን ስንብቱ ህገ-ወጥ መሆኑን ያሣያል በማለት የሰጠውን ውሣኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሣያርም እንዳለ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሸሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው ሠራተኛው(ተጠሪ) ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት በመፈፀሙ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥና ሌሎች ነጥቦች ለማስረዳት በግራ ቀኙ በኩል ያቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 50009

መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የአ/አ ሂልተን ሆቴል - ጠ/ሃሳብከፋይ ጌራወርቅ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ዮናስ ጥላሁን - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የሥራ ውል ማቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ ከሥራው ጋር በተያያዘ ከባድ የማጭበርበር ድርጊት ፈጽሟል በማለት አመልካች ከሥራ ያሰናበተው ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ የፈፀመው ድርጊት ከስራ ለማሰናበት የሚያበቃ አይደለም ሲል በመወሰኑ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የተጠሪ ድርጊት የሥራ ውልን ለማቋረጥ የሚያበቃ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የቀረበውን ክርክር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት እንደተቻለው ተጠሪ የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ ተጠሪው የሥራ ውል የተቋረጠው ለድርጅቱ ሰራተኞች በተዘጋጅ ካፍቴሪያ የውጪ ሰው አስገብቶ እንዲመገብ አድርጓል በሚል ነው፡፡ ተጠሪው ይህንን ድርጊት አልፈጸምኩም ሲል የካደ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ምስክር ሰምቶ ተጠሪውን ድርጊቱን ፈጽሟል በማለት በውሳኔው አረጋግጧል፡፡ ነገር ግን የተጠሪ ድርጊት ከባድ የማጭበርበር ድርጊት ነው ሊባል አይችልም በማለት ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ብሏል፡፡

ይህ ችሎትም የተጠሪ ድርጊት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሐ/ የሚሸፈን ስለመሆኑ መርምሯል፡፡ የተጠቀሰው አንቀጽ ድንጋጌ ይዘት "እንደጥፋቱ ክብደት በሥራው ላይ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር መፈጸም" የሥራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ እንደሚያስችል ያመለክታል፡፡ ተጠሪ ሥራው ሹፌር እንደነበር ተጠቅሷል፡፡ ተጠሪ ፈጽሟል የተባለው ድርጊት ደግሞ በሰራተኞች ካፍቴሪያ የውጪ ሰው አስገብቶ ጋብዟል የሚል ነው፡፡ ይህ ተግባር በራሱ በቀጥታ ከተጠሪው ሥራ ጋር የሚያያዝ አለመሆኑን መረዳት አዳጋች አይደለም፡፡ ካፍቴሪያው ደግሞ በራሱ የቁጥጥር ሥርአት መስተንግዶ እና አገልግሎት እንደሚሰጥ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ ለዚህ የተመደቡት ሰራተኞች ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ግልጽ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ተጠሪው ከሥራ ጋር በተያያዘ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር ፈጽሟል ለማለት አይቻልም ሲል የሥር ፍ/ቤት የደረሰበትን ድምዳሜ ለማስተባበል የሚያስችል አሳማኝ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት በአመልካች በኩል አልቀረበም፡፡ ከዚህም ባሻገር ተጠሪው ፈጽሟል የተባለው ድርጊት በራሱ እንደሕጉ አገላለጽ እና እሳቤ "ከባድ የማጭበርበር ወይም የማታለል ተግባር" የሚያሰኝ ሁኔታ ስለመኖሩም አመልካች አላስረዳም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የተጠሪ ድርጊት ያልተገባ መሆኑን ተቀብለው እንደ ሕጉ አነጋገር ግን ከባድ የማጭበርበር ድርጊት ሊባል አይችልም በዚህም የተነሳ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ስለሆነም ባለበት ሁኔታ በማጽናት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 30209 ሐምሌ 22/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 83534 የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡

   በዚህ መዝገብ ጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰበር መ/ቁ 50205

መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት

**ተጠሪ፡-** አቶ ምናለ በሪሁን

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች የሥራ ውል አላግባብና ማስጠንቀቂያ ሣይሰጠኝ ያቋረጠ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዜን ከፍሎ ወደ ሥራ ይመልሰኝ የሚል ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ተጠሪ የተቀጠረው ድርጅቱ በፍርድ ቤት የሚከራከርባቸው ጉዳዮች እስኪ.ቃለሉ ድረስ ለጊዜያዊነት ነገረ ፈጅ ሆኖ እንዲሠራ በመሆኑና ሥራው ያለቀ በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የነገረፈጅ አገልግሎት የሚጠይቀው ሥራ ያላለቀ በመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት አመልካች የስድስት ወር ደመወዝ በመክፈል ወደ ሥራ ይመልሰው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች የአሥራ አምስት ቀን የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ውሉን የማቋረጥ መብት ያለው መሆኑ በሥራ ውሉ ተገልጿል አመልካች የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚችል ቢሆንም የሥራ ውሉን ያቋረጠው በሥራ ውሉ መሠረት የአስራ አምስት ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ባለመሆኑና ሥርዓቱን ባለመጠበቁ አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 የተለያዩ ድንጋጌዎች መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን ይክፈሉ፣ ተጠሪ ወደ ሥራ መልስ ሊባል አይገባውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን አሻሽሎ ወስኗል፡፡

አመልካች የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪን ለማሰናበት እንደምንችልና ማሰናበታችንም ተገቢ ነው ብሎ ከወሰነ በኋላ የተለያዩ ክፍያዎችን ተገቢነት የሌላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ እንድንከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ የከፍተኛው ፍርድ ቤት እኔን በሚጎዳ ሁኔታ ውሉንና ህጉን ከመተርጎሙ ውጭ አመልካችን የሚጎዳ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የሥራ ውል በማናቸውም ጊዜ የአስራ አምስት ቀናት ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ለማቋረጥ የሚችል መሆኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥራ ውሉን በማስቀረብ እንዳረጋገጠ በውሣኔው ገልጿል፡፡ ተጠሪ ሥራው ከማለቁ በፊት አመልካች የሥራ ውሉን ማቋረጡ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር ከአመልካችና ከተጠሪ የሥራ ውል በግልፅ የተመለከተውን ፍሬ ጉዳይ የሚቃረንና የህግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው በውሉ የተቀመጠውን ሥርዓት ማለትም የአስራ አምስት ቀናት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሣያሟላ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል በውሉ ከተመለከተው ሥርዓት ውጭ በአሠሪና ሠራተኛ ህግ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል ሁኔታ ሣያጋጥመው ካቋረጠ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 39(1/ለ) መሠረት በአንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 2፣ በአንቀፅ 44 እና

በአንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 4(ለ) የተደነገጉትን ክፍያዎች ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለው በመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት አፅንተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል
2. በዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 4 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 48476

ሚያዝያ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ በለጠ ቂጤሳ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ደረጀ መኮንን - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 515/1999 "ን" መሰረት ያደረገ የስራ መልቀቂያ ይሰጠኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት ነው፤በዚህ ፍርድ ቤት ያሁኑ ተጠሪ ያቀረቡት ይግባኝ ከስራ ከለቀቁ ከሁለት ወራት በላይ ቢሆናቸውም ለአመልካች መስሪያ ቤት የስራ መልቀቂያ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ጥያቄ አቅርበው መስሪያ ቤቱ ፈቃደኛ አለመሆኑን፣ከመስሪያ ቤቱ ጋር በገቡት የትምህርት ስልጠና ውል መሰረት የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት የተወጡ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩ ከስራ መልቀቂያ ጋር መያያዙ አግባብ አለመሆኑን በተመለተ ከሚመለከታቸው ከሰው ሐብት ስራ አመራር ክፍሎች የተነጋገሩበት መሆኑን፣ይህንኑ መሰረት በማድረግ የፁሁፍ ማብራሪያ እንዲያቀርቡ ተስማምተው የፁሁፍ ማብራሪያ ማቅረባቸውን የገለፁ ቢሆንም አመልካች መስሪያ ቤት መልቀቂያውን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆኑን በመጥቀስ አመልካች የስራ መልቀቂያ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ የካቲት 29 ቀን 1996 ዓ.ም ከቀድሞው የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ካሁኑ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ጋር የስልጠናና የትምህርት ውል ገብተዋል፣በትምህርት ላይ የቆዩት ለሦስት አመታት ሲሆን ትምህርቱ ከተጠናቀቀ በኂላ ለስድስት አመት አገልግሎት ለመስጠት ተስማምተዋል፣ትምህርታቸውን አጠናቅቀው በውሉ መሰረት የሰጡት አገልግሎት ሃያ ሁለት ወራት ከአስራ አምስት ቀናት ነው፣ተጠሪ በውሉ መሰረት ግዴታቸውን ሳይወጡ የአገልግሎት ምስክር ወረቀት የሚያገኙበት ምክንያት የለም በማለት ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የአስተዳደር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኂላ ተጠሪ በውሉ የገቡትን ግዴታ ካልተወጡ አመልካች መስሪያ ቤት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ከማቅረብ በስተቀር የስራ መልቀቂያ ማስረጃውን ለውሉ መያዣ እንዲሆን ማድረግ አይችልም የሚል ምክንያት በመያዝ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 87 መሰረት የአገልግሎት ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች መስሪያ ቤት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር ማመልከቻ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ንብረት ሳያስረክብ ወይም የበኩሉን ግዴታ ሳይወጣ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመረመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ሕዳር 10 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብተው በአመልካች ወጪ ለሦስት አመታት የጋዜጠኝነት ትምሕርት የተከታተሉ ሆኖ ከአመልካች ጋራ ባደረጉት ውል ለአመልካች ከምረቃ በኋላ ለስድስት አመታት አገልግሎት ለመስጠት ግዴታ መግባታቸውን፣ከምረቃ በኋላ ተጠሪ ለአመልካች ሓያ ሁለት ወራትና አስራ አምስት ቀናት የማይበልጥ አገልግሎት ከሰጡ በኋላ የስራ መልቀቂያ እንዲሰጣቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ አመልካች የትምህርት ስልጠና ውሉ ላይ የተመለከተውን የተጠሪን ግዴታ ምክንያት በማድረግ ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 78/1/ ድንጋጌ ሲታይ በሕግ ወይም በውል የተቀመጡ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ በማንኛውም ጊዜ የአንድ ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስራውን በገዛ ፈቃዱ ሊለቅ የሚችል ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን የተጠቀሰው አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ ሁለት ደግሞ በአንቀፁ ንኡስ አንድ ድንጋጌ ስር በተቀመጠው መሰረት የአንድ ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ አገልግሎቱን ያቋረጠ የመንግስት ሰራተኛ ግዴታውን ባለመወጣቱ ለሚደርሰው ጉዳት እንደተገቢነቱ በፍትሐብሔር እና በወንጀል ሕግ መሰረት ተጠያቂነት ያለበት ስለመሆኑ ተቀምጧል፡፡ የአዋጅ አንቀጽ 87 ድንጋጌ ሲታይም የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ በስራ ላይ እያለ ወይም በማናቸውም ምክንያት አገልግሎት ሲያቋረጥ የስራ ልምድ ማስረጃ ከጠየቀ ሲያከናውን የነበረውን የስራ ዓይነት፣የአገልግሎት ዘመኑና ሲከፈል የነበረውን ደመወዝ የሚገልጽ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የሚሰጠው መሆኑን አስቀምጧል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው የአገልግሎት ምስክር ወረቀት ለማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ከስራ ላይ እያለም ቢሆን የማይከለከል መሆኑን ሲሆን ሰራተኛው በመስሪያ ቤቱ የሚፈለግበት እዳ ካለ በሕጉ አግባብ ሰራተኛውን የመጠየቅ መብት ለመስሪያ ቤቱ በሕግ የተጠበቀ መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ መስሪያ ቤቱ ከሰራተኛው የሚፈልገው እዳ አለ የሚል ከሆነ ለሰራተኛው የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት ከመስጠት ባለፈ የስራ መልቀቂያ ወይም ክሊራንስ እንዲሰጠው የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ማስረጃዎች መስሪያ ቤቱ ከሰራተኛው ላይ የሚፈልገው እዳ ካለ በሕጉ አግባብ መብቱን ለማስጠበቅ የራሳቸውን የሆነ ጠቀሜታ ያላቸው ናቸውና፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት የመስጠት በሕግ የተጣለበት ግዴታ ሲሆን የስራ መልቀቂያ እና ክሊራንስ ግን ከተጠሪ የሚፈልገው እዳ አለ የሚል እስከሆነ ድረስ በዚህ ረገድ ማስረጃ እንዲሰጥ የሚገደድ አይሆንም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ እንዲሰጠው የወሰኑት በአዋጁ አንቀጽ 87 መሰረት የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት እንጂ የስራ መልቀቂያ እና ክሊራንስ ባለመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ፍርድ ቤቶቹ ስህተት ፈጽመዋል በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 00721/2001 መጋቢት 22 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 45242 ሐምሌ 28 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰበር መ/ቁ 49273

ሚያዝያ 27 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ደረጀ ውለታው - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ዋሊያ ሌዘርና ሌዘር ፕሮዳክትስ ኃ/የተ/የግ/ማ

## ፍ ር ድ

አመልካች በስራ ላይ በደረሰባቸው አደጋ በሁለቱም እጆቻቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ስለደረሰባቸው የጉዳት ካሳ እንዲከፈላቸው ክስ መስርተው የስር ፍ/ቤት ጉዳቱ ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ነው በማለት ካሳው በዚህ መሰረት እንዲከፈል የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማሻሻሉ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በማሽን መጭመቂያ ስራ ተሰማርተው ሲሰሩ በስራ ላይ እያሉ በግራና በቀኝ እጃቸው ላይ ዘላቂ የአካል ጉዳት ስለደረሰባቸው የጉዳት ካሳ፣ ክፍያ ለዘገየበት፣ የስንብት ክፍያና ለማስጠንቀቂያ ጊዜ ሊከፈል የሚገባው እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ጉዳቱ በስራ ላይ መድረሱን ሳይክድ የጉዳቱና የሚከፈለው የጉዳት ካሳ መጠን ላይ ክርክር አቅርቧል፡፡ ችሎቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ላይ የደረሰው ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት በመሆኑ ለአመልካች ብር 24,900 /ሃያ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ/ እና ክፍያ ለዘገየበትና የአገልግሎት ካሳ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱ አመልካች ላይ የደረሰው 65% የአካል ጉዳት ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት ስለሆነ የጉዳቱ ካሳ ሊከፈል የሚገባው በአ/ቁ 377/96 አንቀፅ 109(3)(ለ) ነው በማለት የአመልካች የአምስት አመት ደሞዝ በ65% ተባዝቶ የሚመጣው ብር 16,185.00 /አስራ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ አምስት/ እንዲከፈላቸውና ክፍያ ለዘገየበት ግን ሊከፈላቸው አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው የደረሰባቸው ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት በመሆኑ የጉዳት ካሳው ሊከፈል የሚገባው በአ/ቁ. 377/96 109(3) (ሀ) መሰረት ነው የሚል ዝርዝር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም አመልካች ላይ የደረሰው ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ነው ወይስ ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት ነው የሚለውን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረጉ ተጠሪ ቀርቦ ክርክሩን በፅሁፍ አቅርቧል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

አመልካች በስራ ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ በግራ ቀኙ አልተካደም፡፡ አከራካሪው የጉዳቱ መጠን ነው፡፡ ከክርክሩ የአመልካች የቀኝ እጃቸው አራት ጣቶችና የግራ እጃቸው ሶስት ጣቶች መቆረጣቸውን ተገንዝበናል፡፡ የህክምና ቦርድም አመልካች ላይ 65% የአካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ አረጋግጧል፡፡ ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ማለት ጉዳት የደረሰበትን ሰራተኛ ማናቸውም ደሞዝ የሚያስገኝ ሥራ ለመሥራት የሚከለክለው የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት እንደሆነ አዋ/ቁ 377/96 አንቀፅ 101(2) ያመለክታል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች የሁለት እጆቻቸውን አብዛኛዎቹን ጣቶች አጥተዋል፡፡ ከሞላ ጎደል ሁሉን ስራ ለመስራት የእጆቻችን ጣቶች አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ አመልካች የሁለቱንም እጆቻቸውን አብዛኞች ጣቶቻቸውን ማጣታቸው ደግሞ ማንኛውንም አይነት ደሞዝ የሚያስገኝ ስራ ለመስራት የሚከለክላቸውና የማይድን መሆኑን ተረድተናል፡፡ በእርግጥ የሃኪሞች ቦርድ ጉዳቱ 65% መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ይህ ጉዳት የተለካው ግን ከአጠቃላይ የሰውነቱ ሁኔታ ጋር በማነፃፀር እንጂ የደረሰው ጉዳት ከመስራት ችሎታ ጋር ተነፃፅሮ የቀረበ አይደለም፡፡ ከፍ ሲል በተገለፀው የህጉ ድንጋጌ ደግሞ የአካል ጉዳቱ ከፊልና ሙሉ ተብሎ የሚከፈለው ከመስራት

ችሎታ ጋር በማነፃፀር እንጂ ከአጠቃላይ በሰውነት አካል ጉድለት ጋር ተነፃፅሮ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች የደረሰባቸው ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ነው፡፡ በሰራተኛው ላይ የደረሰው ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ከሆነ የሚከፈለው የጉዳት ካሳ መጠን የሰራተኛው የዓመት ደሞዝ በአምስት ተባዝቶ እንደሆነ አንቀፅ 109(3)(ሀ) ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአመልካች የጉዳት መጠን ዘላቂ ከፊል ጉዳት ነው በማለት ካሳው በአንቀፅ 109(3)(ለ) እንዲሰላ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ፀንቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 77981 ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ብር 24,900 (ሃያ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ) ይከፈላቸው፡፡
3. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ክፍያ የዘገየበትን አስመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 50148

ሚያዝያ 04 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** 1. አቶ ወርቁ ደረጀ
2. አቶ ወልዱ ገብሩ ወ/ጊዮርጊስ } ጠበቃ መንበረስላሴ በዛብህ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አባርኪሮ ሁመድ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ፍርድ እና አፈፃፀሙን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ለአፈፃፀሙ መሰረት የሆነው ውሳኔ የተሠጠውም በዚሁ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1481 ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ነው፡፡ በዚሁ በመ/ቁጥር 1481 ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የተሠጠው ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች ላይ የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ሲሆን የክሱ ይዘትም ባጭሩ፤ ተከሳሾች በውላቸው መሰረት ስራውን እራሳቸው ወይም በሚወክሉት ሰው ማሰራት ሲገባቸው ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ ውል ሰጪው እራሱ የጨው ምርቱን እያመረቱ ከጨው ማህበር ድርሻቸውን እየወሰዱ መሆናቸውን፣ የጨው ማምረቱን ስራ እራሳቸው ወይም የሚወክሉት ሰው እንዲጀምር በተደጋጋሚ ቢነገራቸውም ተከሳሾች ፍቃደኛ አለመሆናቸውን በመግለፅ የጠየቁት ዳኝነት ውሉ እንዲፈርስ እንዲወሰንላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ውሉ እንዲፈርስ ሲል በግልፅ ወስኗል፡፡ ለአፈፃፀም የቀረበው ውሳኔም ይህ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻቸው ላይ ውሉ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፈርስ መወሰኑን ገልፀው በውሉ መፍረስ ምክንያት የደረሰባቸውን ጉዳት አይነት እና መጠን ዘርዝረው ፍርድ ቤቱ አመልካቾች እንዲከፍሏቸው የአፈፃፀም ትዕዛዝ እንዲሰጥ ሐምሌ 06 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካቾችም ለአፈፃፀሙ ክስ በሠጡት መልስ በሕጉ አግባብ የተሠጠና ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ ስለሌለ ልንገደድ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን የአፈፃፀም ክርክር በመመርመር አመልካቾች ለተጠሪ ብር 71,000.00፣ 5789 ኩንታል ጨው እንዲሁም የ20343 ኩንታል ጨው 30% እንዲከፍሉ እና እንዲሰጡ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ በሕጉ አግባብ የተፈረደ ውሳኔ ሳይኖር አመልካቾች ለተጠሪ ገንዘብ እንዲከፍሉ፣ ጨው በኩንታል እንዲሰጡ መወሰኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን የፍርድ አፈፃፀም ስርዓት ያላገናዘበ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርበው በፅሑፍ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም የአሁኑ አመልካቾች ለተጠሪ ገንዘብ እንዲከፍሉ እና ጨው በኩንታል እንዲሰጡ በአፈፃፀም መዝገብ የተወሰነው ባለእዳ በሚያደርግ ፍርድ መሰረት ነው? አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ተጠሪ በዋናው ጉዳይ ክስ ሲመሰርቱ ለውሉ መፍረስ ምክንያቶች ናቸው ያሏቸውን ነጥቦች ዘርዝረው ውሉ እንዲፈርስ በጠየቁት ዳኝነት መሰረት ውሉ እንዲፈርስ የሚገልፅ ውሳኔ መሰጠቱን፣ ለአፈፃፀሙም መሰረት የሆነው ውሳኔ ይሕ ሲሆን የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲያቀርቡ ግን በውሉ መፍረስ ምክንያት የደረሰባቸውን ጉዳት ዘርዝረው ጉዳቱን አመልካቾች እንዲተኩ እንዲወሰንላቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው በአፈፃፀም ሊገደድ የሚችለው በሕጉ አግባብ የተፈረደ ፍርድ ሲኖር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ በሌላ አገላለፅ አንድ ሰው የፍርድ ባለእዳ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ፍርድ ሳይኖር በአፈፃፀም ሊገደድ አይገባም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ለአፈፃፀሙ መሰረት የሆነው ውሳኔ በመ/ቁጥር 1481 ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የተሠጠው ሲሆን ይህ ውሳኔ በአመልካቾች እና በተጠሪ መካከል የነበረውን የጨው መሬት ኪራይ ውል እንዲፈርስ በማለት ከመግለፁ ውጪ አመልካቾች ለተጠሪ በዓይነትም ሆነ በመጠን እንዲከፍሉ የተወሰነ የጉዳት መጠን ሁኔታ የለም፡፡ ተጠሪ በውሉ መፍረስ ምክንያት የደረሰባቸው ጉዳት እንዲከፈላቸው የጠየቁት ዳኝነት በዝምታ ታልፏል በማለት በበላይ ፍርድ ቤት ያሳረሙት ሁኔታ የለም፡፡ በእርግጥ ውሉ እንዲፈርስ ሲደረግ ሕጉ ያስቀመጠው አንዱ መፍትሔ የጉዳት ኪሳራ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1771(2) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በዚህ ረገድ ዳኝነት ተጠይቆ በግልፅ የተሠጠ ፍርድ ሲኖር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡ ከዚህ ውጪ በግልጽ ፍርድ ያላረፈበት ፍርድ የሚፈፅምበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ለተጠሪ ብር 71,000.00፣ 5789 ኩንታል ጨው እንዲሁም የ20343 ኩንታል ጨው 30% እንዲከፍሉ እና እንዲሰጡ በማለት የሠጡት ውሳኔ ያልተፈረደ ፍርድን ማስፈፀም ከመሆኑም በላይ የአመልካቾችን የመዳኘት ሕገ-መንግስታዊ መብት ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1631 ሐምሌ 07 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 2067 ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካቾችን ባለዕዳነት፣ የተጠሪን ባለገንዘብነት የሚያረጋግጥ ፍርድ ሳይኖር አመልካቾች በፍርድ አፈፃፀም የሚገደዱበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ በለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

- በዚህ ችሎት ሕዳር 03 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው አካል ይጻፍ፡፡
  መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 49931

ሚያዝያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የጎሽና እርግብ መለስተኛና አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ባለንብረቶች

ማህበር - ጠበቃ ምክሩ ወልደአረጋይ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ተሰማ ኃይሉ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ያሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ የክስ ይዘት ባጭሩ ከአመልካች ጋር ሕዳር 12 ቀን 2002 ዓ.ም በመሰረቱት የስራ ውል በድርጅቱ የፋይናንስ አገልግሎት ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ መቆየታቸውን ገልፀው የስራ ውሉ ጥቅምት 19 ቀን 2001 ዓ.ም ከሕግ ውጪ መቋረጡን ጠቅሰው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ፣ የሞባይል ስልክ አበል ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ እንዲከፈል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ያሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳው ክርክር ተጠሪ የስራ መሪ ስለሆነ የስራ ክርክር ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም የሚል ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ በስራ አፈፃፀም ላይ ባሳዩት ጥፋትና የብቃት ማነስ ችግር የተሰናበቱ በመሆኑ እርምጃው ሕጋዊ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ለማየት ስልጣን እንዳለው በመግለፅ ዋናውን ክርክርም ተመልክቶ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ በመድረስ አመልካች የስድስት ወራት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ በስራቸው ላይ የብቃት ማነስ ያሳዩ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ተጠሪ በብቃት ማነስ ምክንያት ለስራው ብቁ አይደሉም በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር መታለፉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ ተጠሪም በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ቀርበው የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገፅ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የሰራ ስንብቱን እርምጃ ሕጋዊ ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች ገልፆ ማስረጃ ጠቅሶ የተከራከረ መሆኑና የበታች ፍርድ ቤቶች የቀረቡት ማስረጃዎች የአመልካች ምክንያት በአሳማኝ ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በመግለፅ ውሳኔ የሰጡ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የተቻለው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረገ መሆኑን ነው፡፡ እንደሚታወቀው ይሕ ሰበር ችሎት ስልጣኑ ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች በሕግ አተረጓጎም ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሲፈፅሙ ማቃናት ነው፡፡ ይህም በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተ ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ ነበር የተባለው የስራውን አሰራር የሚገልፅ ነው በሚል ምክንያት ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት የደመደሙት ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቱም አመልካች የተሳሳተ ነው ብሎ ቢከራከርም ተጠሪ ሪፖርቱ በሰነድ ችግር ያልተሟላ ስለመሆኑ በመግለፅ ለአመልካች የገለጸ መሆኑን አረጋግጠው ሂሳቡ የተሳሳተ ነበር ለማለት ያልቻሉ መሆኑን ያመኑበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ የማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችልበት የህግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ባለመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩ በሰበር ችሎቱ እንዲታይ ሲደረግ በጭብጥነት ያልተያዘውን ተጠሪ በስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር ሊፈጥሩ ስለሚችሉ ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት በአማራጭ አመልካች በመልስ መልሱ ላይ ጠይቋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ተጠሪ ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይወሰን ዘንድ ምክንያት ይሆናል ያለው ነጥብ ተጠሪ ለአለቃ የማይታዘዙ ናቸው የሚለው ሆኖ በስር ፍርድ ቤቶች የክርክር ነጥብ ያልሆነ እና በተገቢው ማስረጃም ያልተረጋገጠ ነው፡፡ አንድ ሰራተኛ ወደ ስራ ከሚመለስ በአማራጭ ካሳ ተከፍሎት እንዲሰናበት የሚደረገው በስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር የሚከሰት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲያምን ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43(3) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከድንጋጌው ይዘት በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው ፍርድ ቤቱ የስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገባል ብሎ ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊኖር ይገባል፡፡ ያለበቂ ማስረጃና ምክንያት አሰሪ የስራ ግንኙነቱ ችግር ውስጥ ሊወድቅ ይችላል ብሎ ስለተከራከረ ብቻ ድንጋጌውን ተግባራዊ ማድረግ የስራ ዋስትናን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ይሆናል፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አልፈነዋል፡፡ በአጠቃላይ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14112 ግንቦት 14 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 80323 ጥቅምት 10 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## <u>ት እ ዛ ዝ</u>

በዚህ ችሎት ሕዳር 30 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 50838

ሚያዝያ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት - ነገረ ፈጅ አንድአርጋቸው በየነ - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ አማረ አበራ

2. አቶ ሽፈራው ጉደታ

3. አቶ ጌታቸው ይማም

4. አቶ አስማረ ቢሆነኝ

5. አቶ መሐመድ ሰይድ

6. አቶ እሸቱ ማሞ

7. አቶ አያሌው አሠፋ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ታህሳስ 1 ቀን 2002 ዓ.ም ስላመለከተ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ተጠሪዎች በከሳሽነት በመቅረብ ተንዳሆ እርሻ ልማት አክሲዮን ማህበር በነበረበት ወቅት ለሀያሁለት ዓመት በፎርማንነት የሥራ መደብ አገልግለናል፡፡ የተንዳሆ እርሻ ልማት ፈርሶ ወደ ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት በመንግስት ውሣኔ ሲዛወር የሠራተኞች መብት ጥቅም መጠበቅ እንዳለበት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 131/99 ተደንግጓል፡፡ ከሳሽ (አመልካች) መዋቅር ሲያፀድቅ የእኛን የሥራ መደብ መያዝና ማፅደቅ ሲገባው አፍርሶታል፡፡ ስለዚህ ከሙያችንና ከልምዳችን ውጭ በሆነ ሁኔታ ደረጃችንን ዝቅ አድርጎ የመደበን በመሆኑ ተንዳሆ እርሻ ልማት ስንሠራ በነበርንበት የፎርማንነት የሥራ መደብ ይመድበን በማለት አመልክተዋል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ እየተደራጀ ያለው ከተንዳሆ እርሻ ልማት የተለየ አዲስ ድርጅት ነው፡፡ ስለዚህ ሥራውን ለመሥራት የሚያስችለው አዲስ መዋቅር ዘርግቷል፡፡ ጥቅማቸውን በማይቀንስ ሁኔታ ባለው መዋቅር መድበናቸዋል፡፡ ድርጅቱ በሌለው የፎርማንነት የሥራ መደብ ለመመደብ ያቀረቡትን ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ አመልካች ተጠሪዎችን በፎርማንነት የሥራ መደብ ይመድባቸው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ አቅርቦ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የቦርዱን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ክርክሩ ግላዊ ባህሪ ያለው ነው፡፡ ከድርጅቱ የሥራ ባህሪ በመነሳት አደረጃጀቱና መዋቅሩ ተቀይሯል፡፡ ስለዚህ በሌለ የሥራ መደብ ተጠሪዎችን እንድንመደብ የሰጠው ውሣኔ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 28 ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መሠረታዊ ቅሬታችን የሀያ ሁለት

ዓመት አገልግሎታችንን ወደ ጎን በመተው የሠራተኛ ማህበር ተወካይ ባልተገኘበት በአዲስ የሥራ መደብ ላይ በመመደባቸው ነው፡፡ ሥለዚህ ቦርዱና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በስር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪዎች ያቀረቡት ጥያቄ አመልካች አዲስ በዘረጋው መዋቅር የሥራ መደባችን ፈርሷል፡፡ ስለዚህ በፊት የነበረንን የሥራ መደብ በአዲሱ መዋቅር በማካተት በፊት በሠራንበት የሥራ መደብ በፎርማንነት ይመድበን በማለት ነው፡፡ የተጠሪዎች ጥያቄና የሚሰጠው ውሳኔ በእነርሱ ብቻ የሚወሰን ውጤት ያለው ሣይሆን የሌሎችንም ሠራተኞች ለተመሣሣይ ጥያቄ የሚጋብዝ የወል የሥራ ክርክር ባህሪ ያለው ነው፡፡ ጉዳዩ የወል የሥራ ክርክር ባህሪ ያለው በመሆኑ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ የአመልካችንና የተጠሪዎችን ክርክር ሰምቶ የመወሰን ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 147 መሠረት አለው፡፡ ስለዚህ አመልካች ቦርዱ ጉዳዩን መርምሮ የመወሰን የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

ቦርዱ ጉዳዩን የማየትና የመወሰን ሥልጣን አለው ከሚል መደምደሚያ ላይ ከደረስን በኋላ የቦርዱ ውሣኔ ህጋዊ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? ሚለውን ጭብጥ በመያዝ መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት በፊት ከነበረው የተንዳሆ እርሻ ልማት አክሲዮን ማህበር የተለየ የሥራ ባህሪ ያለው ድርጅት ነው፡፡ አመልካች ለሥራ ባህሪው የሚስማማ የሥራ መዋቅርና የሥራ መደብ በጥናት ላይ በመመርኮዝ እንዲፀድቅ በማድረግ የሠራተኛ ምደባ አከናውኗል፡፡ ተጠሪዎች በፊት ያላቸው የሥራ ልምድና የትምህርት ዝግጅት አዲስ ለፀደቀው የሥራ መዋቅር የትኛው ቦታ ላይ ሊያስመድባቸው እንደሚችል በኮሚቴ ተጠንቶና ታይቶ በፊት ያገኙት የነበረው ደመወዝ ሣይቀነስ በአዲሱ የሥራ መዋቅር አዲስ ሥራ መደብ ላይ ተመድበዋል፡፡ ድርጅቱ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ሥራውን ለማከናወንና አትራፊና ተወዳዳሪ ለመሆን በሚያስችለው አደረጃጀትና የመደራጀትና የሥራ መደብ የማዋቅር ሥልጣን እንዳለው ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 28 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች የተጠሪዎችን ደመወዝ ሣይቀንስ በአዲሱ መዋቅር ሊመጥናቸው በሚችለው የሥራ መደብ መድቦ የማሠራት ሙሉ ኃላፊነት ያለው ሲሆን የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ በአዲሱ መዋቅር ባልተካተተና በሌላ የሥራ መደብ አመልካች ተጠሪዎችን መድቦ እንዲያሠራ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ሠራተኞችን ባለው መዋቅርና አደረጃጀት መድቦ የማሠራት መብት የሚጋፋውን የቦርዱን ውሣኔ በይግባኝ ሣያርም ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 45746

ሚያዝያ 6 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰለ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ነ/ፈጅ አየለ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ በለጠ ጫላ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ በተፈጠረ የመኪና ግጭት አደጋ አደጋው ከደረሰ ከ4 ወራት በኋላ መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም ያለአግባብ የስራ ውላቸው ስለተቋረጠ ወደስራቸው እንዲመለሱ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም በመልሱ መኪናውን በቸልተኛነት አጋጭተዋል፣ የትራፊክ ፖሊስ ስለአደጋው ውጤቱን የገለፀው የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በመሆኑ እርምጃው በይርጋ አይታገድም፣ በመሆኑም ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የቀረበው የትራፊክ ሪፖርት ተጠሪ ጥፋተኛ መሆናቸውን ስለማይናገር አደጋው በተጠሪ ጥፋት ነው ማለት ስለማይቻልና አደጋው በተጠሪ ቸልተኛነት የደረሰ መሆኑን አመልካች ማስረዳት ስላልቻለ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን በመሰረዝ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው ተበላሽቶ መንገድ ዳር የቆመ ከባድ መኪና ለማመልከት ተደርድረው የነበሩትን ድንጋዮችና ሌሎች ምልክቶች ደርምሰው በማለፍ አደጋው መድረሱን የትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት ስላረጋገጠ ስንብቱ በአ/ቁ 377/96 አንቀፅ 27(1/ሸ) መሰረት ህጋዊ ነው፣ የተረከቡትን የድርጅቱን ንብረትና ገንዘብ ያስረከቡና ያወራረዱ ለመሆኑ ክሊራንስ ባለማቅረባቸው በገዛ ጥፋታቸው የዘገየ በመሆኑ ልንቀጣ አይገባም ብሏል፡፡ ችሎቱም ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ክርክራቸው በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ተጠሪ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው የሚሉት አንደኛው ለስንብቱ ምክንያት የሆነው መኪና ላይ የደረሰው የግጭት አደጋ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ በመከሰቱ ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት አደጋው ከደረሰ ከአራት ወራት በኋላ የተወሰደ እርምጃ በመሆኑ ነው፡፡ ችሎቱም አንደኛውን ምክንያት ከማየቱ በፊት በቅድሚያ ስንብቱ በሁለተኛው ምክንያት ህገ-ወጥ ሊባል የሚችል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ከክርክሩ ሂደት አደጋው ጥቅምት 23 ቀን 2000 ዓ.ም ከደረሰ በኋላ የተጠሪ የስራ ውል የተቋረጠው መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም ስለመሆኑ ተረድተናል፡፡ ይህም ተጠሪ የስንብቱ ምክንያት የሆነውን ድርጊት ከፈፀሙ ከ4 ወራት በኋላ ከስራ የተሰናበቱ መሆኑን ያሳያል፡፡ በአ/ቁ 377/96 አንቀፅ 27(3) መሰረት አሰሪው የስራ ውሉን ለማቋረጥ ያለው መብት ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱን ካወቀ ከሰላሳ ቀናት በኋላ በይርጋ ይታገዳል፡፡ አመልካች በበኩሉ የስራ ውሉን ለማቋረጥ ያለው መብት በይርጋ አለመታገዱን ተከራክሯል፡፡ በክርክሩም የትራፊክ ሪፖርቱ የደረሰው የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በመሆኑ የይርጋው ጊዜ ሊቆጥር የሚገባው ከዚሁ ቀን ጀምሮ ነው ብሏል፡፡ አመልካች ተጠሪ መኪናውን ያጋጩ ስለመሆኑ ያወቀው የትራፊክ ሪፖርት ሲቀርብለት ሳይሆን ወዲያው አደጋው እንደደረሰ ስለመሆኑ ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም እርምጃውን ለመውሰድ የትራፊክ ፖሊስ ሪፖርቱን የሚጠብቅበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ምናልባት የተጠሪን ጥፋተኛነት ለማረጋገጥ ሪፖርቱ ያስፈልግ ነበር የሚባል ቢሆን እንኳን ሪፖርቱ በወቅቱ እንዲቀርብለት መጠየቅ ይገባው ነበር፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የፈፀሙት ድርጊት አመልካች ባወቀ

በአንድ ወር ውስጥ የስራ ውሉን ያላቋረጠ በመሆኑ መብቱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የስር ፍ/ቤት የይርጋውን መቃወሚያ በዝምታ በማለፉ ተጠሪ ይግባኝ ወይም መስቀለኛ ይግባኝ ባለማቅረባቸው በሰበር ደረጃ ሊከራከሩበት እንደማይችሉ ተከራክሯል፡፡ ነገር ግን የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በሌላ ምክንያት ቢሆንም ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ብሎ መወሰኑ፣ ተጠሪ ይግባኝ የሚያቀርብበት ምክንያት አይኖርም፡፡ አመልካች ያቀረበውም የይግባኝ ቅሬታ ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልግ መዝገቡ የተዘጋ በመሆኑ ተጠሪ መስቀለኛ ይግባኝ የሚያቀርቡበት ስርዓት ስለሌለ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች መብቱ በይርጋ ቀሪ ከሆነ በኋላ የስራ ውሉን ማቋረጡ ህጋዊ ስላልሆነ የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት አልተቻለም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33592 የካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 78022 ግንቦት 4 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. ይህ ችሎት ሰኔ 1 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 44405

ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ፊንፊኔ የቤትና የቢሮ እቃዎች ፋብሪካ ኃ.የተ.የግል ማህበር -

ነ/ፈጅ ወ/ዮሐንስ ይርጉ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ደጀ ደምሴ ጎበና - ወኪል ጥሩነሽ ዘውዴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ከአመልካች ጋር የመሰረቱትን የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ውል በራሳቸው ፈቃድ ያቋረጡ መሆኑን ገልፀው ስራ ሰርተው ያልተከፈላቸውን የሐምሌ ወር 2000 ዓ.ም ደመወዝ አመልካች የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ እና ክፍያው ለዘገየበት ክፍያ እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ከተጠሪ ጋር የስራ ውል ግንኙነት የነበረው መሆኑንና ተጠሪ ግንኙነቱን በገዛ ፈቃዳቸው ያቋረጡ መሆኑን እንዲሁም የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ሳይከፈላቸው የቀረና የዘገየ መሆኑን ሳይክድ ክፍያው ያልተፈፀመው ተጠሪ የተረከቡትን ንብረት በአግባቡ ያልመለሱና ጉድለት የታየባቸው መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካች በተጠሪ ላይ ጉድለት ታይቷል የሚል ከሆነ ዳኝነት ከፍሎ በሌላ ክስ ከሚጠይቅ በስተቀር የስራ ስንብት ክፍያውን አልከፍልም ለማለት አይችልም የሚል ምክንያት ይዞ የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጎ አመልካች ለተጠሪ የሐምሌ ወር 2000 ዓ.ም ደመወዝ፣ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ እንዲከፍላቸውና ስራ ልምድ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 14 ቀን 2001 ዓ.ም በተጻፈ አንድ ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ በስራ ምክንያት የተረከቧቸውን ንብረቶች ያጎደሉ በመሆኑ ክፍያውን አመልካች በወቅቱ ያለመፈፀሙ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 36 መሰረት ሕጋዊ ሆኖ እያለ የአመልካች ክርክር ታልፎ ክፍያውን እንዲፈፅም መደረጉ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ የተጠሪ ወኪል ቀርበው መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡ የመልሳቸው ይዘትም ባጭሩ አመልካች ተጠሪ አጎደሉ ለተባለው ንብረት ሌላ የፍትሐብሔር ክስ መስርቶ በክርክር ላይ ያሉ መሆኑን ገልጸው በዚህ ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ ግን ሊጸና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል ሲሉ መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩላቸው ሚያዚያ 15 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ አንድ ገፅ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ በስራ ምክንያት የተረከቧቸውን ንብረቶች ያጎደሉ በመሆኑ ጉድለቱን ሳያወራርዱ የሚፈፀም ክፍያ የለም በማለት ገልጾ ያቀረበው ክርክር ታልፎ አመልካች ክፍያዎችን እንዲከፍል መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱትን የስራ ግንኙነት በገዛ ፈቃዳቸው ያቋረጡ መሆኑን፣ ተጠሪ አመልካች ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ዳኝነት የጠየቁት የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ እና ስራ ሰርተው ያልተከፈላቸው የሐምሌ ወር 2000 ዓ.ም ደመወዝ መሆኑን፣ አመልካች ለተጠሪ ክፍያዎችን አልከፍልም በማለት የሚከራከረው ተጠሪ በስራ ምክንያት የተረከቧቸውን ንብረቶችን ያጎደሉ በመሆኑ የማወራረድ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡

በመሰረቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 36 ስር የስራ ውል ሲቋረጥ የሰራተኛው ደመወዝና ከደመወዝ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች ሁሉ በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ መከፈል ያለበት ሲሆን የክፍያው ጊዜ ሊራዘም የሚችለው ሠራተኛው ከአሰሪው የተረከበውን ንብረት የማስረከብ ወይም የሚፈለግበትን ማናቸውንም ሂሳብ በማወራረድ የራሱ ጥፋት በሆነ ምክንያት ካዘገየ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ሠራተኛው ስለጠየቀው ክፍያ አለመግባባት የተፈጠረ እንደሆነ አሠሪው በአንቀፅ 36 በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለሰራተኛው ያመነውን ያህል ሊከፍል እንደሚገባ ደግሞ የአዋጁ አንቀፅ 37 ደንግጓል፡፡ እነዚህን ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ የክፍያ ማዘግየት ውጤቱ በአንቀፅ 38 ስር የተመለከተው የሰራተኛውን እስከ ሶስት ወር ሊደርስ የሚችል ደመወዝ መክፈል ነው፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው ሠራተኛው ለአሰሪው ማስረከብ ያለበት ንብረትና ማወራረድ ያለበት ማናቸውም ሂሳብ አለመግባባት የሌለበት መሆን እንዳለበት እና አለመግባባት ካለ ግን ሰራተኛው ክፍያውን ከአሰሪው ለመጠየቅ ክስ ከማቅረብ ሙሉ በሙሉ ሊከለከል የማይችል መሆኑን ነው፡፡ ሠራተኛው ጉድለት ስለአለበት ሂሳቡን ሳያወራርድ ተገቢ ክፍያዎችን ሊጠይቅ አይችልም ከተባለ በሕጉ የጊዜ ገደብ መብቶችን የማስከበር መብቱንም ዋጋ የሚያሳጣ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በመሆኑም አንድ ሰራተኛ የማያምንበት ጉድለት ካለ አሰሪው በተገቢው መንገድ ክስ መስርቶ መብቱን ከሚያስከብርና ምናልባት በራሱ ክስ ረቺ የሚሆን ከሆነ በአፈፃጸም ጊዜ ስርአቱን ጠብቆ የዕዳ ይቻቻልልኝ ጥያቄ ከሚያቀርብ በስተቀር ለሠራተኛው መከፈል ያለበትን ክፍያ ከመጠየቅ ክስ ሊቀርብ አይገባም ወይም ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ሲከራከር ተቀባይነት ያገኛል ማለት አለመሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 36 እስከ 38 ድረስ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች ያቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉ ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች መንፈስ እና ባሁኑ ጊዜ አመልካችና ተጠሪ በንብረት ጉድለቱ ላይ በፍትሐብሔር ጉዳይ ክርክር ላይ ያሉ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35485 ታህሳስ 27 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75673 ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 53064

ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ደሬሳ ኮቱ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የአምቦ ገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩኒየን - ነ.ፈጅ  አልቀረቡም

መዝገቡ በአዳሪ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡

ለአፈፃፀሙ መነሻ በሆነው የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ጉዳይ ግራ ቀኙ ተከራክረው በተጠሪ በኩል የተደረገው የሥራ ስንብት ህግ ከደነገገው ውጭ ስለሆነ አመልካች ከልዩ ልዩ ክፍያዎች ጋር ወደ ሥራው ይመለስ ተብሎ ተወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች የተወሰነለትን ውሳኔ ለማስፈፀም የአፈፃፀም ክስ አቅርቧል፡፡ የጠየቀውም ዳኝነት ወደ ሥራ ለመመለስ እንደማይችል ገልፆ በምትኩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(4) መሠረት ካሣ እና የተወሰነለት ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉት ጠይቋል፡፡

አፈፃፀሙን የያዘው የሥር ፍ/ቤትም በአንቀጽ 43(4) መሠረት ለአመልካች እንዲከፈለው የተወሰነ ነገር የለም፡፡ በውሳኔው ከተገለፀው ውጭ ማስፈፀም አይቻልም በማለት ወደ ሥራ መመለሴ ቀርቶ በምትኩ ካሣ ይከፈለኝ የሚለውን ውድቅ አድርጎ ሌሎች ክፍያዎች እንዲፈፀሙለት አዟል፡፡

የአሁን አመልካች የጠየቀው የካሣ ክፍያ ውድቅ መደረጉ አግባብ አለመሆኑን በመግለፅ በየደረጃው በይግባኝ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኝነት ቢጠይቅም በተመሳሳይ ምክንያት ጥያቄው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በአሠሪው ችግር ምክንያት ወደ ሥራ ለመመለስ አለመቻሉ ከታወቀ በፋንታው በአዋጅ አንቀጽ 43 መሠረት የካሣ ክፍያ ሊከፈለኝ ሲገባ ይህ መታለፉ የህግ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ሲሆን፤ በዚህ ቅሬታ መነሻ ሁለቱም ወገኖች በሰበር የቃል ክርክራቸውን አሰምተዋል፡፡ እኛም ጉዳዩን ተመልክተን እንደሚከተለው ተርጉመናል፡፡

በሥር ፍ/ቤትም ሆነ በየደረጃው ባሉት ይግባኝ ሰሚውና ሰበር ሰሚው ችሎት የፍርድ ሐተታ ላይ እንደተገለፀው አፈፃፀም የፍርድን ይዘት መሠረት ሊያደርግ ይገባል፡፡ በአፈፃፀም ጉዳይ ከፍርድ ይዘት ውጭ መጨመርም ሆነ መቀነስ እንደማይቻል ግልፅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አሁን በተያዘው ጉዳይ የግራ ቀኙ ክርክር የመነጨው ከሥራ ግንኙነት ሲሆን የሥራ ግንኙነቱም በአዋጅ ቁጥር 377/96 በሆነው የአሠሪና ሠራተኛ ህግ የሚገዛ ነው፡፡ በዚህም ህግ አንቀጽ 43/3/ ላይ አከራካሪ የሆነው ስንብት ህግ ከደነገገው ውጭ ሆኖ በመገኘቱ ወደ ሥራው እንዲመለስ የተፈረደለት ሠራተኛ ወደ ሥራ ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ የሥራ ክርክሩን የሚያየው ችሎት መመለሱ ቀርቶ በምትኩ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት በማድረግ ሊወሰን እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡ ከዚሁ ድንጋጌ ይዘት አንፃር ይኸው መብት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው ወደ ሥራ እንዲመለስ ከተፈረደለት በኋላ እንደመሆኑ መጠን ይህ የሠራተኛ አማራጭ የሆነው መብት ተፈፃሚ የሚያደርገው

ችሎት ፍርዱን በማስፈጸም ላይ የሚገኘው ችሎት ስለመሆኑ እንጂ ቀድሞ ፍርዱን የፈረደው ችሎት ሊሆን አይችልም ወደ ሚለው ትርጓሜ ያደርሰናል፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች በዚሁ ድንጋጌ መሠረት ሠራተኛው በእራሱ ምርጫም ሆነ በአሠሪው ችግር ምክንያት እንደፍርዱ ወደ ሥራ ለመመለስ ካልፈለገ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ተብሎ ወደ ሥራው እንዲመለስ ፍርድ ማግኘቱ ከተረጋገጠ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(3) መሠረት በምትክነት በሰጠው መብት መሰረት በመመለሱ ፋንታ ካሣ ሊከፈለው ይገባል፤ ይህንንም የሚያስከፍለው አፈፃፀሙን የያዘው ችሎት ሆኖ እያለ ይህንኑ ድንጋጌ በማለፍ ከተፈረደው ፍርድ ውጭ በመውጣት ማስፈፀም አይቻልም በማለት የአመልካችን የካሣ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአፈፃፀም ክሱን በማመልከት ወደ ሥራ በመመለስ ፋንታ ካሣ እንዲከፈል ውሳኔ አላረፈበትም በሚል ምክንያት የአምቦ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 17733 በ12/5/2001፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 24165 በ17/11/2001 የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፋይል ቁጥር 88091 በ28/3/2002 ዓ.ም የሰጠውን ዳኝነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ሽረናል፡፡
2. በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/3/ መሠረት እንደተደነገገው ወደ ሥራ እንዲመለስ የተፈረደለት ሠራተኛ ወደ ሥራ አለመመለሱ ከታወቀ በምትኩ ካሣ የማግኘት መብት ያለው ስለሆነ ሊከፈለው ይገባል ብለናል፡፡ በመሆኑም ሊከፈል የሚገባውን የካሣ መጠን በአንቀጽ 43/4/ መሠረት አስልቶ ክፍያውን ያስፈፅም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 50182

ግንቦት 13 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የአዲስ አበባ ቁራዎች ድርጅት - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** አቶ አበበ ተፈራ ይልማ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ኀዳር 2 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በሥጋ አከፋፋይ ቡድን መሪነት ሲያገለግል መቆየቱን ገልፆ አመልካች ከግንቦት 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ለሥራው ብቁ አይደለህም በማለት ወደ **በፌብልት** ሰራተኛ 11 አዛውረውኛል፡፡ ስለዚህ ወደ ነበርኩበት የሥራ መደብ እንዲመልሰኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ የድርጅቱ ደንበኞች ቁጥር በመቀነሱ ምክንያት በተደረገው ጥናት በእርድና ሥርጭት ክፍል ችግር ያለበት መሆኑ ተረጋግጧል ስለዚህ ሥራና ሰራተኛን ለማገናኘት ሰራተኞችን በህብረት ስምምነቱ መሰረት በመመደብ እየሰራን የምንገኝ ስለሆነ የጣስነው ሕግ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ የተማመኑ በመሆኑ ስለጥናቱ ለማስረዳት የተዘረዘሩ ምስክሮች መስማትም ሆነ የጥናት ሰነዱን አስቀርቦ ማየት አስፈላጊ ሆኖ አላገኘውም በማለት በጥናቱ የከሳሽ (ተጠሪ) ችሎታ ምንም ሳይሆን ጠቅላላ የድርጅቱ ችግር የተገለፀ በመሆኑ አመልካች ተጠሪን የሥራ መደብ በማዛወር ማሰራቱ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካች ተጠሪን ወደ ቀድሞው የእርድና የሥጋ ስርጭት አገልግሎት የቡድን መሪነት የሥራ መደብ እንዲሰራ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ህግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ሰራተኞችን የበለጠ ውጤታማ በሚሆኑበት የሥራ መደብ ጥቅምና ደረጃቸውን ሣይቀንስ አዛውሮ ማሰራት የአሰሪው መብትና ሥልጣን ነው፡፡ ተጠሪ አሁን የተመደበበትና የተዛወረበት የሥራ መደብ ደረጃ ስድስት የሆነና ተመሣሣይ ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤት አሰሪው ሰራተኞቹን አዛውሮ የማሰራት ህጋዊ ሥልጣንና በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 12 ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን በመተላለፍ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝን በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በነበርኩበት የሥራ መደብ የሥራ ችሎታ ማነስ ያለበኝ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የአዋጅ ቁጥር 377/96 እና የሕብረት ስምምነቱን ድንጋጌዎች በማገናዘብ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በጽሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በአመልካች ድርጅት አግልግሎት የሚፈልጉ ደንበኞች መቀነስ ዋናው ምክንያት የእርድና የሥጋ ስርጭት አገልግሎት የሚሰጠው ክፍል ችግር ያለበት መሆኑ በጥናት ተረጋግጧል፡፡ ምንም እንኳን አመልካች

ከሃያ በላይ የሚሆኑ የእርድና የሥጋ ስርጭት አገልግሎት የቡድን መሪዎች ያሉትና ለድክመቱ ተጠሪ በግል ኃላፊ ናቸው ባይባልም አመልካች የጥናትቱን ውጤት መነሻ በማድረግ ችግሩን ለማስወገድ አስፈላጊ ነው የሚለውን አስተዳደራዊ ማስተካከያ በመውሰድ ድርጅቱን ትርፋማነት ማስቀጠል ይገባዋል፡፡

አመልካች ተጠሪን ከነበሩበት የሥራ መደብ ተመሣሣይ ደረጃ ደመወዝና ጥቅም ወደአለው የሥራ መደብ አዛውሮ ለማሰራት የወሰደው አስተዳደራዊ ማስተካከያ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ያከናወነው ተግባር ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች በሕጉ በግልጽ የተፈቀደለትን አስተዳደራዊ ተግባር እንዳይፈጽም ክስ የሚያቀርብበት ምክንያት የሌለ ሲሆን በተመሣሣይ የሥራ መደብ ተዛውሮ በመሥራቱ የተነካበት መብትና ጥቅም የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ሌሎቹ የእርድና የሥጋ ሥርጭት የቡድን መሪዎች ሣይዛወሩ እኔ ተዛወርኩ በሚል ምክንያት በመነሣሣት ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የሌለው በመሆኑ ከጅምሩ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 33 ንኡስ አንቀጽ እና በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 231 መሰረት መዝጋት ነበረባቸው፡፡

የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች የድርጅት አስተዳደር ሥልጣን በመጋፋት ተጠሪ ወደ ሌላ ተመሣሣይ ደረጃ ወደ አለው የሥራ መደብ በመዛወራቸው የቀረባቸው የደመወዝ ወይም ሌላ ህጋዊ ጥቅም ያለመሆኑን ባላሥረዳበት ሁኔታ ሌሎቹ የቡድን መሪዎች ወደ ሌላ የሥራ መደብ አልተዛወሩም፣ ተጠሪ የችሎታ ማነስ ያለበት ስለመሆኑ አላስረዳህም በሚል ምክንያት አመልካች ተጠሪን ወደ ቀድሞው የሥራ መደብ አዛውሮና መድቦ እንዲያሰራ የሰጠው ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13 ንኡስ አንቀጽ 2 የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የተጠሪ የሥራ ደረጃ ደመወዝና ጥቅም በማይነካ ሁኔታ ወደ ሌላ የሥራ መደብ አዛውሮ የማሰራት ሥልጣን አለው ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸ ይቻሉ፡፡

ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 44218

ግንቦት 13 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** እነ አቶ ታጁ አባጋሮ( 21 ሰዎች ) - የቀረበ የለም

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው የስራ ክርክርን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከተቀጠሩበት ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ መታወቂያ፣የበረሃ አበል፣ነፃ የመብራት አገልግሎት፣የደሞዝ ጭማሪ፣የቦነስ መብት፣ጥንድ የስራ ልብስ፣የካሳ መብት፣የአመት እረፍት መብት፣የቅዳሜ ክፍያ መብት፣የጡረታ መብት እንዲሁም በጥር ወር 2000 ዓ.ም የተደረገው 20% የደሞዝ ጭማሪ የማግኘት መብት እንዲጠበቅላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም የቋሚነትና የጡረታ መብት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም፣ክሱ የወል የስራ ክርክር ነው፣ጥያቄው በይርጋ ቀሪ ነው የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ካነሳ በኋላ ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች በመሆናቸው በህብረት ስምምነቱ መሰረት ጥቅሞችን ማግኘት አይችሉም 20% የደሞዝ ጭማሪ ተከለከልን ያሉት ሃሰት ነው በማለት መልስ አቅርቧል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ክርክሩ የግል የስራ ክርክር ነው፣ጥያቄውም የክስ ምክንያት አለው፣6 ወር ያለፈው የደሞዝ ጭማሪና አንድ አመት ያለፋቸው ሌሎች የመብት ጥያቄዎች በይርጋ ቀሪ ይሆናሉ ካለ በኋላ ዋናው ጉዳይ በተመለከተ ደግሞ በግራ ቀኙ በተደረገው የቅጥር ውል የጊዜ ገደቡ መቀመጡ ብቻ ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ አያስቆጥራቸውም በማለት ተጠሪዎች ላልተወሰነ ግዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች ስለመሆናቸው ግምት በመውሰድና በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14 መሰረት በሰራተኞች መሃከል ልዩነት መፍጠር ስለማይቻል ለተጠሪዎች መታወቂያ የማግኘት፣የበረሃ አበል፣ነፃ የመብራት አገልግሎት፣የደሞዝ ጭማሪ፣የቦነስ መብት፣የደንብ ልብስና የዓመት እረፍት የማግኘት መብታቸው እንዲጠበቅላቸውና 20% ደሞዝ ጭማሪ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ ሲጠቃለል፣ጥያቄው የወል የስራ ክርክር ነው፣ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፣የአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 14 ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የለውም፣ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ በመሆኑ የጠየቁት መብቶችና ጥቅሞች ሊያገኙ አይችሉም በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባዋል፣የሚል ነው፡፡ ችሎቱም አመልካች በሰበር አቤቱታው ያነሳቸውን ቅሬታዎች ከስር ፍ/ቤት ውሳኔና ከህጉ ጋር አገናዝቦ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ በዚህ መሰረት የግራ ቀኙ የቃል ክርክር የተሰማ ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን እንደሚመለከተው መርምሯል፡፡

በቅድሚያ የተጠሪዎች ጥያቄ የወል የስራ ክርክር በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የስረ-ነገር ስልጣን የለውም የሚለውን የአመልካች ቅሬታ ተመልክተናል፡፡ የተጠሪዎች ጥያቄ ሌሎች ሰራተኞች የሚያገኙት ጥቅማ-ጥቅሞችና መብቶች ይጠበቁልን የሚል ነው፡፡ አመልካች የሚከራከረው በሕብረት ስምምነቱ መሰረት በተጠሪዎች የተጠየቁት ጥቅማ ጥቅሞች የሚከፈለው ላልተወሰነ ጊዜ ለተቀጠሩ ሰራተኞች በመሆኑና ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ በመሆናቸው ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡ ቋሚ ሰራተኞች መሆናቸው ከተረጋገጠ የጠየቁትን መብቶችና ጥቅሞች ሊገኙ የማይገባበትን ሌላ ምክንያት አመልካች አልገለጸም፡፡ በመሆኑም የክፍያ ጥያቄው በተጠሪዎች የቅጥር ውሉ ይዘት

የሚወሰን ስለሆነና ውጤቱም በተጠሪዎቹ ላይ ተወስኖ የሚቀር እንጂ ለሌሎች ሰራተኞች ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽኖ የሚያሳድር ስላልሆነ ጥያቄው የወል የስራ ክርክር ነው ለማለት የሚቻል ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለኝ በማለት መወሰኑ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የይርጋውን መቃወሚያ በተመለከተ ተጠሪዎች የጠየቁት የመብት ጥያቄዎች ቀጣይነት ያላቸው በመሆኑ 6 ወር ያለፈው ደሞዝ ጭማሪና አንድ አመት ያለፋቸው ሌሎች የጥቅም ጥያቄዎች ብቻ በይርጋ ቀሪ መደረጋቸው ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመቀጠል ችሎቱ የተመለከተው ተጠሪዎች ለተወሰነ ግዜ የተቀጠሩ መሆን አለመሆኑን ነው፡፡ ስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ የተደረገው የስራ ውል የጊዜ ገደብ ከማስቀመጡ በቀር በአዋጁ አንቀጽ 10 ስር በተዘረዘሩት ምክንያቶች መቀጠራቸውን ስለማይናገር ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ መሆኑን ግምት ወስዷል፡፡ ችሎቱም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲያመቸው ተጠሪዎች የተቀጠሩበትን የቅጥር ውል የስር ፍ/ቤትን መዝገብ በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡ የቅጥር ውሉ በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 10 መሰረት ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ ለሚቀጠሩ ሰራተኞች ተፈፃሚ የሚሆን ስለመሆኑ በርእሱ አመልክቶ በዝርዝር ውስጥ ተጠሪዎች የተቀጠሩበት የጊዜ ገደብ፣ የተቀጠሩበት ፕሮጀክት እንዲሁም የተቀጠሩት በአዋጅ አንቀጽ 10 መሰረት በጊዜያዊነት በመሆኑ መብቶቻቸውና ጥቅማቸው በቅጥር ውሉ የተመለከቱት ብቻ መሆናቸውን ሌሎችንም ዝርዝር ሁኔታዎች አካቶ የያዘ ነው፡፡ አንድ ሰራተኛ የተቀጠረው ላልተወሰነ ጊዜ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 9 ግምት የሚወስድ ሲሆን አሰሪው የስራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ነው የሚል ከሆነ ይህንኑ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ አመልካች ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ስለመሆናቸው ለማስረዳት ያቀረበው የስራ ውሉን ነው፡፡ በእርግጥ የስር ፍ/ቤት እንዳለው በውሉ ላይ የግዜ ገደብ መጠቀሱ ብቻውን ሰራተኛው ለተወሰነ ግዜ የተቀጠረ ነው ወደሚለው መደምደሚያ ሊያደርስ የሚችል አይደለም፡፡ ከጊዜ ገደቡ ባሻገር ግራ ቀኙ ውሉን ሲዋዋሉ ሃሳባቸው ምንድን ነበር የሚለውን መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት ውሉን ስንመረምር የተጠሪዎች ቅጥር በጊዜ ገደብ ከመወሰኑ በተጨማሪ የተቀጠሩት ለግልገል ግቤ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ለደነባ ሳይት መሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በውሉ አንቀጽ 4.1.3 ስር ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ በመሆናቸው መብቶቻቸውና ጥቅሞቻቸው የሚወሰኑት በቅጥር ውሉ በተዘረዘሩት መሰረት ብቻ መሆኑ ሰፈሮ ይገኛል፡፡ ይህም የሚያሳየው ምንም እንኳን በውሉ በግልጽ ባይመለከትም ተጠሪዎች ሲቀጠሩ የነበረው የግራ ቀኙ ሃሳብ ተጠሪዎች በውሉ ላይ በግልጽ ለተመለከተው የፕሮጀክት ስራ ብቻ የተቀጠሩ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም በአዋጅ አንቀጽ 10/1/ሀ/ ሥር የሚወድቅ የቅጥር ሁኔታ ነው፡፡ በመሆኑም በአመልካችና በተጠሪዎች መሃከል የተደረገው የቅጥር ውል ይዘት ሲታይ ተጠሪዎች ለተወሰነ ስራ የተቀጠሩ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች አጠቃላይ የውሉን ይዘት ሳይመረምሩ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች ናቸው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች ናቸው ከተባለ የጠየቋቸውን ጥቅማ ጥቅሞች እና መብቶች ሊያገኙ ይገባል ወይ? የሚለውን ቀጥለን ተመልክተናል፡፡ አመልካች ከስር ጀምሮ የሚከራከረው በህብረት ስምምነቱ መሰረት ተጠሪዎች የጠየቋቸው የመብት ጥያቄዎች ለቋሚ ሰራተኞች የሚሰጡ ናቸው በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎችም ቢሆኑ ለሌሎች ሰራተኞች ስለሚከፈል ለእነሱም እንዲከፈላቸው ከመጠየቅ ባለፈ እነዚህ የጥቅማ ጥቅም እና መብቶች ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ለተቀጠሩ ሰራተኞችም ሊከፈል የሚገባበት የውልም ሆነ የሕግ መሰረት ያላቸው ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪዎች ሊያገኙ የሚችሉት ጥቅምም ሆነ መብቶች በውሉ ላይ የተዘረዘሩትን ብቻ መሆናቸው በቅጥር ውሉ ላይ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 14/ረ/ ስር የተመለከተው ልዩነት ያለመፍጠር ግዴታ በድንጋጌው እንደተመለከተው በብሔረሰብ፣በፆታ፣ በሐይማኖት፣በፖለቲካ አመለካከት እና እነዚህን የመሳሰሉትን ሌሎች ሁኔታዎችን የሚመለከት እንጂ የቅጥር ውልን መሰረት በማድረግ ልዩነት እንዳይፈጠር የማይከለክል ስለመሆኑ ይህ የሰበር ችሎት በመ/ቁ 43197 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አመልካች በተጠሪዎች የጠየቋቸውን የጥቅማ ቅጥምና ሌሎች የመብት ጥያቄዎች የቅጥር ሁኔታን መሰረት በማድረግ ልዩነት እንዳይፈጥር ሕጉ ክልከላ አላደረገበትም፡፡ በተጠሪዎች የክስ ማመልከቻ ላይ የተጠየቁት ነገሮች በህብረት ስምምነቱ መሰረት ለቋሚ ሰራተኞች ብቻ የሚከፈሉ ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር ተጠሪዎች አላስተባበሉም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች በክሳቸው የጠየቋቸውን ጥቅማ ቅጥምና ሌሎች መብቶች ለመጠየቅ የሚያስችል ከሕግም ሆነ ከውል ያገኙት መብት መኖሩን ስላረጋገጡ ጥያቄአቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ

ሰራተኞች ናቸው በማለት በጥያቄአቸው መሰረት እንዲፈፀምላቸው የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24365 ሐምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 69792 ታህሣሥ 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች በመሆናቸው ክሳቸው ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የስር ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰበር መ/ቁ 46363

ግንቦት 19 ቀን 2002

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ሣሊኒ ኮንስትሩቶሪ ኤስ ፒ - ኤ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** አቶ ትግሉ ፍሬህይወት - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የየም ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤትና የየም ልዩ ወረዳ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ሰኔ 1 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በየም ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ የአመልካች ሠራተኛ መሆኑን ገልፆ በዋሻ ውስጥ ሥራ በመሥራት ላይ እያለሁ ህዳር 4 ቀን 1999 ዓ.ም በባቡር ግጭት ምክንያት ከፍተኛ የአካል ጉዳት ደርሶብኛል፡፡ በአገር ውስጥ ህክምና ስከታተል የቆየሁ ቢሆንም የደረሰብኝ ጉዳት በአገር ውስጥ ከሚሰጠው ሕክምና በላይ መሆኑን በማረጋገጥ አምስት ዶክተሮች ውጭ ሄጄ ሕክምና መከታተል ያለብኝ መሆኑን በማረጋገጥ ማስረጃ ሰጥተውኛል፡፡ ተከሳሽ /አመልካች/ ውጭ ሊያሣክመኝ ፈቃደኛ ባመሆኑ በውጭ አገር ህክምና እንድከታተል እንዲያደርግ ትእዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ተጠሪ በአገር ውሰጥ አስራ ስምንት ጊዜ ኦፕሮሽን ያደረገና ህክምና የተከታተለ መሆኑን ገልፆ የውጭ አገር ሀኪሞች /ዶክተሮች/ በሚመጡበት ሆስፒታል በአገር ውስጥ አለ፡፡ ተጠሪን ዶክተሮቹ ጋር ቀርቦ እንዲታከም ብንጠይቀው ፈቃደኛ አልሆነም የውጭ አገር ህክምና ለመሸፈን በውል ያልተስማማን በመሆኑ የተጠሪ ክስ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 105 አሠሪው ሠራተኛ በሥራ ላይ ጉዳት ሲደርስበት የማሣከም ግዴታ እንዳለበት ከሚደነግግ በስተቀር ህክምናው በአገር ውስጥ ወይም በውጭ አገር መሆኑን ስለማይገልጽ አመልካች የሀኪሞች ቦርድ በሰጠው የሙያ አስተያየት መሠረት ውጭ አገር ልኮ የማሣከም ኃላፊነት አለበት በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የየም ልዩ ወረዳ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የፍሬ ጉዳይ ወይም የህግ ስህተት የለም በማለት ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 ሠርዞታል፡፡

አመልካች ተጠሪ ታክሞ እንዲድን ያደረግነውን ጥረት ከግምት ውስጥ ሣያስገባ የህክምና ቦርዱ ውሣኔ ግልጽነት ያጉደለው መሆኑን ሣያገናዝብና በአገር ውስጥ የተሻለ ህክምና ሊሰጥ የሚችል የውጭ ዶክተሮች የሚሠሩበት MCM የተባለ ሆስፒታል ልናሣክመው ፈልገን ተጠሪ እንቢተኛ መሆኑን ሣያገናዝብ አላግባብ ውጭ አገር ወስዳችሁ አሳክሙ በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ችሎቱ ተጨማሪ ማስረጃዎን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377(3) መሠረት በመቀበል ውሣኔ እንዲሰጥልን በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በአገር ውስጥ ባሉ የህክምና ተቋሞች ታክሜ ከህመሜ ለመዳን ያልቻልኩ በመሆኑ በውጭ ሄጄ መታከም እንዳለብኝ የሀኪሞች ቦርድ አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ አመልካች ውጭ አገር ወስዶ ያሣክመው በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪን በውጭ አገር የማሣከም ግዴታና ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ይህንን ጭብጥ እልባት ለመስጠት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 105 ድንጋጌ አሠሪው በሠራተኛው ላይ ያደረሰበት ጉዳይ በውጭ አገር የሚደረግ የህክምና ወጭ እንዲሸፍን ያስገድደዋል ወይስ አያስገድድም? የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 105 ድንጋጌ ቃልበቃል ሲነበብ "በሥራ ላይ ሚመጣ ጉዳት ለደረሰበት ሠራተኛ ለሚከተሉት ህክምና አገልግሎት የሚያስፈልግ ውጭ አሠሪው ይከፍላል

1. የጠቅላላና የልዩ ህክምና የቀዶ ጥገና ህክምና ውጭዎች
2. የሆስፒታል መድሀኒት ወጭዎች
3. ማንኛውም አስፈላጊ ሰው ሠራሽ ምትክ ወይም የተጨማሪ አካሎችና ጥገና ወጭዎች የሚል ነው፡፡

ድንጋጌው አሠሪው የመሸፈንና የመክፈል ግዴታ ያለበት በአገር ውስጥ ህክምና ተቋማት የሚደረገውን የህክምና ውጭ ብቻ ነው ወይስ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚደረግ የህክምና ወጭ የሚለውን በግልጽ ምላሽ የሚሰጥ አይደለም፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 105 ድንጋጌ አገላለጽ ጠቅላላ መብቱ የተቀመጠ በመሆኑ አሠሪው ሠራተኛው ላይ በሥራው ላይ የሚደርስበትን ጉዳት የሚያወጣውን የውጭ አገር የህክምና ወጭ መሸፈን አለበት ወይስ የለበትም በሚለው ጥያቄ ግልጽ ምላሽ የማይሠጥ በመሆኑ ድንጋጌውን መተርጐም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 105 ድንጋጌ ለመተርጐም አዋጁን ሳያወጣ ህግ አውጭው የነበረውን ሀሳብና ሊያሣካው የሚፈልገውን ግብ ማገናዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ህግ አውጭው አዋጁን ያወጀው በአገሪቱ ውስጥ አሠሪና ሠራተኛ ግንኙነትና መሠረታዊ የሆኑ መብትና ግዴታዎች ለመቆጣጠር እንደሆነ በአዋጁ መግቢያ ገልፅታል፡፡ አዋጁ በአገሪቱ ውስጥ በየትኛውም ሥፍራና በማናቸውም ሁኔታ የተመሠረቱ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ላይ እኩል ተፈፃሚነት እንዲኖረው ታስቦ የታወጀ በመሆኑ ሁሉም አሠሪዎች ሠራተኛው በሥራ ላይ ለሚደርስበት ጉዳት የውጭ አገር ህክምና ወጭ እንዲሸፍኑ በማሰብ የአዋጁን አንቀጽ 105 ደንግጓል ብሎ ለመደምደም የሚቻል አይደለም፡፡ ስለዚህ ህግ አውጭው ማናቸውም አሠሪና ሠራተኛው በሥራ ላይ ለሚደርስበት ጉዳት በአገር ውስጥ የሚደረገውን የህክምና ወጭ የመሸፈን ግዴታና ኃላፊነት እንዳለበት በማሰብ ህግ አውጭው ድንጋጌውን አውጇል ተብሎ መተርጐም ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 በአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት አሠሪው ለሠራተኛው ሊያከብር የሚገባውን ዝቅተኛ ደረጃ ጥበቃ የሚደነግግ ነው፡፡ ሠራተኞች ከአዋጅ ከተደነገገው ጥበቃ በላይ የተሻለ መብትና ጥቅም ለማስከበር ሠራተኞች በአዋጅ ቁጥር 377/96 የሥራ ውል ሲዋዋሉ ወይም አንቀጽ 124 በሚደነግገው መሠረት ከአሠሪው ጋር በመደራደር የህብረት ሥምምነት መዋዋል አለባቸው፡፡ የውጭ አገር የህክምና ወጭ በአሠሪው የሚሸፈን መሆኑ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ ለሠራተኛው የሰጠው ዝቅተኛው ጥበቃ ነው ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ የአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 105 አሠሪው ሠራተኛው በሥራ ላይ በሚደርስበት ጉዳት የአገር ወስጥ የህክምና ወጭ መሸፈን እንዳለበት በመደንገግ ዝቅተኛውን ጥበቃ ሰጥቷል፡፡ በውጭ አገር የሚደረግ የህክምና ወጭ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በአሠሪው መሸፈን ያለበት መሆኑ ከፍተኛ ጥበቃ ነው፡፡ ይኸም በመሆኑ ሠራተኞች ከአሠሪው ጋር በመደራደር በውል ወይም በህብረት ስምምነት ሊያስከብሩት የሚቻሉት መብት እንጂ በህግ በሁሉም አሠሪዎች ላይ ግዴታና ኃላፊነት ሆኖ ተደነገገ አይደለም፡፡ አመልካች ሠራተኞችን በውጭ አገር ለማሣከም ውል ያልተዋዋለ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተገልጿል፡፡ አመልካች ሠራተኞች ለሚደርስባቸው ጉዳት ከአገር ውጭ የህክምና ወጭ በሙሉ ወይም በከፊል የሚሸፈን ግዴታ ያለበት መሆኑን የሚያረጋግጥ የህብረት ሥምምነት በአመልካችና በአመልካች ሠራተኞች መካከል የተደረገ መሆኑን የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች በተጠሪ ላይ የደረሰውን ጉዳት በውጭ አገር ለማሣከም ግዴታ ከህግ፣ ከውል ወይም ከህብረት ሥምምነት የመነጨ ሀላፊነት የሌለበት በመሆኑ የየም ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪን ውጭ አገር ወስዶ እንዲያሣክም የሰጡት ውሣኔና የህግ ትርጉም መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታውና ለሥር ፍርድ ቤት በቀረበው ክርክር መሠረት MCM ሆስፒታል ሌሎች የአገር ውስጥ የህክምና ተቋማት የማሣከምና ሌሎች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 በሚደነግገው መሠረት

የተጠሪን መብትና ጥቅም የመጠበቅ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ከዚህ ውጭ አገር ወስዶ የማሣከም ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የየም ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት እና የየም ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪ ውጭ አገር የማሣከም ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
3. አመልካች ተጠሪን በ MCM ሆስፒታልና ሌሎች የአገር ውስጥ የህክምና ተቋማት የማሣከምና የተጠሪን መብትና ጥቅም በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የመጠበቅ ግዴታ አለት ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

የሰ/መ/ቁ. 50923

ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

አመልካች፡- ፋውንዴሽን አፍሪካ -ጠበቃ መላኩ ካሰኝ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዓለሙ ታደሰ- ጠበቃ አብደላ ዓሊ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ሲሆኑ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ የስር ከሣሽ ክስ ይዘት ሲታይም በአመልካች ድርጅት ከጥር 1 ቀን 1977 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 22 ቀን 2001 ዓ.ም. ድረስ ለሃያ አራት አመታት ሲሰሩ እንደቆዩ፣ ከሣሽና ተከሣሽ ታህሳስ 22 ቀን 1996 ዓ.ም. በተፈራረሙት ውል አለመግባባት ከተፈጠረ በኔዘርላንድስ ሕግና ፍርድ ቤቶች ለመዳኘት የተፈራረሙ ቢሆንም ውሉን የተፈራረሙት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚሠራ ስራና ስራው የተሰራውም በኢትዮጵያ ውስጥ በመሆኑ፣ ተከሣሽም በኢትዮጵያ ውስጥ ተመዝግቦ የሚሰራ መሆኑን ገልፀው ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት መሆኑን ገልፀው የስራ ውሉ ያለምንም ጥፋት ስለተቋረጠ ካሣ፣ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የዓመት እረፍት፣ ክፍያ ለዘገዬበት ክፍያ ከተለያዩ ክፍያዎች ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሠጠው መልስም፣ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ስምምነት ሕጋዊ አለመሆኑን ገልጾ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት መታየት ያለበት ነው ብሎ በዚሁ አንፃር ተመልክቶ ስንብቱን ሕገ ወጥ ነው ሲል ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ችሎቱ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ ከሚችል በስተቀር በይግባኝ ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት ዋናውን ጉዳይ ሳይመረምር አልፎታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ታህሳስ 05 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት የሰበር ማመልከቻ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ጉዳዩ የግለሠብ ዓለም አቀፍ ሕግ የሚያስነሳ ስለሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተመልክቶ ብይን ይስጥበት ተብሎ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተሰጥቶ ይኸው ትዕዛዝ በይግባኝ ፀንቶ ባለበት ሁኔታ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ በቀረበለት ጉዳይ ብይን ሳይሰጥ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የሚታይ ነው ብሎ ራሱ በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታቸውም ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ የተጠሪ ጠበቃ ቀርበው የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ ሶስት ገፅ ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም. የመልስ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዮን በሚከተለው መልኩ

መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የሚገዛው ግራ ቀኙ ባደረጉት ስምምነት መሠረት ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ነው ካለ በኃላ ጉዳዩን ራሱ በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ማየቱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ግራ ቀኙ ታህሳስ 22 ቀን 1996 ዓ.ም. ባደረጉት ስምምነት መሠረት በመካከላቸው የሚነሣው አለመግባባት በኔዘርንላድስ ሕግና ፍርድ ቤቶች የሚታይ መሆኑን መስማማታቸውን፣ በመካከላቸው ያለው ግንኙነትም የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት መሆኑን፣ ተጠሪ ኢትዮጵያዊ ሆነው የሚኖሩትና ስራውን ለመስራት ግዴታ የገቡት በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን፣ አመልካች የውጪ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበውና ስራውን የሚሰራው በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11/2(ሀ) ስር የግለሠብ ዓለም አቀፍ ሕግ (Private international law) የሚመለከቱ ጉዳዮች በሚኖሩ ጊዜ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐብሔር የዳኝነት ሥልጣን እንደሚኖረው ተደንግጓል፡፡ አዋጁ ይህን ድንጋጌ ሲያስቀምጥ የራሱ የሆነ ምክንያት አለው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህም መሠረት ሕግ አውጪው ይህንን ድንጋጌ ያስቀመጠው አንድም ወደፊት በስራ ላይ የሚውለውን የአገሪቱን የግለሠብ ዓለም አቀፍ ሕግ በሕግ አውጪው አካል ፀድቆ በስራ ላይ ሲውል በዚህ ረገድ የሚነሱ የሕግ ክርክሮችን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን አይቶ እንዲወስን ወይም አሁን ባለው ሁኔታ ለኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ለዳኝነት በቀረበ አንድ ጉዳይ ላይ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ የኢትዮጵያ ሕግ ከአመልካቹ አገር ሕግ ወይም ከሌላ አገር ሕግ ጋር ይጋጫል ወይም ይቃረናል በማለት በኢትዮጵያ ሕግ እንዳይዳኝ ወይም በራሱ ወይም በሌላ አገር ሕግ ጉዳይ እንዲታይና እንዲወሰንለት ሲያመለክት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ለዳኝነት የቀረበው ጉዳይ በባሕርይው ከአንድ በላይ የሆኑ የሕግ ሥርዓቶችን ለጉዳዩ አወሳሰን የሚጋብዝና የየትኛው ሥርዓት ሕግ ተመራጭ ሊሆን ይገባል የሚለው ክርክር ሲነሳ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐብሄር የዳኝነት ሥልጣን አይቶ እንዲወስን ከመደረጉ ውጪ በማናቸውም ሁኔታ ተከራካሪዎች የአገሪቱን ሕግ በሚፃረር መልኩ ስምምነት አድርገው ሲገኙ ሁሉ ተከራካሪ ወገን ክርክር ስላነሳ ብቻ የግለሠብ አለም አቀፍ ሕግ ጥያቄ የሚያስነሣ ነው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ ከዚህ አንፃር ግራ ቀኙ አደረጉ የተባሉትን ስምምነት ስንመለከት የኢትዮጵያ አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው የሚያደርግ፣ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችም ጉዳዩን እንዳይመለከቱ የሚገልጽ መሆኑ ሲታይ ስምምነቱ ተቀባይነት አለው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ከአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ዓላማ እና መንግሥት አዋጁ ላይ ካለው ጠቅላላ ፍላጎት አንፃር የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የመንግሥትም ፍላጎት የሚንፀባረቅበት ሕግ ሲሆን ይህን አዋጅ የሚመለከቱ ስምምነቶች ሕጋዊ እና የሕዝብን ጥቅም የማይፃረሩ መሆን ይገባቸዋል፡፡ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ካልወሰነ በስተቀር አዋጅ ቁጥር 377/96 የውጪ አገር ድርጅት ሆኖ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሚሠራ የበጎ አድራጎት ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ከአዋጁ ድንጋጌ 3/3/ለ/ ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የወጣ ደንብ የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ አዋጅ ቁጥር 377/96 ለጉዳዮ ተፈጻሚነት ያለው በመሆኑ ጉዳዩ የግለሠብ አለም አቀፍ ሕግ ጥያቄን ስምምነቱን መሠረት አድርጎ ያስነሣል ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96 ተፈፃሚነት እንዳለው መወሰኑ አግባብነት ያለው ቢሆንም ጉዳዩ የአለም አቀፍ የግለሠብ ሕግ ጥያቄ እንደማያስነሳ በመግለጽ ጉዳዩን ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መመለስ ሲገባው ራሱ በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ መመልከቱ ተገቢነት የሌለውና የአመልካችን የይግባኝ መብት ያጣበበ ሆኖ ስለተገኘ በዚህ ረገድ የተሠጠው የውሣኔው ክፍል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 78810 ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም. የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ተመልክቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ሽ

የሰ/መ/ቁ 51912

ሰኔ 07 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት - ነ/ፈጅ ስዩም ጌራወርቅ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሶፋኒት አጥናፉ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የሥራ ውል ማቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው ጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት ላይ ነው፡፡ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ አመልካች ያለአግባብ ከሥራ እንዳሰናበታቸው ገልፀው የሥራ ስንብት እና ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው እንዲወሰን የሚል ነበር፡፡ በአመልካች በኩል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበው ፍ/ቤቱ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ እና ክሱ የቀረበው ስድስት ወር ጊዜ ካለፈ በኋላ በመሆኑ በይርጋ ሊታገድ እንደሚገባ በሚል ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም በአማራጭ ክርክር አቅርቧል፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ የተመለከተው የጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 138 መሠረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን እንዳለው አረጋግጦ የይርጋ ክርክርን በተመለከተ ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት ሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ሆኖ ጉዳዩ በሶማሌ ብ/ክ/መንግሥት ሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት እንዲታይ ተጠሪ አመልክተው ጽ/ቤቱ በ24/11/2000 ዓ.ም ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ ክሱ የቀረበው በ10/05/2001 ዓ.ም ጊዜ ድረስ ያለው ሲታይ የስድስት ወር /6/ ጊዜ አላለፈበትም ሲል በብይን መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ በፍሬ ነገር ረገድም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር ተሰኝቶ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤትም መቃወሚያውን ባለመቀበል በፍሬ ነገር ረገድ ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ መጠን ብቻ በማሻሻል የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም የካሳውን መጠን ብቻ በማሻሻል ወስኗል፡፡

ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ድርጅት ነ/ፈጅ ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም ጽፎ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ክሱ በይርጋ ይታገድ ይገባው እንደነበር እና የሥር ፍ/ቤቶች የይርጋ ክርክሩን ውድቅ ለማድረግ የሰጡት ምክንያት መሠረታዊ የሕግ ትርጉም ስሕተት የተፈፀመበት ስለመሆኑ እንዲሁም በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 16648 የተሰጠውን ውሳኔ የሚፃረር መሆኑን፣ በፍሬ ነገር ረገድም የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን ውል በአግባቡ ያላገናዘበ ስለመሆኑ በማብራራት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲታረም አመልክተዋል፡፡

የሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ የአመልካች ድርጅት የይርጋ መቃወሚያ የታለፈበትን አግባብ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡

የተጠሪ ወኪል ሰኔ 4 ቀን 2002 ዓ.ም በጽሑፍ ባቀረቡት መልስ የሥራ ውል ከተቋረጠው ሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ክስ እስከቀረበበት ጥር 10 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ 6 ወር ከ10 ቀን መሆኑን አምነው ይህ ጊዜ ያለፈው ተጠሪ ክስ ከማቅረባቸው በፊት ጉዳዩ በክልሉ ሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት እንዲታይ አመልክተው እንደነበር እና ጽ/ቤቱም ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት አለመቻሉን ገልፆ በ24/11/2000 ዓ.ም ውሳኔውን ያሳወቃቸው በመሆኑ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ከ24/11/2000 ዓ.ም ነው በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና አመልክተዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከፍሲል በዝርዝር እንደተመለከተው በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው ሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም መሆኑ እና ክስ የቀረበው ጥር 10 ቀን 2001 ዓ.ም መሆኑ አላከራከረም፡፡ ይህ ጊዜ ሲሰላም ስድስት ወር ያለፈው መሆኑን ተጠሪም አምነዋል፡፡ በተጠሪ በኩል የቀረበው ክስ የሥራ ውል የተቋረጠው አለአግባብ ነው በሚል ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲወሰኑ በሚል ነው፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ልዩ ልዩ የመብት ጥያቄዎችን አስመልክቶ ክሱ መቅረብ ያለበትን የጊዜ ገደብ ወስኗል፡፡

ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የአዋጁ አንቀጽ 162(4) የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሠራተኛውም ሆነ በአሠሪው የሚቀርብ ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ የሥራ ውሉ በተቋረጠ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ በግልፅ ደንግጓል፡፡ በዚህ መዝገብ የቀረበው የክፍያ ጥያቄም የሥራ ውል ከተቋረጠበት ከሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ክስ እስከቀረበበት ጥር 10 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ ስድስት ወር ያለፈው ስለመሆኑ ተረጋግጧል የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካችን የይርጋ ክርክር ውድቅ ለማድረግ የሰጡት ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ እነሱን አንድ በአንድ እንመረምራለን፡፡ አንደኛው ምክንያት ተጠሪ የሥራ ውል እንደተቋረጠባቸው አቤቱታቸውን ለክልሉ ሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት አመልክተው ጽ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጠው ሐምሌ 24 ቀን 2000 ዓ.ም ስለሆነ የይርጋ ጊዜ መቆጠር ያለበት ከሐምሌ 24 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ነው የሚል ነው፡፡ በግራ ቀኙ መካከል ያለው ክርክር የሥራ ውል በማቋረጡ ሊከፈል የሚገባ ልዩ ልዩ ክፍያን የሚመለከት ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ላይ የሥራ ውል አመሠራረት እና በግኙኝነት ሂደት የሚፈጠሩት ክርክሮች ለመፍታት የተለያዩ አካላት ሥልጣን የተሰጣቸው ስለመሆኑ የአዋጁን ክፍል ዘጠኝ አንቀጽ 136 እና ተከታዮችን ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ አሁን ለተያዘው ጉዳይ የሥራ ውል በመቋረጡ ሊከፈል የሚገባ ክፍያን አስመልክቶ ሥልጣን የተሰጠው አካል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ስለመሆኑ ከአዋጁ አንቀጽ 138 ድንጋጌ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡

ተጠሪ ይህንኑ ጥያቄ ለክልሉ ሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት አቅርበውም ቢሆን በተያዘው ጉዳይ ላይ ለመወሰን በህግ ስልጣን ያልተሰጠው አካል እንደመሆኑ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በመ/ቁ 16648 የሰጠው የሕግ ትርጉም ይህንኑ ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ለክልሉ ሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ነበር በሚል የይርጋው ጊዜ ከሐምሌ 24 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ሊቆጠር ይገባል ያሉት የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ችሎት ፍ/ቤት በመ/ቁ 16648 የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት የይርጋ ጊዜው አቆጣጠር የሥራ ቀናትን ብቻ መሠረት ያደረገ ነው የሚል ሲሆን ለዚህም የጠቀሱት የአዋጁን አንቀጽ 163 ነው፡፡ ተጠቃሽ ድንጋጌ የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር የሚመለከት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀናት አቆጣጠር የመጀመሪያው እና የመጨረሻውን ቀን የሚያመለክት ነው፡፡ የመጨረሻው ቀን የሥራ ቀን ካልሆነ በተከታዩ የሥራ ቀን እንደሚወሰድ የሚያመለክት ቢሆንም ሙሉ ጊዜው የሚሰላው የሥራ ቀናትን ብቻ በመለየት ነው የሚል ይዘት ያለው ስለመሆኑ የድንጋጌው አንቀጽ 163(2) አያመለክትም፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ትርጉም የሕጉን መንፈስ የያዘ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ባጠቃላይ የሥር ፍ/ቤቶች ይርጋ ጊዜው ክሱን አያስቀረውም ለማለት የሰጡት ምክንያቶች በሕግ ረገድ የተሳሳተ ትርጉም የሰጡበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

ስለዚህ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 23/2002 የሰጡት ውሳኔ እና የሱማሌ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ የክፍያ ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162(4) መሠረት በይርጋ ታግዷል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 55189

ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

***ዳኞች፡-*** *ሂሩት መለሰ*

*ታፈሰ ይርጋ*

*ብርሃኑ አመነው*

*አልማው ወሌ*

*ዓሊ መሐመድ*

***አመልካች፡-*** *አዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል - ጠ/ ሃሣብ ከፋይ - ቀረቡ*

***ተጠሪ*** ፡- *አቶ ዘላለም መንግስቱ - ጠ/ ሻምበል የሥጋት - ቀረቡ*

***ፍ ር ድ***

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ አመልካች ያለአግባብ ከስራ ያሰናበታቸው በመሆኑ ደሞዝና ጥቅማ ጥቅም ከፍሎ ወደ ስራ እንዲመልሳቸው አመልክተዋል፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት የተለያዩ ጥፋቶች በመፈፀማቸው ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች ተጠሪን ከስራ ለማሰናበት ምክንያት ናቸው በማለት በስንብት ደብዳቤው ላይ የዘረዘራቸውን ጥፋቶች ለመፈፀማቸው ያቀረባቸው ምስክሮች ስላላስረዱ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት ተጠሪ የ3 ወር ደሞዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን አመልካች በቅሬታው ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት በፈፀሙት ጥፋቶች መሆኑን በበቂ ሁኔታ አስረድቶ እያለ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው መባሉ ስህተት መሆኑን ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ቢባል እንኳን ተጠሪ ወደ ስራ ቢመለሱ መልካም የስራ ግንኙነት ስለማይኖር በአ/ቁ 377/96 በአንቀጽ 43/3/ መሠረት ካሳ ተከፍሏቸው ከስራ ሊሰናበቱ ሲገባ ወደ ስራ መመለሳቸው ተገቢ አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲሻር ጠይቋል፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ ወደ ስራ ቢመለሱ መልካም የስራ ግንኙነት አይኖርም በማለት የቀረበውን አቤቱታ ከአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 43/3/ አንፃር ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ተጠሪም ቀርበው በሰጡት መልስ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ፍሬ ነገርን የሚመለከት እንጂ የህግ ስህተትን የሚመለከት ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

አመልካች ተጠሪን ከስራ ማሰናበቱን ሳይክድ የሚከራከረው ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት በፈፀሙት ጥፋት በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ነው፡፡ አመልካች ለስር ፍ/ቤት በሰጠው መልስ ተጠሪ ፈፀሙ ያላቸውን ጥፋቶች ዘርዝሮ ገልጿል፡፡ ጥፋቶቹንም ስለመፈፀማቸው ያስረዳሉ ያላቸውን ምስክሮች ቆጥሮ ተሰምተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የምስክሮች ቃል መዝኖ አመልካች በተለይ ተጠሪን ከስራ ሲያሰናብት በስንብት ደብዳቤው ላይ የገለፃቸውን ጥፋቶች ስለመፈፀማቸው እንዳላስረዱ በፍሬ ነገር ረገድ አረጋግጧል፡፡ ይህ ችሎትም በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠን ፍሬ ነገር እንዳለ የሚቀበለው ከሚሆን በቀር ማስረጃውን በድጋሚ ሊመዝን የሚችልበት ስልጣን የለውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከስራ የሚያሰናብታቸው ጥፋት መፈፀማቸው ባለመረጋገጡ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በመባሉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፃሚል ማለት አይቻልም፡፡

ሌላው ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱ በህገ-ወጥ መንገድ ነው ቢባል እንኳን ወደ ስራ ቢመለሱ መልካም የስራ ግንኙነት ስለማይኖር ካሣ ተከፍሏቸው ሊሰናበቱ ይገባ ነበር በማለት አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ነው፡፡ በእርግጥ በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 43/3/ ስር የስራ ስንብቱ ህገ-ወጥ ቢሆን እንኳን ከስራ ግንኙነቱ ፀባይ የተነሳ ከፍተኛ ችግር የሚፈጥር ከሆነ ሰራተኛውን ወደ ስራ ከመመለስ ይልቅ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ የህጉ ድንጋጌም ሊተረጎም የሚገባው በአንድ በኩል የሰራተኛውን የስራ ዋስትና በሌላ በኩል ደግሞ ኢንዱስትሪን ሰላም በማመዛዘን ሊሆን ይገባል፡፡

በመሆኑም ሰራተኛው ወደ ስራ መመለሱ የአሰሪውን ስራ በከፍተኛ ደረጃ ሊጎዳ የሚችል መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ሰራተኛው በሆነው ባልሆነው ከስራ እንዲሰናበቱ ማድረግ ተገቢ አይሆንም፡፡ የህጉም አላማ ይህ አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ ጥፋቶች ናቸው ከሚባሉት ውስጥ አንዱና አመልካች ተጠሪ ስራ ቢቀጥሉ መልካም የስራ ግንኙነት ሊኖር አይችልም በማለት የሚከራከረው የተጠሪ የስራ አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ለማስረዳት በአመልካች በኩል የቀረቡ ምስክሮች ደግሞ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው እንደአመልካች ክስ አቀራረብ አላስረዱም፡፡ ከዚህ ውጪ ግንኙነቱ ቢቀጥል የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር ላይ ሊጥል የሚችል ሁኔታ ስለመኖሩ አመልካች ያስረዳው ነገር የለም፡፡ የአመልካች የስራ አፈፃፀም ዝቅትኛ መሆኑ ካልተረጋገጠ ደግሞ ተጠሪ ወደ ስራ ቢመለስ የስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር ላይ ሊወድቅ ይችላል ለማለት ስለማይቻል ተጠሪ ወደስራ ከሚመለሱ ይልቅ ካሣ ተከፍሏቸው ሊሰናበቱ ይገባል በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር ችሎቱ የሚቀበለው አይደለም፡፡ በመሆኑም በስር ፍ/ቤት ተጠሪ ወደ ስራ እንዲመለሱ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለው ለማለት አልተቻለም፡፡

## ***<u>ው ሣ ኔ</u>***

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33071 መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 91456 ሚያዚያ 6 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. ይህ ሰበር ችሎት ሚያዚያ 19 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም.አ

የሰ/መ/ቁ. 53358

ሰኔ 18 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ፖስታ አግልግሎት ድርጅት - ማስረሻ በለጠ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ጥላሁን ኩማ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የተነሳውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ሲሆን፣አመልካችን የከሰሰው የሥራ ውሌ ከሕግ አግባብ ውጪ አቋርጦብኛል በማለት ነው፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ የሥራ ውሉን ሊያቋርጥ የቻለው ተጠሪ በፈጸመው ከሥራ የሚያሰናብት ጥፋት ምክንያት እንደሆነ በመግለጽ የተከራከረ ቢሆንም፤ፍ/ቤቱ ግን የሥራ ውል ማቋረጥ እርምጃውን የወሰድከው እርጃውን ለመውሰድ በሕጉ የተፈቀደልህ የይርጋ ጊዜ ካበቃ(ካለፈ) በኋላ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ክርክሩን ውድቅ አድርጐአል፡፡ በዚህ መሰረትም ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደሥራው እንዲመለስ ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጸመ የሚለውን ስህተት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ እኛም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው ተጠሪ ፈጽሞታል የተባለውን ጥፋት በዲሲፕሊን ኮሚቴ ለማጣራት የወሰደው ጊዜ እግምት ውስጥ ሳይገባ ድርጊቱ በይርጋ ቀሪ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው በዚህ ሰበር ችሎት ሊወሰን የሚገባው የሕግ ጭብጥ የይርጋው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ጉዳዩ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጣርቶ ጥፋቱ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ ነው ወይንስ ጥፋቱ ተፈጽሞአል ከተባለበት ቀን ጀምሮ ነው? የሚለው ነው፡፡ ለዚህ ጭብጥ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ድንጋጌ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3/ የተመለከተው ነው፡፡ አንቀጽ 27 ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችሉ ምክንያቶችን በዝርዝር የያዘ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ አሰሪው ወገን ምክንያቶቹን መሰረት በማድረግ የሚወስደው የሥራ ውል የማቋረጥ እርምጃ በጊዜ ውስጥ የተገደበ መሆኑን የሚያመላክት ድንጋጌ ይዞአል፡፡ ድንጋጌው ከፍ ሲል የተጠቀሰው በንኡስ አንቀጽ /3/ የተቀመጠው ሲሆን፣ይዘቱም አሰሪ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ ያለው መብት ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱን ካወቀበት ከ30/ሰላሣ/ የሥራ ቀናት በኋላ በይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡ እንግዲህ እዚህ ላይ በቁልፍነት መታየት የሚገባው "... ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱን ካወቀበት ..." የሚለው የሕጉ አግባብ ነው፡፡ ከዚህ አባባል መገንዘብ የሚቻለው የመጀመሪያው ሁኔታ አሰሪው ውሉን ለማቋረጥ የማቋረጫ ምክንያቱን ማወቅ ይኖርበታል የሚለው ነው፡፡ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ ምክንያት መኖሩን ማወቅ የግድ ነው ከተባለ ደግሞ መቼ ነው ያወቀው የሚለው በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ይሆናል፡፡ ጥፋቱ ወይም የሥራ ውል ማቋረጫ ምክንያቱ መከሰቱን ለማረጋገጥ የተወሰነ

የማጣራት ሥራ የሚያስፈልግ ከሆነ ይህ የማጣራት ሥራ ከተከናወነ በኂላ ነው አሰሪው ምክንያት ወይም ጥፋት መኖሩን አውቆአል ሊባል የሚችለው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ምክንያቱ በእርግጠኝነት ያወቀው ጉዳዩን በዲሲፕሊን ኮሜቴ አማካይነት ካጣራ በኂላ እንደሆነ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል፡፡ ከተረጋገጠ በኂላም የሥራ ውሉን አቋርጧል፡፡ በዚህ መሃልም በተመለከተው ድንጋጌ የተቀመጠው የ30/ሰላሳ/ የሥራ ቀናት ጊዜ አልፎአል አልተባለም፡፡ ሁኔታው ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የሥራ ውሉን የማቋረጥ እርምጃ የወሰደው የይርጋው ጊዜ ካበቃ በኂላ ነው ለማለት የሚቻልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከዚህ አንፃር ሲታይ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሰረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32585 ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 89003 የካቲት 16 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች የሥራ ውል የማቋረጥ እርምጃውን የወሰደው የይርጋ ጊዜው ከማለፉ በፊት ነው ብለናል፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ወደ ጉዳዩ ሥረ ነገር በመግባት የሥራ ውሉ የተቋረጠው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ላይ ግራ ቀኝ ወገኖችን እንዲያከራክር እና ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 341/1/ መሰረት ይመለስለት ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 43160

ሰኔ 22 ቀን 2002 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች**፡- 1. እንደገና ተሾመ - ቀረቡ፡፡

2. ዳንኤል ባለ - አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ**፡- ኒው ጄኔሬሽን ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ነቀምቴ ቅርንጫፍ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኞች መካከል የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር አመልካቾች ከሣሾች የነበሩ ሲሆን፣ በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረቱት የሥራ ውላችን ከሕግ ውጪ ስለተቋረጠብን ልዩ ልዩ በአዋጁ የተመለከቱት ክፍያዎች ይክፈሉን በማለት ነው፡፡ ተጠሪም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ውሉ የተቋረጠው ዘመኑ በማብቃቱ ነው በማለት ሲከራከር፣ ፍ/ቤት ደግሞ ውሉ የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ነው የሚለውን የተጠሪ ክርክር በመቀጠል የአመልካቾች የውሉ ዘመን ከማብቃቱ በፊት ለሚሠሩበት ጊዜ የሥራ ስንብት ክፍያ ይከፈላቸው በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቾች በውሣኔው ባለመስማማት ይግባኝ ለሚሰማው የበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ ፍ/ቤቱም ውሉ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 10 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የተገባ ስለመሆኑ አሠሪው /ተጠሪ/ አላስረዳም የሚል ምክንያት በመስጠት ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው በማለት ደምድሟል፡፡ በዚህ መሠረትም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል የሥራ ውል ከሕግ ውጪ ሲቋረጥ ሊከፈሉ የሚገባቸውን ክፍያዎች በሙሉ አመልካቾች ይከፈላቸው በማለት ወስኖአል፡፡ በመጨረሻም ተጠሪ ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ በመቀጠልም የሰበር ችሎቱ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሣኔዎች ሽሮአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካቾች ጥር 27 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪ አቤቱታው ላይ ያለውን መልስ እንዲያቀርብ በተደጋጋሚ እድል የተሰጠው ቢሆንም፣ የሰጠው መልስ የለም፡፡ በመሆኑም ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እንደተመለከተው ተጠሪ በከፍተኛ ትምህርት መስጠት የተሰማራ ሲሆን፣ አመልካቾችን ቀጥሮ ሲያሠራ የነበረው በመምህርነት ነው፡፡ እንደሚታወቀው የመማር ማስተማር ሥራ ቀጣይነት ያለው ማለትም የማያቋርጥ ባሕርይ ያለው ሥራ ነው፡፡ አመልካቾች የሥራ ውላችን ያለአግባብ ተቋርጦብናል በማለት ክስ በመሠረቱበት ጊዜ ተጠሪ ሥራውን ሲቀጥል እንደነበረም አላከራከረም፡፡ አመልካቾችን የቀጠርኩት ለተወሰነ ጊዜ ነው በማለት ሲከራከር የቆየው ሥራው የለም የሚል ምክንያት በመስጠት ሳይሆን፣ ውሉ የተፈረመው ለተወሰነ ጊዜ ተብሎ ነው በማለት ነው፡፡ በዚህ መልክ ያቀረበው ክርክር ግን በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ በፍሬ ነገር ረገድ ሊያስረዳ አልቻለም፡፡ አንድ የሥራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ የተደረገ ነው ሊባል የሚችለው በአንቀጽ 10 ከተመለከቱት ሁኔታዎች በአንዱ ምክንያት የተደረገ ከሆነ ስለመሆኑ በአንቀጽ 9 ተደንግጎአል፡፡ በመሆኑም ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ተብሎ ተፈርሞአል የሚለው የተጠሪ ክርክር

የሕግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔም ከዚህ አንፃር ስናየው በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 65098 ኅዳር 1 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13964 ሚያዝያ 24 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቶአል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 52459

ሐምሌ 16 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** እነ ወ/ሮ ሙሉ ታደሰ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አለሙ መራ ኮንስትራክሽንና ጠቅላላ ብረታ ብረት ስራ ድርጅት

- ባለቤት ወ/ሮ አልማዝ - ቀረቡ

# ፍ ር ድ

የአንደኛ አመልካች ባለቤትና የቀሪዎቹ አመልካቾች አባት በተጠሪ ድርጅት ሲሰሩ ከዚህ አለም በሞት ስለተለዩ የስንብት ክፍያና የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ ስለተደረገባቸው የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካቾች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የአንደኛ አመልካች ባለቤትና የቀሪዎቹ አመልካቾች አባት በተጠሪ ድርጅት ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በዘበኛነት ተቀጥረው ሲሰሩ የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት በመለየታቸው የሚገባቸው የአገልግሎት ክፍያና የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ የተጠሪ ድርጅት ባለቤት ቀርበው በሰጡት መልስ የጋራዥ ስራውን መስራት ባለመቻላቸው ለሌላ ሰው በኮንትራት የሰጡ መሆኑንና ሟች ከሳቸው ጋር ያለውን ስራ ውል ከሰኔ 1 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ ተቋርጦ ስራውን በኮንትራት ከያዘው ሰው ጋር ተዋውለው ይሰሩ ስለነበር ጥያቄው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የአንደኛ አመልካች ባለቤትና የቀሪዎቹ አመልካቾች አባት የስራ ውል የተቋረጠው በሞት ምክንያት በመሆኑና በዚህ ሁኔታ የስራ ውል ሲቋረጥ የስንብት ክፍያ እንዲከፈል የሚያስገድድ ህግ ስለሌለና የአመት እረፍትም ቢሆን በሞት ምክንያት የስራ ውሉ ለተቋረጠ ሰራተኛ ስለማይሰጥ ጥያቄውን ተቀባይነት የለውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው የስር ፍ/ቤት የሟች አገልግሎት ክፍያም ሆነ የአመት እረፍት ለሚስታቸውና ለልጆቻቸው አይከፈልም መባሉ ስህተት በመሆኑ እንዲታረምላቸው አመልክተዋል፡፡ ይህ ችሎትም የሟች የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ለአመልካቾች ሊከፍል አይገባም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም ቀርበው በሰጡት መልስ የሟች ስራ ውል የተቋረጠው ከሞታቸው በፊት በመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

አመልካቾች የጠየቁት የሟቹ አገልግሎት ክፍያና አመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው ነው፡፡ የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄን በተመለከተ ለሰበር ችሎት ያስቀርበዋል ያልተባለ ከመሆኑም ባላይ ይህን ነጥብ አስመልክቶ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 45264 ከሰጠው ትርጉም ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ይህንኑ ቅሬታ የምንመለከተው አይሆንም፡፡ ሁለተኛው የክፍያ ጥያቄ የአመት እረፍትን የሚመለከት ነው፡፡ በአ/ቁ 377/1996 አንቀፅ 77(5) በአዋጁ መሰረት የስራ ውሉ የተቋረጠ ሰራተኛ ያልወሰደው የአመት ፈቃድ ታስቦ በገንዘብ ተለውጦ እንደሚሰጠው ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ የሚሰጠው በአዋጁ ከተደነገጉት የስራ ማቋረጫ ምክንያቶች በተወሰኑት ምክንያቶች ብቻ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ነው የሚል ገደብ አላስቀመጠም፡፡ በመሆኑም በማንኛውም በአዋጁ

በተመለከቱ ድንጋጌዎች የስራ ውሉ ከተቋረጠ የሰራተኛው የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአዋጁ መሰረት የስራ ውል ከሚቋረጥባቸው መንገዶች አንዱ ደግሞ የሰራተኛው መሞት እንደሆነ ከአንቀፅ 24(2) የምንገነዘበው ነው፡፡ በመሆኑም የሰራተኛው የስራ ውል በሰራተኛው ሞት ምክንያት ከተቋረጠ የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ለወራሾቹ ሊከፈል የማይገባበት የህግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት የስራ ውሉ በሞት ምክንያት ሲቋረጥ የአመት ዕረፍት በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል አይገባም ሲል የደረሰበት መደምደሚያ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን ተጠሪ ከስር ጀምሮ በተጠሪና በአንደኛ አመልካች ባለቤት እና በቀሪዎቹ አመልካቾች አባት መሃከል የነበረው የስራ ውል ሰኔ 1994 ዓ.ም የተቋረጠና ሟች ጋራዡን በኮንትራት ከያዙት ሰው ጋር ባደረጉት የስራ ውል የሚሰሩ ስለመሆኑ የሚከራከሩ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ይህን የአመልካች ክርክር ሳይመለከት ማለፉን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳን የሟቹ አመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል የሚገባ ቢሆንም ተጠሪ ክፍያውን የመፈፀም ሃላፊነት ያለባቸው መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 39535 ህዳር 7 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 86994 ጥር 12 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካቾች የሟች የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው፡፡ ነገር ግን የስራ ውሉ በሞት ምክንያት በመቋረጡ የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል አይገባም የሚለው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የስር ፍ/ቤት በሟችና በተጠሪ መሃከል የስራ ውል መኖር አለመኖሩን ግራ ቀኙ ካቀረቡት ማስረጃ አኳያ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 45170

ሐምሌ 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የቅድስተ ማሪያም አፀደ ሕፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት - የቀረበ የለም

**ተጠሪ**፡- መ/ት ሲሳይ ሙሉጌታ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥራ ውል ማቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪ የክስ ምክንያት አመልካች ያለአግባብ የሥራ ውል አቋርጦብኛል ተገቢው ካሣና ጥቅማጥቅም ይክፈለኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ የክረምት ሥራ እንድትሰራ መመሪያ ተሰጥቷት እያለ ያለፈቃድ ወይም በቂ ምክንያት ከሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ነሐሴ 5 ቀን 2000 ዓ.ም ሥራ ላይ ባለመገኘቷ የሥራ ውል የተቋረጠው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1//ለ/ መሰረት ነው ሲል ስንብቱ ሕጋዊ ስለመሆኑ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ጊዜው የመምህራን የዓመት እረፍት ጊዜ ነው በማለት ከሥራ መቅረቷን የተቀበለች ቢሆንም መምህራን በክረምት ወራት ሙሉ ለሙሉ እረፍት ስለመሆናቸው በአዋጅ፣በደንብ ወይም በመመሪያ የተደነገገ የለም፣አሰሪ ስራ እንዲሰራ መመሪያ ከሰጠ መሥራት ይጠበቅበታል በሚሉ ምክንያቶች የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው በአግባቡ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባለች፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ መምህራን በክረምት ወራት እረፍት እንደሚያደርጉ ሲሰራበት የቆየ ልምድ ነው በዚህ መዝገብም የቀረቡት ማስረጃዎች ይህንኑ ያረጋግጣሉ ተጠሪም በእረፍት ወቅት ሥራ ላይ አለመገኘታቸው የሥራ ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ሊሆን አይገባም የሚሉ ምክንያቶችን በመዘርዘር የሥራ ውል ያለአግባብ ተቋርጧል በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ለተጠሪ የካሣ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ እና ክፍያ የዘገየበት ጊዜ እንዲከፈል ወስኗል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የሰራተኛ የዓመት እረፍት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ በተደነገገው አግባብ በአሰሪና ሰራተኛ ስምምነት የሚወሰን እንጅ ሰራተኛው በዘፈቀደ የሚወስነው አይደለም፣በት/ቤቱ ደንብ መሰረት የዓመት እረፍቷን በነሐሴ ወር ወስዳለች እንዲሁም የ2000 ዓ.ም የዓመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ተከፍሏል በሚሉ ምክንያቶችን በመጥቀስ የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲታረም አመልክቷል፡፡

ሰበር ችሎቱም የአመልካችን አቤቱታ ከአዋጅ አንቀጽ 13/1/ አንፃር ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ተጠሪም ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርባለች በይዘቱም የሥር ፍ/ቤት ክርክር በማጠናከር የክረምት ወራት ለመምህራን በተለየ ሁኔታ የእረፍት ጊዜ እንደመሆኑ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለመሥራት ግዴታ የለብኝም በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቃለች፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ ለማየት የተቻለው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡ አመልካች አጥብቆ የተከራከረው ተጠሪ በክረምት ወቅት እንድታስተምር

መመሪያ ተሰጥቷት ፈቃደኛ ሳትሆን ቀርታለች በሚል ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው የክረምት ትምህርት ለመስጠት አመልካች ከተወሰኑ መምህራን ጋር ውይይት በማድረግ በስምምነት የማስተማር ሥራ ሲያከናውኑ እንደነበር ተመልክቷል፡፡ ይህውም ሐምሌ 4 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገ ስብሰባ የተወሰነ ስለመሆኑ ተገልጧል፡፡ ስለሆነም በዚህ መልክ ተጠሪ ፈቅዳ ግዴታ የገባች ስለመሆኑ በዚሁ ክርክር የተረጋገጠ ፍሬ ነገር አላገኘንም፡፡ ከዚህም ሌላ ተጠሪን የሚያስገድድ ግልጽ መመሪያ ወይም ደንብ ስለመኖሩ አመልካች አላስረዳም፡፡

ስለሆነም ግልጽ ደንብ ወይም መመሪያ መኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ በክረምት ወቅት ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ አልሆነችም ተብሎ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13/1/ የተመለከተውን ግዴታ ጥሳለች ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘንም፡፡

ስለሆነም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ በፍሬ ነገርም ሆነ በሕግ ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

በዚሁ ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04326 በ01/07/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ሚያዝያ 14 ቀን 2001 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

# ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

የሰ/መ/ቁ. 43424

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን

**ተጠሪ**፡- እነ አቶ መስፍን ጀምበሩ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የንብረት ግምት ይከፈለን ጥያቄ ሲሆን፤ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች አመልካች ከቡታጅራ ሆሣእና በሚያሰራው መንገድ ምክንያት በሆሣእና ከተማ የሚገኙ ንብረቶቻቸው እንዲነሱ የግምት ስራ ተሰርቶላቸው በዚሁ መጀመሪያ ግምት የከተማው አስተዳደር ንብረቶቻቸውን ያስነሳቸው መሆኑን፣የንብረቶቻቸው ዓይነትና ግምት ምን ያህል እንደሆነ ዘርዝረው አመልካች ካሣ እንዲከፈለን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካች ላይ በሐድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት የተናጠል ክስ ሲሆን የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ ለመንገድ ሥራው የዲዛይን ለውጥ ማድረጉንና በተለወጠው ዲዛይን መሰረትም ንብረቶቹ መነሳት የማያስፈልጋቸው በመሆኑ ኃላፊነት እንደሌለበት፣ተነሱ ወይም እንዲፈርሱ የተደረጉ ንብረቶች በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 3/1/ እና 4/1/ ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን ሥርአት ባልተከተለ መልኩ የተከናወነ በመሆኑ ሊጠየቅ የማይገባ መሆኑን፣እንዲሁም አዋጁን ባልተከተለ መንገድ የራሱን ሥራ ለመስራት ንብረቶችን አስነሳ የተባለው የሆሳእና ከተማ አስተዳደር በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ይታዘዝለት ዘንድ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪዎችን ክርክርና የተለያዩ መዛግብት መርምሮ የሆሳእና ከተማ አስተዳደር ወደ ክርክሩ ይግባልኝ የሚለውን የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጐ አመልካች ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመግለጽ ተጠሪዎች በጠየቁት ዳኝነት መሰረት ወስኖላቸዋል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ይኸው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ካራከረ በኋላ መዛግብትን በአንድ ላይ በማጣመር መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይሁንኑ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ-ፈጅ የካቲት 06 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት 3(ሦስት) ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- በመጀመሪያ መንገዱ ሊሰራበት በታሰበው ስፋት መሰረት የተሰራው ግምት እጅግ የተጋነነ በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለው ለከተማ አስተዳደሩ አመልካች ከገለጸለት በኋላ አስተዳደሩም ይህንን አውቆ የዲዛይን ክለሳ እና በዚህም መሰረት የግምት ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ በቀድሞው ዲዛይን መሰረት ተነስቷል ለሚባል ንብረት ቦታው ለሕዝብ ጥቅም ባልዋለበትና በሕጉ አግባብ ላልተነሳ ንብረት ካሣ ለመክፈል ሕጋዊ ግዴታ የሌለበት መሆኑን በመዘርዘር የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ሙሉ በሙሉ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው መጋቢት 09 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም አመልካች የሆሳእና ከተማ አስተዳደር ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ያቀረበው ጥያቄ መታለፉ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በመጀመሪያ መንገዱ ሊሰራበት በታሰበው ስፋት መሰረት የተሰራው የንብረቶች ግምት ባልተለመደ ሁኔታ እጅግ የተጋነነ በመሆኑ እንደማይቀበለው ለከተማ አስተዳደሩ ገልጾና አሳውቆ የዲዛይን ክለሳና የግምት ስራ ተጠናቅቆ ከአለቀ በኋላ ንብረቶቹ እንዲነሱ ወይም እንዲፈርሱ ለተደረገው ሁኔታ አመልካች ኃላፊነት እንደሌለበትና ይህንን ድርጊት የከተማው አስተዳደር ለራሱ ሥራ ሲል ስለአከናወነው ኃላፊነት ሊወስድ ስለሚገባ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ሊታዘዝ ይገባል በማለት የሥነ-ሥርአት ጥያቄ ማንሳቱን ነው፡፡ ይህ የአመልካች ጥያቄ የስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረበው የተጠሪዎች አመልካች የመንገዱን ስፋት በመቀነስ ዲዛይኑን ስለማስተካከሉ ለማወቃቸው ወይም የከተማው አስተዳደር ንብረታቸውን ያፈረሰው አዲስ በተስተካከለው ዲዛይን ለመሆኑ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ የለም፣አስተዳደሩ እውነታውን እያወቀ አፍርሶ ከሆነ አመልካች ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚያደርገው ክርክር ተጠሪዎች መጉዳት የለባቸውም፣አመልካች በውል ወይም በሕግ ከአስተዳደሩ ጋር ግንኙነት ወይም ስምምነት ካለው ከሶ ማስከበር ከሚችል በስተቀር ተጠሪዎችን ሊጎዳ አይገባም በሚል ምክንያት ነው፡፡

በመሰረቱ በአንድ ጉዳይ ላይ ክስ ሲቀርብና የክሱም ምክንያት የብዙ ሰዎችን መብትና ጥቅም የሚነካ ሆኖ ከእነሱ አንዱ ወይም ከፊሉ ክስ በቀረበ ጊዜ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጉዳዩ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ወይም ፍርድ መብትና ጥቅም የሚነካ ሲሆን በክሱ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 39/1/ እና 40/2/ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል፡፡ እነዚህ ወገኖች ተካፋይ ሳይሆኑ የሚሰጠው ውሣኔ ወይም ፍርድ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑም የተጠቃሽ ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም በክሱ መግባት ያለበት ተከሣሽ የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የክርክር ተካፋይ እንዲሆንና በቀረበው ክስ የመልስ መከላከያውን እንዲያቀርብ ሊያዘው የግድ የሚል ስለመሆኑ ሥነ ሥርአቱ ያሳያል፡፡ በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች ማለት ደግሞ ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ጥቅማቸው፣መብታቸው ወይም ግዴታቸው የሚነካ፣በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች ስለመሆናቸውም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይም የሆሳእና ከተማ አስተዳደር ከተማውን የማስተዳደር ኃላፊነትና ተግባር ያለበት ሲሆን በከተማው ውስጥ በሚካሄደው የልማት እንቅስቃሴ ቀጥተኛ የሆነ ተሳታፊነት፣ቁጥጥር የማድርግ እና ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን እንደሚያከናውን የሚታመን ነው፡፡ በተለይም በሚያስተዳድረው ከተማ በአመልካች የሚሰራው ዓይነት ሥራ ሲሰራ በመንገዱ ስራ ለሚነሱም ሆነ ለሚፈርሱ ንብረቶች ተገቢው ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ በግምት ወቅትም ሆነ በአከፋፈሉ ጊዜ ተሣታፊነት ያለበት ስለመሆኑ በዚህ ረገድ የተደነገጉት ሕጐች ያሳያሉ፡፡ በሕጐቹ የተጣሉበትን ግዴታዎችን መወጣት ደግሞ የግድ ይሏል፡፡ አመልካች ለሆሳእና ከተማ አስተዳደር የተጠሪዎች ንብረቶች ሊነሱ ወይም ሊፈርሱ የማይገባ መሆኑን ከዲዛይን ክለሳ በኋላ ማሳወቁን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ እንዲህ ከሆነም ደግሞ ንብረቶቹ የተነሱት ወይም የፈረሱት በመንገድ ስራ ምክንያት መሆን አለመሆኑን፣ኃላፊነቱ የየትኛው ወገን እንደሆነ አከራካሪ የሚያደርገውና የከተማ አስተዳደሩን ወደ ክርክሩ እንዲገባ የግድ የሚል ጉዳይ ነው፡፡ ለክርክር ማስረጃ የማቅረብ ጉዳይ ደግሞ ይኸው ሥነ-ሥርአት ከተከናወነ በኋላ የሚከተል ጉዳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ተገቢ ባልሆነ የክርክር ደረጃ አመልካች ማስረጃ አላቀረበም በሚል ምክንያት የከተማው አስተዳደር ወደ ክርክሩ ይግባልኝ የሚለውን የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ ስለሆነም የሆሳእና ከተማ አስተዳደር ወደ ክርክሩ ሳይገባ የተሰጠው ውሣኔ ሥነ-ሥርአታዊ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በሐድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 03332፣ 02799፣ 02803፣03388፣ 03302፣02797፣ 03028 እና 02798 ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 57916፣ 57284፣ 59917፣ 64576፣ 64577፣ 66578፣ 66599 ተከፍቶና በመዝገብ ቁጥር 59916 ተጣምሮ ታይቶ ጥር 19 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡

2. የሆሳእና  ከተማ አስተዳደር በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን ያለበት ወገን በመሆኑ ለቀረበው ክስና መልስ መከላከያውን እንዲያቀርብ የሐድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰጥቶ ጉዳዩን እንደገና በመመልከት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡
3. ለክርክር የወጣን ወጪና ኪሳራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 43410

ህዳር 30 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ አሠገደች ጎርፌ

**ተጠሪ፡-** ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል - አልቀረበም

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስነ-ስርዓት ህግን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ አመልካች ባለመቅረቡና ተጠሪ ቀርበው መዝገቡ እንዲዘጋ በመጠየቃቸው ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2) መሰረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች ለፍ/ቤቱ በታህሣሥ 14 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መዝገቡ እንደገና እንዲከፈትለት የቃል ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ያልቀረበበት ምክንያት በቂ ባለመሆኑ መዝገቡ ሊከፈት አይገባም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ትዕዛዞች ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው የቃል ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ አመልካች ሳይቀርብ ተጠሪ ከቀረበ መዝገቡ ሊዘጋ የሚገባው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሰረት እንጂ በቁጥር 62(2) አይደለም፣ በቀነ-ቀጠሮው የቀረንበት ምክንያትም የብሔር ብሔረሰቦች በዓል የሚከበርበት ቀን ስለነበር መንገድ በመዘጋጋቱ አርፍደን ስለደረስን ስለሆነ መዝገቡ እንዲከፈት ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡ አቤቱታውም ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፁሁፍ አቀርበዋል፡፡ መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች ቃል ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ሳይቀርብ ተጠሪ መቅረቡ አልተካደም፡፡ የባለጉዳዮች ወደ ፍ/ቤት መቅረብና አለመቅረብ የሚያስከትለውን ውጤት ምን እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከቁጥር 65 እና ተከታዮች ባሉት ድንጋጌዎች ተዘርዝረው ተቀምጠዋል፡፡ በዚህ መሰረት ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ሳይቀርብ ተከሳሹ ቀርቦ ክሱን በከፊል ወይም በሙሉ ያመነ ከሆነ ሳመነው ጉዳይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ለመስጠት እንደሚችልና ከካደ ደግሞ መዝገቡ እንደሚዘጋ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 ያመለክታል፡፡ በዚህ አንቀፅ ከሳሽና ተከሳሽ የሚለው አነጋገር ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪ እንደሚጨምር ከሥነ-ሥርዓቱ ድንጋጌ አንቀጽ 32(2) ሥር መመልከት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2) አግባብነት የሚኖረው ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ሁለቱም ተከራካሪዎች ያልቀረቡ ከሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ይግባኝ ባይ የነበረው አመልካች ሳይቀርብ ተጠሪ ቀርቧል፡፡ በዚህም ምክንያት አግባብነት የሚኖረው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 እንጂ ቁጥር 69(2) አይደለም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2)"ን" መሰረት አድርጎ መዝገቡን መዝጋቱ ተገቢ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ ከአመልካች ጋር ሲከራከር የነበረ በመሆኑና ክርክር በሚሰማበት እለት አመልካች ባለመቅረቡ ተጠሪ መዝገቡ እንዲዘጋለት መጠየቁ ተጠቃሎ ሲታይ አቤቱታውን ያላመነ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በቀነ-ቀጠሮው ያልቀረበው በበቂ ምክንያት ነው ቢልም ፍ/ቤቱ ምክንያቱን መዝኖ በቂ አይደለም የሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ የምክንያቱ በቂ መሆን አለመሆን ደግሞ የማስረጃ ምዘና እንጂ የህግ ክርክር ባለመሆኑ ለሰበር አቤቱታ የሚቀርብበት ነጥብ ነው ሊባል አይችልም፡፡ በአጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሰረት መዝጋት ሲገባው በቁጥር 69(2) መሰረት መዝጋቱ ትክክል ባይሆንም መዝገቡ በመዘጋቱ ግን መሰረታዊ የህግ ስህተት ፈፅሟል ማለት አልተቻለም፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. **የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ** 39200 **ህዳር** 30 **ቀን** 2001 **ዓ.ም እና ጥር** 18 **ቀን** 2001 **ዓ.ም የሰጣቸው ትዕዛዞች ፀንተዋል፡፡**
2. **ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የቻቻሉ፡፡**

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

*ራ/ታ*

የሰ/መ/ቁ.47551

ታህሣሥ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ንግድ ማተሚያ ድርጅት - ነ/ፈጅ ጌታቸው ብርሃኑ

**ተጠሪ፡-** አቶ ካሱ ሙላት - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ያለ አግባብ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን በመግለጽ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለቀረበው ክስ በሰጠው መልስ ተጠሪ ለ6 ተከታታይ ቀናት ከስራ በመቅረታቸው ከስራ እንደተሰናበቱ በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲሆንለት አመልክቷል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ ከስራ ታመው የቀሩ መሆኑን ቢገልፁም ታመው ስለመቅረታቸው ማስረጃ እንዲያቀረቡ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጠይቀው ማቅረብ አልቻሉም፣ ያቀረቡት የሕክምና ማስረጃ በወቅቱ ያልቀረበና ከስራ ከተሰናበቱ በኋላ የተፃፈ ስለሆነ ከስራ የተሰናበቱት በአግባቡ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው ለማስረዳት የቀረበው አንደኛው ማስረጃ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የሌለው የትርፍ ሰአት ክፍያ የሚመለከት ነው፡፡ ሁለተኛው ማስረጃ የዲሲ□ሊን ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ ሲሆን አንድ ሰራተኛ ቀሪ መሆኑን ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባው የሰነድ ማስረጃ እንጂ የዲሲ□ሊን ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ ስላልሆነ ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ የ6 ወር ደሞዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት በህገ-ወጥ መንገድ ነው በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ተጠሪ በስር ክሳቸው በህመም ምክንያት ከስራ በመቅረታቸው አመልካች ያለአግባብ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ከስራ የተሰናበቱት ለ6 ተከታታይ ቀናት ከስራ ስለቀሩ መሆኑን ተከራክሯል፡፡ ከክርክሩ ሂደት እደተረዳነው ተጠሪ ከስራ መቅረታቸውን አልካዱም፡፡ ክርክራቸው የቀሩት በህመም ምክንያት ነው የሚል ነው፡፡ ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ግልባጭ በህመም ምክንያት ከስራ ለመቅረታቸው ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ማቅረብ አለመቻላቸውን ተረድተናል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ቢሆን ተጠሪ ማስረጃቸውን ለዲሲፕሊን ኮሚቴ አቅርበዋል አላለም፡፡ ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የአንድን ሰራተኛ ከስራ መቅረት ማስረዳት የሚቻለው በሰነድ ማስረጃ እንጂ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ አይደለም የሚል ነው፡፡ በመሰረቱ ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው ክደው አልተከራከሩም፡፡ የሚከራከሩት ከስራ የቀሩት በህመም መክንያት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በህመም ምክንያት ስለመቅረታቸው የማስረዳት ሸክም ያለባቸው ተጠሪው ናቸው፡፡ ተጠሪ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ማቅረብ አለመቻላቸው በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ከዛ በኋላ ደግሞ ያቀረቡት ማስረጃ ከስራ ከተሰናበቱ በኋላ የተፃፈና እጅግ ዘግይቶ የቀረበ ማስረጃ ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ ፍሬ ነገር ለማስረዳት ተለይቶ የተመለከተ ማስረጃ እንዲቀርብ ህጉ ካላስገደደ በቀር ይህን ፍሬ ነገር በማንኛውም የማስረጃ አይነት ከማስረዳት የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ በማስረጃነት ሊቀርብ የማይገባበትን የሕግ መሰረት አልገለፀም፡፡ ቢያንስ ማስረጃንውን መዝኖ ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው በበቂ ሁኔታ ማስረዳት የሚችል መሆን አለመሆኑን ሊመዝን ይገባ ነበር፡፡ በመሆኑም በማስረጃነት ሊቀርብ የማይችልበትን ምክንያት ሳይገልጽ በድፍኑ ቃለ-ጉባኤው ሊቀርብ የማይችል ማስረጃ ነው በሚል ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ

ሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከስራ የቀሩት በህመም ምክንያት መሆኑን ቢገልፁም ይህን ሳያስረዱ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 79174 ሰኔ 12 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27244 መጋቢት 14 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 40229

ታህሳስ 15 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ኸይሮ መሐመድ - ጠበቃ አታክልት ሃ/ስላሴ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ መዲና በያን - ቀረቡ

2. አቶ ደኑር አብደላ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ሲሆን የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ በአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ከተወሰነ በኋላ የንብረት ክፍፍሉንም ፍ/ቤቱ ተመልክቶ በ8-2-2000 ዓ.ም ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት የካቲት 17 ቀን 2000 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት አቤቱታ አመልካችና ተጠሪ የእኔን ሚስትነት ሰርዘው እኔ በማላውቀው ሁኔታ የባልና ሚስት ፍቺ አስወስነው የንብረት ክፍፍልም እንዲደረግ የተወሰነ ስለሆነ ይህ ውሳኔ የእኔን መብት የሚጐዳ ስለሆነ ይሰረዝልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ የመቃወም አመልካች በተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር በቀጠሮ ላይ እንዳለ ግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም የጣልቃገብነት አቤቱታ አቅርባ አመልካችና ተጠሪ (የአሁን ተጠሪዎች) መልስ እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ተሰጥቶ ነገር ግን የመቃወም አመልካች ትዕዛዙን ባለማድረሳቸው ድጋሚ ትዕዛዝ ተሰጥቶ በድጋሚውም ትዕዛዝ መሠረት ባለመፈጸማቸው አቤቱታቸውን ባለመቀበል ክርክሩ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለው ደግሞ ክርክር እየተደረገ መሆኑን ያልተገነዘበ ወገን በሌለበት ክርክር ተደርጎ የተሰጠው ውሳኔ መብቱን የነካበት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ነገር ግን ክርክር መኖሩን የተገነዘበ ሰው ከበስተጀርባ ሆኖ የክርክሩን ሚዛን በመገምገም እርሱን በሚመለከት አጥጋቢ ፍርድ ባልተሰጠ ጊዜ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ አቤቱታ ማቅረብ ከሥነ-ሥርዓት ሕጉ ዓላማ አኳያ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በዚህም ጉዳይ የመቃወም አመልካች የክርክሩ ተካፋይ ለመሆን አቤቱታ አቅርባ መጥሪያ እንድታደርስ ለሁለት ጊዜ ትዕዛዝ የተሰጠ ቢሆንም በትዕዛዙ መሠረት ሳትፈጽም ቀርታ ከውሳኔ በኋላ ወደ ክርክሩ ለመግባት አቤቱታ ማቅረቧ ክርክር መኖሩን እያወቀች ስለሆነ አቤቱታው በተገቢው አኳኋን አልቀረበም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ መ/ሰጭዎችን ሳይጠራ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ተገቢነቱን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችንም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና እንደዚሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማንኛውም ሰው ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያውን ለማቅረብ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 ላይ ተመልክቷል፡፡

መቃወሚያ ማቅረብ የሚፈቀድበት ደንብ መሠረታዊ ዓላማም ምንአልባት ፍርድ መስጠቱን ያላወቀና በተሰጠው ፍርድም ጥቅሙ የሚነካ ሰው ፍርዱ ቢፈጸም በጥቅሙ ላይ ሊከተል የሚችለውን ጉዳት ለመከላከል ነው፡፡ አንድ ሰው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ ለማቅረብ የሚችለውም በጉዳዩ የሚያገባውና በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 41 መሠረት የክርክሩ ተሳታፊ ሊሆን የሚችል ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ነው፡፡ አመልካችም በተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር ስለሚመለከተኝ የክርክሩ ተሳታፊ መሆን ይገባኛል ብለው በፍ/ብ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 41 መሠረት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ነበር፡፡ አቤቱታቸውም ተቀባይነት አግኝቶ ፍ/ቤቱ ክርክሩን አግዶ የጣልቃገብነት ማመልከቻው ለተከራካሪ ወገኖች እንዲደርስና መልስ እንዲሰጡበት ከአንድም ሁለት ጊዜ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የጣልቃገብነት አቤቱታ ለተከራካሪ ወገኖች ሳይደርስ የቀረው በአመልካቹ ጉድለት በሆነ ጊዜ ደግሞ ጣልቃገቡ ነገሩን ሆነ ብሎ እንደተወው ተቆጥሮ መብቱ እንደሚሰረዝበት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 41(4) ላይ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም አመልካች በተጠሪዎች መካከል ክርክር እየተደረገ መሆኑን ተገንዝበው በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ጠይቀው ተፈቅዶላቸው የጣልቃገብነት አቤቱታውን ለተከራካሪ ወገኖች ማድረስ ሲገባቸው ይህን ሳይፈጽሙ ቀርተው መብታቸው ከተሰረዘ በኋላ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ ማቅረባቸው ክርክር መኖሩን በሚገባ በተገነዘቡበት ሁኔታ ስለሆነ በዚህ መልኩ የሚቀርብ አቤቱታ ከሕጉ ዓላማ ጋር ስለማይጣጣም የሥር ፍ/ቤቶች አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ እንጂ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 56832 በ20/8/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 67878 በ21/11/2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ 43731

ታህሳስ 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ሲ.ጂ.ሲ.ኦቨርሲስ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ሊሚትድ - እሌኒ አስራት ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ሰለሞን እንዳለ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በሌለሁበት ክርክሩ እንዲሰማ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቶ ወደክርክሩ እንድገባ ይፈቀድልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከሣሽ የነበረ ሲሆን፣ መልስ እንዲሰጥ በተጠራበት ቀነቀጠሮ ባለመቅረቡ ክርክሩ እሱ በሌለበት እንዲሰማ ታዟል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ትዕዛዙ እንዲነሳለት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.72 መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ እንዲፈቀድለት ጠይቆአል፡፡ ፍ/ቤቱም ጥያቄውን ከተመለከተ በኋላ፣ አቤቱታው ትዕዛዙ በተሰጠ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑና የአንድ ወር ጊዜው ያለፈው በበቂ ምክንያት ለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ ትዕዛዙ ሊነሳ አይችልም በማለት ብይን ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ትዕዛዙን አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች የካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክርም አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13262 ጥቅምት 7 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ብይን እንደተመለከተው አመልካች ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቶለት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ባመለከተበት ጊዜ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ አልተሰጠም ነበር፡፡ ከመዝገቡ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች ተከሣሽ የነበረ ሲሆን፣ በቀረበበት ክስ በጽሑፍ መልስ ሰጥቶ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለቃል ክርክር በተቀጠረበት ዕለትም የአመልካቹ ሠራተኛ የሆነ ቀርቦ የነበረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ግን ክርክር ለማቅረብ የሚያስችል የውክልና ሥልጣን የለህም በማለት ክርክሩ አመልካቹ በሌለበት እንዲታይ አዞአል፡፡ ከዚህ በኋላም ነው አመልካች ክርክሩ በሌለበት ይሰማል የሚለው ትዕዛዝ ተነስቶለት ወደክርክሩ እንዲገባ የጠየቀው፡፡ ፍ/ቤቱ በዚህ መልክ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ያደረገው ጥያቄው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.78(1) መሠረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አልቀረበም፡፡ በህጉ ከተመለከተው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለማቅረብ ያልቻለበት በቂ ምክንያት ያለው ለመሆኑም አላስረዳም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረት የሚመራው የፍትሐብሔር ክስ በቀረበ ጊዜ ክርክሩን ለመስማት ፍ/ቤቱ በያዘው ቀነቀጠሮ ተከራካሪ ወገኖች ይቀርባሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 69(1) ከተቀመጠው ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ወይም አንዳቸው ሳይቀርቡ ቢቀሩ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የሥነ-ሥርዓት እርምጃዎች በሚመለከት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.69 እስከ 78 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች በዝርዝር ተቀምጦአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ክርክሩ እንዲሰማ ቀነ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ሳይቀርብ የቀረው አመልካች (ተከሣሽ የነበረው) ነው፡፡ በዚህ ቀነ ቀጠሮ የአመልካች ወኪል ነኝ በማለት የቀረበው ሠራተኛ የተሟላ የውክልና ሥልጣን የለውም በሚል አመልካች

እንዳልቀረበ ተቆጥሮ ክርክሩ አመልካች በሌለበት እንዲታይ የመታዘዙን አግባብነት ወደኋላ የምንመለከተው ይሆናል፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን እምነት በመያዙና ክርክሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 70(ሀ) መሠረት አመልካች በሌለበት እንዲሰማ ትዕዛዝ በመስጠቱ የተነሣ አመልካች ለጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ያቀረበው አቤቱታ የሚስተናገደው በምን አግባብ ነው? የሚለውን ነጥብ በቅድሚያ እንመለከታለን፡፡

በመጀመሪያው ቀነቀጠሮ ባለመቅረቡ ምክንያት ክርክሩ በሌለበት እንዲሰማ ትዕዛዝ የተሰጠበት ተከሣሽ በሚቀጥለው ቀነቀጠሮ ቀርቦ በቀዳሚው ቀነቀጠሮ ለመቅረብ ያልቻለው በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን ያስረዳ እንደሆነና ፍ/ቤቱም ምክንያቱን በቂ አድርጎ የተቀበለው እንደሆነ በቀረበበት ቀን መከላከያውን አቅርቦ እንዲከራከር እንደሚፈቅድለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 72 ተደንግጎአል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተቀመጡት ዋነኞቹ ነጥቦች አቤቱታው የሚቀርበው በሚቀጥለው ቀጠሮ ማለትም ጉዳዩ በውሳኔ ከመቋጨቱ በፊት መሆኑን እና በቀዳሚው ቀነ ቀጠሮ ላለመቅረብ በቂ ሆኖ የሚገመት ምክንያት (እክል) መኖር ናቸው፡፡ ከዚህ ውጪ ድንጋጌው አቤቱታው የሚቀርብበትን ግልጽ የሆነ የጊዜ ገደብ አላስቀመጠም፡፡ በዚህ ይዘቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 78(1) ከተደነገገው የሚለይ ነው፡፡ የኋለኛው "ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠውን ውሳኔ ስለማንሳት" የሚል ርእስ ያለው ሲሆን፣ የመጀመሪያው ግን "በሚቀጥለው ቀነቀጠሮ ስለመቅረብ" በሚል የተደነገገ ነው፡፡ ከዚህም በሁለቱ ድንጋጌዎች መካከል ያለውን ልዩነት ጉዳዩን በያዘው ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት እና ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በሚል ሊለይ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 72 እና 78 መካከል ያለው ልዩነት ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ የቀረ ነገር ግን በሚቀጥለው ቀነ ቀጠሮ የቀረበው ተከሣሽ ጥያቄው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 78(1) አኳያ የሚታይበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቁ. 78(1)"ን" መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ያየው በአግባቡ አይደለም፡፡

በመቀጠል ያየነው አመልካች በአንድ ወር ውስጥ ቀርቦ ያላመለከተበትን ምክንያት አላስረዳም የሚለውን የፍ/ቤቱ ትችት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደገለጽነው አመልካች አቤቱታውን ለማቅረብ የቀናትም ይሁን የወራት ገደብ አልተቀመጠለትም፡፡ በመሆኑም እንዲያስረዳ የሚጠበቀው ክርክሩ ሊሰማ በተያዘው ቀነ ቀጠሮ ያልቀረበበትን ምክንያት ነው፡፡ ለክሱ መልስ በተሰጠበት ጊዜ በኋላ በቃል የመከራከር የተሟላ ውክልና የለህም የተባለው ሠራተኛው ከመቅረቡም በላይ፤ መልሱን እራሱ ፈርሞ እንዳቀረበው በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ጉዳዩን ለመስማት (በቃል) ቀጠሮ በተያዘበት ዕለትም ይኸው ለመከራከር ይችላል ተብሎ ከአመልካች ውክልና የተሰጠው ሠራተኛ የቀረበ በመሆኑ ቢያንስ በኋላ ትዕዛዙ እንዲነሳለት ላቀረበው አቤቱታ አወሳሰን እንደበቂ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድለት ይገባ ነበር፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካች ያቀረበው በጽሑፍ የተዘጋጀው መልስ ከመዝገቡ የተያያዘ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ከዚህ በመነሳት ወደፊት ያለውን ክርክሩ መሰማት ሲገባው ወደ ውሳኔ ማምራቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስናጠቃልለው ፍ/ቤቱ ክርክሩን የመራው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 72 የተቀመጠውን ድንጋጌ በአግባቡ ሳይጠቀም በመሆኑ አፈጻጸሙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13262 ጥቅምት 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 72956 የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ወደ ክርክሩ እንዲገባ በማድረግ ከገባበት ቀን ጀምሮ ወደፊት ያለውን ክርክሩን ከሰማ በኋላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 39581

ጥር 25 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አቶ ውብሸት ካሳዬ - ጠበቃ ኃይሉ ገ/ሥላሴ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ማዕድን ሃብት ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ግርማ አለሙ ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው ከፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ከሳሽ ነበሩ፡፡ የክርክሩም አመጣጥ የሚከተለው ነው፡፡ ተጠሪ ያለአግባብ ከስራ አሰናብቶኛል በሚል ክፍያ እንዲከፈላቸውና ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ክስ አቅርበው ተጠሪ አመልካች የአሰሪ ወገን ሳይሆኑ የሰራተኛ ወገን ናቸው በሚል መቃወሚያ በማቀረቡ ፍ/ቤት ተጠሪ የአሰሪ ወይም የሰራተኛ ወገን ስለመሆናቸው በስራ ክርክር ችሎት አስወስነው ሲቀርቡ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብታቸውን ጠብቆ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካችም በዚሁ መሰረት በስራ ክርክር ችሎት የአሰሪ ወገን መሆናቸውን አስወስነው መዝገቡን እንዲንቀሳቀስላቸው ሲያመለከቱ መዝገቡ በመጥፋቱ የቀድሞ ክስና የተጠሪ መልስ ተያይዞ ክሱ በአዲስ መዝገብ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ፍ/ቤቱም የአመልካች አቤቱታ ከነአባሪው ለተጠሪ ደርሶ ተጠሪ አስተያየት እንዲያቀርብ አዟል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች በተከታታይ ቀጠሮዎች ባለመቅረባቸው ፍ/ቤቱ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 መሰረት ዘግቷል፡፡ አመልካችም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 71(2)"ን" መሰረት አድርገው መዝገቡ እንዲከፈትላቸው ሲያመለክቱ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 የተዘጋ መዝገብ አመልካች በጠቀሱት የሥነ-ሥርዓት ህግ መሰረት ሊከፈት አይችልም በማለት ጥያቄውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት አጥቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካችም በቅሬታቸው በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ለተጠሪ ደርሶ መልስ እና የመልስ መልስ የተቀባበልን ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መወሰን ሲገባው መዝገቡን መዝጋቱ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበትን ትዕዛዝ ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል፡፡

ከፍ ሲል የተገለፀው የግራ ቀኙ ክርክርና የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሲሆን በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት የሚያስፈልገው ጭብጥ የስር ፍ/ቤት መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 መሠረት መዝጋቱ እንዲሁም አመልካች መዝገቡ እንዲከፈት ሲጠይቁ ጥይቄአቸው ውድቅ መደረጉ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች ክስ አቅርበው ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ ተቀባብለው ጨርሰዋል፡፡ ተጠሪ ቀድሞ የቀረበው ክስ፣ መልስ፣ የመልስ መልስ እንደሁም ሌሎች ማስረጃዎች ደርሶት አስተያየት እንዲሰጥ የታዘዘው የቀድመውን ተከሳሽ ተክቶ በክሱ ውስጥ በመግባቱ ብቻ ነው፡፡ ፍ/ቤቱም መዝገቡን በዘጋበት እለት ለመዝገቡ ቀጠሮ ተሰጥቶ የነበረው አመልካች አቤቱታቸውን ከነአባሪዎቹ ለተጠሪ አድርሰው ተጠሪ የሚያቀርበውን አስተያየት ለመቀበል እንጂ ክስ ለመስማት አልነበረም፡፡ አመልካች በቀጠሮው እለት ባለመቅረባቸውም ፍ/ቤቱ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 መሰረት መዝገቡን ዘግቷል ይህ የሥነ-ሥርዓቱ ድንጋጌ የሚገኘው ክርክርን ስለማቋረጥ በሚናገረው ሥነ-ሥርዓት ህጉ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ የተጠቀሰው ድንጋጌም ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር ተቋርጦ በሚቀርብበት ጊዜ ፍ/ቤቱ ስለሚወስደው እርምጃ የሚናገር ሲሆን የድንጋጌው ይዘትም፤ ***"ክሱ በሚቀጥልበት በማንኛውም ጊዜ ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር መቋረጡን ወይም ጨርሶ መቅረቱን ፍ/ቤቱ በቂ በሆነ ማስረጃ የተገነዘበ እንደሆነ ስለ ኪሳራና ስለ ካሳ ተገቢ የሆነውን ትእዛዝ በመስጠት ክሱን ይዘጋዋል፡፡ ምክንያቱንም ዘርዝሮ በመዝገቡ ላይ ያሰፍራል፡፡"*** በሚል ይነበባል፡፡ ድንጋጌው ከሚገኝበት ክፍልና ከድንጋጌው

ዝርዝር ይዘት በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው ፍ/ቤቱ ክሱን የሚዘጋው የክሱ ምክንያት ሲቋረጥ ወይም ጨርሶ ሲቀር ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ፍ/ቤቱ መዝገቡን የዘጋው የክሱ ምክንያት በመቋረጡ ሳይሆን አመልካች በተከታታይ ቀጠሮ በመቅረታቸው በመሆኑ ፍ/ቤቱ የተጠቀሰውን የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ መሰረት አድርጎ መዝገቡን መዝጋቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች መዝገቡ እንዲከፈትላቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 71(2)"ን" መሰረት በማድረግ ለፍ/ቤቱ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ በዚህ ሥነ-ሥርዓት መሰረት መዝገብ እንደከፈት ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2) ክስ በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ከሳሽና ተከሳሽ በመቅረታቸው ወይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 70(መ) መሰረት ከሳሽ ለተከሳሽ መጥሪያ ሳያደርስ በመቅረቱ መዝገቡ ተዘግቶ ከነበረና ከሳሹ የቀረው ወይም ለተከሳሽ መጥሪያ ያልደረሰው በቂ ሆኖ በሚገመት ምክንያት መሆኑን በማስረዳት ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአመልካች የክስ መዝገብ የተዘጋው ክስ በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ በመቅረታቸው ስላልሆነ መዝገቡ እንዲከፈት ይህን ሥነ-ሥርዓት መጥቀሳቸው ተገቢ አልነበረም፡፡ ነገር ግን አንድ ተከራካሪ ወገን ፍሬ ነገሩን ከገለፀ ትክክለኛውን የህግ ድንጋጌ አለመጥቀሱ መብቱን ሊያስቀርበት አይችልም፡፡ ይልቁንም ፍ/ቤቶች ለቀረበላቸው ጥያቄ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ተገቢ ነው ያሉትን ውሳኔ የመስጠት ሃላፊነት አለባቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ፍ/ቤቱ አመልካች ባለመቅረባቸው መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 መሰረት መዝጋቱ ሥነ-ሥርዓታዊ ባለመሆኑ ምንም እንኳን አመልካች የጠቀሱት አንቀፅ ለጉዳዩ አግባብነት ባይኖረውም ተገቢውን ድንጋጌ በመጠቀም ስህተቱን ሊያርም ይገባው ነበር፡፡ በክርክሩ ውስጥ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ የሆነው ጉዳይ ሲያጋጥም ማንኛውም ተከራካሪ ወገን በሚያቀርበው ጥያቄ ፍ/ቤቱ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ የሆነው ነገር በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሰረዝ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 209 ስልጣን ይሰጠዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አመልካች ለስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ማመልከቻ ከተጠሪ ጋር መልስና የመልስ መልስ ተሰጥቶበት ለውሳኔ ያደረ ጉዳይ መሆኑን በመግለፅ መዝገቡ እንዲከፈትላቸው በ21/4/2000 ዓ.ም ስለመጠየቃቸው የስር ፍ/ቤት መዝገብ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ የአመልካች ክስ የክስ ምክንያቱ ሳይቋረጥ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 መዝጋቱ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ በመሆኑ አመልካች ባቀረቡት ጥያቄ መነሻነት ይህንን ስህተቱን በማረም መዝገቡን መክፈት ሲገባው አመልካች የጠቀሱትን የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ አግባብ አለመሆኑን ብቻ መሰረት በማድረግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 መሰረት የተዘጋ መዝገብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 71(2) መሰረት አይከፈትም በሚል ምክንያት ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎቹን በአግባብ ያላገናዘበና መሰረታዊ የሥነ-ሥርዓት ህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 92294 ጥር 13 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 64486 ሚያዚያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ክስ ያቀረቡበት መዝገብ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ 45984

ጥር 26 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ፕሮፌሰር ረዳ ተ/ኃይማኖት - አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** አቶ ልመንህ ተፈራ - ቀረቡ

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ያለአግባብ ከስራ ስላሰናበቷቸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ ተጠሪን በትምህርት ቤታቸው እንዲያስተምሩላቸው ቀጥረዋቸው ተጠሪ የተቀጠሩበትን ስራ በመተው ከሌላ ት/ቤት ተማሪዎች ግቢ ውስጥ በማምጣት የሚያስተምሩ በመሆኑ ማስጠንቀቂያም ቢሰጣቸው ከድርጊታቸው ያልተቆጠቡ በመሆኑና ተጠሪው በአዳማ ልዩ ዞን ትምህርት ቢሮ ፅ/ቤት ተቀጥረው ደሞዝ የሚከፈላቸው በመሆኑ ከስራ የተሰናበቱት በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ይግባኝ ቀርቦ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ወረዳ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ እንዲወስን በመመሪያ ተመልሶለታል፡፡ በዚህ መሰረት ወረዳ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ማዘዙንና ሁለቱም ወገኖች ግን ማስረጃ አለማቅረባቸውን መዝግቦ አመልካች ተጠሪ ፈፀሙ የተባሉትን ጥፋት በማስረጃ ያላስረዱ በመሆኑና በስራ ስንብት ደብዳቤው ላይ ለስንብቱ በምክንያትነት የተጠቀሰው የተማሪዎች ቁጥር መቀነስ እንጂ ተጠሪ ፈፅመዋል የተባለው ጥፋት ባለመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት ተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት ውሳኔውን አፅንተዋል፡፡ የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ ተጠሪ በስራቸው ላይ ጥፋት የፈፀሙ ለመሆኑ የቀረቡትን ማስረጃዎች ፍ/ቤቱ ሳይሰማ ውሳኔ መስጠቱን የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች ማስረጃዎች ሳይሰሙ ውሳኔ የመስጠቱን ህጋዊነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፅሁፍ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በመልሳቸው በአመልካች የተነገረውን ጥፋቶች ያልፈፀሙ መሆኑን እና አመልካች በማስረጃ ዝርዝራቸው ላይ የቆጠሩዋቸውን ምስክሮች ማቅረብ ሲገባቸው ምስክሮቻቸውን በመለወጣቸው ፍ/ቤቱ ማስረጃቸውን ሳይሰማ ማለፉ አግባብ ነው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህ መዝገብ መልስ ማግኘት ያለበት ጭብጥ አመልካች ያቀረቧቸው ምስክሮች ሳይሰሙ ውሳኔ መሰጠቱ በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ ከክርክሩ ሂደት እንደተረዳነው ጉዳዩ ቀደም ሲል የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ወደስር ፍ/ቤት የመለሰው ተጠሪ ሙሉ ቀን ሥራ መስራት አለመስራታቸው፣ ሥራ ትተው ሌላ ቦታ ሲሰሩ የቆዩ መሆን አለመሆኑን፣ ከሌላ ት/ቤት ተማሪዎች እያመጡ ያስጠኑ የነበረ መሆን አለመሆኑን፣ በአመልካች ላይ ጉዳት የሚያደርስ ድርጊት መፈፀም አለመፈፀማቸውና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው የነበረ መሆን አለመሆኑን በማስረጃ እንዲረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ ማስረጃ እንዲቀርቡ ታዘው አመልካች ምስክሮቻቸውን በሚያሰሙበት ቀነ ቀጠሮ በ29/05/2001 ዓ.ም በተፃፈ በቃለ መሃላ በተደገፈ አቤቱታ ሁለት ምስክሮቻቸው መኖሪያ አድራሻቸውን በመቀየራቸውና አንደኛዋ በመውለዳቸው ምክንያት ሊያቀርቧቸው ባለመቻላቸው ተለዋጭ ምስክሮች እንዲሰሙላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የአመልካችን ጥያቄ በሁለት ምክንያቶች ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ አንደኛው የምስክሮቹ ስም በመዝገቡ ውስጥ የሌለና ተጠሪ መልስ ያልሰጡባቸው መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አመልካች ምስክሮቻቸውን ሊለውጡ የሚችሉት መልሳቸውን

በማሻሻል እንጂ እንዲሁ አይደለም የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገባቸው ምክንያቶች በህጉ ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑ መመርመር ይገባል፡፡

የስር ፍ/ቤት ከሰጣቸው ከምክንያቶች ውስጥ አንደኛው ተለውጠው የቀረቡት ምስክሮችን አስመልክቶ ተጠሪ መልስ አልሰጠባቸውም የሚል ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካች እንደክሳቸው አቀራረብ የሚያስረዱላቸው ምስክሮች ዘርዝረው ማቅረባቸው አልተካደም፡፡ ነገር ግን እነዚህ ምስክሮች ሊሰሙ በተያዘው ቀን ቀጠሮ በተለያየ ምክንያት መቅረብ ባለመቻላቸው ተለዋጭ ምስክሮች እንዲሰሙ አመልካች በቃለ-መሃላ በተደገፈ አቤቱታ ጠይቀዋል፡፡ በማስረጃ ዝርዝር ላይ የተቆጠሩ ምስክሮችን ማግኘት ባልተቻለ ጊዜ ምስክሮች የሚቀየሩበት የተለየ ሥነ-ሥርዓት በፍትሐ-ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ውስጥ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ጊዜ በማስረጃ ዝርዝር ላይ የተጠቀሱ ምስክሮች በምንም ሁኔታ መለወጥ የማይቻል ስለመሆኑ የሥነ-ሥርዓት ህጉ ያስቀመጠው ገደብ የለም፡፡ በመሆኑም እንደየነገሩ ሁኔታ ፍ/ቤቶች ተለዋጭ ምስክሮች እንዲሰሙ ለመፍቀድ የሚከለክላቸው ህግ የለም፡፡ በተያዘው ጉዳይም ፍ/ቤቱ ተለዋጭ ምስክሮቹ በመከላከያ ማስረጃ ላይ ስላልተጠቀሱ አልሰማም ከማለት በቀር ምስክሮቹን እንዳይሰሙ የሚከለክል ህግ መኖሩን አልጠቀሰም፡፡ በእርግጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223(2) እና 234 መሰረት የክሱ ማመልከቻና ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው የቀረቡት የፅሁፍና ሌሎች ማስረጃዎች እንዲሁም የምስክሮች ዝርዝርና ማንኛውም ለፍ/ቤቱ የደረሱትን መግለጫዎች ትክክለኛ ግልባጮች ለተከሳሹ ሊደርሰው እንደሚገባ ሁሉ ተከሳሹም የሚያቀርበው መልስና የመከላከያ ማስረጃ፣ የምስክሮች ዝርዝር ለከሳሽ ሊደርሰው እና ሊከራከርበት ይገባል፡፡ ፍ/ቤቱም እንዲሰሙ በተጠየቁት አዲስ ምስክሮች ላይ ተጠሪው አስተያየት የመስጠት እድል ሊሰጠው ይገባል የሚል ከሆነ ይህንኑ እድል ከመስጠት ባለፈ አመልካች ማስረጃቸውን እንዳያሰሙ የሚከለክልበት ህጋዊ ምክንያት አልነበረም፡፡ ተጠሪም ቢሆን ምስክሮቹ ሲመሰክሩ መስቀለኛ ጥያቄ በመጠየቅ ዕውነቱ እንዲወጣ የማድረግ መብት ስላላቸው ምስክሮቹ እንዳይሰሙ የሚከለከሉበት የህግ ምክንያት ይህ ችሎት አላገኘም፡፡

ሌላው ፍ/ቤቱ የሰጠው ምክንያት አመልካች ምስክሮቹን የሚለውጡ ከሆነ መልሳቸውን ማሻሻል ነበረባቸው የሚል ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 91 መሰረት አቤቱታ ሊሻሻል የሚችለው የአቤቱታው መሻሻል ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራውና ለትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ የድንጋጌው ይዘት ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ክስ ወይም መከላከያ የሚሻሻለው ጉዳዩን በይበልጥ የሚያብራራው ወይም የቀረበውን ክርክር በተሻለ ዓይነት ገልፆ የሚያስረዳው ወይም ሁኔታውን በዝርዝር አገላለፅ የሚያመለክት መሆኑ ሲታመን ብቻ እንጂ ምስክሮች ለመለወጥ ሲባል ብቻ የመልስ አቤቱታ እንዲሻሻል የተጠቀሰው የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ አይፈቅድም፡፡ በመሆኑም ስር ፍ/ቤት አመልካች ምስክሮቻቸውን ለመለወጥ የመከላከያ መልሳቸውን ሊያሻሽሉ ይገባ ነበር በማለት አመልካች ምስክሮቻቸውን እንዳያሰሙ መከልከሉ የሥነ-ሥርዓት ህጉን ያልተከተለ እና በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 20(4) ስር የተመለከተውን የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብና ምስክሮቻቸውን የማሰማት መብታቸውን ያጣበበ ውሳኔ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 20744 የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 07592 ሚያዚያ 19 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 79715 ግንቦት 12 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት አመልካች በተለዋጭ ያቀረቡዋቸውን ምስክሮች ሰምቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 47252

የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ፑሽፓላት ጆሴፍ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሠይፈ ጎሣዬ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 66502 ግንቦት 10 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረን ጋብቻ በፍች ከፈረሰ በኂላ በተስማማነው ሰኔ 27 ቀን 1998 ፍርድ ቤት ባፀደቀው ስምምነት መሠረት አመልካች ከጥቅምት 5 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ትምህርት ቤቱን ለብቻቸው በማስተዳደር ያገኙት ገቢ ተጣርቶ እንድካፈል ይወሰንልኝ በማለት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርበው ከጥቅምት 1 ቀን 1998 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም በተጣራው ሪፖርት ላይ ባለሙያዎች ቀርበው መጣራት ያለበት ነጥብ እንዳለ በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጌታቸው ዋቅጅራና ጓደኞቹ የሂሳብ ባለሙያዎች ከጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ሰኔ 1 ቀን 1998 ዓ.ም ያለውን ሂሳብ ኦዲት በማድረግ ስቴፕስ ትምህርት ቤት በዚህ ጊዜ ውስጥ ብር 663,863 (ስድስት መቶ ስልሣ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሥልሳ ሶስት ብር) የተጣራ ትርፍ ያገኘ በመሆኑ ግማሹን ማለትም ብር 331,931.50(ሶስት መቶ ሰላሣ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሣ አንድ ብር ከሀምሳ ሣንቲም) ግራ ቀኙ ሰኔ 21 ቀን 1998 ዓ.ም ባደረጉትና ፍርድ ቤት ባፀደቀው መሠረት አመልካች ለተጠሪ እንድታካፍል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች ጋብቻችን በፍች ከፈረሰ በኂላ የጋራ ንብረታችንን ለመካፈል ባደረግነው ስምምነት ለዋይዜድ ህንፃ እና ለወ/ሮ ራሔል ህንፃ የኪራይ ቤቶችና ሻንበል ግቢ የተከፈለ የኪራይ ገንዘብ የጋራ እዳ እንደሆነ ተስማምተናል፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር ፍርድ ቤት የኦዲት ሪፖርቱን ከውሉ ጋር ሣያገናዝብና ሌሎች ማየት የሚገባውን ማስረጃ ሣያገናዝብ እኔን እዳ ተሸካሚ እንድሆን በማድረግ ተጠሪ ትርፍ እንዲካፈል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በኦዲት ተረጋግጦ በቀረበው መሠረት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ሚዛናዊ ነው፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም የሚል ይዘት ያለው ሁለት ገፅ መልስ አቅርቧል፡፡

በሥርና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ አመልካች ጋር የነበረን ጋብቻ በፍች ከፈረሰ በኂላ ስለ ጋራ ንብረት ክፍፍል ባደረግነውና በፍርድ ቤት ቀርቦ ሰኔ 27 ቀን 1998 ዓ.ም ባደረግነው ስምምነት አንቀፅ 5 መሠረት አመልካች ስቴፕስ ትምህርት ቤት በግሏ ከጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ሰኔ 1 ቀን 1998 ዓ.ም ያስተዳደረች በመሆኑ በዚህ ጊዜ የተገኘውን የተጣራ ትርፍ በሂሳብ ባለሙያ ተጣርቶ እንድታካፍለኝ በማለት ክስ ያቀረበ መሆኑን አመልካች በበኩሏ በዚህ ጊዜ የተገኘውን ትርፍ ተጠሪ ለመጠየቅ

የሚችለው በመጀመሪያ በስምምነታችን አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 በጋራ እዳነት የተዘረዘሩት ዕዳዎች ተከፍለው የሚቀር ሲኖር ነው የሚል ክርክር ያቀረቡ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪና አመልካች ያደረጉት ክርክርና የሚለያዩበት ነጥብ ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ከሆነ የሥር ፍርድ ቤት ተገቢውን ጭብጥ በመመሥረት ጉዳዩን ወስኗል ወይስ አልወሰነም? የሚለው ነጥብ በመጀመሪያ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የአንድ ክርክር ጭብጥ የሚመሠረተው ከሳሽ ያቀረቡትን ክስና ማስረጃ በተከሳሽ ያቀረበውን የመከላከያ መልስና ማስረጃ እንዲሁም ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ሥነ- ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሠረት የቃል ምርመራ ሲያደርግ ያገኘውን ፍሬ ጉዳይ መሠረት በማድረግ መሆን እንዳለበት በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ይደነግጋል፡፡ ተጠሪ አመልካች ስቴፐስ ትምህርት ቤት ለብቻቸው ማስተዳደር ከጀመሩበት ከጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ያለው ትርፍ ተጣርቶ እንዲሰጠው ሲጠይቅ ተጠሪ በበኩሏ ከዚህ በፊትም ሆነ በኋላ (ለዋይ ዜድ ህንፃ የወ/ሮ ራሔል የኪራይ ቤቶችና የሻንበል ግቢ) የኪራይ ዕዳዎች የጋራ እዳ በመሆኑ በስምምነታችን መሠረት ያለብን ዕዳ ተከፍሎ ቀሪ ካለ ብቻ ነው ለመጠየቅ የሚችለው የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርባለች፡፡ ፍርድ ቤት በኦዲት ተጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ የሰጠው ስቴፐስ ትምህርት ቤት ከጥቅምት 1 ቀን 1998 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ያገኘውን የተጣራ ትርፍ(ገቢ) ነው፡፡ ለውሣኔውም መሠረት ያደረገው በእነዚህ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ያለው ወጭና ገቢ ተሰልቶ የተገኘውን የኦዲት ውጤት ነው፡፡ አመልካች ያቀረበችው ክርክር በኦዲት ዘመኑ የማይሸፈኑ ለህንፃ ኪራይ የተከፈለ ዕዳዎች የተጠሪ የጋራ እዳ መሆናቸው በስምምነታችን አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሠረት የጋራ እዳችን መጀመሪያ ተሰልቶ ነው መወሰን ያለበት በማለት ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በማስረጃነት ያቀረበውንና አመልካችና ተጠሪ ስለ ጋራ ንብረት ክፍያ ያደረጉትን ስምምነት አመልካች ያቀረበችውንና በኦዲት ዘመኑ የማይሸፈን ክፍያ እና የኦዲት ዘመኑ ያወጣውን ወጭና የተገኘውን ገቢ መነሻ በማድረግ ከኦዲት ከተሸፈነው ጥቅምት 1 ቀን 1998 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ካለው ጊዜ ውጭ ያለው የአመልካችና የጋራ ዕዳ ተከፍሎ የሚቀር ተጠሪ ሊካፈለው የሚጠይቀው ገንዘብ ያለ መሆን አለመሆኑን በስፋት አይቶ ለመወሰን የሚያስችል ጭብጥ አልመሠረተም፡፡ ይኸም የሥር ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ድንጋጌዎች መሠረት መመሥረት የሚገባውን ጭብጥ ሣይመሰርት ከጥቅምት 1 ቀን 1998 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ስቴፐስ ትምህርት ቤት ያገኘውን የተጣራ ገቢ ብቻ መነሻ በማድረግ ውሣኔ የሰጠና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ተጠሪ አመልካች የስቴፐስ ት/ቤት የተጣራ ገቢ እንድታካፍለው የጠየቀው አመልካችና ተጠሪ ስለ ጋራ ንብረት ክፍፍል ተስማምተው ሰኔ 27 ቀን 1998 ፍርድ ቤት ቀርቦ የፀደቀውን ውል አንቀፅ 5 መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች በበኩሏ ተጠሪ የተጣራ ትርፍ ልካፈል የሚል ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው በመጀመሪያ በውሉ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 የተገለፁት ዕዳዎች ከተከፈሉ በኋላ ነው የሚልና ውልን መሠረት ያደረገ ክርክር አቅርባለች፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ለውሣኔው ብቸኛ ማስረጃ አድርጎ የወሰደው የኦዲት ሪፖርት አመልካችና ተጠሪ ሰኔ 27 ቀን 1998 ዓ.ም በፍርድ ቤት ያፀደቁትን ውል የተሸፈኑ ጉዳዮች በሙሉ በማጣራት ያቀረበ አይደለም፡፡ የኦዲት ሪፖርቱ ከጥቅምት 1 ቀን 1998 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ያለውን የስቴፐስ ት/ቤት ወጭና ገቢ የሚመለከት ነው፡፡ የኦዲት ሪፖርቱ የአመልካችና የተጠሪን ክርክር ለመፍታት እንደ አንድ ጠቃሚ ግብዓት ማስረጃ ከሚያገለግል በስተቀር አመልካች ከጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም በፊት የከፈሉትን የህንፃ ኪራይም ሆነ ከሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም በኋላ የከፈሉትን የህንፃ ኪራይ በተሟላ ሁኔታ የማይሸፍን ማስረጃ ነው፡፡ የኦዲት ሪፖርቱ ከኦዲት ዘመን ውጭ 416,680 (አራት መቶ አስራ ስድስት ሺ ስድስት መቶ ሰማንያ ብር) አመልካች ወጭ ያወጡ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ይህም የሚያሳየን አመልካችና ተጠሪ በውል የገቡትን ግዴታ በሚሸፍንና የተሟላ የሂሳብ ማጣራት ያልተደረገ መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችና ተጠሪ ተስማምተውበት በፍርድ ቤት የፀደቀውን ውል በአንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገውን በማለፍ የውሉን አንቀፅ 5 ብቻ ውጤታማ ለማድረግ የሚችል ሂሳብ ተጣርቶ እንዲቀርብ የሰጡት ትዕዛዝና ከጥቅምት 1 ቀን 1998 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ስቴፐስ ትምህርት ቤት ያገኘውን የተጣራ ገቢ ብቻ መነሻ በማድረግ አመልካች ለተጠሪ ብር 331,931.50 (ሶስት መቶ ሰላሣ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሣ አንድ ብር ከሀምሳ ሣንቲም) እንድትከፍል የተሰጠው ውሣኔ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር አንቀፅ 1734 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ሰኔ 27 ቀን 1998 ዓ.ም በፍርድ ቤት የፀደቀውን ውል አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ከጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም በፊትና ከሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም በኂላ ለዋይዜድ ህንፃ፣ የወ/ሮ ራሔል ኪራይ ቤቶችና የሻንበል ግቢ የከፈሉትን የኪራይ ገንዘብ በማስረጃ በማጣራትና በውሉ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የጋራ ዕዳ መሆኑን በመገንዘብ ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት መልሰንለታል ግልባጩ ይላክለት፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ.ም በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 43821

ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**:- ወ/ሮ ትርሐስ ፍስሐዬ - ወኪል ዚርኡ ፍስሃዬ - ቀረበ

**ተጠሪ**:- ወ/ሮ ዘነበች በሪሁን - ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 መሰረት ዳኝነት እንዲታይ የቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ዋናው ክርክር ሲጀመር ከሣሽ የነበረችው ተጠሪ ስትሆን፣ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጥያቄ ያቀረበችው የአመልካች ባል ከነበረው ሟች ወልዳቸዋለሁ የምትላቸውን ሁለት ልጆች ልጅነት እንዲረጋገጥላት ነው፡፡ በዚህ ጥያቄ ክስ መነሻነት ክርክር ከተካሄደ በኋላም ተጠሪ እንደ ጥያቄዋ ተወስኖላታል፡፡ ውሳኔው እስከ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ደርሶ እንደፀና በመዝገቡ ተመልክቷል፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ነው አመልካች ዳኝነት ይታይልኝ በማለት አቤቱታ ያቀረበችው፡፡ ተጠሪ ያስወሰነችው ሐሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ ፍ/ቤቱን በማሳሳት በመሆኑ ጉዳዩ በኋላ በተገኘው እውነተኛው ማስረጃ ተረጋግጦ ሊወሰን ይገባል የሚል ምክንያት በመስጠት ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ለሰማው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታዋን አቅርባለች፡፡ ፍ/ቤቱም የተጠሪንም መልስ ካየ በኋላ፣ጉዳዩ እስከ ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ደርሶ የተወሰነ በመሆኑ በዚህ ደረጃ ሊስተናገድ አይችልም የሚል ምክንያት በመስጠት አቤቱታውን ውድቅ አድርጐአል፡፡ ጉዳዩን በመጨረሻ ያየው የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም በዚህ ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብሎአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ዳኝነት እንዲታይላት ያቀረበችው ጥያቄ በበቂ ምክንያት የተደገፈ እንደሆነ፣የሥር ፍ/ቤቶች ሕጉ ሳይከለከል ጥያቄውን ውድቅ በማድረጋቸው በሕጉ አተረጓጐም ረገድ

መሰረታዊ የሆነ ስህተት መፈጸማቸውን፣ባቀረበችው ጥያቄ መሰረት ጉዳዩ እንደገና ቢታይ ተጠሪ ቀደም ሲል ያሰጠችው ውሳኔ እንደሚሻር በመግለጽ አቤቱታዋን አቅርባለች፡፡ ተጠሪም ለአቤቱታው በሰጠችው መልስ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 "ን" መሰረት በማድረግ ዳኝነት እንዲታይ መጠየቅ የሚቻለው ቀደም ሲል በተሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ከመባሉ በፊት ነው፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 16624 በሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ከተባለ በኋላ ድንጋጌው ተፈፃሚ እንደማይሆን በመግለጽ የሕግ ትርጉም ሰጥቶአል፡፡ አመልካች በኋላ አገኘሁ ያለችው ማስረጃም እኔን በወንጀል ሊያስቀጣ የማይችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የሚሉት ነጥቦች በመከራከሪያነት አቅርባ አቤቱታው ውድቅ እንዲሆን ጠይቃለች፡፡

እኛም ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡ አመልካች ያቀረበቸው አቤቱታ በሰበር ችሎት እንዲታይ ተወስኖ ክርክሩ እንዲሰማ የተደረገው ቀደም ሲል ለተሰጠው ውሣኔ መሰረት የሆነው ማስረጃ በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው እየተባለ ውሣኔው ይግባኝ ተብሎበታል በሚል ብቻ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 ሊስተናገድ አይችልም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ ይግባኝ ከተባለ በኋላ ዳኝነት በድጋሚ ሊታይና አቤቱታው ሊስተናገድ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጥያቄ በአግባቡ መመልስ የሚቻለው የድንጋጌው መንፈስ ምን እንደሆነ ትርጉም በመስጠት አንድ መደምደሚያ ላይ መድረስ ሲቻል ነው፡፡ ከዚህ ችሎት የሚጠበቀውም በዚህ ረገድ ተገቢ ነው የሚለውን የሕግ ትርጉም በመስጠት በተደጋጋሚ እየተነሱ ላሉት ተመሣሣይ ጥያቄዎች እልባት መስጠት በመሆኑ ጉዳዩን እንደሚከተለው በዝርዝር ተመልክተናል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 የተቀመጠው ድንጋጌ አዲስ ክስ የሚስተናገድበት ሥርአት አይደለም፡፡ በቀረበው ክስ መሰረት ክርክር ተካሂዶ ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ ጥያቄ የሚቀርብበት ሥርአት የተዘረጋበት ነው፡፡ ጥያቄውን የሚያቀርበው ወገን ለጉዳዩ አዲስ ሳይሆን፣ ከመጀመሪያውም ተከራካሪ የነበረ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት መቃወሚያ ከሚያቀርበው ወገን በተለየ ሁኔታ የሚስተናገድ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ጥያቄው የሚቀርበው ይግባኙን ለሚሰማው ፍ/ቤት ሳይሆን፣ውሣኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት በመሆኑ ይህም የድንጋጌውን የተለየ ባህርይ ሊያሳይ እንደሚችል አድርጐ ለማየት የሚያስችል ነው፡፡ እንግዲህ ከእነዚህ ሁኔታዎች መገንዘብ የሚቻለው ሕጉ በቁጥር 6 የተቀመጠውን ሥርአት በመዘርጋት ሊያሳካው የፈለገው አንድ ግብ እንዳለ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳትም የድንጋጌው ዓላማ ምንድን ነው የሚለውን ነጥብ ማየቱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው አግባብነት የሚኖረው መቼ ነው? ይግባኝ ከመባሉ በፊት ወይንስ ይግባኝ ከተባለ በኋላም ጭምር የሚለውን ለጊዜው አቆይተን ዓላማው ምንድን ነው? የሚለውን እንመለከታለን፡፡፡ በዚህ ረገድ ጠቃሚ ሆነው የምናገኛቸው በንኡስ ቁ. (1)(ሀ) እና (ለ) የተቀመጡት ድንጋጌዎች ስለሆኑ ለአጠቃላይ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ሙሉ ይዘታቸውን እንመልከት፡-

ሀ. የመጨረሻው ፍርድ ወይም ውሳኔ ወይም ትእዛዝ የተሰጠው በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበውን ሰነድ ወይም ሐሰተኛ የምስክርነት ቃልን ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሰረት በማድረግ ሲሆንና አቤት ባዩም ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊውን ትጋት አድርጐ ለማወቅ ያለመቻሉን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ በሚል የተደነገገ ሲሆን(ለ) ደግሞ

ለ. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ተግባሮች መፈጸማቸው ቢገለጽ ኖሮ ለፍርዱ መለወጥ ወይም መሻሻል በቂ ምክንያት ሊሆኑ ይችሉ እንደነበር ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ፤

ነው ይላል፡፡ ሁለቱን ድንጋጌዎች አጣምረን ስንመለከት ሕጉ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ያኔ(ውሣኔው ሲሰጥ) ሊደረስባቸው ባልተቻለ ሐሰተኛ እና ወንጀል ጠቀስ የሆኑ ተግባሮችን ወይም ድርጊቶችን መሰረት አድርጐ የተሰጠ ሆኖ ከተገኘ ሕገ ወጥ ነው፡፡ በመሆኑም በሕገ ወጥነቱ ሊቀጥል ወይም ተፈፃሚነት ሊያገኝ አይገባም እሚል መነሻ ይዞ ነው የተደነገገው ወደሚለው ድምዳሜ ነው የምንደርሰው፡፡ ይህ ደግሞ በክርክር ሂደት እውነትን አንጥሮ ማውጣት ዋነኛው የፍርድ አመራር ስርአቱ ግዴታ ነው የሚል መሰረት ያለው እንደሆነ መገመቱ አይከብድም፡፡

ለተያዘው ክርክር መነሻ የሆነው ቁ. 6 በተካተተበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከሚከናወኑት አበይት ተግባራት አንዱ (ዋነኛው) ክርክሩን በተገቢው መንገድ መምራት እና በመጨረሻም እውነትን አንጥሮ በማውጣት ትክክለኛ ፍርድ መስጠት ነው፡፡ በዚህ አግባብ የሚሰጠው ፍርድ ፍትሐዊ እንደሚሆን የሚታመን ሲሆን፣እውነትን ለማውጣት ወሳኝ ሚና የሚጫወተው ደግሞ ማስረጃ ነው፡፡ የክርክር ጭብጦች የሚነጥሩት በማስረጃ በመሆኑ ሕጉ በዚህ ረገድ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ማስረጃ የሚቀርብበትን ብቻ ሳይሆን፣የሚገኝበት ሁኔታም(መንገድም) የሕግ መሰረት ያለው ወይም ሕጋዊ ሊሆን ይገባል፡፡ የክርክሩ አመራርም እንደዚሁ ሕጋዊ እና ወደ እውነት የሚያደርስ መንገድ ሊከተል ይገባል ብሎ ሕጉ ያምናል፡፡

የሥነ ሥርአት ሕጉ ማስረጃ የሚቀርብበትን አግባብ እና የጊዜ ወሰን በመርህ ደረጃ በአንድ በኩል ሲያስቀምጥ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከመርሁ ወጣ ባለ ልዩ ሁኔታ ማስረጃ ሊቀርብ የሚችልበትን አግባብ ደንግጐ እናገኛለን፡፡ በመርህ ደረጃ ማስረጃ ማቅረብ ያለበት በማስረጃው እጠቀማለሁ የሚለው ተከራካሪ ወገን እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 223 እና 234 የተደነገገ ሲሆን፣ፍ/ቤቱ እውነት ላይ ለመድረስ የሚቻለው በዚህ ብቻ አይደለም የሚል እምነት ከያዘ ግን በራሱ ተነሳሽነት ማስረጃ አስቀርቦ እንደሚሰማ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 264 እና በሌሎችም ድንጋጌዎች ተመልክቶአል፡፡ ማስረጃ የሚቀርብበት የጊዜ ወሰንም እንደዚሁ በቁ. 137 የተቀመጠ ድንጋጌ ቢኖርም፣ይህ ጊዜ ካለፈም በኋላ ማስረጃ ማቅረብ የሚቻልበት ሁኔታ እንዳለ በቁ. 256 ተደንግጓል፡፡ ክሱን በሰማው ፍ/ቤት ያልቀረበን ማስረጃ በይግባኝ ደረጃ የሚሰማበት

አግባብ እንዳለም በቁ. 345 ከተቀመጠው ድንጋጌ እንመለከታለን፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች እንግዲህ መገንዘብ የምንችለው አንዱና ዋነኛው ቁም ነገር ማስረጃ እውነትን አንጥሮ በማውጣት ረገድ ካለው ወሳኝ ሚና በመነሳት ከዋናው የማስረጃ አቀራረብ መርህ ወጣ ባለ ሁኔታም የሚቀርብበትና የሚሰማበት አግባብ በሥነ ሥርአት ሕጉ ተቀባይነት ማግኘቱን ነው፡፡ ዓላማውም የሚሰጠው ውሣኔ እውነት ላይ ብቻ የተመሰረተ እንዲሆን ለማስቻል ነው፡፡

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ለዳኝነት እንደገና ይታይልኝ ጥያቄው መሰረት የሆነው ምክንያት የቀድሞው ውሣኔ የተሰጠው በሐሰት ተዘጋጅቶ በቀረበው ማስረጃ ላይ በመመስረት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ውሣኔው እውነትን አንጥሮ ያወጣ አይደለም ወይም እውነት የሆነውን ነገር ሐሰተኛ (ሕገወጥ) በሆነ ማስረጃ ተድበስብሶ ቀርቶአል የሚል መነሻ ያለው ነው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች የያዘችው እምነት ዳኝነቱ እንደገና ከታየ የቀድሞው ውሣኔ በእርግጥ ይሻራል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ጥያቄ የሚቀርብበት አግባብ አክትሞአል ወይም በሩ ዝግ ነው የሚል መከራከሪያ ነው ያላት፡፡ ይህ በተጠሪ የተነሳው የመከራከሪያ ነጥብ ዳኝነቱ እንደገና ታይቶ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ሊገኝ የሚችለውን ውጤት ግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም፡፡ የአመልካች ክርክር ግን እውነት የሚገኝበትን አግባብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም የሕጉ ትርጉም ይህ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ከመድረሳችን በፊት በድንጋጌው ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉት ሁለት አማራጮችን አንድ በአንድ ማየት ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የመጀመሪያው አማራጭ ለቀድሞው ውሣኔ መሰረት የሆነው ማስረጃ በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ መሆኑን በክርክሩ ሂደት አረጋግጦ ውሳኔውን መለወጥ ወይም ማሻሻል የሚቻልበት ሁኔታ እንደሚኖር ቢገመትም፣ድንጋጌው ስለማይፈቅድ(ይግባኝ ስለተባለ) አቤቱታውን ከወዲሁ ውድቅ ማድረግ የሚለው ነው፡፡ የመጀመሪያውን አማራጭ ስንመለከት ክርክሩ በሕግ አግባብ ብቻ ተመርቶ እና በሕግ መሰረት ብቻ የተገኘውን ማስረጃ መሰረት አድርጐ የተሰጠው ውሣኔ እውነትን አንጥሮ ያወጣል የሚለው የሕጉን ዓላማ ስለሚያሳካ ውጤቱ መልካም ነው የሚል ግንዛቤ እንይዛለን፡፡ ሁለተኛው አማራጭ በሁለት መልክ ሊታይ ይችላል፡፡ አንዱ በእርግጥም ሕጉ የሚከለክል ከሆነ ሕግን መጣስ በራሱ ክልክል በመሆኑ ሕጉን አክብሮ መቀበሉ ተገቢ ነው ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ ነጥብ እንመለከታለን፡፡

ቀደም ሲል እንዳየነው አከራካሪ የሆነው በንኡስ ቁ. /1/ የተመለከተው ድንጋጌ በተለይም “…..ይግባኝ ሊቀርብበት በሚችል ፍርድ ወይም ውሣኔ ወይም ትእዛዝ ላይ ቅሬታውን አቅርቦ ከማሰማቱ በፊት” የሚለው ሐረግ ነው፡፡ “ቅሬታውን አቅርቦ ከማሰማቱ በፊት” የሚለውን ሐረግ ለብቻው ወስደን ቃል በቃል ብንተረጉመው በእርግጥም ዳኝነት እንዲታይ የሚቀርበው ጥያቄ አቤቱታ አቅራቢው በተሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ አቅርቦ ከማሰማቱ በፊት ነው ወደሚለው ድምዳሜ ያደርሳል ልንል እንችላለን፡፡ ይሁንና ድንጋጌው በአጠቃላይ ሊተረጐም የሚገባው በውስጡ ከያዛቸው ሌሎች ሐረጐች እና

በንኡስ ቁ. /1/ሀ/ እና /ለ/ ከተቀመጡት ሁኔታዎች እንዲሁም ከጠቅላላው የሥነ-ሥርአት ሕጉ ዓላማ ጋር ተገናዝቦ በመሆኑ በትርጉም የምንደርስበት መደምደሚያ አንድዋን ሐረግ ብቻ ወስደን ቃል በቃል በመተርጐም ከምንደርስበት የሰፋ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

ሌላው ድንጋጌው ሲተረጐም ግምት ውስጥ መግባት ያለበት በድጋሚ ዳኝነት ይታይ ጥያቄ ከይግባኝ በፊት ይቅረብ የተባለበትን ምክንያት ነው፡፡ ውሣኔው በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይታረማል (በድጋሚ ይታያል) በሚል እሳቤ ይግባኝ ተብሎበት በክርክር ሂደት ባለበት ጊዜ ውሣኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት የዳኝነት እንደገና ይታይ ጥያቄ ማቅረብ አንድን ጉዳዩ በተመሳሳይ ጊዜ በበታች እና በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንዲሰማ በማድረግ ወጪን፣ጊዜን እና ጉልበትን ያለአግባብ ከማባከን እንደዚሁም ክርክሩ እንዲወሳሰብ ከማድረግ አልፎ የሚያስገኘው ጠቀሜታ የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጉዳዩን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 345 እንዲሁም ቁ. 182 አንፃር በማየትም ተገቢውን ማስተካከያ ያደርጋል የሚለውንም እንደ አንድ ታሳቢ ሁኔታ አድርጐ መውሰድ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሕጉ በዚህ ደረጃ የተሻለውንና ምክንያታዊ የሆነውን አካሄድ ቢመርጥም፤ ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ ከተወሰነ በኋላ ለውሣኔው መሰረት የሆነው በቁ. 6/1/ሀ/ ከተመለከቱት ተግባሮች (ወይም ሁሉም) ነው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል ብሎ አላሰበም ማለት ግን የሚቻል አይደለም፡፡ ቀደም ሲል በዝርዝር ለማሳየት እንደሞከርነው ከሁሉም በላይ መታየት ያለበት ሕጉ ዓላማ አድርጐ የተነሳው እውነት ላይ መድረስ ነው የሚለው ነው፡፡ እውነት ላይ መድረስ መቻል በፍትሕ አሰጣጥ ረገድ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ውጤታማ ሥራ ነው፡፡ ሕግ ሲተረጐም ተጨባጭ ውጤት ሊሰጥ በሚችል አኳኋን መሆን እንዳለበት ከአጠቃላይ የሕግ አተረጓጐም መርህ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 ተጨባጭ ውጤት ሊሰጥ በሚችል አኳኋን ሊተገበር የሚችለው ውሣኔው ሐሰተኛ እና ወንጀል ጠቀስ የሆኑ ተገባሮችን መሰረት በማድረግ የተሰጠ ነው የሚል አቤቱታ እስከቀረበበት እና በቂና አሣማኝ መሆኑን ፍ/ቤቱ እስካመነበት ድረስ ይግባኝ ይባልበትም አይባልበትም ያለልዩነት ሥራ ላይ እንዲውል በሚያስችል ሁኔታ ሲተረጐም ነው የሚል እምነት መያዙ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ በመቀጠል የተመለከትነው በሰበር መ/ቁ. 16624 በተሰጠው ውሣኔ ለድንጋጌው የተሰጠው ትርጉም አሁን በያዝነው መዝገብ ከተሰጠው ትርጉም ጋር እንዴት ይጣጣማል? የሚለውን ነው፡፡ ድንጋጌውን እንደገና በስፋት ማየት ያስፈለገው የዳኝነት በድጋሚ ይታይ ጥያቄ በተደጋጋሚ እየቀረበ በመሆኑና የሚነሳው ክርክርም እውነት ሳይወጣ እየቀረ ነው የሚል ስለሆነ፤ከዚህ በላይ ደግሞ ጥያቄው የሚነሳው ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ ውሣኔ ካገኘ በኋላ እንደሆነ ግንዛቤ ስለተወሰደ ነው፡፡ በእርግጥም ጉዳዩ አሳሳቢ ሆኖ በመገኘቱ ከዚህ በፊት የተሰጠው ትርጉም እንደገና አይቶ በተደጋጋሚ

እየተነሱ ላሉት ጥያቄዎች ምላሽ ሊሰጥ የሚችል እልባት ማድረግ አማራጭ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህ የፌዴራል ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2/1/ በተደነገገው መሰረት ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረውን ትርጉም ለውጠን በዚህ በያዝነው መዝገብ የተሰጠው ትርጉም ገዥ ይሆናል ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተጠሪ በሰበር መ/ቁ. 16624 የተሰጠውን ውሣኔ መሰረት በማድረግ ያቀረበችውን ክርክር አልተቀበልንም፡፡ በመጨረሻም አመልካች ያቀረበችውን የዳኝነት ጥያቄ በመቀበል ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01789 ኀዳር 5 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን፣የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 70413 ታህሣሥ 14 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. በሰበር መዝገብ ቁጥር 16624 ተሰጥቶ የነበረው ትርጉም ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ተለውጧል፡፡
3. አመልካች ያቀረበችው የዳኝነት ይታይልኝ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 መሰረት ሊስተናገድ የሚገባው ነው ብለናል፡፡
4. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበችውን አቤቱታ በመቀበል እና ተጠሪ የምትሰጠውን መልስ አይቶ ጉዳዩን በመመርመር ተገቢ ነው የሚለውን ውሣኔ እንዲሰጥ ይመለስለት ብለናል፡፡
5. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 42871

ጥር 12 ቀን 2002 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሠ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የቀድሞ ወረዳ 07 ቀበሌ 32 አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ደረጀ ይታገሱ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ጆሮ ዋቅጅራ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ የሚቀርብ አቤቱታ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በተጠሪ በተመሰረተበት የቤት ይለቀቅልኝ ክርክር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መጋቢት 18 ቀን 1994 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ቁጥራቸው 508 እና 509 የሆኑት ቤቶች ለአሁኑ ተጠሪ እንዲመለሱላቸው ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ጥር 13 ቀን 1995 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 መሠረት ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይለት ምክንያቱን ገልፆ ፍርዱን በድጋሚ እንዲያየውና እንዲለውጠው የመጀመሪያውን ፍርድ ለሰጠው ለዚሁ ፍርድ ቤት አቤቱታውን አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በመጀመሪያው ፍርድ ቤት ይግባኝ ከተባለ በኋላ ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ አቤቱታ ሊቀርብ እንደማይችል፣ እንዲሁም አቤቱታው በቀረበበት ጉዳይ የመጀመሪያው ፍርድ የተሰጠበት አግባብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 ሥር የተመለከቱትን ነገሮች ባሉበት ስለመሆኑ በድጋሚ የቀረበው አቤቱታ እንደሚያሳይ ገልፆ ዳኝነቱ በድጋሚ ሊታይ አይገባም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ ይህ ፍርድ ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 መሠረት አቤቱታ ቀርቦ ከታየ በኋላ ብይኑ ይግባኝ የሌለው በመሆኑ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የማታይበት አግባብ የለም በማለት ዋናውን ጉዳይ ሳይመለከተው መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች አቤቱታውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ በይግባኝ ሰሚው ችሎት የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በሚል ውድቅ ሆኖበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም. በፃፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ቤቶች በፍርድ ባለመብት የሆኑበት የባለቤትነት ደብተር ሐሰተኛ መሆኑ ተረጋግጦ በሚመለከተው የአስተዳደር አካል የተሠረዘ ስለመሆኑ በመግለጽ ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ለሥር ፍርድ ቤት አቤቱታ ቀርቦለት ሳይቀበለው መቅረቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ስለሆነ ታርሞ ለረጅም ጊዜያት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የነበሩት ቤቶች ላይ ተጠሪ መብት የላቸውም ተብሎ ሊወሰን ይገባል ሲሉ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮም አመልካች ዳኝነት እንደገና እንዲታይለት ያቀረበው ጥያቄ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ስለተጠየቀበትና የቀረበው አዲስ ማስረጃ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ስለመገኘቱ አልተረጋገጠም በሚሉት ምክንያቶች ውድቅ የመደረጉ ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 ድንጋጌን በትክክል በመተርጎም መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ጥቅምት 19 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ሦስት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩላቸው ታህሣሥ 27 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ሦስት ገጽ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን አድርገዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚፈልገው አቢይ ነጥብ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው የመጨረሻ ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላልን የሚለው ነጥብ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይለት አቤቱታ አቅርቦ የሥር ፍርድ ቤት ዳግመኛ ዳኝነት እንዲታይ የቀረበውን አቤቱታ ከመቀበሉ በፊት የአቤቱታው ግልባጭ ለተጠሪ በመላክ አቤቱታው ሊሰማ የማይችልበትን መከራከሪያ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቶ ክርክሩን መስማቱን፣ ክርክሩን ከሰማ በኋላ የአመልካችን አቤቱታ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የተባለበት በመሆኑ ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ የተጠየቀበት ሰነድም በሐሰተኛ መንገድ የተገኘ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ዳኝነቱን በድጋሚ ሊታይ አይገባውም ሲል ብይን መስጠቱን፣ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቅርቦም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በሚል ምክንያት የአመልካችን ዋናውን ክርክር ሳይመለከተው መዝገቡን ከዘጋው ብኋላ አመልካች በዚህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሣኔ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ተቀባይነት ማጣቱን ነው፡፡ ከዚህ በግልጽ መረዳት የሚቻለው ለዚህ ችሎት ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መሠረት የሆነው ውሣኔ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ሊባል የሚችልበት አይደለም የተባለበትን ውሣኔ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ይህ ችሎት ማየትና ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለበት በዚህ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በፀናው፣ በጉዳዩ ላይ የሰጠው ብይን ይግባኝ የለበትም ተብሎ በተሰጠው ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟልን የሚለውን መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም የሚለውን የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሣኔም ሆነ በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪን ክርክር ተገቢ አይደለም በማለት የሚከራከሩት የሥር ፍርድ ቤት ወደ ዋናው ጉዳይ ገብቶ ሲያከራክር ቆይቷል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሥር ፍ/ቤት የውሣኔ ግልባጭ የሚያሳየው ፍርድ ቤቱ በአመልካች በኩል ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ አቤቱታ ሲቀርብ ተጠሪን በመጥራት ማከራከሩ አቤቱታው ሊሰማ የማይችልበትን መከራከሪያ እንዲያቀርቡ እድል ለመስጠት ስለመሆኑ ሲሆን ተጠሪ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት ዳኝነቱ በድጋሚ ሊታይ የማይችልበትን ምክንያት አቅርበው ተከራክረዋል፡፡ ይህም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6/3/ ሥር የተመለከተው የሥነ-ሥርዓት አካሄድ ሲሆን ተገቢነት ያለውም ነው፡፡ የሥር ፍርድ በዚህ መሠረት አቤቱታውን ካስተናገደ በኋላ ግን አመልካች ዳኝነቱ እንደገና እንዲታይ ያቀረበውን አቤቱታና ተጠሪ ዳኝነቱ በድጋሚ ሊታይ አይገባውም በማለት ያቀረቡትን መከራከሪያ መሠረት በማድረግ ዳኝነቱ በድጋሚ ሊታይ አይገባውም በማለት ብይን ሰጥቶታል፡፡ ይህ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ በግልጽ የሚያሳየው ፍርድ ቤት ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ ይገባዋል በማለት ብይን ከሰጠ በኋላ በዋናው ጉዳይ ግራ ቀኙን አከራክሮ የቀድሞውን ውሣኔ ያፀናው ስለመሆኑ አይደለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች ነገረ ፈጅ የሥር ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ገብቶ ከአከራከረ በኋላ ውሣኔ ሠጥቶ እያለ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በሚል የከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሆነ የሰበር ችሎት ውሣኔ መስጠታቸው ያላግባብ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የክርክሩን ሂደት ባግባቡ ያገናዘበ ባለመሆኑ የምንቀበለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ቀጠሎ መታየት ያለበት ጉዳዩ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም የመባሉን አግባብነት ነው፡፡ አንድ ጉዳይ በድጋሚ ዳኝነት ሲቀርብ ዳኝነቱ በድጋሚ ሊታይ አይገባውም ወይም ይገባል ሲል ፍርድ ቤቱ ውሣኔ ሲሰጥ ይግባኝ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6/3/ እና /4/ ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ በግልጽ ያሳያሉ፡፡ በዚህም መሠረት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ሆነ የሰበር ችሎቱ ውሣኔ ሲታይ ሕጋዊ ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ አቤቱታ ሊያቀርቡ ይገባ የነበረው ሥርዓቱን ጠብቀው ለሰበር ሰሚ ችሎት እንጂ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አይደለም፡፡ የዚህ ችሎት ኃላፊነትና ተግባር ደግሞ በበታች ፍርድ ቤት በተሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሲፈፀም ማረም ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ- መንግሥት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 እና 22 ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም የአዲስ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የሰበር ችሎቱ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት የተሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6/3/ እና /4/ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህ ምክንያት የአመልካች ነገረ ፈጅ በዋናው ጉዳይ ላይ ያቀረቡትን ክርክር ለመመርመር የሚያስችል ሥነ-ሥርዓት ባለመኖሩ አልፈነዋል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04111 ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጥቶ በከተማው ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 07548 ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም. መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የሥር ፍርድ ቤት ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ አይገባውም በማለት በሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ የለውም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 37214

የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

መስፍን እቁበዮናስ

ኂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አቶ ተስፋዬ አለሙ - ጠ/ሃይሉ ንጋቱ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ሐጂ ይማም ሙዘይን - ጠ/ገብረእግዚአብሔር ተስፋዬ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሳኒያ ሱልጣን

3. አቶ አብዱልናስር አማን

(2 እና 3) በሌሉበት

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በክሳቸው ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪ ባልና ሚስት ሆነው የሳሙና ፋብሪካ ድርጅት በብር 450,000 እንደሸጡላቸው፣ አመልካች ብር 250,000 ከፍለው ድርጅቱን ተረክተው ብር 150,000 አውጥተው ግንባታ መስራታቸውን፣ሁለተኛ ተጠሪ ሆነ ብለው ስንቅ የሌለው ቼክ ለአንደኛ ተጠሪ ሰጥተው ሲፈረድባቸው ለአመልካች የሸጡት ቤት ለውሳኔው ማስፈጸሚያ መያዙን፣በዚህም ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት መቃወሚያ አቅርበው መቃወሚያው ውድቅ በመደረጉ ክሱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሰረት ማቅረባቸውን ገልፀው ንብረቱ የተከበረው ያለአግባብ ነው እንዲባልና በድርጅቱ ላይ አመልካች መብት ያላቸው መሆኑ ተረጋግጦ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ በመ/ቁ. 137/93 በተሰጠው ውሳኔ እና በመ/ቁ. 11684 በተሰጠው ትእዛዝ የመልካች ጥያቄ ውድቅ የተደረገ በመሆኑ ድጋሚ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎችም አመልካች ውል እንዲፈፀምላቸው ክስ አቅርበው እያለ በድጋሚ ይህን ክስ ማቅረባቸው ተገቢ እንዳልሆነና አንደኛ ተጠሪ ከሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪ ጋር ተጣምረው መከሰሳቸው ከሥነ-ሥረአት ውጪ ነው በሚል ክሱን ተቃውመዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አንደኛ ተጠሪ የሚከሰሱበት ምክንያት የለም በማለት ከክሱ ሲያሰናብታቸው ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ደግሞ አመልካች ውል ይፈፀም በሚል ክስ ስላቀረቡ በተመሳሳይ ጉዳይ ዳግመኛ ክስ ሊቀርብ አይገባም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጐታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ አንደኛ ተጠሪ ልከሰስ አይገባም ብለው ሳይቃወሙ ከክሱ ውጪ መደረጋቸው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421ን ያላገናዘበ ነው፣በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 የቀረበ መቃወሚያ ውድቅ ከተደረገ በሁለቱ ወገኖች መሃከል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 "ን" መሰረት መብት ለማረጋገጥ ክስ ሊቀርብ እንማይችል ተደርጐ የተሰጠው ብይን የተሳሳተ ነው፣እንዲሁም ውል እንዲፈፀም የቀረበው ክስ በከፍተኛ ፍ/ቤት የተያዘው ክርክር ውጤት እዲጠብቅ ተብሎ የቆመ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ተሰጥቶበት እደገና ክስ እንደቀረበ ተደርጐ የተሰጠው ብይን አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶች የአመልካች ክስ ካሁን በፊት የታየ ነው በሚል ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው አግባብ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህ መሰረት አንደኛ ተጠሪ ቀርበው መልስ የሰጡ ሲሆን ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ግን መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሰረት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው አመልካች ከሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ላይ ገዛሁት የሚሉት የሳሙና ፋብሪካ በሁለተኛ ተጠሪና በአንደኛ ተጠሪ መሐከል በነበረው ክርክር በአፈፃፀም በመያዙ አመልካች ለፍርዱ አፈፃፀም በተያዘው ንብረት ላይ

የቀዳሚነት መብት ያላቸው መሆኑን በመግለጽ መቃወሚያ አቅርበው ውድቅ ተደርጕባቸዋል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 421 ስር የቀዳሚነት መብት አለኝ በሚል መቃወሚያ አቅርቦ መቃወሚያው ውድቅ የተደረገበት ሰው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ንብረት ላይ ክስ ለማቅረብ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ ስለተደረገባቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሰረት ክስ ማቅረባቸው የሕግ ድጋፍ አለው፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ እንዳሉት ሳይሆን ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን እንደተገነዘበው መዝገቡ ያሳያል፡፡ ፍ/ቤቱ የአመልካች ክስ ውድቅ ያደረገው አመልካች ቀደም ሲል ውል ይፈፀምልኝ የሚል ክስ ያቀረቡ በመሆኑ በተመሳሳይ ጉዳይ ድጋሚ ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም በማለት ነው፡፡ ይህ ችሎትም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳው ዘንድ አመልካች ውል እንዲፈፀምላቸው ክስ ያቀረቡበትን መዝገብ ቁጥር 01520 አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካች በሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ላይ ሳሙና ፋብሪካ ድርጅት መግዛታቸውንና ድርጅቱን መረከባቸውን ገልፀው በውሉ መሰረት የሸጡትን ንብረት በከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 137/93 የተሰጠውን እግድ ትእዛዝ ጨምሮ ከማናቸውም እዳና እገዳ ነፃ በማድረግ የውል ግዴታቸውን እንዲፈጽሙ፣ግዴታቸውን መፈፀም የማይችሉ ከሆነ ውሉ ፈርሶ ወደነበሩበት እንዲመለሱና መቀጫ እንዲከፍሉ እንዲወሰንባቸው ክስ መስርተዋል፡፡ ለቀረበው ክስ ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ ከተቀባበሉ በኂላ ፍ/ቤቱ ግንቦት 26 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት በአፈፃፀም ምክንያት በመያዙ አመልካች መቃወሚያ ያቀረቡ በመሆኑ ፍ/ቤቱ በመቃወሚያው ላይ የሚሰጠው ውሳኔ እስኪታወቅ መዝገቡ ለጊዜው እንዲዘጋ አድርጓል፡፡ ነገር ግን የከፍተኛው ፍ/ቤቱ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት ያቀረቡትን መቃወሚያ አይቶ ውሳኔ ከሰጠ በኂላም ቢሆን አምልካች የመ/ቁ. 01520 የሆነውን መዝገብ አላንቀሳቀሱም፡፡ አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሰረት አድርገው በመሰረቱት ክስ የጠየቁት የመብት ጥያቄ በመ/ቁ. 01520 የሚጠይቁት ጋር ልዩነት የለውም፡፡ በዚህ መዝገብ በጠየቁት መሰረት ቢወሰንላቸው በድጋሚ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሰረት ክስ ማቅረብ አያስፈልጋቸውም፡፡ በመሆኑም አመልካች በአንድ በኩል ውል እንዲፈፀምላቸው ክስ መስርተው ይህ ጉዳይ እልባት ሳያገኝ በድጋሚ በሌላ መዝገብ ተመሳሳይ ጥያቄ ማቅረባቸው አግባብ አይደለም፡፡ የቀዳሚነት መብት አለኝ በሚል መቃወሚያ አቅርቦ ጥያቄው ውድቅ የተደረገበት ሰው በድጋሚ ክስ ማቅረብ የተፈቀደለት በአፈፃፀም ችሎቱ የንብረቱ ባለመብትነት በጭብጥነት ተይዞ በመደበኛው የሙግት ስርአት አይነት የአመልካቹ ጥያቄ ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ አንፃር ተመርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ባለመሆኑ ይህንን እድል ለመስጠት ነው፡፡ አመልካቹ ይህንን መብት የሚያስከብርለት ሌላ ክስ የመሰረተ ከሆነ ግን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 421 ክስ ለማቅረብ ስለሚፈቅድ ብቻ በተመሳሳይ ጉዳይ ዳግመኛ ክስ ማቅረብ ስነ-ስርአት ህጉ አላማ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ውል ይፈጽምልኝ በሚል ክስ ያቀረቡበትን መዝገብ በማንቀሳቀስና ክርክሩን መቀጠል እየቻሉ በድጋሚ ክስ ማቅረባቸው ተገቢ ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ በመደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24926 ሚያዝያ 3 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ብይንና ፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 25423 ጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 44634

የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አቶ ታዬ ሆሳዕና - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ መሰረት ወልደየስ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ የጋራና የግል ንብረት ነው የሚሏቸውን ንብረቶች ዘርዝረው ለመካፈል ጠይቀዋል፡፡ በአቤቱታቸውም ከሌሎች ንብረቶች በተጨማሪ የመለዋወጫና የሕንፃ መሳሪያ ሱቅ ከእንቁላል ፋብሪካ ጉለሌ ከነበረበት ወጥቶ ተጠሪ በ22 ማዞሪያ በከፈቱት ሱቅ ውስጥ ስለተቀመጠ ንብረቶቹን በአይነት ለመካፈል ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የመለዋዋጫና የሕንፃ መሣሪያው ሱቅ ከፍቺ በፊት ንግዱ ተዘግቶ የንግድ ፈቃዱ መመለሱን በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ነጥብ ላይ ውሳኔ ሳይሰጥ አልፎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ይግባኝ የመለዋወጫና የሕንፃ መሣሪያ ድርጅቱን ከነሙሉ እቃው ክፍፍሉ ውስጥ እንዲገባ ጠይቀው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሳይሰጥ በማለፉ ይኸው እንዲወሰንላቸው አመልክተዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ አመልካች በስር ፍ/ቤት ድርጅት ለመካፈል አልጠየቁም፣የመለዋወጫ እቃዎችን በተመለከተ የእቃዎቹን ዝርዝር ካለማቅረባቸውም በላይ ተጠሪ እነዚህ ንብረቶች መሸጣቸውን ገልፀው የሚከራከሩ ቢሆንም አመልካች ግን እቃዎቹ ስለመኖራቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን የስር ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሳይሰጥ ማለፉ አግባብ ባይሆንም ከውጤቱ አንፃር የሚያመጣው ለውጥ የለም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን አመልካች በቅሬታቸው ላይ ንግድ ፍቃዱም ቢመለስ ንብረቶቹ በተጠሪ እጅ ስለሚገኙ መካፈል ሲገባን መታለፉ ስህተት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ የአመልካችን ቅሬታ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረጉ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡ መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት የመለዋወጫና የህንፃ መሳሪያ ለመካፈል ጠይቀዋል፡፡ ነገር ግን በስር ፍ/ቤት እንዲሁም በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክር አመልካች የሚጠይቁትን ንብረቶች ዝርዝር አለማቅረባቸውን ተረድተናል፡፡ አንድ ከሳሽ የሚጠይቀውን ነገር ለይቶ ማስቀመጥ እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 225/1/ ያመለክታል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች የሚጠይቁትን ንብረቶች ዝርዝር ለይተው ማስቀመጥ ሲገባቸው ይህ አላደረጉም፡፡ ከዚህ ሌላ ተጠሪ በክርክራቸው የመለዋወጫና የህንፃ መሳሪያ ሱቅ ሲዘጋ እቃዎቹ መሸጣቸውን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ንብረቱ አለ በማለት የሚከራከሩ በመሆኑ ስለንብረቱ መኖር የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡ በፍትሐብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም አለበት(one who alleges in the affirmative shall prove it)፡፡ ይህ መብት ወይም ግዴታ መኖሩን ካላስረዳ ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርገው ይገባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ንብረቶቹ አሉ በማለት ይከራከሩ እንጂ ስለመኖራቸው ማስረጃ እንዳላቀረቡ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪ እንዲያካፍሏቸው የሚጠይቁት የንብረት አይነቶች ዘርዝረው ያላቀረቡ ከመሆኑም በላይ ንብረቶቹ ስለመኖራቸው እንኳን ማስረጃ ስላላቀረቡ የስር ፍ/ቤቶች ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረጋቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል ለማለት አይቻልም፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 51214 ጥቅምት 6 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 60553 ጥር 25 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 45371

የካቲት 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሃይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የገነተ-ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ማህበር በኩር ሰንበቴ - ም/ሰብሣቢ ደሣለኝ ዲባባ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ማሞ ተሰማ - ቀረቡ

2. አቶ ጌታቸው ይልማ - ቀረቡ

3. ወ/ሮ ወይንሸት ሙላት - ቀረቡ

**ብ ይ ን**

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ተጠሪች ለፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በአመልካች ማሕበር ውስጥ አባል መሆናቸውን ገልፀው ማሕበሩ ያለአግባብ ለ6 ወራት ከማህበሩ ስላገዳቸው ይኸው ውሳኔ እንዲነሳላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ለቀረበው ክስ የተለያዩ መቃወሚያዎችና በአማራጭ መልስ የሰጠ ሲሆን በመልሱም አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎቹ ከማሕበሩ የታገዱት የማሕበሩን ገንዘብ ገቢ አላደርግም በማለታቸው እና ሦስተኛ ተጠሪ ደግሞ በስብሰባ ላይ ፀያፍ ንግግር በማናገራቸው በመሆኑ እገዳው ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች ያቀረባቸውን መቃወሚያዎች ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎቹ ጥፋት ለመፈፀማቸው በቂ ማስረጃ አልቀረበም በሚል እግዱ ተነስቶ ከሙሉ መብታቸው ጋር ወደ ማሕበሩ አባልነት እንዲመለሱ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን አመልካች በቅሬታው በዋናነት ተጠሪዎች የታገዱት በማሕበሩ የመጨረሻ የስልጣን አካል በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፣ተጠሪዎችም የታገዱት በጥፋታቸው በመሆኑ ውሳኔው ሊሻር ይገባል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ከማህበሩ ያለአግባብ ያገዳቸው መሆኑን ጠቀሰው ይኸው ውሳኔ እንዲነሳላቸው ነው የጠየቁት፡፡ አመልካች ደግሞ በተጠሪዎችን ከማህበሩ ማገዱን ሳይክድ እርምጃው ተገቢ ነው በማለት ነው የሚከራከረው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ በጭብጥነት ሊመለስ የሚገባው ተጠሪዎቹ ለ6 ወር ሊታገዱ ይገባል አይገባም የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ከክርክሩ ሂደት እንደተገነዘብነውም ተጠሪዎች ጥፋት አጥፍተዋል በሚል ከማህበሩ የታገዱት ከጥር 25 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ የታገዱትም ለ6 ወራት ስለመሆኑ ተጠሪዎች በክሳቸውም የጠቀሱት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በክርክር ላይ እያለ ግን ተጠሪዎቹ ከማህበሩ የታገዱበት የጊዜ ገደብ አብቅቷል፡፡ ጊዜው ካበቃ ደግሞ እገዳው አግባብ ነው አይደለም የሚለው ነጥብ መወሰኑ ውጤት የሚኖረው አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ አብቅቷልና ነው፡፡ ክሱ በሚቀጥልበት በማንኛውም ጊዜ ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር መቋረጡን ወይም ጨርሶ መቅረቱን ፍ/ቤቱ በቂ በሆነ ማስረጃ የተገነዘበው ከሆነ ክሱን ሊዘጋው እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 280 ስር ተመልክቷል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የእገዳውን ግዜ በመጠናቀቁና የክሱም ምክንያት በዚሁ ስለተቋረጠ ክርክሩ ሊቀጥል የሚገባበት የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ሊታገዱ ይገባል አይገባም የሚለውን ፍሬ ጉዳይ መወሰን ሳያስፈልግ መዝገቡን መዝጋቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር ስለተቋረጠ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 280 መሰረት ተዘግቷል፡፡

መዝገቡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 36776

መጋቢት 7 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሃይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** መብራቱ፣ ተ/ማርያም፣ ገ/ማርያም የሽርክና ማሕበር - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** አቶ መብራቱ ዓንዳይ - የቀረበ የለም

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች ማህበር በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(4) መሰረት ውድቅ በመደረጉ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ የማህበሩ ሊ/መንበር ሆነው በሚሰሩበት ወቅት በእጃቸው የገባውን የማህበሩን ቼክ ለግል መኪና መግዣ የከፈሉት በመሆኑ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ገንዘቡ ከባንክ ከተወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪም ክስ የቀረበበትን ገንዘብ አመልካች ቀደም ሲል አቅርቦ በነበረው ክስ አጠቃሎ ሊያቀርበው ሲገባ ሌላ ክስ ማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216 መሠረት ተገቢ አይደለም የሚል መቃወሚያና በፍሬ ጉዳይ ላይ ሌሎች ክርክሮች አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም የተጠሪን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ተጠሪ ገንዘቡን ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ቀደም ሲል አቅርቦት የነበረው ክስና አሁን ያቀረበው ክስ ተጠሪ የማህበሩን ገንዘብ ለግል ጥቅም አውለዋል የሚል በመሆኑ ተጠቃለው ሊቀርቡ ሲገባ ለያይቶ ማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 መሰረት ህጋዊ አይደለም በማለት የከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ክስ የቀረበበት ጉዳይ አመልካች ቀደም ሲል ካቀረበው ክስ ጋር ተጣምሮ መቅረብ የሚገባው በመሆኑ ተነጣጥሎ መቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት ተጠሪ ገንዘቡን ከወለድና ከሌሎች ወጪና ኪሳራ ጋራ እንዲከፍሉ የተሰጠውን ውሳኔ መሻሩ ተገቢ ነው በማለት ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ ሲያፀናው ዳኝነትን አስመልክቶ የተሰጠውን ውሳኔ ብቻ በማሻሻል አመልካች ብር 1,675.00(አንድ መቶ ሺህ ስድስት መቶ ሰባ አምስት ብር) ብቻ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በአቤቱታው ተጠሪ ብር 100,000(መቶ ሺህ ብር) የያዘ ቼክ ለመኪናቸው መግዣ ያዋሉት መሆኑ የተረጋገጠው የመጀመሪያው ክስ ከቀረበ በኋላ በመሆኑ አመልካች ሆነ ብሎ ቀንሶ ያስቀረው ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216(3) መሰረት ክሱ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ መልስና የመ/መልስ በሬጅስትራር ጽ/ቤት በኩል እንዲለዋወጡ የታዘዘ ቢሆን ተጠሪ መልስ ባለማቅረባቸው መልስ የመስጠት መብታቸውን አልፈን መዝገቡን መርምረናል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ አቅርቦ የነበረው ከላይ እንደተመለከተው ተጠሪ የማህበሩ ሊ/መንበር ሆነው ሲሰሩ በእጃቸው የገባውን ቼክ ለራሳቸው ለገዙት መኪና መክፈያ አውለውታልና ገንዘቡን ከነወለዱ ይመልሱ በሚል ነው፡፡ ተጠሪም በመልሳቸው አመልካች ቀደም ሲል በተመሳሳይ ጉዳይ ክስ ሲመሰርት ይህንኑ ክስ አጠቃሎ ሊከስ ሲገባ ቀንሶ ባስቀረው ገንዘብ ላይ ድጋሚ ክስ እንዳይመሰርት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 የከለክለዋል የሚል መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ በመሆኑም የአመልካች ክስ በተጠቀሰው የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ወይ የሚለው ጭብጥ ፍ/ቤቱ መርምሯል፡፡ ለዚህ ይረዳ ዘንድ ድንጋጌውን መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 በአጠቃላይ ስለ ክስ አቀራረብና አገላለፅ የሚመለከት ድንጋጌ ነው፡፡ በተለየ ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር 2 እና 3 ነው፡፡ የንዑስ ቁጥር 2 የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር አንድ ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች

በሙሉ አጠቃሎ መቅረብ እንደሚገባ የሚናገር ሲሆን ንዑስ ቁጥር 3 ደግሞ አንድ ከሳሽ ሊከስበት ሲችል ሆነ ብሎ በመቀነስ ባስቀረው ሃብት ምክንያት እንደገና ሌላ ክስ ለማቅረብ እንደማይፈቀድለት ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ክሱን ለማቅረብ ምክንያት የሆኑት ነገሮች በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ የሚጠበቅበት ሲሆን ማቅረብ ሲችል ሆነ ብሎ ቀንሶ ባስቀረው ሃብት ላይ ግን ድጋሚ ክስ ሊያቀርብ እንደማይችል ከድንጋጌዎቹ መረዳት ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የማሕበሩ ሊ/መንበር ሆነው በሰሩበት ጊዜ ያለአግባብ ያባከኑትን የማሕበሩን ገንዘብ ብር 100,000(መቶ ሺህ ብር) እንዲከፍሉ ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች እኚሁ ተጠሪ የማሕበሩ ሊ/መንበር ሆነው ሲሰሩ በስራቸው ምክንያት በእጃቸው ከገባው የማሕበሩ ገንዘብ ውስጥ ብር 689,306.49(ስድስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ሦስት መቶ ስድስት ብር ከአርባ ዘጠኝ ሣንቲም) ስላጎደሉ ይህንን ገንዘብ እንዲከፍሉ ሚያዚያ 24 ቀን 1997 ዓ.ም ክስ የመሰረተባቸው ስለመሆኑ ችሎቱ ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም በሁለቱም ክስ ጥያቄ የቀረበው ተጠሪ የማሕበሩ ሊ/መንበር ሆነው ሲሰሩ ያጎደሉትን ገንዘብ እንዲከፍሉ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በሁለተኛ ክስ የቀረበውን ጥያቄ በመጀመሪያው ክስ አጠቃሎ ሊያቀርበው የሚገባው ነበር፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው ተጠሪው ብር 100,000(መቶ ሺህ ብር) ቼክ ለመኪናቸው መግዣ የከፈሉ መሆኑ የታወቀው የኦዲት ሪፖርት ከተሰራና የመጀመሪያው ክስ ከቀረበ በኋላ በመሆኑ ሆነ ብሎ ገንዘቡን ቀንሶ ክስ መስርቷል ሊባል አይችልም የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡ በእርግጥ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(3) ድጋሚ ክስ እንዳይቀርብ የሚከለክለው ከሳሹ ሊከስ ሲችል ሆነ ብሎ በመቀነስ ባስቀረው ሃብት ላይ ነው፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ እንዲያስችለው አመልካች ቀደም ሲል ባቀረበው ክስ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ተጠሪ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያስከፈቱት መዝገብ ቁጥር 33585ን ተመልክቷል፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካች የመጀመሪያውን ክስ ያቀረበው ሚያዚያ 24 ቀን 1997 ዓ.ም መሆኑን ተረድተናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ብር 100,000(መቶ ሺህ ብር) እንዲከፍሉ ክስ የተመሠረተው የመጀመሪያው ክስ ከቀረበ 10 ቀን ሳይሞላው በ03/09/1997 ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪ ተጨማሪ ብር 100,000(መቶ ሺህ ብር) ማጉደላቸው የተረጋገጠው የመጀመሪያው ክስ እንደቀረበና እንዳውም ተጠሪ ለመጀመሪያው ክስ መልስ ሳይሰጡ በመሆኑ አመልካች ክሱን በማሻሻል በዚህ መዝገብ ክስ ያቀረበበትን ጉዳይም አጠቃሎ ሊያቀርብ ይችል ነበር፡፡ ተጠሪ ላይ የሚፈለግ ተጨማሪ ጉድለት መኖሩን የመጀመሪያው ክስ እንደቀረበ ወዲያው ያወቀው በመሆኑ በመጀመሪያው ክስ አጠቃሎ ሊያቀርበው ሲገባ ሁለተኛ ክስ ማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216(3) መሰረት የማይቻል በመሆኑ በዚህ ምክንያት ክሱ ውድቅ በመደረጉ ተፈፀመ ሊባል የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 22131 የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት የመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 44545

መጋቢት 07 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ተገኔ ጌታነህ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች**:- ክፍሉ መሓሪ - ወኪል ተ/ገብራይ መሓሪ ቀረቡ

**ተጠሪ**:- በላይ ከመላ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አቶ ቂሬንሳ ፌይሳ የግል ቤትና ይዞታቸው የሆነውን ከባለቤታቸው ከወ/ሮ ደስታ ኩምሳ ጋር በመሆን ሐምሌ 21 ቀን 1984 ዓ.ም በተፃፈ ውል ለአመልካች አባት ለአቶ መሓሪ ገ/እየሱስ ሸጠውላቸው ቤቱን ያስረከቧቸው ሲሆን፤ በእጃቸው ያለውን ቤት በስማቸው እንዲዛወር ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ሲሆን፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ በጋዜጣ ጥሪ አድርጐ ባለመቀረቡ የአቤቱታ አቅራቢውን ማስረጃ አጣርቶ ቤቱ በስማቸው እንዲዛወር ሰኔ 08 ቀን 1985 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ውሳኔውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት በመቃወም አቤቱታቸው ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤትም አቤቱታውን ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360(2) መሰረት በመሰረዝ ገዥ ሻጭን የመጠየቅ መብት አለው በማለት ወስኗል፡፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለምእራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የሚገኘው ከወልመራ ወረዳ ግዛት ክልል ወጪ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ የውል ይፈፀምልኝ ጥያቄን ከመጀመሪያውኑም ቢሆን ተቀብሎ ማስተናገዱ ያለስልጣኑ በመሆኑ ስህተት ነው የሚለውን ምክንያት በመያዝ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ከዚያም የአሁኑ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኛቸውን አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይኸው ፍርድ ቤት በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጠቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የፀናውን ውሳኔ በመሻር የወረዳውን ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ነበረው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 15 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት የወረዳው ፍርድ ቤት ስልጣን አለው ብሎ የዞኑ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ከሻረ በኋላ ጉዳዩ ወደ ዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተመልሶ እንዲታይ ሳያደርግ መቅረቱ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመረመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐአል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ ታሕሣሥ 06 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ የተፋጠነ ፍትሕ ከማግኘት መብት አኳያ ተገቢ ነው በማለት ውሳኔ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መሰረት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ ይግባኝ የቀረበለት የምእራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የተመለከተው ከሥልጣኑ ውጪ ነው በማለት ፍሬ ጉዳዩን ሳይመረምር ውሳኔውን መሻሩን፣የክልሉ ሰበር በበኩሉ የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው በሚል ምክንያት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሲሽር በፍሬ ጉዳዩ ላይ የዞኑ ፍርድ ቤት እንደገና አከራክሮ እንዲወስን ሳያደርግ መቅረቱን፣ይኸው ፍርድ ቤት ዋናውን ጉዳይ ራሱ የመረመረ ስለመሆኑ በግልጽ ሳያስቀምጥ የወረዳው ፍርድ ቤት የወረዳው የፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ የማጽናት ውጤት ያለው ውሳኔ መስጠቱን ነው፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት የወረዳው ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የሰጠውን ውሳኔ የተቀበለበትን ምክንያት አለመግለፁ ወይም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት አለማድረጉ የአመልካችን የይግባኝ መብት ያጣበበ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የራሱን ውሳኔ ካላሳለፈና የበላይ ችሎቱ የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ካልተቀበለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341፣342፣343 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ተገቢውን መወሰን አለበት፡፡ በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣንን መሰረት አድርጐ የሰጠውን ውሣኔ ከሻረ በኂላ የወረዳው ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ያለምክንያት ማጽናቱ የአመልካችን የይግባኝ መብት ያጣበበ እና ስነ-ስርአታዊ ያልሆነ ሆኖ አገኝተነዋል፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 49541 ታህሣሥ 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በዋናው ጉዳይ ላይ የምእራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደገና በማየት ተገቢውን ይወስን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት መልሰንልታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 44883

መጋቢት 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሃይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ፈንታ ምህረቱ - ወኪል አልማዝ ፈንታ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - አልቀረበም

## ፍ ር ድ

አመልካች በም/ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ሁለት ቤቶች በመያዣ አስይዘው ገንዘቡን ባለመክፈላቸው ተጠሪ ቤቶቹን ለመሸጥ ማስታወቂያ አውጥቶ ገዢ ባለመቅረቡ ቢበዛ በ3 ወር ውስጥ ሁለተኛ ጨረታ ማውጣት ሲገባው ከሶስት አመት በኋላ በማውጣቱና አንደኛው ቤት ላይ ከህግ ውጪ ለሶስተኛ ጊዜ ጨረታ አዘግይቶ በማውጣቱ ወለዱ ጨምሮ አመልካች ላይ ጉዳት ስለደረሰ ተጠሪ ብር 152,222.40(አንድ መቶ ሃምሣ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሃያሁለት ብር ከአርባ ሣንቲም) እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ ቤቶቹን ለመሸጥ የመጀመሪያው ጨረታ ሲወጣ ገዢ በመጥፋቱ ሁለተኛ ጨረታ የወጣ ሲሆን ቁጥር 276 ለሆነው ቤት ገዢ ባለመቅረቡ ባንኩ ቤቱን የተረከበው ሲሆን ቁጥር 247 ለሆነው ቤት የቀረቡት ተጫራቾች ግን ከቤቱ ግምት በጣም የወረደ ዋጋ በመጥራታቸው ጨረታው ሰዓት ከመድረሱ በፊት ስለተሰረዘ ሁለተኛ ጨረታ እንደወጣ ሊቆጠር አይችልም፣ ድጋሚ ጨረታ ለማውጣት የዘገየው ቤቱን ለመሸጥ ገበያ ሲፈላለግ ነው፣ በሶስት ወር ውስጥ ጨረታ እንድናወጣ የሚያስገድድ ህግ የለም፣ ይርጋ እስካላገደን ጨረታ ማድረግ እንችላለን፣ ወለድ ልከፍል አይገባም የሚለው ተገቢነት የሌለው ክርክር ነው፣ አመልካች ቤቱን እንዲለቁ ቢነገራቸውም እስከ መስከረም 25 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ ይጠቀሙበት ነበር በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን አመልክቷል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ ጨረታውን ሲያካሂድ አላግባብ አዘግይቷል፣ በሁለተኛ ጨረታ ቤቱ ካልተሸጠ መረከብ ነበረበት፣ ተጠሪ በጨረታው መነሻ ግምት ተረክቦ ዕዳውን የሚቃለልበት መንገድ መፈለግ ነበረበት፣ ሶስተኛ ጨረታ መደረጉ ህጉን የተከተለ አይደለም፣ ሁለተኛ ጨረታ እጅግ ቢዘገይ በሶስት ወር ውስጥ መደረግ ነበረበት፣ ጨረታው ከሶስት አመት በላይ ዘግይቶ በመደረጉ በወለድ ምክንያት ከፍ ላለው ዕዳ ኃላፊ ነው በማለት ተጠሪ ብር 112,738.80(አንድ መቶ አስራ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሰማንያ ሣንቲም) እንዲከፍል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱ ሁለቱን ወገኖች አቅርቦ ካከራከረ በኋላ ከብድሩም ሆነ ከመያዣ ውሉና እነዚህን ከሚመለከቱ ህጎች አኳያ አመልካች ብድሩን ሳይመልሱ ቢቀሩ ንብረቶቹ በአፋጣኝ እንዲሸጡ ለማስገደድ ወይም ቢዘገይ ጉዳት ካሳ ለመጠየቅ የሚያስችል መብት የላቸውም፣ አዋጁ ጨረታ የሚወጣበትን ጊዜና ቢዘገይ ወለድ መታሰብ እንዲቆም ብሎ አልደነገገም፣ ቤቱም እስከ መስከረም 25 ቀን 1997 ዓ.ም አመልካች እጅ ስለነበር መያዣው ባለመሸጡ ወይም ባንኩ ባለመረከቡ አመልካች ላይ የደረሰ ጉዳት የለም፣ ለወለዱ መጨመር ብቸኛ ምክንያት አመልካች ብድሩን አለመክፈላቸው ነው፣ ስለሆነም ባንኩ ሃላፊ የሚሆንበት የህግ አግባብ የለም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆን ችሎቱ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለውም በማለት አቤቱታው ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ በአጭሩ፤ በአዋጅ ቁጥር 97/90 ተጠሪ አመልካችን ወክሎ መያዣውን ሲሸጥ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2211 የተቀመጠውን የወኪልነት ስነ-ምግባር በመከተል ባለእዳው እዳ እንዳይበዛበት ተግቶ መስራት ይገባዋል፣ በአዋጁ አንቀፅ 6 እንደተመለከተው ሊከተል የሚገባውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 394(2) እና 428(2) ወደጎን በመተው ለዕዳው ተመጣጣኝ በሆነ ቤት ላይ ብቻ ጨረታ ማውጣት ሲገባው በሁለቱም ቤቶች ላይ ጨረታ ማውጣቱ፣ በሁለተኛ ጨረታ ካልተሸጡ ከእዳው ጋር ተመጣጣኝ የሆነውን ቤት በመረከብ እዳውን ዘግቶ አንዱን ቤት ነፃ ሊሆን ሲገባ እንዲዘገይ በማድረግ ወለዱ እንዲቆለል ማድረጉ ተረጋግጦ እያለ የጠቅላይ ፍ/ቤትና ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም የመያዣ ንብረቶቹን ከረጅም ጊዜ ቆይታ በኋላ ተጠሪ እንዲረከብ ሲደረግ የተከማቸው ወለድ መታሰቡና አመልካች ያቀረቡት የጉዳት ካሳ ጥያቄ ውድቅ መደረጉን አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አኳያ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም ህዳር 24 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ክርክሩን አቅርቧል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ የተገኘው አበዳሪ ባንኮች ለዕዳው በመያዣ የያዙትን ንብረቶች ሊሸጡ የሚገባበት የጊዜ ገደብ አለ? ወይስ የለም? አለ ከተባለ በጊዜ ገደቡ ውስጥ ንብረቶቹ ባለመሸጣቸው ኃላፊ ሊሆኑ ይገባል? አይገባም? የሚለው ነው፡፡

ለባንክ በመያዣ የተሰጡ ንብረቶችን በተመለከተ በወጣው አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀፅ 3 መሰረት የማንቀሳቀስ ንብረት በዋስትና የያዘ ባለገንዘብ ባንክ ዕዳው ካልተከፈለው ከሰላሳ ቀናት ያላነሰ ማስታወቂያ ለባለዕዳው በመስጠት ንብረቱን በሃራጅ መሸጥ ይችላል፡፡ በተጨማሪ የመጀመሪያ ጨረታ አውጥቶ ገዢ ካልተገኘ ሁለተኛ ጨረታ እንደሚወጣና በሁለተኛው ጨረታ ገዢ ከጠፋ ንብረቱን እንደሚረከብ ያመለክታል፡፡ ይህን አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 216/92 አንቀፅ 2 ባንኩ ንብረቱን የሚረከበው በመጀመሪያው ጨረታ መነሻ ዋጋ ስለመሆኑ ይናገራል፡፡ ከዚህ በቀር ንብረቱ መሸጥ ያለበት መቼ እንደሆነ ወይም ሁለተኛ ጨረታ በስንት ጊዜ ውስጥ መውጣት እንደሚገባ የጊዜ ገደብ ወስኖ አላስቀመጠም፡፡

በሌላ በኩል ባንኩ የሃራጅ ሽያጩን ሲያከናውን አግባብነት ያላቸውን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 394-449 ያሉትን ድንጋጌዎች በመከተል መሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 6 ስር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚሸጥበት ሁኔታና ጊዜ የሚመለከቱትን የሥነ-ሥርዓትቱን ድንጋጌዎች መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡ ፍርድን ለማስፈፀም የማይንቀሳቀስ ንብረት በሃራጅ ሲሸጥ በቅድሚያ ማስታወቂያ መውጣት እንዳለበት ንብረቱም ሊሸጥ የሚችለው ማስታወቂያ ከወጣ ጀምሮ ለሰላሳ ቀን ቆይቶ መሆኑን የሥነ-ሥርዓት ህጉ አንቀፅ 423(1) እና 426 ተጣምረው ሲነበቡ የሚያስገነዝቡት ጉዳይ ነው፡፡ በመጀመሪያ ጨረታ ገዢ ካልቀረበ ባለገንዘቡ ንብረቱን እንደሚረከብ ይናገራል፡፡ ከዚህ ውጪ ጨረታዎቹ የሚወጡበት የጊዜ ገደብ የሥነ-ሥርዓት ህጉ ወስኖ አላስቀመጠም፡፡ በመሆኑም ባንኩ መብቱን ለመጠየቅ የሚችልበት የጊዜ ገደብ በይርጋ ቀሪ እስከሚሆንበት ድረስ በመብቱ መጠቀም ይችላል፡፡ አበዳሪውን ባንክ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ካሳ መጠየቅ የሚቻለው ደግሞ ባንክ ሽያጩን ሲያከናውን አግባብነት ያለውን ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች ባለመከተሉ ጉዳት አድርሶ ከሆነ ነው (የአዋጁን አንቀፅ 7 ይመለከቷል)፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ባንኩ ፈፀመ ሊባል የሚችለው የሥነ-ሥርዓት ህግ ጥሰት አለ ማለት አልተቻለም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በተያዘው ጉዳይ ባንኩ ጨረታውን በሚከናውንበት ጊዜ ሁሉ አመልካች ቤቱን ይዘው ይገለገሉበት እንደነበር ያልካዱት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ በኩል አመልካች ቤቱን ይዘው እየተጠቀሙበት በሌላ በኩል ቤቱ ዘግይቶ ስለተሸጠ ጉዳት ደርሷል በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ምናልባት ባንኩ ጨረታ ሲያወጣ ቤቱን ከአመልካች ተረክቦ በራሱ ይዞታ ስር አድርጎ ቢሆን ሁኔታው የተለየ ሊሆን ይችል ነበር፡፡ አመልካች ቤቱን ይዘው በማከራየት ሆነ በሌላ መንገድ በመጠቀም እዳውን ሊያቀሉ የሚችሉበት ሁኔታ ስለሚኖር ባንኩ ቤቱን በቁጥጥሩ ስር አድርጎ እንደገና ጨረታውን ሳያወጣ ቢያዘገይ በአመልካቹ ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ባንኩ ቤቱን እስከተረከበበት ጊዜ ድረስ በአመልካች ይዞታ ስር ስለነበር ጨረታ ዘግይቶ በመውጣቱ አመልካች ላይ ጉዳት አድርሷል ሊባል አይችልም፡፡ በአጠቃላይ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤትና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካችን ካሳ ሊጠይቁ አይችሉም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ የህግ ስህተት የለውም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 12810 ጥቅምት 4 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 00557 ጥር 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 39799

መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃነ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢት/መድን ድርጅት ነ/ፈጅ ማህሌት አለሙ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ገነት ስዩም - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው የመድን ሰጪ የክርክር አድማስ አስመልክቶ የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43 ጠቅሶ የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት አለው በሚል ነው፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክርክር የተጀመረው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ጣልቃገብ ተከራካሪ ነበር፡፡ የተጠሪ የክስ ምክንያት ንብረትነቱ በሥር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ቴስትድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሆነ መኪና ሰሌዳ ቁጥር 3-13690 ኢት. በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ እየተሽከረከረ በከሳሽ መኪና ሰሌዳ ቁጥር 3-06622 አ/አ ገጭቶ ጉዳት አድርሷል በሚል ለጥገና የወጣ ወጪ እና የተቋረጠ ገቢ እንዲከፍል እንዲወሰን የሚል ሲሆን አንደኛ ተከሳሽ ቀርቦ መድን ሰጪው (አመልካች) በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43 መሠረት ጣልቃ ገብነት እንዲከራከር እንዲታዘዝ አመልክቷል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤትም አመልካች በክርክሩ እንዲገባ ካደረገ በኂላ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ተከሳሽ እና ጣ/ገብ አላፊ ናቸው ካለ በኂላ የካሣ መጠን አስመልክቶ ለመኪናው ማስጠገኛ የወጣውን ወጪ ብር 44,451(አርባ አራት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ አንድ ብር) እና የተቋረጠ ገቢ በቀን አንድ መቶ(100) ብር ሂሳብ መኪናው ተጠግኖ እስኪጠናቀቅ ጊዜ ድረስ ተሰልቶ እንዲከፈል በማለት ይህንንም ጣልቃገብ (አመልካች) እስከ ብር አንድ መቶ ሺህ (100,000) በመድን ውል በሰጠው ዋስትና መሠረት እንዲሸፍን ቀሪውን አንደኛ ተከሳሽ (ባለንብረት) እንዲከፈል ፈርዷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43(1) መሠረት በተከሳሽ ጠያቂነት ወደ ክርክሩ የገባ መሆኑን በመጥቀስ ጣልቃገብ ከተከሳሹ ጋር ያለውን ኃላፊነት ከመከራከር ውጪ ተከሳሽን ተክቶ ከከሳሽ ጋር መከራከር አይችልም በማለት በአመልካች በኩል ቀርቦ የነበረውን የሕግ እና የፍሬ ነገር ክርክር ሳይመረምር የሥር ፍ/ቤት ውሳኔን አፅንቷል፡፡

አቤቱታ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በፌዴራል መንግሥት የተመዘገበ ድርጅት በመሆኑ በአዋጅ 25/88 አንቀጽ 5(6) መሠረት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የለኝም ሲል አቤቱታውን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ለዚህ የቀረበው የሰበር አቤቱታ በዚሁ ላይ ሲሆን አመልካች የሥር ፍ/ቤቶች የሕግ እና የፍሬ ነገር ስሕተት ያላቸውን ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ተጠሪን አስቀርቦ ሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን ጉዳዩን ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት እልባት ሊያገኝ የሚገባው ጭብጥ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43(1) አተረጓጎም አግባብነት እና የአመልካች የክርክር አድማስ(ወሰን) እስከምን ድረስ ነው የሚለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሠረቱ አመልካች ወደ ክርክሩ የገባው በሥር ፍ/ቤት ተከሳሽ ከነበረው ባለንብረት ጋር ባለው የመድን ውል መሠረት እንደሆነ ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡ አንድ ተከሳሽ ከእሱ ጋር ኃላፊነት ሊወስድ ወይም ሊከፈል የሚችል ሦስተኛ ወገን ወደ ክርክሩ እንዲገባለት እንዲታዘዝ ማመልከት እንደሚችል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43(1) ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ በዚህ ጥያቄ መነሻ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገ ተከራካሪ ወገን በክርክሩ ውስጥ ሊያነሳ የሚችለው የኃላፊነት እና የኃላፊነት መጠን አስመልክቶ የክርክሩ ዘንግ ከተከሳሽ፣ ከከሳሽ ወይንስ ከሁለቱም ወገን ጋር ሊሆን ይገባል የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ በሁለት አቅጣጫ ምላሽ ሊያገኝ እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ይኸውም የጣልቃገብ ኃላፊነት ምንጭ ውል ወይንስ ሕግ የሚለው በመሠረታዊ ሕግ ድንጋጌዎች የሚወሰን መሆኑ እና በሌላ በኩልም የክርክሩ አቀራረብ እና ይዘት በሥነ-ሥርዓት ሕጉ በተደነገገው አግባብ መሆን እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የመድን ሰጪ ኃላፊነት መሠረቱ ውል መሆኑ እሙን ነው፡፡ መድን ሰጪ የሚኖረው መብት እና ግዴታ በውል የተመለከተ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በመሠረታዊ ሕጉ የተደነገጉትን አስፈላጊ እና አስገዳጅ ሁኔታዎችንም መጠበቅ ያለበት ስለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43(1) መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገው ሦስተኛ ወገን በክርክሩ ሂደት ሊያነሳ የሚችለው ክርክር ምን ድረስ ነው የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ አስመልክቶ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 23692 የሰጠውን የህግ ትርጉም መመልከት አግባብ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በተጠቃሹ መዝገብ ላይ የክርክሩ ተካፋይ ሦስተኛ ወገን የሚያቀርበው ክርክር ሁለት ፈርጅ ሊይዝ የሚችል መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይኸውም "አንደኛው ከተከሳሽ ጋር ሆኖ ድርሻ ክፍያ ወይም ስለተከሳሽ ሆኖ የካሣ ክፍያ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ተቀብሎ በተከሳሽ እግር በመተካት ተከሳሽ ለከሳሽ ኃላፊነት የማይኖርበት መሆኑን፣ ኃላፊነት አለበት እንኳ ቢባል ሊከፈል በሚገባው የካሣ መጠን ላይ ከከሳሽ ጋር ንጥጥር ማድረግ፣ መሟገት የሚችልበት ክርክር ሲሆን ሌላው እና ሁለተኛው ደግሞ ድርሻ ወይም ካሣ ለመክፈል ለተከሳሽ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ የለብኝም በማለት መከራከር የሚችልበት መንገድ ነው፡፡" ስለሆነም የድንጋጌው ይዘት ጣልቃገብ ሦስተኛ ወገን ተከሳሽ በክርክሩ ከገባ በኋላ መሟገት የሚችለው ከተከሳሽ ጋር እንጂ ከከሳሽ ጋር ለመከራከር የሚያስችለው መብት የለውም የሚለው ድምዳሜ የሕግ መሠረት የለውም የሚል ትርጉም ሰጥቷል፡፡ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁ 23692 ላይ ይህንን ትርጉም ለመስጠት መሠረት ያደረገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማ እና የሙግት አመራር ውጤታማነት እንዲሁም የድንጋጌ ቁጥር 43(1) እና 76 እንዲሁም የመሠረታዊ ሕጉ ድንጋጌዎች ውስጥ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1896፣ 1897፣ 1908 እና 1909 አፈጻጸም እንዲሁም በንግድ ሕግ ቁጥር 687,688 እና 683 ድንጋጌዎች በክርክር አመራር ረገድ የሚፈፀሙበትን ሁኔታ እና ግብ መነሻ በማድረግ መሆኑ በፍርዱ ሀተታ ተገልጿል፡፡ ለማጠቃለል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 43 አስፈላጊነትም ተከታታይ ክስ ሳይኖር በአንድነት እንዲታይ በማድረግ የኃላፊነት እና መጠኑን እንዲሁም ከፋዩን ወገን በመለየት የመጨረሻ እልባት መስጠት ማስቻል እንደመሆኑ በተለይ ካሣ (indemnity) የመክፈል ግዴታ ያለበት አመልካችን መሰል የመድን ድርጅት ከከሳሹ ጋር ያለውን አጠቃላይ ክርክር ማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ በውሳኔው ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የሕግ ትርጉም እስካልተለወጠ ድረስ በማናቸውም ድርሻ በሚገኙ ፍ/ቤቶች አስገዳጅነት ያለው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(4) ሥር ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ከተከሳሽ ጋር እንጂ ከከሳሽ ጋር መከራከር አይችልም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43(1) በመጥቀስ የሰጠው ፍርድ በፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ ፍርዱ መሠረታዊ የህግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለዚህም አመልካች በክርክሩ ሊያነሳ የሚችለው የኃላፊነት እና የኃላፊነት መጠን ከተከሳሽ ጋር ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ከከሳሽ ጋር ሊሆን እንደሚችል የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁ 43(1) ይዘት እና የሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም ያስገነዝባል፡፡ በዚሁ መሠረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 47210 መጋቢት 25/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ከከሳሽ ጋር በሕግም ሆነ በፍሬ ነገር ረገድ መከራከር የሚችል በመሆኑ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ መዝገቡን አንቀሳቅሶ ይግባኝ ክርክሩን ተመልክቶ የመሰለውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 343(1) መሠረት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው ብለናል፡፡ የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 43845

መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ጌታይዳ ኃ/የተ/የግል ማህበር - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ያላግባብ የተከፈለ ቀረጥ ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባሁኑ አመልካች ላይ መጋቢት 07 ቀን 1998 ዓ.ም በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ተጠሪ ድርጅት ሄርታለን ከሚባል የኔዘርላንድ ድርጅት የፈሳሽ መከላከያና ተዛማጅ እቃዎችን በአምራቹ የመሸጫ ዋጋ መሰረት የጉምሩክ ቀረጥን እየከፈለ ሲያስገባ መቆየቱንና በሦስት የተለያዩ ጊዜያት ከከፈላቸው ክፍያዎች ውስጥ ድምሩ ብር 60,858.82(ስልሳ ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ስምንት ብር ከሰማንያ ሁለት ሳንቲም) የሆነውን ገንዘብ ያላግባብ አመልካች ማስከፈሉንና ይኸው ያላግባብ የተከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት ተጠሪ ጥያቄ ቢያቀርብም አመልካች ፈቃደኛ አለመሆኑን በመዘርዘር ክሱ የተመሰረተበትን ገንዘብ ያለአግባብ ከተከፈለበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድና ከክሱ ወጪና ኪሣራ ጋር አመልካች እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር ነጥቦችን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት የአመልካችን ምስክሮች መስማት አስፈላጊ አለመሆኑን ገልፆ ጉዳዩን በመመርመር የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጐ ለክሱም ኃላፊ በማድረግ ክሱ የተመሰረተበትን ገንዘብ ክሱ ከተመሰረበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ 9%(ዘጠኝ በመቶ) ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የስር ፍርድ ቤት ይርጋን በተመለከተ የቀረበውን መቃወሚያ ማለፉም ሆነ የአመልካችን ምስክሮችንም ሳይሰማ መቅረቱ ያለአግባብ ሆኖ የደረሰበት ድምዳሜም የአዋጅ ቁጥር 68/89 አንቀጽ 48/7/,/11/ እና መመሪያ ቁጥር 10/1996 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን የሚፃረር በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ በጠበቃቸው አማካኝነት ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አግባብነት ገልጸው ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩላቸው ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የአመልካች ምስክሮች ሳይሰሙ ውሳኔ መስጠቱ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ክሱን ሊመሰርቱ የቻሉት ያላግባብ የከፈልኩት የቀረጥ ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በሚል ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ ክፍያውን ያስፈጸመው በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የዋጋ መረጃን በማየት መሆኑን ገልፆ ያላግባብ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋጋ መረጃ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ጉዳዩን ለማስረዳት የተቆጠሩት ምስክሮችንም መስማቱ አስፈላጊ አለመሆኑን ገልፆ አመልካች በተጨማሪነት የወሰደውን የቀረጥ ገንዘብ ባግባቡ የወሰደ መሆኑን፣አላስረዳም በሚል ምክንያት ክርክሩን ውድቅ ማድረጉን ነው፡፡

የጉምሩክ ባሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም እና አሰራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 47 ላይ እንደተመለከተው ወደ ሐገር ውስጥ ለሚገባ ማናቸውም እቃ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ የሚሆነው በትክክል ለእቃው የተደረገ ጠቅላላ ወጪ ነው፡፡ እቃው የተገዛበት ዋጋ ደግሞ ከወጪዎች አንዱ ነው ስለሆነው ለቀረጥ ማስከፈያ መሰረት የሚሆነው ትክክለኛ የእቃው ዋጋ ስለመሆኑ ሕጉ በዋናነት ያስቀመጠው አስራር ነው፡፡ ከዚሁ የሕጉ መንፈስ መረዳት የሚቻለው ሌላው ቁም ነገር ደግሞ በአስመጪው የሚቀርበው የእቃው ግምት ትክክለኛውን የእቃውን ዋጋ የማይናገር መሆኑ ከተረጋገጠ የቀረጥ ሂሳብን ለማስላት መነሻ(መሰረት) ሊሆን የማይችል መሆኑን ነው፡፡ በመሰረቱ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ እቃ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ምን ያህል እንደሆነና እንዴት እንደሚሰራ በአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀጽ 48 ስር ተዘርዝሯል፡፡ የተጠቀሰው የአዋጅ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 7 እና 8 ድንጋጌዎች ሲታዩም የጉምሩክ ባለሥልጣን ባስመጪው የቀረበለትን የዋጋ ግምት አልቀበልም በማለት የቀረጥ ሂሳቡን ለማስላት ሌሎች አማራጭ መንገዶችን መከተል የሚችል ስለመሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡ የተጠቀሰው የአዋጅ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 6 ድንጋጌ ደግሞ፣የጉምሩክ ባለስልጣን በአስመጪዎች የቀረበለትን የዋጋ ግምት አልቀበልም ስለሚልበት ሁኔታ የገቢዎች ቦርድ መመሪያ ማውጣት የሚችል መሆኑን ደንግጓል፡፡ በዚሁ ሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረትም የተጠቀሰው አካል መመሪያውን ማውጣቱ የተረጋገጠ ሲሆን በዚህ መመሪያ መሰረትም በትራንዛክሽን ዋጋ ላይ የተመሰረተ የጉምሩክ ዋጋ አተማመን ተግባራዊ የማይሆንባቸው ምክንያቶች ተቀምጠዋል፡፡ ከነዚህም ምክንያቶች መካከል ወደ ሐገር ውስጥ የገባው እቃ ዋጋ ከአንድ ዓይነት እና ከተመሳሳይ እቃዎች ዋጋ በጉምሩክ ከተፈቀደው ልዩነት በላይ እንሶ መገኘት ስለመሆኑ መመሪያው በአንቀጽ 1/5/ ስር አስቀምጧል፡፡ ወደ ሃገር በገባ ወይም ከሐገር በወጣ እቃ ላይ የተከፈለው ቀረጥ በማናቸውም ምክንያት ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥ ያነሰ መሆኑ በምርመራ የተደረሰበት እንደሆነ ደግሞ ባለሥልጣኑ የእቃውን ባለቤት ወይም ወኪሉን በልዩነት ያልተከፈለውን ቀረጥ ማስከፈል እንደሚችል በአንቀጽ 57/1/ ስር በግልጽ አስፍሯል፡፡ በሌላ በኩል በብልጫ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ ለከፋዩ ሊመለስ እንደሚገባ አዋጁ በአንቀጽ 55 ስር በግልጽ ደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ቀረጡን አስከፈልኩ የሚለው በመመሪያ ቁጥር 10/1996 መሰረት ስለመሆኑ፣በዚህ መመሪያ መሰረት የተፈፀመ ስለመሆኑ ደግሞ የሚያስረዱት ምስክሮች ያሉት ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃነት ዘርዝሮ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ አመልካች የቆጠራቸውን ምስክሮች መስማት አስፈላጊ አይደለም ብሎ ከአለፈ በኂላ አመልካች ክርክሩን በማስረጃ አላስረዳም በማለት ለክሱ ኃላፊ አድርጎታል፡፡ በአርግጥ በተከራካሪ ወገን የተቆጠረውን ምስክር ሁሉ ፍርድ ቤቱ እንዲሰማ የማይገደድ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ-ስርአት ሕጉ ስለማስረጃ አቅራረብ እና አቀባበል የተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት የሚያስገነዝበን ነጥብ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ስልጣኑን መተግበር ያለበት በዘፈቀደ ሊሆን አይገባም፡፡ በመሆኑም በተከራካሪ ወገን የተቆጠሩት ምስክሮች ሳይሰሙ የሚቀሩት ለጉዳዩ የሚሰጡት ምስክርነት አግባብነት የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የአመልካች ምስክሮች ሊያስረዱ ይገባል የተባለው አመልካች በሕጉ የተሰጠውን ስልጣን ባግባቡ በመጠቀም የተጠሪን ጥያቄ ያልተቀበለው ስለመሆኑ እና በመመሪያ ቁጥር 10/1996 መሰረት ብልጫ ቀረጥ የተባለው አለመከፈሉን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ በምስክሮች የሚሰጠው ቃል ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነው ለማለት የሚያስችል አለመሆኑን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ ሳይሰማ ደግሞ ማስረጃውን የቆጠረው ተከራካሪ ክርክሩን በማስኛ አላስደገፈም ሊባል አይችልም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመራው አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 48 እና መመሪያ ቁጥር 10/1996 እንዲሁም በፍትሐብሔር ስነ ስርአት ሕጉ ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ባገናዘበ መልኩ ባለመሆኑ የፍርድ አካሄዱ የተሟላ ነበር ለማለት አልተቻለም፡፡ የፍርድ አካሄድ

ሳይሟላ የተሰጠ ፍርድ ደግሞ የሕግ ሥርአቱን ያልጠበቀ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 66236 ሐምሌ 23 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጠቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 59649 ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ቀረጡን ያስከፈለበትን ሁኔታ ለማስረዳት የቆጠራቸው ምስክሮች ተሰምተው እና ሌላም ተገቢ ነው የተባለ ሁሉ ተፈጽሞ በጉዳዩ ላይ እንደገና ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው በመሆኑ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን ምስክሮችን በመስማት ጉዳዩን እንደገና አይቶ ይወስን በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. እስከአሁን ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 44931

መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ሰዓዳ ኢድሪስ - ወኪል አደም እንድሪስ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ረሺድ ቡባ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥነ-ሥርአት ህጉን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በድሬዳዋ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከአውራሻቸው ከወ/ሮ ሉላ መሐመድ በኑዛዜ ያገኙሁትን ቤትና ቦታ የመሬት ልማት ባለስልጣን (የስር አንደኛ ተከሳሽ) መብት ሳይኖረው አሳልፎ ለአመልካች ስለሰጠ ተከሳሾቹ ቤቱና ቦታውን እንዲያስረክቧቸው እንዲወሰንላቸው አመልክተው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የከሳሽ አውራሽ ራሳቸው በቤቱ ላይ መብት የነበራቸው ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጐታል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪ ለድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ የስር ፍ/ቤት በውሳኔው ላይ የቤቱን ካርታ ቁጥር 6001 ከማለት ፋንታ 001 ብሎ ስለመዘገበው ይኸው የቁጥር ስህተት እንዲታረም ለስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት አመልክተው ፍ/ቤቱ የቁጥሩን ስህተት አርሟል፡፡ ተጠሪም ይህን ትእዛዝ መነሻ በማድረግ ቀደም ሲል በድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ውድቅ የተደረገባቸውን መዝገብ ያንቀሳቅሳሉ፡፡ ፍ/ቤቱም የተዘጋውን ይግባኝ ከቀረበው ማስተካከያ አንፃር ለመመረመር ይግባኙ አመልካችን ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ ቤቱ ላይ መብት አላቸው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ሽሯል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካችም የድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት የዘጋውን የይግባኝ መዝገብ የስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት የሰጠውን እርምት መሰረት በማድረግ እንቀሳቅሶ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ ሥነ-ሥርአት ሕግ ስህተት ነው የሚልና ሌሎች ቅሬታዎች አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ ነጥብ ለመመርመር ሲል አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ቀርበው ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡

በሌላ በኩል የስር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው የመሬት አስተዳደር የድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ በሰበር መ/ቁ. 45172 የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም መዝገቡ ከመ/ቁ. 44931 ጋር እንዲታይ ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኝ ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ በሁለቱ መዝገቦች የቀረበው ጉዳይ ተመሳሳይ በመሆኑም ችሎቱ ሁለቱንም መዝገቦች አጣምሮ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

ተጠሪ የድሬዳዋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 መሰረት ተዘግቶ መዝገቡ የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ ከማቅረብ ይልቅ የወሰዱት አማራጭ ውሳኔ እንደገና እንዲታይላቸው ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማመልከትን ነው፡፡ ተጠሪ ውሳኔ ያገኘው ጉዳይ እንደገና እንዲታይላቸው ያመለከቱትም የስር ፍ/ቤቱ በውሳኔው ላይ የቤቱን ካርታ ቁጥር አሳስቶ የፃፈው መሆኑን በመግለጽ ቁጥሩ እንዲታረምላቸው ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የተሰጠው የማስተካከያ ትእዛዝ መሰረት አድርገው ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ማስተካከያ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ለመሻር ወይም ለማረም ሥልጣን ይሰጠዋል ወይ? የሚለው መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡

አንድ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ ውሳኔው የሚታረመው የይግባኝ ቅሬታ በማቅረብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320/1/ እና 348/1/ አገናዝቦ በማንበብ መረዳት ይቻላል፡፡ በእርግጥ በተሰጠ ፍርድ ላይ ይግባኝ ማለት የሚቻል ቢሆንም ውሳኔውን የሰጠው ፍ/ቤት በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ፍርዱን ለማረም ወይም ለማሻሻል ወይም እንደገና ለማጣራት የሚችል ከሆነ ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለው የኸው ስርዓት ከተፈፀመ በኂላ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320/2/ ያመለክታል፡፡ ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤትም የሰጠውን ፍርድ በድጋሚ አይቶ ፍርዱን የሚያርምበት የተለያዩ ሥርአቶች በስነ-ሥርዓት ሕጉ ውስጥ ተካተዋል፡፡ ለምሳሌ በክርክሩ ውስጥ ከሥነ-ሥርአት ውጪ የሆነው ጉዳይ ሲኖር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 209 መሰረት አቤቱታ ሲቀርብ ወይም ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 መሰረት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ አቤቱታ ሲቀርብ ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤት ጉዳዩን በድጋሚ ማየት ይችላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በድጋሚ አይቶ የለወጠው ከፍ ሲል እንዳየነው ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ማስተካከያ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በተሰጠው ፍርድ፣ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ላይ የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ ድንገተኛ ቃል ስህተት መኖሩን ሲረጋገጥ ስህተቱ የሚታረምበትን ስርአት የዘረጋ ድንጋጌ ነው፡፡ በድንጋጌውም እንዲታረም የተፈቀደው የውሳኔውን ይዘት ሊቀይሩ የማይችሉ መሰረታዊ ያልሆኑ የጽህፈት ወይም የቁጥር ስህተቶች ወይም ግድፈቶች ብቻ ናቸው፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የካርታ ቁጥሩ መስተካከል ውሳኔውን ሊያስቀይር የሚችል ነው በማለት መዝገቡን ለማንቀሳቀስ የሚችልበት የስነ-ሥርዓት ሕግ የለም፡፡ በመሰረቱ በስር ፍ/ቤት የተጠሪ ክስ ውድቅ የተደረገው ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት እዳንለኝ ያስረዳልኛል ያሉት የቤት ካርታ በስር ፍ/ቤት ቀርቦ ታይቶ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በመጀመሪያ ይግባኙን ውድቅ ሲያደርግም ይህንኑ ሰነድ ተመልክቶ ነው፡፡ የካርታው ቁጥር በመሳሳቱ በውሳኔው ላይ ያስከተለው አሉታዊ ውጤት ስለመኖሩም በተጠሪም በኩል ሆነ በድጋሚ ጉዳዩን ባየው የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሰጠውን መጨረሻ ውሳኔ በድጋሚ አይቶ እንዲያርመው ስልጣን የሚሰጠው የሥነ-ሥርአት ሕግ የለም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት የሰጠው የቁጥር ማስተካከያ ትእዛዝን ብቻ መሰረት በማድረግ የሰጠውን ውሳኔ በድጋሚ አይቶ መሻሩ መሰረታዊ የሥነ-ሥርአት ስህተት ነው፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00248/2001 መጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቀደም ሲል ውድቅ ያደረገውን የይግባኝ ቅሬታ ያለህጋዊ ምክንያት በድጋሚ አይቶ ውሳኔውን መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከመ/ቁ. 45172 ጋር ይያዝ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 48237

መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሰኢዳ ሁሴን ይመር

**ተጠሪ፡-** የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 480 ስር የተመለከተውን መሰረት በማድረግ ያስተላለፈውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አመልካች ነሐሴ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ስላመለከቱ የቀረበ ነው፡፡ አመልካች በጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉት አመልካች ፈፀሙ የተባሉት ድርጊት ስለመፈፀሙ በአሳማኝ ማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን፣ ድርጊቱ ስለመፈፀሙ ከችሎቱ ውጪ ሌላ ምርመራ ተከናውኖ ባግባቡ ሊጣራ ይችል የነበረ እንጂ ለውሳኔው መሰረት የሆነውን ድንጋጌ የማያሟላ መሆኑን፣ ችሎቱ የአመልካችን መከላከያ ማስረጃዎችን የመዘነበት አግባብ የማስረጃ አሰማም እና ምዘና ሥርዓትን ያልተከተለ መሆኑን ያሳያሉ ያሏቸውን ምክንያቶችን በመዘርዘር ነው፡፡

ይህ ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ ለአቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ ግልባጭ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሶሪቲ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ጋር በነበረባቸው የፍትሐብሔር ይግባኝ ክርክር ጉዳዩ ገና በምርመራ ላይ ባለበት ሁኔታ ጉዳዩ አልቋል፣ አስጨርሼአለሁ፣ የተፈረደላችሁን ገንዘብ አታገኙም፣ ጉዳዩን ለማስጨረስ ከዳኞች ጋር ተነጋግሬ ገንዘብም ከፍያለሁ እያሉ ስለመናገራቸው ለጉዳዩ መልስ ሰጪ የነበረው ሶሪቲ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ባቀረባቸው ማስረጃዎች ተረጋግጧል ተብሎ እና ይህ አድራጎት ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 480 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ያሟላል በሚል ነው፡፡ አመልካች የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ድርጊቱ ስለመፈፀሙ የሰማቸው ምስክሮች ቃል ክብደት ተሠጥቶ በአንፃሩ የአመልካች ምስክሮች ቃል ክብደት ውድቅ ያደረገው ያላግባብ ነው፣ ድርጊቱ ስለመፈፀሙ በቂና አሳማኝ ማስረጃ አልቀረበብኝም በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት በቂ ማስረጃ አስቀርቦ የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን ቃል በመመዘን የወሰነ መሆኑን ስለተገነዘብን እና ይህ ችሎት የማስረጃ ምዘናን በተመለከተ ስልጣን የሌለው በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር የምንቀበለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ሌላው ነጥብ፤ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 480 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የማያቋቁም፣ ራሱን የቻለ ምርመራ ሊደረግበት የሚችል እንጂ ችሎቱ በራሱ ወዲያውኑ በቀጥታ ቅጣት እንዲያስተላልፍ ስልጣን የሚሰጠው አይደለም በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 480 ይዘት ሲታይ የማንኛውም ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ የፍርድ ቤቱን የዳኝነት ስራ አካሔድ ስነ ስርዓት ለማስከበር ማናቸውንም አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ ሊወስድ እንደሚችል፣ ይህንንም

ለማስፈፀም ለፍርድ ቤቱ ችሎት ክብር ወይም ለዳኝነቱ ሥነ-ሥርዓት መልካም አመራር ተቃራኒ የሆነ ጠባይ የሚያሳየውን ማናቸውንም ተከራካሪ ወገን ወይም ጠበቃ ወይም በችሎቱ ውስጥ የሚገኘውን ማናቸውንም ሰው ተቃራኒ ተግባር በሰራበት ጊዜ በያዘው መዝገብ ላይ የገንዘብ መቀጮ ሊወስንበት የሚችል ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡ ድንጋጌው በፍርድ ቤቱ እይታ ውስጥ ወይም ፊት ለፊት የተፈፀሙ፤ የፍርድ ቤቱን ስራ የሚያውኩ ተግባሮችን ማስቆም፣ አስፈላጊ እርምጃዎች እንዲወሰድ ለፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ በቀጥታ የመወሰን ስልጣን የሚሰጥ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ የድንጋጌው አስፈላጊነትም ተከራካሪ ወገኖችም ሆኑ ማናቸውም ግለሰብ የሚፈፅሟቸው ተግባሮች የፍርድ ቤትን ሥርዓትና ክብር የሚያናጉ፣ ህብረተሰቡ በፍርድ ቤት ላይ ያለውን አመኔታ የሚቀንሱ ከሆነ ማስወገድ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሶሪቲ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ጋር በነበረባቸው የፍትሐብሔር ይግባኝ ክርክር ጉዳዩ ገና በምርመራ ላይ ባለበት ሁኔታ ጉዳዩ አልቋል፣ አስጨርሼአለሁ፣ የተፈረደላችሁን ገንዘብ አታገኙም፣ ጉዳዩን ለማስጨረስ ከዳኞች ጋር ተነጋግሬ ገንዘብም ከፍያለሁ እያሉ ማስወራታቸው በሚገባ በማስረጃ ተረጋግጦባቸው ነው፡፡ ይህ አድራጎት የዳኝነትን ክብርን፣ የዳኝነት አስተዳደርን የሚነካ፣ ሕብረተሰቡ በፍርድ ቤቱ ላይ እምነት እንዳይኖረው የሚያደርግ ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያስወሩት ተግባር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 480 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የሚያሟላ ነው በማለት አመልካችን ወዲያውኑ በቀጥታ በያዘው መዝገብ ጥፋተኛ በማድረግ በብር 10,000.00(አስር ሺ.ህ) መቅጣቱ ሕጋዊ እንጂ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሆኖ ስላላገኘነው ውሳኔው ሊፀና የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 42643 ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የሠጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 50022

መጋቢት 29 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** 5 ብራዘርስ ኃ.የተ.የግል ማህበር - ክበበው ደስታ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** ዓብደላ ኢብሮ ዮሴፍ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ቀደም ሲል በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ወደ ክርክሩ እንድገባ በማለት ያቀረብኩት ጥያቄ ከሕግ ውጪ ተቀባይነት አጥቶአል በማለት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ተጠሪ በአመልካች እና ሰሎሞን ጀንበሩ በተባለው ግለሰብ ላይ ክስ መስርቶ የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው አስወስኖአል፡፡ ተጠሪ ክሱን የመሠረተው በሰሎሞን ጀምበሩ ሹፌርነት ሲሽከረከር የነበረው የአመልካች ንብረት የሆነው መኪና ገጭቶ ጉዳት አድርሶብኛል በማለት ሲሆን፣ በፍ/ቤቱ የታዘዘለትን መጥሪያ ለማድረስ ሞክሮ ተከሳሾችን ማግኘት እንዳልቻለ ለፍ/ቤቱ በመግለጹም ፍ/ቤቱ መጥሪያው በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ እንዲለጠፍ በማለት ምትክ የመጥሪያ አደራረስ ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡ ከዚህ በኂላም ተከሳሾች ተጠርተው አልቀረቡም በማለት ክርክሩን ተከሳሾች በሌሉበት ሰምቶ ውሳኔውን ሰጥቶአል፡፡ አመልካች ከዚህ በኂላ ነው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.78 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ አቤቱታ ያቀረበው፡፡ አቤቱታው የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግን አቤቱታውን ባለመቀበል ብይን የሰጠ ሲሆን፣ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ብይኑን አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ጥቅምት 24 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች በአግባቡ ተጠርቶ ሳይቀርብ ቀርቶአል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.78 መሠረት የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ያደረገበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከቀረበልን ክርክር፣ የሥር ፍ/ቤቶች ከሰጡት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተካሄደው ክርክር እና ፍ/ቤቶቹ ከሰጡት ውሳኔ መገንዘብ እንደቻልነው መጥሪያው በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ እንዲለጠፍ ምትክ የመጥሪያ አደራረስ ትዕዛዝ የተሰጠው ተጠሪ የአመልካችን አድራሻ አላውቅም በማለቱ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ግን አመልካች የንግድ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.97 በተመለከተው አይነት መጥሪያው እንዲደርሰው ስለመታዘዙ ወይም በዚህ መሠረት ትዕዛዙ ተላልፎ ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆን ስለመቅረቱ በተመለከተ ምንም የተባለ ነገር የለም፡፡ ሌላው ቀርቶ ተጠሪ አመልካችን ፈልጎ ለማግኘት ያልቻለው መጥሪያውን በየትኛው አድራሻው ወስዶ ፍለጋ አድርጎ እንደሆነ አልተረጋገጠም፡፡ አመልካች የንግድ ድርጅት (ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር) ስለሆነ ተመዝግቦ ንግዱን የሚያካሂድበት መስሪያ ቤት ወይም ጽ/ቤት እንዳለው ይገመታል፡፡ ተጠሪ ጉዳቱን ያደረሰበት መኪና የአመልካች ንብረት መሆኑ እስካወቀ ድረስ አድራሻውን ማወቅ አይችልም ማለትም የሚያስቸግር ነው፡፡

ተከሳሽን በአግባቡ መጥራት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከተቀመጡት የመስማት መብት ከሚረጋገጥባቸው መርሆዎች አንዱ ነው፡፡ ይህን መርህ ባለመጠበቅ የሚሰጠው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ በሕጉ አግባብ እንደተሰጠ አይቆጠርም፡፡ በመሆኑም ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ወደጉዳዩ ሥረ-ነገር ገብቶ ተከሣሹን ባለዕዳ የሚያደርግ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት

ተከሳሹን በአግባቡ ስለመጠራቱ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ክሱን የሰማው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.95(3) እና 97 በተደነገገው መሠረት መጥሪያው ለአመልካች ስለመላኩ አላረጋገጠም፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.105 መሠረት ምትክ የመጥሪያ አሰጣጥ ትዕዛዝ የሰጠው በአግባቡ አልነበረም፡፡ ሲጠቃለል ፍ/ቤቱ አመልካችን በሕጉ አግባብ መሠረት እንዲጠራ አድርጎአል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ሁኔታው ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.78(1) መሠረት ያቀረበለትን ጥያቄ አልቀበልም የሚልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ጥያቄውን ውድቅ በማድረጉም የአመልካችን የመከራከር መብት የሚጎዳ ውሳኔ ሰጥቶአል ለማለት የሚቻል በመሆኑ ውሳኔው በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 12201 ሰኔ 3 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 04822 ጥቅምት 11 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.78(1) መሠረት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ክሱ አመልካች ባለበት ይሰማ ብለናል፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካችን ወደ ጉዳዩ በማስገባት ክሱን እንደገና ከሰማ በኋላ ተገቢውን ይወስን ብለናል፡፡ ይጻፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 45038

መጋቢት 23 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች**፡- 1. ወ/ሮ ዓለሚቱ ጓዱ - ቀረቡ

2. አቶ ዋስ ጓዱ - አልተጠሩም

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ አስረስ አህመድ ወ/አበባ ጓዱ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካቾች የውርስ ንብረት ከተጠሪ ለመካፈል ያቀረቡትን የአፈፃፀም ክስ የተመለከተው የምሥራቅ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በብቸና ከተማ የሚገኘው ድርጅት እና መኖሪያ ቤት በአፈፃፀም ተከሳሽ ሳይሆን በሌላ ሦስተኛ ወገን ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ስለመሆኑ ማዘጋጃ ቤቱ ማረጋገጫ ሰጥቷል በሚል የአመልካቾችን የአፈፃፀም ጥያቄ ሌላ ንብረት አፈላልገው ያቅርቡ በሚል ተዘግቷል፡፡ የአሁን አመልካቾች ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

ለዚህ ሰበር ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ አከራካሪው ንብረት ውሳኔ ያፈረበት መሆኑን ጠቅሰው የአፈፃፀም ሂደት ለማሰናከል ተጠሪ በተንኮል በልጃቸው ስም ያዛወሩ ስለመሆኑ ገልፀው ቀደም ሲል በተወሰነው መሰረት እንዲፈጸም እንዲታዘዝ አመልክቷል፡፡

ሰበር ሰሚ ችሎትም መዝገቡን መርምሮ ውሳኔ ያረፈበትን ቤት በተጠሪ ሳይሆን በሌላ ሰው ስም ነው በሚል አመልካቾች ሌላ ንብረት እንዲጠቁሙ መታዘዙ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ተጠሪ ህዳር 8/2002 ዓ.ም በጽሑፍ ባቀረቡት መልስ ወ/ሮ አበባ ደርሰሕ በስሟ አዘዋውራ የያዘቸው ቤት በተመለከተ ተጠሪ የፈጸሙት ተንኮል የሌለ ስለመሆኑ የቤቱም መገምት ባለመብት እንደማያደርግ እንዲሁም በብቸና ከተማ ቀበሌ 02 አዲስ ገበያ ተብሎ በሚጠራ የድርጅት ቤት የወ/ሮ ዘምዘም ጓዱ ደርሰህ የግል ሐብት ስለመሆኑ እና የቤት ቁጥር 772 የወ/ሮ አበባ ጓዱ ደርሰህ በሰሟ አዛውራ ይዛ የምትገኝ መሆኑን ዘርዝረው ተጠሪ ኃላፊነት የሌለባቸው ስለመሆኑ አጥብቀው ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም በመልስ መልሳቸው በልጆቻቸው ስም ያዛወሩዋቸው ንብረቶች ውሳኔ ያረፈባቸው መሆን ጠቅሰው ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡ እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ከሥር ፍ/ቤት ውሳኔ አንፃር መርምረናል፡፡ ስለዚህ የአፈፃፀም ክርክር መነሻ የሆነው ውሳኔ በም/ጐጃም ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 2284 በ2/13/98 ዓ.ም የተሰጠው መሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ከዚህ ውሳኔ ይዘት መረዳት የተቻለው አንደኛ በአዲሱ ገበያ አካባቢ የሚገኝ የድርጅት ቤት ቁጥር አዲስ በአቶ ጓድ ደርሰህ ስም መሆኑ፤ሁለተኛ በብቸና ከተማ 02 ቀበሌ ከድሮ ገበያ አካባቢ የሚገኘው መኖሪያ ቤት በወ/ሮ አበባ ጓድ ስም መሆኑ እና በሦስተኛ ደረጃ ከብት ገበያ መሔጃ መንገድ ያለው ቤት በወ/ሮ አስረስ አህመድ ስም ያለ መሆኑ ተጠቅሶ ከማዘጋጃው በተሰጠ ማረጋገጫ መሰረት ወደ ከብት ገበያ መሔጃ የሚገኘው ቤት የውርስ ንብረት ሆኖ ግራ ቀኙ እንዲከፋፈሉ መወሰኑን ነው፡፡ እንዲሁም በሚች ስም የሚታወቅ ድርጅት ቤት ከገበያ አካባቢ የሚገኝ እንዲካፈሉ መወሰኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ውሳኔ መነሻ አፈፃፀም ላይ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ ውሳኔ ያረፈበትን ቤት እና ድርጅት ተጠሪ ከውሳኔው በኋላ በልጆቻቸው ስም አዛውረዋል የሚል ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት በተጠሪ ስም ያለ አንድ

መኖሪያ ቤት እና በሚች ስም ያለ አንድ ድርጅት ቤት አመልካቾች እንዲካፈሉ ከወሰነ በኋላ በአፈፃፀም ክርክር ሂደት እነዚህ ቤቶች እንዴት ሊተላለፉ እንደቻሉ ሳያጣራ ቤቶቹ በሦስትኛ ወገን ስም የተመዘገቡ ናቸው በማለት ውሳኔውን ሳያስፈጽም መቅረቱን ተረድተናል፡፡

በመሰረቱ አፈፃፀም የያዘው ፍ/ቤት በዋናው ፍርድ የተሰጠውን ውሳኔ ማስፈጸም ይጠበቅበታል፡፡ ፍርድ አስፈፃሚው ፍርድ ቤት እንደ ፍርድ ማስፈጸም አሊያም ያልተፈፀመበትን ምክንያት በመዘርዝር በግልጽ ማመልከት እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 374 ያመለክታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ዋና ፍርድ ያፈረበትን ቤትና የድርጅት ቤት በአፈፃፀም ተከሳሽ ሳይሆን በሌላ ሦስትኛ ወገን የተመዘገበ ስለመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ሳለማስፈጸም መሰናክል መሆኑን የጠቀሰ ስለመሆኑ ከውሳኔው ተረድተናል፡፡ በአመልካቾች በኩል የቀረበው አቤቱታ ደግሞ የሚያመለክተው ተጠሪ ንብረቶቹን በተንኮል ድርጊት ከፍርድ በኋላ በልጆቻቸው ስም አዙረዋል የሚል ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤት ያደረገው ማጣራት ሥራ የለም፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ንብረቶቹ የውርስ ንብረት ናቸው ተብሎ ውሳኔ ካረፈበት በኋላ በምን አግባብ ወደ ሦስተኛ ወገን እንደተላለፉ ማጣራት አስፈላጊ እና በመሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም ይህንን ፍሬ ነገር ማጣራት እና ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መወሰን ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለዚህም የሥር ፍ/ቤት ይህንኑ ሳያጣራ አመልካቾች ሌላ ንብረት ይጠቀሙ ሲል የአፈፃፀም መዝገቡን ለጊዜው መዝጋቱ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የምስራቅ ጉጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአፈፃፀም መ/ቁ. 17589 ጥቅምት 2/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ፣የአማራ ብ/ክ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20042 የሰጠው ትእዛዝ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 00580 የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በተጠሪ እና በሚች ስም የነበረው ቤት እና ድርጅት የውርስ ንብረት ነው ተብሎ በዋናው ፍርድ እንዲከፋፈሉ ከተፈረደ በኋላ በአፈፃፀም ክርክር ሂደት ንብረቶቹ በሦስተኛ ወገን የተመዘገቡበት አግባብ እና ውጤቱን አስመልክቶ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መዝገቡን ለምሥራቅ ጉጃም ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 43005

ሚያዚያ 19 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አብዱራሂም አህመድ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** 1. አቶ አውግቸው እርገጤ
2. ወ/ሮ ማህደር ቢተው
3. አቶ አደራጀው ዘውአለ

ሁሉም ከጠበቃ ሳሕሉ ሀብቴ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 ስር የተመለከተውን መሰረት በማድረግ ያስተላለፈውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አመልካቾች ጥር 22 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ስላመለከቱ የቀረበ ነው፡፡

የአመልካቾች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ችሎት የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት በሰበር አቤቱታቸው ላይ ዘርዝረዋል፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካቾችን አቤቱታ ለአቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ ግልባጭ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተያዘው የጉዲፈቻ ውል ይፅደቅልኝ ጥያቄ ሂደት ውስጥ ሐሰተኛ አቤቱታና አስተያየት በማቅረብና ፍርድ ቤቱን ለማሳሳት ሞክረዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሕጻን ሂክማን ኢብራሂምን ተቀብሎ የሚያሳድጋት ብርሃን ሕይወት የሕጻናትና ቤተሰብ መርጃ ድርጅት አቶ አውግቸው እርገጤ ወኪል ለሆኑላቸው ጀርመናዊያን ባልና ሚስት በጉዲፈቻ ለመስጠት ያደረገውን ውል ፍርድ ቤት ለማስፀደቅ ጥቅምት 07 ቀን 2001 ዓ.ም ማመልከቻ ለፍርድ ቤቱ ቀርቦለት የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር አስተያየት እንዲሰጥበት ችሎቱ ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም ትዕዛዝ መስጠቱን፣ ለሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የተላከው የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት ቡድን መሪ ለሆኑት ላሁኑ ሁለተኛ አመልካች ቀርቦላቸው የጉዲፈቻ ማንነት ሲመረመር ሕጻናት ማሳደጊያው ተግባሩን እንዳይቀጥል በፍትሕ ሚኒስቴር እንደታገደ በመታወቁ ሕፃኗ በቅድሚያ ሕጋዊ ለሆነው የህፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ባሁኑ ሦስተኛ አመልካች በሚተዳደረው የእናት ዓለም ሕፃናት ማሳደጊያ እንደተላለፈች፣ ከዚህም በኋላ ያሁኑ አንደኛ አመልካች ከአዲሱ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ጋር የጉዲፈቻ ውል ፈፅመው ሁለተኛ አመልካች አንደኛ አመልካች ሕፃኗን አዲስ ከተረከበው ድርጅት ጋር ያደረጉት የጉዲፈቻ ውል እንዲፀድቅ ታህሳስ 07 ቀን 2001 ዓ/ም አስተያየት መስጠታቸውን ሲሆን ፍርድ ቤቱ አመልካቾችን ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት ሊያስተላልፍ የቻለው በተዘጋና እንደገና አስተያየት እንዲሰጥ ባልተጠየቀበት መዝገብ አስተያየት የተሰጠው ፍርድ ቤቱን ለማሳሳት ነው የሚለውን ምክንያት በመያዝ መሆኑን፣ አንደኛ አመልካች ብርሃነ

ሕይወት የሕጻናት እና ቤተሰብ መርጃ ድርጅት መፍረሱን አያውቁም ነበር ተብሎ ታህሳስ 13 ቀን 2001 ዓ.ም በኋላ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በተሰጠበት መዝገብ ውሳኔ የተሠጠ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 ይዘት ሲታይ በዳኝነት ስራ ላይ ወንጀል ሲፈፀም ፍርድ ቤቱ ጥፋቱ በተደረገበት ጊዜ በያዘው የፍትሐብሔር መዝገብ ወዲያውኑ ቀጥታ ቅጣት ሊያስተላልፍ የሚችል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መንገድ ቅጣት ሊያስከትል የሚችለው ድርጊት በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 452(1) ስር የተመለከተው በተከራካሪ ወገን የሚሰጠው ሐሰተኛ ቃል ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ተጠያቂነት የሚመጣው ማንኛውም ተከራካሪ ወገን በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ባለው አካል ዘንድ ቀርቦ እውነት እናዲናገር ታዞ በፍርድ ቤቱ ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ባለው አካል በሚወሰን ጭብጥ ላይ አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮችን በሚመለከት እያወቀ ሐሰተኛ ቃል የሠጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

የድንጋጌው አይነተኛ ዓላማ የዳኝነትን ክብርን፣ የዳኝነት አስተዳደርን የሚነካ፣ ሕብረተሰቡ በፍርድ ቤቱ ላይ እምነት እንዳይኖረው የሚያደርግ ድርጊት መከላከልና እውነትን መሰረት ያደረገ ፍርድ እንዲሰጥ ማስቻል ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህንን ለማሳካት ደግሞ ፍርድ ቤት ድንጋጌውን ሲያስፈጽም በድንጋጌው ስር የተመለከቱ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች መሟላታቸውንና በተገቢው ማስረጃ መደገፋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ እንዲሁም ጉዳዩ የወንጀል ባሕርይ ያለው እንደመሆኑ መጠን በወንጀል ስነ-ሕግ ተቀባይነት ያላቸው መርሆዎችንና በሕገ መንግስቱ ውስጥ የተካተቱትን መሰረታዊ መብቶችን ግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባ ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አንደኛ ተጠሪ በጉዳዩ ባንድ መዝገብ ሁለት ጊዜ ውሳኔ የተሠጠባቸው ሲሆን በመጀመሪያው ብይን ይኸው አመልካች በጉዳዩ ላይ የፈፀሙት ድርጊት እንደሌለ ተገልፆ በነጻ ከተሰናበቱ በኋላ እንደገና እንዲቀጡ መደረጉ ተገቢውን ስርዓት በተከተለ ሁኔታ አይደለም፡፡ አንድ ሰው ባንድ የወንጀል ድርጊት ነጻ ተብሎ ከተወሰነ በኋላ በዚያው ጉዳይ እንደገና ሌላ ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጎ የሚቀጣበት አግባብ የለምና፡፡ ሁለተኛ አመልካችን በተመለከተም አመልካች ሰጡ የተባሉት አስተያየት በሕጉ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ለሕፃን ጥቅም ማስጠበቅ መሆኑ የሚገለፅ እስከ ሆነ እና ፍርድ ቤቱ አስተያየቱ ተቀባይነት ያለው መሆኑ ያለመሆኑን በመመርመር በጉዲፈቻ ውል መፅደቅ አለመጽደቅ ላይ ተገቢውን ውሳኔ የሚሠጥበት ከሚሆን በስተቀር ሐሰተኛ ነው ተብሎ የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስከትል አይሆንም፡፡ ከሁሉም በላይ ሁለተኛ ተጠሪ አስተያየት ሰጡ የተባሉበት ድርጅት የፈረሰ መሆኑን እያወቁ አስተያየት መስጠታቸው በእርግጠኝነት የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ አይደለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ሁለተኛ አመልካች ሐሰተኛ ምስክርነት ቃል ሰጥተዋል ሊባሉ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ሦስተኛ አመልካችን በተመለከተም የተላለፈውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ስንመለከተው ይኸው አመልካች ተፈፀመ ለተባለው ድርጊት የነበራቸው የድርጊት ተሳትፎ ምን እንደሆነና ሐሰተኛ የምስክርነት ቃል የሚያሳይ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ የገለፀው ነገር የለም፡፡ አንድ ሰው ደግሞ በወንጀሉ ድርጊት የነበረው ተሳትፎ ባግባቡ ሳይረጋገጥ የሚቀጣበት ሕግ የለም፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ያስተላለፉት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሕጋዊ ስርዓቱን መሰረት ያላደረገ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 እና በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 452(1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የማያሟላ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128857 ታህሳስ 20 እና 22 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75302 ጥር 21 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናውን የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር አመልካቾችን በነፃ አሰናብተናል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 45839

ሚያዝያ 5 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ይርጋአለም ከበደ - ጠ/ደሣለኝ ቀነኒ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** እነ ወ/ሮ ፅጌ ሚካኤል - ጠ/ወጋየሁ ታደሠ (የ1ኛ,2ኛ,3ኛ,5ኛ ተጠሪዎች ጠበቃ) 4ኛ ተጠሪ አልቀረቡም

## ፍ ር ድ

ተጠሪዎች የውርስ ንብረት እንዲጣራላቸው አመልክተው ውርስ ከተጣራ በኋላ ክፍፍሉን አስመልክቶ በስምምነት ስለጨረሱ ይኸው እንዲፀድቅላቸው ለፍ/ቤት አመልክተው ፍ/ቤቱ ስምምነቱን ከመዘገበ በኋላ አመልካች ስምምነቱ ወንጀል መሰል ተግባር የተፈፀመበት በመሆኑ ዳኝነት እንደገና እንዲታይላቸው አመልክተው ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ውድቅ በማድረጉ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6ን መሰረት በማድረግ ባቀረቡት አቤቱታ አራተኛ ተጠሪ የህፃን ማራናታ ወኪል ሳይሆኑ ወኪል ነኝ በማለት ስምምነቱን መፈረማቸው፣ አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች የአቶ ባቻ ቱሉ ወራሾች ሳይሆኑ ወራሾች ናቸው ተብሎ ስምምነቱ መደረጉ፣ የሚጣራው ንብረት የአቶ ባልቻ ቱሉ ብቸኛ ሃብት ሆኖ እያለና ንብረቱ የወ/ሮ አስካለ የጋራ ንብረት ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ሳይኖር እንዲካፈሉ የተደረገው ስምምነት በወንጀል መሰል ተግባር የተገኘ በመሆኑ ስምምነቱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎችም ቀርበው ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤትም የአመልካች ልጅ ማራናታ ተስፋዬ የመዝገቡ አካል ሆና በጠበቃም ተወክላ ጉዳዩን ስትከታተል የቆየች በመሆኑ አመልካች ወንጀል ነክ ተግባር መፈፀሙን ሰኔ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ነው ያወኩት በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፣ እንዲሁም አራተኛ ተጠሪ የልጃቸውን መብት በሚነካ መልኩ ስምምነት ስለማድረጋቸው በማስረጃ አላረጋገጡም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን አመልካች በቅሬታቸው ለአራተኛ ተጠሪ ውክልና የሰጡት ጠበቃ ወክለው እንዲከራከሩ እንጂ የእርቅ ስምምነት እንዲያደርጉ አለመሆኑ፣ ውክልናውንም የሰጡት እሳቸው እንጂ ልጃቸው ባለመሆናቸው ተጠሪው ልጅቷን ወክለው ስምምነት ማድረጋቸው፣ እንዲሁም አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች አቶ ባልቻ ቱሉ ወራሽ ሳይሆኑ ወራሽ ነን ብለው ስምምነት ማድረጋቸው ሲታይ በሃሰት የተደረገ ስምምነት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ብይንና ውሳኔ እንዲሻርላቸው አመልክተዋል፡፡ ችሎቱም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 አኳያ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

አከራካሪው ጉዳይ የአመልካች ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 ስር የሚወድቅ ነው አይደለም የሚለው ስለሆነ ይህን ድንጋጌ ማየቱ ለጉዳዩ አወሳሰን ይጠቅማል፡፡ ይህ ድንጋጌ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል የመጨረሻ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ ውሳኔው ወይም ትዕዛዙ የተሰጠው በሃሰት ተዘጋጅቶ በቀረበ ሰነድን ሃሰተኛ የምስክርነት ቃልን፣ ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቅሶ የሆነ ተግባርን መሰረት አድርጎ መሆኑን አቤት ባዩ ሲረዳው ጉዳዩ በይግባኝ ከመታየቱ በፊት ውሳኔውን የሰጠው ፍ/ቤት ራሱ ዳኝነቱን በድጋሚ እንዲያይ ጥያቄ ለማቅረብ መብት የሚሰጠው ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የሚከራከሩት ፍ/ቤት የመዘገበው ስምምነት ወንጀል መሳይ ተግባር የተፈፀመበት ነው በማለት ነው፡፡

እዚህ መደምደሚያ ላይ ያደረሳቸውም አንደኛው ምክንያት አራተኛ ተጠሪ ስምምነቱን የፈረሙት ከውክልና ስልጣናቸው በላይ ነው በማለት ነው፡፡ አራተኛ ተጠሪ ጠበቃ ወክለው እንዲከራከሩ ብቻ ከተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን አልፈው ስምምነት አድርገው ከሆነ አመልካች ስምምነቱን ከመቃወም ወይም በይግባኝ ፍ/ቤቱ ስምምነቱን በመመዝገብ የሰጠው ትዕዛዝ ከሚያስለውጡ በቀር ድርጊቱ ወንጀል ተብሎ ዳግመኛ ዳኝነት ሊጠየቅበት የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡ ከክርክሩ ሂደትም የአመልካች ልጅ የክርክሩ አካል የነበረችና አመልካች ክርክሩን የሚያውቁ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም በወቅቱ ስምምነቱ እንዳይፀድቅ ወይም በይግባኝ እንዲሻር ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችሉ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ለአራተኛ ተጠሪ ውክልና የሰጡት እሳቸው እንጂ ልጃቸው ባለመሆኗ ተጠሪው የልጃቸው ወኪል በመምሰል ያደረጉ ስምምነት በተንኮል የተደረገ ነው የሚል ክርክር የቀረበ ቢሆንም አመልካች ለአራተኛ ተጠሪ ውክልና መስጠታቸው ያልተካደና አመልካችዋ የልጃቸው ሞግዚት እንደመሆናቸው ልጃቸውን ወክለው ህጋዊ ተግባራትን የሚፈፅሙ እሳቸው በመሆናቸው ከሳቸው በተሰጣቸው ውክልና መሰረት አራተኛ ተጠሪ ስምምነቱን ማድረጋቸው ወንጀል ነክ ተግባር ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመጨረሻም አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪ የሟች አቶ ባልቻ ቱሉ ወራሽ ነን በማለት ያልተከራከሩ መሆኑን አመልካች በሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ወቅት ያመኑ በመሆኑ በውል ስምምነቱ ላይ ወራሽ ነን ብለው በመመዝገብ ፍ/ቤቱን አሳስተዋል በሚል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነው፡፡ በአጠቃላይ የስምምነት ሰነዱ ወንጀል ጠቀስ ተግባር የተፈፀመበት ስለመሆኑ አመልካች ያላስረዱ ስለሆነ ጥያቄአቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 ስር አይወድቅም ሲል የስር ፍ/ቤት የደረሰበት መደምደሚያ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ለማለት አያስችልም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 12405 መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ 39853

ሚያዝያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ

**ተጠሪ፡-** 1. የአፋር ነፃ አውጪ ግንባር

2. አቶ ዮሐንስ ወ/አማኑኤል

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች በክሱ በወረዳ 23 ቀበሌ 12 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥር 1801/01 የሆነ ቤት ሰኔ 09 ቀን 1989 ዓ.ም በተፈረመ ውል በወር ብር 900(ዘጠኝ መቶ) ለአንደኛ ተጠሪ አከራይቶ የነበረ ቢሆንም አንደኛ ተጠሪ የውል ግዴታውን በመጣስ ሁለተኛ ተጠሪ እንዲኖሩበት በማድረጉ የኪራይ ውሉ ተቋርጦ ቤቱን እንዲያስረክበውና ከመስከረም 23 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ድረስ ያለውን ውዝፍ ኪራይ እንዲከፍል እንዲሁም ሁለተኛ ተጠሪ የውል ግንኙነት ሳይኖራቸው በቤቱ እየተገለገሉ በመሆኑ ያለአግባብ የበለፀጉበትን ኪራዩ ከቅጣቱ ጋር እንዲከፍሉና ቤቱን እንዲያስረክቡ ጠይቋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ከታዘዘ በኋላ አቤቱታ አቅርቦ መልስ እንዲያቀርብ የተፈቀደለት ቢሆንም በተደጋጋሚ ቀጠሮ መልስ ባለማቅረቡ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ግን ቀርበው ከአመልካች ጋር ውል ስሌላቸው ክሱ እንደማይመለከታቸው፣ ሁለት አመት ያለፈው ኪራይ ገንዘብ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(መ) መሰረት እንደተከፈለ እንደሚቆጠር፣ ውሉ የተደረገው ለአንድ አመት ስለሆነና ስላልታደሰ ክስ ማቅረብ እንደማይችል፣ ቤቱን የያዙት በአደራ ጠባቂነት መሆኑን እንዲሁም ስምንት አመት ሙሉ ያልታደሰ ውል መሰረት አድርጎ የቀረበው ክስ ተቀባይነት እንደሌለው ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ሁለት አመት ያለፈው ክፍያ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(መ) መሰረት እንደተከፈለ ይቆጠራል፣ ሁለት አመት ያላለፈውን ኪራይ ገንዘብ ከነቅጣቱ አንደኛ ተጠሪ ይክፈል፣ በዚሁ ጊዜ ሁለተኛ ተጠሪ በቤቱ መገልገላቸውን ስላልካዱ ገንዘቡን ይክፈሉ፣ ቤቱን ለአመልካች ያስረክቡ፣ ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን እስኪያስረክቡ በወር ብር 900.00(ዘጠኝ መቶ) ይክፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ በቅሬታውም አንደኛ ተጠሪ ውዝፍ እዳ እንዳለበት ያመነ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2025(ሀ) መሰረት ውዝፍ እዳውን ሊከፍል ይገባል እንዲሁም ከ2ኛ ተጠሪ ጋራ የኪራይ ውል የሌለውና ክሱ የቀረበው አለአግባብ በመበልፀጋቸው በመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(መ) በመጥቀስ የክፍያው ጥያቄ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ችሎቱም ይህን የሰበር አቤቱታ ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪዎች እንዲቀርቡ መጥሪያ ቢላክም ሁለተኛ ተጠሪ ብቻ በመቅረባቸው አንደኛ ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩ ታይቷል፡፡ ችሎቱም የቃል ክርክሩን ሰምቷል፡፡ መዝገቡንም እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የአመልካች የቅሬታ ነጥቦች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው አንደኛ ተጠሪ ውዝፍ የኪራይ እዳ ያለበት ለመሆኑ ስላመነ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(መ) ስር የተመለከተው የህሊና ግምት ተጠቃሚ ሊሆን አይገባም የሚል ነው፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(መ) ስር ለቤቶች ኪራይና ለእርሻ ሃብት ለሆነ የሚከፈል እዳ እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት

አመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ እንደሚቆጠር ተመልክቷል፡፡ የስር ፍ/ቤትም አመልካች ዳኝነት ከጠየቀባቸው ውዝፍ የቤት ኪራይ ገንዘብ ውስጥ ሳይጠየቁ ሁለት አመት ያለፈባቸው እንደተከፈሉ የህግ ግምት የሚወሰድባቸው ናቸው በማለት ውድቅ አድርጓቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች አንደኛ ተጠሪ ያልከፈለው ውዝፍ የቤት ኪራይ እዳ እንዳለበት አምኖ ለአመልካች የፃፈው ደብዳቤ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2025(ሀ) መሰረት ግምቱን ቀሪ ያደርገዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2025(ሀ) ባለእዳው በጽሑፍ እዳውን ያመነ እንደሆነ እዳው እንደተከፈለ መቆጠሩ ቀሪ እንደሚሆን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አንደኛ ተጠሪ እዳውን ማመን አለማመኑ መረጋገጡ ሁለት አመት ያለፈው እዳ ሊከፈል ይገባል አይገባም? የሚለውን ጭብጥ ለመፍታት አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ ባቀረበበት ወቅት አንደኛ ተጠሪ መልስ ስላላቀረበ እዳውን በማመንም ሆነ በመካድ የሰጠው መልስ የለም፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ባቀረበበት ወቅት በስር ፍ/ቤት ክስ ከቀረበ በኋላ አንደኛ ተጠሪ ያልከፈለው ውዝፍ የቤት ኪራይ ገንዘብ እንዳለበት አምኖ ገንዘቡን እንደሚከፍል ደብዳቤ ስለፃፈ ይኸው ማስረጃ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርብለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 327(3) እና 345(ለ) መሰረት ጥያቄውን ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ይግባኙን መልስ ሰጪን መጥራት ሳያስፈልግ ስለዘጋው ማስረጃዎቹንም አልተመለከተም፡፡

በመሰረቱ ከሳሽ ክሱን ሲያቀርብ አስፈላጊ ማስረጃዎችን በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ፣ ሊያቀርባቸው የማይችላቸውን ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሰረት በፍ/ቤቱ በኩል እንዲቀርቡለት መጠየቅ ይገባዋል፡፡ በመሆኑም ከሳሹ ሊያቀርባቸው ሲችል ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኛነት ያላቀረባቸውን ማስረጃዎች በክርክር ሂደት ሁሉ እያንጠባጠበ ሊያቀርብ አይችልም፡፡ የስነ-ስርዓት ህጉ አላማም ይህ አይደለም፡፡ ተጨማሪ ማስረጃዎች ሊቀርቡ የሚችሉት ክሱ በተጀመረበት ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 256 እና በይግባኝ ደረጃ ደግሞ በቁጥር 345 ስር በተመለከቱት የተወሰኑ ሁኔታዎች ስለመሆኑ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ በይግባኝ ደረጃ ማስረጃ የሚቀርብባቸው ምክንያቶችን ስንመለከት የስር ፍ/ቤት ማስረጃውን ሊቀበል ሲገባ ያለበቂ ምክንያት ያልተቀበለው ከሆነ፣ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ወይም ተገቢ መስሎ ሲታየው ማናቸውም ምክንያት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ሲያዝ ወይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 327 መሰረት ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ምስክር እንዲቀርብ ማመልከቻ ከቀረበ ወይም በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አስተያየት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ከሆነ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በይግባኝ ፍ/ቤት እንዲቀርብለት የጠየቃቸው ማስረጃዎች በስር ፍ/ቤት እንዲቀርቡ ተጠይቀው ፍ/ቤቱ አልቀበልም ያላቸው አይደሉም፡፡ ነገር ግን አመልካች አንደኛ ተጠሪ ከክስ በኋላ እዳውን በማመን የፃፈው፣ ሁለተኛ ተጠሪም እንዲሁ እዳውን ለመክፈል የፃፉት ደብዳቤዎች ሲሆኑ እነዚህ ማስረጃዎች ክስ ሲቀርብ ያልነበሩ ናቸው፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው አንደኛ ተጠሪ እዳውን ያመነ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2025(ሀ) መሰረት የህግ ግምቱ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም በማለት በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አንደኛ ተጠሪ የህግ ግምቱ ተጠቃሚ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ በትክክለኛ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ተጠሪው እዳውን በማመን ፅፏል የተባለውን ደብዳቤ ሊያስቀርበው ይገባ ነበር፡፡ በተለይ ደብዳቤው ክስ ከቀረበ በኋላ ዘግይቶ የተፃፈ በመሆኑና አመልካች ክስ ሲያቀርብ በማስረጃነት ሊያቀርበው የሚችል ባለመሆኑና ትክክለኛ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚረዳ ማስረጃ እንደመሆኑ ፍ/ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ የቀረበውን ጥያቄ ሳይመረምር ይግባኙን መሰረዙ የተጠቀሰውን የስነ-ስርዓት ህግ በአግባቡ ያላገናዘበ መሆኑን ተረድተናል፡፡

በሌላ በኩልም ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን የያዙት ከአመልካች ጋር የውል ግንኙነት ሳይኖራቸው ከውል ውጪ ነው፡፡ እሳቸውን በተመለከተም ተጠሪው በቤቱ ከመቼ ጀምሮ ይኖሩ እንደነበር እንዲሁም ውዝፍ ኪራዩን ለመክፈል ለአመልካች የፃፉት ደብዳቤ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርብ ተጠይቋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ከውል ውጪ የያዙ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(መ) ስር የተመለከተው የህግ ግምት ተጠቃሚ የሚሆኑበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ተጠሪው ክስ የቀረበባቸው ቤቱን ያለ ውል ይዘው ያለአግባብ በልፅገዋል በሚል ነው፡፡ ነገር ግን የስር ፍ/ቤት ሁለት አመት ያለፈው የኪራይ ገንዘብ እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት ውድቅ ስላደረገው ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ከመቼ ጀምሮ እንደያዙት ያረጋገጠው ነገር የለም፡፡ ተጠሪው ቤቱን ከመቼ ጀምሮ የያዙት እንደነበር የሚያስረዳው ማስረጃ በስር ፍ/ቤት ክርክር ወቅት ሊገኝ ያልቻለ መሆኑና ኪራዩን ለመክፈል የፃፉት ደብዳቤም ቢሆን ክስ ከቀረበ በኋላ ዘግይቶ የተፃፈ በመሆኑ በስር ፍ/ቤት ሊቀርብ አለመቻሉን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪው ያለአግባብ በልፅገዋል ሊባል የሚችለው ከመቼ ጀምሮ ነው የሚለውንም ለመወሰን ተጨማሪ ማስረጃ መቅረቡ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት በስር ፍ/ቤት ሊቀርቡ ያልቻሉትንና በተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርቡ የተጠየቁትን ማስረጃዎች መርምሮ ሊወስን ሲገባ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት መዝጋቱ ከፍ ሲል የተጠቀሰውን የሥነ-ሥርዓት ህጉን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን ተገንዝበናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 65544 ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርቡ የጠየቃቸው ማስረጃዎች በመቀበል ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ2 41526

ግንቦት 2 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ትራንስ አፍሪካ ትራንስፖርት አ.ማ - ጠበቃ አቶ መከተ ዳኘው-ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ሙሉ ኤሌክትሮኒክስ ኢንጂነሪንግ ኃ.የተ.የግል ማሕበር - ጠበቃ እሸቴ ደምሴ - ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የትራንስፖርት አገልግሎት ክፍያ ገንዘብን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች የክስ ይዘት ባጭሩ ተጠሪና አመልካች ለስምንት ዓመታት ያህል የስራ ግንኙነት የነበራቸው መሆኑን አመልካች ለተጠሪ ጅቡቲ ወደብ ላይ በቃል በተደረገው ውል መነሻነት ለሰጠው የክሊሪንግና የትራንዚት አገልግሎት ተገቢውን አገልግሎት ከሰጠ በኋላ በተለያዩ ጊዜያት በተጻፈለት የአገልግሎት ሒሳብ ክፍያ መጠየቂያ ደብዳቤዎችና ኢንቮይሶች ብር 332,834.27(ሦስት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ አራት ብር ከሃያ ሰባት ሳንቲም) የጠየቀ ቢሆንም ተጠሪ ፈቃደኛ አለመሆኑን አመልካች ለተጠሪ ከጅቡቲ አዲስ አበባ ድረስ የጭነት የማጓጓዝ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጥቶ አመልካች ንብረቶችን ከተረከበ በኋላ ብር 39,600.00(ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ) እንዲከፍለው አመልካች ሲጠይቀው ተጠሪ ፈቃደኛ አለመሆኑን ገልፆ ለክሱ መሰረት የሆነው ገንዘብ ብር 332,834.27(ሦስት መቶ ሠላሣ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ አራት ብር ከሃያ ሰባት ሣንቲም) ከተጠየቀበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድና ከተለያዩ ወጪና ኪሳራዎች ጋረ እንዲከፈለው ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሠጠው መልስም አመልካች የክሊሪንግና የትራንዚት አገልግሎት ሰጥቻለሁ በማለት እንዲከፈለው ያቀረበው ገንዘብ ሕጋዊና ታዓማኒ ሰነድ ወይም ደረሰኝ ያልቀረበበት መሆኑን አመልካች ለማስረጃነት የዘረዘራቸው ኢንቮይስ (የክፍያ ሰነድ) ሁሉ ራሱ ባዘጋጀው ወረቀቶችና ጽሑፎች የተዘጋጀ መሆኑን የጭነት ማጓጓዣ ብር 39,600.00(ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ብር) በቼክ ቁጥር BB430772 በደረሠኝ ቁጥር 03325 ለአመልካች የከፈለው መሆኑን በመጥቀስ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል ውል መኖሩን ካረጋገጠ በኋላ ተጠሪ ለአመልካች ብር 38,808.00 (ሰላሳ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር) የከፈለው በመሆኑ ይኸው የገንዘብ መጠን ተቀንሶ ቀሪውን ብር 293,234.27(ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ አራት ብር ከሃያ ሰባት ሳንቲም) ግን ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ አለቀ ድረስ ዘጠኝ ከመቶ ወለድና ከተለያዩ ወጪና ኪሳራዎች ጋር እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች የስር ፍ/ቤት ብር 38,808.00(ሰላሳ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር) ለተጠሪ እንዲከፈል ሲል በሰጠው የውሳኔ ክፍል ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይኸው ፍርድ ቤት አመልካች አከራካሪው ብር ተከፍሎበታል የተባለውን ሰነድ ሐሰተኛ መሆኑን የሚያስተባብል ማስረጃ አላቀረበም የሚል ምክንያት ይዞ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የውሳኔ ክፍል ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሕዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ብር 38,808.00 (ሰላሳ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር) ተጠሪ ለአመልካች ስለመክፈሉ ተረጋግጧል የተባለበት ሰነድ ለጉዳዩ

አግባብነት የሌለው እና ሊታመን የማይችል በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም ይገባል ሲሉ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም አከራካሪው የሆነው ገንዘብ ብር 38,808.00(ሰላሳ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር) አመልካች አስቀድሞ ተከፍሎታል የሚለው የስር ፍርድ ቤት መደምደሚያ አግባብነት ባለው ማስረጃ የተደገፈ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ የተጠሪ ጠበቃ ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ የአመልካች ክርክር በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ገልፀው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ መስከረም 21 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ አራት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈፀመም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክስ ሲመሰርት አከራካሪውን ገንዘብ ለመጠየቅ መሰረት ያደረገው የተጠሪን ደረቅ ጭነት አጓጉዞ ያልተከፈለው የትራንስፖርት ገንዘብ ክፍያ መኖሩን ሲሆን ተጠሪን ገንዘቡን ለአመልካች መክፈሉን ገልጾ ይህንኑ ክስ ለማስተባበል ደግሞ የገንዘብ መክፈያ ሰነድና ቼክ ለማስረጃነት ማቅረቡን ሲሆን አመልካች የተጠሪ ማስረጃዎች ሐሰተኛ ናቸው በማለት ተከራክሮም ይህንኑ ክርክር የሚደግፍለት ማስረጃ ያለማቅረቡን የበታች ፍርድ ቤቶች በውሳኔአቸው ላይ በግልፅ ያሰፈሩት ነጥብ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች በሰበር ደረጃ የሚከራከረውም ክፍያው መፈፀሙን ያሳያል የተባለው ሰነድ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነበር በማለት ሲሆን ይህንኑ ለማስረዳት በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ማስረጃ ያቀረበው ግልጽ ማስረጃ ስለመኖሩ ግን ያረጋገጠው ሁኔታ አለመኖሩን ተመልክተናል፡፡ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ የአመልካች የሰበር ክርክር በማስረጃው ምዘና ላይ የሚያተኩር መሆኑን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡ ተጠሪ ክፍያውን ፈፅሟል? ወይስ አልፈጸመም? እና ክፍያው የተፈፀመው አመልካች ለተጠሪ ለሠጠው አገልግሎትና ዳኝነት ለጠየቀበት ጉዳይ ወይስ ለሌላ? የሚለው ጉዳይ የፍሬ ነገር ክርክር እንጂ የሕግ ክርክር የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡ በዚህ ረገድ ደግሞ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመመርመር ተገቢ ነው ያሉትን የየራሳቸውን ምዘና አድርገዋል ተገቢ ነው ያሉትንም ክብደት ሰጥተዋል፡፡ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ደግሞ በዚህ ችሎት የሚታረምበት የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሠጡት ውሳኔ የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት እንጂ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት ጥያቄ መመዘኛን የሚያሟላ ሆኖ ስላላገኘነው የአመልካችን ክርክርን አልተቀበልነውም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 59208 ጥቅምት 04 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 61553 ጥቅምት 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 52752
ሰኔ 16 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** 1ኛ ከድር ሐጂ ሁሴን
2ኛ ሉሲ ኮሌጅ አ.ማ } አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** 1ኛ አቶ አሚን ዑስማን
2ኛ ወ/ሮ ኑሪያ ጀማል } ጠበቃ ደረጀ ኢታቻ ቀረቡ

መዝገቡን በአዳሪ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በተከራካሪ ወገኖች መካከል የነበረውን የፍርድ ቤት መሰረት በመተው እርቅ ተደርጎ ለፍርድ ቀርቦ ከተመዘገበ በኋላ ያለውን ሕጋዊ ውጤት የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ አመጣጥም በሚከተለው መልኩ የተመዘገበው ነው፡፡

የአሁኖቹ ተጠሪዎች እና አመልካቾች ተጠሪዎች በሉሲ ኮሌጅ አ.ማ ውስጥ ያላቸውን የባለአክሲዮንነት መብት በተመለከተ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ላይ የይግባኝ ክርክር የነበራቸው ሲሆን ክርክሩ በዚህ ደረጃ ላይ እያለ ግራ ቀኙ በመካከላቸው ያለውን አለመግባባት ከፍርድ ቤት ውጪ ለመጨረስ ተስማምተዋል፡፡ በዚህም መሰረት የካቲት 30 ቀን 2000 ዓ.ም በተፈረመ የእርቅ ስምምነት አድርገው በስምምነቱ መሰረትም በፍርድ ቤት እንዲፀድቅ በመገለጹ ስምምነቱ ጉዳዩን በይግባኝ ይመለከተው ለነበረው ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ ፍርድ ቤቱም የእርቅ ስምምነቱን ግራ ቀኙ ባሉበት ተመልክቶና መርምሮ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 277(1)(2) መሰረት መዝግቦት በእርቁ መሰረት እንዲፈፀም ዘንድ ለስር የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልኮለታል፡፡ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፀደቀውን ስምምነት እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍርድ ቤትም ከተመለከተ በኋላ ተጠሪዎች በአመልካቾች ላይ የተከፈተውን የወንጀል መዝገብ ያላዘጉ ስለሆነ በእርቁ መሰረት ሊፈጸም የሚችል አይደለም የሚል ምክንያት በመያዝ የእርቅ ይፈፀምልኝ ጥያቄን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጓል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ተጠሪዎች የወንጀል መዝገብ ለማዘጋት እርቅ አድርገዋል ለማለት እንደማይቻል ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችን ዘርዝሮና እርቅ በተቻለ መጠን እንዲፈፀም መደረግ እንዳለበት በመተንተን የስር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በእርቁ መሰረት እንዲያስፈፅም ጉዳዩን መልሶ ልኮለታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት የሰበር አቤቱታ በክልሉ የሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ እርቅ ውል እንደመሆኑ መጠን ስለውል አመሰራረትና አተረጓጎም የተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ መታየት እያለበት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ተጠሪዎች የወንጀል መዝገብ ካለማዘጋታቸው ጋር ሳያገናዝብ የሚፈፀም ሕጋዊ እርቅ አለ በማለት መወሰኑ

ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነ እርቅ ስምምነት ከአንደኛው ተጠሪ ግዴታ አንጻር ሊፈጸም የማይችል ለህግ ተቃራኒ የሆነ ስምምነት ነው ከተባለ አመልካቾች እንደስምምነቱ ለመፈፀም ተነጻጻሪ ግዴታ ይኖርባቸዋል ወይስ አይኖርባቸውም? የሚለውን ነጥብ ለማየት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ተብሎ በመታዘዙ ተጠሪዎች እንዲቀርቡ ተደርጎአል፡፡ የተጠሪ ጠበቃ ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው ውሳኔው ሊፀና ይገባል ሲሉ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡ አመልካቾችም ሰኔ 09 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ ግልባጭ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ጉዳይ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ግራ ቀኙ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ይታይ የነበረውን ክርክር በመተው ጉዳዩን በእርቅ ጨርሰው የእርቅ ስምምነቱ ሰነድ ለፍርድ ቤቱ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ሰነዱን ተቀብሎ ከመረመረ በኋላ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አይደለም በሚል ምክንያት መመዝገቡንና በእርቁ መሠረት እንዲፈጸምም ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን የላከለት መሆኑን በእርቁ ሰነድ በአንቀፅ 4 ስር ደግሞ የተጠሪዎች ግዴታ በፍርድ ቤቶች ያስከፈቷቸውንና የከፈቷቸውን የፍትሐብሔር እና የሌሎች ክርክሮችን ማዘጋት ተብሎ መቀመጡን አመልካቾች ተጠሪዎች በዚህ የእርቅ ሰነዱ አንቀፅ መሰረት ያለባቸው ግዴታ የፍትሐብሔርና የወንጀል መዛግብትን ማዘጋት መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን፣ የወንጀል መዝገብ በተጠሪዎች አቤቱታ ባይሆንም ጉዳዩን ሲመለከቱ በነበሩት ፍርድ ቤቶች የሚያስከስስ አይደለም ተብሎ መዘጋቱ በአሁኑ የክርክር ደረጃ መረጋገጡን ነው፡፡

በመሰረቱ በፍርድ ቤት ጉዳዩ እየታየ ባለበት ሁኔታ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በእርቅ ጨርሰው ሲመጡና ፍርድ ቤቱ ይህንኑ እንዲመዘገብላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ፍርድ ቤት የእርቅ ስምምነቱን ሕጋዊነትና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆን መርምሮ ተገቢውን ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችልበት ጉዳይ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 277 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ከመዘገበው እርቁ እንደፍርድ ቤት ውሳኔ ሊታይ የሚችል ስለመሆኑንም ከተጠቀሰው ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት ያስገነዝባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካቾች የእርቅ ስምምነቱን ማድረጋቸውንና በፍርድ ቤት መፅደቁን እንዲሁም ይኸው በፍርድ ቤት የፀደቀው የእርቅ ስምምነት ቅሬታ ያሳደረበት ወገን ኖሮ ቅሬታውን ለበላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ እርቁን አለማስለወጡን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት የእርቅ ስምምነቱ በፍርድ ቤት ያሉትን የፍትሐብሔር ክርክሮችን ማዘጋት ብቻ ሳይሆን የወንጀል መዛግብትን ጭምር ለማዘጋት በመሆኑ እና የወንጀል መዛግብትን ደግሞ ተጠሪዎች ያላዘጉ በመሆኑ እርቁ የአመልካቾች ፍላጎትና ሐሳብ መሰረት ባደረገ መልኩ ተፈጽሟል ለማለት አይቻልም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የእርቁ ሰነድ ስለወንጀል መዛግብት መዘጋት እንደቅድመ ሁኔታ የማያስቀምጥ መሆኑን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያረጋገጠው ከመሆኑም በላይ ተደርጓል የሚል ድምዳሜ ቢኖር እንኳ ወንጀሎቹ በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚዘጉ ባለመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የወንጀል መዛግብት የተባሉት ባሁኑ ጊዜ ጉዳዩ አያስከስስም በሚል ምክንያት በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት የተዘጉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የወንጀል መዛግብት አለመዘጋት ለእርቁ ሕጋዊ አለመሆን ምክንያት ሊሆን ይገባል በሚል የቀረበው የአመልካቾች ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የእርቅ ስምምነቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 277 አግባብ የፀደቀ በመሆኑ የማይፈፀምበት ሕጋዊ ምክንያት የለውም፡፡ በዚህም ምክንያት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፤ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 81625 ጥር 24 ቀን 2002 ዓ.ም የተሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት መጋቢት 08 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 45247

ሰኔ 17 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አቶ ደጀኔ በላቸው - ከጠበቃ ዳኜ አዲሴ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ነስሩ አወል- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶታል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውል ይፈፀምልኝ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፤ተጠሪ በብር 149,000.00(አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ ብር) የደረቅ ጭነት ማመላለሻ መኪና ሸጠውላቸው በእለቱ ብር 145,000.00(አንድ መቶ አርባ አምስት ሺህ ብር) ተቀብለው ሊብሬውንና መኪናውን ያስረከቡ መሆኑን፣ቀሪውን ገንዘብ ስም ሃብቱን ሲያዛውሩላቸው አመልካች ለተጠሪ ለመክፈል እንደተስማሙ፣ተጠሪም መኪናውን ከእዳና እገዳ ነፃ በማድረግ ስመ ሃብቱን ለማዛወር በውሉ ላይ በግልጽ ግዴታ መግባታቸውን፣ሆኖም ተጠሪ በገቡት ግዴታ መሰረት መኪናውን ከእዳና እገዳ ነፃ ለማድረግ እና ስመ ሃብቱንም ለማዛወር ፈቃደኛ ሊሆኑ አለመቻላቸውን ገልጸው በውሉ መሰረት መኪናውን ከእዳና እገዳ ነፃ አድርገው ስመ ሃብቱን እንዲያዛውሩላቸው እንዲሁም የገደብ ገንዘብ ብር 10,000.00(አስር ሺህ ብር) እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ በመካከላቸው የመኪና ሽያጭ ውል መደረጉንና በክሱ ላይ የተገለጸውን ገንዘብ በመቀበል መኪናውንና ሊብሬውን ለአመልካች ማስረከባቸውን እንዲሁም በውሉ ላይ መኪናውን ከእዳና እገዳ ነፃ ለማድረግ እና ስመ ሐብቱንም ለማዛወር ግዴታ መግባታቸውን ሳይክዱ መኪናውን ከእዳና እገዳ ነፃ ሊያደርጉት ያልቻሉት በወንጀል ጉዳይ ዋስ የሆኑላቸው ግለሰብ በመሰወራቸው መሆኑን፣ስመ ሃብቱንም የማዛወር ስልጣን የሌላ አካል እንጂ የተጠሪ አለመሆኑን፣እንዲሁም ውሉ ፈራሽ ነው ያልተባለ በመሆኑም የገደብ መቀጫ የሚጠየቁበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ውሉ መኖሩን ከአረጋገጠ በኂላ ተጠሪን አመልካች ሊጠየቁ የሚገባው ውሉ እንዲፈርስ እንጂ እዳና እገዳውን ነፃ እንዲያደርጉ አይደለም፣ስመ ሃብቱን የማዛወር ስልጣንም የተጠሪ ሳይሆን በሕጉ አግባብ ስልጣን የተሰጠው አካል ነው የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ ክሱ የክስ ምክንያት የለውም ሲል ውድቅ አድርጉታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸው ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሚያዝያ 16 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ጥሪ ተደርጉላቸው ቀርበው የጽሑፍ መልስ እንዲሰጡ በችሎት ተነግሯቸው የፁሑፍ መልሳቸውን ባለማቅረባቸው የጹሑፍ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም ለስመ ንብረት ዝውውር ሲባል በተሸጠው መኪና ላይ አስቀድሞ የተሰጠውን የእግድ ትእዛዝ ሻጩ እገዳ እንደሚያስነሳ በውሉ ግዴታ መግባቱ ከተረጋገጠ፣ይኸው ግዴታ እንዲፈጸም ክስ ማቅረብ በጉዳዩ ላይ የክስ ምክንያት የለውም ለማለት ይቻላል? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሲሆን ሌሎች ነጥቦች በዚሁ ነጥብ ስር የሚሸፈኑ ሆነው አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት የመነጨው ከመኪና ሽያጭ ውል መሆኑን፣ውሉ ስለመኖሩና በይዘቱ ላይ ግራ ቀኙ ያልተካካዱ መሆኑን፣ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኪና በገዢው ስም ሊዛወር ያልቻለው ተጠሪው ለሌላ ግለሰብ በወንጀል ጉዳይ በብር 10,000.00(አስር ሺህ) በፍርድ ቤት ዋስ ስለሆኑ እግድ በመሰጠቱ መሆኑን፣ እግዱም ለመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ተላልፎ ከመኪናው ማህደር ጋር ስለመያያዙ ተጠሪ ያልካዱት ፍሬ ነገር መሆኑ ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ በፍርድ ቤት የቀረበ ጉዳይ የክስ ምክንያት አለው ብሎ ለመወሰን የሚቻለው በክሱ ላይ የተገለፀው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሹ የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ሕግ ይፈቅድለታል ወይ? የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ፍርድ ቤቱ አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት የሚችል የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ በዚህ ረገድ የተፃፉት የማብራሪያ ፁሑፎች ያሳያሉ፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም በግራ ቀኙ መካከል የመኪና ሽያጭ ውል መኖሩና ተጠሪ መኪናውን ከእዳና እገዳ ነፃ በማድረግ ስመ ሐብቱን ለአመልካች ለማዛወር ግዴታ የገቡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በክሳቸው የገለፁትም ይህንኑ ፍሬ ነገርና ተጠሪ በገቡት ግዴታ መሰረት ውሉን ያልፈፀሙ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ፍሬ ነገር ደግሞ በተጠሪ በኩል ማስተባበያ ያልቀረበበት የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ መኪናው ላይ የተላለፈውን የእግድ ትእዛዝ እንዲያስነሱ ጥያቄ ማቅረባቸው ደግሞ በሕግ የተፈቀደ ነው፡፡ ማንም ሰው በገባው ዋስትና መሰረት በንብረቱ ላይ እግድ ተሰጥቶ ከሆነ ንብረቱን ለሌላ ሰው በሽያጭ ሲያስተላልፍ ገዢው በንብረቱ ላይ የሚያገኘውን የባለቤትነት መብት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲችል እግድን የማስነሳት ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ስለክስ ምክንያት አጠቃላይ መንፈስ እና ይዘት በሕጉ ላይ የተመለተውን መመዘኛን ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ክሱ የክስ ምክንያት አለው ከተባለ አመልካች ያላቸውን መፍትሔ ይህ ችሎት በዚሁ የክርክር ደረጃ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ተጠሪ በመኪናው ላይ ያሰጡትን እግድ የማያስነሱበት ሕጋዊ ምክንያት ያላቸው ስለመሆኑ አላስረዱም፡፡ ተጠሪ መኪናቸውን ከሸጡ ደግሞ የመኪናውን ባለሃብትነት ለገዢው ለማዛወር ሕጋዊ ግዴታ የአለባቸው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2273/2/ ድንጋጌ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ የመኪናው ስመ ሃብት ሊዛወር የሚችለው ተጠሪ በመኪናው ላይ ያሰጡትን እግድ ሲያስነሱ ነው፡፡ ተጠሪ ስመ ሃብቱን ለማዛወር ስልጣን የላቸውም ቢባል እንኳ በአዋጅ ቁጥር 465/97 አንቀጽ 3/2/ ድንጋጌ መሰረት ሥልጣን ያለው አካል ተግባርን ሊወጣ የሚችለው በፍርድ ቤት የተሰጠው እግድ መነሳቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ስለሆነም በሕጉ አግባብ ስልጣን የተሰጠው አካል ስመ ሃብቱን ለማዛወር እንዲችል ተጠሪ የፍርድ ቤቱ የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳ የበኩላቸውን ግዴታ ሊወጡ የማይገደዱበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ ስለውል አፈፃፀም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1740 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተመለከቱትን ደንቦችንም ሆነ የግራ ቀኙን የውል ይዘት ባግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚሁም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13195 ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 73431 ጥር 19 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ የክስ ምክንያት አለው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ በገቡት ውል መሰረት በአከራካሪው መኪና ላይ የተላለፈውን እግድ በማስነሳት የሚመለከተው አካል ስመ ሃብቱን ለአመልካች እንዲያዛውር እንዲያደርጉ ብለናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ውሳኔ እንዲያስፈጽምም የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍለት ብለናል፡፡
5. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 49857

ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ ፋንታ - ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ኪዳነ ቀረበ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ በላይነሽ ወ/ኪዳን - ወኪል ተሾመ አባይ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት እና የቦታ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ ናት፡፡ ተጠሪ ክስ የመሰረተችው እማሆይ ፀሃይነሽ በተባለች ሰው እና በአሁንዋ አመልካች ላይ ሆኖ አመልካች ባለመቅረብዋ ክርክሩ በሌለችበት ተሰምቶ ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡ አከራካሪ ከነበሩት ጭብጦች አንዱ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በሚል በእማሆይ ፀሃይነሽ የተነሳው መቃወሚያ ስለሆነ የወረዳው ፍ/ቤት መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ በጉዳዩ ሥረ-ነገር ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ እማሆይ ፀሃይነሽ ውሳኔውን በመቃወም ይግባኝ አቅርባ ተቀባይነት እንዳላገኘ እና እስከ ሰበር ድረስም አቤቱታ አቅርባ ውድቅ እንደሆነባት በመዝገቡ ተመልክቶአል፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በኂላ መዝገቡ(የወረዳው ፍ/ቤት) የተንቀሳቀሰው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78 መሰረት አቤቱታ በማቅረብዋ ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም የአመልካችን ተቀብሎ ግራ ቀኝ ወገኖችን አከራክሮአል፡፡ በመቀጠልም የአመልካችና የይርጋ መቃወሚያ በመቀበል የቀድሞው ውሳኔውን ለውጦአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ በየደረጃው ለበላይ ፍ/ቤቶች ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ በማቅረብዋ ጉዳዩ እንደገና ታይቶአል፡፡ ጉዳዩን በመጨረሻ የሰማው የትግራይ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ ቀደም ሲል ታይቶ በውሳኔ እልባት ያገኘ በመሆኑ አመልካች ያቀረበችው የይርጋ መቃወሚያ በድጋሚ የሚታይበት አግባብ የለም በማለት በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ በሥር የሰበር ችሎት በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የምትልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታዋን አቅርባለች፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች ያቀረበችው የይርጋ መቃወሚያ ቀደም ሲል አንደኛ ተከሣሽ የነበረችው የአመልካች እናት አንስታው ውድቅ ሆኖአል በማለት ተቀባይነት ማጣቱ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካች እና ተጠሪ ያስሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው አመልካች በዚህ ጉዳይ ተከራካሪ የሆነችው ተጠሪ ክስ ስላቀረበችበት ነው፡፡ በእርግጥ ክሱ በተሰማበት ጊዜ ልትቀርብ ባለመቻልዋ ጉዳዩ በሌለችበት ተሰምቶ ውሳኔ ተሰጥቶ እንደነበረ ግልጽ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 የተመለከተውን ድንጋጌ በመጠቀም ወደክርክሩ እንድትገባ ተፈቅዶላታል፡፡ በዚህ የሥነ-ሥርአት ሕግ ድንጋጌ እንደተመለከተው አቤቱታ አቅራቢው ወገን ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ የቀድሞው ውሳኔ ይነሳለታል፡፡ በዚህም ክርክሩ እንደና ይሰማል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ክርክሩ እንደገና ከተሰማ በኂላ የቀድሞው ውሳኔ ሊለወጥ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል ማለትም ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች ለቀረበባት ክስ በሰጠችው መልስ ያዋጣኛል ያለችውን ክርክር አቅርባለች የተከሰሰችው በስምዋ እንደመሆኑ መጠን መከራከር የምትችለው(መከራከር ያለባት) እሷን (በግልዋ) የሚመለከት የመከራከሪያ ነጥብ በማንሳት ነው፡፡ የክርክር አቀራረብ ስልትዋም ሆነ የማስረጃ አቀራረብዋም እንደዚሁ በግልዋ ባቀረበችው ክርክር የሚወሰን ነው፡፡ ይህም ማለት ከስዋ ጋር ተከሳ የነበረችው ሰው ያነሳችው ክርክር የስዋም የመከራከሪያ ነጥብ እንደሆነ ተደርጐ የሚወሰድበት አግባብ የለም፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበችውን የይርጋ መቃወሚያ መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መታየት ያለበት ከዚህ አንፃር ነው፡፡ የሥር አንደኛ ተከሣሽ የነበረችው እማሆይ ፀሃይነሽ ያቀረበችውን የይርጋ መቃወሚያ መሰረት በማድረግ ከተሰጠው ውሳኔ ጋር የሚያያዝበት አግባብ የለም፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለጸው አመልካች የክርክሩ ተካፋይ የሆነችው በግልዋ በቀረበባት ክስ ምክንያት በመሆኑ ክሱን መከላከል የምትችለው የግልዋ የመከራከሪያ ነጥብ እና የመከላከያ ማስረጃ በማቅረብ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳም ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ ከተመለከተው ድንጋጌ አንፃር የሚታይ አይደለም፡፡ የሥር ሰበር ችሎት የአመልካች የይርጋ መቃወሚያ እማሆይ ፀሃይነሽ ባቀረበችው የይርጋ መቃወሚያ በተሰጠው ውሳኔ እልባት አግኝቶአል በማለት ያስቀመጠው ትችም ሆነ የደረሰበት መደምደሚያ ከሕጉ አተረጓጐም አንፃር ሲታይ መሰረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ የይርጋው መቃወሚያ በዚህ አግባብ ታይቶ ከመወሰኑ በፊት ወደ ጉዳዩ ሥረ-ነገር ገብቶ መወሰኑም ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ. 30402 መስከረም 29 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡

2. የሰበር ችሎቱ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል አከራካሪ ሆኖ የቀረበው የይርጋ መቃወሚያ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖችን እንደገና ካከራከረ በኂላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 48632

ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አቶ ሙልሳ በየቻ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** አቶ ደበሌ በየቻ - በሌሉበት

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት የተሰማ ክስ ላይ ማስረጃ ሳይሰማ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

ሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ ነበር፡፡ የተጠሪ ክስ የነበረው አመልካች በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል ግምት ብር ሦስት ሺህ አንድ መቶ አሥራ አምስት ብር እንዲከፍል እንዲወሰን የሚል ነበር፡፡

አመልካች (ሥር ተከሳሽ) ቀርቦ ባለመከራከሩ የሥር ፍ/ቤት በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ በከፍተኛው ፍ/ቤት እና በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፀንቷል፡፡

አመልካች በውሳኔው የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል በማለት ነሐሴ 28 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው አቤቱታ የቀረበው ክስ በከሳሽ ማስረጃ ሳይረጋገጥ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም ይህንኑ ለመመርመር ተጠሪ እንዲቀርብ ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም መጥሪያ ተቀብሎ ባለመቅረቡ በሌለበት ጉዳዩ ተሰምቷል፡፡ እኛም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው አመልካች በተጠሪ ንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል መነሻ ተጠሪ ይገባኛል ያለውን የካሣ መጠን ገምቶ ክስ ያቀረበ ስለመሆኑ ነው፡፡ አመልካች (ሥር ተከሳሽ) ቀርቦ ባለመከራከሩ ጉዳዩ በሌለበት የተወሰነ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት የካሣውን መጠን እንደከሳሽ ጥያቄ የወሰነው ተከሳሽ ቀርቦ አልካደም በሚል ነው፡፡ ይህ አካሄድ ከሥነ-ሥርዓት አንፃር በአግባቡ ስለመሆኑ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 235(2) የሚደነግገው በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ ይቆጠራል የሚል ሲሆን ይህ ተፈጻሚነቱ ተከሳሽ ቀርቦ ክርክሩን ባሰማ ጊዜ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 83 እንደተመለከተው በመርህ ደረጃ በተከሳሽ በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ የሚቆጠር ቢሆንም የካሣ ጥያቄ ላይ ግን ይህ ግምት ተፈጻሚ ሊሆን እንደማይችል ነው፡፡ ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ አመልካች ቀርቦ ያልተከራከረ ቢሆንም የዳኝነት ጥያቄው የካሣ ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን ቀርቦ እንኳ ቢከራከር ፍ/ቤቱ በማስረጃ ጉዳዩን ማጣራት እንዳለበት አመላካች ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ እንደ ክሱ ያስረዳልኛል ያለውን ማስረጃ ሰምቶ መወሰን ሲገባው ተከሳሽ ቀርቦ አልተከራከረም ወይም አልካደም በሚል ብቻ ውሳኔ መስጠቱ ከተጠየቀው የዳኝነት ጥያቄ እና ከሥነ ሥርዓት ሕጉ የሙግት አመራር መርህ አኳያ ጉድለት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም ይህ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የሜታ ሮቢ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 05257 የሰበር ውሳኔ እና የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 27266 የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 88090 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሜታ ሮቢ ወረዳ ፍ/ቤት የሥር ከሳሽ (ተጠሪን) ማስረጃ ሰምቶ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መዝገቡን መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 49660

ሰኔ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡-1. መንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ት/ቤት } ወኪል ይሁን አየነው - ቀረቡ

2. መንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ጽ/ቤት

**ተጠሪ፡-** መምህር ሲሳይ ደጀኔ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሠረት አድርጐ የተደረገ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካቾች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከየካቲት 27 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር የመሰረቱት የስራ ውል ከሕግ ውጪ ከመጋቢት 22 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ መቋረጡን ገልጸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪን መቅጠሩን ሳይክድ ራሱ ያላሰናበታቸው መሆኑን ገልጾ ልጠየቅ አይገባም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን የተከራከረ ሲሆን አንደኛ አመልካች ደግሞ ተጠሪ የስራ ውልና ቅጥር የፈፀሙት ከሁለተኛ አመልካች ጋር በመሆኑ ክሱ እንደማይመለከተው በመጀመሪያ መቃወሚያነት ጠቅሶ የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም ስንብቱ የተከናወነው ተጠሪ ከስራ ገበታቸው በመቅረታቸው፣የስራ ሰዓት ባለማክበራቸው እንዲሁም ያለፈቃድ በሌላ ቦታ እያስተማሩ እንደሚገኙ ገልጾ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተክራክሯል፡፡ የስር

ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ከሰማ በኋላ በአመልካቾች በኩል የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ውድቅ አድርጐ በፍሬ ነገርም ማስረጃ ያለማቅረባቸውን ጠቅሶ አመልካቾችን ለክሱ ኃላፊ አድርጐ ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካቾች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች ነገረ ፈጅ ጥቅምት 09 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ከስራ ከአምስት ተከትታይ የስራ ቀናት በላይ በመቅረታቸው ነው በሚል ገልፀንና ማስረጃም ቆጥረን እያለ ማስረጃዎቻችን ሳይታዩና ሳይሰሙ ማስረጃዎችን አላቀረቡም በሚል ምክንያት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካቾች የመከላከያ ማስረጃዎች ሳይሰሙ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪ ቀርበው ጥር 26 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የአመልካቾችን የሰበር ቅሬታ ነጥቦች ተገቢ አለመሆን ያሳያሉ ያሏቸውን ነጥቦችን በመዘርዘር የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የአመልካቾች ነገረፈጅም የካቲት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ተጠሪ የስራ ውላቸው ያላግባብ የተቋረጠ መሆኑን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ላቀረቡት ክስ አመልካቾች ስንብቱ ሕጋዊ ነው የሚሉበትን ምክንያት ጠቅሰው ለዚህም የሰነድና የሰው ምስክሮች ያሏቸው መሆኑን በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ማቅረባቸውን የስር ፍርድ ቤትን ዋና መዝገብ በማስቀረብ ተመልክተናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው አንደኛ አመልካች ተጠሪ ከስራ የቀሩ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው ክስ የመከላከል ሕጋዊ መብት ያለው ሲሆን ፍርድ ቤት ይህንኑ መብቱን ሲያልፍ የሚገባው ተከራካሪ ወገን የቆጠረው ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን እርግጠኛ ሲሆን ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 223፣234፣137፣249 እና 256 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ሊሰጥ የሚገባው የማስረጃ አቀራረብ ሥርአት ምዘና ሥነ-ሥርአቱ በሚያስቀምጠው መንገድ ተከናውኖ መሆኑን እነዚህ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ተከራካሪ ወገን ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ማስረጃ ቆጥሮ እያለ ማስረጃ ሳይሰማ ፍርድ መስጠት የመከራከር መብቱን የሚያጣብብ ነው፣ ውሳኔውም ሕጋዊ ሥርአቱን ተከትሎ ተሰጥቷል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካቾች ከተጠሪ ጋር የተመሰረተው የስራ ውል የተቋረጠበትን ምክንያት በመከላከያ መልስ ማመልከቻው ላይ ከመግለፃቸውም በተጨማሪ ይህንኑ ፍሬ ነገር ለማስረዳት የሰነድና የሰው ማስረጃዎቻቸውን በመከላከያ ማስረጃው መግለጫ ዝርዝር ላይ ጠቅሰው እያለ እና የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዘው ከማቅረባቸውም በላይ የቆጠሯቸውን የሰው ምስክሮችን ለማቅረብ ያልቻሉ መሆኑ ሳይረጋገጥ የስር ፍርድ ቤት ማስረጃ በደፈናው ማስረጃ አላቀረቡም በሚል ምክንያት ማለፉ ስለማስረጃ አቀራረብ ሥርአት የተመለከቱትን የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ድንጋጌዎችን መሰረት ያላደረገ ነው፡፡ አንድ አሰሪ የስራ ውልን ለማቋረጥ ምክንያት ነው ብሎ በስንብቱ ደብዳቤ ላይ የገለፀውን ምክንያት ለማስረዳት የቆጠረውና አግባብነት ያለው ማስረጃ ሊሰማለትና ሊመዘንለት ይገባል፡፡ የኸው ሥርአት ሳይከናወን የሚሰጥ ፍርድ የተሟላ አካሄድ ተከትሎ የተሰጠ ነው ሊባል የማይችልና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በሥነ-ሥርአቱ መሰረት ማስረጃዎቻቸውን ዘርዝረው አቅርበው እያለ የቆጠሯቸው የሰነድና የሰው ምስክሮች ሳይታዩና ሳይሰሙ ማስረጃ አላቀረቡም በሚል የተሰጠው ውሳኔ የአመልካቾችን የመከላከል ሕጋዊ መብት ያጣበበ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 29808 ሐምሌ 06 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 82545 ነሐሴ 19 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን ሰምቶ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## <u>ት እ ዛ ዝ</u>

በዚህ ችሎት ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 52525

ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጉስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ የትምወርቅ ሰብስቤ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሸዋረጋ ደመቀ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የአመልካች የክስ ምክንያት ቀደም ሲል ውሳኔ የተሰጠበት ነው በማለት የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ለመሆኑ ለመመርመር ነው፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር የእርሻ መሬት ይዞታን የሚመለከት ነው፡፡ ከሳሽ አመልካች ሆና ተጠሪ ተከሳሽ ነበር፡፡ ተጠሪ ያለአግባብ የያዘውን የእርሻ መሬት እንዲለቅልኝ ስትል አመልካች በሽርካ ወረዳ ፍ/ቤት ክስ ያቀረበች ሲሆን ተጠሪ በተመሳሳይ ጉዳይ በመ/ቁ. 345/97 በ14/6/2001 ዓ.ም ውሳኔ ተሰጥቷል ሲል መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን የወረዳው ፍ/ቤት ቀደም ሲል በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ ያልተሰጠ እና ይልቁንም ከሳሽ ማስረጃ አሟልታ ክስ እንድታቀርብ መብት ተጠብቆላት መዝገቡ የተዘጋ መሆኑን ጠቅሶ መቃወሚያውን ውድቅ ማድረጉን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ማስረጃ ሰምቶ ተጠሪውን መሬት ለአመልካች እንዲለቅ ወስኗል፡፡ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ አጽንቷል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኂላ በጉዳዩ ላይ ቀደም ሲል ውሳኔ ተሰጥቶበታል ይህ ከሆነ ደግሞ በድጋሚ ሊታይ አይገባም (res judicata) በሚል የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሯል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ ተጠሪም በሰጠው መልስ ቀድሞ ለአመልካች የተጠበቀ መብት የለም መዝገቡ በውሳኔ ተዘግቷል በማለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና አመልክቷል፡፡

እኛም ከፍ ሲል ከተመለከተው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ የሻረው ጉዳዩ ቀድሞ ውሳኔ ያገኘ ነው በሚል ምክንያት መሆኑን ከውሳኔው ተረድተናል፡፡

ከሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ይዘት መረዳት የቻልነው አመልካች ቀደም ሲል ያቀረበችው ክስ በፍርድ ቤቱ ከተሰማ በኂላ የአመልካች ክስ ግልጽነት የሚጐድለውና ማስረጃም ያልተሟላ በመሆኑ ማስረጃዋን አሟልታ ክስ እንድታቀርብ መብት ተጠብቆላት መዝገቡ የተዘጋ ስለመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በፍሬ ጉዳዩ ላይ የተሰጠ ውሳኔ አለ ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ ሙሉ በሙሉ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ፍርድ አልሰጠም፡፡ ይልቁንም ማስረጃ አሟልተሽ ማቅረብ ትችያለሽ የሚል ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ይህ አካሄድ በመርህ ደረጃ አግባብነት ያለው ነው ባይሰኝም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 91/4/ በተደነገገው አግባብ ለጉዳዩ ፍትሐዊ ውሳኔ አሰጣጥ ይበጃል ብሎ ካመነ ፍ/ቤቱ ማሻሻያ እንዲደረግ ማዘዝ ይችላል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ከዚህ ይልቅ አመልካች ማስረጃ አሟልታ ክስ እንድታቀርብ በማድረጉ ይህ ውሳኔው ሥነ-ሥርአታዊ አይደለም የሚለው ወገን በይግባኝ አስካላሻረ ጊዜ ድረስ ውሳኔውን መሰረት በማድረግ አዲስ ክስ መቅረቡ ተገቢ አይደለም ሊባል አይገባም፡፡

ከዚህ ሌላ የቀድሞ መዝገብ ላይ በፍሬ ጉዳይ ረገድ የተሰጠ ውሳኔ ስለመኖሩ አልተጠቀሰም፡፡ እንግዲህ የጉዳዩ አጠቃላይ ይዘት ይህንን የመሰለ መሆኑን ከተገነዘብን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ መሰረት የሚሸፈን ነውን? የሚለውን እንመለከታለን፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ መሰረት በማድረግ ድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይቻለው በቀድሚው ክርክር የተያዘው ጭብጥና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑ የተከራካሪ ወገኖች አንድነት ብቻ ሳይሆን በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑም መረጋገጥ አለበት፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ቀደም ሲል በተጠሪ ላይ ያቀረበችው ክስ በተመሳሳይ ፍሬ ነገር ላይ ቢሆንም በቀድሞ መዝገብ በፍሬ ነገር ረገድ የመጨረሻ ውሳኔ እንዳልተሰጠበት ይልቁንም አመልካች ክሷን በማስረጃ አሟልታ እንድታቀርብ መብት የተጠበቀላት መሆኑን ከፍ ሲል ተመልክተናል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ላይ በቀዳሚው መዝገብ የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡ ይህ መሰያ እስካልተሟላ ድረስ ደግሞ አመልካች ያቀረበችው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ ሥር የሚሸፈን አይሆንም፡፡ ስለዚህም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በድጋሚ የቀረበ ነው (res judicata) በሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 5/1/ ይሸፈናል ሲል የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም ውሳኔው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ በሌላ በኩል አከራካሪው መሬት የማን ነው የሚለውን በተመለከተም ማስረጃ በማጣራት የወረዳው እና ከፍተኛው ፍ/ቤት የተሻለ ማስረጃ የአመልካች መሆኑን ስለማረጋገጣቸው ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ስለሆነም በፍሬ ነገር ረገድ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ማስረጃ መሰረት ያደረገ መሆኑን ስለተገነዘብን ባለበት ሊፀና የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡

በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 88224 በ17/05/2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሸርካ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06008 በ4/7/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19080 በ24/11/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 43331

ሐምሌ 19 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ገመቹ ቡቻላ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** አቶ በቀለ ኩማ(ቡቻላ) - በሌሉበት

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የውርስ ንብረት ክፍፍል የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ 22866 የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በማጽናቱ በውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል ሲል አመልካች አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር የተያዘው ጭብጥ በተጠሪ በኩል ክስ የቀረበለት የወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም ያለውን የከፍተኛው ፍ/ቤት አጽንቶታል፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ጉዳዩ የውርስ ክርክር ነውና የወረዳው ፍ/ቤት ሥልጣን አለው ካለ በኋላ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙ ወደ ወረዳው ፍ/ቤት ሳይመልስ መወሰኑ እና ቀደም ሲል በክልሉ ሰበር ችሎት የተወሰነ ነው ሲል የጠቀሰው መዝገብ ውሳኔ ይዘት አግባብነት ለመመርመር ሲባል ተጠሪ እንዲቀርብ ታዟል፡፡ ተጠሪ መጥሪያ ተቀብሎ መልስ አልሰጠም በዚሁ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

እኛም የቀረበውን አቤቱታ ከሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ከአመልካች አቤቱታ መረዳት የተቻለው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው ክርክር የውርስ ንብረት የሚመለከት ነው፡፡ ቀደም ሲል አመልካች የአባቴን የውርስ ንብረት ድርሻ ያካፍለኝ ሲል ተጠሪ ያቀረበው ክስ በቀበሌው በማህበራዊ ፍ/ቤት ታይቶ ከተወሰነለት በኋላ አመልካች እስከ ክልሉ ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርቦ የክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 4665 በሰጠው ትእዛዝ የአሁን አመልካች (ሥር ተከሳሽ) የመከላከያ ምስክር ሳይሰማ ውሳኔ መስጠቱን በመንቀፍ ይህው እንዲፈፀም ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለሱን፣ከዚያም ክርክር ተደርጐ ከተወሰነ በኋላ በይግባኝ በድጋሚ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲደርስ ተጠሪው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው የውርስ ንብረት መጠየቁ ተገቢ አይደለም ተብሎ መሻሩን ተጠቅሷል፡፡ እንግዲህ ለአሁኑ የሰበር ማመልከቻ መነሻ የሆነው ክርክር ከዚህ በኋላ በአደሳ መልክ የተጀመረ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ካገኘ በኋላ የውርስ ንብረት ክፍያ ጥያቄ ለወረዳው ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ወረዳው ፍ/ቤት የክልሉን የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 110/99 በመጥቀስ የይዞታ ክርክር በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት መታየት አለበት ሲል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤቱም ይህንኑ አጽንቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንን ውሳኔ ለመስጠት የጠቀሰው ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል ያለው ክርክር የውርስ ንብረት የሚመለከት በመሆኑ የወረዳው ፍ/ቤት ሥልጣን አለው የሚል ነው፡፡ እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ይህንን የመሰለ መሆኑን ከተረዳን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፍሬ ነገሩ ላይ ውሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1/ በግልጽ እንደተመለከተው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሥር በመጀመሪያ መቃወሚያ ብቻ የወሰነውን ውሳኔ የለወጠ እንደሆነ የሥር ፍ/ቤት ወደ ክርክሩ ገብቶ እንደገና እንዲመለከተው መዝገቡን ሊመልስለት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በርግጥ የዚህ ድንጋጌ የተቀመጠው መሪ ቃል አስገዳጅ ሆኖ አይታይም፡፡ ነገር ግን በግራ ቀኙ በኩል የሚቀርቡት የፍሬ ነገር ክርክሮች እና ማስረጃዎች በአግባቡ ለማጣራት ይቻል ዘንድ ለሥር ፍ/ቤት

መመለሱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በተለይም በዚህ ጉዳይ ላይ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ክርክር ከመመርመር እና ማጣራት አንፃር የመጨረሻው የሥልጣን እርከን በመሆኑ የግራ ቀኙን የይግባኝ እድል የሚያጣብብ መሆኑንም መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም ሌላ የመ/ደረጃው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ስልጣን የለኝም ሲል መዝገቡን መዝጋቱ እንጂ አመልካች ያነሳው የይርጋ ክርክርም እልባት ያልተሰጠው ነጥብ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት በተገቢው ሥነ-ሥርአት ክርክር ያልተደረገበትን ፍሬ ነገር ጉዳይ በዚያው አጠቃሎ ውሳኔ መስጠቱ የሙግት አመራር እና የሥነ-ሥርአቱን የሥልጣን ክፍፍል መነሻ ሐሳቦች በአግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ከሥነ-ሥርአት መርህ አንፃር ስሕተት ያለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከዚህም ሌላ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ በይዘቱም ሲታይ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ማቅረቡ ተገቢ አልነበረም ሲል ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ጉዳዩ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሶ በአዲስ መልክ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ይዞ ክስ አቅርቦ በሥልጣን ጉዳይ ውሳኔ ተሰጥቶበት ከፍተኛው ፍ/ቤት ያፀናውን ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሁለት የከፍተኛ ፍ/ቤት መዛግብት በማጣመር የሰጠው ውሳኔም ሥነ-ሥርአቱን ተከትሎ የቀረበ አይደለም፡፡ በመጨረሻም ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የጠቀሰው የሰበር መ/ቁ. 4665 ንብረት ይከፋፈሉ የሚል ሳይሆን የአመልካች የመከላከያ ምስክር እንዲሰማ ወደ ሥር ፍ/ቤት የተመለሰ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የግራ ቀኙ የፍሬ ነገር ክርክር በጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአግባቡ ያልተጣራ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 22866 የሰጠው ውሳኔ ከሙግት አመራር መርህ እና ሥነ-ሥርአት አንፃር መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎትም ይህንኑ ማረም ሲገባው ማለፉ ተገቢ አይደለም፡፡

ስለሆነም ውሳኔው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22866 በ26/03/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 24680 በ27/4/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሻሽሎ ተከታዩ ተወስኗል፡፡
2. የግራ ቀኙ ክርክር የውርስ ጉዳይ ነውና የወረዳው ፍ/ቤት የመዳኘት ሥልጣን አለው ሲል የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን የፍሬ ነገር ክርክር የወረዳው ፍ/ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሰረት መልሰናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 36730

ሐምሌ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - አልቀረቡም

**ተጠሪ**፡- አቶ አማረ ገላው - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 27947 መጋቢት 8 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይንና የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 20224 መጋቢት 16 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስላመለከተ ነው፡፡

በዚህ መዝገብ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 164 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ እውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸውን መብቶች ለማስከበር የሚቀርብ አቤቱታ ወይም ጥያቄ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለደሴ ወረዳ ፍርድ ቤት ኀዳር 21 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ/ አመልካች/ የደረጃ እድገት እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪ ያቀረበው ክስ ከዚህ በፊት በፍርድ ያለቀ ነው፡፡ የከሳሽ /ተጠሪ/ ክስ በይርጋ ይቋረጣል የደረጃ እድገት በወድድር የሚሰጥ በመሆኑ ከሳሽ ይገባኛል በማለታቸው የሚሰጥ አይደም የሚል ክርክር ለወረዳው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ቀደም ብሎ በአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ የደረጃ እድገት እንዲሰጣቸው ክስ አቅርበው የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ውሣኔ ከሰጠላቸው በኂላ የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመግለጽ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የቦርዱን ውሣኔ የሻረ በመሆኑ ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አልተሰጠበትም፡፡ ክስ በይርጋ ይቋረጣል የሚለው የተከሳሽ/የአሁን አመልካች/ መቃወሚያ በተመለከተ የአሁን ተጠሪ ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የተደነገገው የጊዜ ገደብ ሣያልፍ ክስ አቅርቦ የነበረና ክርክር ሒደት እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ደርሶ ቦርዱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን እንደሌለው የተወሰነ በመሆኑ ተጠሪ ለቦርዱ የቀረበው ክስና ክርክር የይርጋው ጊዜ የማያቋርጥ ነው በማለት የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ በመቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ተጠሪና አመልካች በዋናው ጭብጥ ላይ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ለተጠሪ የደረጃ እድገቱን ሊሰጣቸው ይገባል የሚል ውሳኔ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ ሶስት ገጽ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን የአቤቱታቸውን ፍሬ ነገርም የወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪ ክስ በይርጋ ይቋረጣል በማለት ያቀረብነው የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ያለፈብን አላግባብ ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ጉዳዩን አይቶ ውሣኔ የመስጠት የሥረ- ነገር ሥልጣን ለሌለው አካል ማለትም ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ያቀረቡ በመሆኑ የይርጋው ጊዜ መቆጠሩን ያቋርጠዋል በማለት የሰጠው ብይን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 አንቀጽ 164 እና አንቀጽ 147 ድንጋጌዎች ያላገናዘበ ነው የወረዳው ፍርድ ቤት ብይን ስለ ይርጋ መቋረጥ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1851/ለ/ የተደነገገውን ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ይኸም ቢታለፍ ያለ ውድድር ለተጠሪ የደረጃ እድገት እንድንሰጥ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኛችንን በመሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር የሚጣራ ነጥብ ያለው በመሆኑ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ተጠሪ ግንቦት 1 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ ሶስት ገጽ መልስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የሚያከራክራቸው ጉዳይ አመልካች ላወጣው የሥራ መደብ የትምህርት ማስረጃዬን ማለትም ለመወዳደር የሚያስችለኝን ዲፕሎማ በማያያዝ ለውድድር ስቀርብ ዲፕሎማውን ሥራ ስትቀጠር ያላስመዘገብከው ስለሆነ እንደማስረጃ አይያዝልህም ብሎ ስለከለከለኝ እየሰራሁ ተምሬ በዲፕሎማ የተመረቅሁበት በፐርቸዚንግ የሥራ ሙያ ያወጣው የሥራ መደብ ብቸኛ ተወዳዳሪ ሆኜ ቀርቤ በእድገት ሊሰጠኝ ሲገባ አላግባብ ሲከለክለኝ በወቅቱ አቤቱታዬን ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ አቅርቤ ቦርዱ የሥራ መደቡ ሊሰጠኝ እንደሚገባ ወስኗል፡፡ አመልካች በውሣኔው ቅር ተሰኝተው ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶት ነበር፡፡ አመልካች ውሣኔው የሕግ ስህተት አለበት በማለት ለዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው ችሎቱ የግራ ቀኞችንን ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩ የግል የሥራ ክርክር በመሆኑ የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም በሚል ምክንያት የቦርዱንና የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮታል፡፡ ከዚህ በኋላ የሰራተኛ ማህበሩና አመልካች ባደረጉት ውድርድር አመልካች የእኔንና የሌሎች ሰራተኞችን ዲፕሎማ ተቀብሎ መድቦኛል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወሰነው መሰረት ለወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረብኩትን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ለቦታው የቀረብኩ ብቸኛ ተወዳዳሪ በመሆኔ አመልካች ያቀረበው የይርጋ እና የፍሬ ጉዳይ ክርክር የሕግ መሰረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በጽሑፍ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር አመልካችና ተጠሪ በጽሑፍ ያቀረቡት ክርክር ይዘት በእጭሩ ካላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪ ክስ በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎችና ይህ የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 16648 ከሰጠው የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ ውሣኔ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካችና ተጠሪ ካቀረቡት ክርክር ለመገንዘብ እንደቻልነው በመጀመሪያ ተጠሪ አመልካች ሥራ ከተቀጠርኩ በኋላ ያገኘሁትን የትምህርት ማስረጃ /ዲፕሎማ/ በመቀበል ብቸኛ ተወዳዳሪ በሆንኩበት የሥራ መደብ የደረጃ እድገት ሰጥቶ ሊመድበኝ ይገባል የሚል ክስ ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ አቅርበው ቦርዱ የአመልካችንና የተጠሪ ክርክር ከሰማ በኋላ ውሣኔ ሰጥቶ ነበር፡፡ አመልካች የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቦርዱን ውሣኔ በማጽናቱ አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው የሰበር ችሎቱ ጉዳዩ የውል የሥራ ክርክር ሣይሆን የግል የሥራ ክርክር በመሆኑ የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ጉዳዩን የማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም በማለት በሰበር መዝገብ ቁጥር 28690 ኅዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ከዚህ በኋላ ለደሴ ወረዳ ፍርድ ቤት ኅዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ አመልካች የደረጃ እድገት እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች የተጠሪ ክስ በይርጋ ይቋረጣል በማለት ያቀረበው መቃወሚያ ውድቅ በመደረጉ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አመልካች በሥርና በሰበር የሚከራከረው ተጠሪ የመጀመሪያውን ክስ ያቀረበው ጉዳዩን አይቶ ውሣኔ ለመስጠት ሥልጣን ለሌለው አካል መሆኑ ይህ የሰበር ችሎት በሰጠው ውሣኔ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ለሌለው አካል ያቀረበው ክስ የይርጋ ጊዜ መቆጠርን አያቋርጠውም በማለት ሲሆን ይህ የአመልካች ክርክርና ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ለሌለው ፍርድ ሰጭ አካል ክስ ማቅረብ ይርጋ አያቋርጥም በማለት በስር መዝገብ ቁጥር 16648 የሰጠውን የሕግ ትርጉም በአጠቃላይ በሕግ የይርጋ የጊዜ ገደብ መደንገግ ካስፈለገበት መሰረታዊ

ምክንያትና ፍርድ ቤቶችና ሌሎች የዳኝነት ነክ ሥልጣን ያላቸው አካላት አንድ ጉዳይ ሲቀርብላቸው ሌላኛውን ተከራካሪ ከመጥራታቸው በፊት ስላለባቸው ግዴታና ኃላፊነትና የይርጋ የሕግ ድንጋጌዎችና ይርጋ የሚቋረጥባቸውን ሁኔታዎች መሰረታዊ አተረጓጐም መርሆች በመመርመር ውሣኔ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ጉዳዩ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ለሌለው ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ላለው አካል ክስ መቅረቡና ክርክር መካሄዱ ይርጋን አያቋርጥም በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ሕግ አውጭው በተለያዩ የሕግ ማእቀፎች መብት አሉኝ ወይም መብቴ ተጥሶብኛል የሚል ማናቸውም የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰውነት መብት ያለው አካል በማቅረብ መብቱን የሚጠይቅበትን የጊዜ ገደብ በሕግ ከሚደነግግበት መሰረታዊ ዓላማ አንፃር መታየት ያለበት ነው፡፡ ሕግ አውጭው ማናቸውም ሰው በሕግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክሱን ለፍርድ ሰጭ አካላት ካላቀረበ ጥያቄው በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን በሕግ የሚደነግግበት አንደኛው ምክንያት መብት አለኝ ወይም መብቴ ተጥሶብኛል የሚል ሰው ተገቢውን ትጋት በማድረግ በሕግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ መብቱን እንዲጠይቅ ለማድረግና መብቱን በሕግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልጠየቅ ዳተኛ የሆነ ሰው ጊዜው ካለፈ በኋላ ክስ የማቅረብ መብቱን ለመገደብና መብቱን ቀሪ በማድረግ ሕግ ማእቀብ መጣልና መቅጣት ነው፡፡ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በተመለከተ የአሰሪና ሰራተኛ የሥራ ክርክር ችሎትና የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የተሰጣቸው ስልጣንና ኃላፊነት ያለ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 138 እና ከአዋጅ አንቀጽ 147 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪ መብቱን ለማስከበር ተገቢውን ጥረት ማድረግ የደረጃ እድገት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ወሳኝ ቦርድ ነው በሚል እምነት ክሱን ለቦርድ ያቀረበ ሲሆን ቦርዱም ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለኝ በሚል እምነት ተከሳሹ አለኝ የሚለውን ክርክር እንዲያቀርብ መጥሪያ ልኮ የከሳሽና የተከሳሽ ክርክር በመስማት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የቦርዱን ውሣኔ በይግባኝ የተፈፀመ የሕግ ስህተት ካለ መርምሮ የማረም ሥልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቦርዱ ውሣኔ የሰጠው በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሰረትና በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት መሆኑን በማረጋገጥ አጽንቶታል፡፡ የትኛው ጉዳይ የግል የሥራ ክርክር ነው?፣ የትኛው የደግሞ የወል የሥራ ክርክር ባህሪ ይኖረዋል? የሚለውን በመተርጐም ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 28690 ቦርዱ ሥልጣን የለውም በማለት መወሰኑ ተጠሪ ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ክስ አቅርቦ እስከ ሰበር ድረስ በተከራከረበት ጊዜ ውስጥ ይርጋ ሊቋረጥለትና ጉዳዩ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 182 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ይርጋው እንደ አዲስ ሊቆጠር አይገባውም በማለት ተጠሪ የሚያቀርበው ክርክር በሕግ የይርጋ የጊዜ ገደብ መደንገግ ያስፈለገበትን አጠቃላይ መሰረታዊ ዓላማ ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

2. በሁለተኛ ደረጃ አመልካች ተጠሪ የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ጉዳዩን አይቶ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የሌለው በመሆኑ ለቦርዱ ያቀረበው ክስ ይርጋው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 164 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት አይቋርጥም በማለት ያቀረቡት ክርክር ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ሥልጣን በሕግ የሰጠው ሌላ አካል የከሳሽ ክስ ከተቀበለ በኋላ ለተከሳሹ መጥሪያ ከመላኩ በፊት በሕግ እንዲያደርግ ከተጣለበት ግዴታና ኃላፊነት አንፃር መታየት አለበት፡፡ አንድ ጉዳይ ዳኝነት አይቶ ውሣኔ እንዲሰጥ የክስ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት ወይም በሕግ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የተሰጠው አካል ለተከሳሹ ክስ አቤቱታውን ከመጥሪያ ጋር በመላክ ከማከራከሩ በፊት የክስ ማመልከቻውን መመርመርና ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የስረ-ነገር ወይም የግዛት ክልል ስልጣን የሌለው መሆኑን ከተረዳ የቀረበለት የክስ አቤቱታ አይቶ የመወሰን ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመግለጽ ውሣኔ ሊሰጥ እንደሚገባው ከፍትሐብሔር ሥነ- ሥርአት ሕግ ቁጥር 9 እና 23 ንኡስ አንቀጽ 1/ለ/ ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ወይም ከሕግ የዳኝነት ነክ ሥልጣን የተሰጠው አካል የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ጉዳዩን አከራክሮ ለመወሰን የሚችል መሆኑን በማመን ከሳሽ ከተከሳሹ መጥሪያ እንዲያደርስ ትእዛዝ ከሰጠና ተከሳሽም የፍርድ ቤቱን መጥሪያ ወጭ በማድረግ ለተከሳሹ በማድረስ አሳውቆ ከሆነ ይርጋው የሚቋረጥ መሆኑ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1851/ለ/ የተደነገገው ድንጋጌ ከሳሽ ክሱን ሰምቶ ለመወሰን ለሚችል አካል የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም ዋንኛው ኃላፊነት የክስ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤት ለተከሳሹ መጥሪያ ከመላኩና ክርክር መስማት ከመጀመሩ በፊት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን መመርመርና መወሰን እንዳለበት የሚያመለክት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ክርክሩ ይህንን ያሕል ጊዜ የፈጀው ተጠሪ ክሱን ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ በማቅረቡ ምክንያት ብቻ አይደለም፡፡ የተጠሪን ክስ የተቀበለው ቦርድ ጉዳዩን ከማየቱ በፊት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው መሆኑን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 231 ንኡስ አንቀጽ 1/ለ/ መሰረት በመመርመር ጉዳዩን አይቶ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የለኝም በማለት ተወስኖ ጉዳዩን ባለመዝጋቱ ምክንያት ነው፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ወይም በሕግ የዳኝነት ነክ

ስልጣን የተሰጣቸው አካላት በሕግ የተጣለባቸውን ግዴታና ኃላፊነት በአግባቡ ባለመወጣታቸው ወይም ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያላቸው ወይም የሌላቸው ስለመሆኑ የሕጉ ድንጋጌ አሻሚ፣በጠቅላላ አነጋገር የተገለፀና ክፍተት ያለበት በመሆኑ ምክንያት አከራካሪና የሕግ ትርጉም መስጠት የሚያስፈልገው በመሆኑ ምክንያት ጉዳዩን መወሰን ሥልጣን እንዳላቸው በመተርጎም ክርክሩን ሲሰሙ ለቆዩበት ጊዜ ይርጋው አይቋረጥም በሚሉት ከሳሽ ክስ የማቅረብ መብቱ ይርጋ እንዲታገድ የሚደረግበት ምክንያት የለም፡፡ በእነዚህ አይነት ሁኔታ የይርጋ ጊዜ መቆጠሩ መቋረጥና ከሳሽ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1852 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት ሥልጣን ላለው አካል ክሱን ሲያቀርብ እንደአዲስ ይጋው ሊቆጠርለት የሚገባ በመሆኑ አመልካች ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

3.አመልካች ያቀረበው ክርክር ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዮችን ለፍርድ ቤት ወይም በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ መብት ያለው መሆኑ በሕገ-መንግቱ አንቀጽ 37 ከደነገጋቸው ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡ የይርጋ የሕግ ድንጋጌዎች መብታቸውን ለመጠየቅ ተገቢውን ትጋት ያደረጉና ዳተኛ ያልሆነ ሰዎች ፍትህ የማግኘት መብት በማያሣጣ ሁኔታ በጠባቡ ሊተረጐሙና ፍትህ የማግኘት መብትን በሚያረጋግጥ መንገድ ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ መብታቸውን ለፍርድ ቤት ወይም በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው ሌላ አካል የሕጉ የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት ለማቅረብ ተገቢውን ትጋት ያደረጉ ሰዎች ላይ የይርጋ ጊዜ መቆጠሩ እንዲያቋረጥ የሚያደርግ የሕግ አተረጓጐም በመጠቀም የይርጋ ጊዜ አላግባብ እንዲቆጠር በማድረግ የዜጐች ፍትህ የማግኘት መብት እንዳይሸራረፍና በዚህ ምክንያት የፍትህ መዛባት እንዳይደርስ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ውስጥ የውል የሥራ ክርክር አይቶ የመወሰን ሥልጣን ባለው የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ክሱን አቅርቦ ክሱ በቦርዱና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በአግባቡ ያቀረበ መሆኑን አረጋግጠው ውሣኔ ሰጥተውበታል፡፡ ጉዳዩ የወል የሥራ ክርክር ነው? ወይስ የግል የሥራ ክርክር? የሚለው እስከ ሰበር ድረስ ያከራከረ ጭብጥ ሲሆን ጭብጡ ይህ በሰበር ችሎት የወሰነው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በመስጠት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ተጠሪ በመጀመሪያ ክሱን ያቀረበው ሥልጣን ለሌለው አካል ስለሆነ ይርጋው ሊቋረጥ አይገባም በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር መብቱን ለማስከበር ተገቢውን ትጋት በማድረግ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው አካል ክስ ያቀረበውን የተጠሪን ሕገ-መንግስታዊ ፍትሕ የማግኘት መብት በሚያጣብብ ሁኔታ ችሎቱ የሕግ ትርጉም እንዲሰጥ የሚጠይቅ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

4. እያንዳንዱ የይርጋ ሕግ ድንጋጌ በራሱና በጠበበ ሁኔታ መተርጐም አለበት የሚለው የሕግ አተረጓጐም መርህ ከላይ የገለጽነውን የዜጐች ፍትህ የማግኘት መብት በማያጣብብ እና አላግባብ የይርጋ ጊዜ እንዲቆጠር በማድረግ የሚደርስ የፍትህ እጦት ለማስቀረት በሚችል መንገድ ተግባራዊ መሆን ይግባዋል፡፡  ይህ አተረጓጐም እኛ ብቻ ሣንሆን የዳበረ የሕግ ሥርአት ያላቸው አገሮች “Limitation periods are to be construed strictly so as not to take away the right of the plaintiffs” በሚል መንገድ የሚከተሉት አተረጓጐም ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በሰበር መዝገብ ቁጥር 16648 የተሰጠውን ትርጉም ለማጠናከር የተጠቀሰው የፍትሐብሔር ሥነ- ሥርአት ሕግ ቁጥር 278 ንኡስ አንቀጽ 3 በጠባቡና በድንጋጌው ግልጽ በተመለከተው ጉዳይ ብቻ እንዲያገለግልና ተፈፃሚነት በሚኖረው ሁኔታ መጠቀስና መተርጐም ይኖርበታል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መልእክትና ይዘት በስፋት በመተርጐምና የማመሣሰል የትርጉም ዘዴ (Analogy) በመጠቀም ሥልጣን ለሌለው ፍርድ ሰጭ አካል የቀረበ ክስ ይርጋን አያቋርጥም በሚል መንገድ የተሰጠው ትርጉም ከላይ የዘረዘርናቸውን መሰረታዊ የይርጋ ሕግ አተረጓጐም መርሆች የሚጥስ መሻሻል ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ፍርድ ቤቶች የይርጋ ጊዜ ገደብ የሚቆጠርበት፣ የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚራዘምበት፣ የይርጋ የጊዜ ገደብ መቆጠር የሚታገድበት (የሚቋረጥበትን) ሁኔታ ሲተረጉሙ ፍትህና ርትእን መሰረት በማድረግና የይርጋው ድንጋጌ አላግባብ ተፈፃሚ እንዲሆን በማድረግ ምክንያት የሚደርሰውን የፍትህ ማዛባት የሚቀነስ የአተረጓጐም ሥልት መከተልና በሕጉ በተገለፀው የጊዜ ገደብ ውስጥ መብታቸውን ለመጠየቅ ተገቢውን ትጋት ያላደረጉና ዳተኛ የሆኑ ሰዎች ክስ የማቅረብ መብት ላይ ማእቀብ በሚጥል መንገድ ብቻ ሕጉን በሥራ ላይ በማዋል የይርጋ የሕግ ድንጋጌዎች በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 37 የተደነገገውን ፍትህ የማግኘት መብት በማያጣብብና የማይሸራርፍ መንገድ መተርጐምና ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸው በመሆኑ አመልካች ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 በዘረዘርናቸው መሰረታዊ ምክንያቶች ከዚህ በፊት አምስት ዳኞች ተሰይመው በመገብ ቁጥር 16648 የይርጋ ጊዜ አቆጣጠርና ስለ ይርጋ መቋረጥ የሰጡትን የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 4 በሚደነግገው መሰረት በመለወጥና የሕግ ትርጉም በመስጠት ወስነናል፡፡

አመልካች ተጠሪ ያለ ውድድር እድገት ሊሰጠው አይገባም በማለት ያቀረበውን ክርክር በተመለከተ አመልካች ያቀረበውን ክርክር ለማስረዳት አለመቻሉንና በአንፃሩ ተጠሪ ክርክሩን ያስረዳ መሆኑን በማረጋገጥ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ሰጥተውበታል፡፡ አመልካች ለቦታው ብቁ የሆኑ ሰራተኞች እንዲወዳደሩ ማስታወቂያ ያወጣና ተጠሪ መስፈርቱን አሟልቶ ያቀረበ ብቸኛ ተወዳዳሪ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጡበት በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ለሰበር ችሎት ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና ክርክር በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ስለሆነም የወረዳውና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት አጽንተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤትና የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ሥልጣን ለሌለው ፍርድ ቤት ወይም በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል ክስ ቀርቦ ክርክር ሲደረግ መቆየቱ የይርጋ ጊዜ መቆጠሩን ያቋርጠዋል ብለናል፡፡
3. የተጠሪ ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ሚያዝያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 50376

ሀምሌ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ገሠሠ - ጠበቃ አቶ መከተ ዳኘው - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07/08 አስተዳደር ጽ/ቤት

ነገረ ፈጅ አቶ ወንድሙ አድማሱ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ችሎት ጥቅምት 2 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ችሎት አመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን የቤት ኪራይና የቤት ባለቤትነት ክርክር ተጠሪ አመልካችን መጥሪያ ለማድረስ በአድራሻቸው አፈላልጎ ማግኘት ባለመቻሉ መጥሪያው ፍርድ ቤት ቅጥር ግቢ እንዲለጠፍለት ባቀረበው ቃለመሀላ መሠረት መጥሪያው በፍርድ ቤቱ ቅጥር ግቢ ተለጥፎ አመልካች ባለመቅረባቸው ጉዳዩን አመልካች በሌሉበት አይቶ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ታህሳስ 4 ቀን 2000 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር የምትከራከረው በቤት ጉዳይ መሆኑና የመኖሪያ ቤቴ እየታወቀ በሀሰት ተፈልጋ አልተገኘችም ተብሎ ቃለመሃላ ቀርቦ ጉዳዩ በሌሉብት የተሰጠው ውሣኔ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 78 መሠረት ተነስቶ ክርክሩ እኔ ባለሁበት እንዲሰማ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ላይ ካከራከረ በኋላ አመልካች ያቀረቡት ምክንያት የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ ታህሣሥ 4 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ የሚነሣበትና ክርክሩ እንደገና የሚታይበት ምክንያት ያለም በማለት የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች መጥሪያ ለማድረስ ከመኖሪያ ቤቴ የመጣ ሰው የለም፡፡ ተጠሪ የመኖሪያ ቤቴንና አድራሻዬን በሚገባ ያውቀዋል፡፡ ተጠሪ መጥሪያ በአካል ለእኔ ማድረስ እየቻለ ያላደረሠ ሲሆን ይኸም ቢታለፍ መጥሪያው እኔ ላየው በምችለው ቦታ በመኖሪያ ቤቴ ላይ መለጠፍ ሲገባው እኔ ልደርስበት በማልችል ቦታ መጥሪያው እንዲለጠፍ በማድረግ የፍርድ ባለመብት የሆንኩበት ውሣኔ በሌለሁበት የተሻረ መሆኑን በመረዳት ፍርዱ ተሰርዞ ወደ ክርክሩ እንደገባ ያቀረብኩት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ለአመልካች መጥሪያ ለማድረስ የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚደነግገው መሠረት ተገቢውን ጥረት አድርገናል ስለዚህ አመልካች በአግባቡ መጥሪያ ሳይደርሰኝ አላግባብ በሌለሁበት ታይቶ ውሣኔ ተሰጥቶብኛል በማለት የሚያቀርቡት ክርክርክ የህግ ድጋፍ የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በህጉ የተቀመጠው ቅደም ተከተል መሠረት መጥሪያ አልደረሰኝም በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች በሌሉበት የተሰጠው ውሳኔ የሚሠረዝበት ምክንያት የለም በማለት የተሰጠው ብይን ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች በህጉ በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሠረት በማድረግ መጥሪያ ደርሷቸዋል ወይስ አልደረሣቸውም የሚለው ነጥብ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ጠቀሜታ አለው፡፡ አመልካች ተጠሪ እኔን ፈልጎ አላጣኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ፈልጌ አላገኘኋቸውም በማለት በቃለ መሀላ አረጋግጧል፡፡ ተጠሪና አመልካች የሚከራከሩት በቤት ኪራይና በአመልካች ወጭ የተሠራ ቤት ባለሀብቱ ማን ነው በሚለው ጭብጥ ዙሪያ ነው፡፡ ተጠሪ የአመልካች የቤት አከራይ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችን የመኖሪያ ቤት ቁጥር በሚገባ ያውቃል፡፡ ተጠሪ አመልካች የምትኖርበት ቤት ባለቤት ነው፡፡ መጥሪያ ለማድረስ በአማራጭ መጥሪያ ማድረሻ መንገዶች መጠቀም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ መከሰሱንና ፍርድ ቤት ክርክር ያለበት መሆኑን ለማወቅ የሚያስችለውን የተሻለውን አማራጭ የመጠቀም ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ፍርድ ቤትም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በአካል ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የአመልካች የመኖሪያ አድራሻ በተጠሪ በኩል የሚታወቅና የአመልካችና ተጠሪ የክርክር መንስኤ መሆኑ በመዝገቡ ተመልክቷል የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪ አመልካችን በአድራሻቸው ፈልጌ አላገኘናቸውም በማለት ቃለመሀላ ሲያቀርብለት መጥሪያው በፍርድ ቤቱ ግቢ ውስጥ እንዲለጠፍ ማድረጉ ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም አመልካች የመኖሪያ አድራሻ በግልፅ የሚታወቅ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 105 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት መጥሪያው በአመልካች የመኖሪያ ቤት ላይ እንዲለጠፍ ትዕዛዝ መስጠት ነበረበት፡፡ ስለሆነም አመልካች በህጉ የተደነገገው ቅደም ተከተል መሠረት መጥሪያ በወቅቱ በአግባቡ እንዲደርሣቸው ሣይደረግ ክርክሩ ታይቶ መወሰኑ ስለተረጋገጠ የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካች በሌሉበት በማየት ታህሣሥ 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 78 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት በመሠረዝ አመልካች በክርክሩ ገብተው የሚያቀርቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሣኔ መስጠት ሲገባው ታህሣሥ 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠሁትን ውሣኔ የማነሳበት ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጥቅምት 6 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አመልካች በሌሉበት አይቶ ታህሣሥ 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የሰበር ችሎት ጉዳዩን እንደገና አመልካች ባሉበት አይቶ ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

## የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎችን /ከቅጽ 1 - 7 / ዝርዝር የሚያሳይ ሰንጠረዥ

**ቅጽ - 1**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 18180 | የኬ.ኬ ብርድ ልብስ ፋብሪካ መሰረታዊ ሰራተኞች ማህበር እና የኬ.ኬ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ | የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የዳኝነት ስልጣን፣ የሰራተኛ ቅነሳ ጉዳይን በሚመለከት ስለሚነሳ ክርክር<br>አዋጅ ቁ.42/85 አንቀፅ 138(1),147 | ሐምሌ 29/1997 |
| 2 | 15493 | አቶ ጳውሎስ ሩምቾ እና ወ/ሮ ጫልቱ መርዳሳ | በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845,2024 | ሐምሌ 29/1997 |
| 3 | 17361 | ወ/ሮ ጋዲሴ ኢርጌ እና ወ/ሮ ወርቅአንጥፉ በቀለ | በስነ-ስርዓት ህጉ የጊዜ ገደብን በሚመለከት የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት ተፈፃሚ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.49, የፍ/ብ/ህ/ቁ.1856 | ሐምሌ 25/1997 |
| 4 | 17352 | ዋዜማ የልብስና ሽራ ምርቶች ኃ/የተ/ የግ/ ማህበር እና የነገው ሰው ትምህርት ቤት | ተገቢው ዳኝነት ክፍያ ሳይፈፀም በፍ/ቤት በቀጠለ ክርክር ስለሚፈፀም ስርዓት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.215,320(2),207,211(2) | ሐምሌ 28/1997 |
| 5 | 14605 | የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት እና እነ ኮሜት ትራንስፖርት ድርጅት (ስድስት ሰዎች) | በመንገዝ ላይ የነበሩ ዕቃዎች መጎዳት በሰው ላይ ሊደርስ ይችል የነበረን የግጭት አደጋ ለማስወገድ በተወሰደ ርምጃ የደረሰ የመኪና መገልበጥ ከዓቅም በላይ በሆነ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ስላለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 590,591, የፍ/ብ/ህ/ቁ.1792 | ሐምሌ 29/1997 |
| 6 | 17068 | የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና ሚ/ር ቢሮኒ አቲክፖ | በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ የህግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1856,2024, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 89 | ሐምሌ 19/1997 |
| 7 | 14974 | ወ/ት ማህሌት ገ/ስላሴ እና እነ አቶ መንግስቱ (ሁለት ሰዎች) | አንድ ተወካይ በወካዩ ላይ ባቀረበው ክስ ወካዩን ወክሎ መከራከር ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2188, 2189, 2208, 2209, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 57,58 | ሐምሌ 28/1997 |
| 8 | 14184 | አቶ ውርጌሳ ታደሰ እና<br>እነ አቶ መለሰ ተካ (ዘጠኝ ሰዎች) | ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የከሳሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73 | ሐምሌ 29/1997 |
| 9 | 14047 | ዶ/ር ዳንኤል አለሙ እና እነ ወ/ሮ ሮማን ወርቅ የማነብርሃን (ሦስት ሰዎች) | በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ የህግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1856, 2024 | ሐምሌ 28/1997 |
| 10 | 15835 | ሼል ኢትዮጵያ አ/ማ እና ወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ | ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የተከሳሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70,233 | ሐምሌ 29/1997 |
| 11 | 15992 | የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና<br>ወ/ት ሶስና አስፋው | በህግ የተደነገገው የውል አፃፃፍ /ፎርም/ የተቀመጠ ደንብ አለመፈፀም ስለሚያስከትለው ውጤት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719, 1720 (1), 1723, 1726, 1727, 1845 | ሐምሌ 19/1997 |
| 12 | 17191 | ወ/ሮ አስቴር አርአያ እና አቶ ግርማ ወይጆ | በአንዳንድ ውሎች የተመለከተን የአገልግሎት ክፍያ መጠን ለመቀነስ ፍ/ቤት ስላለው ስልጣን<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1711, 1731, 1676(2), 2635, 2640, 2646 | ሐምሌ 29/1997 |

**ቅጽ 2**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 13 | 13223 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ አስፋው አበበ | ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በተከራካሪ ወገኖች ባይቀርብለትም ተገቢ በሆነ ጊዜ ማንኛውም ዓይነት ሰነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በተጨማሪ እንዲቀርብለት መስጠት ስላለበት ትዕዛዝ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(2) 342, 345(1)(ለ) | ጥቅምት 9/1998 |
| 14 | 14414 | የጊምቢ ከተማ አስተዳደር ጽህፈት ቤት<br>እና ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ | በሕዝብ አስተዳደር አካል ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ ከመ/ቤቱ ጋር ባለው ስራ ክርክር የአዋጅ ቁ. 42/85 ተፈፃሚ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 2(1),3(2)(ሠ) | ጥቅምት 1/1998 |
| 15 | 15270 | የመቶ አለቃ ተሻገር አስታጥቄ እና አቶ አዊል አው አብዲ | በከተማ ቦታ ላይ ስለሚኖር መብት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33(2), 231, (1)(ሀ), አዋጅ ቁ.47/67 | ጥቅምት 28/1998 |
| 16 | 15410 | አቶ ተሾመ ጅፋር እና የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን | አጠቃላይ የአሰሪን የደመወዝ ጭማሪ አወሳሰን ስርዓትን ሳይሆን የግል ጥቅምን መሰረት አድርጐ የሚቀርብን የደመወዝ ጭማሪ ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 147 | ጥቅምት 1/1998 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 17 | 16273 | የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና<br>አቶ ገንታ ገምአ | ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠርኩ እንደሆንኩ ብቻ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄን የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ እና የግል ጥቅምን መሰረት አድርጐ የሚቀርብን የጥቅማጥቅም ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 9,10, 138, 142, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33 | ጥቅምት<br>22/1998 |
| 18 | 16624 | ወ/ት አጅጋየሁ ተሾመ እና የእቴነሽ በቀለ ሞግዚት ወ/ሮ<br>እታገኝ ዘነበ | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1) መሰረት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ጥያቄው የሚቀርበው ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1) | ጥቅምት<br>18/1998 |
| 19 | 16720 | ወ/ሮ አበራሽ ጉቱ እና እነ የመካከለኛው አዋሽ እርሻ<br>ልማት ድርጅት (አራት ሰዎች) | በከፊል የፍርድ ባለመብት የሆነ ሰው ባለመብት የሆነበት የፍርድ ክፍል እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም ክስ ካቀረበ በኋላ በመጀመሪያ የፍርድ ባለዕዳ የሆነበትን ፍርድ በይግባኝ አሽሮ የፍርድ ባለመብት ሲሆን አዲስ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው ቀደም ሲል የተከፈተው የአፈፃፀም መዝገብ ቢዘጋም እንኳን ማንቀሳቀስ ስለመቻሉ እና በአፈፃፀም ደረጃ ወለድ የሚከፈለው በዋናው ፍርድ ወለድ እንዲከፈል ከተወሰነ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378(3)(ሰ) | ጥቅምት<br>22/1998 |
| 20 | 16896 | ዘምዘም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር<br>እና የኢሊባቦር ዞን ትምህርት መምሪያ | የተዋዋዮች በውሉ አለመግባባት ሲፈጠርና ጉዳዩን በገላጋይ ዳኞች እንዲታይ ሲስማሙ ፍ/ቤት ይህንን ስምምነት ማስፈፀም ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1711,1731(1) | ጥቅምት<br>16/1998 |
| 21 | 17077 | ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ | የዕዳ መክፈያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ባለገንዘቡ ለባለዕዳው የሚያደረገው የዕዳ ክፍያ ጊዜ ማራዘም ዋሱን ከዋስትናው ነፃ የሚያደርገው ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1928(1)እና(2) | ጥቅምት<br>14/1998 |
| 22 | 17189 | የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጭ ድርጅት እና አቶ ንጉሴ<br>ዘለቀ | በአሰሪ "ገንዘብ" ላይ ሰራተኛው ያደረሰው ጉዳት በአሰሪው "ንብረት" የደረሰ ጉዳት ስለመሆኑ እና ሰራተኛ የስራ ውሉ ተቋርጦ ስራ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 27(1) (በ), 53(1),54 | ጥቅምት<br>17/1998 |
| 23 | 17429 | ወ/ሮ ሎሚ ሆርዶፋ እና አቶ ተስፋዬ ከበደ | በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ ኑዛዜው መነበቡን የሚያመለክት ከሆነ በግልጽ "ተነቧል" የሚል ቃል አለመኖሩ ኑዛዜውን ፈራሽ የሚያደርግ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 | ጥቅምት<br>21/1998 |
| 24 | 17533 | የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና<br>ሙሉ ብርሃን | የጉምሩክ ባለስልጣን በህጉ መሰረት የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ ከጉምሩክ መጋዘን እንዳይወጣ በማድረጉ ወይም ዴክላራሲዮን ባለመስጠቱ ምክንያት በዕቃው ባለቤት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 2(18), 43(1) (ሀ) | ጥቅምት<br>18/1998 |
| 25 | 17712 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና የወ/ሮ ሳዲያ እስማኤል ወራሾች | በተሰረዘ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚገኝ የባለሀብትነት መብት ስላለመኖሩ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195(1), 1196 (1) | ጥቅምት<br>16/1998 |
| 26 | 18307 | ንብ ትራንስፖርት አ.ማ.<br>እና<br>አቶ ተገኑ መሸሻ | በድርጅት ውስጥ የስራ መሪ የሆነ ሰራተኛ ከአሰሪው ጋር ያለው የስራ ክርክር የሚገዛው በፍትሐብሔር ህጉ የስራ አገልግሎት መስጠትን ስለሚመለከቱ ውሎች ክፍል በተመለከቱት ድንጋጌዎች ስለመሆኑ እና የስራ ውሉ ተቋርጦ የስራ መሪው ስራ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2534, 2540 ,2541(1) | ጥቅምት<br>25/1998 |

**ቅጽ 3**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 27 | 15815 | አርሲ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ ሰለሞን አበበ | የስራ ውሉ በህግ ወጥ መንገድ የተቋረጠ የስራ መሪ ስለሚያገኘው መፍትሔ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2570, 2573, 2574,2571 | ታህሳስ<br>10/1998 |
| 28 | 16648 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ<br>አንለይ ያየህ (ሃያ ሰባት ሰዎች) | ስለ ስራ ክርክር የይርጋ ጊዜ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 162,163,164,165,166, አዋጅ ቁ. 377/96 | ታህሳስ<br>20/1998 |
| 29 | 17483 | የኦሮሚያ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እና<br>ወ/ሮ ሮማን ደምሴ | የስራ ውል በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል የሚቀርብ ክስ መቅረብ ስላለበት የጊዜ ገደብ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 162(1) | ታህሳስ<br>20/1998 |
| 30 | 11924 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ት<br>ትዕግሥት ወርቁ | ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ስለማድረግ<br>አዋጅ ቁ.42/85 አንቀፅ 9,10 እና 24 | ህዳር<br>15/1998 |
| 31 | 14057 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና አቶ ጌታሁን ኃይሉ | አንድ ሰራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበት የአመት እረፍት ቀናት በገንዘብ ተቀይሮ ስለሚከፈልበት የህግ አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 79(2)እና (5), 77(5),77(3) | ጥቅምት<br>30/1998 |
| 32 | 16270 | አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ መሐሪ ማታ | በመኪና ግጭት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳት ካሣ ለማግኘት የመኪናው ባለቤት ጥፋት እንዳለበት ማስረዳት የማይኖርበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066(2),2086(2),2081,2091,2102 እና 2092 | ታህሳስ<br>17/1998 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 33 | 18581 | በአዲስ አበባ እስላማዊ ድርጅት የአወሊያ ጤና ጥበቃ እና ሲ/ረ ቀቡላ ከድር | በህገ ወጥ መንገድ የስራ ውሉ የተቋረጠ ሰራተኛ ወደ ስራ እንዲመለስ ስለሚወሰንበት የህግ አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 23(1),43(3),40(1) እና (2),44 | ህዳር<br>20/1998 |
| 34 | 15631 | እነ የሻረግ መንግስት (ሁለት ሰዎች) እና እማሆይ የሻረግ ፈረደ | የወራሽነት ጥያቄን ለማቅረብ ስለተወሰነ ጊዜ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1001(2),1168,1845,1853 | ታህሳስ<br>17/1998 |
| 35 | 15551 | ዮናይትድ ቴክኒካል ኢኩፕመንት ኩባንያ እና የኢትዮጵያ መተርና መሐንደስነት ኩባንያ | ውል እንዲፈርስ ከተወሰነ በኋላ ተዋዋዮች ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚወሰነው በውሉ መሰረት የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ካልሆነ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1716(1), 1815,1816 እና 1817 | ጥቅምት<br>29/1998 |
| 36 | 16062 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ አረጋሽ ከበደ | ከውል ውጭ በደረሰ ጉዳት ካሣ በመጠየቅ የሚቀረብ ክስ መቅረብ ስለሚኖርበት ጊዜ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143(1),2143(2) | ህዳር<br>19/1998 |
| 37 | 14554 | ወ/ሮ ጽጌ አጥናፌ እና ባላምባራስ ውቤ ሽበሽ | ፍርድ ቤት በአስተዳደር አካል የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርን የመሰረዝ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808(2),1198(2) | ታህሳስ<br>20/1998 |
| 38 | 15672 | አቶ ታደለ ገለቻ እና አቶ ውድመጣስ ኑሮ | ንብረት በሐራጅ ስለሚሸጥበት የህግ አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 442 | ታህሳስ<br>27/1998 |
| 39 | 16301 | ተገኘ እንግዳ እና አስናቀች ኬዳኔ | መጥሪያ አደራረስን አስመልክቶ የሚቀርብ ጥያቄ ስለሚስተናገድበት መንገድ<br>የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ. 99, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 103,105 | ህዳር<br>2/1998 |
| 40 | 10797 | ሼክ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ እና እነ ወ/ሮ ሻዲያ ናዲም (ሦስት ሰዎች) | ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በወንጀል ጉዳዩ በፍርድ የተወሰነው ገንዘብ እውነተኛ ባለቤት በቀረበ ጊዜ በቀጥታ የሚመለስ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 | ታህሳስ<br>27/1998 |
| 41 | 18199 | ዶ/ር ምናሴ እሸቴ እና እነ ግርማ አያና ( ሰባት ሰዎች) | በጨረታ ለገዛው ንብረት ገገር ዋጋውን ሳይከፍል ወይም ግዴታውን ሳይፈጽም ከቀረ ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ሊከተለው ስለሚገባው ስነ-ስርዓት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 429 | ህዳር<br>7/1998 |
| 42 | 16378 | የ10 አለቃ ጌታቸው ባዩ እና የቤ/ጉ/ክ/መ ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን | የመንግስት ሰራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ መስራቱ ስለሚኖረው ውጤት<br>ድንጋጌ ቁጥር 46/53, አዋጅ ቁ. 209/55 አንቀፅ 30(2) | ታህሳስ<br>17/1998 |
| 43 | 18342 | የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን እና እነ አቶ ብርሀኑ ሀሩይ (ሁለት ሰዎች) | የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.38/88 አንቀፅ 11(1) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 4 | ታህሳስ<br>17/1998 |
| 44 | 14699 | የኢንጂነር ወርቁ መኮንን ወራሾች እና የቦሌ ክፍለ ከተማ ገቢዎች መምሪያ | ገቢን ለመፍጠር የሚወጣን ወጪ በትክክለኛ ሰነድ እንዲረጋገጥ ህጉ ስለሚያስቀምጠው ሁኔታ<br>ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀፅ 29 | ህዳር<br>7/1998 |

**ቅጽ 4**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 45 | 20885 | የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ገቢሳ የማነ | ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ ስለሚደረግ የስራ ውል<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 9,10 | ጥር<br>3/1999 |
| 46 | 15531 | የኢት/ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አዱኛ ገመዳ | የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን | የካቲት<br>6/1999 |
| 47 | 21730 | ወ/ሮ ፍሬህይወት እርቄ እና የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን | ወደ ሥራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሰራተኛ የሚከፈለው ውዝፍ ደሞዝ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(5) | መጋቢት<br>11/1999 |
| 48 | 21119 | ቃሊቲ ምግባ አክሲዮን ማህበር እና ማስተዋል ጫኔ | የህመም ፈቃድ ጊዜ አቆጣጠር<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ (2) | መጋቢት<br>18/1999 |
| 49 | 21961 | አቶ ግርማ ነጋሽ እና ቢግ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር | የስራ ውልን ስለማቋረጥ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1) ሐ | መጋቢት<br>18/1999 |
| 50 | 20457 | የኢት/ንግድ ባንክ እና ወ/ሮ አለሚቱ ሞገስ | የስራ ውል በተቋረጠ ጊዜ ስራ ላልተሰራበት ውዝፍ ደሞዝ የሚከፈል ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 43,53(1), 54 | መጋቢት<br>20/1999 |
| 51 | 24153 | አቶ መንግስቱ አባተ እና የባህር ትራንዚት ድርጅት | ስለ መሠረታዊ የህግ ክርክር<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)ሐ | መጋቢት<br>26/1999 |
| 52 | 16653 | ግዮን ሆቴሎች ድርጅት እና ወ/ሮ ስለእናት ወርቅነህ | የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን | መጋቢት<br>27/1999 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 53 | 25526 | መምህር ጥላሁን አስፋው እና አዲስ ኮሌጅ | ሰራተኛው በየአመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሰራ መቆየቱና የሰራተኛው የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻ ለተወሰነ ጊዜ ተቀጣሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 9,10 | ሚያዝያ 16/1999 |
| 54 | 15662 | የኢት/ልማት ባንክ እና ሐዲ አብዲራህማን ቱሊሳ | ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጎም ስላለመቻላቸው<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2298,1733 | መጋቢት 13/1999 |
| 55 | 19081 | አቶ ዓሊ ቃሌብ አህመድ እና እነ አቶ ሚሊዮን ተፈራ (ሦስት ሰዎች) | ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የተገናኙ ተከሳሾች በአንድ ላይ በተከሰሱ ጊዜ አንዱ ተከሳሽ የሚያነሳውን የይርጋ መቃወሚያ በሌሎች ላይ ስላለው ውጤት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677,1901 | መጋቢት 18/1999 |
| 56 | 23320 | አቶ ገብሩ አብሴ እና እነ የአቶ ሁሴን አብዲረህማን ወራሾች (ሦስት ሰዎች) | የኪራይ ውል በአከራይና በተከራይ መካከል የሚደረግ ስለመሆኑ | መጋቢት 20/1999 |
| 57 | 14493 | የኢት/ልማት ባንክ እና አቶ ሚደቅሳ ቱለማ | ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጎም ስላለመቻላቸው<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.2298,1733 | መጋቢት 13/1999 |
| 58 | 18786 | ወ/ሮ አለሚቱ አግዛቸው<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ዝናሽ ሐይሌ | የውል አብዛኛው ግዴታ በተፈፀመ ጊዜ የተወሰነ ቀሪ ገንዘብ አለመከፈሉ ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ መሰረታዊ የሆነ የግዴታ መጣስ የሚያሰኝ ምክንያት ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771(1), 1785(2), 1789 | ሚያዝያ 18/1999 |
| 59 | 21448 | ወ/ሮ ጉርሬ ወርቅነህ እና እነ ወ/ሮ አበራሽ ዱባርጌ (ሁለት ሰዎች) | የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723, 1727 ,2877, 2878 | ሚያዝያ 30/1999 |
| 60 | 15557 | ወ/ሮ አልማዝ ዓለማየሁ እና አቶ ብርሀኑ ተሊላ | በአፈፃፀም ጉዳይ በስህተት በፍ/ባለመብት እጅ ስለገባ የከተማ መሬት ይዞታ | መጋቢት 11/1999 |
| 61 | 22260 | የጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ገደሪፍ ውብነህ (ሦስት ሰዎች) | የወጪና ኪሣራ አወሳሰን<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 463 | መጋቢት 18/1999 |
| 62 | 17984 | የጌዲዮን ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት እና ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ | ጉድለት ያለበት ሀራጅ ቀሪ ሲደረግ ሻጭና ገገርን ወደነበሩበት ለመመለስ ስላለመቻል<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1817(1) እና (2) | መጋቢት 20/1999 |
| 63 | 19205 | አቶ ሽኩር ሲራጅ እና አቶ ሙላት ካሣ | አንድ ፍርድ ተፈፀመ ሊባል የሚገባው ለፍርድ ቤቱ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ለፍርድ ባለመብቱ ሲደርሰው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 395 | መጋቢት 25/1999 |
| 64 | 19479 | ወ/ሮ አመለወርቅ ገለቱ ወራሾች እና እነ አቶ ቢሻው አሻሜ (አራት ሰዎች) | አከራካሪ የሆነው ቤት የግልም ሆነ የጋራ ቤቱ ያረፈበት ቦታ የመንግስት በመሆኑ ከቤቱ ተነጥሎ እንዲገመትና አስፈላጊም ከሆነ እንዲሸጥ የሚያደርግ ውሣኔ መሬትን የመንግስት ለማድረግ የወጣውን ሕግ የሚፃረር ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 47/67 | መጋቢት 20/1999 |
| 65 | 16109 | አቶ ከበደ አርጋው እና የኢት/ንግድ ባንክ | የሽያጭ ውል በሶስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ተዋዋዮች  ውላቸውን በመዝገብ እንዲፃፍ ከማድረግ የዘለለ ግዴታ የማይጥልባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1587, 1620, 1613, 2878 | ሚያዝያ 12/1999 |
| 66 | 14094 | የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት<br>እና<br>የአቶ ሰለሞን ወረዳ ወራሽ | ለረጅም አመታት በመንግስት እጅ የነበረ ቤትን በተመለከተ ባለቤት ነኝ የሚል ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁ. 47/67 የተፈቀደለት መሆኑን ወይም ያለአግባብ ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሣኔ አግኝቶ ባለመብት ስለመሆኑ ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, አዋጅ ቁ 47/67,ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33/2/ | ሚያዝያ 18/1999 |
| 67 | 17937 | ወ/ሮ ድንቄ ተድላ<br>እና<br>አቶ አባተ ጫኔ | ጋብቻ በአንደኛው ተጋቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የጋራም ሆነ የግል ንብረት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677 መሠረት በቁ. 1845 ላይ የተቀመጠው ይርጋ ተፈፃሚ ስለመሆኑ<br>ፍ/ብ/ህ/ቁ. 17,68, 100,1677,1845 | መጋቢት 20/1999 |
| 68 | 20938 | ወ/ሮ ሸዋዬ ተሰማ እና ወ/ሮ ሣራ ልነጋነ | ስለ ጋብቻ መፍረስ | ሚያዝያ 11/1999 |
| 69 | 22243 | ወ/ሮ ደሐብ ሰኢድ እና አቶ አብርሃም ካሣ | ልጅነትን ስለማስረዳት<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126(1),143(መ) እና (ሠ) | ሚያዝያ 16/1999 |
| 70 | 17058 | አቶ አንበሶ ወ/ገብርኤል እና አቶ መሣይ መኮንን | ኑዛዜ ህጋዊ ነው መባሉ ሌሎች ሰዎች በሰነዱ ላይ ተቃውሞ ካላቸው ጉዳዩ በዳኝነት መታየትን የሚከለክል ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881, 884, 892, 996-1000, ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | መጋቢት 25/1999 |
| 71 | 22712 | አቶ እንደሻው በቀለ<br>እና<br>እነ ወ/ት አይናለም ያለው | የኑዛዜ እያንዳንዱ መስፈርት መሟላት መመዘን የሚገባው የኑዛዜውን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከትና ተናዛዥም ሆነ ምስክሮች /እማኞች/ በኑዛዜ ባሰፈሩት ቃላትና ሃረጎች ሊሰጡ የሚችለውን ትርጉም ግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ | ሚያዝያ 9/1999 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ( ሁለት ሰዎች) | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 | |
| 72 | 22162 | አፍሪካ ኢንሹራንስ እና አቶ ብስራት ጉላ | መድን ሰጭ የካሣን ክፍያ በተመለከተ በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው በላይ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ | ሚያዝያ 9/1999 |
| 73 | 23339 | የኢት/ጉምሩክ ባለሥልጣን እና እነ አበሮ ኢርጋኖ | የጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች የፌዴራል ገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚተዳደሩ ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀፅ 6(2)ለ | መጋቢት 13/1999 |
| 74 | 16195 | የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና እነ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃ/ስላሴ (ስድስት ሰዎች) | ሚኒስቴር መ/ቤቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ማስተካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 4187 አንቀፅ 11(1), አዋጅ ቁ.47/67 አንቀፅ 21(2), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 74(4) | ሚያዝያ 11/1999 |
| 75 | 22317 | የምስራቅ ጉምሩክ የሐረር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ<br>እና<br>አቶ አብዱ አሉ አዩ | የጉምሩክ ባለስልጣን በኮንትሮባንድ ወደ ሀገር የሚገቡትን ወይም ከሀገር የሚወጡትን እቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሳቀሱ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን የተሰጠው ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 5-6 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2010(2) | ሚያዝያ 18/1999 |
| 76 | 12025 | አቶ ምናሴ አልማው እና ዓቃቤ ህግ | ጥብቅና ፈቃድ ከተሰረዘ በኂላ የጥብቅና ስራ እሰራለሁ ብሎ ገንዘብ መቀበል የማታለል ወንጀል ስለመሆኑ<br>የ1949 ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ.656(ሀ) እና (ለ) | መጋቢት 18/1999 |

**ቅጽ 5**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 77 | 17320 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ዶ/ር ሻውል ገብሬ (ሁለት ሰዎች) | ንብረትን ለመሸጥ ለመለወጥ ብሎም ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ በሚል የተሰጠ ውክልና ንብረቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችል ስልጣን እና ችሎታን የሚያጐናጽፍ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3049(2),2206(1) | መጋቢት 18/2000 |
| 78 | 20809 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ አለምነሽ ሃይሌ | በባለስልጣን ፊት በተረጋገጡ ሰነዶች ላይ ያሉትን ፊርማዎችና የሰነዶቹን ይዘት ማስተባበል ስላለመቻሉ | ሐምሌ 10/2000 |
| 79 | 23861 | ሊቀ ስዩማን አሰፋ ባሻህውረድ እና የሣህሊተ ምህረትና ክርስቶስ ሣምራ ደብር አስተዳደር | ወኪል የሆነ ሰው ውክልናውን በሚገባ እስካሳየ ድረስ በማመልከቻው ላይ የራሱን ወይም የወካዩን ስም አስቀድሞ መፃፉ ወኪልነቱን ለውጦ ባለቤት የሚያደርገው ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 58 | ጥቅምት 14/2000 |
| 80 | 26399 | አቶ ኃ/ማርያም ባዩ እና እነ አቶ ሣሙኤል ጉሣዬ (አምስት ሰዎች) | የውክልና ስልጣኑ ቀሪ ከተደረገበት እንደራሴ ጋር በቅን ልቦና ውል ፈፅመው በተገኙ ጊዜ ውሉ እንዲፈርስ ላይወሰን የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808, 1816, 2191(2), 2193 | ህዳር 5/2000 |
| 81 | 32241 | ወ/ሮ ካሰች ተካልኝ<br>እና<br>እነ አቶ ኃ/ማርያም አበበ<br>(ሁለት ሰዎች) | • እንደራሴ የሆነ ሰው የውክልና ስልጣኑን መሠረት በማድረግ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞች (Conflict of interest) ማስወገድ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ከእንደራሴው ጋር ውል የፈፀመው ሦስተኛ ወገን እንደራሴው የውክልና ስልጣኑን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞችን የማስወገድ ግዴታውን አለመወጣቱን ማወቁ ወይም ማወቅ የሚገባው መሆኑ ያደረጉትን ውል ፈራሽ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1) | መጋቢት 9/2000 |
| 82 | 21355 | አንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ | የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የሰጠ ወገን ከዋናው ውል አለመፅናት ጋር በተያያዘ የዋስትና ውሉ እንዲፈርስ ሊጠይቅ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1923(2) | ሐምሌ 3/2000 |
| 83 | 25115 | አቶ ማሞ ጉበና እና አቶ ወርቅነህ ተክለማርያም | ተራ ዋስ የሆነ ሰው ከባለዕዳው ጋር ተጣምሮ ክስ በቀረበበት ጊዜ ከገባው የዋስትና ግዴታ ሙሉ በሙሉ ከኃላፊነት ነፃ ሊደረግ የሚችለው ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለባለገንዘቡ ከመወጣቱ ጋር በተያያዘ ስለመሆኑ | ጥቅምት 5/2000 |
| 84 | 26565 | ግሎባል ኢንሹራንስ /አ.ማ/<br>እና<br>ንብ ትራንስፖርት /አ.ማ/ | ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገመት ወይም ሊታሰብና ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚቻል ሁኔታ ድንገተኛ ደራሽ ቢሆን እንኳ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ (Force majeure) ተብሎ የማይወሰድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 1792(2) | ጥቅምት 19/2000 |
| 85 | 17742 | ወ/ሮ አበበች ታደሰ እና እነ አስር አለቃ ሲሳይ ካብትህይመር (አራት ሰዎች) | በህግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት የሚያስችል ማንኛውም ዳኛ ውል የማዋዋል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678(ለ) እና 1715 | መጋቢት 2/2000 |
| 86 | 23921 | ወ/ሮ ዘለቃሽ መንግስቱ እና አስር አለቃ ታደሰ ወርቁ | የስጦታ ውሉ በስጦታ ተቀባዩ ላይ ግዴታ ያልጣለ ቢሆንም እንኳን ስጦታ ሰጪው በድህነት ላይ መሆኑ ከተረጋገጠ ተቀባዩ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2458(1) | ጥቅምት 12/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 87 | 32337 | ወ/ሮ ፀሐይነሽ ይህደጐ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ትሕሽ በርሔ | “የቁም ኑዛዜ ስጦታ” ተራ የክፍያ ደንብ እንጂ ሌሎች ወራሾች ያላቸውን ውርሱን የመካፈል መብት የማይገድብ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 913 | ግንቦት<br>21/2000 |
| 88 | 22891 | ወ/ሮ ማና ኃ/ሚካኤል እና እነ አቶ ገ/ማርያም ከበደው<br>(ሁለት ሰዎች) | በጋብቻ ወቅት በአንደኛው ተጋቢ ምክንያት የተፈጠረ ዕዳ ለጋራ ጥቅም መዋሉ በተረጋገጠ ጊዜ የዕዳው ወደ የጋራ ንብረት ወይም ወደ ሌላኛው ተጋቢ የግል ንብረት በመሄድ ሊከፈል የሚችለው በፍርድ አፈፃፀም ላይ ስለመሆኑና ከዚህ ጋር በተያያዘ በሌላኛው ተጋቢ ላይ ዕዳውን መሠረት በማድረግ ክስ ሊመሰረትበትም ሆነ ፍርድ ሊሰጥበት የማይገባ ስለመሆኑ | ህዳር<br>24/2000 |
| 89 | 31737 | አቶ ገብሩ ገ/መስቀል እና ቄስ ገ/መድህን ረዳ | በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2472 መሠረት በባንክ የተሰጠ የሃዋላ ወረቀት ብድርን ለማስረዳት ስለመቻሉ | የካቲት<br>27/2000 |
| 90 | 24173 | የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና<br>ወ/ሮ አይዳ ሐሰን | በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት የተላከ ፖስታ /ዕቃ/ በመጥፋቱ፣ መሠረቁ፣ በመበላሸቱ፣ ወዘተ ምክንያት ካሣ የሚጠየቀው መጠኑም የሚወሰነው የፖስታ አገልግሎት ሕግን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 24/58 መሠረት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 24/58 አንቀፅ 50,51,53 እና 54 | ህዳር<br>11/2000 |
| 91 | 24574 | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ/ቤ/መ/ፖ/ጠ/ጽ/ቤት እና አቶ ይትባረክ ማህሉ | በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሣኔ ሳይሰጥበት የታለፈ ጉዳይ እንደተነፈገ ይቆጠራል የሚለው የሥነ- ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ | ህዳር<br>11/2000 |
| 92 | 25434 | የአዲስ አበባ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን<br>እና<br>ፋሬተርስ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግል ማህበር | በውል ውስጥ አጠራጣሪና ግልፅነት የጐደላቸው ጉዳዬች በፍ/ብ/ህ/ቁ.1738 መሠረት እልባት ሊሰጣቸው የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1738 | መጋቢት<br>25/2000 |
| 93 | 29369 | በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሆለታ<br>የግብርና ምርምር ማዕከል<br>እና<br>አቶ ተመስገን አድነው | • የባለዕዳው ቀጥተኛ የውል ፈፃሚነት ከውሉ ባህሪ አኳያ ማስፈፀም አለመቻል ውሉ እንዲሰረዝ መጠየቅ ሳያስፈልግ ኪሣራ ካለ መጠየቅ ስለመቻሉ<br>• በውል መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ ወገንን አስገድዶ ለማስፈፀም የማይቻል በሆነ ጊዜ በውሉ ግዴታውን የተወጣው ወገን ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰውን ኪሣራ ለመጠየቅ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771(1) እና (2) | መጋቢት<br>9/2000 |
| 94 | 19338 | ዘይነባ ሐሰን<br>እና<br>ፍሬው ተካልኝ | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ተጐጂ የሆነ ወገን የወደፊት ህይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚኖር ስለመሆኑ ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለ እንደሆነ ዳኞች ለተጐጂው የሚከፈለውን ካሣ በርትዕ መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102 | መጋቢት<br>2/2000 |
| 95 | 21296 | የኔዘርላንድ ልማት ድርጅት እና ውበት አድባሩ | የፍ/ብህ/ቁ. 2089 ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089(1) እና (2) | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 96 | 22509 | አቶ ግርማ ኃ/ጊዮርጊስ እና ዳርጊ ሰምሮ | የቀረበን ክስ ለማስረዳት አግባብነት የሌለው ማስረጃን መሠረት በማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | ጥቅምት<br>7/2000 |
| 97 | 24818 | ይልቃል በእውቀቱ እና ስዩም አባዲ | ጥቅም በሌለው ግንኙነት በመኪና ተሣፍሮ ሲሄድ አደጋ በመድረሱ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው ካሣ ሊጠይቅ የሚችለው የመኪናው ባለቤት ወይም ጠባቂው ጥፋት መፈፀሙን በማስረዳት ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089(2) | የካቲት<br>4/2000 |
| 98 | 27565 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ደምሴ ወርቅነት<br>(ሁለት ሰዎች) | ጉዳት ሊካስ የሚገባው ለደረሰ ጉዳት ብቻ ሳይሆን በጉዳቱ ምክንያት ለሚመጣ ኪሣራ ጭምር ስለመሆኑ | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 99 | 27623 | ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>ወ/ሮ ውባየሁ አበበ | • የማህበራዊ ዋስትና መብት ጥቅምን በሚመለከት የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንጂ መደበኛ ፍርድ ቤቶች የመዳኘት የሥረ ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>• የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 38/88 አንቀፅ 5,8 እና 11 | ህዳር<br>24/2000 |
| 100 | 28612 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና<br>የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን | ለደረሰ ጉዳት ሃላፊ የተባለ ሰው ላደረሰው ጉዳት ካሣ አይከፍልም ሊባል የሚችልበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2091 | የካቲት<br>25/2000 |
| 101 | 28750 | የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ከውልና ከውል ወጪ በሆነ ግንኙነት ከሁለት የተለያዩ የክስ ምክንያቶች የሚመነጭ ኃላፊነትን መሠረት በማድረግ በአንደኛው ግንኙነት ብቻ ተጠያቂ የሆነን ወገን ሁለቱን የኃላፊነት ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ካሣ እንዲከፍል በአንድነትና በነጠላ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2035, 1896 | ህዳር<br>24/2000 |
| 102 | 28865 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ ካሣ ግዛው | ንብረትን ከመስሪያ ቤት በኃላፊነት የተረከበ ሰው ንብረቱ በጠፋ ጊዜ ከንብረቱ መጥፋት ጋር በተያያዘ ጥፋት ያልፈፀመ መሆኑን ወይም ንብረቱ ከሥራ ሰዓት ውጪ የጠፋ መሆኑን የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2027 | ህዳር<br>24/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 103 | 30032 | የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ<br>እና<br>ወ/ሮ ምንትዋብ የኔነህ | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት የክልሉ መንግስት ቋሚ ሠራተኛ በስራ ላይ በደረሰበት ጉዳት የሞተ እንደሆነ ለተተኪዎች የጡረታ አበል እንጂ ሌላ ተጨማሪ ካሣ ሊከፈል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የአማራ ክልል አዋጅ ቁ.74/1994 አንቀፅ 46(5) (ሀ) | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 104 | 30442 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ሰሜን ምዕራብ ሪጅን እና ወ/ሮ ድንቋ አመኔ | • ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት የሞት አደጋ በደረሰ ጊዜ የሟች የቅርብ ዘመዶች ሊኖራቸው የሚችለው መብት እና<br>• የደረሰውን የሞት አደጋ ተከትሎ የሚቀርብ የቀለብ ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095 807, 812 | ህዳር<br>3/2000 |
| 105 | 31099 | የተንዳሆ እርሻ ልማት አ/ማ<br>እና<br>ወ/ሮ ርሻን አለማየሁ | ሟች ከመሞቱ በፊት ቀለብ የማይሰፈርለት ግለሰብ በሟች ሞት ምክንያት የጉዳት ካሣ በቀለብ መልክ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095, 2069(1) | ግንቦት<br>14/2000 |
| 106 | 32144 | ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር<br>እና<br>ወ/ሮ ኢልሻ ሲራጅ | • በሞት ምክንያት ቀረ የሚባል ጥቅም የሚሰላው ከጠቅላላው የሟች ደሞዝ ላይ የሚቀነሱት በህግ የታወቁት ተቀናሾች ተቀንሰው የሚገኘውን የተጣራ ገቢ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ<br>• የህሊና ካሣ ከአንድ ሺህ ብር ሊበልጥ የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2116 | መጋቢት<br>23/2000 |
| 107 | 32250 | ወ/ሮ አስናቀ ወ/ማሪያም እና እነ አቶ ከተማ ተሰማ<br>(ሁለት ሰዎች) | በሞት አደጋ ምክንያት የተቋረጠ የመተዳደሪያ ጥቅም ጋር በተያያዘ በየወሩ የሚከፈል ካሣ አከፋፈል ስርአት በፍርድ ቤት የተወሰነውን ካሣ አጠቃሎ በባንክ ወይም በሌላ የገንዘብ ተቋም በማስቀመጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095(2) | መጋቢት<br>25/2000 |
| 108 | 33975 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>ወ/ሮ አበበች ስዩም | የመሬት ይዞታ ባለቤት የሆነ ሰው ለህዝብ ጥቅም በሚል ይዞታውን በተጨባጪ እንዲለቅ ባልተደረገበት ሁኔታ ሊጠይቅ የሚችለው የካሣ ክፍያ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.455/97 አንቀፅ 7(1) | መጋቢት<br>25/2000 |
| 109 | 34138 | እነ ሲስተር ገነት ጌታቸው (ሁለት ሰዎች) እና<br>ወንድወሰን ኃይሉ ወልደ ማሪያም | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት የደረሰበት ሰው ከደረሰበት የአካል ጉዳት በተጨማሪ በደሞዝ ረገድ የቀረበት ጥቅም (ገቢ) መኖሩ ከተረጋገጠ ሊካስ የሚገባ ስለመሆኑ | ግንቦት<br>26/2000 |
| 110 | 34906 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የምስራቅ ሪጅን ጽ/ቤት<br>እና ወ/ሪት ፍሬሕይወት እርቄ | በሥራ ግንኙነት ውስጥ የቅርብ አለቃ የሆነ ሰው በሥሩ ያሉ ሠራተኞችን አስመልክቶ ለበላይ ኃላፊዎች የሚፅፈውና የሚልከው ሪፖርት ሥም ከማጥፋት ጋር በተያያዘ የፍትሐብሔር ሃላፊነት ሊያመጣበት የማይችል ስለመሆኑ | ግንቦት<br>5/2000 |
| 111 | 21740 | ወ/ሮ አስረስ መስፍን እና ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ | የጋብቻ ጽሁፍ በሌለ ጊዜ ጋብቻ መኖሩን ለማስረዳት የሚቻለው የባልና ሚስትነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 699(1), (2) | ጥቅምት<br>28/2000 |
| 112 | 23021 | ወ/ሮ አበባ ወርቅ ጌታነህ<br>እና<br>ወ/ሮ ዋጋዬ ኃይሌ | በፍቺ ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ የቀድሞ ተጋቢዎች እንደ ገና አብሮ መኖር የትዳር ሁኔታ መኖሩን የሚያስገነዝብ ከሆነ ጋብቻ መፈፀሙን የህግ ግምት መውሰድ የሚቻል ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 96 እና 97(1) | ሐምሌ<br>12/1999 |
| 113 | 23493 | ወ/ሮ እንማው ዘገየ እና ወ/ሮ ወርቁ መኮንን | በፍርድ ቤት ያልፈረሰ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በፈፃሚው ሞት ምክንያት የፈረሰ እንደሆነ የሟች ባለቤቶችን እኩል የጡረታ አበል የመከፈል መብት የሚሰጥ ስለመሆኑ | ሰኔ<br>26/1999 |
| 114 | 23632 | ወ/ሮ ፀዳለ ደምሴ<br>እና<br>አቶ ክፍሌ ደምሴ | ወላጆች ለህፃናት ልጆቻቸው ሞግዚትና አስተዳዳሪ የመሆን መብታቸው ሊከበር የሚችለው ለህፃናቱ ጥቅምና ደህንነት እስከሰሩ ወይም ሊሰሩ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ሲቻል ብቻ ስለመሆኑ<br>የደቡብ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስተ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 75/96 አንቀፅ 235(1), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 36(2) | ጥቅምት<br>26/2000 |
| 115 | 24625 | ወ/ሮ ሳድያ አሕመድ እና ወ/ሮ ሊህማ አሊ | በህግ ፊት ያልፈረሰ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በፈፃሚው ሞት ምክንያት የፈረሰ እንደሆነ የጋራ ሀብትን ሁለቱ ባለቤቶች ግማሹን ለሁለት ቀሪውን ግማሽ ልጆች የሚካፈሉ ስለመሆኑ | ጥቅምት<br>28/2000 |
| 116 | 25005 | መኮንን በላቸው እና ወ/ሮ አለሚቱ አደም | በጋብቻ ውል ላይ የግል ተብሎ ያልተመለከተና ጋብቻ ከመፈፀሙ በፊት ግንባታው የተጀመረ ቤት ግንባታው የተጠናቀቀው በጋብቻ ወቅት ከሆነ የጋራ ንብረት ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(1) , 63(1) | ህዳር<br>3/2000 |
| 117 | 25281 | ወ/ሮ መሠረት ፍስሐ<br>እና<br>አቶ ቀልቤሣ አለሙ | የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ነው በሚል የተወሰነ መኖሪያ ቤት ጋር በተያያዘ አንደኛው ተጋቢ ቤቱ የተሰራበትን መሬት (ቦታ) ከጋብቻው በፊት የተመራ በመሆኑ ሌላኛው ተጋቢ የቤቱን ግማሽ ዋጋ ተቀብሎ እንዲለቅ በሚል የሚሰጥ ውሣኔ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 92<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. አንቀፅ 1131,1132 | ጥር<br>29/2000 |
| 118 | 25588 | መርየንሃሰን ዑመር እና መውሊድ ተሽልእስማን | አንድ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን ያለው መሆኑና አለመሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ጉዳዩን ማየት ከመጀመሩ በፊት እንጂ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ስላለመሆኑ | የካቲት<br>6/2000 |
| 119 | 26839 | ወ/ሮ አስካለ ለማ<br>እና<br>ሣህለ ሚካኤል በዛብህ | ጋብቻ ከመመስረቱ በፊት የግል የነበረ ሃብት ከጋብቻ በኃላ የጋራ ከሆነ ንብረት ጋር ተቀላቅሎ በተገኘ ጊዜ የግል የሆነው ንብረት ተለይቶ የግሉ ለሆነው ተጋቢ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 57,86(1) | ህዳር<br>10/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 120 | 26953 | አቶ ብዙነህ ጨርቆሴ እና ወ/ሮ መዓዛ እንግዳዬ | በጋብቻ/በትዳር ላይ/ ከተጋቢዎች መካከል በአንደኛው ተጋቢ አማካኝነት በካሣ መልክ የተገኘ ሃብት የጋራ ሃብት/ንብረት/ ተደርጉ የሚቆጠር ስለመሆኑ | ህዳር 13/2000 |
| 121 | 27697 | አቶ ርዕሶም ገ/መድህን እና ወ/ሮ አልማዝ ጊላ ሚካኤል | ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የጋራ ንብረት የተሸጠ ቢሆንም የሽያጩ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል እንደሚገኝ ካልተረጋገጠ ለጋራ ትዳር ጥቅም እንደዋለ የህግ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 85 -93 | ጥቅምት 19/2000 |
| 122 | 27869 | ፍቅርና ሠላም ኃ/የተ/የግ/ማ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ<br>(ሁለት ሰዎች) | • የማይንቀሳቀስ ንብረት ለንግድ ማህበር በመዋጮ መልክ የተሰጠ ሆኖ ሲገኝ የንብረቱ ስም በኩባንያው ተመዝግቦ ያለመገኘቱ በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ለመሆን የማይችል ቢሆንም ንብረቱ በአይነት መዋጮ መስጠቱን የሚያስቀረው ስላለመሆኑ<br>• የጋራ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ያለ አንደኛው ተጋቢ ፈቃድ ለንግድ ማህበር በዓይነት መዋጮ የተሰጠ እንደሆነ ንብረቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 517(ሠ),(ረ)<br>የፍ/ብ/ሀ/ቁ. 2878<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(1), 69(2) | ህዳር 10/2000 |
| 123 | 29343 | እነ ወ/ሮ አምሳለ ተፈራ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ት አበባ አድማሱ | ተጋቢዎች በጋብቻ ወቅት የተፈራ ቤታቸውን በትርፍነት ለመንግስት ያስረከቡ እንደሆነ የአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረት የሆነን ቤት ያለምንም ተጨማሪ ስምምነት የጋራ የሚያደርገው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 47/67 አንቀፅ 11(1) | ሚያዝያ 7/2000 |
| 124 | 29402 | ወ/ሮ ሐዳስ ታረቀ እና የ፱ አለቃ አስመላሽ ኃይለስላሴ | ቤት የጋራ ሃብት ነው ከተባለ ቤቱ የተሰራበት መሬት ላይ የጋራ ባለሃብቶቹ እኩል የመጠቀም መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ | ጥቅምት 19/2000 |
| 125 | 30959 | እነ ወ/ሮ ተወዳጅ ገ/ሥሴሴ (ሁለት ሰዎች) እና<br>እነ አቶ ዘለቀ ዘውዱ( ሁለት ሰዎች) | • ሟች በኑዛዜው አንድን ሰው ልጄ አይደለም በማለት መግለፅ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማፍረስ የሚያበቃ ስላለመሆኑ<br>• በቤተሰብ ህጉ ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቻልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154,156,157 | ታህሳስ 1/2000 |
| 126 | 31430 | ወ/ሮ አዲስአለም አከለ እና የመቶ አለቃ አክሊሉ አበበ | ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የሚገኝ ድጉማ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ስለመሆኑ<br>የአማራ ብ/ክ/መ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 73(1) እና (2) | ሚያዝያ 7/2000 |
| 127 | 31891 | እነ አቶ አንለይ እንየው (ሰባት ሰዎች) እና ወ/ሮ መሬም ጠሃ | የተጋቢዎች ተለያይቶ ለረዥም ጊዜ መኖርና በዚህም ጊዜ ሌላ ትዳር መስርቶ መገኘት የቀድሞው ጋብቻ በህጋዊ መንገድ ተቋርጧል የሚያስብል ስለመሆኑ /የሰ/መ/ቁ. 14290/ | ሚያዝያ 14/2000 |
| 128 | 31946 | ወ/ሮ ዘውዲቱ ጌታቸው እና ተመስገን ደሳለኝ | የጋብቻ ውል በህግ አግባብ አልተደረገም በሚል ተቃውሞ ያቀረበ ተጋቢ በውሉ መሠረት ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 34(2), 35(2) እና 9(1) | ግንቦት 14/2000 |
| 129 | 32130 | እነ እማዋይሽ ካሣ (ስድስት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ አስቴር አህመድ | አንድን ሰው አባት ነው ብሎ ለማለት ለልጅ እንክብካቤ ማድረጉና ልጁም በእሱ ስም መጠራቱ ብቻ ሣይሆን ግለሰቡ ድርጊቱን አባት ነኝ ከሚል ስሜትና መንፈስ በመነጨ ያደርግ የነበረ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የአማራ ክ/መ/ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 79/95 አንቀፅ 154(ሐ)(ሠ) | መጋቢት 18/2000 |
| 130 | 33411 | ወ/ሮ ሙሉብርሃን አባዲ እና አለቃ ኪሮስ ገብሩ | ተጋቢዎች ጋብቻቸው ፀንቶ ባለበት ወቅት የገዙት ንብረት በስማቸው ያልዞረ ቢሆንም እንኳን ንብረቱ የእኔ ነው በሚል የቀረበ የ3ኛ ወገን ተቃውሞ እስካልቀረበ ድረስ ንብረቱ የጋራ ሀብት ተደርጐ የሚወሰድና ሊከፋፈል የሚገባ ስለመሆኑ | መጋቢት 25/2000 |
| 131 | 33440 | ወ/ሮ ኪሮስ ገ/ማርያም እና አቶ ግርማ ገብረ ስላሴ | • ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ ጥያቄ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ቀርቦ ሊስተናገድ የሚገባ ስለመሆኑ<br>• ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ የልደት ምስክር ወረቀት ተቃውሞ የማይቀርብበት የመጨረሻ ማስረጃ ተደርጐ ሊወሰድ የማይችል ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154 | ሚያዝያ 21/2000 |
| 132 | 33875 | ወ/ሮ የሻረግ አባትኩን እና ወ/ሮ መሠረት አድማሱ | ጋብቻ በባህላዊ መንገድ ተመስርቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብና መመስረቱን ማስረዳት የሚቻልበት ሁኔታ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 4 እና 97(2) | መጋቢት 25/2000 |
| 133 | 34149 | እነ ወ/ሮ ዘለቃሽ በቀለ እና አቶ አለሙ በቀለ | የአንድ ሰው አባት ነኝ በሚል የሚቀርብ ሰው አባትነቱን በህግ አግባብ በማስረጃ ማስረዳትና ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 147(1), 97(2) | መጋቢት 25/2000 |
| 134 | 34387 | አቶ ከበደ መሔ እና ወ/ሮ ፋናዬ ብዙነህ | የጡረታ አበል እንደማንኛውም ገቢ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ተደርጐ የሚወሰድ ስላለመሆኑ | ግንቦት 14/2000 |
| 135 | 35376 | እነ አቶ ዳንኤል አሰፋ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ ሔለን ውብቱ | ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት ላይ ያለን ዕዳ ለመወጣት ከጋብቻ በኃላ ከባልና ሚስት የጋራ ገንዘብ መከፈሉ ንብረቱን የጋራ ንብረት የማያደርገው ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(1) እና 70(1) | ግንቦት 28/2000 |
| 136 | 23389 | የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማ<br>እና<br>እነ ባህሩ አብርሃም (አስራ ሁለት ሰዎች) | የአክስዮን ማህበር አባላት የአክስዮን አስተዳዳሪዎች መብታቸውን በሚጐዳ መልኩ መስራታቸውን ማረጋገጥ ከቻሉ በቀጥታ መክሰስ የሚችሉ ስለመሆናቸው<br>የንግድ ህግ ቁ. 367 | ሐምሌ 10/1999 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 137 | 25306 | አቶ ተስፋዬ ገለቴ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ገንዘብን በአደራ ለማድረስ የተቀበለ ባንክ አደራ አስቀማጩ ይሰጥልኝ ላለው ሰው እስካልሰጠ ድረስ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 898(1) | ህዳር<br>12/2000 |
| 138 | 27161 | አቶ ኤልያስ ከፈለ<br>እና<br>እነ አቶ ከድር አህመድ (አራት ሰዎች) | የክሱ መሠረት የሆነው ጉዳይ መቅረቱን በክሱ ሂደት በማንኛውም ደረጃ የተረዳ ፍ/ቤት ክሱን መሰረዝ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280 | ህዳር<br>12/2000 |
| 139 | 28923 | የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር እና<br>.እነ የባህር ዳር ልዩ ዞን አስተዳደር (ሁለት ሰዎች) | የመንግስት ልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማህበራት ሲቀየር በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ያልታወቀና ውሣኔ ያልተሰጠበት እንኳን ቢሆን የልማት ድርጅቱ ዕዳ ወደ አክሲዮን ማህበር የማይተላለፍ ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 208/92 አንቀፅ 5(1), 6(1)ሐ | ግንቦት<br>7/2000 |
| 140 | 23608 | የኢትዮጵያ ፕራይቬተይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ እና የአቶ ኑርበዛ ተረጋ ወራሾች | በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲም ሆነ በኤጀንሲው ስራ አመራር ቦርድ ቀርቦ ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ እንደገና ለማየት ፍ/ቤቶች ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ.110/87 አንቀፅ 4(1) እና 5(3) | ህዳር<br>3/2000 |
| 141 | 27548 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ቆፀላ መርሻ (ሁለት ሰዎች) | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አጠራጣሪነቱ በታወቀ ጊዜ ከሚመለከተው አካል ተገቢውን ማብራሪያና ማስረጃ ሳይጠየቅ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1196(1) | መጋቢት<br>18/2000 |
| 142 | 29822 | የወረዳ 6 ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>ወ/ሮ በቀለች አማረብህ | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ስልጣን ላለው የአስተዳደር ክፍል መመለስና መሰረዝ ጋር በተያያዘ ፍ/ቤቶች የባለቤትነት ደብተሩ እንዳይመለስ በሚል ውሣኔ ለመስጠት የማይችሉ ስለመሆናቸው<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1196(1) | ግንቦት<br>28/2000 |
| 143 | 29860 | ወ/ሮ አስናቀች ሲሻው<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አሰለፈች ከተማ (አራት ሰዎች) | በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የባለቤትነት መብት ለመንግስት የተላለፈ መሆኑን እንደመከራከሪያ በማንሳት መሟገት የሚችለው የሚመለከተው የመንግስት አካል እንጂ ግለሰብ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ 47/67 አንቀፅ 13(1) | መጋቢት<br>18/2000 |
| 144 | 31490 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>ሴርኮ እስራኤላዊያን | ተከሳሽ የሆነ ወገን ካቀረባቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች መካከል ፍ/ቤቱ አንዱን ብቻ መሠረት በማድረግና ሌሎቹ ላይ ብይን ሣይሰጥ ክሱን ውድቅ ያደረገው እንደሆነ ብይን ባልተሰጠባቸው መቃወሚያዎች ላይ ይግባኝ ማቅረብ የማይጠበቅበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244,341 | ሚያዝያ<br>2/2000 |
| 145 | 31682 | አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ ዘላለም ይልማ ባልቻ<br>( ሦስት ሰዎች) | ተወርሰዋል ተብለው በመንግስታዊና ህዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ሥር ያሉ ቤቶች ጋር በተያያዘ ይመለሱልኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መሠረት በማድረግ ፍ/ቤቶች መወረስና አለመውረስን በተመለከተ ማስረጃዎችን መርምሮ ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 47/67<br>አዋጅ ቁ.110/87 | መጋቢት<br>12/2000 |
| 146 | 32376 | አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሸዋንግዛው | የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸው ቤቶች ላይ የባለቤትነት /የባለቤትነትን መፋለም/ ክርክር በተነሣ ጊዜ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የማይኖራቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀፅ 41(ረ) | ግንቦት<br>19/2000 |
| 147 | 34249 | እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ<br>እና<br>እነ አቶ አለሙ ወንድሙ | በክርክር ተካፋይ እንዲሆን የሚያስፈልግ ወገንን ተከራካሪ ወገኖች እንዲገባ ያልጠየቁ ቢሆንም ፍ/ቤቶች ይህንኑ ወገን በራሳቸው ተነሣሽነት በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2) | ሚያዝያ<br>28/2000 |
| 148 | 22857 | እነ አቶ ተክሌ ደግፌ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>እነ አቶ በፍቃዱ ኃይሌ<br>(ሁለት ሰዎች) | • በፍርድ ሂደት ላይ ያለ ጉዳይን ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በክርክሩ ማናቸውም ደረጃ ላይ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጪ በእርቅ እንዲያልቅ ለመጠየቅ የሚችሉ ስለመሆናቸው<br>• በፅሁፍ ተዘጋጅቶ የቀረበ የእርቅ ስምምነት ለፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ስምምነቱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑን አረጋግጦ በፍ/ቤት የተያዘውን ጉዳይ ማቋረጥ የሚገባው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 274(1),275,(1),277(1) | ታህሳስ<br>15/2000 |
| 149 | 25912 | አቶ ብሩ ቆርቾ እና አቶ ክፍሌ ሐብደታ | የግልግል ስምምነት እንደመጨረሻ ፍርድ የሚቆጠር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3312 | ሚያዝያ<br>2/2000 |
| 150 | 29386 | ወ/ሮ ወለላ ተሰማ<br>እና<br>እማሆይ በላይነሽ መለሰ | ከወራሾች መካከል አንዱ በሌለበት የተካሄደ የንብረት ክፍፍል በሌለበት ክፍያው የተፈፀመበት ወራሽ በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1080 | የካቲት<br>25/2000 |
| 151 | 30536 | ወ/ት አለምነሽ ዋቅቶላ እና አቶ ይልቃል ጌጤ (ሁለት ሰዎች) | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት ሳያደርስ ወገን የመድን ሽፋን የሰጠ አካል በሃላፊነቱ መጠን ለተጐጂው መካሱ ተጐጂው በጉዳት አድራሹ ላይ የሚያቀርበውን ተጨማሪ (ቀሪ) የካሣ ጥያቄ የሚከለክል ስላለመሆኑ | መጋቢት<br>23/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 152 | 20036 | ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>ወ/ሮ ወለተብርሃን ካሣዬ | ጋብቻ የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ለማሳየት /ለማረጋገጥ/ የሚቻል ስለመሆኑና ይህንንም ለማስረዳት ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ሊቀርብ ስለመቻሉ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 95,96 እና 97 | ግንቦት 16/1998 |
| 153 | 25899 | የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ር ስዩም ካሣ | የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ ደሞዝ በሚያስገኝ የመንግስት ስራ ላይ ከተቀጠረ የቅጥሩ ሁኔታ በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት ከደሞዝ በተጨማሪ የወሰደውን የጡረታ አበል መመለስ ያለበት ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 209/55 አንቀፅ 30(2) | ግንቦት 28/2000 |
| 154 | 26480 | የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ<br>እና<br>አቶ ቢንያም አለማየሁ | ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ የተሰጠባቸው ጉዳዩችን አይተው ለመወሰን ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ<br>አዲስ አበባ አስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 12/91 አንቀፅ 9(4) | ጥቅምት 14/2000 |
| 155 | 28883 | ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>ሚስተር ኒኮላ አስፓፓቻት ዚስ | ከተከራካሪ ወገን አንዱ የውጭ ሀገር ዜጋ ስለሆነ ብቻ ክርክሩ ሁልጊዜ የግለሰብ አለማቀፍ ሕግ ጥያቄ ያስነሳል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 11(2)ሀ | ህዳር 26/2000 |
| 156 | 29005 | አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ግርማቸው ይላላ (ሁለት ሰዎች) | በክፍለ ከተማ ስልጣን ክልል ውስጥ የሚነሱ ክርክሮች ላይ ክፍለ ከተማው ጣልቃገብቶ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 361/95 አንቀፅ 10(2),30<br>አዋጅ ቁ. 18/97 አንቀፅ | ሚያዝያ 14/2000 |
| 157 | 30298 | አቶ የሲወንድም አቡሕይ<br>እና<br>አቶ አየነው ማለደ | ጠፋ የተባለ ሰው በተመለሰ ጊዜ ንብረቶቹ የተሸጡ ከሆነ ለማግኘት መብት የሚኖረው የንብረቶቹን የሽያጭ ዋጋ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 171(1) | ጥር/2000 |

**ቅጽ 6**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 158 | 08751 | ወ/ሮ አበበች በጅጋ እና እነ ዶ/ር ተስፋዬ አካሉ<br>(ሁለት ሰዎች) | • ፍርድ ከተሰጠ በኋላ አዲስ ማስረጃ ተገኝቷል በሚል የተሰጠው ፍርድ በድጋሚ ሊታይ የሚችልበት አግባብ<br>• ውሣኔ ያልተሰጠበት ጉዳይ በድጋሚ ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ሊቀርብበት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 | ግንቦት 26/2000 |
| 159 | 19142 | አቶ መላኩ ማሞ እና እነ ወ/ሮ ፈለቀች ማሞ<br>( ሦስት ሰዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጋር በተያያዘ በሚሰጥ ብይን ላይ ፍ/ቤቱ በሥረ- ነገር ረገድ የመጨረሻ ውሣኔ ሣይሰጥ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320 (3) | ጥቅምት 26/2000 |
| 160 | 20465 | አዋሽ ኢንተርናሽናል ኩባንያ እና<br>ፀሐይ ዮሐንስ የህፃን ተመስገን ቱጂ ሞግዚትና አሳዳሪ | በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሠረት የቤንሻንጉልን ጨምሮ የአምስት ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ባላቸው የውክልና ስልጣን ያዩዋቸውን የፌዴራል ጉዳዩች በይግባኝ ተቀብለው የማየት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 322/95, የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 80(2) | ሰኔ 26/2000 |
| 161 | 21270 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ<br>እና<br>ወ/ሮ ወይንሸት አበራ | አንድ ንብረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከመታገዱ በፊት በባንክ በመያዣነት የተያዘ እንደሆነ ባንኩ በህግ ተሰጠው መብት መገልገል ይችል ዘንድ ፍ/ቤት የሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ ማስነሳት የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 158, አዋጅ ቁ. 97/90 | ሐምሌ 30/1999 |
| 162 | 22556 | ታደሰ አብዛ እና እነ የአቶ ጉሳዬ ሩገቶ ወራሾች<br>(ሁለት ሰዎች) | በክርክር አመራር ሂደት የተከራካሪ ወገኖች የመሰማት መብት ተግባራዊ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ | ጥቅምት 14/2000 |
| 163 | 22603 | የድሬዳዋ ጊዜ/አስ/ቀበሌ 20 ጽ/ቤት<br>እና<br>ወ/ሮ ሽሪፍ አሊ | ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ልዩነት ያላቸው በመሆናቸው ጥርጣሬን የፈጠሩ እንደሆነ ፍ/ቤት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ ጥርጣሬ ያለበትን ጉዳይ አጥርቶ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 255,257 | ሐምሌ 26/1999 |
| 164 | 23363 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ፈርሀን አህመድ<br>(ሦስት ሰዎች) | የመድን ሰጪ አካል ኃላፊነት በመድን ሽፋን ፖሊሲው ላይ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በላይ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 665(2) | ግንቦት 26/2000 |
| 165 | 23628 | ሶሎ ሲርካርና ኤ.ኤስ እና እነ.ጌትያን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ<br>(ሁለት ሰዎች) | በውጭ ሀገር ተመዝግቦ የህግ ሰውነት ያገኘ ኩባንያ በኢትዮጵያ የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ አቅርቦ በሂደት ላይ ያለ መሆኑ በውጭ አገር ያገኘውን የህግ ሰውነት ቀሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 100 | ጥቅምት 21/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 166 | 23692 | አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ<br>እና<br>እነ አሊ መሐመድ | • የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 ሊተረጐም የሚችልበት አግባብና አፈፃፀሙ<br>• በሦስተኛ ወገን ተከሳሽነት በክርክር ውስጥ እንዲገባ የተደረገ ወገን ከተከሳሽ ጋር ከመሟገት በቀር ተከሳሹን ተክቶ ከሣሽን መከራከር አይችልም ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 687, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2), 43 | ሐምሌ<br>03/1999 |
| 167 | 23744 | አቶ በቀለ በድዬ እና እነ ወጋገን ባንክ አዋሳ ቅርንጫፍ<br>(ሦስት ሰዎች) | ዳኝነት ሣይከፈል በነፃ ክስ እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ በሚል አቤቱታ አቅርቦ ጥያቄው በፍ/ቤት ትዕዛዝ /ውሣኔ/ ውድቅ የተደረገበት ተከራካሪ ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320(1), (3) | ሐምሌ<br>26/1999 |
| 168 | 23769 | ኢንጅነር ጋሪፉፋ እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ጥናት<br>ኢንስቲትዩት | ከአገልግሎት ብዛት ከጥቅም ውጭ የሚሆኑና ሊያስረክቧቸው የማይችሉ ዕቃዎች ላይ የዋጋ ግምታቸውን መጠየቅ የክሱ ምክንያት ቀሪ በሆነ ነገር ላይ ክስ እንደመመስረት የሚቆጠር ስለመሆኑ | ሐምሌ<br>12/1999 |
| 169 | 24111 | የቂርቆስ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን<br>እና<br>ወ/ሮ የዕለተወርቅ ገ/አብ | የተከሳሽን መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ተከሳሽ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ተከሳሹ ሊያጣ የሚችለው መልሱን በፁሁፍ የማቅረብ መብቱን ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70(ሀ), 195 | የካቲት<br>11/2000 |
| 170 | 24627 | ዶ/ር ቤተልሄም ታደሰ እና የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ | ከቤት ባለቤትነት ክርክር ጋር በተያያዘ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት በመመሪያ፣ በቀላጤ ወይም በቃል ትዕዛዝ ከግለሰቦች የተወሰደና በመንግስት ቁጥጥር ሥር ያለ መሆኑ ካልተገለፀ በስተቀር ጉዳዩን ለማስተናገድ ፍ/ቤቶች ስልጣን የሚኖራቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.110/ 87 አንቀፅ 3(1) | ሚያዝያ<br>30/2000 |
| 171 | 24775 | ማታዶር አዲስ ጉማ<br>እና<br>ቢተው ረታ | ተከሳሽ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘበት ዕለት ባለመቅረቡ ብቻ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ በሚል የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241(1), 233 | ጥቅምት<br>21/2000 |
| 172 | 25026 | ወ/ሮ ሁዳ መሐመድ<br>እና<br>ሃጂ አህመድ አህመዲን | ተከሳሽ በራሱ ቸልተኝነት በታችኛው ፍርድ ቤት መከራከሪያ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ነጥቦችን በስር ፍርድ ቤት ባላነሳበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት አንስቶ ውሣኔ መስጠት የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 328(2) እና 182(2) | ግንቦት<br>14/2000 |
| 173 | 25890 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ዝናሽ አሰፋ<br>(ሁለት ሰዎች) | ሌሎች ተከራካሪዎች በፍርድ ቤት በማካሄድ ላይ ባሉት ክርክር ያገባኛል የሚል 3ኛ ወገን ከውሣኔ በፊት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 | መጋቢት<br>18/2000 |
| 174 | 26670 | አዲስ አለም ሲሳይ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | ባለገንዘብ በፍርድ አፈፃፀም ከፍርድ ባለዕዳው የተረከበው ንብረት ከዕዳው በላይ ከሆነ ልዩነቱን ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 428(2) | ህዳር<br>03/2000 |
| 175 | 27739 | አቶ ድንቁ ገላው<br>እና<br>ወ/ሮ ዋለ እሸቴ | ከመሬት ሽያጭ ውል ጋር በተያያዘ የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለውና በፍ/ቤት ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(2) | ጥቅምት<br>28/2000 |
| 176 | 27808 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ ማይገነት ብርሃኑ<br>(ሁለት ሰዎች) | ከፍርድ በፊት የሚሰጥ የማገጃ ትዕዛዝ በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነን ወገን የእግድ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት ያገኘውን መብት የማይነካ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 153 (2) | የካቲት<br>7/2000 |
| 177 | 28522 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ የሞያሌ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት (አራት ሰዎች) | ውሣኔ የተሰጠበትና አዲስ ክስ የቀረበበት ክርክር የሥረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ የተለያየ ከሆነ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | ህዳር<br>3/2000 |
| 178 | 28802 | እነ ወ/ሮ በየነች ይገዙ እና አቶ ሳሙኤል ዝቅአርጋቸው | በክስ በተጠየቀውና በታመነው መሰረት ውሣኔ መስጠት የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.182(2) | ታህሳስ<br>8/2000 |
| 179 | 29738 | የአፓርታማ 79/6 የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር<br>እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት እና ወ/ት ዘርአዳም<br>አስገኘሽ | የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይግባኝ አይቶ መወሰን የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 10(1) | ግንቦት<br>14/2000 |
| 180 | 29761 | እነ አቶ ዳባ ደበሌ (አምስት ሰዎች) እና እነ የአቶ ደበበ<br>ተፈራ ወራሾች (ሁለት ሰዎች) | ያላግባብ በመንግስት የተወረሰ ንብረትን ለማስመለስ ሲባል የሚቀርበው የፍትሐብሔር ክርክር በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ስር የማይወድቅ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 41(ሀ) | ጥቅምት<br>14/2000 |
| 181 | 29780 | እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ አለሙ እና ወ/ሮ ከተማሽ ቸርነት | አስቀድሞ ውሣኔ ከተሰጠበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሌላ የክርክር ጭብጥ ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | ጥር<br>29/2000 |
| 182 | 30631 | ወ/ሮ ዘቢዳ ሙሣ እና እነ ወ/ሮ አሻ የሱፍ (ሁለት ሰዎች) | በህገ ወጥ መንገድ ተወስዷል /ከአዋጅ ውጭ ተወርሷል/ የተባለ ቤትን ባለቤትነት በማጣራት ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 110/87 | ህዳር<br>10/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 183 | 30704 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ የአቶ በቀለ ወ/ማሪያም ወራሾች<br>(ሦስት ሰዎች) | • አዋጅ ቁጥር 47/67"ን" መሠረት አድርጕ የምርጫ ቤቱ ተወስዷል /ተወርሷል/ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርበው መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ<br>• በመንግስታዊና በህዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ስር ያሉ ቤቶች ይመለሱልኝ እንዲሁም ውዝፍ ኪራይ ይከፈለኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ ውሣኔ መስጠት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ የፍ/ቤት ስልጣን ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 110/87, አዋጅ ቁ. 47/67 | መጋቢት<br>18/2000 |
| 184 | 31547 | አቶ ኪዳኔ ገ/ጊዮርጊስ እና ወ/ሮ አብርሃ ተስፋሁን | ተከራካሪ ወገኖች በግልጽ ባላመለከቱት ነገር ላይ ተመስርቶ ውሣኔ መስጠት ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.182 | መጋቢት<br>7/2000 |
| 185 | 31833 | ሀጅ አብዱልቃድር አህመድ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ደስታ ገ/ዮሐንስ (ሁለት ሰዎች) | በቤት ላይ የተደረገ እድሳትና ለውጥ ምን ያህል የመጠንና የአይነት ለውጥ እንዳመጣ ክርክር በተነሣ ጊዜ ልዩ አዋቂ መድቦ በማስጠናት መወሰን የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136 | ግንቦት<br>14/2000 |
| 186 | 32147 | አቶ መሐመድ አብዱ<br>እና<br>አቶ አብዱራሂም አብዲ | የክስ ምክንያት የሌለው አቤቱታ ተቀባይነት የማይኖረው በመሆኑ ተከሳሽ የሆነውን ወገን መጥራት ሳያስፈልግ መዝገቡ ሊዘጋ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(1) (ሀ) | መጋቢት<br>9/2000 |
| 187 | 32376 | የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሸዋንግዛው | ከቤት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ባለቤትነትን የመፈለም ክስ ለማየት የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የስረ-ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 41(ረ) | ግንቦት<br>19/2000 |
| 188 | 32638 | የቂርቆስ ክ/ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ጉዳይ ጽ/ቤት እና እነ አቶ ይርጋ ንጋኔ (አራት ሰዎች) | ወደ ክርክር መግባት ያለበት አካል በክርክሩ ተሳታፊ ሳይሆን የተወሰነው ውሣኔ መብቱን የሚነካ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔው ከመፈፀሙ በፊት ውሣኔው እንዲነሳና ክርክሩ እርሱ ባለበት እንዲቀጥል መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 | መጋቢት<br>12/2000 |
| 189 | 33606 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ አቶ ደጀኔ አበበ (አምስት ሰዎች) | በጊዜያዊነት የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሣ ጥያቄ ቀርቦ ውድቅ ከተደረገ በኋላም ቢሆን በድጋሚ በተመሳሳይ ሁኔታ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሣ ጥያቄ ሊቀርብ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158 | የካቲት<br>20/2000 |
| 190 | 34249 | እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ<br>እና<br>እነ አቶ አለሙ ወንድሙ | ለክርክር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ የሚታመን ወገን በመካሄድ ላይ በሚገኝ ክርክር ተካፋይ እንዲሆን መደረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2) | ሚያዝያ<br>28/2000 |
| 191 | 34313 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>ከበደ ታደሰ | የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብ ተከሳሽ ኃላፊነት የሚመነጨው ከተከሳሹ ኃላፊነት ስለመሆኑ እና የሦስተኛ ወገን ተከሳሽ ተጠያቂ የሚሆነው ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ ሲኖር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.43(1) | መጋቢት<br>25/2000 |
| 192 | 35403 | አቶ አብዱልነጠፍ ሙሔ<br>እና<br>እነ ትዕግስት በርሃ<br>(ሁለት ሰዎች) | • ተከሳሽ ቀርቦ ያልተከራከረው በበቂ ምክንያት ማለትም መጥሪያ ሳይደርሰው መሆኑ ከተረጋገጠ የተወሰነውን ውሣኔ በማንሳት ግራ ቀኙን ማከራከር የሚገባ ስለመሆኑ<br>• ፍ/ቤት ተከራካሪ የሆነን ወገን መከላከያ ክርክር ሳይሰማ በማለፍ ውሣኔ ለመስጠት የሚችለው ተከራካሪው በችሎት ሳይቀርብ የቀረው በቂ ባልሆነ ምክንያት መሆኑን በቀረቡለት ማስረጃዎች ማረጋገጥ ሲችል ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.78 | ግንቦት<br>14/2000 |
| 193 | 22008 | የኪራይ ቤቶች አ/ድርጅት እና እነ አቶ ኦላና ጥርቅ ( ሦስት ሰዎች) | መክፈል የማይገባውን የከፈለ ወገን እንዲመለስለት መጠየቅ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.2164 | ሐምሌ<br>3/1999 |
| 194 | 22297 | የጅሚ ከተማ የአካባቢ አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ሸዋረገድ አድበር | በፍ/ብሔር ክርክር ሂደት ማን ክርክር መጀመርና ማስረዳት እንዳለበትና የተሻለ ማስረጃ ከማቅረብ አንፃር ለማን ፍርድ ሊሰጥ እንደሚገባ በተመለከተ አግባብነት ያላቸውን የህግ መርሆዎች ወደጎን በመተው የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የማይኖረው ስለመሆኑ | ሐምሌ<br>24/1999 |
| 195 | 22469 | የጀጀጋ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክ እና እነ አዳነት መንግስቱ (ሰባት ሰዎች) | • የህዝብ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ሊረጋገጥ የሚችልበት አግባብ<br>• የቤተክርስቲያንን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ለማረጋገጥ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ አስገዳጅ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1578 | ሐምሌ<br>5/1999 |
| 196 | 22719 | የአ/አ ከተማ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ተተኪ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ ነጋሽ ዱባለ | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን አስመልክቶ በሚመለከተው አካል የሚሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰረዘ በኋላ በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የማይኖረው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195 | ጥቅምት<br>14/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 197 | 23608 | የኢትዮጵያ ፕራይቬታዜሽና የመንግስት ልማት ድርጅት<br>እና<br>አቶ ኑርበዛ ተረጋ | • የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በሰጠው ውሣኔ ላይ ቅሬታ ሊቀርብ የሚችለው ለኤጀንሲው የስራ አመራር ቦርድ እንጂ ለፍ/ቤት ስላለመሆኑ<br>• የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻና አሣሪ (Binding) ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.110/87 | ህዳር<br>3/2000 |
| 198 | 24269 | የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር እና<br>ተክለማሪያም መኮንን | • ግለሰቦች በከተማ ቦታ የመጠቀም /የመያዝ/ መብት የሚኖራቸው አግባብ ባለው መንግስት አካል /ባለሥልጣን/ ተፈቅዶ ሲሰጣቸው ስለመሆኑ<br>• ከሚመለከተው ባለስልጣን ፈቃድ ሳይኖር የተሰራ የከተማ ቤት ህጋዊነት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 292/78 አንቀፅ 7(1) | ህዳር<br>24/2000 |
| 199 | 26130 | አቶ ገ/እግዚያብሔር ከበደው<br>እና<br>ወ/ት ሰላማዊት ወ/ገብርኤል | • የከተማ ቦታ በግል ባለቤትነት ሊያዝ የማይችል ስለመሆኑ<br>• ግለሰቦች በመሬት ላይ ሊኖራቸው የሚችለው የይዞታ መብት እንጂ የባለቤትነት መብት ስላለመሆኑ<br>• ከጋብቻ በፊት በአንደኛው ተጋቢ የግል ይዞታ ሥር የነበረ መሬት ላይ በጋብቻ ወቅት የጋራ ቤት የተሰራ እንደሆነ ተጋቢዎቹ በመሬቱ ይዞታም ሆነ በቤቱ ላይ እኩል መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 47/67<br>የኢ...ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 40(3)<br>የትግራይ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 85 | የካቲት<br>4/2000 |
| 200 | 27506 | እነ ሣሙኤል ውብሸት<br>እና<br>ብዙነህ በላይነህ | • ሁከት እንዲወገድ በሚል በቀረበ ክስ ላይ ተከሳሽ የሚያነሳው ባለቤትነትን የተመለከተ ክርክር አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>• ሁከት ይወገድልኝ በሚል ክስ በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ሊይዝ የሚገባው ጭብጥ ሁከት ተፈጥሯል ወይስ አልተፈጠረም የሚል ጥያቄ አዘል መሆን ያለበት ስለመሆኑ | ሐምሌ<br>19/1999 |
| 201 | 27600 | ሕብረት ባንክ አክሲዮን ማህበር እና<br>እነ አቶ ጀማል መሐመድ<br>(ሁለት ሰዎች) | በመያዣ በተያዘ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በማሻሻልም ሆነ ሌሎች አዲስ የሚሰሩ ስራዎች መያዣው የሚያጠቃልላቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.3066 | ታህሳስ<br>06/2000 |
| 202 | 29005 | አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና እነ ግርማቸው ይላላ<br>(ሁለት ሰዎች) | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚገኙና በየክፍለ ከተማው የተደራጁ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤቶች ራሳቸውን የቻሉ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ስለመሆኑና በስልጣን ክልላቸው ሥር በሚነሱ ክርክሮች ተካፋይ የመሆን መብት ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 36/95 አንቀፅ 10(2)<br>አዋጅ ቁ. 1/95 /አዋጅ ቁ. 18/97 | ሚያዝያ<br>14/2000 |
| 203 | 30101 | አቶ ገዛኸኝ አድነው እና እነ ወ/ሮ ዳሳሽ ባይነሳኝ<br>(ሦስት ሰዎች) | በሌላ ሰው የመሬት ይዞታ ላይ በባለይዞታው ፈቃድ ህንፃ የሠራ ሰው የህንፃውን ግምት ተቀብሎ ህንፃውን ለማስረከብ የማይገደድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179(1) እና (2) | ህዳር<br>24/2000 |
| 204 | 30461 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ ኢሣ መሐመድ | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን መሬትና ድንጋይ ነክ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶችን በነፃ መጠቀም የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 80/89 አንቀፅ 6(18) | ህዳር<br>3/2000 |
| 205 | 33499 | አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ ዶቶር ደሌቦ | ለጊዜው ለመኖሪያነት የተሰጠ ቦታ ላይ ሳያስፈቅዱ ቤት መስራት የተሰራውን ቤት በገንቢው ወጪ እንዲፈርስ የሚያስደርግ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1178(2) | መጋቢት<br>25/2000 |
| 206 | 33711 | በቀድሞ ወረዳ 3 ቀበሌ 07 አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ክብርነሽ ቀደመ | የቤት ባለቤት ሳይሆን ወይም ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ለኪራይ የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስ የሚቀርብ አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ | መጋቢት<br>23/2000 |
| 207 | 33831 | ሃሰን ኢብራሂም እና ኢብራሂም ይመር ሃሰን | በህግ በግልጽ የተረጋገጠ መብት እያለ በህሊና ግምት ላይ የተመሰረተ ፍርድ መስጠት አግባብ ስላለመሆኑ | ሚያዝያ<br>14/2000 |
| 208 | 33924 | ወ/ሮ ገብርኤላ ኒኮላቶማስ<br>እና<br>የኪራይቤቶች ኤጀንሲ | ከቤት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ክስ የሚያቀርብ ሰው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካላቀረበ በስተቀር ሁልግዜም ቢሆን በጉዳዩ ላይ መብት ወይም ጥቅም ሊኖረው አይችልም ብሎ ለመደምደም የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195(1) | ሚያዝያ<br>16/2000 |
| 209 | 34406 | ወ/ሮ መገርቱ ነጋሣ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ፀሃይ ልጋ | ያላግባብ መበልፀግ ጋር በተያያዘ የሚነሳ የካሣ ጥያቄ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብ ከውል ውጭ በሚደርስ ሃላፊነት ሥር የተመለከተው የይርጋ ዘመን ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143(1) | ሚያዝያ<br>7/2000 |
| 210 | 20295 | አቶ ደጀኔ ለገሠ<br>እና<br>እነ አቶ መላኩ ጌታቸው | ወራሽነትን ካረጋገጡ በኋላ ንብረት ተይዞብኛል ይመለስልኝ የሚል ጥያቄ ከሦስት አመት በኋላ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(1) | ሐምሌ<br>5/1999 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 211 | 25567 | ወ/ት አይናለም አበበ<br>እና<br>አቶ ደገፉ ጉርሙ | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000 ወራሽ ነኝ ወይም ወራሽነቱ ይረጋገጥልኝ ከሚል ጥያቄ ጀምሮ የውርስ ንብረት ያለ አግባብ ተይዞብኛል በሚል ለሚቀርብ አቤቱታ ጭምር ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 999, 1000 | ህዳር<br>12/2000 |
| 212 | 25664 | አቶ ተገኝ ይማም<br>እና<br>እነ አቶ ካሣሁን ደሳለኝ | በወራሾችና ወራሽ ባልሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሳ የውርስ ንብረትን የተመለከተ ክርክር በአሥር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 | ግንቦት<br>7/2000 |
| 213 | 26422 | ወ/ሮ ስንልሽ ማዘንጊያ<br>እና<br>እነ አቶ ተስፋ ማዘንጊያ | ከውርስ ሀብት ጋር በተያያዘ ወራሽ ነኝ የሚል ወገን መብቱንና የውርስ ንብረቶቹ በሌላ ወራሽ መያዛቸውን ካወቀ ከሦስት ዓመት በኋላ የሚያቀርበው የወራሽነት ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(1) | ጥቅምት<br>28/2000 |
| 214 | 28686 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ ግዛው መንጀታ | ውል የመጣስ ተግባር ተጀምሮ ያልቆመ ይልቁንም በመቀጠል ላይ ያለ ተግባር መሆኑ በማናቸውም ጊዜ ግዴታን ለመጠየቅ የሚያስችል ስለመሆኑና በይርጋ ታግዷል ለማለት የማያስችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845, 1846 | ህዳር<br>24/2000 |
| 215 | 28997 | ስለ አሶሳ ዞን ግብርና እና ትምህርት መምሪያ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መንግስት ፍትህ ቢሮ<br>እና በላይ ወርቁ | የመብት ጥያቄን ከፍርድ ቤት ውጪ ላሉ አስተዳደር አካላት ማቅረብ የይርጋ ጊዜን የማያቋርጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1851(ለ) | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 216 | 29920 | የባህር ዳር ጨ/ጨ/አ/ማኅበር እና አቶ አመሸ ሰይድ | ዳኝነት የተጠየቀበት ነገር ተቀባይነት ሣያገኝ የታለፈ እንደሆነ እንደተከለከለ የሚቆጠር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(3) | ጥቅምት<br>26/2000 |
| 217 | 31185 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ይርጋ በተቋረጠ ጊዜ ቀድሞ የነበረው የይርጋ ጊዜ እንደ አዲስ መቆጠር የሚጀምር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1852(1) | ግንቦት<br>12/2000 |
| 218 | 31217 | የቴሌኮምኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ጫሊ ሐሰን | የደሞዝ ጭማሪና ቦነስን የተመለከተ ክስ በስድስት ወር ውስጥ አለመቅረቡ መብቱን በይርጋ የሚያሳግድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 162(3) | ግንቦት<br>14/2000 |
| 219 | 31857 | መሐመድ አብደላ<br>እና<br>የድሬዳዋ ኢትዮ ጂቡቲ ምድር ባቡር | የአሰሪ የስራ ስንብት እርምጃ የመውሰድ መብት ለስንብቱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ከተከሰተበት ጀምሮ በሰላሳ የስራ ቀናት ውስጥ ተግባራዊ ካልሆነ መብቱ በይርጋ የሚቀር ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/97 አንቀፅ 27(3) | መጋቢት<br>17/2000 |
| 220 | 32788 | የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት<br>እና<br>አቶ ግርማ ተገኝ | አሠሪ የሠራተኛን መብት በጽሁፍ ያወቀ መሆኑ ሠራተኛው በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ገደብ የሚያቋርጥ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 164(3) | መጋቢት<br>18/2000 |
| 221 | 34011 | እልፍነሽ አማረ እና አቶ ግርማ አማረ | ቤት በፍ/ብሔር ህጉ ውስጥ እንደ ርስት የማይቆጠርና የይርጋ መርሆ ተፈፃሚ የሚሆንበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(2) | መጋቢት<br>25/2000 |
| 222 | 31748 | ይስማው ድረስ<br>እና<br>ይበልጣፍ ፍቅር | ክርክር የቀረበበትን ጉዳይ የሚገዛው የህግ ክፍል ይርጋን አስመልክቶ በተለይ የሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ በሌለ ጊዜ የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677(1),1845 | የካቲት<br>18/2000 |
| 223 | 18832 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>እነ አቶ ከበደ ቱሉ<br>(ስድስት ሰዎች) | ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ የተወሰነው ጊዜ ከማብቃቱ በፊት የስራ ውሉ ያለ በቂ ምክንያት ከተቋረጠ ሠራተኛው የውሉ ጊዜ ወይም ስራው እንኪያልቅ ቢቆይ ያገኘው የነበረውን ደሞዝ የሚያህል ደሞዝ የሚከፈለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 43(4)(ለ) | ህዳር<br>3/2000 |
| 224 | 20416 | አቶ ቢንያም ገረመው<br>እና<br>የቻይና መንገድና ድልድል ስራ ድርጅት | ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ፍርድ ቤት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራ ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ከሆነ ክሱ እንዲሻሻልና ክርክሩ እንዲለወጥ ሊፈቀድ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91 | ታህሣሥ<br>8/2000 |
| 225 | 21329 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ በቀለ ኩምሳ | የሥራ መሪ የሆነ ሰው የሥራ ውሉ ተቋርጧል በሚል ሣይሰራ ለቆየበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈለው የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | ጥቅምት<br>19/2000 |
| 226 | 22275 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>አቶ ኃይሌ ገ/ሥላሴ | • አሰሪ የሥራ ውሉ ዘመን ከማለቁ በፊትም ቢሆን በቂና ህጋዊ ምክንያት ካለው የሠራተኛን የሥራ ውል ሊያቋርጥ ስለመቻሉ<br>• በበቂ ምክንያት የተደረገ የሥራ ውል ማቋረጥ ማስጠንቀቂያ አልተሰጠም በሚል ህገ-ወጥ ስንብት ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ<br>• በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለን የስራ መደብ በሌላ ሦስተኛ ወገን እንዲከናወን አስተላልፎ መስጠት (out sourcing) የሥር ውል ለማቋረጥ ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 35 | ሐምሌ<br>10/1999 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 227 | 25317 | ጥቁር አባይ ትራንስፖርት እና ደሳለኝ አብርሃ | በህገ ወጥ መንገድ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ በሞተ ጊዜ ለጥገኞቹ ክፍያ የሚፈፀምበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/ 96 አንቀፅ 39(2),110(2), 40 | ህዳር<br>10/2000 |
| 228 | 25511 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና አቶ አብራራው ከፍያለው | በህጋዊ መንገድ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋድ ቁ. 377/96 አንቀፅ 39 | ጥቅምት<br>2/2000 |
| 229 | 26077 | አቶ አይናለም ባይሌ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ከተደነገገው ይልቅ በአሰሪና ሠራተኛው መካከል የሚደረገው የህብረት ስምምነት ለሠራተኛው የተሻለ መብትና ጥቅም የሚያስገኝ በሆነ ጊዜ የህብረት ስምምነቱ ተፈፃሚ የሚሆን ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 134(2) | ሐምሌ<br>12/1999 |
| 230 | 27704 | ድራጋዶስ ጂ እና ፒ የመንገድ ስራ ድርጅት<br>እና<br>አብዲ ሁሴን | የሥራ ውሉ በህገ-ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል ወደሥራ  እንዲመለስ የተወሰነለት ሠራተኛ ካልሆነ በስተቀር ውዝፍ ደመወዝ የማይከፈል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(5) | ጥቅምት<br>5/2000 |
| 231 | 27959 | የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>አቶ አሊ መሐመድ | • አንድ ሠራተኛ የሥራ ውሉ ተቋርጦ ለነበረበት ጊዜ የዓመት ዕረፍት ሊያገኝ የማይችል ስለመሆኑ<br>• የዓመት ፈቃድ ከሁለት ዓመታት በላይ ሊተላለፍ የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 79(5) | ህዳር<br>3/2000 |
| 232 | 29692 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ አለማየሁ ከበደ | አሠሪ ቋሚ ስራ ሆኖ እየተቋረጠ አልፎ አልፎ የሚሰራ ስራ እንዳለቀ የሠራተኛን ውል ለማቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ | ጥቅምት<br>12/2000 |
| 233 | 29740 | አቶ ስሜነህ ተክሉ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ | ፍርድ ቤቶች በቀረበ ክስ ላይ የዕዳ ማቻቻል ጥያቄ በተነሣ ጊዜ ማስረጃዎችን በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ | ሚያዝያ<br>2/2000 |
| 234 | 29866 | ቻይና ዋንቦ ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን እና ወርቅነህ ምህረቴ | የውክልና ስልጣን ማስረጃ በወካይና በተወካይ መካከል የቅጥር ውል ስለመኖሩ የሚያስረዳ ስላለመሆኑ | ግንቦት<br>7/2000 |
| 235 | 29949 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ዋሲሁን አዳነ | ፍርድ ባልተሰጠበት ጉዳይ ላይ የሚሰጥ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ | ሐምሌ<br>19/1999 |
| 236 | 30956 | የወረዳ 5 አጠቃላይ ነጋዴዎች ማህበር እና አቶ በድሉ ጫላ | ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠት አግባብ ስላለመሆኑ | ሚያዝያ<br>9/2000 |
| 237 | 31402 | የኢትዮጵያ አገር አቋራጭ ከፍተኛ አውቶብስ የግል ባለንብረቶች ማህበር እና አቶ አያሌው ይርጉ | በጡረታ የተገለለን ወይም የጡረታ ዕድሜው ያለፈን ሠራተኛ ወደ ሥራ መልስ ተብሎ አሰሪ የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 24(3)<br>አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀፅ 12(1)(ሐ) | ሚያዝያ<br>30/2000 |
| 238 | 32545 | አቶ ግርማ ሽፈራው<br>እና<br>የክርስቲያን በጐ አድራጐት ልማት ድርጅት | የፕሮቪደንት ፈንድ ባለመብት የሆነ ሰው በአስር አመት ውስጥ መብቱን  ካልጠየቀ መብቱ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 162<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677(1),1845 | ግንቦት<br>14/2000 |
| 239 | 33314 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ አቶ አለማየሁ ወልዴ<br>(አስር ሰዎች) | በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ሥራውን በማከናወን ላይ የነበረን ፋብሪካ የተረከበ ባንክ ከሠራተኞች መብቶች ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጥ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 16<br>አዋጅ ቁ. 97/90 | ግንቦት<br>28/2000 |
| 240 | 33513 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>ዘውዴ ተናኘ | በአንድ የስራ መደብ ላይ በቋሚነት የደረጃ እድገት ይሰጠኝ በማለት የሚቀርብ ክስን ለማየት የክልል ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 138 | ጥር<br>27/2000 |
| 241 | 34588 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>ደረጀ ወልደ ኪዳን | በወንጀል ጉዳይ ተከሶ ነፃ የተባለ  ሰው በፍትሐብሔር ረገድ ከቀረበበት ክስም የግድ ነፃ ይሆናል ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27 | ግንቦት<br>5/2000 |
| 242 | 35440 | የዋልያ አገር አቋራጭ አውቶቡስ ድርጅት<br>እና<br>ብርሃኑ አለሜ | ከሠራተኞች ማህበር ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር በአሰሪ የሚደረግ የሠራተኞች ቅነሳ የህግ አግባብ ያለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 28(1) | ግንቦት<br>19/2000 |
| 243 | 29415 | ዋተር አክሽን እና ይልማ አሰፋ | አዲስ ወደ ተዛወሩበት ቦታ በመሄድ ስራ አለመጀመር እና ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በስራ ገበታ ላይ አለመገኘት በአሰሪው አነሳሽነት የስራ ውልን ለማቋረጥ በቂና ህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(2)(ለ) | ጥር<br>27/2000 |
| 244 | 32822 | ጂ.ሰቨን የንግድና ኢንዱስትሪ የመኸር ቃጫ ውጤቶች ፋብሪካ እና መኮንን አበራ | ያለ በቂ ምክንያት ከስራ መቅረት አሠሪ የስራ ውልን ለማቋረጥ የሚያስችለው  ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1) (ለ) | ጥር<br>27/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 245 | 32229 | መሪጌታ ልሣነወርቅ በዛብህ<br>እና<br>ጠቅላይ ቤ/ክህነት ጽ/ቤት | የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሣኔ መሻር ሳያስፈልገው ጉዳዩ ስልጣን ወዳለው አካል ቀርቦ መታየት የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | ሚያዝያ<br>30/2000 |

**ቅጽ 7**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 246 | 12719 | ሉክሰር የቱሪስትና የጉዞ ወኪል ኃላ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>ብሩኔይስ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር | በሁለት ወገኖች መካከል የተፈረመ ሰነድን እንደ ህጋዊ ስምምነት ለመውሰድ የፈራሚ ወገኖችን ሃሳብና ፍላጐት መመርመር አስፈላጊ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1734, 1952/1/ | ታህሳስ<br>17/2000 |
| 247 | 20232 | አቶ ትዕግስቱ ብዛ<br>እና<br>አቶ ይሃ ይብሬ | የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታዎች የሚፈጠሩባቸውና የሚረጋገጡባቸው በመሆናቸው የውል ህግ መሰረታዊ ድንጋጌዎች መሟላታቸው አስፈላጊ ሁኔታ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 715, የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1706, 1679 | ሐምሌ<br>24/1999 |
| 248 | 23609 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና አቶ አሰበወርቅ ዘገዬ | የስራ መሪ የሥራ ውል ያለአግባብ በተቋረጠ ጊዜ የስራ መሪው ሊያገኝ ስለሚገባው ልዩ ልዩ ክፍያዎች እና ጥቅማጥቅም<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2573, 2574/2/, 2570/2/, 2577, 2562 | ታህሳስ<br>15/2000 |
| 249 | 30298 | አቶ የሺወንድም አቡሃይ<br>እና<br>አቶ አየነው ማለደ | የመጥፋት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው ንብረቱ ወደ 3ኛ ወገን የተላለፈ በሆነ ጊዜ የንብረቱን ዋጋ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 171 | ጥር<br>20/2000 |
| 250 | 16218 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አስካለ ሁንዴ(ሁለት ሰዎች) | ባንኮች ከሚሰጡት ብድር እና የመያዣ ውል ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች አዋጅ ቁ. 97/90"ን" ዓላማ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በባንኮች የሚወጡትን የፎርክሎዥርር መመሪያዎችና አግባብነት ያላቸውን ህግጋት ግምት ውስጥ በማስገባት እልባት ማግኘት ያለባቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3 እና 4, አዋጅ ቁ. 216/92 | መጋቢት<br>16/2000 |
| 251 | 25863 | የኢት/ልማት ባንክ እና የኢት/ንግድ ባንክ (ሁለት ሰዎች) | ለባንክ በመያዣነት በተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚኖር የቀዳሚነት መብት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3088, 3052, 3081,3059 | ጥቅምት<br>26/2000 |
| 252 | 29269 | የኢት/ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ አቶ ዋለልኝ አያሌው(ሁለት ሰዎች) | • በፍርድ የተቋቋመ መያዣ ላይ ፍርዱ እንዲሰጥ ያደረገው ባለገንዘብ መያዣ በሆነው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ስለመሆኑ እና<br>• የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403 ተፈፃሚነት የአንድ ፍርድ ባለዕዳ ንብረት በእርሱ ላይ የቀረቡትን ገንዘብ ጠያቂዎች ፍላጐት የሚያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ክፍፍሉ ጋር በተገናኘ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3041, 3044, 3059/1/, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403,154 | ጥቅምት<br>15/2000 |
| 253 | 29375 | የት/ንግድ ባንክ<br>እና<br>ተስፋዬ ገ/ጊዮርጊስ | የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣነት ከተሰጠ በኋላ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ የሚደረግ ማናቸውም የማሻሻል ሥራ የመያዣ ውሉ አካል ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3066 አዋጅ ቁ. 97/90 | ጥቅምት<br>19/2000 |
| 254 | 33295 | ወ/ሪት ብርሃኔ አበበ እና እነ አቶ ማርቆስ ተርፋ (አራት ሰዎች) | የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በማንኛቸውም ሰነድ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ከተፃፈበት ቀን አንስቶ የማይንቀሳቀሰው ንብረት በሚገኝበት አገር ባለው በማይንቀሳቀስ ርስተ መዝገብ ካልተፃፈ በቀር ምንም አይነት ውጤት የማያስገኝ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3052, 3053,1605, 1607, 1606 | ግንቦት<br>21/2000 |
| 255 | 23024 | ወ/ሮ ፋጤ በሽር እና መልዓከ ገነት ዮሐንስ አምባው<br>እና<br>የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ | በጣልቃ ገብነት ተሳታፊ ሆኖ የፍርድ ተጠቃሚ የሆነ ወገን ዋና ተከራካሪ ከሆኑት ወገኖች መካከል በአንዱ አነሣሽነት ጉዳዩ በይግባኝ በሚታይበት ጊዜ በሥር ፍርድ ተጠቃሚ የሆነው ጣልቃ ገብ ባልተጠራበት ሁኔታ የሚሰጥ ውሣኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40/5/"ን" የሚፃረር ስለመሆኑ | ሐምሌ<br>24/1999 |
| 256 | 24221 | ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና 4እነ ወ/ሮ አረጋሽ አምደሚካኤል | ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር ጋር የተደረገን የኪራይ ውል መሰረት በማድረግ የተያዘ ቤትን ያለአከራዩ ፍቃድ ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ለኪራይ ውሉ መሰረዝ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ | ህዳር<br>24/2000 |
| 257 | 25938 | ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና<br>የአቶ ገ/ሕይወት ከ7ዶም ወራሾች<br>(ሁለት ሰዎች) | የኪራይ ውል የተለየ ፎርም መከተል እንዳለበት የሚያስገድድ የህግ ድንጋጌ የሌለ ስለመሆኑ እና በሁለት ተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚፀና ውል /ህጋዊ ውጤት ያለው ውል/ ለመመስረት በሁለቱም መካከል ስምምነት መኖሩ ብቻ በቂ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719/1/,1719-1930, 2898/3/ | መጋቢት<br>25/2000 |
| 258 | 28025 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና | ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ለተከራዩ በሚሰጥ ማስታወቂያ በማናቸውም ጊዜ ሊቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ እና የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ/ለማፍረስ ለተከራዩ ማስታወቂያ /ማስጠንቀቂያ/ መስጠት አስገዳጅ ቅድመ | ጥር<br>20/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አቶ ታደለ አበበ | ሁኔታ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966/1/ | |
| 259 | 31601 | ወ/ሮ መዓዛ ይሕደጐ እና እነ አየለ ወልዴ (ሁለት ሰዎች) | የኪራይ ውል ተቋርጦ ውዝፍ ኪራይ እንዲከፈለኝና ቤቱንም ልረከብ በሚል የሚጠየቅ ዳኝነት የኪራይ ገንዘብ የተጠየቀበትን ቤት ግምት ጭምር ታሳቢ ተደርጐ የዳኝነት ክፍያ ሊቀርብበት የሚገባ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 227/2/, 226 | የካቲት<br>11/2000 |
| 260 | 31634 | ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ የአቶ ወርቁ ሚስት ወ/ሮ ጽጌ በየነ<br>(ሰባት ሰዎች) | መጠየቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ እስከ 2 ዓመት ድረስ ሳይከፈል የቀረ የኪራይ ዕዳ እንደተከፈለ የህግ ግምት ይወስድበታል ማለት ባለገንዘቡ /አከራዩ/ ክስ መስርቶም ቢሆን ዕዳውን ለማሰብሰብ የማይችል መሆኑን ለማመላከት እንጂ ተከራዩ /ባለዕዳው/ ግዴታውን እንደተወጣ የሚያስቆጥረው ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024/መ/ | መጋቢት<br>4/2000 |
| 261 | 32521 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ዳባ ኢጃቶ | የታወቀ የኪራይ ውል ግንኙነት ሳይኖር ወይም ባለቤት ሳይሆኑ በማይንቀሳቀስ ንብረት መገልገል የተገለገለውን ወገን በንብረቱ በበለፀገው መጠን ኃላፊ የሚያደርገው ስለመሆኑ | ሚያዝያ<br>7/2000 |
| 262 | 34456 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>ወ/ት ደብሪቱ ወልደሃና | ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ውሉ የተደረገበት ጊዜ ካለቀና ውሉ ወደ ያልተወሰነ ጊዜ ከተቀየረ የኪራይ ውሉን በማናቸውም ጊዜ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ የሚቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966 | ግንቦት<br>14/2000 |
| 263 | 18380 | አቶ ማሞ ደምሴ እና እነ አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር<br>(ሁለት ሰዎች) | ውል ይጽደቅልኝ በሚል ለፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231/1//ሀ/ | ጥቅምት<br>5/2000 |
| 264 | 22448 | ኦርቢስ የንግድና ቴክኒክ ክፍል አ/ማህበር እና አቶ ሙሉነህ ካሰ | ፍርድ እንዲፈፀም ለመጠየቅ ችሎታ ያለው ፍርድ የተፈረደለት ሰው /ወገን/ ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378/1/ | ጥቅምት<br>28/2000 |
| 265 | 22860 | ሰንሻይት ኢንዱስትሪና ማከፋፈያ ኩባንያ<br>እና<br>አቶ ካሣዬ ዘውዴ | አንድ ግዴታ መኖሩን ለማስረዳት ህጉ የተለየ ማስረጃ እንዲቀርብ ያዘዘ ካልሆነ በቀር ግዴታው መኖሩን በጽሁፍ፣ በምስክር፣ በህሊና ግምት በተከራካሪው ወገን እምነት ወይም በመሃላ ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2002 | የካቲት<br>18/2000 |
| 266 | 23331 | ጀማል ሐሚድ እና እነ ወ/ሮ ለተሃይማኖት ተክሌ<br>(አምስት ሰዎች) | በህግ ፀንቶ ያለ የሽያጭ ውልን መሰረት በማድረግ የተገኘ መብት ውሉ ፈራሽ እስካልተደረገ ድረስ የሚቀጥል ስለመሆኑ | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 267 | 24974 | እነ አቶ ፈቃዱ ደሬሴ (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ ንጉሴ ወርቁ<br>(ሁለት ሰዎች) | በውል ከተገባ ግዴታ አመዛኙ ክፍል ተፈፀመ ወይም/እና አይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ተከስቷል ለማለት ባልተቻለ ጊዜ ውል እንዲሰረዝ ለመወሰን የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771,1784, 1785 | ታህሳስ<br>8/2000 |
| 268 | 26996 | አቶ በቀለ ደቦጭ እና እነ ወ/ሮ አዛለች ደሣለኝ (ሰባት ሰዎች) | ውል የተደረገበት ጉዳይ ሊፈፀም የማይችል ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተዋዋይ ወገኖችን ወደ ነበሩበት ቦታ የመመለስ ውጤት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1715, 1815 | የካቲት<br>18/2000 |
| 269 | 27349 | ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኪባንያ እና ዘላቂ ግብርና ተሐድሶ ኮሚሽን | ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው የሚፈጠርን አለመግባባት በስምምነት ወይም ደግሞ በአስታራቂ አማካኝነት ለመፍታት የተስማሙ ከሆነ ይኼው ስምምነት ተፈፃሚ መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1765, 1731/1/ | ታህሳስ<br>8/2000 |
| 270 | 28663 | አቶ ካሣሁን ገዛኸኝ እና ወ/ሮ አልማዝ ወልዴ | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658 ተጋቢ ወገን ከሦስተኛ ወገን ጋር ያደረገውን ውል ለማፍረስ ምክንያት ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658, 686 | ጥር<br>27/2000 |
| 271 | 29233 | አቶ ሙሂዲን ፋሪስ እና አቶ እያሱ በዕደ ማርያም | በተዋዋይ ወገኖች መካከል የተደረገ ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 መሰረት የተሟላ አይደለም በሚል ውሣኔ ሲሰጥ ተዋዋይ የነበሩ ወገኖች በፍ/ብ/ህ/ቁ 1815 መሰረት ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723, 1720/1/, 1815 | ግንቦት<br>7/2000 |
| 272 | 32222 | አቶ መሐመድ ኢብራሂም እና አቶ ታይደር ማች | ያልነበረ ቤትን ሠርቶ ለማስተላለፍ በሚል የሚደረግ ስምምነትን በተመለከተ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2876, 1723, 3019, 3020/2/ | የካቲት<br>4/2000 |
| 273 | 32899 | ወ/ሮ አስካለ ማርያም ታደሰ እና አቶ ተሾመ ካሣዬ | የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን በተመለከተ የተደረገ የሽያጭ ውል ተቀብሎ ከማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ላይ ከማያያዝና ከመፃፍ በስተቀር የሽያጭ ውሉን የማዋዋልና የማረጋገጥ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ | ግንቦት<br>21/2000 |
| 274 | 23322 | ወ/ሮ አዳነች ወርዶፋ እና እነ ወ/ሮ አስናቀች ወርዶፋ | የውርስ ሀብት አጣሪ የንብረት ባለቤትነትን የመወሰን ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 956 | ሰኔ<br>19/2000 |
| 275 | 25869 | ወ/ሮ አየለች አልታዬ<br>እና<br>ወ/ሮ አስናቀች አየለ | የማይንቀሳቀስ ንብረት የጋራ ባለሀብት የሆኑ ሰዎች ንብረቱን በአይነት ለመከፋፈል ባልቻሉ ጊዜ ንብረቱ በሃራጅ ተሸጦ ገንዘቡን መካፈል ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1272, 1273 | ሰኔ<br>19/2000 |
| 276 | 30158 | እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ አደም ሞግዚት ሐይሉ ሲሳይ<br>እና<br>የኮ/ል እሸቱ ተሰፋዬ ወራሾች | በፍ/ብ/ህጉ ውስጥ "ከዘር የወረደ ርስት" በሚል የተቀረበው አገላለጽ በህገ-መንግስቱ የተሻረ ወይም ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000/2/ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 40 | ሰኔ<br>19/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 277 | 32414 | ወ/ሮ ባዩሽ ደጀኔ እና እነ ወ/ሮ ሃሳብከፋይ ጌራወርቅ (ሁለት ሰዎች) | ኑዛዜ ፈራሽ ነው ይባል በሚል የሚቀርብ ክስ እና የተሰጠ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ በሚል የሚቀርብ ተቃውሞ የተለያዩ ይዘትና ውጤት ያላቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996/1/, 998/1/, 973, 996/2/ | ሰኔ 24/2000 |
| 278 | 34076 | ወ/ሮ ዘነበወርቅ ወልዱ ፀጋ እና እነ እማሆይ ድብቅነሽ ግዛው (ሁለት ሰዎች) | የውርስ ሃብቶች በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ በሆነ ጊዜ የሚነሱ ክርክሮች የውርሱ ክፍያ በተጀመረበት ቦታ ለሚገኝ ፍ/ቤት የሚቀርቡና የሚስተናገዱ ስለመሆናቸው<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 23 | ሰኔ 10/2000 |
| 279 | 24703 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ት/ቢሮ | በህግ ተቀባይነት ያለው የኢንሹራንስ ውል የሚቋቋምበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1725, 1727 የንግድ ህግ ቁጥር 651, 654, 657 | ሚያዝያ 9/1999 |
| 280 | 22069 | የአማራ ብ/ክ/መንግስት ፍትሕ ቢሮ እና አቶ አስማማው አራጌ | በወንጀል ህግ የሃሳብ ክፍል የሚረጋገጠው ከወንጀል ድርጊት አፈፃፀሙ በመነሳት ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ቁ. 522 /1/ /ሀ/ | ጥቅምት 28/2000 |
| 281 | 22452 | የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና አሣምነው ገ/መስቀል | በወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ /ሀ/ ሥር የተመለከቱት የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦች ለየራሳቸው የሚቆሙ ስለመሆናቸው<br>የወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ /ሀ/ | ሐምሌ 30/2000 |
| 282 | 23855 | የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ<br>እና<br>አቶ ፀጋሁን መንግስቱ | የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይፈፀምበት የመንግስት ቀረጥ ያልተከፈለበት መኪና ይዞ የተገኘ ግለሰብ በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ ያልተባለ ቢሆንም ግለሰቡ ተገቢውን ቀረጥ ከፍሎ መኪናውን መረከብ አልያም ደግሞ መኪናው መወረስ ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 74 አዋጅ ቁ. 388/95 አንቀጽ 80/3/ | ጥቅምት 26/2000 |
| 283 | 24278 | ሰለሞን ሄርጳቦ<br>እና የደ/ብ/ብ/ ሕ/ክ/መ/ የሥ/ፀ/ሙ/ኮ/ዓ/ሕግ | በአዋጅ ቁ. 214/74 አንቀጽ 13/1/ መሠት የተከሰሰ ሰው ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው እንዲጠብቃቸው በአደራ የተረከባቸውን ወይም በሥራው አጋጣሚና ምክንያት በእጁ የገቡትን ንብረቶች የወሰደው/የሰወረው/ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ | ህዳር 10/2000 |
| 284 | 28952 | የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ<br>እና<br>አቶ ባንቲ ታኤራ | በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 122/2/ መሠረት ከሣሽ አቅርቦት የነበረውን ክስ ካነሣ በኋላ እንደገና ክሱን ለመቀጠል የሚችል ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 122/2/, /5/ | መጋቢት 16/2000 |
| 285 | 29325 | ኤርምያስ ካሣ ተፈራ እና ዓቃቤ ሕግ | በወንጀል ክስ የቀረበበት ሰውን አስመልክቶ ጉዳዩ በሌለበት ነው የታየው ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ. 161/1/ | የካቲት 18/2000 |
| 286 | 31734 | አቶ አስናቀ በቀለ እና ዓቃቤ ሕግ | በወንጀል ተከሶ የተያዘ ሰው ዋስትና በጠየቀ ጊዜ ፍ/ቤት ተከሳሹ ተመልሶ ሊቀርብ አይችልም የሚል ግምት ለመውሰድና ዋስትናን ለመከልከል በቂ ምክንያት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 67/ሀ/ | ጥቅምት 15/2000 |
| 287 | 34077 | አቶ ሰይድ ይመር እና የአማራ ክልል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን | በወንጀል የተከሰሰ ሰው የሚያነሳው የዋስትና ጥያቄ መታየት ያለበት ሊወሰንበት ከሚችለው ቅጣት አንፃር ስለመሆኑ | መጋቢት 9/2000 |
| 288 | 34280 | አቶ ግርማይ ደስታ እና ዓቃቤ ሕግ | በወንጀል ህግ ቅጣት ሊገደብ የሚችልበት አግባብ<br>የወንጀል ህ/ቁ. 192,194 | ግንቦት 14/2000 |
| 289 | 34521 | የአማራ ብ/ክ/መ/ፍትሕ ቢሮ እና ስንታየሁ ተፈራ | በወንጀል ህግ ቅጣትን በልዩ የህጉ ክፍል ከተወሰነው መነሻ ዝቅ አድርጐ በማቅለል ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ<br>የወ/ህ/ቁ. 184, 179 | ሰኔ 3/2000 |
| 290 | 35611 | ሻለቃ ታደሰ ካሕሳይ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ | በወንጀል ህግ ጉዳዩን ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት አቤቱታ አቅራቢው ባልቀረበ ጊዜ አቤቱታው እንዲሰረዝ የሚደረገው አቤቱታ አቅራቢው ጉዳዩን በትጋት ያልተከታተለ ወይም በቸልተኝነት የተወው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ 193/1/ | ሰኔ 19/2000 |
| 291 | 18809 | አቶ ሚሊዮን ዑመር<br>እና<br>ዮፌዴራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን | በደንብ ቁጥር 75/1993 ኮምፒዩተርን ጨምሮ ከተለያዩ መሳሪያዎች ህንፃዎችና ሌሎች ዕቃዎች ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ለመሰብሰው የተደነገገው መኪናን በማከራየት የሚገኝን ገቢ የሚያካትት ስለመሆኑ<br>ደንብ ቁጥር 75/93 አንቀጽ 2/9/ ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 24/2/ /ሸ/ | ሰኔ 12/2000 |
| 292 | 19258 | አቶ ተክሌ ዋቅጅራ እና አቶ ሾንጣ ጉቡ | የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር መዋጮ መከፈል ያለበት ማህበሩ ሲቋቋም እንጂ ተቋቁሞ ሥራው ከተጀረ በኋላ ስላለመሆኑ | ሐምሌ 12/1999 |
| 293 | 23389 | የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማኅበር እና እነ ባህሩ አብርሃም (ሁለት ሰዎች) | የአክሲዮን ማህበር አባላት መብታቸውን የሚነካ ድርጊት በማህበሩ አስተዳዳሪዎች በተከናወነ ጊዜ በቀጥታ አስተዳዳሪዎቹን ሊከሱ ስለመቻላቸው<br>የንግድ ህ/ቁ. 364,365,367 | ሐምሌ 10/1999 |
| 294 | 28923 | የባህር ዳር ጨ/ጨ አክስዮን ማሕበር እና የባህር ዳር ልዩ አስተዳደር እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ | የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ ከመቀየራቸው በፊት ያለባቸውን የዕዳ ክርክር በኃላፊነት ይዞ መከራከር ያለበት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባላደራ ቦርድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 208/1992 አንቀጽ 5/1/, 6/1/ /ሐ/, አዋጅ ቁ. 182/1992 | ግንቦት 7/2000 |
| 295 | 10489 | የስራና ከተማ ልማት ሚ/ሮ ተተኪ መሠረተ ልማት ሚ/ር<br>እና | በበጀት የሚተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤት የፍርድ ባለዕዳ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔውን ለማስፈፀም ለሌላ ጉዳይ በበጀት የተያዘውን እና የሰራተኛ ደመወዝን የሚያካትተውን ገንዘብ ከብሔራዊ ባንክ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል ለማዘዝ | ሐምሌ 24/1999 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የቀድሞ ብሐራዊ መሐንዲሶችና ሥራ ተቋራጮች ኃ/የተ/የግ/ማ | ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 404 | |
| 296 | 18576 | ወ/ሮ ደስታ መኮንን<br>እና<br>ወ/ት መሰሉ ጌታሁን | የውርስ ማጣራት ሪፖርት ከፀደቀ ወይም በፍ/ቤት ተቀባይነት ካገኘ በኋላም ቢሆን እንደ ፍርድ ተቆጥሮ በቀጥታ የአፈፃፀም አቤቱታ ሊቀርብበት ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 944, 946, 956, 960, 996 | ግንባት<br>26/2000 |
| 297 | 19283 | ወ/ሮ መድሐኒት ኃይሉ<br>እና<br>የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ | ባንክ ለሰጠው ብድር በመያዣነት እጁ ያስገባውን የተበዳሪ ንብረት በመጀመሪያም  ሆነ በሁለተኛው የሃራጅ ጨረታ ለሽያጭ አቅርቦ ገዢ ያልተገኘ እንደሆነ ንብረቱን ሊያስቀር የሚችለው ለመጀመሪያው ጨረታ መነሻ በተሰጠው የዋጋ ግምት መሰረት ስለመሆኑ | መጋቢት<br>9/2000 |
| 298 | 22481 | አቶ ክፍሌ ወልዴ<br>እና<br>ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | በሀራጅ ጨረታ የአሻሻጥ ስርዓት ላይ "ግዙፍ የሆነ ጉድለት" ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር እንደተፈፀመ ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 422/3/, 428/5/, 455, 428/1/ | መጋቢት<br>4/2000 |
| 299 | 22930 | ወ/ሮ ታድሬ አባተ<br>እና<br>ወ/ሮ ዓለም ገ/የሱስ | ባልና ሚስት በፍቺ ከተለያዩና የንብረት ክፍፍል ከተደረገ በኋላ ከአንደኛው ተጋቢ የግል ተግባር የሚመነጭ ዕዳ አፈፃፀም የተጠየቀው /የቀረበው/ ከፍቺ በኋላ እስከሆነ ድረስ ለዕዳው ምክንያት ከሆነው ተጋቢ ብቻ የሚጠየቅ ስለመሆኑ | ሚያዝያ<br>30/2000 |
| 300 | 23733 | እነ ሃፍቶም ገ/እራሃ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>እነ ሙሉ ካሣ (አራት ሰዎች) | ከንብረት ክፍፍል ጋር በተያያዘ በዋናው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ንብረት መካፈል ከተቻለ እንዲካፈል ካልሆነ ደግሞ በባለሙያ ተገምቶ እንዲካፈሉ በሚል የተሰጠን ፍርድ መነሻ በማድረግ የአፈፃፀም ችሎት /ፍ/ቤት/ ከተከራካሪ ወገኖች መካከል አንደኛው ግምቱን ከፍለው ንብረቱን እንዲያስቀሩ በሚል ትዕዛዝ ለመስጠት የማይችል ስለመሆኑ | ህዳር<br>24/2000 |
| 301 | 23989 | አቶ ደስታ ሠርዳ እና<br>የመተከል ዞን ፍትህ መምሪያ | የማይንቀሳቀስ ንብረት ስመ ንብረት /ባለቤትነት/ ከሻጭ ወደ ገዥ ያለመዛወሩ ብቻ ሦስተኛ ወገኖች በሻጭ ላይ ሽያጭ የተካሄደበት ንብረት ላይ የጀመሩት አፈፃፀም እንዲቀጥል ለማስደረግ በቂ ሁኔታ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2878 | ታህሳስ<br>17/2000 |
| 302 | 25031 | ወ/ሮ አልታየወርቅ ኃ/ማርያም እና<br>አቶ ዓለማየሁ ገለቱ | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 መሰረት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358,418 | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 303 | 26553 | የባህርዳር ልዩ ዞን ገንዘብ መምሪያ እና የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ እና<br>ሙክታር መሐመድ | • የማይንቀሳቀስ ንብረት በሃራጅ በሚሸጥበት ጊዜ በሃራጅ እንዲሸጥ የሚወጣው ማስታወቂያ ለ30 ቀናት መቆየት ያለበት ስለመሆኑ<br>• ንብረቱ በመያዣ የተያዘ እንደሆነም የመያዣው ልክ ምን ያህል እንደሆነ በጨረታ ማስታወቂያ ላይ መገለጽ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ሽያጩ ባልተገባ መንገድ ተከናውኗል ከተባለም ጨረታው በድጋሚ  መካሄድ ያለበት ስለመሆኑ<br>• በመያዣ የተያዘን ንብረት በሌላ ባለገንዘብ ጠያቂነት እንዲሸጥ ሊደረግ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/, 3084, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418, 426, 423/2/ /ለ/, 445-447, 415 | ሐምሌ<br>3/1999 |
| 304 | 27574 | ወ/ሮ አለሚቱ ተረፈ እና የትግል ፍሬ ልብስ ስፌት ማኅበር | በሽምግልና ጉባኤ አማካኝነት የተሰጠ ውሣኔ በፍ/ቤት ሊፈፀም የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 215/1/, 319/2/ | ጥቅምት<br>26/2000 |
| 305 | 28019 | አቶ ብርሀኑ ገ/እግዚአብሔር እና ወ/ሮ ገርጊስ ናይዝጊ | ፍርድን በአግባቡ ውጤት ለመስጠት የአፈፃፀም ችሎት የፍርዱን ትክክለኛ ቃል እና መንፈስ መከተል ያለበት ስለመሆኑ | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 306 | 28154 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ 3ኛ ወገኖች መብት ያቋቋምን ስለሆነ አፈፃፀም ሊቀጥል አይገባም በሚል አቤቱታ ያቀረቡ እንደሆነ ፍ/ቤት ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በአቤቱታው ላይ ያላቸውን ክርክር በቅድሚያ በመስማት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418/1/, 419 | ሚያዝያ<br>14/2000 |
| 307 | 29344 | ወ/ሮ ዝማም ህሉፍ<br>እና<br>አቶ መረሣ ገ/ዮሐንስ | ውሣኔን የሚያስፈጽም ፍ/ቤት በውሣኔው መሰረት ከማስፈፀም ወጪ በአፈፃፀም ጊዜ ዋናውን ፍርድ ሊለውጥ የሚችልበት የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418 | ግንቦት<br>5/2000 |
| 308 | 29653 | አቶ ነጋ ደምሴ<br>እና<br>ሃምሳ አለቃ አዲሱ ደምስ | በዋናው ክርክር ገብቶ ተከራክሮ ውሣኔ ያላገኘ ተከራካሪ ወገን በአፈፃፀም ጊዜ ውሣኔ እንዲፈፀምለት ጥያቄ የሚያቀርብበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418 | መጋቢት<br>9/2000 |
| 309 | 33760 | ሐጂ ታጁ ለገሠ<br>እና<br>የጎንደር ከተማ የመሃል አራዳ ቀበሌ አስተዳደር | የንግድ ድርጅት /መደብር/ ላይ ያለ መብት የድርጅቱ ንግድ የሚካሄድበትን ቤት የኪራይ መብት የሚያካትት ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 127 | መጋቢት<br>18/2000 |